መስከረም

HOOVER INSTITUTION 1986
STANFORD LIBRARIES

- በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳደርና አመራር
  - አንዳንድ ነጥቦች
- የኢንዱስትሪ ዕድገት አቅጣጫ
  - ከምንከተለው የዕድገት ፈለግ አንጻር
- የዜጎች መሠረታዊ መብቶች ፣ ነጻነቶችና ግዴታዎች
  - ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ገጽታዎች
- የፖለቲካ ሥርዓትና ተግባሩ
- መሪ ፓርቲና መሪ ዕቅድ
  - ሁለት የአብዮታችን አበይት ድሎች

DT
371
M469
1977

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 5 ቁጥር
መስከረም 1977

19

Digitized by Google

Digitized by Google

Meskerem No. 19

መስከረም

ቅጽ 5 ቁጥር 19
መስከረም 1977

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ 3
- በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳደርና አመራር አንዳንድ ነጥቦች 5
- የኢንዱስትሪ ዕድገት አቀጣጫ-ከምንከተለው የዕድገት ፈለግ አንጻር 14
  — አያልነህ የሻው
- የዚጉች መሰረታዊ መብቶች፣ነጻነቶችና ገደታዎች--ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ገጽታዎች (ክፍል ሁለት)..... 35
  — መዝገቡ ምትኬ
- የፖለቲካ ሥርዓትና ተግባሩ 61
  — አበበ ወርቄ
- የአስተያየት ገጽ 76

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google



ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

የመሪ ፓርቲ ፕሮግራምና ደንብ ሚና

ሶሺያሊዝምን የመመሥረትና የመገንባት ታሪካዊ ተልዕኮ ይዞ የተነሳና ይህንንም ተልዕኮውን በተግባር ለመተርጐም የሚታገል ማናቸውም አብዮታዊ ፓርቲ የሚመራው ኅብረተሰብ የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ መሠረት በማድረግ የሚቀይሰው ስትራቴጂና ታክቲክ፣ በስትራቴጂውና በታክቲኩም አማካይነት የሚነድፈው የፖለቲካ መሥመር የሚገለጽበት ሰነድ የፓርቲ ፕሮግራም ይባላል። ከዚህ ሰነድ ጋር በቁርኝት የሚዘጋጀውና ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ በመሣሪያነት የሚያገለግለው ደግሞ የፓርቲ ደንብ ሲሆን፣ የፓርቲ ደንብ የፓርቲ አባሎች መብትና ግዴታ፣ የፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅር፣ የአሠራርና የአመራር መርህ፣ አባላት ሊከተሉት የሚገባውን የሥነ ምግባርና ዲሲፕሊን ዓይነት የሚገልጽ ሰነድ ነው።

አንድ የማሌ ፓርቲ ፕሮግራም የሠራተኛውን መደብ ትግል የቅርብና የሩቅ ጊዜ ዓላማዎችና ተግባሮች፣ እነዚህን ዓላማዎች በተግባር የሚተረጐሙበትን ዘዴ ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሚያመለክት ነው። በመሆኑም የማሌ ፓርቲ ፕሮግራም በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት የፓርቲውን ዓላማ የሚያመለክትና ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ ፓርቲው የሚቀይሰውን ዘዴ የሚያካትት ሳይንሳዊ ሰነድ ነው።

ታላቁ ሌኒን የፓርቲ ፕሮግራምን ምንነት አስመልክቶ ሲናገር፣ «ፕሮግራም ፓርቲው ሊያከናውን የሚፈልገውንና የሚዋጋለትን በጥላ በአጭር፣ ግልጽ በሆነ መንገድና በማያሻማ ሁኔታ የሚያስረዳ ነው፤» ማለቱ ይታወቃል።

የማሌ ፓርቲ ደንብም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ፓርቲው ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነቱን የሚያረጋግጥበት፣ ዓላማውን በአብዮታውያን ግንባር ቀደም አመራርና የተቀናጀ ድርጅታዊ አሠራር በተግባር ለመተርጐም የሚገለገልበት እጅግ አስፈላጊ የሆነ ሰነድ ነው።

ፕሮግራምና ደንብ ለአንድ አብዮታዊ ፓርቲ ሕልውና፣ እንቅስቃሴና ዕድገት ወሳኝ የሆኑ መሠረታዊ ሰነዶች ናቸው። ፓርቲው በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ ኑሮ፣ በመከላከያ፣ በውጭ ግንኙነት፣ በፓርቲ ግንባታ ሂደትና በሌሎችም መስኮች የሚከተለው ፖሊሲ የሚነደፈው በፕሮግራሙ ውስጥ ሲሆን፣ የፓርቲ ደንብ ደግሞ በፕሮግራሙ የተቀየሱ ፖሊሲዎችን አባላት በተቀናጀ አመራርና ጥብቅ ዲሲፕሊን በተግባር ለመተርጐም በመመሪያነት የሚገለገሉበት ሰነድ ነው። ፕሮግራምና ደንብ የአንድ አብዮታዊ ፓርቲ አባላት የዓላማና የተግባር አንድነት መገለጫ በመሆናቸው ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው።

የአንድ አብዮታዊ ፓርቲ የፖለቲካዊና የድርጅታዊ አሠራር ብቃት የሚለካው በፕሮግራሙ ሳይንሳዊነትና በፕሮግራሙ ውስጥ የተጠቀሱ ዓላማዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በሚገለገልበት ደንብ በሚገባ ለመጠቀም ባለው ችሎታ ነው።

Digitized by Google

የአንድ አብዮታዊ ፓርቲ ፕሮግራም የፓርቲውን ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን የፖሊሲውን መደባዊ ባህርይ የሚያመለክት እንደሚሆኑ፣ ሠራተኛው መደብና በአጠቃላይም ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የመሪ ፓርቲውን ተላላኪና ተግባር የሚመዝነው በፕሮግራሙ ውስጥ የተተለመውን ፖሊሲ ከፓርተው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጋር በማነጻጸር ነው። በመሆኑም አንድ አብዮታዊና መሪ ፓርቲ ፕሮግራሙ በተግባር መተርጐሙን ባላሰለሰ ሁኔታ መከታተሉ አብዮታዊና የኅብረተሰቡ መሪ ኃይል ሆኖ ለመቀየት ያለው ብቸኛው መንገድ ነው።

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት አስመሪ ፓርቲ የተነደፈው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በወቅቱ የአብዮቱን ኃይሎች በማሰባሰብ፣ በዋናዋና የመደብ ጠላቶቻቸው ላይ የተቀናጀ ትግል እንዲያካሂዱ ከፍተኛ እገዛ ያደረገ ከመሆኑም በላይ፣ እስካሁንም ድረስ አብዮቱ አቅጣጫውን እንዳይስት በመመሪያነት ሲያገለግል ቆይቷል። በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራማችን ከተጠቀሱት ተግባሮች መካከል አብዛኞቹ በተግባር የተተረጐሙና በመተርጐም ላይ ያሉ ሲሆኑ፣ በኢሠፓ ምሥረታ ጉባኤ ላይ የጸደቀው የኢሠፓ ፕሮግራም በአብዮቱ ሂደት እስካሁን የተጠናቀቁትን ተግባሮች በትክክል የገመገመ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሶሺያሊዝም ግንባታ ልምዶችን በሚገባ ያገናዘበ፣ ለተጀመረው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ስፋትና ጥልቀት በመስጠት ለሶሺያሊስቱ አብዮት መጀመርና ለሶሺያሊዝም ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት በየትግል ዘርፉ መከናወን ያለባቸውን ግቦች ያመለከተና የአፈጻጸም ስልቶችን የቀየሰ ሳይንሳዊ ሰነድ ነው። ደንቡም ኢሠፓ በፕሮግራሙ ውስጥ የገለጸውን ዓላማና መሥመር በተቀላጠፈ ድርጅታዊ የአሠራር አንድነትና ጥብቅ ዲሲፕሊን ዕውን ለማድረግ የሚያስችል ወሳኝ ሰነድ ነው።

በአጠቃላይ የኢሠፓ ፕሮግራምና ደንብ የአንድ የማሌ ፓርቲ ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አሠራር መሠረታዊ መመሪያዎች፣ የኢትዮጵያ አብዮታውያን ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በማስተባበርና በመምራት በዚች አገር ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ለማጠናቀቅና ሶሻሊዝምን ለመገንባት የተነሱበትን ክቡር ዓላማ ግብ ለማድረስ የሚችሉበትን ስልትና የተግባር መመሪያ በግልጽ ያመለክቱባቸው ሰነዶች በመሆናቸው፣ በአባላት ዘንድ ዘወትር በጥንቃቄና በጥሞና መታየትና መጠናት አለባቸው።

የኢሠፓ ፕሮግራምና ደንብ የትግል አቅጣጫ አመላካከታችን፣ በአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ጥረታችን የየዕለት ተግባራችን መመሪያ ሰነዶች በመሆናቸው፣ የኢሠፓ አባላት እነኝህን ሰነዶች ጠንቅቆ የማወቅ፣ የማክበርና በተሰማሩበት የሥራ መስክም ሆነ በማኅበራዊና በግል ኑሮአቸው ሁሉ በተግባር መግለጽ አብዮታዊ ግዴታቸው ነው።

በተለይ ከአባላት የሚጠበቀው የኢሠፓን ፕሮግራምና ደንብ ጠንቅቆ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ያወቁትን ለሰፊው ሕዝብ በማሳወቅ በፕሮግራሙ ውስጥ ለተተለመው ዓላማ ተግባራዊነት ሰፊውን ሕዝብ ማንቀሳቀስና መምራት፣ በአጠቃላይ በቆራጥነት መታገልም ጭምር ነው። የኢሠፓ አባላት የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ንድፈ ሐሳብ ግንዛቤያቸውን የማዳበር፣ በሕዝቦች መካከል የጋራ መረዳዳት፣ ሰላም ወዳድነትና ወንድማማችነት እንዲሰፍን ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣ በማናቸውም መስክ የፓርቲያቸውን ድርጅታዊና ርዕዮተ ዓለማዊ አንድነት ማጠናከር፣ ዲሲፕሊንን በጥብቅ ማክበር፣ በማኅበራዊም ሆነ በግል ኑሮአቸው ሥራ ወዳድና ሐቀኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ከዚህም ሌላ ሕገ ወጥና ፀረ-ሕዝብ አዝማሚያዎችን ያለርኅራኄ መዋጋት፣ በሂስና በግለሂስ ድክመቶችን ለማስወገድ ዝግጁ ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል።

Digitized by Google

በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳ ደርና አመራር

አንዳንድ ነጥቦች

ሶሻሊዝምን ብሎም ኮሚኒዝምን ለ
መገንባት እንደ እያንዳንዱ አገር የእድገት
ደረጃና ተጨባጭ ሁኔታ ሊረዝም ወይም
ሊያጥር የሚችል የሽግግር ወቅት የግድ አስ
ፈላጊ መሆኑ በንድፈሀሳብ ከመጠናቀሩም
በላይ በሶሻሊስት አገሮች የአዲስ ኅብረተሰብ
ግንባታ ታሪክ ተረጋግጧል ። ከካፒታሊዝም
ወደ ከፍተኛው የጋርዮሽ ሥርዓት ማለትም
ወደ ኮሚኒዝም በሚደረገው ጉዞ ሶሻሊዝም
የመጀመሪያው ደረጃና የሽግግር ምዕራፍ
መሆኑ ማርክስና ኤንግልስ በግልጽ አስ
ቀምጠውታል ።[1] ወደካፒታሊዝም ሳይገቡ
ከቅድመ ወይም ከከፊል ካፒታሊዝም ወደ
መደብ አልባው ከፍተኛ የኅብረተሰብ እድ
ገት ሕዝቦች ለመሸጋገር እንደሚችሉ ሌኒን
በአደረጋቸው ጥናቶችና ትንተናዎች በግ
ልጽ አሳይቷል ።[2] ከታላቁ የጥቅምት የሩ
ስያ ሶሻሊስት አብዮት ወዲህ ያለው የምዝ
ብርና ጭቁን ሕዝቦች አብዮታዊ የትግል
ታሪክ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾችና
አስፋፊዎች የገነቧቸውን ንድፈ ሐሳቦች ትክ
ክለኛነት አረጋግጧል ።

በተራ ትርጉሙ የሽግግር ወቅት
ካንድ ሁኔታ ወደሌላው ፣ ካንድ ሥርዓተ
ማኅበር ወደሚቀጥለው መተላለፍን የሚ
ያመለክት ሊሆን ይችላል ። በዚህ ጽሑፍ
ውስጥ የሽግግር ወቅት ሲባል በግል
ሀብት ላይ ከተመሠረተ ሥርዓተ ማኅበር
የወል ወይም የጋራ ይዞታ ላይ ወደተመሠ
ረተ የኅብረተሰብ ሥርዓት የሚደረገውን
ጉዞ የሚያመለክት ነው ። በመሠረቱ
የሽግግር ወቅት የሚባለውም ከግል ወደ
ወል ይዞታ የሚደረገው ሂደት ነው ።
ልዩ የሚያደርገውም በግል ሀብትና በጋራ
ሀብት መካከል ያለው የዓይነት ልዩነት
ሲሆን ይህም ውስብስብና መራራ ትግል
ከፍተኛና ከባድ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ
መሆኑ ነው ።

የሽግግርን ወቅት ውስብስብና መራራ፣
ከባድና ውጣውረድ የበዛበት የሚያደርገው
በሁለቱ ሥርዓቶች ማለትም በሶሻሊዝምና
በካፒታሊዝም መካከል የሚካሄደው የሞት
ሽረት ፍልሚያ ነው ። የካፒታሊዝም ከፍ
ተኛውና የመጨረሻ የእድገት ደረጃ የሆነው
ኢምፔሪያሊዝም የአድሀሪ በዝባዥ መደቦች
ወኪልና አፈቀላጤ በመሆን በግል ሀብት

Digitized by Google

ላይ የተመሠረተው ሥርዓት እንዳይናጋ ምዝብርችና ጭቁኖች ዲሞክራሲን ፣ ብልጽግናን ፣ ነፃነትንና ፍትሕን እንዳይጐናጸፉ በብዝበዛ ባካበተው ኃይሉ በሙሉ ለመጠቀም ወደኋላ ስለማይል በሶሻሊዝም አቅጣጫ የሚጓዙት ሕዝቦች የዕድገት ጥረትና ፍላጐት እንዳይሳካ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ እስከ ወታደራዊ ጣልቃገብነት ፣ ከኤኮኖሚ ማዕቀብ እስከቀጥታ ያገጠጠ ወረራ ያካሔድባቸዋል ። የውስጥ አድኃሪያንና የአካባቢ ቡችሎችን በማሰባሰብ ፣ በማደራጀትና በማስተባበር የተለያዩ የኤኮኖሚ አሻጥሮችን በማካሄድ በወረሱት የመነመነ ቅርስና በከፍተኛ መስዋዕትነት ያገኙትን ጥሪት ለኤኮኖሚና ማኅበራዊ ግንባታቸው እንዳያውሉት በየአቅጣጫው ጥረታቸውን ያደናቅፉል ። የሶሻሊስቱና የተራማጁ ጐራ ዛሬ የኢምፔሪያሊዝምን የማንአለብኝነትና የአብራት እንቅስቃሴ ለመግታት ቢቻልም በኤኮኖሚው ግንባታ አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢያደርግም እጅግ ኋላቀር ከሆነ የዕድገት ደረጃ ተነስተው ወደሶሻሊዝም የሚጓዙት ሕዝቦች የሽግግር ወቅት በቀላሉ የሚጠናቀቅ አይደለም ። ይልቁንም ኢምፔሪያሊዝምና አድህሮት ግብዓተ መሬታቸው እየተቃረበ መምጣቱን በእውን ስለተገነዘቡት «አጥፍቼ ልጥፋ» በሚል ቀቢጸ ተስፋ ዓለምንና የሰውን ዘር ከጥፋት አዘቅት ውስጥ ለመጣል ከፋኛ እየተወራጩ በመሆናቸው የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ የሚከተሉት አገሮች ችግር የበለጠ ከባድና ውስብስብ እየሆነ ነው ።

የሽግግር ወቅት አጠቃላይና ራሱን የቻለ ምዕራፍ ወይም ወቅት እንደመሆኑ ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ እውነታዎች ወይም የተግባር መስኮች አንፃር ሊታይ ይችላል። ኤኮኖሚ ከሀብት ማፍራት ፣ ሥርጭት ወይም ክፍል ፣ ከኅብረተሰቡ መሠረታዊ ፍላጐቶች መሟላት ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ በርዕሱ እንደተመለከተው የኤኮኖሚው አስተዳደርና አመራር በሽግግር ወቅት ምን ችግሮች እንደሚያጋጥሙት ፣ በምን ሕግ እንደሚገዛና ፣ የኢትዮጵያም አብዮት በአለፉት አሥር ዓመታት በዚህ በኩል የነበረውን አጠቃላይ ገጽታ ለመቃኘት ይሞከራል ።

የሶሻሊስት የኢኮኖሚ አስተዳደር መሠረተ ሐሳቦች

በኅብረተሰብ ውስጥ አስተዳደር የረዥም ጊዜ ታሪክ ያለው ሲሆን ፣ በተሟላ መልኩ ሊከሰት የቻለው ሰዎች በማኅበራዊ መልክ መደራጀት ሲጀምሩ ነው ። ከዚያም ከምርት ኃይሎችና ከምርት ግንኙነት ጋር አብሮ እያደገና ውስብስብ እየሆነ መጥቷል ። የሰዎች ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐቶች መዳበርና መስፋፋት ለአስተዳደር ሥርዓት መጐልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። አስተዳደር በተለያዩ ማኅበራዊ ሥርዓቶች ውስጥ የተለያዩ ስልቶችና መልኮች አሉት ። በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ አስተዳደር የብዝበዛና የተጽእኖ ባህርይ ያለው ነው ። በሶሻሊስት ሥርዓት የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት የሚረጋገጥበት እንደመሆኑ ፣ ወዝአደሩ የምርት መገልገያዎችና የምርቱም ባለቤት በመሆኑ እንደካፒታሊስቱ ሥርዓት አስተዳደር የመበዝበዣ መሣሪያና በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ላይ ጫና አይሆንም ። እንዲያውም የግለሰቦችን ጥቅምና ፍላጐት ከኅብረተሰቡ አጠቃላይ ጥቅምና ፍላጐት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረጊያ ከመሆኑም በላይ የግል ጥቅም ለኅብረተሰቡ አጠቃላይ ጥቅም ተገዥ እንዲሆን ማድረጊያ መሣሪያ ነው ። በዚሁ መሠረት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ አስተዳደር አዲስ ዓይነት የምርትና የማኅበራዊ ግንኙነት መገንቢያ ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል ።

አስተዳደር ከማኅበራዊ ተግባራት መካከል አንዱና የኤኮኖሚውንም ዘርፍ የሚያጠቃልል ነው ። ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ አስተዳደርን እንደ አንድ የኅብረተሰብ አስተዳደር ክፍል አድርጐ ይወስደዋል ። የኤኮኖሚ አስተዳደር በተራው የኤኮኖሚ ክስተቶችን በመከታተል ይመረምራል ። በአጠቃላይ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የኤኮኖሚ አስተዳደር መሠረታዊ ዓላማ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ የዕድገት ሕግጋትን በመገንዘብ መጠቀም ፣ የሰው ፣ የገንዘብና ቁሳዊ ሀብትን በማደራጀት ለሶሻሊዝም ግንባታ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው ።

Digitized by Google

የሶሻሊስት ኤኮኖሚ አስተዳደር አጠቃላይ መርህ ከሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጣዊ ባህርይ ፣ ከሶሻሊስት ምርት ፣ ከማኅበራዊ ይዞታ መጠናከር የሚመነጭ ነው ። ዳሩ ግን በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የኤኮኖሚ አስተዳደርን ገጽታና ተግባር የሚወስኑ ተጨባጭ ነባራዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎች አሉ ። ከእነዚህም መካከል ፤—

— የምርት ኃይሎች ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ዕድገትና ጥልቀት ደረጃ ፣

— የምርት ግንኙነት ልዩ ባህሪና ዕድገት ፣

— በሠራተኛውና በገበሬው መካከል ያለው የትግል አጋርነት የጥንካሬ ደረጃ ፣

— የምርት መገልገያዎች የማኅበራዊነት ደረጃ ፣

— የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሕግጋትን የማወቅና በሚገባ የመጠቀም ሁኔታ ፣

— የኅብረተሰቡ የባህል እድገት ደረጃ፣

— ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተግባሮች በኅብረተሰቡ ጥቅም ላይ የመመሥረታቸው ሁኔታ ፣

— ለኅብረተሰቡ ሁለገብ ዕድገት መሳካት ያለው ዋስትና ወዘተ . . .

የመሳሰሉት ይገኙበታል ።

ሳይንሳዊ የኢኮኖሚ አስተዳደር ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በሶሻሊዝም ነው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ አስተዳደር በሚከተሉት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የተመሠረተ ነው ።

— የምርት መገልገያዎች የወል መሆን፣

— የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መስፈን፣

— በምርት ዓላማና በኅብረተሰቡ ፍላጎት መካከል የተጣጣመ ሁኔታ መኖር ።

በሶሻሊዝም ሠርቶአደሩ ሕዝብ በአስተዳደር ውስጥ ሰፊ ተሳትፎ የሚያደርግ በመሆኑ ፣ ሶሻሊስት የኤኮኖሚ አስተዳደር በዲሞክራሲያዊ መርህ ላይ የተመሠረተ ነው።

የሶሻሊስት የኤኮኖሚ አስተዳደር ገንቢ ጥረቶችን በማቀናጀት ፍሬያማ ያደርጋል ። ያለውንም የሰውና የገንዘብ ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ዕድገትን ያፋጥናል ።

በአጠቃላይ የኢኮኖሚ አስተዳደርን ከሚከተሉት ሶስት ተግባራቱ አንጻር ለመመልከት ይቻላል ፣

— ዕቅድ ማውጣት ፣

— ማደራጀት ፣

— ማቀናጀትና መቆጣጠር ፣

የኢኮኖሚ አስተዳደር ዕቅድ የማውጣት ተግባር ፣

በሶሻሊስት የኤኮኖሚ አስተዳደር ዕቅድ ማውጣት በዕቅድ መመራትና መሥራት መሠረታዊ ጉዳይ ነው ። የዕቅድ ሥራ በጥናትና በምርምር ላይ የተመሠረተ ነው ። ጥናትና ምርምሩ የሀገሪቱን ቁሳዊና አእምሮአዊ ሀብት ሁኔታ ያጤናል ፤ የሰፊውን ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎቶች የማማላት ሁኔታን ይገመግማል ፤ አቅምንና አለኝታን በትክክል ይመዝናል ፤ ዓለምአቀፍና የሀገር ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማገባ ያጤናል ፤ ተግባራትን በቅደም ተከተል ያስቀምጣል ። እቅዱ የሩቅና የቅርብ ጊዜ ዓላማዎችን በትክክል ካስቀመጠ በኋላ የተግባራትን የክንዋኔና የአፈጻጸም ቅደም ተከተል የየዙ ፕሮግራሞችን ያነድፋል ። የማየቋርጥና ተከታታይነት ያለው የዕድገት መጠኑን ያረጋግጣል ። ኤኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በብቃትና (ጥራትና ቅልጥፍና) በቁጠባ የክንዋኔ መርህ ላይ እንዲመሠረቱ ያደርጋል ።'

ዕቅዳዊ የኤኮኖሚ አስተዳደር በማኅበራዊ ዕድገት ነባራዊ ሁኔታዎች አስገዳጅነት፣ ከምርት ኃይሎች ዕድገት ፣ ከምርት ማኅበራዊ ባህርይ የመነጨ መርህ ነው ። ስለዚህ የሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ከዕቅዳዊ አስተዳደር ውጭ ማሰብ የማቻል አይደለም ። በሶሻሊስት አገሮች የኢኮኖሚ ግንባታ ልምድ ዕቅዳዊ የኤኮኖሚ አስተዳደር ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ ለመገንዘብ ይቻላል ። በዚሁ መሰረት ከፍተኛ የምርት እድገት እንዲያስገኙ ፣ የሰው ኃይልና ቁሳቁስን ምርታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እንዲችሉ ፣ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ እንዲያደርሱ ረድተዋል ። በአጠቃላይ ዕቅዳዊ የኤኮኖሚ አስተዳደር ሁለንተናዊ መሠረት ያለው በመሆኑ ለተስፋፋ ሶሻሊስት የምርት ዕርባታ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው ።

Digitized by Google

በዕቅድ የሚመራ የኢኮኖሚ አስተዳደር
ከፍተኛ የሆነ ዕድገትን በማስገኘት የሰፊው
ን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ የሚያሳድግ በመሆኑ፣
ለሶሻሊዝም ግንባታ ዓይነተኛ መሣሪያ
ሆኖ ያገለግላል ። ቀደም ሲልም እንደተጠቀ
ሰው የአጭርና የረዥም ጊዜ ፍላጐትን በማ
ቀናጀት ብሔራዊ ገቢን ለልማት አመች
በሆነ መንገድ ለመጠቀም ያስችላል ። በተ
ጨማሪም የአንድ ሀገር ክፍለ ሀገራዊ የል
ማት ሥርጭት ተመጣጣኝ እንዲሆን በማ
ድረግ የምርት ኃይሎች ዕድገት እንዲፋ
ጠን ያደርጋል ።

ዕቅዱ በመሠረቱ ከአጠቃላይ ዕድገት
ጋር እየዳበረና እየሰፋ የሚሄድ ስለሆነ ተን
ቀሳቃሽና የማያቋርጥ ባህርይ ያለው ነው ።
በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠ
ቀሰው ዕቅድን የማውጣቱ ተግባር በጥና
ትና በምርምር ላይ የተመሠረተ ስለሆነ
ከተጨባጭነትና ከስሜታዊነት የተላቀቀ ሳ
ይንሳዊ መሠረት ላይ የተመረኮዘ ነው ።

ዕቅዳዊ የኢኮኖሚ አስተዳደር በሶሻሊ
ዝም ውስጥ የሶሲዮ—ኢኮኖሚያዊ ሂደቶ
ችን መቆጣጠሪያ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ።
ዕቅዳዊ የኢኮኖሚ አስተዳደር የጋራ መመ
ሪያና የጋራ ተግባርም ጭምር ነው ። በዚሁ
መሠረት የአንድን ሀገር የዕድገት እንቅ
ስቃሴ የሚቆጣጠርና ከሶሻሊስት የተስፋፋ
የምርት ዕርባታ መዳበር ጋር የተያያዘ እን
ዲሆን የሚረዳ ነው ።

በዕቅድ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ
አስተዳደር በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት
መርህ ላይ የተገነባ ነው ። ' በሶሻሊዝም
ዲሞክራሲ በፖለቲካው መስክ ብቻ የሚ
ዘረጋ ሳይሆን በአጠቃላይ በማኅበራዊ ሕይ
ወት ውስጥ ሁሉ ተግባራዊ ሊሆን የሚ
ገባው ጉዳይ ነው ። ሌኒን ዲሞክራሲን በኢ
ኮኖሚው መስክ የማስፋፋቱን ሁኔታ ሲገ
ልጽ ፣ “ ዲሞክራሲን ለማስፈን ከፖለቲ
ካው መስክ ይልቅ የኢኮኖሚው መስክ አስ
ቸጋሪ ይሆናል ፤ ለሶሻሊዝም ግንባታ ግን
በኢኮኖሚው መስክ ያለው ዲሞክራሲ ከፍ
ተኛ አስተዋጽኦ አለው ”፣ ብሎ ነበር ። በእ
ምራች መስኮች ዲሞክራሲን ማስፈን ማለት
በየኢኮኖሚው ተቋም የሶሻሊስት የምርት
ግንኙነትን መመሥረት በዕቅድ አወጣጥ
ሕዝባዊ ተሳትፎን ማሳደግና የአካባቢ
የዕቅድ አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ
ነው ። ይህም ሁኔታ ሠራተኛው ሕዝብ
በመንግሥታዊ አካላት አማካይነት የሚ
ያደርገውን አስተዳደራዊ ተሳትፎ ያዳ
ብራል ። እጅግ ጠቃሚ በሆኑ ውሳኔዎች
ላይ ተሳታፊ ስለሚሆን ሙሉ በሙሉ ተግ
ባራዊ እንዲሆኑም ከፍተኛ ጥረት ያደር
ጋል ። በዚሁ መሠረት በዲሞክራሲያዊ
ማዕከላዊነት መርህ ላይ የተመሠረተው
ዕቅዳዊ የኢኮኖሚ አስተዳደር በመሠረቱ
ሁለት ነገሮችን በተመሳሳይ ጊዜ ማከናወን
የሚጠይቅ ነው ። ይኸውም በአንድ በኩል
በብሔራዊ ደረጃ የሚታዩ የሶሲዮ- ኢኮና
ሚያዊ መሠረታዊ ችግሮች በበላይ አካል
ዘንድ መግከል ሲሆን ፣ በሌላ በኩል
ደግሞ በተለያዩ ደረጃዎች ላሉ የኢኮኖሚ
ተቋሞች የተወሰኑ አውቶኖሚዎች (መ
ብት) መስጠት ነው ። በአገር አቀፍ ደረጃ
የሚታዩ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አገር አቀፍ
ባህርይ አላቸው ፤— ከነዚህም ውስጥ ዓበ
ይቶቹ ፣

— የኢኮኖሚ ዕድገት መጣኔን ማሳደግ
— የዕድገት ደረጃዎችን መወሰን ፣
— የፍጆታንና የመዋዕለ ንዋይን ድር
ሻዎች መወሰን ፣
— የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ደረጃ
በደረጃ ማሳደግና የመሳሰሉት ናቸው ።

አቅምና ሁኔታ በፈቀደ መጠን ለተለያዩ
ኢኮኖሚ ተቋሞች የሚሰጠው አውቶኖሚ
በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚወሰዱ ዕርምጃ
ዎች ውጤታማነት የሚያደርገው አስተ
ዋጽኦ ከፍተኛ ነው ። በተለይም እንዲህ
ዓይነቱ አሠራር የሠራተኛውን መደብ ተሳ
ትፎ የሚያዳብር ፣ የፈጠራ ችሎታውን
ከፍ የሚያደርግ ስለሆነ የሚጫወተው ሚና
ከፍተኛ ነው ። በተቃራኒው ደግሞ በዲሞ
ክራሲና በማዕከላዊነት መካከል ያለውን
ዲያሌክቲካዊ ቁርኝት መዘንጋት በኢኮኖሚ
አስተዳደር ውስጥ ችግርን ከመፍጠሩም
ሌላ የማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችንም
የሚያናጋ ይሆናል ። በሌላ በኩል ደግሞ
ሁለቱን በአንድ ላይ በማየት የሚወጣው
እቅዳዊ የኢኮኖሚ አስተዳደር የአንድን ሀገ
ር ቁሳዊ ሀብት ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጥቅ
ም እንዲውል ከማድረጉም ሌላ አስፈላጊ
የሆኑ የሶሲዮ - ኢኮኖሚያዊ ሽግግሮችን
ለማካሄድ የሚፈጀውን የጊዜ መጠን ለመ
ጠቀም ያስችላል ። በሽግግር ወቅት ለሶሻ
ሊዝም ኢኮኖሚያዊ ግንባታ መሳካት በዲ
ሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ላይ የተመሠረተ
እቅዳዊ የኢኮኖሚ አስተዳደር ዓይነተኛ
መሣሪያ ነው ።

የኢኮኖሚ አስተዳደር የማደራጀት ተግባር

በሽግግር ወቅት በኢኮኖሚው መስክ

Digitized by Google

ተፃራሪ የሆኑ የኢኮኖሚ ይዞታዎች፣ ማለትም የግል ይዞታና ሶሻሊስት ይዞታ ከመኖራቸው የተነሳ በዚህ ወቅት ኢኮኖሚውን የማደራጀቱ ተግባር ውስብስብ ይሆናል ። ኢኮኖሚውን በአዲስ መልክ ለማደራጀት በቀድሞው ሥርዓት ሥር የሰደዱትን ገብታዊ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች መግታትና ማስወገድ፣ ብሎም በምትካቸው በሶሻሊስት የግንባታ ሕግ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚና የአስተዳደር መዋቅሮችን መዘርጋት ቅድሚያ የሚጠይቁ ዓበይት ተግባሮች ናቸው ። በተለያዩ ደረጃዎች የግል ይዞታው መቀጠል የሚፈጥራቸውን ችግሮች ለመቋቋም አዲስ ማኅበራዊ አደረጃጀትና በጋራ ብልጽግና ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ።

በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳደርን የማደራጀት ተግባር ፣ በአንድ በኩል ሶሻሊስት ይዞታን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ያለበት ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ካለፈው ሥርዓት የተወረሱትን ቁሳዊ ሀብቶች ለአዲሱ ሥርዓት ግንባታ አስተዋጽኦ በሚያደርጉበት መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል በኢኮኖሚ አደረጃጀትና አሠራር ብቃት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ። በዚሁ መሠረት የኢኮኖሚያዊ አስተዳደር የማደራጀት ተግባር የምርት ኃይሎችንና የምርት ግንኙነቶችን ሁኔታ ማጤን ይኖርበታል ። የኢኮኖሚ ተቋሞች መዋቀር ያለባቸው ከእያንዳንዱ አገር ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በቅደም ተከተል መሠረት መከናወን ያለባቸውን ተግባራት መሠረት በማድረግ መሆን አለበት ። በተለይም የአንዳንድ የኢኮኖሚ ተቋሞች አወቃቀር ካላቸው የተግባርና የዓላማ ስፋት በላይ ሊሆን ስለሚችል ውጤታማ ላይሆኑ ይችላሉ ። በዚህ በኩል ከፍተኛ ጥንቃቄ ካልተደረገ ሀብትንና በተለይም የሠለጠነ የሰው ኃይልን በማባከን ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ።

በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳደር የማደራጀት ተግባር ዋንኛ ዓላማ አስተዳደር ከምርት ተግባር አለመገንጠሉን ማረጋገጥ ነው ። አንዳንድ ጊዜ አብዛኛው የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚገኘው በማዕከላዊ ደረጃ ማለትም በሚኒስቴር መ/ቤቶችና እንዲሁም በተለያዩ ማዕከላዊ የኢኮኖሚ ተቋሞች ስለሚሆን፣ አስተዳደር ከምርት ተግባር ጋር ሊራራቅ ይችላል ። በአመራራት ስልትና ዘዴ፣ በምርት ማደራጀት ረገድ የሚከሰቱት ችግሮች ገና ሲከሰቱ በእንጭጩ ለመቅጨት ያለውን ችሎታ ሊያሳንሰው ይችላል ። ስለዚህ የኢኮኖሚ ካድሬዎች የምርት ተግባር በሚከናወንበት አካባቢ ተገኝተው ሥራውን ለመምራት የሚያስችላቸው የአስተዳደር ስልት መዘርጋት አማራጭ የማይገኝለት ነው ።

በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳደር የማደራጀት ተግባር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በተለያዩ መዋቅሮች መካከል ያለውን ግንኙነትና ተዛምዶ ነው ። በእያንዳንዱ መዋቅር አማካይነት ስለሚከናወኑ ተግባሮች ማጤን የሥራ ድርርቦሽ እንዳይኖር ይረዳል ። ቁሳዊና ሰብአዊ ሀብትንም በቁጠባ ለመጠቀም ያስችላል ። የተዛባ የኢኮኖሚ መዋቅር ለሀብት መባከን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ። እንዲህ ዓይነቱም መዛባት ከሚኒስቴር መ/ ቤቶች እስከ ትናንሽ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ድረስ ሊከሰት ይችላል።ስለሆነም በኢኮኖሚ ተቋሞች መካከል የተመጣጣነ ሁኔታን ለመፍጠር በነዚህ ተቋሞች መካከል ያለውን ግንኙነትና ተዛምዶ ማጤን አስፈላጊ ይሆናል።በዚህ በኩል የሚደረገው ጥንቃቄ ቢሮክራሲያዊ አሠራርንም ለማስወገድ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ።

በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳደር የማደራጀት ተግባር ሌላው ትኩረት የጋራ አመራርን ለማስፈን አመቺ ሁኔታን መፍጠር ነው ። በሶሻሊዝም ውስጥ የሚገኙ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ድሎች በሰፊው ሕዝብ መስዋዕትነት የተገኙ ድሎች የመሆናቸውን ያህል ለግንባታው ተግባር መሳካት የብዙሀኑ ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው ። የሰፊውን ሠርቶአደር ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ ተግባራዊ ለማድረግ የኢኮኖሚ ተቋሞች ከዚሁ አንጻር መደራጀት ይኖርባቸዋል ። የሰፊውን ሕዝብ ተሳትፎ ለማዳበር ከሚረዱ የአስተዳደር ስልቶች መካከል የጋራ አመራር አንዱ ነው ። የጋራ አመራርን አስፈላጊ ከሚያደርጉት ምክንያቶችም መካከል የሶሻሊስት ንብረት ባህርይ፣ የኢኮኖሚ አስተዳደር ተግባር ስፋትና ውስብስብነት ይገኙበታል ።

የጋራ አመራር ዲሞክራሲን በማስፋፋት የሠራተኛውን የፈጠራ ችሎታ ያዳብራል ። ሠራተኛው ዕቅዱን ተግባራዊ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ደረጃዎች ዕቀድ በማውጣቱም ተግባር ተሳታፊ እንዲሆን ያደርገዋል ። በአጠቃላይ የኢኮኖሚ አስተዳደር የማዳራጀት ተግባር የኢኮኖሚ አስተ

ዳደር አደረጃጀት ዘዴዎችን መጠቀም ስለሆነ ኤኮኖሚያዊ ግቦችን በከፍተኛ ብቃትና ውጤታማነት ለመወጣት የሚያስችል መሆን አለበት ።

በሽግግር ወቅት የኤኮኖሚ አስተዳደር የማደራጀት ተግባር የሶሻሊስት ኤኮኖሚ አስተዳደር ዓይነተኛ መርህ የሆነውን አንድ ወጥ አመራር ለማስፈን ማስቻል አለበት ። ፓርቲው የሚቀይሳቸውን የኤኮኖሚ ፖሊሲዎች መንግሥት ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው ሳይንሳዊ የኤኮኖሚ የአደረጃጀት ስልት መቀየስ አለበት ። የፓርቲና የመንግሥት እንደዚሁም የሌሎች ክፍሎች ተግባሮች በውል ተለይተው መመልከት ለክትትልና ለአፈጻጸም አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ።

የኤኮኖሚ አስተዳደር የቅንጅትና የቁጥጥር ተግባር

የኤኮኖሚ አስተዳደር የቅንጅትና የቁጥጥር ተግባር ፣ በኤኮኖሚና በአስተዳደር በኩል የሚወሰዱ የማይጣጣሙ የተናጠል ዕርምጃዎችን በማስወገድ ቀናና የሰመረ የሥራ ሂደትን ለማስፈን የሚያስችል ነው ። ዝርክርክነትንና ዕቅድ አልባነትን በማስወገድ የጊዜ ፣ የሰውና የመሣሪያ ኃይልን በቁጠባ ለመጠቀም ያስችላል ። የምርት ውጤትንም ያዳብራል ። በእርግጥ የኤኮኖሚ አስተዳደር የቅንጅትና የቁጥጥር ተግባርን ማከናወን የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀምን ይጠይቃል ። ከእነዚህም መካከል ሥራን ማቀድና ማደራጀት ፣ ሠራተኛን ማስተባበርና የሥራ ውጤቶችን መከታተልና መገምገም አበይት ገጽታዎች ናቸው ።

ሥራን ማቀድና ማደራጀት

በሶሻሊዝም የምርት መገልገያዎች የኅብረተሰቡና የአምራቹ የጋራ ሀብት በመሆናቸው ሥራን ለማቀድና ለማደራጀት ሁኔታው የተመቻቸ ነው ። ሥራን ማቀድና ማደራጀት የሰው ኃይልንና ሀብትን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ያስችላል ። ማኅበራዊ ሥራም እንዳይባክን ይረዳል ። ብሔራዊ ኤኮኖሚ በዕቅድ የመምራት ሥራ ሳይንሳዊ አደረጃጀት እንዲኖረው ያደርጋል ። በአጠቃላይ ሥራን ማቀድና ማደራጀት ፡—

— በአገር አቀፍ ደረጃ የሰው ኃይልን በተመጣጠነ ሁኔታ ለማሠራጨት ፣

— ካድሬዎችን በጥራት ለመመልመልና ሙያቸውንም እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ፣

— በሠራተኛ ቁጥርና በሥራ መጠን መካከል የተመጣጠነ ተዛምዶ እንዲኖር ለማድረግ ፣

— የሥራ ኃይል በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ለመከታተል ፣

— በምርት ዘርፍና አምራች ባልሆነው የኤኮኖሚ ዘርፍ የተሠማሩትን ሠራተኞች ቁጥር ለማመዛዘን ፣

— የሠራተኛውን የሥራ ጊዜ በቁጠባና ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም ፣

— የሥራ ቦታዎችን ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ለማደራጀት ፣

— የሥራ ዲስፕሊን እንዲሰፍን ለማድረግ ይረዳል ።

ሥራን ማቀድና ማደራጀት ከቴክኒካዊ የአደረጃጀት ዘዴ ሌላ የሶሲዮ-ኤኮኖሚውንም መስክ የሚጨምር ነው ። ምክንያቱም ሥራን ማቀድና ማደራጀት የሥራ ኃይልን ከምርት ቴክኒክ ጋር ለማገናኘት ፣ የሰውን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያበረታቱ የማደራጀት ሥልቶች መጠቀም ስለሚያስችልና ለሥራ ብቁ የሆኑ ዜጎች ሁሉ ሥራ ጠቃሚና አስፈላጊም እንደሆነ እንዲረዱ ለማድረግ ስለሚረዳ ነው ። ይህ ተግባር የሶሻሊስት ግንባታ ሥራን በሚያጠናክር ሁኔታ ከማቀድና ከማደራጀት ሂደት ተገንጥሎ የሚታይ አይደለም ። ምክንያቱም አምራች ድርጅቶች በሰው ኃይል ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶችና በጥሬ ዕቃዎች በቁጠባ ለመጠቀም ሥራን ማቀድና ማደራጀት አለባቸው ። እንደአስፈላጊነቱም በየጊዜው የአደረጃጀት ስልታቸው መሻሻልና መጠናከር አለበት ።

ማኅበራዊ ሥራን በሚገባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ማደራጀት የሚቻለው ተመዛዛኝ የሆነ የሥራ ክፍፍል በማድረግ ነው ። ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ደግሞ የሚያመለክተው የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን ከአጠቃላይ ማኅበራዊ ሥራ የመለየቱንና የመወሰኑን ተግባር ነው ። የዚህ ዓይነቱ ሂደት የሚያንጸባርቀው የምርት ኃይሎችን ዕድገትና መስፋፋትንም ጭምር ነው ።

የሥራ ክፍፍል ሳይንሳዊ የሥራ አመራር ከሚገለጽበት መልክ አንዱ ነው ። የሥራ ክፍፍል ኃላፊነትን በሚገባ ለመወጣት ፣ ሙያን ለማዳበር ፣ የሥራ መደራረብንና ግጭትን ለማስወገድ የሚረዳ ዓይነተኛ

Digitized by Google

ዘዴ ነው ። እንደሚታወቀው ኃላፊነትን በሚገባ ለመወጣትና ተገቢ አመራርን ለመስጠት ሕጋዊ አቋምና ችሎታን አጣምሮ የያዘ ሥልጣን አስፈላጊ ነው ። በእርግጥ አንዳንድ ኃላፊዎች ሥልጣንን ለራሳቸው ክብርና ዝና መግለጫ አድርገው የሚጠቀሙበት ስለሆነ ከሠራተኛው ጋር ለመቀራረብ አይችሉም ። የሥራ አመራራቸውም የሠራተኛውን የመሥራት ፍላጎት የሚቀሰቅስ ሳይሆን የሚያዳክም ይሆናል ።

ሳይንሳዊ የሥራ አመራር ተግባራዊ እንዲሆን ከሚረዱ ሁኔታዎች መካከል ዕቅድ ማውጣት ፣ ማደራጀት ፣ መምራት ፣ ማስተዳደርና መቆጣጠር ይገኙበታል ። ስለዚህ የሥራ አመራር ውጤታማ እንዲሆን እነዚህን ሁሉ አጠቃሎ መያዝ ይኖርበታል ። የሥራ አመራር ምርታማነትን ከፍ ለማድረግና በብሔራዊ ገቢ በቁጠባ ለመጠቀም ስለሚያስችል በአመራር ውስጥ ተግባራዊ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው ።

ሠራተኛን ማስተባበርና ማበረታታት

በተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች ሠራተኛውን ለሥራ የሚገፋፉ የተለያዩ ምክንያቶች መኖራቸው ሲታወቅ አበይቶቹ በባለሥልጣን ኃይል በቀጥታ መገደድ ፣ ለሥልጣን ኃይል በቀጥታ መገደድ ፣ ቁሳዊና ሌሎች ፍላጎቶችን ለማርካት አንዳንድ ገጼታዎችን ማሟላት ፣ በተለምዶ ሥነ ምግባር ተጽዕኖ ወደሥራ የመሠማራትና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ይገኛሉ ። ሠራተኛችን በኃይል አስገድዶ ማሠራት በባሪያውና በከፊል ፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ጉልቶ የታየ የሥራ አመራር ዘዴ ነበር ። ሠራተኛው የዕለት ጉርሱንና ሌሎች ቁሳዊም ሆኑ ሕሊናዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ፣ በአጭሩ ለመኖር ሲል ለመሥራት የሚገደድበት ሁኔታ የካፒታሊስት ሥርዓት ነው ። እንዲህ ዓይነቱ የሥራ መገፋፊያ ስልት ከሠራተኛው ፍላጎትና ጥቅም ጋር የተጣጣመ ስለአይደለ ሠራተኛው ሥራን መሥራት ማኅበራዊ ጠቀሜታ እንዳለው አድርጎ እንዲቆጥር አያደርገውም ።

በመሠረቱ በሶሻሊዝምና በኮሚኒዝም ሰዎች ወደሥራ የሚሠማሩት በአሠሪው ኃይል ተገድደው አይደለም ። እርግጥ በሽግግር ወቅት በተለይም ከዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ተነስቶ ወደ ሶሻሊዝም ብሎም ኮሚኒዝም በሚደረገው ጉዞ ወደ መጀመሪያሪያውና እስከ ተወሰነ የኅብረተሰቡ የንቃትኅሊና ዕድገት ድረስ ማስገደድ ወይም ልዩ ልዩ ተጽእና ማድረግ የማይቀር መሆኑን ከእውን ወይም ተግባራዊ ከሆነው ሶሻሊዝም ልምድ ለመረዳት ይቻላል ። ይህ ግን የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሶሻሊስት ንቃተኅሊና ካለመዳበሩ ወይም የንቃተኅሊና እድገት ጊዜ የሚወስድ ከመሆኑና የጸረ ሶሻሊስት ኃይሎችን ቡርቦራ ለመቋቋም ሲባል እንጂ ፣ በሶሻሊዝም ሠርቶአደሩ ለሥራ የሚገፋፋበት ዋናው ምክንያት የሥራን አስፈላጊነት በመገንዘቡ ነው ። ከዚህ ላይ ለመድረስ የማያቋርጥ የሶሻሊስት ንቃተኅሊና ማዳበሪያ ትምህርትና ተግባራዊ አርአያነትን ይጠይቃል ። ሆኖም እስከዚያው ድረስ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሥራን ምርታማነት ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ።

የሠርቶ አደሩን ምርታማነት ከፍ ለማድረግ ዓይነተኛው ዘዴ ሶሻሊስት የሥራ ውድድር ሲሆን ፣ ይኸም በሞራልና በቁሳዊ ማበረታቻዎች ላይ የተገነባ ነው ። ቁሳዊ ጥቅም ሠራተኛውን ማበረታቻ ጠንካራ ዘዴ ስለሆነ ግንባር ቀደም አምራቾችን በደመወዝ ጭምር ልዩ ልዩ ቁሳቁሳዊ መልክ በያዙ ሽልማቶች ማበረታታት አስፈላጊ ይሆናል ። ከዚህም በተጨማሪ ሠራተኛውን በሞራል ማበረታታት ምርታማነቱን እንዲያሳድግ በከፍተኛ ሁኔታ ይረዳዋል ። የሞራል ማበረታቻ ሠራተኛው ሳይለግም ያለውን የሥራ ኃይልና ችሎታ እንዲጠቀም ስለሚገፋፋው ውጤታማነቱ ከዕለት ወደ ዕለት እየጐለበተ ይሄዳል ። የሞራል ማበረታቻ ግንባር ቀደም አምራቾች በኅብረተሰቡ ዘንድ እንዲታወቁ በማድረግ ማኅበራዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል ። በአስገኙትም ከፍተኛ ምርት ሽልማት ያገኛሉ ። ይህም መንፈሳቸውን ስለሚያጠናክረው ለሥራ የበለጠ እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ ዝቅተኛ ምርታማነት ያላቸው ሠራተኞችን መዘንጋት አያሻም ። በእነዚህ ሠራተኞች ላይ ማኅበራዊ ተጽዕኖ ማድረግ አስፈላጊ ነው ። ይህ ተጽእኖ ሠራተኞቹ የሥራ ኃላፊነት እንዲሰማቸው ፣ ሥራ ወዳድ እንዲሆኑ ፣ ጠባብ የሆነውን የግል ጥቅማቸውን ለኅብረተሰቡ አጠቃላይ ጥቅም እንዲያስገዙ ፣ የርዕዮተዓለምና የፖለቲካ ንቃታቸውን ከፍ ማድረግንና የመሳሰሉትን እርምጃዎች ያጠቃልላል ።

ማንኛውም ሰው የሚሠራው የተሻለ ኑሮ ለመኖር ነው ። እንዲህ ዓይነቱን አመለካከት እንደ አፍራሽ አድርጎ መመልከት የተሳሳተ ነው ። ምክንያቱም የእያንዳንዱ ሠራተኛ ደኅንነትና መልካም

Digitized by Google

ኑሮ የምርታማነቱ መገለጫ ስለሆነና ምርታማነቱም የምርት ኃይሎች በኅብረተሰቡ ዘንድ የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ ስለሚያንጸባርቅ ነው ። ይህ ደግሞ የሚያንጸባርቀው በግልና በኅብረሰቡ ጥቅም መካከል ያለውን አንድነት ነው ። ስለዚህ ለሠራተኛው የሚደረገውን ቁሳዊና ሞራላዊ ድጋፍ የኅብረተሰቡን ጥቅም እንደሚጻረር አድርጐ መውሰድ ወይም ሠራተኛው ለህብረተሰቡ ጥቅም ሲል የሚያደርገው አስተዋጽኦ ራሱን እንደጐዳ አድርጐ መቁጠር ሳይንሳዊ መሠረት የሌለው ነው ። ምክንያቱም ሁለቱም ተደጋጋፊነት አላቸው ።

<u>የሥራ ውጤቶችን መከታተልና መገምገም ፡—</u>

ዕቅድ ማውጣት ፣ መዋቅሮችን መዘርጋትና ለሥራ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች መመደብ ወይም ማሟላት ብቻውን ብሔራዊ ኤኮኖሚን በማሳደግ የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ አይችልም ። በዕቅዱ አማካይነት የተተለሙት ግቦች ተግባራዊ በሚሆኑበት መስክ ሁሉ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ውጤታማነታቸውን መገምገምና ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ። ከአጠቃላይ የዕድገት ጽንሰ ሐሳብና ከተግባርም ለመረዳት እንደሚቻለው ክትትል የአንድን ሥርዓት ጤንነት በቅርብ ለመመልከት ፣ ጉድለት ሲገኝ ዕርምት ለማድረግ የሚያስችል ክንውን ነው ። ፕላን ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ ከተለያዩ ተጨባጭ ዕውነታዎች ጋር ላይጣጣም ስለሚችል በዚሁ ሁኔታ የሚፈጠሩትን ችግሮች ተከታትሎ በማወቅ ተገቢው ዕርምት መደረግ አለበት ። የሚያመረታ ወይም የተጠበቀውን ውጤት ለማግኘት የእቅዱን አፈጻጸም ከሥር ጀምሮ ደረጃ በደረጃና ሳያቋርጡ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው ። በሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታ ባንድ በኩል መልካም አዝማሚያዎችን ለማበረታታት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የማይፈለጉና ጐጂ ሁኔታዎችን ለማስወገድ በዕቅድ አፈጻጸም ላይ የቅርብ ክትትል ማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ።

አንዳንድ ጊዜ ከነባራዊ ወይንም ከኅሊናዊ ሁኔታዎች ያለመሟላት የተነሳ ዕቅዶች ሙሉ በሙሉ ግባቸውን ላይመቱ ይችላሉ ። የኤኮኖሚ ተቋሞች ግባቸውን ሊመቱ ወይንም ከግባቸው በላይ ምርት ሊያስገኙ ያስቻሏቸውን ምክንያቶች ከነባራዊና ከኅሊናዊ ሁኔታዎች አንጻር መገምገምና መከታተል ለሚሰጡት አስተያየቶችና ለሚወሰዱት እርምጃዎች ሳይንሳዊነት ማረጋገጫ ይሆናሉ ። አንዳንድ የኤኮኖሚ ተቋሞች ነባራዊ ሁኔታዎች ስለሚፈቅዱላቸው ባለው ኅሊናዊ ሁኔታዎች በሚገባ ሳይጠቀሙ ከኮታው በላይ በማምረት ከፍተኛ ምርት ሊያስገኙ ይችላሉ ። ሌሎች ድርጅቶች ነባራዊ ሁኔታዎች ባይሟሉላቸውም በኅሊናዊ ሁኔታዎች በመጠቀም የሚያመርቱትም ምርት መጠን ከፍተኛ ሊሆን ይችላል ። ድርጅቶቹ ባላቸው ኃይል (ከነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች ተሟልተው) በሚገባ ቢጠቀሙ ኑሮ ውጤታቸው የበለጠ ከፍተኛ ይሆን ነበር ። ሳይንሳዊ መሠረት ያለው የሥራ ግምገማ እነዚህን ሁኔታዎች በማጤን ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል።

ሌላው የሥራ ውጤቶችን ለመገምገምና ለመከታተል የሚረዳው የቁጥጥር ሥርዓት ነው ። እንደሚታወቀው ቁጥጥር ሰዎች በጋራም ሆነ በተናጠል በተፈጥሮ ክስተቶች በዕድገት ሂደቶችና በተግባር መመሪያዎች ላይ ያላቸውን ወይንም ሊኖራቸው የሚችለውን ሚናና ንቁ ተሳትፎ የሚያመለክት ነው ። በዚሁ መሠረት ሕዝባዊ ቁጥጥር ሠራተኛው ምርትን በማስተዳደር ረገድ በሰፊውና በግንባር ቀደምትነት እንዲሳተፍ መድረክ የሚሰጠው ነው። ሕዝባዊ ቁጥጥር ማኅበራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ የሚያገለግል ስለሆነ የመንግሥት መመሪያዎች በትክክል ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ በየደረጃው በመከታተል ተፈጻሚነትም እንዲኖራቸው ያደርጋል።በአጠቃላይ ቁጥጥር ካለው ሚናና ተግባር አንጻር የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያጠቃልላል ።

ተከላካይ

— መጥፎና አፍራሽ አዝማሚያዎች ከመከሰታቸው አስቀድሞ በእንጭጩ የሚያስተራቸውና የኤኮኖሚ የዕድገት ሂደት ጤናማ በሆነ ሁኔታ እንዲቀጥል ማድረግ ፣

አሻሻይ

መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ በሚሆኑበት ሂደት ውስጥ የሚከሰ

Digitized by Google

ቱትን ጉድለቶች አዝማሚያዎችና እንቅፋቶች በማስወገድ የተሻለ የሥራ እንቅስቃሴ እንዲሰፍን ማድረግ ፣

መረጃ

መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ በመከታተልና ያሉትን ደካማና ጠንካራ ጎኖች በወቅት እንደአስፈላጊነቱ ዕርምጃዎች እንዲወሰዱ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሳሰብ ፣ ማሳወቅ ፣

ትምህርት

ቁጥጥር በዚህ ተግባሩ የመሪነት ሚና ይጫወታል ፤ የሠራተኞችን የመሥራት ችሎታ እንዲዳብር ይረዳል፤ ያበረታታል ፤ መልካም የሥራ ልምዶች እንዲ[illegible] ያደርጋል ፤ ሃገር ታማኝነት ከፍ እንዲል አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል ።

ቁጥጥር ከዚህ አንጻር ሲታይ የሳይንሳዊ አስተዳደር ሥርዓት አካል መሆኑን መረዳት አያዳግትም ። ሳይንሳዊ አስተዳደር ተግባራዊ እንዲሆን ተጨባጭ ዕውነታዎችን በትክክል ለመረዳት የሚያስችሉ መረጃዎች ያስፈልጋሉ ። እነዚህን መረጃዎች ማግኘት የሚቻለው በክትትልና በቁጥጥር ሥርዓት አማካይነት ስለሆነ ይህን ሥርዓት ማጠናከር የግድ አስፈላጊ ነው ። የኢኮኖሚ አስተዳደር የቁጥጥር ተግባር እንደየተጨባጩ ሁኔታ መካሄድ ያለበት ሲሆን ፣ የተከላካይነትና የገንቢነት ርምጃዎችን ያቀፈ ነው ። በተለያዩ ጊዜያት የሚከሰቱትን ችግሮች መንስኤ በማጤንና ምንነታቸውን በማሳወቅ ተገቢው የዕርምት እርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርግ ነው ። የቁጥጥር ሥርዓት በሽግግር ወቅት መዘርጋትን አስፈላጊ የሚያደርገውም ይኸው ተግባሩ ነው ።

የግርጌ ማስታዎሻ

1. K. Marx, Critique of the Gotha Programme, Progress Publishers, Moscow, 1978, p. 17.
2. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 31, pp. 242-44.
3. K. Varlamov: Socialist Management Leninist Concept, (Progress Publishers: Moscow, 1977), p. 17.
4. L.I. Abackin: The Economic System of Socialism, (Progress Publishers: Moscow, 1980), p. 111.
5. *Ibid.*, p. 119.
6. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol 27, p. 260.
7. N.P. Fedorenko, Optimal Functioning System for Socialist Economy, (Progress Publishers, 1974), p.10.
8. *Ibid.*, p. 31.
9. Abockin, p. 97.

Digitized by Google

የኢንዱስትሪ የእድገት አቅጣጫ–

ከምንከተለው የእድገት ፈለግ አንፃር

አያልነህ የሻው

ኋላቀርነትን በማስወገድና የዳበረ ሶሻሊስት ኢኮኖሚን ለመገንባት የኢንዱስትሪ በተለይም የከባድ ኢንዱስትሪ ዕድገት አማራጭ የሌለው ብቸኛ ዘዴ ነው ። ከረዥሙ የሶሻሊስት ብሎም ኮሙኒስት ህብረተሰብ ግንባታ አንጻር ሲታይ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የመሪነትና የወሳኝነት ሚና በጉልህ የሚታይ ነው ። ያለ ከባድ ኢንዱስትሪ እድገት ሶሻሊዝም ሆነ ኮሚኒዝም ሊሳኩ አይችሉም ። በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ደረጃም ቢሆን ኋላቀርነትን ለማስወገድና ብሔራዊ ኢኮኖሚ ነፃነትን ለመጐናጸፍ የሚቻለው በኢንዱስትሪው ክፍለ ኤኮኖሚ ግንባታ መሳካት ነው ።

በመነሻው ደረጃ በተለይም በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሂደት ግብርና የኤኮኖሚው መሠረት ቢሆንም ኢንዱስትሪ እንደ ትራክተሮች ያሉ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን ፣ ማዳበሪያዎችን ወዘተ ለእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ካላቀረበ የሰፊውን ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጐት ማርካትና አስፈላጊውን የጥሪት ክምችት በአስተማማኝ ለማፍራት አይቻልም ። ኢንዱስትሪ ጥንካሬ ያላቸውን የሕንጻ መሣሪያዎችን አምርቶ በብቃት ለኮንስትራክሽን ክፍለ ኢኮኖሚ ካላቀረበ ይህ ክፍለ ኢኮኖሚ ተልዕኮውን ለማሟላት እንደማይችል የታወቀ ነው ። ዘመናዊ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችም በኢንዱስትሪ እቃዎች ካልታገዙ በቂ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ሊሰጡ አይችሉም ።

በአጠቃላይ ኢንዱስትሪ የአንድ ብሔራዊ ኤኮኖሚ አንድ ክፍል ቢሆንም ፣ ከሌሎች የሚለይበት ከላይ እንደተመለከተው የወሳኝነትና የመሪነት ሚና ያለው በመሆኑ ነው ። ይህም ከሌሎች ክፍላተ ኤኮኖሚዎች ጋር ባለው ግንኙነት የሚያንጸባርቅ ነው ። በዚህ መሠረት ከብሔራዊ ኤኮኖሚ መስፋፋትና ዕድገት ከሶሻሊዝም ግንባታ አንጻር ሲታይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች የበለጠ አንቀሳቃሽና መሪ ኃይል መሆኑ በግልጽ ይታያል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ኢንዱስትሪ ራሱ በሌሎች ክፍለ ኢኮኖሚዎች ላይ ጥገኛ ነው ። ለምርት የሚያስፈልጉትን ጥሬ ዕቃዎችና የተለያዩ አገልግሎቶች ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ይቀበላል ። ኢንዱስስትሪ ጥሬ ዕቃ አምራቾችን በማበረታታት በጥሬ ዕቃዎች በብቃት ለመጠቀም ያስችላል ። በአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሰፊ የሥራ መስክ በመክፈት ለኅብረተሰቡ የሚያደርጉትን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ

Digitized by Google

ያደርጋል ። በአጠቃላይ ኢንዱስትሪ በማቀበልም ሆነ በመቀበል ረገድ ለብሔራዊ ኤኮኖሚ ዕድገት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው ።

ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ሂደት ኢንዱስትሪ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረትን በመጣል ማኅበራዊ ምርታማነትን ከፍ በማድረግ ረገድ የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም ። በተለይም እጅግ ኋላቀር የሆነ ኤኮኖሚን የወረሱ አገሮች የተመጣጠነ ዕድገት እንዲኖራቸውና ማኅበራዊ ምርታቸው እንዲዳብር ፣ የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚያቸው ዘመናዊ የአመራረት ስልትን እንዲከተል ፣ የሕዝባቸው ኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲል ለማድረግ የኢንዱስትሪ ዕድገት አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው ። ይህንን ሃቅ በመገንዘብ ነው ዛሬ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪን ልማት መሠረት ለማጠናከርና ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ ውስብስብ ትግል የሚደረገው ። ነገር ግን ሀገሪቷ የወረሰችው የኢንዱስትሪ ትርስ ኋላቀርና ጥገኛ በመሆኑ የግንባታው ሂደት የበለጠ ውስብስብና አስቸጋሪነቱ በግልጽ የሚታይ ነው ። በዚህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ አጀማመር ፣ እድገት ፣ ባሕሪ ምን እንደነበረና ዛሬ ደግሞ ምን አቅጣጫ በመያዝ ላይ እንደሆነ ለማብራራት ይሞከራል ።

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ አጀማመር ፣ ዕድገትና መልክ

ካፒታሊዝም በምዕራብ አውሮፓ ተስፋፍቶ የሞኖፖል ካፒታል ባህርዩን ከያዘ በኋላ ሸቀጦችን ለመሸጥና ለፋብሪካዎች የሚውሉ የእርሻ ውጤቶችን ፣ የደን ሃብቶችንና የማዕድን ጥሬ ዕቃዎች ለመግፈፍ በልዩ ልዩ መንገዶች የእስያንና የአፍሪካን አገሮች በቁጥጥሩ ሥር አደረገ ። በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ መላው የእስያና የአፍሪካ አገሮች ጥሬ ዕቃዎች አቀባይና የሸቀጦች ማራገፊያ እንዲሁም የርካሽ ሰው ጉልበት ምንጭ በመሆን በምዕራብ አውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ ልውውጥ ውስጥ ተዋጡ ።

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ የኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ሁኔታዎችና የውጭ ግንኙነቶች ፣ የሀገሮች ዳርና ድንበር ለማያግደው የሞኖፖል ካፒታል መግባትና መስፋፋት በመጠኑም ቢሆን አመች ሁኔታዎችን ፈጥረው ነበር ። በክፍለ ዘመኑ መጨረሻ አካባቢ የነበረው የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ ይበልጥ አመች የነበረው በንግድ በኩል ለሚደረገው የሞኖፖል ካፒታል የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ይሁን እንጂ በመጠኑም ቢሆን ለኢንዱስትሪዎች (የፋብሪካዎች) መቋቋም ቅድመ ሁኔታዎች በመመቻቸት ላይ ነበሩ ።

ያለፈው ክፍለ ዘመን አልቆ የያዝነው ክፍለ ዘመን በተጀመረበት ወቅት አካባቢ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፖለቲካዊ ፣ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ገጽታዎች የሚከተለውን ይመስሉ ነበር ።

— የማዕከላዊ መንግሥት በአዲስ መልክ መዋቀር (የሚኒስቴር መ/ቤቶች መመሥረት) የሀገር ውስጥ የጸጥታና የፖለቲካ ሁኔታ መረጋጋት ፣

— የከተሞች (በተለይም የባቡር ሐዲድ በተዘረጋባቸው አካባቢዎች) መስፋፋትና በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ በተለይም የገዥው መደብ አባሎችና ጭፍሮቻቸው ከአውሮፓ የሚመጡ ሸቀጦችን በብዛት መጠቀም መጀመር ፣

— ከውጭ አገሮች ጋር የሚያገናኙ የትራንስፖርት (የባቡር መስመር) እና የመገናኛ መስመሮች ፣ በዚህም ምክንያት ከአውሮፓ ጋር በልዩ ልዩ ደረጃዎች ተጀምረው የነበሩ ግንኙነቶች የበለጠ መስፋፋት ፣

— አንዳንድ የውጭ አገር ዜጎች (አርመን ፣ ግሪክ ፣ ጣሊያን ፣ ሕንድ) በጊዜው በነበሩት ከፍተኛ ከተሞች መስፈራቸውና በአስመጭና ላኪ ንግድ መሠማራታቸው ፣ ወዘተ . . .

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ብሔራዊ ነጻነቷን ጠብቃ የቆየች አገር ብትሆንም የገዥው መደብ በጊዜው ከነበሩት የኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር ባለፈው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ በጀመራቸው ልዩ ልዩ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ግንኙነቶች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ ሥርዓት ተቀጽላ ሆነ ። ይህም የተከሰተው በመጀመሪያ በውጭ ንግድ እንቅስቃሴ ሲሆን በዚሁ ዘመን ኢትዮጵያ የእርሻ ውጤቶችን ከምንጊዜውም በበለጠ ለአውሮፓ አገሮችና ዩናይትድ ስቴት መላክ ስትጀምር በአንጻሩ የእነዚህ አገሮች የንግድ ሸቀጦች ማራገፊያ

Digitized by Google

ሆነች ። በኢምፔሪያሊዝም የውጭ ንግድ ሰንሰለት የተጀመረው ያልተመጣጣነ የኢኮኖሚ ግንኙነት እየጠነከረ ሲሄድ በክፊል የዚሁ ሥርዓት የኢኮኖሚ ተቀጥላ የሆነ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመጀመር የሀገር ውስጥና የውጭ ሁኔታዎች ተመቻቹ ።

በኢምፔሪያሊዝም የንግድ ልውውጥ አማካይነት ከውጭ የሚመጡት የሸቀጦች አይነትና መጠን በየጊዜው እየጨመረ ቢሄድም በሀገር ውስጥ በተለይም በከተሞች አካባቢ የተፈጠረውን የሸቀጥ ፍላጐት ለማርካት አዳጋች ነበር ። በተጨማሪም ተፈላጊነት የነበራቸው አንዳንድ የሸቀጥ ዓይነቶች በአካላዊ ጠባያቸው ከባሕር ማዶ አስጭኖ ለማምጣት አስቸጋሪና ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል ወይም ለማምጣት የማይቻል በመሆኑ እነዚህን ሸቀጦች አገር ውስጥ ማምረት አስፈላጊ ሆነ ። ለምሳሌ በከተሞች አካባቢ ተፈላጊነት ከነበራቸው እቃዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ለሕንጻ ሥራ የሚያገለግሉ እንደጣውላና ጡብ (ሸክላ) ያሉ እቃዎች ነበሩ ። በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ በመስፋፋትና በዘመኑ "ትልልቅ" ቤቶች የሚባሉ ይሠሩባት ስለነበር ከላይ የተጠቀሱት እቃዎች ፍላጐት ከፍተኛ ነበር ። በተጨማሪም የነበረው ሕዝብ በተለይም የገዥው መደብ አባሎችና ፥ የውጭ አገር ዜጎች በቀሰሙት የአውሮፓ ኑሮ ጠባይ አንዳንድ እቃዎች (ምግብ ፥ ዘይት ፥ ጫማ ወዘተ) ከውጭ ከማስመጣት ይልቅ በሀገር ውስጥ ማምረት የሚያዋጣ መሆኑ በጊዜው በነበሩ የውጭ አገር ዜጎች ግንዛቤ አገኘ ።

ስለዚህ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ከላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎችና ምክንያቶች የተነሳ የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በመጠኑም ቢሆን የሚቀበል ገበያ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥሮ ነበር ። በሌላ በኩል ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም በአንዳንድ ከተሞች ሰፍረው በአስመጭና ላኪነት ተሠማርተው የነበሩ የውጭ አገር ተወላጆች ከንግድ በሚያጠራቅሙት ትርፍና ከሀገራቸው ቀስመውት ከመጡት የፋብሪካዎች ማቋቋም እውቀት በመነሳት በወቅቱ አንዳንድ ፋብሪካዎችን ማቋቋም ጀመሩ ። በመሆኑም በኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚና የባሕል ግንኙነት ሳቢያ የተፈጠረው የኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጐት በሀገር ውስጥ ይኖሩ ከነበሩ የውጭ ዜጐች የትርፍ ፍላጐት ጋር በመጣመር እነዚህም ዜጐች በኢትዮጵያ ውስጥ ያጠራቀሙትን የንግድ ትርፍ ወደ ኢንዱስትሪ ካፒታል በመለወጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ አንዳንድ አነስተኛ ፋብሪካዎች መቋቋም ጀመሩ ።

በዚህ መሠረት እስከ 1920 ድረስ በአዲስ አበባ ፥ በድሬዳዋ ፥ በሐረር ፥ በአሥመራና በምጽዋ አካባቢ የጣውላ መሰንጠሪያና የሸክላ ፋብሪካዎች ፥ የቆዳ ፋብሪካዎች ፥ የምግብ ዘይትና የሣሙና ፋብሪካዎች ፥ የማተሚያ ቤቶች ፥ የጥይት ፋብሪካዎች ፥ የቢራ ፋብሪካ ፥ የሲጃራ ፋብሪካዎች ፥ የአረቂ ፋብሪካ ፥ የሲሚንቶ ፋብሪካ ፥ የዱቄት ፋብሪካና የጨው ማምረቻ ድርጅቶች ወዘተ ሊቋቋሙ ችለዋል ።

ምንም እንኳ በዚያን ጊዜ የኤርትራ ክ/ሀ በኢጣሊያኖች አስተዳደር ሥር የነበረች ቢሆንም ከላይ ከተጠቀሱት ፋብሪካዎች ሌላ ጣሊያኖች ሌሎች ፋብሪካዎች በክፍለ ሀገሯ አላቋቋሙም ነበር ። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ከ1920 በፊት ከተቋቋሙት ፋብሪካዎች ውስጥ አሁን በመሥራት ላይ የሚገኙና በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚተዳደሩ ዘጠኝ ፋብሪካዎች ይገኛሉ ። እነሱም ሆለታ ዱቄት ፋብሪካ ፥ ምጽዋ ጨው ማምረቻ ፥ ኤርትራ ሲሚንቶ ፋብሪካ ፥ አሥመራና አዲስ አበባ ሲጋራ ፋብሪካዎች ፥ ብሔራዊ አልኮል ማጣሪያና አረቄ ፋብሪካ ፥ አሰብ ጨው ማምረቻ ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፥ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ ፥ አዋሽና አዲስ አበባ ቆዳ ፋብሪካዎች ናቸው ።

በዚያው ክፍለ ዘመን መግቢያ አካባቢ በኢትዮጵያ የፋብሪካዎች መቋቋም በነበረው የቅድመ ካፒታሊስት የመደብ ክፍፍል ላይ አዳዲስ መደቦች በሀገሪቱ ውስጥ ፈጠረ። ይኸውም በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ካፒታል ወይም የፋብሪካ መሣሪያዎች ባለቤት የሆነው የካፒታሊስት መደብ ፥ በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በፋብሪካ ሥራ ተሠማርቶ የሥራ ኃይሉን የሚሸጥ የፋብሪካ ወዝአደር መደብ ብቅ አሉ ።

በአጠቃላይ ሲታይ ኢንዱስትሪዎቹ የሚከተሉትን ዋና ዋና ባህርያት ነበራቸው ።

— ከጥይት ፋብሪካዎቹና ከአንድ ማተሚያ ቤት ሌላ የቀሩት ፋብሪ

Digitized by Google

ካዎች በሙሉ የውጭ አገር ተወላጆች ሀብት ነበሩ ።

— የሚመረቱት እቃዎች ለፍጆታ የሚያገለግሉ ነበሩ ።

— የፋብሪካዎቹ መሣሪያዎች የመጡት ከውጭ አገር ነበር ።

— በቴክኒክና በአስተዳደር ረገድ ፋብሪካዎቹን የሚያንቀሳቅሱትና ቁልፍ ቦታዎችን የያዙት የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ ።

ከ1921 ጀምሮ እስከ ፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ጊዜ (1928) አሁንም በመሥራት ላይ የሚገኙ ሁለት ፋብሪካዎች ብቻ ተቋቁመው የነበረ ሲሆን ፥ እነሱም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤትና አምቦ ጠበል ውኃ ነበሩ ። በፋሺሽት ኢጣሊያ ወረራ ጊዜ (1928—1933) የነበረውን የኢንዱስትሪ «እድገት» ስንመለከት በአይነትም ሆነ በይዞታ ከዚያ ተደሞ ከነበረው ሁኔታ እምብዛም አይለይም ነበር ። በጠላት ወረራ ዘመን ተቋቁመው ከነበሩት ጥቂት ፋብሪካዎች ውስጥ ድሬዳዋ ሲሚንቶ ፋብሪካ ፥ ድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ፥ ቃሊቲ ምግብ ማደራጃ ፥ እንበሳ ሜግ ፋብሪካ ፥ መሎቲ ቢራ ፋብሪካና ፖሊግራፊክ ማተሚያ ቤት ይገኙባቸዋል ። በወቅቱ ተቋቁመው የነበሩ ፋብሪካዎች የወራሪውን ጠላት ጦር የሎጂስቲክስ ፍላጐት ለማሟላት የተቋቋሙ ነበሩ ። ወራሪው ጠላት በ1928 መግባደጃ አካባቢ የኢትዮጵያን ዋና ዋና ከተሞች ሲይዝ የጦር ሠፈሮቹንና የቅኝ ግዛት አስተዳደር ማዕከሎችን በዘመናዊ መንገዶች ማገናኘት አንዱ የቅኝ ግዛት ዓላማው ነበር ። ለእነዚህ መንገዶችና በአንዳንድ ከተሞች ለሠራቸው ሕንጻዎች ሲሚንቶ ከጣሊያን አገር ወይም ከሌላ ቦታ ማስመጣት ከፍተኛ ወጭ የሚያስከትል መሆኑን በመገንዘብ በተጨማሪ የድሬዳዋ ሲሚንቶ ፋብሪካን አቋቋመ ። በወቅቱ ተቋቁመው የነበሩት ሌሎች ፋብሪካዎች ለወራሪው ጦር ስንቅና ትጥቅ ጥሎት የሄደው ቅርስ ቢኖር በመንገዶች ሥራ እንጂ በኢንዱስትሪ ማስፋፋት በኩል አልነበረም ። በኢምፔሪሊያዝም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትራኔዎች ተገፍቶ የሚመጣ ጠላት በወረረው አገር ውስጥ ሁኔታዎች ካላስገደዱት በቀር ኢንዱስትሪዎችን አያቋቁምም ፤ የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት ይዘርፋል ፤ የሸቀጡ ማራገፊያ ያደርጋታል እንጂ ።

ከ1934 እስከ 1950 በነበረው ጊዜ ውስጥ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር በተለይም ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ጋር ግንኙነቱን በበለጠ ያጠናከረበትና ሀገሪቱን በኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚና የፖለቲካ መዋቅር ውስጥ በይበልጥ ማስገባት የጀመረበት ወቅት ነበር ። ካለፉት ዓመታት ጋር ሲወዳደር በዚህ ጊዜ የኢንዱስትሪ ካፒታሊዝም በመጠኑም ቢሆን ያደገበትና የተወሰኑ ፋብሪካዎች የተቋቋሙበት ወቅት ነበር ። በወቅቱ ከተቋቋሙት ፋብሪካዎች አንጋፋዎቹ የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ፥ ወንጂ ስኳር ፋብሪካ ፥ ኤርትራ ሜግ ፋብሪካ ፥ የኢትዮጵያ ቃጫ ፋብሪካና ኢትዮ ሲደር ናቸው ። በጊዜው የተቋቋሙት ፋብሪካዎች አብዛኞቹ የፍጆታ እቃዎች የሚያመርቱ ቢሆንም ፥ ብረታ ብረት ፥ የህንፃ መሥሪያ እቃዎች ፥ ጆንያዎችና የኬሚካል ውጤቶች የሚያመርቱ ጥቂት ፋብሪካዎች በወቅቱ ተቋቁመዋል ። በመሆኑም የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን በተለይም ኮንስትራክሽንን መደገፍ የጀመረበት በዚህ ወቅት ነበር ።

ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋር በኢኮኖሚ፥ በፖለቲካ ፥ በማኅበራዊና በወታደራዊ መስኮች ጥብቅ ግንኙነት የነበረው የወደቀው የፊውዶ ካፒታሊስት መንግሥት አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ መዋቅር ጥገኛና ተቀጽላ ሆና እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ ነበር ። የብሔራዊ ኢኮኖሚው ፖሊሲ አቢይ ጠባይ በባለ ግል ሀብቶች አማካይነት የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብትና ውጤቶች ወደ ካፒታሊስት አገሮች «የዓለም ገበያ» መላክና ከዚሁ ገበያ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተለይም የፍጆታ እቃዎችን ወደ ሀገር ማስመጣትና አልፎ አልፎ አንዳንድ ቀላል ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም ነበር ።

በወጪና በገቢ ንግድ መካከል አለመመጣጠን የተፈጠረውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግር በመጠኑም ቢሆን ለማቃ

Digitized by Google

ለልና በተጨማሪም «የሀገሪቱን ሀብት በኢንዱስትሪ ምርት በኩል ጥቅም ላይ ለማዋልና የሥራ እድልም ለመፍጠር» ከውጭ የሚመጡትን የኢንዱስትሪ ፍጆታ እቃዎች በሀገር ውስጥ መተካት የግዴታ ሆነ ። ዳሩ ግን በሀገር ውስጥ ሊገኝ የሚችለው የኢኮኖሚ ትርፍ ወይም የክምችት አቅም መጠን ዝቅተኛ በመሆኑና የተገኘውም ለሀገር ልማት በማይሆኑ ወጪዎች ላይ ይባክን ስለነበር እንደሚታወቀው ውጤቱ ደካማ ነበር ። ጥገኛ የነበረው የብሔራዊ ከበርቴውም ቢሆን የነበረውን ሀብት በአብዛኛው የሚያውለው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ትርፍ ሊያገኝ ወደሚችልበት በሕንጻ ሥራ ፣ በመሬት ግዥና በንግድ ሥራዎች ላይ ነበር ።

በኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ መዋቅር የተዋጡ ጥገኛ አገሮች ዋናው የኢንዱስትሪ ፖሊሲ በኢንቨስትመንት አዋጆች አማካይነት ልዩ ልዩ ጥቅሞችና ማበረታቻዎችን በመስጠት የውጭ ካፒታል ወደ ሀገራቸው እየገባ ፋብሪካዎችንና ሌሎች የኢኮኖሚ ድርጅቶችን እንዲያቋቁሙ አመች ሁኔታዎችን መፍጠር እንደመሆኑ ፣ የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያም የኢንዱስትሪ እድገት ፖሊሲ ከዚህ የተለየ አልነበረም ። ከ1942 ጀምሮ የውጭ ካፒታል ወደ ሀገሪቱ እንዲገባና ፋብሪካዎች እንዲቋቋሙ የሚያበረታቱ ልዩ ልዩ አዋጆችና የሕግ ማስታወቂያዎች ወጥተው ነበር ። በወጡት አዋጆችና የሕግ ማስታወቂያዎች በተለይም በ1959 ተሻሽሎ በወጣው የኢንቨስትመንት አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ጥቅሞችና ማበረታቻዎች ፋብሪካ ለሚያቋቁሙ የውጭ ካፒታሊስቶች ተሰጥተው ነበር ።

1. የኢንቨስትመንት ወጪያቸው ከ ብር 200,000 ያላነሰ የሆኑና አዲስ የሚቋቋሙ ፋብሪካዎች ምርት ከሚጀምሩበት ጊዜ አንስቶ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ከገቢ ታክስ ነጻ እንዲሆኑ ፣

2. ፋብሪካን ለማስፋፋት ከ ብር 200,000 በላይ ወጪ ያደረጉ ባለ ፋብሪካዎች ያስፋፉት ፋብሪካ ለሶስት ዓመታት ከገቢ ታክስ ነጻ እንዲሆንላቸው ፣

3. የብሔራዊ ባንክ ለሚከተሉት የውጭ ምንዛሪ ወደ ውጭ እንዲሄድ እንዲፈቀድ ፣

   — የውጭ ካፒታሊስቶች በኢትዮጵያ ያገኙትን ትርፍ ወደ ውጭ ለመላክ ሲጠይቁ ፣

   — የውጭ ካፒታሊስቶች የኢንዱስትሪ ሀብታቸውን ሸጠው ገንዘቡን ወደ ውጭ ሲልኩ ፣ የውጭ ብድር ለመክፈል ወደውጭ ገንዘብ ሲልኩና ለፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ መተኪያ መሣሪያዎች ፣ መለዋወጫዎችና ሌሎች እቃዎች ከውጭ ሲያስመጡ ፣

   — በፋብሪካዎች ውስጥ የሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች ያጠራቀሙትን ገንዘብ ወደ ሀገራቸው ሲልኩ ፣

4. ፋብሪካዎችን ለማቋቋም የውጭ ካፒታሊስቶች በኢትዮጵያ ውስጥ መሬት መግዛት እንዲፈቀድላቸው ፣

5. ከፋብሪካዎች ከሚገኘው ትርፍ ውስጥ ለመዋዕለ ንዋይ የሚሆነው ድርሻ ገቢ ታክስ እንዳይከፈልበት ፣

6. «አስፈላጊነቱ ሲታመንበት» በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ እቃዎች ከውጭ በሚመጡ ተመሳሳይ እቃዎች ውድድር ምክንያት ገበያ እንዳያጡ ከውጭ በሚመጡት እቃዎች ላይ ታሪፍ ማስከፈልና አንዳንድ ጊዜም እቃዎች ወደሀገር እንዳይገቡ መከልከል ወይም ማገድ ፣

በአንዳንድ ይዘቶች ይለያዩ እንጂ ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሞችና ማበረታቻዎች ሁሉም የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ የሆኑ አገሮች «የሚጠቀሙባቸው» የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሣሪያዎች ናቸው። ከ1951 እስከ 1965 በነበረው ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲወዳደር መጠነኛ ፋብሪካዎች በውጭ አገርና በአገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች ተቋቋመዋል ።

Digitized by Google

በዚህ ወቅት ከተቋቋሙት ፋብሪካዎች ውስጥ አብዛኞቹ የፍጆታ እቃዎችን የሚያመርቱ የፋብሪካ ዓይነቶች ስለነበሩ በምርት ዓይነት ሲታይ በዚህ ወቅት የተቋቋሙት ፋብሪካዎች ባለፉት ዓመታት ከተቋቋሙት ፋብሪካዎች የተለዩ አልነበሩም ። ይሁን እንጂ ብዛታቸው ትንሽ ቢሆንም ከፍጆታ እቃዎች ሌላ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በወቅቱ ተቋቁመዋል ። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ኤርትራና አዲስ አበባ ሲሚንቶ ፣ አዲስ ጐማ ፣ ፕላፕና ወረቀት ፣ አቃቂ ብረታ ብረትና የቀለም ፋብሪካዎች ናቸው። የእነዚህ ፋብሪካዎች መቋቋም የኢንዱስትሪ ክፍለ ኤኮኖሚ የኮንስትራክሽንና የትራንስፖርትን ክፍላተ ኤኮኖሚ እንዲሁም የሕትመት ኢንዱስትሪን በመርዳት መጠነኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

በሌላ በኩል በዚህ ወቅት ከተቋቋሙት ፋብሪካዎች ውስጥ ከፊሎቹ ጥሬ እቃዎቻቸው የሚመጡት ከውጭ ስለነበር የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኤኮኖሚ የበለጠ የውጭ ጥገኛ እንዲሆን ኣድርገውታል ። ይህ ጥገኝነት በበለጠ ጐልቶ የሚታየው በለስላሳ መጠጥና በ«ኬሚካል» ፋብሪካዎች ውስጥ ነው ።

የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ አጠቃላይ ገጽታና ጠባዮች ክፍለ ኢኮኖሚው የዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ ሥርዓት ጥገኛና ተቀጥላ እንደነበር ያንጸባርቃል ። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ለብዙ ዓመታት የኢንዱስትሪው መስፋፋት ፖሊሲ የተመሠረተው የውጭ ካፒታልን በማስገባት ስለነበር ፣ በዚህ ፖሊሲ መሠረት የተቋቋሙት የአብዛኞቹ ፋብሪካዎች ባለቤቶች የውጭ አገር ካፒታሊስቶች ነበሩ ። ለምሳሌ በ1963 የተከናወነ አንድ ጥናት በዚያን ዘመን አሥርና ከአሥር ሠራተኞች በላይ የነበሯቸው 273 ጥቃቅን ፣ መለስተኛና ትልልቅ ፋብሪካዎች እንደነበሩና ከነዚህ ውስጥ አንድ መቶ አንድ ፋብሪካዎች ሙሉ በሙሉ የውጭ ካፒታሊስቶች ሀብት እንደነበሩ ያመለክታል ። ትላልቅ ከሚባሉት ሀምሳ አንድ ፋብሪካዎች ውስጥ ደግሞ ሰላሳ ስምንቱ በውጭ ባለቤትነትና አብዛኞቹም በውጭ አመራር ሥር እንደነበሩ ጥናቱ ያስረዳል ። [1]

በተጠቀሱት 273 ፋብሪካዎች ውስጥ ጠቅላላ የዓመቱ ደመወዛቸው 53 ሚሊዮን ብር የነበረ 58,000 ኢትዮጵያውያን ወዛደሮች እንደነበሩና በአንጻሩም በዓመት 12 ሚሊዮን ብር ደመወዝ የሚከፈላቸው 765 የውጭ አገር ዜጐች የማኔጅመንት ፣ የፋይናንስና የቴክኒክ ቁልፍ ቦታዎችን ይዘው እንደነበር ከጥናቱ ለመረዳት ይቻላል ።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ አብዮት ዋዜማ የኢንዲስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ከአገሪቱ ጠቅላላ ኢኮኖሚ ጋር ተቀናጅቶ ሲታይ የሚከተሉትን ገጽታዎች ያሳይ ነበር ።

ሀ/ አብዛኛው የኢንዱስትሪ ሀብት በውጭ አገር ካፒታሊስቶች ቁጥጥር ሥር ሆኖ የወዝአደሩ መበዝበዣና ለውጭ ካፒታሊስቶች ትርፍ ማካበቻ መስክ ነበር ። በዚህ ምክንያት ከዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚመነጨውና የሚጠራቀመው የኢኮኖሚ ትርፍ ወደ ውጭ ስለሚላክ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከማዳበር ይልቅ ያራቁት ነበር ።

ለ/ ክፍለ ኢኮኖሚው ከአገሪቱ ጠቅላላ የዓመት ምርት ከ10 በመቶ ያነሰና ከውጭ ንግድም ከ5 በመቶ ያልበለጠ ድርሻ ብቻ ነበረው ። ስለሆነም ክፍሉ ለልማት በሚያስፈልግ መዋዕለ ንዋይ ማበርከት በኩል ያደረገው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነበር ።

ሐ/ በአብዛኛው ክፍለ ኢኮኖሚው ያቀፈው የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርት

Digitized by Google

የቀላል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ስለነበር ፣ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ያለው ተደጋጋፊነትና ቅንጅት ዝቅተኛ ነበር ። ይህም በመሆኑ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለማንቀሳቀስ ምንም ኃይል አልነበረውም ።

መ/ የክፍለ ኢኮኖሚው እድገትና መስፋፋት ዝቅተኛ ስለነበር ፣ የሥራ መስክ በመፍጠር በኩል ያደረገው አስተዋጽኦ ከከተማው ደመወዝተኛ ውስጥ ከ10 በመቶ ያነሰ ነበር ።

ሠ/ ክፍለ ኢኮኖሚው የተመሠረተው የኢምፔሪያሊዝም ኢኮኖሚ ተቀጽላ በመሆን ስለነበር ፣ ማምረቻ መሣሪያዎች መለዋወጫ እቃዎች ፣ ጥሬና ከፊል ጥሬ እቃዎች በማግኘት በኩል የኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ መዋቅር ጥገኛ ነበር ።

በአጭሩ አብዮታዊት ኢትዮጵያ የወረሰችው የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ የሚገኝ ፣ በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ በጣም ዝቅተኛ የነበረ ፣ ክፍለ ሀገራዊ ስርጭቱ በጣም የተዛባ ፣ በመለዋወጫና በጥሬ እቃዎች በኩል በውጭ ጥገኝነት ላይ የተመሠረተ (የተቆራኘ) ፣ የውጭ ምንዛሪ የማፍራት ችሎታው አነስተኛ የሆነ ፣ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ተደጋጋፊነቱ የተወሰነ ፣ ለውጭ ከበርቴዎችና ለብሔራዊ መሰሎቻቸው ትርፍ ማጋበሻ ሆኖ የቆየና ወዝ አደሩን ለብዝበዛ ያጋለጠ ኋላቀር የኢኮኖሚ ዘርፍ ነበር ።

በኢንዱስትሪው ዘርፍ የሶሻያሊስት ይዞታን ለመመስረትና ለማስፋፋት ተደረጉ ጥረቶች

በየካቲት 1966 የፈነዳው የኢትዮጵያ አብዮት የፊውዶ ቡርዧውን ሥርዓት የላ እላይ መዋቅር አካሎች እያፈራረሰ ፣ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የማኅበር መዋቅሮችን መዘርጋት ጀመረ ። በዚሁ መሠረት በታህሣሥ ወር 1967 የኢትዮጵያ የእድገት መመሪያ ሶሻሊዝም መሆኑ በይፋ ተገለጸ ። በወጣው የሀገሪቱ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የሶሻል መመሪያ መሠረት የኢኮኖሚውን ዘርፍ በሚመለከት «ለኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ እድገት መሠረታዊ የሆኑና ያልተቋረጠ አገልግሎት መስጠት የሚገባቸው ሀብትና ንብረቶች ሁሉ በመንግሥት ቁጥጥር ስር መዋል ይገባቸዋል ። እንዲሁም ለኅብረተሰቡ እጅግ በጣም አስፈላጊ ሆነው ስለ ይዞታቸው በአንድ መጠቃለል የማይችሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ምንም እንኳ ለጊዜው በመንግሥት ይዞታ ሥር ባይሆኑም መቆጣጠሩና ለጠቅላላው የህብረተሰብ ጥቅም መዋሉ የመንግሥት ዓይነተኛ ግዳጅ ይሆናል ። ነገር ግን የኅብረተሰቡን የጋራ ጥቅም የማይጻረሩ ለግለሰቡ የግል ፍላጐት የሚያገለግሉ ይዞታዎች ደግሞ በግል እጅ ቢሆኑም የኢትዮጵያን ትትደም ዓላማ እስከአላደናቀፉ ድረስ የሚፈቀድ ይሆናል ።»[2] የሚል መሠረታዊና ሥር ነቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተቀየሰ ።

በዚህ ፖሊሲ መሠረት የሀገሪቱ ዋና ዋና የማምረቻ ፣ የማከፋፈያ ፣ የአገልግሎት ሰጪና የገንዘብ ድርጅቶች የወዝ አደሩ መበዝበዣና የውጭና የብሔራዊ የግል ባለሀብቶች መበልጸጊያ መስኮች መሆናቸው ቀርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት ሆነው ለሠርቶአደሩ ሕዝብ ጥቅምና ግልጋሎት የሚውሉበት ፣ በኢትዮጵያውያን የሚመሩበትና የሚተዳደሩበት መንገድ ተቀየሰ ። ሶሻሊዝም የሀገሪቱ መመሪያ መሆን በኢኮኖሚው መስክ ውስጥ ከሚገኙ ዋና ዋና የማምረቻ ፣ ማከፋፈያና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚመነጨው ትርፍ ለግል ባለሀብቶች መንደላቀቂያ መሆኑ ቀርቶ የሀገሪቱን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማቶች ለማዳበር እንዲውል ለማድረግ አመቺ ሁኔታን ፈጠረ ። የሶሻሊዝም የኢኮኖሚ ይዞታና ሥርዓት በሀገሪቱ ውስጥ እንዲሰፍን ለማድረግ የወጣው መመሪያ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በእቅድ እንዲመራና ማንኛውም ዓይነት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

Digitized by Google

የሚካሄደው ትርፍ ከማካበት አንጻር ብቻ ሳይሆን ለሠርቶ አደሩ ህዝብ የኑሮ ደረጃ ማሻሻልና ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ አንፃር ጭምር እንዲሆን ተደረገ ። በወደቀው የፊውዶ ቡርዧ ሥርዓተ ማኅበር ተከስቶ የነበረው የምርት ግንኙነትና የምርት ኃይሎች አለመጣጣም ተወግዶ ታፍኖ የነበረው የምርት ኃይሎች እድገት ነፃ እንዲሆንና እድገቱ እንዲፋጠን አቅጣጫው ተቀየሰ ።

ሶሻሊዝም የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ እድገቶች መመሪያ እንዲሆን በይፋ ከተገለጸ በኋላ ይህን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ በዚያው በታህሣሥ ወር 1967 በካፒታሊስት ስልተ ምርት የተዋቀረውን የኢኮኖሚ ክፍል በማንቀሳቀስ ከፍተኛ ሚና ይጫወቱ የነበሩ ባንኮች ፣ ሌሎች የገንዘብ ነክ ድርጅቶችና የመድን ኩባንያዎች በመንግሥት ቁጥጥር የሕዝብ ሀብት ሆኑ ። በእነዚህ ድርጅቶች በተለይም በመድን ኩባንያዎች ፣ (አማካይነት የሀገሪቱን ሀብት በልዩ ልዩ ዘዴዎች ወደ ውጭ መላክና በድርጅቶቹ ውስጥ ይካሄድ የነበረው ብዝበዛ እንዲቆም ተደረገ ።

በጥር ወር 1967 በካፒታሊስት ስልተ ምርት ተዋቅረው የነበሩት የኢኮኖሚ አውታሮች (ዋና ዋና የማምረቻ ፣ የማከፋፈያ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች) በመንግሥት ተወረሱ ። በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አበይት የሀብት ማፍሪያ ድርጅቶች ይዞታ ማኅበራዊ ሆነ ። መንግሥትም እነዚህን የኢኮኖሚ ድርጅቶች በመምራት ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ፣ በማከፋፈልና አገልግሎት በመስጠት በከፊል ብሔራዊ ኢኮኖሚውን በቀጥታ ማንቀሳቀስ ጀመረ ።

ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሆኑና የሕዝብ ሀብት በሆኑት የኢኮኖሚ ድርጅቶች ውስጥ መጠነኛ ፣ መለስተኛና ከፍተኛ ፋብሪካዎች ነበሩ ። እነዚህን ፋብሪካዎች በማኅበራዊ ይዞታ ሥር ማድረግ በፋብሪካዎቹ ውስጥ ይካሄድ የነበረውን ብዝበዛ እንዲቆም ከማድረጉም በላይ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ቁሳዊ ፍላጐት አቅም በፈቀደው መጠን እንዲሟላ ለማደራጀት ፣ ለመምራት እንዲሁም የማምረት አቅሙን ለማስፋፋት የሚያመች የኢኮኖሚ ዘርፍ ሆነ ። በነዚህ ፋብሪካዎች ውስጥ ይሰራ የነበረው ወዝአደርም ከብዝበዛ ነፃ ሆኖ የመደራጀት መብቱን ተቀዳጅቶ የኢኮኖሚ ጥቅሙንና የፖለቲካ መብቱን በማስጠበቅ ኑሮውን የሚያሻሽልበትንና ጠንካራ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያደርግበትና ታሪካዊ ሚናውን የሚጫወትበት ቅድመ ሁኔታ ተፈጠረ ።

እንደሚታወቀው ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በበለጠ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የማምረቻ መሣሪያቸው ፣ መለዋወጫ እቃዎች ፣ ሙሉና ከፊል ጥሬ እቃዎች በመግዛትና ትርፍንና ልዩ ልዩ ገቢዎችን ወደ ዳበሩ የካፒታሊስት አገሮች በመላክ ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ መዋቅር ጋር የተሳሰረና የዚህ ኢኮኖሚ ሥርዓት ጥገኛ ነበር ። በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚገኙ መለስተኛና ከፍተኛ ፋብሪካዎች በማህበራዊ ይዞታ ሥር መሆን ሁኔታዎች በፈቀዱት መጠን ክፍለ ኢኮኖሚው ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ ጥገኝነት ደረጃ በደረጃ ነፃ እንዲሆንና ከረዥም ጊዜ አንፃር የብሔራዊ ኢኮኖሚው መሠረት ለማድረግ አመችቷል ። በዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ የነበሩትን መለስተኛና ከፍተኛ ፋብሪካዎች በማኅበራዊ ይዞታ ሥር ማድረግ ክፍለ ኢኮኖሚው የአብዮቱን ዓበይት ዓላማዎች ግብ ለመምታት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ለማደራጀትና ለማስፋፋት ከምንጊዜውም የበለጠ የተሻለ ሁኔታ ተፈጥሯል ።

በኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ የነበሩትን መለስተኛና ከፍተኛ ፋብሪካዎች በማኅበራዊ ይዞታ ሥር ማድረግ ክፍለ ኢኮኖሚው ከላይ እንደተጠቀሰው ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን በመደገፍ ብሔራዊ ኢኮኖሚውን ለማንቀሳቀስ እንዲችል ለማደራጀትና ለማስፋፋት ያስችላል ። በዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ ከሚገኘው ተረፈ ምርት ውስጥ ዘርፉን ለማስፋፋትና ለማዳበር ሁኔታውን አመቻችቷል ። በተጨማሪም በአብዮቱ ሂደት በተቀየሰው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አማካይነት በኢኮኖሚው መስክ ለታቀዱት ዓላማዎች የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች የኢንቨስትመንት ድርሻቸውን ከፍ ማድረግ ለሶሻሊስት የኢኮኖሚ ግንባታ የሚያስፈልገውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት ለመጣል የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የማቴሪያል ፍላጐት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም

Digitized by Google

የፈቀደውን ያህል ለማርካት እንዲቻል አመች ሁኔታ ፈጥሯል ።

በዚህ መሠረት በመንግሥት ቁጥጥር የሕዝብ ሀብት ሆነው በኢንዱስትሪ ሚኒ ስቴር ሥር በሚተዳደሩ ፋብሪካዎች ባለ ፉት አሥር ዓመታት የተገኘውን የምርት ውጤትና የተከናወነውን የግንባታ ሥራ ቀጥለን እንመለከታለን ። [3]

ሀ. የምርት ክንውን፡— በ1967 ወደ መንግሥት ይዞታ የተዛወሩት ፋብሪካዎች የ1968 የምርት መጠን በዋጋ የሚከተለው ነበር ።

የኢንዱስትሪ ዘርፍ	ምርት በዋጋ (በሺህ ብር)	ድርሻ በ%
ምግብ	176,133	23.4
መጠጥ	101,947	13.5
ትንባሆ	30,590	4.1
ጨርቃ ጨርቅ	245,916	32.6
ቆዳና ጫማ	57,807	7.7
እንጨት	13,188	1.8
ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች	19,137	2.5
ሕትመት	28,144	3.7
ኬሚካል	39,161	5.2
ብረታ ብረት	41,320	5.5
ድምር	753,343	100.0

በአሁኑ ወቅት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሕዝብ ሀብት የሆኑ በርከት ያሉ ፋብሪ ካዎች ይገኛሉ ። ከእነዚህ ውስጥ አብ ዛኞቹ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚተዳ ደሩ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ በሌሎች ሚኒስ ቴሮች (በመንግሥት እርሻ ፣ ግብርና ፣ ጤና ጥበቃ) አስተዳደር ሥር ይገኛሉ ። በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከሚገኙት ፋብ ሪካዎች ውስጥ ሀምሳ ስምንቱ በምግብ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመደቡ ናቸው ። ከ1967 ወዲህ ለመንግሥት ፋብሪካዎች ቁጥር መጨመር ዋና ምክንያቶች በግል ይዞታ ሥር የነበሩ ፋብሪካዎች ወደ መን ግሥት ይዞታ በየጊዜው በመዛወራቸውና በጥቂቱም ቢሆን አዲስ ፋብሪካዎች በመ ቋቋማቸው ነው ።

በመንግሥት ይዞታ ከሚገኙ ፋብሪካ ዎች ውስጥ 85,000 ቋሚ ሠራተኞች የሚ ገኙ ሲሆኑ ፣ ከእነዚህ ሠራተኞች ውስጥ 40 በመቶ ያህሉ በጨርቃ ጨርቅና 25 በመቶ ያህሉ በምግብ ኢንዱስትሪ ዘር ፎች ተሰማርተው የሚሠሩናቸው ። ይ ህም ከጠቅላላ የመንግሥት ፋብሪካ ቋሚ ሠራተኛ ውስጥ ሁለት ሶስትኛው በሁለት የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ የተ ሠማራ መሆኑንና አንድ ሶስተኛው ብቻ በቀሩት ስምንት የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ እንደሚገኝ ያሳያል ።

በመንግሥት ይዞታ ሥር በሆነው የኢ ንዱስትሪ ክፍለ ኤኮኖሚ ከ1968 - 1975 የተመረተው ምርት በዋጋና በየዘርፉ በሚ ቀጥለው ገጽ 23 በታየው ሠንጠረዥ ቀርቧ ል ። በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በ1968 የበጀት ዓመት የተመረተው ጠቅላላ ምርት ከ1975 የበጀት ዓመት ከተመረተው ጋር ሲነፃጸር በ93 በመቶ እድገት ያሳያል ። ለዚህ የምርት እድገት ዋና ምክንያቶች የሚከ ተሉት ናቸው፡—

— በክፍለ ኤኮኖሚው ውስጥ የመንግ ሥት ይዞታ እየተጠናከረ መሄድና ቁጥራቸው በርከት ያሉ የግል ፋብ ሪካዎች ወደ መንግሥት ይዞታ በመ ዛወራቸው ፣

— በተለይ የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ ከተጀመረ ወዲህ የማምረት ተግባር በእቅድ በመመራቱና ብዙ ዎቹ የመንግሥት ፋብሪካዎች በሙሉ ጉልበታቸው እንዲያመርቱ በመ ደረጉ ፣

Digitized by Google

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ከ1968—1975 የምርት ውጤት በኢንዱስትሪ ዘርፍ [4]

(በ'000 ብር)

የኢንዱስትሪ ዘርፍ	1968	1969	1970	1971	1972	1973	1974	1975	1976 (ዕቅድ)
ምግብ	176,133	189,984	240,154	32,4484	360,022	389,458	400,367	447,114	452,307
መጠጥ	101,947	107,145	109,512	13,7264	149,599	167,569	180,476	193,133	200,003
ትምባሆ	30,590	29,508	28,442	38,543	41,118	41,817	49,498	57,804	63,584
ጨርቃጨርቅ	245,916	231,997	195,101	262,360	302,953	324,133	331,484	340,484	371,684
ቆዳና ጫማ	57,807	66,977	59,719	85,290	107,242	108,337	113,073	119,896	133,593
እንጨት	13,188	14,059	13,326	17,121	17,898	20,246	23,012	25,116	25,936
ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች	19,137	21,649	16,276	18,141	26,645	27,707	34,569	32,964	37,261
ሕትመት	28,144	30,680	30,341	43,574	53,864	58,570	65,720	68,793	77,048
ኬሚካል	39,161	36,227	41,054	61,867	66,107	70,919	80,480	92,240	97,857
ብረት ብረት	41,320	45,344	54,009	78,649	87,278	92,670	96,974	106,139	109,777
ድምር	753,343	773,570	787,934	1,067,293	1,212,726	1,301,420	1,375,653	1,483,673	1,569,050
ዕድገት በመቶ	100	103	105	142	161	173	183	193	208

Digitized by Google

— አንዳንድ ፋብሪካዎች ስለተስፋፉ የማምረት አቅማቸው ስለተጠናከረ ፣

— በብዙ ፋብሪካዎች ውስጥ የምርት ማነቆዎች ስለተወገዱ ፣

— ለማምረቻ መሣሪያዎች የሚደረገው እንክብካቤና ጥገና ከጊዜ ወደጊዜ በመሻሻሉ ፣

— በተለይም የፋብሪካ ሠራተኛው ምርትን ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት በማድረጉ ነው ።

የግንባታ ሥራዎች

ከኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ ወዲህ አብዮቱ ባስገኘለት ድልና ባስከተለው ለውጥ ምክንያት የሠርቶ አደሩ ሕዝብ የፍጆታ እቃዎች ፍላጐት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ሄዷል ። እንዲሁም ያገሪቷ የልማት እንቅስቃሴ በመጨመሩ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ኮንስትራክሽን ከኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚፈልጋቸው የእቃዎች መጠን በየጊዜው እየጨመረ የመሄድ አዝማሚያን ያሳያል ። የሀገሪቱ ብሔራዊ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው መሠረት የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የኢንዱስትሪ የፍጆታ እቃዎች ፍላጐት ለማሟላትና ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚያስፈልጉትን ዓይነታቸው መጠነኛ የሆነ ምርቶችን ለማቅረብ የነባር ፋብሪካዎችን ምርት ከመጨመር ሌላ አንዳንድ ነባር ፋብሪካዎችን በማስፋፋት (ማደስና አዲስ ፋብሪካዎችን በማቋቋም) አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ምርት መጠን እንዲጨምር ጥረት ተደርጓል ።

በዚህ መሠረት እስከ 1976 አጋማሽ ድረስ አዲስ የተቋቋሙና ከፍተኛ መስፋፋትና (እድሳት የተደረገላቸው ፋብሪካዎች ብዛት 43 ሲሆን ለዚህ ተግባር በጠቅላላ ወጭ የተደረገው ኢንቬስትመንት ብር 318.13 ሚሊዮን ነው ። ከዚህ ውስጥ በየኢንዱስትሪ ዘርፉ የተደረገው የኢንቬስትመንት መጠንና የተፈጠረው የሥራ መስክ እንደሚከተለው ነው፦—

በመንግሥት የኢንዱስትሪ ክፍል የተደረገ የግንባታ ሥራ [5]

የኢንዱስትሪ ዘርፍ	የካፒታል ወጪ (በሚሊዮን ብር)	ድርሻ በ%	ተጨማሪ ሠራተኛ
ምግብ	118.8	37.3	3,834
መጠጥ	92.1	29.0	1,581
ትምባሆ	3.7	1.2	70
ጨርቃ ጨርቅ	84.4	26.5	2,796
ቆዳና ጫማ	3.5	1.1	633
ኬሚካል	4.6	1.4	381
ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች	9.5	3.0	70
ብረታ ብረት	1.5	0.5	170
ድምር	318.1	100.0	9.535

Digitized by Google

የግንባታ ሥራቸው ከተጠናቀቀ አዲስና ከተስፋፉ (ከታደሱ) ፋብሪካዎች የተገኙት ተጨማሪ ዋና ዋና ምርቶች የሚከተሉት ናቸው ። [6]

የኢንዱስትሪ ዘርፍ	ተጨማሪ ዓመታዊ ምርት	
የምርት ዓይነት	መለኪያ	መጠን
ምግብ		
የሕጻናት ምግብ (ፋፋ)	ቶን	20,000
ስኳር	,,	45,000
ዱቄት	,,	56,400
ዳቦ ጋሌጣና ብስኩት	,,	15,200
ፓስታና ማካሮኒ	,,	9,000
መጠጥ		
ለስላሳ መጠጥ	ጠርሙስ (በሺህ)	69,566
ቢራ	ሄክቶ ሊትር	500,000
ወይን ጠጅ	ጠርሙስ	2,400,000
ትምባሆ		
ሲጋራ	ቶን	2,800
ጨርቃጨርቅ		
ብትን ጨርቅ	ካሬ ሜትር	910,000
ድርና ማግ	በቶን	4,732
ብርድ ልብስ	በቁጥር	100,000
ጆንያ	በቶን	2,958
ቆዳና ጫማ		
ጫማዎች	በጥንድ	4,120 000
	ሳሙና	
ኬሚካል	በቶን	2,400
ብረታ ብረት		
ምስማርና ሽቦ	ቶን	10,000
ባትሪ ድንጋይ	ቁጥር	25,000,000
ጃንጥላ	ቁጥር	4.000,000

ባጠቃላይ በመንግሥት የኢንዱስትሪ ዘርፍ እስከ አሁን ለተከናወኑትና አሁን በመከናወን ላይ ለሚገኙት የግንባታ ሥራዎች (የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ማስፈጸም) እስከ 1976 የበጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በጠቅላላው ወደ ብር 1,020.67 ሚሊዮን ያህል ወጪ የተደረገ ሲሆን ፣ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው ፡[7] —

1. የግንባታ ሥራቸው ለተጠናቀቀ ፕሮጀክቶች ብር 318.13 ሚሊዮን
2. የግንባታ ሥራቸው በመካሄድ ላይ ላሉ ፕሮጀክቶች 523.65 ሚሊዮን
3. ለአረጁ መሣሪያዎችና ሕንጻዎች መተኪያ 187.89 ሚሊዮን ድምር 1,020.67 ሚሊዮን ነው ።

ከላይ ከተጠቀሱት የግንባታ ሥራዎች በተጨማሪ ወደፊት ወደ ግንባታ ሥራ የሚሸጋገሩ 36 ያህል የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች በልዩ ልዩ የቅድመ ግንባታ ሥራዎች ደረጃ (መለስተኛ ጥናት ፣ ዝርዝር ግምገማና ውሳኔ ፣ መዋዕለ ንዋይ ጥያቄ ፣ ጨረታና ኮንትራት ነድፍ ሥራ) ላይ ይገኛሉ ። እነዚህ ፕሮጀክቶች የሀገሪቱ የፋይናንስ አቅም በፈቀደው መጠን በሚቀጥሉት ቅርብ ዓመታት ወደ ግንባታ ሥራ ይሸጋገራሉ ።

ከዚህ በላይ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማስፋፋት በተጨባጭ ስለተወሰዱት እርምጃዎችና ስለተከናወኑት ተግባሮች ባጭሩም ቢሆን ለመግለጽ ተሞክሯል ። እስከ አሁን ማምረት የጀመሩትና በቅርብ ጊዜም የሚጀምሩት ፕሮጀክቶች ከሠርቶ አደሩ

Digitized by Google



በኢትዮጵያ ፣ በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክና በአብዮታዊት ኪዩባ መንግሥታት
ትብብር የተሠራው የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ
— ከቅርብ ሲታይ



— ፋብሪካው ከሩቅ ሲታይ

Digitized by Google



ኋላቀር የእርሻ መሣሪያዎችን የሚተካው በኢትዮጵያና በሶቪየት ህብረት መንግሥታት ትብብር
የተሠራው የትራክተር መገጣጠሚያ ፋብሪካ

— በፋብሪካው የተገጣጠሙ የመጀመሪያ ትራክተሮች

Digitized by Google



በኢትዮጵያና በቼኮዝሎቫኪያ መንግሥታት ትብብር የተሠራው የሐረር ቢራ ፋብሪካ



በኢትዮጵያና በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ መንግሥታት ትብብር በባህርዳር የተሠራው
የምግብ ዘይት ፋብሪካ

Digitized by Google



በኢትዮጵያ፤ በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክና በቼኮዝሎቫኪያ መንግሥታት ትብብር የተሠራው
የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ

Digitized by Google

ሕዝብና ከአገሪቷ የልማት ፍላጐት አን
ፃር ሲታዩ በቂ ናቸው ተብሎ ባይገመትም፣
ከነበሩትና ካሉት የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔ
ታዎች አኳያ ሲታይ በግንባታ ረገድ የተ
ከናወኑት ሥራዎች የሚያበረታቱ ናቸው
ለማለት ይቻላል ።

ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ከነባር ፣
ከአዲስና ከተስፋፉ ፋብሪካዎች የሚገኘው
ምርት በሀገሪቷ ውስጥ ያለውን የኢንዱስ
ትሪ ዕቃዎች ፍላጐት ሙሉ በሙሉ አር
ክቷል ባይባልም ፣ በአንዳንድ ዕቃዎች
ላይ የነበረው ከፍተኛ እጥረት በመጠኑም
ቢሆን እየተቃለለ ነው ።

ግንባታን በሚመለከት ከላይ የተዘረዘ
ሩት ሁኔታዎች እስካሁን በመንግሥት የኢ
ንዱስትሪ ዘርፍ የተከናወኑትን ሥራዎች
የሚያመለክቱ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በዚ
ህ የሥራ መስክ በአሁኑ ወቅት የግንባታ ሥ
ራቸው ተጠናቆና በቅርቡም ሥራቸ
ውን የጀመሩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች
አሉ።ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናዝሬት
ትራክተር ፣ሙገር ሲሚንቶ ፣ኮምቦልቻ ጨር
ቃ ጨርቅና ሐረር ቢራ ፕሮጀክቶች ናቸው።

የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶች የሀገሪቱ
የኤኮኖሚ አቅም በፈቀደው መሠረት እን
ዲጨምር ለማድረግ አዲስ ፋብሪካዎችን
ከማቋቋምና አንዳንድ ነባር ፋብሪካዎችን
ከማስፋፋት በተጨማሪ የብዙዎቹ ነባር
ፋብሪካዎች አሮጌ መሣሪያዎችና ሕንጻ
ዎች በአዲስ እንዲተኩና እንዲጠገኑ በማ
ድረግ ረገድ የግንባታ ሥራ ተካሂዷል ።

የዚህ ግንባታ ሥራ ዋና ዓላማ ብዙዎቹ
ነባር ፋብሪካዎች አሮጌ እንደመሆናቸው
መጠን ምርታቸው እንዲጨምር አለበለዚ
ያም እንዳይቀንስ ለማድረግ ነው ። ቀደም
ብሎ ለታየው የነባር ፋብሪካዎች የምርት
ጭማሪ አንዱ ምክንያት አሮጌ መሣሪያዎ
ችና ሕንጻዎች በአዲስ በመተካታቸውና
በመጠገናቸው ነው ። በዚህ ግንባታ የማም
ረቻና የአገልግሎት ሰጪ መሣሪያዎችንና
ሕንጻዎችን ለመተካት፣ ለማደስና ተጨማሪ
አዲስ ለመግዛት ወይም ለመሥራት እስከ
1973 የበጀት ዓመት በጠቅላላ ብር 187.9
ሚሊዮን የካፒታል ወጪ ተደርጓል ።

የኢንዱስትሪ ድርጅቶች በመንግሥት
ቁጥጥር የሕዝብ ሀብት ከሆኑበት ጊዜ
ጀምሮ ክፍለ ኢኮኖሚውን በማስተዳደር ፣
በማደራጀትና የግንባታ ሥራዎች በማከ
ናወን በኩል በተከናወኑት ሥራዎች አኳያ
ባለፉት ዓመታት በርከት ያሉ ችግሮች
አጋጥመዋል ። ችግሮቹ በአብዛኛው ያለ
ፈው ሥርዓት ቅሪቶችና በአብዮቱ ሂደት
ውስጥ የተከሰቱም ናቸው ። ክፍለ ኤኮኖ
ሚው ካጋጠሙት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ
የሚከተሉት ናቸው ።

የማምረቻ መሣሪያዎች ሁኔታ፣— ከአብ
ዮቱ በፊት የተቋቋሙት አብዛኛዎቹ ፋብ
ሪካዎች ከተለያዩ አገሮች የተገዙ ፣ ለረ
ዥም ዘመን ያገለገሉና ያረጁ በመሆና
ቸው ፣ ለእነዚህ መሣሪያዎች የመለዋወጫ
ዕቃዎች የማግኘቱ ችግር የጐላ ከመሆኑም
በላይ አብዮቱ ያስኮረፋቸውና ጥቅማቸ
ውን የነካባቸው የመለዋወጫ እቃ ሻጮች
የማቅረቢያ ጊዜን በማራዘም ፣ ዋጋን በማ
ስወደድ ፣ ቀድሞ ያልነበሩ የክፍያ ግዴ
ታዎችን በመጠየቅ ፣ አልፎ አልፎም ለመ
ሸጥ ፈቃደኛ ባለመሆንና በመሳሰሉት ምክ
ንያቶች የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት ፈጥ
ረዋል ። የጥገና መመሪያዎችን በማው
ጣት ፣ በእቅድ ወቅታዊ ጥገናን በማካ
ሄድ ፣ ለመሣሪያዎች ከፍተኛ እንክብካቤ
በማድረግ ችግሮቹን ለመቅረፍ ጥረት ተደ
ርጓል ።

የሰለጠነ የሰው ኃይል፣— የቀድሞ ባለን
ብረቶች ዋና ዓላማቸው ከፍተኛ ትርፍን
ለረዥም ጊዜ ለማጋበስ ስለነበር ለብዝበዛ
የሚያመቻቸውን የአሠራር ዘዴ በመጠ
ቀም የቴክኒክ ፣ የሒሳብ ፣ የሥራ አመራርና
ከፍተኛ የሥራ መደቦችን እራሳቸውና
ሌሎች የውጭ ዜጎች እንዲይዙ በማድረግ
ሰፊው የፋብሪካ ሠራተኛ የቴክኒክና
ሌሎች ሙያዎች እንዳይገበይ አድርገውት
ነበር ። የማምረቻ ድርጅቶች በመንግሥት
ቁጥጥር ስር ውለው ባለንብረቶችና የውጭ
ዜጎች ሲለቁ በፋብሪካዎች ውስጥ የቴክ
ኒሽያኖችና የሌሎች ባለሙያዎች እጥረት
ሊፈጠር ችሎአል ። በልዩ ልዩ የሙያ ማሻ
ሻያ መስኮች ሠራተኞችን በማሰልጠንና
በሥራው ላይ እንዲለማመዱ በማድረግ

Digitized by Google

የውጭ ምንዛሪ ሁኔታ ፤ — ሀገሪቱ በወረሰችው የምርት ኃይሎች እድገት ደረጃ ዝቅተኛነት የተነሳ ለኢኮኖሚና ለሶሻል ልማቶች የሚያስፈልጉት መሣሪያዎች የሚመጡት ከውጭ በመሆኑ እነዚህን ለማስመጣት የውጭ ምንዛሪ ማስፈለጉ ግልጽ ነው ። ይሁን እንጂ በውጭ ንግድ በኩል የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ መጠን የሚፈለገውን ያህል ባለመሆኑ ለኢንዱስትሪ ግንባታ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችንና ዕቃዎችን ለማስመጣት የውጭ ምንዛሪ እጥረት አንዱ ከፍተኛ ችግር ነው ። ይህ ችግር ከወዳጅ የሶሻሊስት አገሮችና ከሌሎች ምንጮችም በሚገኘው እርዳታና ብድር በመጠኑም ቢሆን የተቃለለ ቢሆንም በመሠረታዊ የኢኮኖሚና የሶሻል እድገታችን ላይ ተጽዕኖ ለማቃለል ያልተቆጠ በጥረት ይጠይቃል ።

የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተግባሮች ግንኙነት

በተለይ ከኢሠፓአኮ መከሰት በፊት በብዙ አካባቢዎች የኢኮኖሚ ግንባታውን ከፖለቲካ ግንባታው ጋር አዋህዶ የመመልከት ዝንባሌ አልሠፈነም ነበር ። ይህ ደግሞ በአብዮቱ ካለማመን ወይም አብዮቱን ካለመደገፍ ብቻ የሚመነጭ ሳይሆን በአብዛኛው በፊውዶ ቡርዣው ሥርዓት ከተወረሱ የአመለካከት ችግሮች ጋር የተያያዘ ነው ። ይህ ችግር በፖለቲካው ሂደትና በኢኮኖሚው ግንባታ መካከል መኖር የሚገባውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ከማዛባቱም በላይ ሁለቱን ከፋፍሎ በማየት አንዱ ለአንዱ የሚሰጠውን ድጋፍ ተግባራዊ ሳያደርገው ቆይቶ ነበር ። ችግሩ በአመዛኙ የሚመነጨው የተያያዝነው የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ማኔጅመንት መርሆዎችና ሥልቶች በሥራ አመራር አካሉች ዘንድ በጥልቀት ያልሰረጸ በመሆኑ ነው ። ይህ ችግር በአንድ በተወሰነ የአሠራር ስልት ላይ የሚንጸባረቅ ሳይሆን በአጠቃላይ የፋብሪካን አመራር በሚመለከት በሚከናወነው ሥራ ሁሉ ተጽዕኖ የሚያሳይ ነው ። ከኢሠፓአኮ መከሰት ወዲህ ችግሩ እየተቃለለ መጥቷል ።

አብዮቱ አሁን በደረሰበት የእድገት ደረጃ በፋብሪካዎች በተቋቋሙት መሠረታዊ ድርጅቶች ፣ የሥራ አመራር ፣ የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴዎች ፣ የሠራተኛ ማኅበራት ልዩ ልዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች የዓላማና የተግባር ውህደት ፈጥረው ለአብዮቱ ግብ መምታት እንዲታገሉ ለማድረግ ፣ በተለያዩ ወቅቶች ሴሚናሮችና ኮርሶች ተሰጥተዋል ። በርዕዮተ ዓለም ሥርጭትም በኩል የተደረገው ጥረት ሁኔታውን ለማስተካከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ይሁን እንጂ ችግሩን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ የበለጠ ጥረትና ትግል ይጠይቃል ።

ለጠንካራ የብሔራዊ ኢንዱስትሪ ግንባታ ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎች

መዋዕለ ንዋይ ፦ አብዮታዊት ኢትዮጵያ የወረሰችውን ደካማና ጥገኛ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ገጽታዎች በመለወጥ ጠንካራና ነፃ ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው ። ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች አንዱና ዋናው ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልገውን መዋዕለ ንዋይ በብዛት ማግኘት ነው ። የሚፈለገውን መዋዕለ ንዋይ በብዛት ለማግኘት ዋናው ስልት የሀገሪቱን የጥሪት ክምችት ማሳደግ ነው ። ይህ የጥሪት ክምችት ከየትኛው የኢኮኖሚ ዘርፍ ሊመነጭ እንደሚችል የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ባሳለፈው ውሳኔ ተገልጿል ። ለስብሰባው በቀረበው የኢኮኖሚ ዘርፍ ሪፖርት እንደተጠቀሰው ፣ «የተያያዝነው የሶሻሊስት ግንባታ የሚጠይቀውን የጥሪት ክምችት ለማስገኘት የሚቻለው ከአገሪቱ አጠቃላይ ምርት ውጤት ውስጥ ከፊሉን ያህል አስተዋጽኦ ከሚያደርገውና ከሠርቶ አደሩም መካከል 85 በመቶው ያህሉ ከሚተዳደርበት ከእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ መሆኑ አያጠያይቅም ።» ይሁን እንጂ የኢንዱስትሪው ኢኮኖሚ ዘርፍ ከእርሻው የሚጠበቀውን የጥሪት ክምችት ከፍ ለማድረግና የዚህን የኢኮኖሚ ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ ኢንዱስትሪ ራሱ አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት ። በሁለቱ የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከልም መኖር የሚገባው መደጋገፍ መጠናከር አለበት ። የሚፈለገው አስተዋጽኦና መደጋገፍ የሚከሰተው ኢንዱስትሪው ለእርሻው ዘርፍ የሚያስፈልጉትን እቃዎች ሲያቀርብና በአንጻሩ የእርሻው ዘርፍ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉትን ጥሬ ዕቃዎች ለማቅረብ ሲችል ነው ። ከድርጅትና ከወል ይዞታ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት የእርሻውን ዘርፍ ምርታማነት ከፍ ለማድረግ ከሚያስፈልጉት ነገሮች ዋና

Digitized by Google

ዎቹ የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎች ፣ የአፈር ማዳበሪያና የጸረሰብል መከላከያ ኬሚካሎች ናቸው ። ምንም እንኳን ኢንዱስትሪው አሁን ባለው አቅም እነዚህን እቃዎች በሙሉ ሊያቀርብ ይችላል ባይባልም የተሻሻሉ መሣሪያዎችን ለማቅረብ እንዲችል ከፍተኛ ጥረት መደረግ አለበት። እነዚህን መሣሪያዎች በማምረት ኢንዱስትሪው እርሻውን ካልደገፈው ፣ ከእርሻው የሚጠበቀው ምርታማነትና ክምችት ሙሉ በሙሉ እውን ሊሆን አይችልም ። ኢንዱስትሪው የአፈር ማዳበሪያና ጸረ ሰብል ኬሚካሎችን ለማምረት እንዲችል ከአሁኑ ዝግጅት መጀመር ያስፈልጋል ።

በአንጻሩ ኢንዱስትሪው የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የፍጆታ እቃዎች በሚፈለገው መጠን ለማቅረብ ከእርሻው የኢኮኖሚ ዘርፍ ጥሬ ዕቃዎችን በሚፈለገው ጥራትና መጠን ማግኘት አለበት ። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ እንደሚያሳየው እርሻው ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ጥሬ ሸቀጥ በበቂ መጠን አያቀርብም ። ኢንዱስትሪውም እንደዚሁ ለእርሻው የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎችን የማቅረብ አቅሙ በጣም ውሱን ነው ።

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው የእርሻውና የኢንዱስትሪው ዘርፎች ካልተደጋገፉ የእርሻውን ምርታማነት ለማሳደግ ስለሚያዳግት ከዚህ ዘርፍ የሚገኘውና ወደ ኢንዱስትሪ ልማት የሚዛወረውን ክምችት በቂ ሊሆን ስለማይችል የጠንካራ ኢንዱስትሪ ግንባታ ዓላማችንን ለማሳካት ከባድ ጥረት ይጠይቀናል ።

<u>የኃይል ምንጭና ሌሎች</u> :- ኢንዱስትሪ ለአንድ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ መሠረት ሊሆን የሚችለው ለዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ ማደግና መስፋፋት የሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው ። መሠረታዊና ተዳሚ ከሆነው ከመዋዕለ ንዋይ አስፈላጊነት በተጨማሪ ኃይል ፣ ጥሬ ዕቃዎች ፣ ትራንስፖርትና ገበያ ተሟልተው መገኘት ለዳበረ እንዲስትሪ ግንባታ ወሳኝ ነው ።

ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገው ኃይል ከፍተኛ ስለሆነ ይህ ኃይል በተፈለገው መጠን ሊመነጭ የሚችለው ከኤሌክትሪክና ከነዳጅ ዘይት እንጂ በሀገራችን ለብዙ ዘመናት ከተለመደው የኃይል ምንጭ ሊሆን አይችልም ። ስለሆነም ለኢንዱስትሪው ግንባታ የሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ ዘመናዊ የኃይል ምንጮችን ማስፋፋት ነው ። ይሁን እንጂ ዘመናዊ የኃይል ምንጮችን ማስፋፋት ራሱ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ ስለሆነ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በየቦታው የኃይል ምንጮችን ለማቋቋም ያዳግታል ። ስለዚህ ፋብሪካዎች የሚቋቋሙባቸው ቦታዎች (ቀጠናዎች) በቅድሚያ ተመርጠው የኃይል ምንጮችም በእነዚህ ቀጠናዎች እንዲቋቋሙ ዝግጅት መደረግ አለበት ።

በአሁኑ ወቅት ከእርሻው ክፍ ለኤኮኖሚ ለኢንዱስትሪው የሚያስፈልጉት ጥሬ ዕቃዎች በበቂ መጠንና ጥራት አይቀርቡም ። ለዚህ ዋና ምክንያት በእርሻው ዘርፍ ያለው የምርት መጠን በቂ አለመሆንና ከቅንጅት ጉድለት የተነሳ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎች ምርት ትኩረት ስላልተሰጠው ነው ።

ይህ የቅንጅት ጉድለት መስተካከል ያለበት ከመሆኑም በላይ ለኢንዱስትሪው ጥሬ ዕቃዎች ምርት የሚሰጠው ትኩረት ከመቸውም የበለጠ መሆን አለበት ። ለዳበረ ብሔራዊ ኢንዱስትሪ ግንባታ የሚያስፈልገው አንዱ ቅድመ ሁኔታ ዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው ። ከአገሪቱ መልክአ ምድር አቀማመጥ አንጻር ሲታይ የዘመናዊ ትራንስፖርት አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱ ግልጽ ነው ። በመሆኑም የኢንዱስትሪው ክፍለ ኤኮኖሚ የሚያስፈልጉትን የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች ለማግኘትና የሚያመርታቸውን ምርቶች ለዋና ዋና ገበያዎች ለማቅረብ ከጠረፍ አካባቢዎች በስተቀር ከፍተኛ የሆነ የትራንስፖርት ችግር አልገጠመውም ። ነገር ግን የትራንርፖርት ችግር ከፍተኛ አይደለም ሲባል ከመንገዶች መስፋፋት አንጻር እንጂ ለትራንስፖርት ከሚጠየቀው ወጭ አንጻር አይደለም ። በልዩ ልዩ ምክንያቶች በአገራችን ውስጥ ለመንገድ ትራንስፖርት የሚከፈለው ወጭ ከሌሎች በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ከሚገኙ አገሮች ወጭ ጋር, ሲወዳደር ከፍተኛ ነው ። በዚህ የተነሳ የእንዱስትሪ ጥሬ እቃዎችንና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማጓጓዝ የሚከፈለው ወጭ ከፍተኛ በመሆኑ በፋብሪካዎች የማምረቻ ወጭ ላይ ተጽእና አለው ። ይህ የማምረቻ ወጭ በኢንዱስትሪ ምርቶች

Digitized by Google

ችግሩን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማቃለል ሙከራ ተደርጓል ። እስከ አሁን 76,540 ያህል የፋብሪካ ሠራተኞች በሥራ አመራር ፣ በሂሳብ አያያዝ ፣ በምርትና በጥገና የሙያ መስኮች በሀገር ውስጥ የሰለጠኑ ሲሆን በውጭ አገርም ከ300 የማያንሱ በአብዛኛው በቴክኒክ ሙያዎች ሰልጥነው ተመልሰዋል ።

<u>የጥሬ ዕቃዎች አቀራረብ</u> ፡— ለፋብሪካ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን በሚመለከት የገጠሙ ችግሮች በልዩ ልዩ መስኮች የተከሰቱ ሲሆን በተለይ በሚፈለገው መጠን አለመገኘትና የዋጋቸው በየጊዜው መናር ጉልሆቹ ናቸው ። የጥሬ ዕቃዎች በሚፈለገው መጠን አለመገኘት ጉልቶ የሚታየው በሀገር ውስጥ በሚመረቱ የጥሬ ዕቃዎች ዓይነት ላይ ነው ። የቆዳ፣ የዱቄትና የዘይት ፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃ በሚፈልጉት መጠን አለማግኘት የተነሳ ከአቅማቸው በታች ለማምረት ተገደዋል ። በተጨማሪም የእንጨት ፋብሪካዎች የሚፈልጉትን ያህል ግንድ ባለማግኘታቸው ማምረት የሚገባቸውን ያህል አያመርቱም ። እነዚህንና የመሳሰሉትን ችግሮች ለመቋቋም ጥረቶች እየተደረጉ ነው ።

የጥሬ ዕቃዎች ዋጋ በየጊዜው መናር በተለይ የሚመለከተው ከውጭ የሚገዙ ዕቃዎችን ሲሆን ይህም ሁኔታ ምርታቸው በውጭ ጥሬ ዕቃዎች ላይ በብዛት ጥገኛ በሆኑ እንደ ብረታ ብረት ፣ ፕላስቲክ፣ ቀለማ ቀለም ፣ ጎማ ፣ ወረቀት ፣ ጆንያ ብርድ ልብስና በመሳሰሉት ፋብሪካዎች ላይ ችግሩ ተባብሷል ። ይህ ችግር በእነዚህ ፋብሪካዎች የፋይናንስ አቋም ላይ ድክመትን አስከትሏል ። የውጭ ጥሬ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት ውሱን ቢሆንም ጥረት እየተደረገ ነው ።

<u>የፋይናንስ አቋም</u> ፡— በቅድመ አብዮት የተቋቋሙ ፋብሪካዎች አብዛኞቹ በተቋቋሙበት ጊዜም ሆነ በኋላ የካፒታልና የእዳ አቅማቸው ያልተመጣጠነ ነበር ። የቀድሞ ባለንብረቶች መጠነኛ ካፒታል ሥራ ላይ በማዋል በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ትርፍ ማግኘትና ትርፍንም እያሟጠጡ መውሰድ ስለነበር ብዙዎቹ ፋብሪካዎች በተወረሱ ጊዜ የተዳከመ የገንዘብ አቋም ነበራቸው ። በዚህ ምክንያት ፋብሪካዎች የሕዝብ ሀብት እንዲሆኑ በተደረገበት ወቅት በአብዛኛው በእዳ የተዋጡና የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ እጥረት የነበራቸው ነበሩ ። ከዚያም በኋላ በየጊዜው የደረሰው የጥሬ ዕቃዎች ዋጋና የሌሎች ወጭዎች ጭማሪ በፋብሪካዎች የትርፍና ኪሣራ ሁኔታ ላይ እንዲሁም ባጠቃላይ በፋይናንስ አቋማቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕና አስከትሏል ። በቁጠባ በመሥራት ከፍተኛ ምርት በአነስተኛ ወጪ ለማስገኘት የሥራ አመራርና የአመራር ዘዴዎች ቢሻሻሉም መፍትሄው ጊዜን የሚጠይቅ ነው ።

<u>የትራንስፖርት ሁኔታ</u> ፡— የኢንዱስትሪን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ረገድ የነበረው የትራንስፖርት ችግር ጥሬ እቃዎችን ወደ ፋብሪካዎች ከማድረስና ከፋብሪካ ምርቶችን ከማከፋፈል ጋር የተያያዘ ነው ። ይህ ችግር በመጀመሪያዎቹ የአብዮት ዓመታት በመላው የሀገሪቱ ፋብሪካዎች የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕና ያስከተለ ቢሆንም አብዮታዊው መንግሥት በወሰዳቸው ልዩ ልዩ እርምጃዎች ለማቃለል ተችሏል።

<u>የአሠራር ሥርዓት</u> ፡— አብዛኞቹ የቀድሞ ባለንብረቶች የፋብሪካዎችን አስተዳደር ፀራሳቸውና በመሰሎቻቸው አማካይነት ያካሂዱ በነበረበት ወቅት ቁጥጥሩና ዲሲፕሊኑ ከሥራ መወገድ ጋር የተያያዘ ስለነበር ሠራተኛው ምንም ዓይነት ዋስትና አልነበረውም። በመሆኑ በፍራቻ ለጥ ሰጥ ብሎ ይሠራ ነበርና ምርታማነቱም የተሻለ ነበር ። አሁን ግን አብዮቱ ሠራተኛውን ቋሚና ባለ ልዩ ልዩ መብቶችና ጥቅሞች ባለቤት አድርጓል ፤ ይሁንና ምርታማነቱ መጠናከር ያለበት ነው ።

Digitized by Google

ዋጋ ላይ ስለሚጨመር የአንዳንድ እቃዎች ዋጋ ከተጠቃሚዎች የመግዛት አቅም በላይ የሚሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል ። ይህ በበኩሉ የእነዚህን እቃዎች ገበያ እንዳይስፋፉ ስለሚያደርገው የኢንዱስትሪውን የመስፋፋት እርምጃ ይገታዋል ።

የሀገራችን ዘመናዊ ትራንስፖርት አብዛኛው በየብስ ላይ ሆኖ በጭነት መኪናዎች አማካይነት የሚከናወን መሆኑ ይታወቃል ። ለዚህ ዓይነት ትራንስፖርት ወጭ መናር ዋናው መንስኤ የነዳጅ ዘይት ዋጋ ከፍተኛ መሆን ነው ። ይህም ደግሞ ከብሔራዊ ኤኮኖሚው አስተዳደር ቁጥጥር ውጭ ስለሆነ የትራንስፖርት ወጭን ዝቅ ለማድረግ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው ። ስለዚህ የትራንስፖርት ወጭን ለመቀነስና ብሎም የኢንዱስትሪ ማምረቻ ወጭን በመጠኑም ቢሆን ለመቀነስ ኢንዱስትሪዎች እንደ ጠባያቸው በጥሬ ዕቃዎች አቅራቢያና ወይም በብዛት ምርታቸውን በሚጠቀመው ክፍል አቅራቢያ መቋቋም ይኖርባቸዋል ። ከኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ ወዲህ በመቋቋም ላይ የሚገኙት ፋብሪካዎች ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ ከሞላ ጎደል ያሟላሉ ። ከትራንስፖርት ወጭ ቅነሳና ከኢንዱስትሪ ልማት ክፍለ ሀገራዊ ስርጭት አንጻር ኢንዱስትሪዎችን የማቋቋሙ ተግባር መቀጠልና መጠናከር ይኖርበታል ።

ሌላው ለዳበረ ኢንዱስትሪ ግንባታ የሚያስፈልገው ቅድመ ሁኔታ የገበያ መስፋት ነው ። የቀላል ኢንዱስትሪዎችን ምርት ገበያ በሚመለከት ላይ ላዩን ሲታይ ከ30 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያላት አገር በዚህ በኩል ችግር ያለ አይመስልም ። ነገር ግን ለገበያ መስፋት የሕዝብ ብዛት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ቢሆንም ወሳኙን ሚና የሚጫወተው ግን የሕዝብ የመግዛት አቅም ነው ። በሌላ በኩል ለገበያ መስፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርገው የእቃዎች ዋጋ ዝቅተኛ መሆን ነው ። ከቅድመ አብዮት በወረስናቸው ልዩ ልዩ ሁኔታዎች የተነሳ በአገራችን ውስጥ በአንድ በኩል የሕዝቡ የመግዛት አቅም ከፍተኛ አይደለም ። በሌላ በኩል የዕቃዎች ዋጋም ዝቅተኛ አይደለም ። እነዚህ ሁኔታዎች ለቀላል ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ገቺ ናቸው ። የሕዝቡን የመግዛት አቅም ለማሳደግ ያለው ዋና መፍትሄ በልዩ ልዩ የኤኮኖሚ መስኮች የተሰማራውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ምርታማነት ማሳደግና ጠቅላላ ብሔራዊ ምርትን ከፍ ማድረግ ነው ። የምርታማነት ማደግና የብሔራዊ ምርት ከፍ ማለት የሕዝቡን ገቢ ይጨምራል ። የመግዛት አቅሙንም ያጠነክረዋል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Befekadu Degefe, *Industrialization Investment Policy and Foreign Capital in Ethiopia* 1950-1974, *Institute* of Development Research, Addis Ababa University, Jan. 1980.
2. ኅብረተሰብአዊነት ፡— የኢትዮጵያ ሶሻሊዚም ፡ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት መመሪያ ፡ ታኅሣሥ 11 ቀን 1967 አዲስ አዲስ አበባ ፡ ገጽ 10 ።
3. የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ታሪክ ፡ ኢንዱስትሪ ሚ/ር የካቲት 1976፡አዲስ አበባ ፡ ገጽ 90 ።
4. ከላይ የተጠቀሰው ።
5. ከላይ የተጠቀሰው ፡ ገጽ 93 ።
6. ከላይ የተጠሰው ።
7. ከላይ የተጠቀሰው ፡ ገጽ 99 ።

Digitized by Google

የዜጐች መሠረታዊ መብቶች ፡ ነፃነቶችና ግዴታዎች

ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ገጽታዎች

(ክፍል ሁለት)

መዝገቡ ምትኬ

በክፍል አንድ (መስከረም ፣ ቅጽ 4 ቁጥር 18) ሰኔ 1976 በሕዝቦች መራራና ያላሰለሰ ትግል ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከጊዜ ወደጊዜ እየዳበሩ መምጣታቸው ተገልጿል። በተለይም በ17ኛውና በ18ኛው ምዕተ ዓመት በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይና በአሜሪካ በተካሔዱት በጊዜው ተራማጅ የነበሩ የቡርዧ አብዮቶች ያስገኙት ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች እያደር የሌሎች አገሮች ሕዝቦችንም መቀስቀሳቸውና የነሱም ጥያቄዎች መሆናቸው አልቀረም። ይሁን እንጂ የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች በየአገሮች የእድገት ደረጃ የሚወሰኑ ናቸው። በመሆኑም በፊውዳሊዝም ሥርዓት የሚጠየቀውና በትግል የሚገኘው መብትና ነፃነት በዓይነቱና በመጠኑ በካፒታሊዝም ሥርዓተ ማኅበር ከሚጠየቀው ዝቅተኛ ነው። ይህም ማለት የፊውዳል ሥርዓት በሰፈነበት አገር ያሉ ሕዝቦች የሚኖራቸው መብትና ነፃነት በካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ ካሉ ሕዝቦች መብትና ነፃነት ያነሰ ነው። የሶሻሊስት ሥርዓት በሰፈነበት አገር ያሉ ሕዝቦች መብትና ነፃነት ደግሞ ከካፒታሊስት አገሮች ከሚኖሩ ሕዝቦች መብትና ነፃነት እጅግ የላቀ ነው።

በሐያኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ የዓለም ሕዝቦች የመብትና የነፃነት መበላለጥ በጣም ጉልህ ሆኖ ታየ። ምዝብር. ሕዝቦችና ደጋፊዎቻቸው ለመብትና ለነፃነት የሚያካሒዱት ትግል እየተጠናከረና እየተስፋፋ መሔዱ የግድ ነበር። የመበላለጡ ሁኔታ ጉልህ መሆንና የትግሉ መስፋፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰው ልጅ የመብትና የነፃነት ጥያቄን ፍጹም ችላ ሊባል የማይችል ጉዳይ አደረጉት። በዚህ ወቅት በተለይ የንግድና የመገናኛ ዘርፎች የበለጠ በመስፋፋታቸው ምክንያት የአንድ አገር ዜጎች ከሀገራቸው ወጥተው በሌሎች አገሮች ውስጥ ስለሚኖሩ የዜጎች መብትና ነፃነት መከበርና አለመከበር ጉዳይ የአንድ አገር ብቻ አሳሳቢ ችግር ሳይሆን ሌሎች ብዙ አገሮችን (መንግሥታትን) የሚመለከት ሆን። ከዓለም መንግሥታት መካከል አንዳ

Digitized by Google

ጉዶች በመሰብሰብ በጋራ ስለሚመለከታቸው ጉዳይ ተወያይተው በስምምነት የሚያሳለፉትን ውሳኔ በማጽደቅ የዓለም አቀፍ ሕግን ቢያወጡም ፣ ሕጉ በተለይ የአባል መንግሥታትን መብትና ግዴታ እንጂ ግለሰቦችን በቀጥታ የማይመለከት ነበር ። ግለሰቦችን የሚመለከት ዓለምአቀፍ ሕግ ቢኖርም የሚያስፈጽሙላቸው የየሀገሮቻቸው መንግሥታት እንጂ ራሳቸው ግለሰቦች አይደሉም ።

ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ የፈረሰው የቀድሞው መንግሥታት ማኅበር (League of Nations) በ1920 ሲቋቋም ስለሰብአዊ መብቶች የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በቻርተሩ ተጠቅሰው ነበር ።[1] ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መፈጸም በኋላ በ 1948 የተቋቋመው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም የሰብአዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ጥያቄ በዝምታ አላለፈውም ። ከድርጅቱ ዓላማዎች መካከል «በዘር ፣ በጾታ ፣ በቋንቋ ወይም በሃይማኖት ላይ ልዩነት ሳይደረግ የሰብአዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን መከበር ማበረታታትና ማራመድ» መሆኑን ቻርተሩ በግልጽ አመልክቷል ። ከዚህም በላይ በሕዝቦች የእኩልነት መብቶችና የራስን ዕድል በራስ መወሰን መብት መርሆዎች መከበር ላይ በመመሥረት የሀገሮችን ሰላማዊና ወንድማዊ ግንኙነት ለመፍጠር እንዲቻል የተባበሩት መንግሥታቱ-

1. ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ፣ የተሟላ ሥራ ፣ የኢኮኖሚና የሶሻል ሁኔታዎች እንዲመሠረቱና እንዲስፋፉ ፤

2. በዘር ፣ በቋንቋ ፣ በጾታና በሃይማኖት ላይ ልዩነት ሳይደረግ ሰብአዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች እንዲከበሩና እንዲጠበቁ ፤

3. ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊ የጤናና የመሳሰሉት ችግሮች መፍትሔዎች እንዲገኙ ፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ የባህልና የትምህርት ትብብሮች እንዲዳብር ያደርጋል በማለት በቻርተሩ አንቀጽ 55 ላይ ተመልክቷል ።

የድርጅቱ አባል አገሮች ሁሉ በዚህ በአንቀጽ 55 ላይ የተመለከቱትን ዓላማዎች በግልና ከድርጅቱ ጋር በመተባበር ተግባራዊ ለማድረግ ቃል መግባታቸውም በዚሁ ቻርተር አንቀጽ 56 ላይ ተደንግጓል ።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር መሠረት የሕዝቦችን መሠረታዊ ነፃነቶችና ሰብአዊ መብቶች ለማክበር አባል መንግሥታት ቃል ይግቡ እንጂ ፣ ሰብአዊ መብቶቹና መሠረታዊ ነፃነቶቹ ተዘርዝረው ባለመገለጻቸው በመብቶችና ነፃነቶች ዓይነት ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች አከራካሪ ሆነው ነበር ። ይሁን እንጂ የድርጅቱ ቻርተር በተፈረመ በሦስተኛው ዓመት በ1948 የሰብአዊ መብቶች ሁለንታዊ መግለጫ (The Universal Declaration of Human Rights) በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉ ባ ኤ መውጣት ለጥያቄዎቹ መልስ ሰጠ ።

መግለጫው እንደ ድርጊት ፕሮግራም የሚያገለግል እንጂ የዓለም አቀፍ ሕግ አካል አይደለም ። ሕጋዊነት የሌለው በመሆኑ በፕሮግራሙ የተዘረዘሩትን ሰብአዊ መብቶች ተግባራዊ የማስደረግ ኃይል የለውም ። ለሰላም ፣ ለፍትሕ ፣ ለነፃነትና ለዜጎች መብት ለሚደረገው ትግል የጋራ አቅጣጫን የሚያሳይ ፣ በዓይነቱ የመጀመሪያው የሰዎችን የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የባህል መብቶችንና ነፃነቶችን ያቀፈ ሰነድ በመሆኑ በታሪክ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው ። መግለጫው የፖለቲካ ሰነድ ይሁን እንጂ ቀስ በቀስ ወደ ሕግነት እንደሚለወጥ ተስፋ ይደረጋል ። እስከ አሁንም ቢሆን በአንዳንድ ሶሻሊስት አገሮች በመግለጫው ላይ ከተጠቀሱት የተሻሉ መብቶችና ነፃነቶች በሕገ መንግሥቶቻቸው በመደንገግና ቁሳዊ ዋስትና በመስጠት ዜጎቻቸው እንዲጠቀሙባቸው አድርገዋል ፤ እያደረጉም ነው ።

ከሰብአዊ መብቶች ሁለንታዊ መግለጫ መውጣት በኋላም ሰብአዊ መብቶችንና ነፃነቶችን የሚመለከቱ አያሌ ዓለም አቀፋዊና

Digitized by Google

አህጉራዊ ጉባኤዎች ተደርገዋል ። በታኅሳስ ወር 1960 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በቅኝ ግዛት ሥር ላሉ አገሮችና ሕዝቦች ሕጋዊ ነፃነት ለመስጠት የተላለፈውን ውሳኔ ሰማንያ ዘጠኝ አገሮች ሲደግፉት፣ ዘጠኝ ቅኝ ገዥ ኢምፔሪያሊስት አገሮች(ፖርቱጋል፣ ስፔን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ አውስትራሊያ፣ ቤልጅየም፣ ዶሚኒካን ሪፐብሊክና ፈረንሳይ) ድምፅ ባለመስጠት ውሳኔውን አልተቀበሉትም ። [2] ይሁን እንጂ ቅኝ ግዛቶች የራሳቸውን ዕድል ራሳቸው የመወሰን መብታቸውን በመጠየቅ ባካሔዱት መራራ የነፃነት ትግልና የዓለም ተራማጅ ኅብረተሰብ ባደረገላቸው ድጋፍ ብዙ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ሊወጡ ችለዋል ።

ከ1960 በኋላ ስለሰብአዊ መብቶች ከተደረጉት ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች መካከል ጉልተው የሚታዩት በሶሻሊስት አገሮች አሳሳቢነት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ መሠረት በ1966 የተደረጉት የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የባህልና የፖለቲካ መብቶችና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ናቸው ። እነዚህ ስምምነቶች ዓለም አቀፋዊ ውዝግቦችን ማስከተላቸው አልቀረም ። በተለይ ከጉባኤው ተካፋዮች መካከል አንዳንድ ምዕራባውያን ካፒታሊስት አገሮች በአሜሪካ መሪነት የመሥራት መብትንና ሌሎች መሠረታዊ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ መብቶችን በመቀበል ለማክበርና በሥራ ለመተርጎም የማይችሉ ስለሆኑ ስምምነቶቹን ለማጽደቅ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በአንቢታ ገልጸዋል ። [3] እነዚህ ምዕራባውያን አገሮች ስምምነቱ በፖለቲካ መብት ላይ ብቻ ማተኮር አለበት በማለት በገሀድ ተሟገተዋል ። የዚህ ሐሳብ ቀንደኛ መሪ የነበረው ሚስተር ጀምስ ገሪን የተባለው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣን ለምን ይህን አቋም እንደወሰደ ሲገልጽ፣ «አሜሪካ በሕገ መንግሥቷ ውስጥ ከተመለከቱት መብቶች እጅግ የበለጠ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶችን የያዘውን ይህን ስምምነት ለመቀበል አስቸጋሪ» ይሆንባታል ብሎ ነበር ። [4] እንግሊዝና አሜሪካ በአንድነት የተቃወሟቸው ሌሎች አያሌ ዓለምአቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ውሳኔዎች አሉ ። [5] በአጠቃላይ ከአርባ የማያንሱ ሰብአዊ መብቶችንና ነፃነቶችን የሚመለከቱ ዓለምአቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶችና ሕጎች ወጥተዋል ። [6]

በዓለም አቀፍ መድረኮች ከውስን የፖለቲካ መብቶች በስተቀር በተለይ የዜጎች የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚና የባህል መብቶችና ነፃነቶች በሕግ እንዳይታወቁና እንዳይከበሩ በመቃወም የታወቀው ራሱን «ነፃው ዓለም» እያለ የሚጠራው በአሜሪካ የሚመራው የካፒታሊስቱ ዓለም ነው ። በተለይ የዓለም ሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ፖሊስ ነኝ የምትለው አሜሪካ በሀቅ ለሰብአዊ መብት የቆመች ቢሆን ኖሮ ለሰው ልጅ ህልውና፣ ለእድገቱና ለክብሩ መሠረት የሆኑትን እነዚህን የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚና የባህል መብቶችና ነፃነቶች በተቀበለች ነበር ።

ከዚህ በላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመግለጫና በዓለም ሕግ የታወቁት የግለሰቦች (የዜጎች) የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች ነፃነቶች በብሔራዊ መንግሥታት የመብትና ነፃነት ሕግ አወጣጥ ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

በአንዳንድ ብሔራዊ መንግሥታት የታወቁ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

የሰዎችን መብቶችና ነፃነቶች በሚመለከት ረገድ በዓለምአቀፍ ደረጃ ብሔራዊ መንግሥታት የተስማሙባቸውን መግለጫዎችና ስምምነቶች የያዙ አያሌ የፖለቲካ ሰነዶች መኖራቸው ተደም ሲል ተጠቅሷል ። ከእነዚህ ሰነዶች አብዛኛዎቹ የዜጎቻቸው መብቶችና ነፃነቶች መካከል ምን መሆን እንዳለባቸው ለብሔራዊ መንግሥታት የሚጠቁሙና ለመብቶችና ለነፃነቶች ተግባራዊነ

ትም መንግሥታቱ ጥረት ማድረግ እንደሚኖርባቸው የሚያሳስቡ ሕጋዊ አስገዳጅነት ያላቸው ሰነዶች ናቸው ።

ብሔራዊ መንግሥታት እንደሚከተሉት ርዕዮተዓለምና እንደሚገኙበት የኅብረተሰብ የእድገት ደረጃ ዓይነት በሕገ መንግሥቶቻቸው ውስጥ የሚደነግጓቸው የሕዝብ መብቶችና ነፃነቶች ዓይነትና መጠን የተለያዩ ናቸው ። የካፒታሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች የሕዝቦች ብሔራዊና የፖለቲካ መብቶችን ብቻ የሚያከብሩ መሆናቸውን ያወጁ ሲሆን ፣ የሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች ግን ብሔራዊና የፖለቲካ መብቶችን ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶችን ጭምር የሚያከብሩ መሆናቸውን ደንግገዋል ።

ብሔራዊ ፣ የፖለቲካ ፣ የማኅበራዊ ፣ የኢኮኖሚና የባህል መብቶች ሲባል ምን ማለት ነው ? ለአቀራረብ እንዲያመች ሰብአዊ መብቶችንና ነፃነቶችን በአጠቃላይ በሁለት መክፈል ይቻላል ። እነሱም፣— 1· የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች ፣ 2· ብሔራዊና የፖለቲካ መብቶችና ነፃነቶች ናቸው ።

የዜጎች የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች

ከዜጎች መሠረታዊ የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊ ፣ የባህል መብቶች መካከል ዋናዎቹ የመሥራት ፣ የማረፍና የመዝናናት ፣ የጤና እንክብካቤ ፣ የኑሮ ዋስትናና የመማር መብቶች ናቸው ። እነዚህ መብቶች በተለይ በሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች ታውቀዋል ። በሕግ መታወቅ ብቻ ሳይሆን ወደፊት በዚህ ጽሑፍ እንደሚገለጠው የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓት የመብቶቹን ተግባራዊ መሆን በሚገባ አረጋግጧል። እነዚህን መብቶች አንድ በአንድ እንመልከታቸው ።

የመሥራት መብት

ይህ መብት ከሰብአዊ መብቶች ሁሉ ዋናው ሲሆን የሰውን ልጅ መሠረታዊ ፍላጎት ከማሟላቱም በላይ የተሟላ እድገቱንም መዳበር የሚያረጋግጥ መሠረታዊ መብት ነው ። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ዜጋ በሥራ ተሠማርቶ ለኑሮው ገቢ የማግኘት መብቱ ስለሚረጋገጥለት ከሥራ አጥነት ሥጋት በመላቀቅ የተስተካከለ ኑሮ የመኖር ዋስትና ያገኛል ።

ሶሻሊስት አገሮች የምርት መሣሪያዎችን የሕዝብ ሀብት በማድረግና የሶሻሊስት ኢኮኖሚን በመገንባታቸው ይህን መብት በሕግ [7] መግለጽ ብቻ ሳይሆን ለተግባራዊነቱም አስተማማኝ ቁሳዊ መሠረት ጥለውለታል።ሶቭየት ኅብረት የመጨረሻው ሥራ አጥ ዜጋዋን ሥራ በማስያዝ የሠራተኛና ሥራ ማገናኛ ቢሮዋን የዘጋችው ገና ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት በ1930 ነበር። [8] ከአዲስ ጀማሪዎች በቀር ሌሎች ሶሻሊስት አገሮችም የሥራ አጥን ችግር መወጣት ችለዋል። እንዲያውም ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ ብዙ የሚሠሩ እጆችን ይፈልጋሉ ።

የካፒታሊስት አገሮች የምርት ግንኙነት በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በክልላቸው ያለው የሥራ አጡ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው (ሠንጠረዥ አንድን ይመለከቷል)። ለምሳሌ በ1974 5,076 ሚሊዮን የነበረው የአሜሪካ ሥራ አጦች ቁጥር በአሁኑ ጊዜ ከ12·5 ሚሊዮን በላይ በመድረስ በእጥፍ ጨምሯል ። በ1976 በአሜሪካ ከተመዘገቡት ሥራ አጦች መካከል 4,000 የሚሆኑት የዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው ሳይንቲስቶች ነበሩ ። [9] የሌሎች አምስት የታወቁ ካፒታሊስት አገሮችን የሥራ አጦች ቁጥር እድገት ብንመለከት ከ1965 እስከ 1976 ባሉ 10 ዓመታት ውስጥ ብቻ የጃፓን በ155%፣ የምዕራብ ጀርመን በ620% የፈረንሳይ በ490 ፣ የእንግሊዝ በ166%፣ የጣሊያን በ102% ጨምሯል ። [10]

Digitized by Google

በእያንዳንዱ ሀገር በ1965 የነበረውን የሥራ አጥ ቁጥር ከ1983 ጋር ብናነፃፅረው እድገቱ በጃፓን 315%፣ በምዕራብ ጀርመን 1.688%፣በፈረንሳይ 1.400%፣ በእንግሊዝ 796%፣ በጣሊያን 264%፣ በአሜሪካ 256% ነው ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ስድስት የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች መካከል ጃፓንና ምዕራብ ጀርመን በሕገ መንግሥታቸው የዜጎቻቸውን የመሥራት መብት አውቀዋል ። ይሁን እንጂ ይህ መብት ቁሳዊ መሠረት የሌለው የይስሙላ ሕጋዊ ዋስትና ብቻ በመሆኑ በየአገሮቹ ውስጥ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሥራ አጦች የሥራ ዋስትና መስጠት አልተቻለም ። እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ ምዕራብ ጀርመን ከ2.487.900 በላይ ሥራ አጦች የሚንገላቱባት ሀገር ስትሆን፣ ጃፓንም ከ1,620.000 በላይ ሥራ አጦች ተጥለቅልቃለች ።[11] በ1983 በፈረንሳይ ሀገር የነበረው የሥራአጥ ቁጥር ከ2 ሚሊዮን በላይ ነበር ።

እንግሊዝ ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ [12] በማውጣት በፎክላንድ ደሴቶች ላይ ያላትን የቅኝ ግዛት «መብቷን» ለማስከበር ጦርነት ባካሄደችበት ወቅት ከሦስት ሚሊዮን የሚበልጡ ሥራ አጦች አጥለቅልቀዋት ነበር ። ይህም በ1977 ከነበራት የሥራ አጥ መጠን ጋር ሲነፃፀር ከሞላ ጎደል በ120% መጨመሩን የሚያመለክት ነው ። ሕዝብን በቦምብ ለመጨፍጨፍ ያፈሰሰችውን ይህን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ የሀገሯን ሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ ብታውለው ኖሮ በአንድ በኩል የጦርነት ሰቆቃና መቅሠፍት ላንዣበበበት ሕዝብ የህልውና መብት፣ በሌላ በኩል የሥራ አጥነት ሥጋት መንፈሱን ላስጨነቀው ሕዝብ የኑሮ ዋስትና ባስገኘ ነበር ።

በአሁኑ ጊዜ በካፒታሊስቱ ዓለም ውስጥ የሥራ አጡ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው ። ይህ ክስተት የካፒታሊስት ሥርዓት በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በርዕዮተ ዓለም መስኮች የተጠናወተው ቀውስ መባባሉን የሚያመለክት ነው ።

የማረፍና የመዝናናት መብት

«ማንኛውም ሰው የማረፍና የመዝናናት መብት አለው ። እንዲሁም የተወሰነ የሥራ ሰዓትና ደመወዝ የሚከፈልበት የበዓል ቀን ዕረፍት» የሚለውን የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ሁለንታዊ መግለጫ ቁጥር 24 ተግባራዊ በማድረግ የዜጎች የማረፍና የመዝናናት መብት በሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች የተደነገገ መብት ሆናል ።[13] ይህ መብት የሥራ ሰዓትን፣ የሕዝብ በዓላትን፣ ደመወዝ የሚከፈልበት የዓመት ፈቃድን በሕግ በመወሰን ዋስትና የተሰጠው ከመሆኑም በላይ፣ ለዚህ መብት ተግባራዊ መሆን የባህልና የመዝናኛ ተቋሞችም ተደራጅተው ይገኛሉ ። እነዚህም የመዝናኛ፣የባህል ተቋሞች፣ የዕረፍት ቤቶች፣ ክበቦች፣ ስታዲየሞች፣ ልዩ ልዩ የስፖርት ቦታዎች፣ ፓርኮች፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ወዘተ . . . ናቸው ። ይህን መብት በሚመለከት የሶቭየት ሶሻሊስት ሪፐብሊኮች ኅብረት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 41 እንደሚከተለው ደንግጎታል ።

የሶ.ሶ.ሪ.ኅ.(የሶቭየት ሶሻሊስት ሪፐብሊኮች ኅብረት)ዜጎች የዕረፍት ፈቃድ የማግኘትና የመዝናናት መብት አላቸው ። የሳምንት የሥራ ሰዓቶች ከ41 ሰዓቶች እንዳይበልጡ መደረጉና በአንዳንድ የሥራ መስኮችና ፋብሪካዎች ውስጥ የተሠማሩ ሠራተኞችና ተቀጣጠሪዎቹ እንዲሁም በሌሊት ሥራ ለሚሰማሩት አጭር የሥራ ጊዜ መመደቡ፣ ከደመወዝ ጋር የሚሰጥ የዓመት ፈቃድና በየሳምንቱ መጨረሻ የሚሰጡ የዕረፍት ቀናት መኖራቸው፣ የባህል፣ የትምህርትና የጤና መንከባከቢያ ተቋሞች መስፋፋታቸው፣(የስፖርት) የሰውነት እንቅስቃሴና የሀገር ጉብኝት በሰፊው መዘጋጀታቸው፣ በየመኖሪያዎቹ አካባቢዎች ልዩ ልዩ የመዝናኛ ዝግጅቶች ተሟልተው መቅረባቸው፣ የዕረፍት ጊዜን በሚገባ ለማሳለፍ ሙሉ፣ ቁሳዊ ዋስትና ይሰጣሉ ።

Digitized by Google

ሠንጠረዥ አንድ

ከ1965—1983 ባለው ጊዜ ውስጥ በየዓመቱ በዳበሩት ስድስት የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ተመዝግቦ የነበረውን የሥራ አጥ እድገት የሚያሳይ ሠንጠረዥ * (በሺህ የሚታሰብ)

	አ ገ ር					
	ጃፓን	ምዕራብ ጀርመን	ፈረንሳይ	እንግሊዝ	ጣሊያን	አሜሪካ
1965	390.0	139.0	142.0	360.0	609.0	3,520.0
1970	590.0	148.8	262.1	612.2	1,111.0	4,088.0
1973	680.0	273.5	393.9	618.8	1.305.0	4,304.0
1974	730.0	582.5	497.7	614.9	1,113.0	5,076.0
1975	1,000.0	1,074.2	839.7	977.6	1,230.0	7,830.0
1976	1,080.0	1,060.3	993.5	1,359.8	1,426.0	7,288.0
1977	1,100.0	1,030.0	1,071.7	1,483.6	1,545.0	6,855.0
1978	1,240.0	992.9	1,166.9	1,390.0	1,571.0	6,047.0
1979	1,170.0	876.1	1,349.8	1,390.5	1,698.0	5,963.0
1980	1,130.0	1,036.5	1,485.4	1,470.6	1,703.0	7,234.0
1981	1,230.0	1,308.6	1,680.3	2,419.5	1,717.0	8,746.0
1982	1,310.0	1,949.6	2,034.0	3,070.6	2,089.0	10,183.0
1983	1,620.0	2,487.1	2,130.0	3,225.2	2,218.0	12,517.0

ምንጭ - የዓለም አቀፍ ሠራተኞች ድርጅት (ILO) የሠራተኞች ጉዳይ ስታቲስቲክስ መጽሔት (የ1980 ፡ የ1984 እትሞች)

* ከ1980—1983 ስታቲስቲክስ የሚያመለክተው በእያንዳንዱ ዓመት በጥር ወር ያለውን የሥራ አጥ መጠን ነው።

የተጠቀሰው የሶቭየት ኅብረት ሕገ መንግሥት የዳበረ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ነፀብራቅ ነው ። መብቱም የዚሁ ኢኮኖሚ ነፀብራቅ እንደመሆኑ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሳይ መሠረት ይህን መብት በሕጋዊና ቁሳዊ መልኩ መቀዳጀት አይቻልም ። ለዚህ መብት መታገል ማለት ለሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታ መታገል ነው ። አብዮታዊት ኢትዮጵያም የእድገት ደረጃዋ የሚፈቅደውን ያህል የሠራተኞችን የሥራ ሰዓት፣ የሕዝብ በዓላትና ደመወዝ የሚከፈልበት የዓመት ፈቃድ በሕግ እንዲወሰን አድርጋለች። በ1968ቱ የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ሠራተኞች በቀን ከ8 ሰዓት ፣ በሳምንት ከ48 ሰዓት ያህል እንዲሠሩ ደንግጓል ። ሠራተኛው ከደመወዝ ክፍያ ጋር የዓመት ፈቃድ የማግኘት መብቱ ተረጋግጦለታል። እንደ መደበኛ የሥራ ሰዓት የሚቆጠር እንደሥራው ጠባይና የሥራው ቦታ ሁኔታ በሥራው መካከል የመዝናኛና የምግብ ዕረፍት ጊዜ ለሠራተኛ ይሰጣል ። ማንኛውም ሠራተኛ ቢያንስ በሳምንት 24 ሰዓት መደዳውን የማረፍ መብት አለው ። የሕዝብ በዓላትም ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሠራተኛ የዕረፍት ጊዜያት ናቸው ። [14]

የጤና እንክብካቤ መብት

የሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች ዜጎች በሚታመሙበት ወይም አካለ ጉዶሎ በሚሆኑበት ጊዜ ነፃ የሕክምና አገልግሎት ወይም ርዳታ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑ ተደንግጓል ። መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ እነዚህ አገሮች ሕመምን ፣ የእርጅና ዘመንንና አካለ ጉደሎነትን የሚሸፍን የማኅበራዊ መድን አገልግሎትን አሻሽለዋል ። ነፃ የሕክምና አገልግሎት ይሰጣሉ ። ሆስፒታሎች ፣ ክሊኒኮች ፣ ጤና ጣቢያዎችና ሌሎች የጤና ተቋሞች በመስፋፋታቸው ለዚህ መብት አስተማማኝ ቁሳዊ መሠረት ሆነዋል ። [15]

ሶቭየት ኅብረት ይህን መብት ተግባራዊ ለማድረግ በወሰደችው ርምጃ ለሕዝቦቿ በሙሉ የሕክምና አገልግሎት በመስጠት በዓለም የመጀመሪያዋ አገር ሆናለች። ዛሬ በዓለም ውስጥ ከሚገኙት ዶክተሮች መካከል ሩቡ የሶቭየት ኅብረት ናቸው። በቅድመ አብዮት ሩስያ የአንድ ሰው ማዕከላዊ ዕድሜ 32 ዓመት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን 70 ዓመት ሆ ል ። [16] ይህ ሊረጋገጥ የቻለው በሀገሪ ር ሶሻሊስት ስልተምርት በመስፈኑ ነው ። በሌላ በኩል «የበለፀገችው አገር» እየተባለች የምትጠራው አሜሪካ ግን የሕክምና አገልግሎት መብትን በሕገ መንግሥቷ አላወቀችም ። በአሜሪካ የአንጀት አልሰር ኦፕራሲዮን ለማድረግ የሚፈልግ አንድ ሰው ከ1,200 የአሜሪካ ዶላር በላይ ያስፈልገዋል ። ደህና የገቢ ምንጭ ያለው የአሜሪካ ቤተሰብ እንኳን ይህን ገንዘብ መክፈል ያዳግተዋል ። የአሜሪካ ኮሚኒስት ፓርቲ እንደገለጠው በ1974 በአሜሪካ የግል ኤኮኖሚ ዘርፍ በ5,915,800 ዜጎች ላይ በሥራ ምክንያት ጉዳቶችና በሽታዎች መድረሳቸው ተመዝግቧል ። ከመደበኛው ሠራተኛ መካከል 10 በመቶ ያህሉ የቆሰለ ነው። ከአሜሪካ ሠራተኞች መካከል 25 በመቶ ሥራቸው ካንሰር ሊያሲይዛቸው በሚችል ሁኔታ ውስጥ ያሉ ወይንም በጣም አደገኛ ለሆነ ሥራ የተጋለጡ ናቸው። በ1975 4,000 የማዕድን ሠራተኞች በሳምባ በሽታ የሞቱ ሲሆን ፣ 7,000 ያህሉ በአካለ ጉደሎነት ይማቅቁ ነበር ። ይህ በጤንነት ፣ በሕይወትና በአካል ላይ የሚደርሰው ከፍተኛ ጉዳት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በግልጥ የቆመው ለትርፍና ለብዝበዛ እንጂ ለሰው ልጅ ደህንነትና ሕልውና አለመሆኑን አጉልቶ ያሳያል ። የአሜሪካ የጤና ጥበቃ ሥርዓት ድኃው ይበልጥ በሽተኛ ፣ በሽተኛው ደግሞ ይበልጥ ድሀ የሚሆንበት ነው ። [17]

በኢትዮጵያም የታገደው የቀድሞው ሕገ መንግሥት እንደሌሎች ብዙ ካፒታሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች ሁሉ የጤና እንክብካቤ መብት አያውቅም ነበር ። ነገር ግን በኢትዮጵያ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ቁጥር 4/ለ/

Digitized by Google



ሲ አይ ኤ ማህበራዊ ኑሮን የሚያናጋና የዜጎችን መብት የሚገፍ ነው ።

"Conspiracy to Stifle Dissent in America" ከተሰኘው መጽ[illegible]ወሰደ

Digitized by Google

«የሰፊው ሕዝብ የተሟላ ኑሮ እንዲረጋገጥ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በቂ የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ» እንደሚያደርግ አረጋግጧል ። በዚህም መሠረት ቀድሞ በከተሞች አካባቢ ብቻ ተወስኖ የነበረው የሕክምና አገልግሎት ዛሬ ወደገጠር በመስፋፋት ላይ መገኘቱ ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ መለስተኛ የጤና ድርጅቶች እስከ 300 በመቶ ፤ መለስተኛ የጤና ባለሙያዎች ደግሞ በ128 በመቶ ዕድገት ማሳየቱ የሚያበረታታ ጅምር ነው ።[18]

የኑሮ ዋስትና መብት

የማናቸውንም ሥርዓተ ማኅበር ሰብዓዊ ርህራሄነት ከሚያሳዩት ነገሮች መካከል የኅብረተሰቡ አባሎች በሚያረጁበት ፤ በሚታመሙበት ፤ ወይም አካለ ስንኩላን በሚሆኑበት ወቅት በሚሰጠው ቁሳዊ ልገስናና እንክብካቤ ይገኙበታል ።

በሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች[19] መሠረት ዜጎች በእርጅና ዘመን ፤ በሕመም ጊዜ ፤ በከፊል ወይንም ሙሉ በሙሉ አካለ ስንኩላን ሲሆኑ ወይም የቤተሰብ ደጋፊ የሞት አደጋ ሲደርስበት እንደሁኔታው ጊዜያዊ አበል ወይም የጡረታ አበል በመስጠት የኑሮ ዋስትና መብትን ተግባራዊ ያደርጋሉ ። በአንፃሩ ከበለጸጉት ካፒታሊስት አገሮች የአሜሪካን የኑሮ ዋስትና ሁኔታ ሲታይ «በ1974 ፤ 5.8 ሚሊዮን ሠራተኞች የጡረታ አበል ተነፍገው ነበር ፤ 19.5 ሚሊዮን ሠራተኞች የሥራ አጥነት መድን ጥቅሞች እንዳያገኙ ተደርገዋል ። »[20]

በአገራችንም እንዳይሠራ የታገደው የቀድሞው ሕገ መንግሥት ለኢትዮጵያ ዜጎች የኑሮ ዋስትና መብትን አላረጋገጠም ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ቁጥር 4/መ/ « ለአርበኞች ፤ ጧሪ ለአጡ ዜጎች ፤ ለሌሎችም የኅብረተሰቡ ባለውለታዎች የኑሮ ዋስትና ለመስጠት ፤ አሳዳጊ የሌላቸውንና ሰብሳቢ ያጡ ሕፃናትን ለማስተማርና ለማሳደግ ፤ ድኩማንን ለመደገፍ ፤ በአደጋ / ድርቅ ፤ ውሀ ሙላት የመሬት መንቀጥቀጥ . . . / ለተጐዱ ወገኖች ለመድረስ፤ አስፈላጊው ጥረት ሁሉ » የሚደረግ መሆኑ ተገልጿል ።

በኢትዮጵያ የፊውዳሉ መንግሥት የጡረታ አበል የሚከፈለው ለመንግሥት ሠራተኛና በመንግሥት ቻርተር ወይም ያለ ቻርተር ተቋቁመው ራሳቸውን በሚያስተዳድሩ የመንግሥት ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች ብቻ በመሆኑ ብዙዎቹ በግል የማምረቻ ፤ ማከፋፈያና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች የጡረታ አበል አያገኙም ነበር ። ዛሬ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የመንግሥት የሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 49/1967 በተገለፀው መሠረት ሙሉ በሙሉ ወይም አብዛኛው ድርሻ ወደ መንግሥት በተዛወረ የእርሻ ፤ የንግድ የኢንዱስትሪ ፤ የትራንስፖርት ፤ የባንክ ወይም የመድን ድርጅቶች ውስጥ ድርጅቶቹ ወደ መንግሥት በተዛወሩበት ቀን ቋሚ ሠራተኛ የነበረ ሰው ፤ ወይም ከዚህ ቀን በኋላ በነዚሁ ድርጅቶች የተቀጠረ ሰው ፤ የመንግሥት ንብረት በሆነ አክሲዮን ማኅበር ቋሚ ሠራተኛ የሆነ ሁሉ የጡረታ አበል እንዲያገኝ ተደርጓል ።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያን አንድነት ለማስከበርና አብዮቱን ከቅልበሳ ለማዳን ከጠላት ጋር በመፋለም አካለ ስንኩላን የሆኑት ጀግኖች የሚያገግሙባቸው ፤ የሚጸጸሙባቸውና የሚጠሩባቸው ማቢያዎችና የጀግኖች አምባ መጽጽም ፤ የጀግኖች ልጆችና አሳዳጊ ያጡ ሕፃናት ተኩትኩተው የሚያድጉባቸው የሕፃናት አምባዎች መመሥረት መንግሥት የኢኮኖሚ አቅሙ የሚፈቅድለትን ያህል በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ እንደተመለከተው ለዜጎች የኑሮ ዋስትና በመስጠት ላይ መሆኑን መረዳት ይቻላል ። ወደፊትም ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ጋር እያንዳንዱ ዜጋ ተገቢ የሆነውን የኑሮ ዋስትና መብት የሚጐናጸፍበት ሁኔታ ይመቻቻል።

Digitized by Google



አብዮታችን አድሃሪያንን ብቻ ሳይሆን ማይምነትንም እየተዋጋ ነው ።

Digitized by Google

የመማር መብት

በሰብዓዊ መብቶች ሁለንታዊ መግለጫ አንቀጽ 26/ሀ «ማንኛውም ሰው የትምህርት መብት አለው ፣ ቢያንስ ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ መሰጠት አለበት። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ግዴታ መሆን አለበት ። የቴክኒክና የሙያ ትምህርት እንዲሁም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉ እንደችሎታው መዳረስና ክፍት መሆን አለበት » ይበል እንጂ ዛሬ ከ800 ሚሊዮን [21] የሚበልጠው የዓለም ሕዝብ ከማይምነት ጨለማ ገና መላቀቅ አልቻለም ። ከዛሬ 36 ዓመት በፊት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንደድርጊት ፕሮግራም መመሪያ ይሆን ዘንድ ከወጣው የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ጋር የሚመሳሰል ሕገ መንግሥታዊ የመማር መብት በየሕገ መንግሥቶቻቸው መደንገግ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊነቱንም በይበልጥ በማረጋገጥ ላይ ያሉት ሶሻሊስት አገሮች ናቸው ።

በሶቪየት ኅብረት ፣ በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ፣ በሩማንያና በኮሪያ ዲሞክራቲክ ሕዝባዊ ሪፑብሊክ የ10ኛ ክፍል /10 ዓመት/ የግዴታ ትምህርት ይሰጣል ። በሌሎቹ ሶሻሊስት አገሮች ግን የ8ኛ ክፍል /የ8 ዓመት/ ወይም ከዚያ በላይ የግዴታ ትምህርት ይሰጣል ።በማናቸውም ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት በነፃ ነው ። በሌላ በኩል ግን አንዳንድ የካፒታሊስት አገሮች የ6ኛ ክፍል/ የ7 ዓመት/ ነፃና የግዴታ ትምህርት ይሰጣል በማለት በሕጐቻቸው ቢያስቀምጡም ተግባራዊ ማድረግ አልቻሉም። ለምሳሌ ስፔን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከደረሱት ዜጐቿ መካከል ከሃያ በመቶ በላይ ትምህርት አይሰጣቸውም ። በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ሴቶችና አናሳ ብሔረሰቦችም በእኩልነት ትምህርት አይሰጣቸውም ። የወዝአደሮች ልጆችም አነስተኛውን የተማሪዎች ቁጥር ይዘው ይገኛሉ ። [22]

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ትምህርቱ የመማር ዕድል ተጓድሎ የነበረው ለጥቂት የሀብታም ልጆች ከመሆኑም በላይ 93 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ በማይምነት ጨለማ ተጋርዶ እንደነበር የሚታወስ ነው። ከዚህም በላይ ትምህርት ቤቶችን የገቢ ምንጭ ወደ ማድረግ አዝማሚያ በማዘንበል ለማስተማር የተሟላ ድርጅት የሌላቸው አያሌ የግል ትምህርት ቤቶች በአንዳንድ ከተሞች እንደአሸን በመፍላት ላይ ነበሩ ።

አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ርምጃዎች ተወስደዋል ። በመጀመሪያ በግል ተይዘው የነበሩት ትምህርት ቤቶች ወደ ሕዝብ ይዞታ እንዲዛወሩ የሚያደርግ አብዮታዊ አዋጅ በመውጣቱ ዛሬ ሕዝቡ የሚያስተዳድራቸውና የሚመራቸው ብዙ ትምህርት ቤቶች አሉ ። የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ቁጥር 4 /ሀ/ «ለሰፊው ሕዝብ ዕድገትና የተሟላ ኑሮ የሚያገለግል ፣ ለሰፊው ሕዝብ ልጆች በሙሉ የሚደረስ ለፀረ ፊውዳል ፣ ለፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስትና ለፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚያግዝ ነፃ ትምህርት ደረጃ በደረጃ እንዲስፋፋ ፣ መሃይምነት ከሀገራችን እንዲጠፋ - - - - - » የሚደረግ መሆኑን አረጋግጧል ። በዚሁ መሠረት ከ1966 ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ባሉት አሥር ዓመቶች ውስጥ ብቻ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ብዛት በ221 በመቶ ፣ የመምህራን ብዛት በ148 በመቶ ፣ የትምህርት ቤቶች ብዛት በ150 በመቶ እድገት አሳይተዋል ።/ዝርዝር እድገቱን በሠንጠረዥ ሁለት ይመለከቷል ።)

በሠንጠረዥ ሦስት ከቀረበው መረጃ ማስላት እንደሚቻለው በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችና በኮሌጆች በመማር ላይ የነበሩትን ተማሪዎች ከ1965እስከ 1974 ድረስ ባሉት ዘጠኝ ዓመቶች ውስጥ የ33 በመቶ እድገት አለ ።

Digitized by Google

ሠንጠረዥ ሁለት

ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ በኢትዮጵያ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በየዓመቱ የተመዘገቡ
የተማሪዎች ፣ የመምህራንና ት/ቤቶች ዕድገት የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ዘመን	1966	1967	1968	1969	1970	1971
ተማሪዎች	1,043,900	1,148,200	1,458,000	1,458,000	1,422,800	1,702,500
መምህራን	24,800	27,300	31,200	33,200	34,582	36,800
ት/ቤቶች	3,287	3,798	4,385	4,852	5,047	5,678

ዘመን	1972	1973	1974	1975	1976
ተማሪዎች	2,182,400	2,558,200	2,865,000	3,046,200	3,353,100
መምህራን	39,590	43,290	49,493	54,930	61,650
ት/ቤቶች	6,094	6,790	7,272	7,598	8,245

ምንጭ ፡- በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በትምህርት ሚኒስቴር የፕላን አገልግሎት /1975/ .

Digitized by Google

ሠንጠረዥ ሦስት

ከ1963—1976 ባለው ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችና ኮሌጆች በትምህርት ላይ የነበሩትንና የተመረቁትን ተማሪዎች ዕድገት የሚያመለክት

ሠ ን ጠ ረ ዥ

ዓመተ ምሀረት	1963	1965	1967	1969	1971	1973	1975
በትምህርት ላይ የነበሩ	4,594	4,945	*	3,795**	13,971	15,037	
የተመረቁ	1,445	1,509	*	1,126**	1,602		

ምንጭ ፡ በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን የሥራ ዘገባ 1973—74

* በዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ምክንያት ትምህርት አልተሰጠም ።

** ፀረ-አብዮተኞች በነዙት ውዥንብር ምክንያት የተማሪዎች ቁጥር ቀንሷል ።

ሠንጠረዥ አራት

ከሐምሌ 1 ቀን 1971 እስከ መስከረም 30 ቀን 1973 (1 ዓመት ከሦስት ወር) በተካሄደው የአንደኛ ፡ የሁለተኛና ሦስተኛ ዙሮች የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ የተገኘውን ውጤት

የሚያሳይ ሠንጠረዥ

የዘመቻው ወቅት	የተመዘገቡ	ለፈተና የቀረቡ	ፈተና ያለፉ
አንደኛ ዙር	6,224,904	3,683.288	1,543,678
ሁለተኛ ዙር	2,091,133	1,380,905	657,842
ሦስተኛ ዙር	2,522,672	1,598,092	973,367
ድ ም ር	10,338,709	6,662,285	3,174,887

ምንጭ ፡ በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ከተገኘ መረጃ የተጠናቀረ ።

Digitized by Google

የመሠረተ ትምህርት ሁኔታን በሚመለከት ከ1965 ጀምሮ ባሉት አሥር ዓመቶች ውስጥ 1,165,525 ሰዎች ከማይምነት ለመላቀቅ ችለዋል ። ከሠንጠረዥ አራት መረዳት እንደሚቻለው ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ ከፍተኛ ድል ተገኝቷል ። ለሶስት ወ[illegible] በተካሄደው የመጀመሪያ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ብቻ 1,543,678 ሰዎችን ከማይምነት ነጻ ማውጣት ተችሏል ። [23]

ከሐምሌ አንድ ቀን 1971 እስከ ታህሣሥ 1976 ድረስ በተካሄደው የዘጠኝ ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ የመሃይማን ቁጥር በቅድመ አብዮት ከነበረው 93 በመቶ ወደ 37.6 በመቶ ዝቅ ሊል ችሏል ። [24] ይህም ማለት ከ1966 በፊት በኢትዮጵያ ማንበብና መጻፍ የሚችለው ሕዝብ 7% ሲሆን ፣ በታኅሣሥ 1976 ግን ወደ 62.4% ከፍ ብሏል ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ሁለት ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻዎች የተካሔዱ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የማይማኑ ቁጥር ከላይ ከተጠቀሰው በጣም ዝቅ እንደሚል ይገመታል ። ማይምነትን ለማጥፋት የተደረገው ታሪካዊ እንቅስቃሴና የተገኘውም አስደናቂ ውጤት አብዮታዊት ኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ ሽልማት ባለቤት እንድትሆን አድርጓታል ።

በአጠቃላይ የሰፊው ሕዝብ ልጆች ትምህርት እንዲያገኙና ማይምነትን ከኢትዮጵያ ለማስወገድ እስከ አሁን ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያካሔደው ጥረት እጅግ የሚያበረታታ ቢሆንም፣ በትግሉ የበለጠ ቀጥሎ የማያነብ ዓይንና የማይጽፍ እጅ የማይገኝባት ፣ ትምህርት የመማር መብት ሕጋዊ እና ቁሳዊ ዋስትና የሚረጋገጥበት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን የመገንባት ታሪካዊ ትግል ከፊቱ ተደቅኗል ።

ሌሎች የግ በራዊ ፣ የኤኮኖሚና የባህል መብቶች

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መብቶች ዋና ዋናዎቹና መሠረታዊ ናቸው የሚባሉት ሲሆን አንዳንድ ሶሻሊስት አገሮች ከደረሱበት የእድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች መብቶችን በሕገ መንግሥቶቻቸው ውስጥ አስፍረዋል ። ለምሳሌ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት በሶቭየት ኅብረት መንግሥት ዋስትና ተሰጥቶታል ። የሌሎች ብዙ ሶሻሊስት አገሮች የኤኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ገና ባለመፍቀዱ ይህን መብት በሕገ መንግሥቶቻቸው ውስጥ አላስገቡም ። በእያንዳንዱ ሶሻሊስት አገር ሕገ መንግሥት የተረጋገጠ ሌላው መብት የራስ ንብረት (Personal Property) የማፍራት መብት ነው ። ይህ መብት ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጐትን ለማርኪያ እንጂ ለትርፍ ማካበቻ ያልሆነ እንደቤት ፣ በአጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ አትክልት ፣ መኪና በየወቅቱ ከሚገኝ ገቢ የተጠራቀመ ገንዘብ ፣ ጥቂት ከብቶች ፤ ወዘተ - - -የመሳሰሉትን በግል ይዞታ ሥር የማድረግ መብት ነው።

2. የዜጐች ብሔራዊ ፖለቲካዊ መብቶችና ነፃነቶች

ከዜጐች ብሔራዊና ፖለቲካዊ መብቶችና ነፃነቶች ዋናዎቹ የእኩልነት ፣ የንግግርና የጽሑፍ ፣ ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ ማድረግ ፣ በኅሊና የማዘዝ ፣ የመደራጀት ፣ በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች የመሳተፍ ፣ ወዘተ- - መብቶችና ነፃነቶች ናቸው። እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች በ17ኛውና በ18ኛው ምዕተ ዓመት የቡርዧ አብዮት ከተካሄደ ጀምሮ በእንግሊዝ፣በፈረንሣይና በአሜሪካ በሕግ ታውቀዋል ። አሁንም ቢሆን የተለያየ ገደብ ቢበጅባቸውም በሌሎች ብሔራዊ መንግሥታት ሕገ መንግሥቶች ውስጥም ተደንግገዋል ። የነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ምንነትና አፈጻጸም የተለያየ ርዕዮተዓለም ከሚከተሉ አገሮ መካከል እን

Digitized by Google

ዳንዶቹን በምሳሌነት በመጥቀስ መመርመር ይቻላል ።

<u>እኩልነት ፣ መብትና ነፃነት ፣</u>

«ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት »በአንድ ወቅት በፓሪስ ከተማ ግድግዳዎች ላይ አሸብርቆ የታየ የፈረንሣይ ቡርዧ አብዮት መፈክር ነበር ። [25] የቡርዧ አብዮት ሠርቶአደሩን ሕዝብም ከጐኑ ለማሰለፍ ከተጠቀመባቸው መፈክሮች መካከል «በሕግ ፊት እኩልነት» የሚለው አንዱ እንደነበር የሚታወስ ነው። ከዚያም ወዲህ ይህ መፈክር በሕገ መንግሥቶች ውስጥ ሕጋዊ ቦታ ተሰጥቶት ከዜጐች መብቶች መካከል አንዱ ለመሆን በቅቷል ።

በሕግ ፊት እኩል መሆን ሕገ መንግሥታዊ መብት መሆኑን ለማሳየት በሕገ መንግሥት ውስጥ ማስፈር ብቻ በቂ አይሆንም ። ይህ ሕጋዊ ዋስትና ነው። ሕጋዊ ዋስትና በቁሳዊ ዋስትና ካልተደገፈ መሠረት የሌለው የይስሙላ መብት ብቻ ሆኖ ይቀራል ። ቁሳዊ ዋስትና ሊገኝ የሚችለውም በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን የምርት ግንኙነት በሶሻሊስት የምርት ግንኙነት መተካትና አዲሱን የምርት ግንኙነት ማዳበር ሲቻል ብቻ ነው ። ይህ ሲሆን እውነተኛና የተሟላ እኩልነት አለ ለማለት ይቻላል ።

ሞሪስ ኮርንፎርዝ እንዳለው እኩልነት ሊረጋገጥ የሚችለው እኩል አለመሆን ሲወገድ ነው። እኩል አለመሆን የሚወገደውም ለእኩል አለመሆን ምንጮቹ ሲደረቁ ነው። የእኩል አለመሆን ምንጮች የምርት መገልገያዎች የግል ንብረት መሆን ኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈልና የሰው በሰው መበዝበዝ ሥርዓት ናቸው ። እነዚህ የእኩል አለመሆን ምንጮች እስካሉ ድረስ እኩል የፖለቲካ መብቶችን በሕግ በመደንገግ ብቻ እኩልነት ሊሰፍን አይችልም ። [26]

በዝባዥ መደቦች የሌሎች ጭቁንና ተበዝባዥ መደቦችን/ ለምሳሌ የባሪያ አሳዳሪ ባሪያውን ፣ የመሬት ከበርቴ ጢሰኛውን መብት በመንፈግ የፖለቲካ መብቶችን ለራሳቸው ብቻ እንዲጠቀሙ አድርገዋል ። ይህን የበዝባዥ መደቦች ይዞታ አጠናክሮ ለማቆየት በማሰብ አያሌ የፖለቲካ ፈላስፎች በፖለቲካ እኩል አለመሆን የተፈጥሮ ምክንያቶች አሏቸው ለማለት ሞክረዋል ። ለምሳሌ አሪስቶትል ባሮች የፖለቲካ መብቶች የተነፈጉት ነፃዎቹ ሰዎች ያላቸውን መብቶች እንዲኖራቸው ተፈጥሮ ያላደላቸውና ባሪያዎች ሆነው የተፈጠሩ በመሆናቸው ምክንያት ነው ብሎ ነበር ።

ሰው በሰው በሚበዘበዝበት ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ በሰዎች መካከል ያለው እኩል አለመሆን እጅግ የሰፋ ሆኖ ሳለ «እኩል የፖለቲካ መብቶች ፣ በሕግ ፊት እኩል መሆን» በሕግ የተረጋገጡ የዜጐች መብቶች ናቸው ማለት የሕግ ሽፋን በመስጠት እውነቱን ለመሰወር የሚደረግ ጥረት እንጂ በርግጥ እውን የሚሆን አይደሉም ።

የምርት መገልገያዎችን በግል የያዘው መደብ የሠራተኞች የሥራ ኃይል ውጤት የሆነውን ምርት እንደፈለገ የመጠቀም መብት ሲኖረው ፣ የሠራተኛው መደብ ግን የዚህ ዓይነቱ መብት የለውም ። ይህ አንዱ እኩል ያለመሆን ምንጭ ነው ። በካፒታሊዝም ወዛደሩ የመምረጥ ፣ የመደራጀት ፣ የመከራከር ፣ የሥራ ሁኔታዎች መከበር ፣ ወዘተ . . . መብቶች ቢኖሩትም እነዚህ በበዝባዥና በተበዝባዥ መካከል እኩል የፖለቲካ መብቶች መኖራቸውን በምንም ዓይነት የሚያሳዩ አይደሉም ። በመሠረቱ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተው የምርት ግንኙነት የፈጠረው እኩል ያልሆኑ መብቶችን ነው። ሕጉም የሚጠብቀው እነዚህን በመሠረቱ እኩል ያልሆኑ መብቶችን እኩል አስመስሎ ነው። እኩል መብቶች የሌሏቸው ሰዎች በሕግ ፊት የሚቆሙት እኩል ሆነው አይደለም ። ምናልባት እነሱ እኩል የሚሆኑት እኩል ሳይሆኑ እኩል አስመስሎ ለደነገገው ሕግ ተጠያቂ በመሆን

Digitized by Google

ረገድ ነው። ሕግ ለምርት መገልገያዎች የግል ባለይዞታ ሠራተኛን አግርጦ የመቅጠርና የአቀማጠሩንም ሁኔታ የመወሰን መብቱን፣ ለሠራተኛው ደግሞ የሥራ ኃይሉን ባወጣለት /ምንዳ/ የመሸጥ «መብቱን» ይጠብቃል። ይህም በመሠረቱ እኩል ያልሆኑ መብቶችን መጠበቅ ነው።[27]

የሰዎች እኩል አለመሆን በተለያየ መልኮች ይታያል። ለምሳሌ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ ወዘተ ... ልዩነትን አስመልክቶ የሚፈጸመው ሰዎችን ማበላለጥ ሁኔታ አለ። ለዚህ ዓይነቱ ሰዎችን እኩል ያለመሆናቸውን ችግር የማያዳግም መፍትሔ ለመስጠት የቻሉት ሶሻሊስት አገሮች ብቻ ናቸው።

በአንፃሩ ከካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ይህ ጉዳይ መፍትሔ ያላገኘ መሠረታዊ ችግር ነው። የጾታ፣ የቀለምና የዘር አድልኦ ከሚደረግባቸው አገሮች መካከል አንዱ የሆነው ኢምፔሪያሊስት አሜሪካን ብንመለከት ለተመሳሳይ ሥራ ወንዶች ከሚከፈላቸው ደመወዝ 60 በመቶ ብቻ ለሴቶች የሚከፈልበት አገር ነው።[28] በተጨማሪም ሜሪላንድ በተባለች የአሜሪካ ግዛት በዘርና በቀለም ሳቢያ የተፈጸመውን አሳዛኝ ድርጊት እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። በማስገደድ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ወንጀል ተከሰው የሞት ፍርድ ከተላለፈባቸው 55 ሰዎች መካከል ሃምሳዎቹ ጥቁሮች ነበሩ። በዚህ ወቅት ተመሳሳይ ወንጀል የተፈጸመባቸው ጥቁር ሴቶች ከ10 እጥፍ በላይ የሚበዙ ቢሆንም ማንኛውም በማስገደድ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ ወንጀለኛ አልተቀጣም። ሕጉ ያው አንድ ሕግ ነው፤ አፈጻጸሙ ግን አንድ ወጥ ሳይሆን ይለያያል፤ በተለያዩ ዘሮች ላይ በተለያየ መንገድ ይሠራል።[29] የአሜሪካ ፍትሕ የተመሠረተው በዘርና በሀብት ላይ በመሆኑ ትክክለኛና እውነተኛ ፍትሕ አይደለም በማለት ጀርም አርባች የተባለው የአሜሪካ የሕግ ባለሙያ ተናግሯል።[30] ይህ የሚያመለክተው የካፒታሊስት ሥርዓት በሕግ ፊት እኩልነት የሚለውን ሕገ መንግሥታዊ መርህ መመሪያ እንደሆነ አድርጎ መመጻደቁን እንጂ እውነተኛ እኩልነት ሊገኝ የሚቻልበት አለመሆኑን ነው።

ስለዚህ «በሕግ ፊት እኩል መሆን» መጀመሪያ በመፈክርነት ቀጥሎም በሕግ መቅረጽ የቡርዧው መደብ የፈጸመው ታሪካዊ ተልዕኮ ቢሆንም፣ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተው የራሱ የምርት ግንኙነት ተግባራዊ ስለማያደርገው በዚህ ሥርዓተ ማኅበር የዜጎች የእኩልነት መብት ከይስሙላ የሚያልፍ አይደለም።

በሌላ በኩል በሶሻሊስት አገሮች የምርት መገልገያዎች በሕዝብ ይዞታ ሥር በመሆናቸው በዝባዥና ተበዝባዥ መደቦች አይኖሩም። በመሆኑም እያንዳንዱ የኅብረተሰብ አባል በሀገሪቱ የኤኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተካፋይ መሆን ይችላል። ሕዝቡ ለሶሻሊዝም ብሎም ለኮሚኒዝም ግንባታ የሚታገል በመሆኑ የዓላማ አንድነት አለው። ሶሻሊስት አገሮች በዚህ ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ላይ በመመሥረት «በሕግ ፊት እኩል መሆን» ሕገ መንግሥታዊ ዜጎች መብት መሆኑን አረጋግጠዋል።

የንግግርና የጽሑፍ ነፃነት

አንዳንድ መንግሥታት ልዩ ልዩ ገደቦች ቢያበጁበትም በአጠቃላይ የጽሑፍና የንግግር ነፃነት በሕገ መንግሥቶች ሁሉ የታወቀ መብት ሆኗል።

ሶሻሊስት አገሮችም የዚህ መብት መጠበቅ ለሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ በጣም ጠቃሚ መሆኑን በማመን በሕገ መንግሥቶቻቸው[31] ማወቅ ብቻ ሳይሆን መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ለምሣሌ እንደማተሚያ ቤቶች፣ የጽሕፈት መሣሪያዎች፣ የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሾች፣ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችና ሌሎችም አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ እንዲሟሉ

Digitized by Google



በካፒታሊስት ሥርዓት ለፖለቲካ ነጻነትና ለሰብአዊ መብት የሚቆሙ ኃይሎች መብታቸው እንደተገፈፈ ነው ።

Igor Geenvsky, Victor Semelov, p. 224

Digitized by Google

አድርገዋል፤ እያደረጉም ነው። ሕዝቦች በመንግሥትና በማኅበራዊ ኑሮ ጉዳይ ላይ ሐሳባቸውንና አስተያየታቸውን ማቅረብ መቻል ብቻ ሳይሆን ለችግሮች መፍትሔ በመስጠትም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በዋና ዋና ሕጎች ላይ ውይይት ያደርጋሉ፤ አስተያየትም ይሰጣሉ። በልዩ ልዩ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሥራዎች ላይ ትችት ሊያቀርቡ፣ ስለሚሻሻሉበትም ሁኔታ ሐሳብ ሊሰጡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ እንደሌሎች መብቶችና ነፃነቶች ሁሉ የንግግርና የጽሑፍ ነፃነትም የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጥቅሞች ወይም ሰላምን፣ ዴሞክራሲን፣ ሶሻሊዝምንና ኮሚኒዝምን በሚጎዳ ሁኔታ መገልገል አይፈቀድም።[32] በክፍል አንድ ነፃነትም ሆነ መብት የመደብ ይዘት እንዳለው ተገልጧል። ቡርዧው መጀመሪያ የራሱን ሥርዓት ሲገነባ ፊውዳሎችን መብት እንዳሳጣቸው ሁሉ ሠርቶ አደሩ ሕዝብም ተመሳሳይ ርምጃ ካልወሰደ በቀር መሸነፋቸውን በቀላሉ ተቀብለው የሠራተኛውን የበላይነት የማይሹት አድኅርያን ሥልጣን ለመያዝ የሚያሴሩበት መድረክ ካገኙ አዲሱን ሥርዓት ለመቦርቦር የማይቦዝኑ መሰሪ ጠላቶች መሆናቸው ታሪክ ያረጋገጠው ሃቅ ነው።

የንግግርና የጽሁፍ ነፃነትን ተግባራዊ ለማድረግ ዛሬ በሶቪዬት ኅብረት ከ8,000 በላይ ጋዜጦች ይታተማሉ። በየዓመቱም ከ37,000 ሚሊዮን በላይ ቅጅዎች ታትመው ይሠራጫሉ። ከ2,200 ሚሊዮን በላይ ቅጅዎች ያሏቸው 1,292 መጽሔቶች አሉ። ከመደበኞቹ ሌላ ገበሬዎች፣ ሠራተኞችና ሌሎችም የኅብረተሰቡ ክፍሎች ብዙ ጽሑፎች ለነዚሁ ጋዜጦችና መጽሔቶች አዘውትረው በመላክ ነፃ ሐሳባቸውን በማናቸውም ጉዳይ ላይ ይገልፃሉ።[33]

በሌላ በኩል ከካፒታሊስት አገሮች መካከል የአሜሪካ ሕገመንግሥት ማሻሻያ አንቀጽ 1 የንግግርና የጽሑፍ ነፃነትን በመቀነስ ኮንግረስ /ሕግ አውጭው የመንግሥት አካል/ ሕግ ማውጣት እንደማይችል ደንግጓል። ይሁን እንጂ የአሜሪካ ኮሚኒስት ፓርቲና የሌሎች ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶችን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ለመገታት ሲባል ሕገ መንግሥታዊ የንግግርና የጽሑፍ ነፃነትን የሚያጣብብና ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን የስሚዝ ድንጋጌ (The Smith Act) በ1940 በኮንግረሱ ታውጇል።[34]

የአሜሪካ የንግግር ነፃነት የገዥው መደብ አባሎች የንግግር ነፃነት ነው። በልዩ ልዩ ምክንያት በአንዳንድ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ የሚደረግ ትችትና አሉባልታ የተጧጧ የንግግር ነፃነት መኖሩን እንደሚያመለክት ይነገራል። እርስ በርሳቸው ቢነታረኩ ምንም ጉዳት የማያመጣባቸው መሆኑን አበክረው የሚያውቁት የገዥው መደብ አባላት ሲነታረኩ ይታያል። ይሁን እንጂ በመሠረታዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ለውጥ ጥያቄዎች ላይ አስተያየት ለመሰንዘርና መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ሕዝብን ለማደራጀት የሚሞክሩትን ቡድኖችም ሆነ ግለሰቦችን ለማፈን ኢያሉ የአሜሪካ የመንግሥት ተቋሞች ወቀ ጠንተት አሰፍስፈው እንደሚገኙ ደግሞ የታወቀ ነው።

<u>ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የማድረግ ነፃነት፣</u>

ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የማድረግ ነፃነት ሲባል ሕዝብ በሚሠራበት፣ በሚማርበት፣ በሚኖርበት ወይም አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ ሁሉ በማናቸውም የጋራ ጉዳይ ላይ ስብሰባና ውይይት ማድረግና ውሳኔ ማስተላለፍ፣ እንዲሁም በአደባባይ፣ በአውራ ጎዳና ወይም በማናቸውም አስፈላጊ ቦታዎች ላይ በመዘዋወር ወይም በመሰብሰብ ሃሳብና አስተያየትን መግለጽ ወይም ውሳኔ ማስተላለፍ መቻል ማለት ነው። ይህም የዜጎች ነፃነት መደባዊ ጠባይ ያለው መሆኑን ሲያስገነዝብ ሌኒን በ1919 ባደረገው ንግግር የመሰብሰቢያ አዳራሾች ሁሉ የግል ሀብት እስከሆኑ ድረስ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ እውነተኛ ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግ ነፃነት እንደ

Digitized by Google

ማይኖር ፥ በ1649 በእንግሊዝ ፤ በ1792—93 በፈረንሣይ የቡርዧ አብዮቶች በተካሄዱበት ጊዜ ቡርዧ አብዮተኞች የፊውዳል መሳፍንት ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የማድረግ ነፃነታቸውን እንደነፈጓቸው ሁሉ ሠርቶአደሩ ሕዝብም ከካፒታል ቀንበር ነፃ ለማውጣት ካፒታሊስቶችን የመሰብሰብ ነፃነት መንፈግ እንዳለበት ገልጾ ነበር ። እንዲያውም በተለይ የአሜሪካንና የእንግሊዝን የመሰብሰብ ነፃነትት መደባዊ ይዘት በመጥቀስ «በታላቋ ብሪታኒያና በአሜሪካ ሕገ መንግሥቶች ውስጥ የተደነገገው የመሰብሰብ ነፃነት ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅት ሁሉ የሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ እጆች ጠፍሮ ስለሚያስር ማታለያ ነው እንላለን »[35] ብሎ ነበር ።

ስለሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የማድረግ « ነፃነት አንድ ምሑር ሲፅፍ የተጀመረው በካፒታሊዝም ሥርዓት ቢሆንም በተሟላ ሁኔታ በሚገባ በሥራ ላይ የሚውለው በሶሻሊስት ሥርዓት ብቻ ነው»[36] በአሜሪካና ሌሎች ካፒታሊስት አገሮች እንደሚደረገው ሁሉ በተጠናከሩ የሶሻሊስት አገሮች ሕዝቦችበ ፓርቲና በአስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች ወይም በፓርላማው ፊት ለፊት ለምን እንደማይሰበሰቡ ፥ ወይም ሠላማዊ ሰልፍ እንደማያደርጉ በአንዳንድ ምዕራባዊያን አእምሮ ውስጥ የሚጉላላ መሆኑን በማንሳት የሶቪየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና ጸሐፊ ጓድ ቸርኔንኮ ሶቪየት ኅብረትን ምሳሌ አድርገው መልስ ሲሰጡ«- - - የሶቪዬት ኅብረት ሠርቶ አደር ሕዝብ ሐሳቡን ለመግለጽ ከፓርላማው ውጭ በመሰብሰብ ከመጮህ ይልቅ በፓርላማው ውስጥ ብዙ መሥራት -- ስለሚችል ነው »[37] ብለዋል ። ይህም ሕዝቡ ሲባል ምንም ዓይነት ሰላማዊ ሠልፍ አይደረግም ማለት አይደለም ። የሠርቶ አደሩ ሕዝብ የትግልና የድል ዕለቶች ፥ አብዮታዊ ክብረ በዓሎችና የትግል አንድነት መግለጫዎች ስብሰባና ሰላማዊ ሰልፍ ይደረግባቸዋል።

በዚህ ጽሑፍ ክፍል አንድ እንደተመለከተው ከምዕራባውያን አገሮች መካከል በተለይ ራሷን የዓለም ሰብዓዊ መብቶች አስከባሪ አድርጋ በሰየመችው በአሜሪካ ሕገ መንግሥት የተደነገገው ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የማድረግ ነፃነት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰላማዊ ሰልፈኞችን ከመታሰር ከመደብደብና ከመገደል አላዳናቸውም።

የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ሕገመንግሥት «የኢትዮጵያ ዜጎች በሕግ ተዘርዝር በሚወሰነው መሠረት የጦር መሣሪያ ሳይዙ ሰላማዊ ስብሰባ ለማድረግ መብት አላቸው»[38](መስመር የጸሐፊው)ይል ነበር። በዚህ ሕገመንግሥት መሠረት የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት ታላቅ ገደብ ነበረበት (የጦር መሣሪያ ሳይዝና « በሕግ ተዘርዝሮ በሚወሰነው መሠረት » ብቻ ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ ማድረግ) ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ የሚደረግበትን ሁኔታ የሚዘረዝረው ሕግ በ1959[39] መውጣት ይታወሳል ። ይሁን እንጂ ሕጉ ይህን ሕገ መንግሥታዊ መብት እጅግ በጣም በማጣበቡ በጊዜው ከፍተኛ ተቃውሞና ሰላማዊ ሰልፍ ማስከተሉ የሚዘነጋ አይደለም ።

ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ ሰፊው ሕዝብ አብዮቱ ያስገኛቸውን ኢኮኖሚያዊ ፥ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ድሎች በመደገፍና በማሰብ ፥ የአብዮቱን ጠላቶች የሚፈጽሟቸውን ልዩ ልዩ አሻጥሮች በመቃወም ፥ ከሌሎች አብዮታውያን አገሮች ፥ የነፃ አውጭ ግንባሮች ፥ ወዘተ . . . ጋር ያለውን የትግል አንድነት ለመግለጽ በሀገር አቀፍ ደረጃና ከወረዳ እስከ ክፍለ ሀገር ድረስ በየአካባቢው ሰላማዊ ስብሰባና ሰልፍ በማድረግ መብቱን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ይገኛል ።

በሕሊና የማዘዝ ነፃነት

በሕሊና የማዘዝ ነፃነት ማለት በሃይማኖት የማመንና የማምለክ መብት ብቻ ሳይሆን ፥ በሃይማኖት ያለማመንና ያለማምለክም መብትንም ያጠቃልላል ። የመንግሥ

ትና የቤተ ክርስቲያን መለያየትና የመንግሥት በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ዜጎች ፖለቲካዊ ዓላማ የሌለውን የፈለጉትን ሃይማኖት የመቀበልም ሆነ ያለመቀበል መብታቸውን ያረጋግጣል ።

በሕሊና የማመን ነፃነትን ሕገ መንግሥታዊ[40] ዋስትና ከሰጡት አገሮች መካከል ሶሻሊስት አገሮች ይገኙበታል ። ለምሳሌ የሶቭየት ኅብረት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 52 የሚከተለውን ይደነግጋል ።

የሶቭዬት ሶሻሊስት ሪፑብሊክ ኅብረት ዜጎች ፣ በኅሊናቸው የማዘዝ መብት አላቸው ። ይህም ማለት ማናቸውንም ሃይማኖት የማመንም ሆነ ያለ ማመን ፣ ሃይማኖታዊ እምነትን የማካሄድም ሆነ ኢሃይማኖታዊ ፕሮፓጋንዳ የማሰራጨት መብት አላቸው ። በሃይማኖት ጉዳይ ጸብ መጫርና ጥላቻን ማዛመት በሕግ የተከለከለ ነው ። በሶ·ሶ·ሪ·ኅ· የሃይማኖት ድርጅቶች ከመንግሥት ጋር ፣ ትምህርት ቤቶችም ከሃይማኖት ድርጅ ቶች ጋር ተለያይተዋል ።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ «የመንግሥት ሃይማኖት» ተብሎ የታወቀውን የማይከተሉ ዜጎች (በተለይ እስላሞች) የግል ሃይማኖታቸውን ክብረ በዓል በይፋ የማክበር ነፃነት ባለማግኘታቸው በዓላቸውን ለማክበር ሲሉ በሥራ ወይም በትምህርት ላይ ለማይገኙበት አግኞች ላይ ይደርስ የነበረው ችግር የሚረሳ አይደለም። በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የሃይማኖት እኩልነትና ነፃ እምልኮን በሕግ ለማስከበር አዋጅ ቁጥር 16/1967 ወጥቷል ። በአዋጁ ላይ እንደተመለከተው «. . . በበዓላት አከባበር ረገድ የኢትዮጵያውያን እኩልነትና አንድነት መጠበቅ ያለበት መሆኑን በመረዳት» የሁሉም እምነቶች በዓላት በእኩልነት እንዲከበሩ ተደርጓል ።

ከዚህም በላይ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ቁጥር 6 መሠረት «በሃይማኖቶች - - - መሀከል ምንም ዓይነት አድልዎ አይደረግም ። ማንኛውም ዜጋ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዮች ለሚኖረው ሚና - - - በሃይማኖት ሳቢያ ምንም ዓይነት ልዩነት አይደረግበትም ።» ይህም በመሆኑ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ በሕሊና የማመን ነፃነት ሕጋዊ ዋስትና አግኝቷል ።

በእምነት ነፃነት ስም በአገር አንድነትና በሰፊው ህዝብ አብዮት ላይ የሚሠራ ደባን፣ በዜጎች መካከል የሚደረግ ልዩነትን አብዮታዊት ኢትዮጵያ አጥብቃ ትቃወማለች።

የመደራጀት መብት

በሶሻሊስት አገሮች የሚታወቀው ሌላ ሕገ መንግሥትዊና ተግባራዊ የሆነ መብት የመደራጀት መብት ነው ። የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ከተፃራሪ የመደቦች ትግሌ ነፃ በመሆኑ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ሁሉ በአንድ ላይ ለማሰባሰብ የሚያስችል የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።ይህም በመሆኑ የሕዝባውያን ድርጅቶችን፣የሙያ ማኅበራትን፣ወዘተ . . . መመሥረትንና ማጠናከርን መንግሥት ያበረታታል፤ድጋፍም ይሰጣል።በአጠቃላይ የተሟላ የመደራጀት መብት የሶሻሊስት ሥርዓት አንዱ መለያና አካል ነው ። የዚህ መብት በሥራ ላይ መዋል ሕዝባዊ ዲሞክራሲን ለማዳበርና ለመንከባከብ ፣ በሶሻሊስት ግንባታ ሥራ የሕዝቡን ተሳትፎ ለማሳደግ ፣ የባህልና ትምህርት ሥራን ለማስፋፋት ፣ የሕዝቡን መብቶች በሥራ ላይ ለማዋልና ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን ለማጠናከር ይረዳል ።

ለምሳሌ የሰፊውን ሕዝብ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ፣የማኅበራዊና የባህል የተሟላ እድገት ለማረጋገጥ በሶሻሊስት አገሮች ከተቋቋሙትና ከተጠናከሩት ድርጅቶች መካከል የሠራተኞች ፣ የገበሬዎች ፣ የኅብረት ሥራ ፣ የወጣቶች ፣ የሴቶች ፣ የአርበኞች ፣ ወዘተ - - - ማኅበራት ይገኙበታል ። እነዚህም ማኅበራት እንደሁኔታው በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዮች ነቅተው ይሳተፋሉ ።

Digitized by Google

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብም በቅድመ
አብዮት ኢትዮጵያ ተነፍጎት የነበረ
ውን የመደራጀት መብት በአብዮቱ ሊጐና
ፀፍ በቅቷል ። በተለይ በኢሠፓአኮ
ርዕዮተ ዓለማዊና ፖለቲካዊ አመራር ሠራ
ተኛው ፣ ገበሬው ፣ ከተማ ነዋሪው ፣ ወጣቱ፣
ሴቱ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ በመደረጉ
እያንዳንዱ ዜጋ ያልታቀፈበት ድርጅት ሊኖ
ር ከቶ አይችልም። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሠራ
ተኞችን የመደራጀት ሁኔታ ብንመለከት ፣
266,082 አባላት ባሏቸው 1639 መሠረታዊ
ማኅበራትና 1131 የመሠረታዊ ማኅበር ዞር
ፎች በመቋቋም አባላቱ በ940%፣ ማኅበራቱ
ደግሞ በ719·5% እድገት አሳይተዋል ።[41]

ዛሬ በአገር አቀፍ የተቋቋሙ ብዙ ሚሊ
ዮን አባላትን ያቀፉ ፣ የገበሬዎች ማኅበር
(መኢገማ) ፣ የሠራተኞች ማኅበር (መኢ
ሠማ) ፣ የሴቶች ማኅበር (አኢሴማ) ፣ የወጣ
ቶች ማኅበር (አኢወማ) ተደራጅተውና
(ሠንጠረዥ 4 ይመለከቷል) ተጠናክረው
በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፣ የሶሻልና የፖለ
ቲካ ጉዳዮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ
መንገድ ከፍተኛ ተሳትፎ በማድረግ ላይ
ናቸው ። ገበሬውና የከተማ ነዋሪው ሕዝብ
(በከነማ አማካይነት) በየደረጃው የራ
ሱን የአስተዳደር ፣ የዳኝነት ፣ የደኅንነት
ጥበቃ ፣ ወዘተ --- ጉዳይ ራሱ በመምራት
ላይ ይገኛል ። ሰፊው ሠርቶ አደር ሕ ዝ ብ
ብሔራዊ ሀብቱን ለመጠበቅና ለመንከባከ
ከብ ፣ ብኩንነትን ፣ ምዝበራንና ጉቦኝነትን
እንዲሁም ሌሎች ማኅበራዊ ጠንቆችን ለመ
ዋጋት የሚያስችለውን ብሔራዊ የሠርቶ
አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴን አቋቁሟል።ከዚህ
ሌላ ብዛት ያላቸው የሙያ ማኅበራት ተመ
ሥርተዋል ።

በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች የመ ሳተፍ መብት

የአንድ መንግሥት ሕዝባዊነት የሚለ
ካው በመንግሥቱ ሥራ ከንውን ው ስ ጥ
ሰፊው ሕዝብ በሚኖረው ተካፋይነት (ተሳ
ትፎ) መጠን ነው ። በ1923 በወጣው የኢ
ትዮጵያ ሕገ መንግሥት መሠረት ሰ ፊ ው
ሕዝብ በወቅቱ ተቋቁሞ ለነበረው ፓርላማ
ሊመረጥ ቀርቶ የመምረጥ መብት እንኳን
አልነበረውም ። ስለሱ ሆነው የሚመርጡ
ለት መሣፍንቱና መኳንንቱ ነበሩ ። በታገ
ደው በ1948 ሕገ መንግሥትም ቢሆን የራ
ሱን ዕድል « የሚወስኑለትን » ከገዢው
መደብ አባሎች መካከል የመምረጥ መብት
ቢኖረውም ፣ ለመመረጥ ቢያንስ (ከሌሎች
ተፈላጊ ነገሮች መካከል) ብር 1,000·0 የሚ
ያወጣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ብር
2000·00 የሚገመት የሚንቀሳቀስ ንብ
ረት [42] የግድ የሚያስፈልግ በመሆኑ በቂ
ገንዘብ የሌለው ግለሰብ የመመረጥ መብ
ቱን በሕግ በመነፈጉ ወደ ፓርላማው መግ
ባት አይችልም ነበር ። ይህን የገዢ መደቦች
መሰብሰቢያ የነበረ ፓርላማ አብዮታዊው
መንግሥት «የኢትዮጵያ የሕግ መምሪያና
መወሰኛ ምክር ቤት (ፓርላማ) ሕዝቡ በት
ክክለኛ የዲሞክራሲ ዘዴ ለሕዝቡ ጥቅም
የሚያገለግሉ እውነተኛ ወኪሎቹን እስኪ
መርጥ ድረስ ተዘግቷል» [43] በማለት ገና
በመጀመሪያው አብዮታዊ አዋጅ አማካይ
ነት እንዲዘጋ አድርጎታል ።

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው እስከ
ሀገር አቀፍ ደረጃ ለተቋቋሙት ሕዝባውያን
ድርጅቶች፣ ለከነማ እና ለሌሎችም ሕዝባዊ
ተቋሞች አመራር ሰጭነት ለመመረጥ ዕ
ድሜው ብቃትና ለአብዮቱ ያለው ፍቅር ይታ
ያል እንጂ ሀብት ለመመረጥ የሚያበቃ መመ
ዘኛ የለም ፤ አይኖርምም ። እንዲያውም ግን
ኛውም ከሩብ ጋሻ መሬት በላይ የነበረው፣
ከሃምሳ ብር በላይ የቤት ኪራይ ገቢ የነበ
ረው ፣ የተወረሰ የምርት መገልገያ ባለቤት
የነበረ ወይም የሱ ጥገኛ የነበረ ግለሰብ
ለጊዜው ከመምረጥም ሆነ ከመመረጥ በሕግ
ተገልለው እንደነበር የሚታወስ ነው ። ዛሬ
ለነዚህ ሕዝባውያን ድርጅቶች አመራር
የሚሰጡትን ጓዶች ለመምረጥ ወይም ለመ
መረጥ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመምረ
ጥና በመመረጥ መብቱ በመጠቀም ላይ ይገ
ኛል ።

Digitized by Google

መንጠረዥ አራት

የእምስቱን ሕዝባዊ ድርጅቶች የመሠረታዊ ማኅበራትና የአባላት ብዛት የሚያሳይ መንጠሬዥ

ተራ ቁጥር	ሕዝባዊ ድርጅቶች	የመሠረታዊ ወይም መደብ ማኅበራት ብዛት	የጠቅላላ አባላት ብዛት
1	መ·ኢ·ሠ·ማ·	1,639*	266,082*
2	መ·ኢ·ገ·ማ·	20,256	6,559,523
3	አ·ኢ·ወ·ማ·	17,423	3,330,165
4	አ·ኢ·ሴ·ማ·	17,325	4,217,074
5	ከ·ነ·ማ·	1,152	3,433,645

ምንጭ፤— የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የኢሠፓአኮ መሠረታዊ ድርጅት ሰኔ 8 ቀን 1976 ለኢሠፓ መሥራች ስብሰባ ያቀረበው ሪፖርት ገጽ 12 ። ከላይ ከተገለጸው መሠረታዊ የሠራተኛ ማኅበራት ሌላ መኢሠማ 170 ለወረዳ 64 የአውራጃ 16 የክፍለ ሀገራት የከልል ሠራተኛ ማኅበራትን አቅፏል ። እነዚህ ማኅበራት እስከ ግንቦት 1976 ድረስ ተመዝግበው የሚገኙ ናቸው ።

—ከተራ ቁጥር 2—5 የተመለከተው የተገኘው ከመስከረም መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 7 ገጽ 21 ነው ።

በሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች መሠረት [44] ሰፊው ሕዝብ በሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የመሳተፍ መብት አለው ።

ሌሎች ብሔራዊና የፖለቲካ መብቶችና ነፃነቶች

ከእነኝህ መብቶችና ነፃነቶች መካከል ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ያለመያዝ መብት ፣ የመኖሪያ ቤት ያለመደፈር መብት ፣ የደብዳቤ ፣ የስልክና የቴሌግራም ልውውጥ ጥበቃ መብት ይገኙበታል ።

ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ያለ መያዝ መብት ማንኛውም ሰው በሕገ ወጥ መንገድ ሊያዝ አይችልም ። ሕገወጥ ድርጊት የፈጸመ ወይም ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው የሚያዘው ብሔራዊ ሕግ በሚያዘው መሠረት ፣ ወይም ከፍርድ ቤት ወይም እንደ ሀገሩ የሕግ ሥርዓት ከዓቃቤ ሕግ ወይም ከሌላ ከፍል በሚሰጠው የመያዣ ትእዛዝ መሠረት ብቻ ነው ።

የመኖሪያ ቤት ያለመደፈር መብት

ማንም ሰው በኪራይም ሆነ ሠርቶ የሚኖርበት ቤቱ ወይም ግቢው በተለይ አገልግሎት ለመስጠት ሥልጣን ከተሰጣቸው ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ወይም ሕግ ከሚፈቅድላቸው ባለሥልጣናት በስተቀር በማንም ሌላ ባለሥልጣን ወይም ግለሰብ ሊደፈር አይችልም ።

የደብዳቤ ፣ የስልክና የቴሌግራም ልውውጥ ጥበቃ መብት

ከባለአድራሻው ወይም ከሚመለከተው በስተቀር ማንም ባለሥልጣን ፣ ድርጅት

Digitized by Google

ወይም ግለሰብ በደብዳቤ፣ በስልክ ወይም በቴሌግራም የሚደረገውን ግላዊ ግንኙነት ለማወቅ ብሎ ማየት ወይም መስማት የተከለከለ ነው። ይህ የተከለከለው የዜጎችን ግላዊ ግንኙነት ለመጠበቅና ሕገ መንግሥታዊ መብትም ስለሆነ ነው። ይህ መሠረታዊ መብት በአሜሪካ ሕገ መንግሥት 4ኛው ማሻሻያ ዋስትና ቢሰጠውም በ1972 ብቻ ከሶቭየት ኅብረትና ወደ ሶቭየት ኅብረት ከተላኩት 4,350,000 ደብዳቤዎች መካከል ኒውዮርክ ውስጥ 2,300,000 ሲመረመሩ፣ 33,000 ያህሉ ፎቶግራፍ ተነሥተዋል፤ 8,700 ያህል ተከፍተዋል።[45]

በተጨማሪም መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጽሟቸውን ስሕተቶች እንዲያርሙ የመጠየቅና ሐሳብ የማቅረብ የቤተሰብ ጥበቃ ከመንግሥት የማግኘት መብት፣ አቤቱታ የማቅረብ በአንዳንድ ብሔራዊ መንግሥታት ሕገ መንግሥቶች የሚታወቁ ናቸው።

የዜጎች መሠረታዊ ግዴታዎች

ከዚህ በላይ ለመግለጽ የተሞከረው የዜጎችን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ነው። መብትንና ነፃነትን ምንጊዜም ቢሆን ከሚጐዳኟቸው ግዴታዎች ነጥሎ መመልከት ትክክል አይደለም። ስለሆነም ዜጎች በዜግነታቸው በአባልነት ለሚገኙበት ኅብረተሰብና ለመንግሥታቸው የሚኖርባቸውን ዋና ዋና ግዴታዎችን እንመልከት።

በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን ሥርዓት አስወግዶ በምትኩ እውነተኛ እኩልነት ነፃነት፣ መብት፣ ዲሞክራሲ፣ ፍትሕና ሰላም የሰፈነበትን የሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብረውን የሶሻሊስት መንግሥት መንከባከብና መጠበቅ የእያንዳንዱ ሀቀኛ ዜጋ መብትና ግዴታ ነው። ዜጎች ያለአንዳች ማወላወል ግዴታቸውን መወጣት ካልቻሉ ሶሻሊስት እናት ሀገርን በሚገባ ማጠናከር፣ ሶሻሊዝምን በተሳካ ሁኔታ መገንባት፣ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ቁሳዊና ባህላዊ ሕይወት ማሻሻል፣ የዜጎችን ሕጋዊና ቁሳዊ፣ መብቶችና ነፃነቶች ማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል። ለማንኛውም ሶሻሊስት ዜጋ ግዴታን መወጣት ማለት እውነተኛ መብትና ነፃነትን መቀዳጀት ማለት ስለሆነ በፈቃዱ ግዴታውን ለመወጣት ወደኋላ አይልም። የሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች ዜጎች የየሀገራቸውን ሕጎች እንዲያከብሩ ግዴታ ይጥሉባቸዋል። በዚህም መሠረት ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሕጎችን፣ ደንቦችን፣ ኮሚኒስታዊ ሥነ ምግባርን ማክበር ብቻ ሳይሆን በሥራ መተርጐማቸውንም መከታተል መብቱ ነው።[46]

በማንኛውም ሶሻሊስት ዜጋ መከበር የሚገባቸው መሠረታዊ ግዴታዎች ሕግንና የሥራ ሥነ ሥርዓትን ማክበር፣[47] ሶሻሊስት ንብረትን መንከባከብና መጠበቅ፣ አገርን ከጠላት መከላከልና ግብር መክፈል ናቸው። ለምሳሌ የሶቭየት ኅብረት ሕገመንግሥት አንቀጽ 60 «ማንኛውም አካለ ሙሉ የሆነ የሶ.ሶ.ሪ.ኅ ዜጋ በተመረጠበትና ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ በሆነው የሥራ ገበታው ላይ የሥራ ሥነ ሥርዓትን ማክበርና በቅን ልቦና ተግባሩን ማከናወን ግዴታውና የከበረ ተግባሩ ነው። ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ ከሆነው ሥራ ቸል ማለት ከሶቭየት ኅብረተሰብ መርሆዎች እንደመውጣት (መጣስ) ይቆጠራል» ይላል።

ሶሻሊስት ንብረት የማናቸውም ሶሻሊስት አገር ጠንካራ የኢኮኖሚ መሠረት፣ እንዲሁም የኃይል፣ የብልጽግናና የነፃነት ምንጭ ነው። የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ሕይወት የተመሠረተው የሕዝብ ሀብት በሆነው በሶሻሊስት ንብረት ላይ ነው። ይህም በመሆኑ ዜጎች ሁሉ ሶሻሊስት ንብረትን የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።[48] ሶሻሊስት ንብረት ሲባል የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት ማለት ነው። የመንግሥትና የኅብረተሰብን ንብረት ያላግባብ

Digitized by Google

ማባከንና ማጉደል በሕግ የሚያስጠይቅና ከፍተኛ ሕገወጥ ተግባር ነው ። በሀገራች ንም በቅርብ የልዩ ፍርድ ቤትና የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴዎች የተቋቋሙት ይህን ከፍተኛ ሕገወጥ ተግባር በመቋቋም የመንግሥትና የኅብረተሰቡን ንብረት ለመ ንከባከብና ለመጠበቅ ዜጎች በነዚህ ድርጅ ቶቻቸው አማካይነትም የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ ታስቦ ነው ።

ሶሻሊስት እናት አገርን ከጠላት መከላ ከል የዜጎች ግዴታና ክብርም ነው ።[49] በማናቸውም ጊዜ በጦር ኃይሎች ውስጥ ተደልድሎ ወታደራዊ አገልግሎት ማበር ከት ለሶሻሊስት ዜጋ የክብር ግዴታው ነው ። ሀገርን መክዳት ፣ የታማኝነትን ቃል ኪዳን ማፍረስ ፣ ለጠላት ከድቶ መግባት ፣ ለጠላት መሰለልና የሀገርን ወታደራዊ ኃይል የሚጎዳ ማናቸውም ተግባር መፈጸም ከባድ ቅጣትን የሚያስከትል ወንጀል ነው ።[50] ይህን የሶሻሊስት ዜጎች ሕገ መንግሥታዊ መብትና ግዴታ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ ጠንካራና የማይበገር የመከላከያ ኃይል በመገንባት ፣ ሶሻሊዝ ምን ፣ እውነተኛ ፍትሕንና ነፃነትን ፣ እንዲ ሁም ሶሻሊስት ዲሞክራሲን በጽኑ አስተ ማማኝ መሠረት ላይ ለመጣል እንዲቻል አብዮታዊው መንግሥት የብሔራዊ ውት ድርና አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 238/1975 እና ወታደራዊ ኮሚሣሪያትና የአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 239/1975 አውጥቷል ። እነ ኝህ አዋጆች ተግባራዊ እየሆኑ ነው ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ግዴታዎችና ዋና ዋናዎቹ ፣ በአጠቃላይ ሁሉም ሶሻሊ ስት አገሮች በሕገ መንግሥቶቻቸው ውስጥ ያስገቧቸው እንጂ ሌሎችም ሕገ መንግሥ ታዊ ግዴታዎች በአንዳንድ ሶሻሊስት አገ ሮች ብሔራዊ ሕገ መንግሥቶች ው ስ ጥ ተደንግገው ይገኛሉ ። ከእነዚህም ግዴታ ዎች መካከል የሌሎችን መብት የማክበር ግዴታና በብሔሮችና በብሔረሰቦች መካ ከል ያለውን ግንኙነት የማጠናከር ግዴታ፣ የራስን ልጅ ተንከባክቦ የማሳደግ ግዴታ ፣ ከሌሎች ሀገሮች ሕዝቦች ጋር ወዳጅነትና ትብብርን የማጠናከር ዓለም አቀፋዊ ግዴታ ታሪካዊ ቦታዎችንና የባህል ቅርሶችን ተን ከባክቦ የመጠበቅ ግዴታ ፣ ግብር የመክፈል ግዴታ ይገኙበታል ።[55]

የአንዳንድ ሶሻሊስት ሕገ መንግሥቶች ግሥቶች ግብር የመክፈል ግዴታን ደንግ ገዋል ። ለምሳሌ ፣ የ1946 የአልባኒያ ሕዝ ባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 33 (1) «ማንኛውም ዜጋ በገቢው መጠን ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት» ሲል ፣ የቡልጋ ሪያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አን ቀጽ 94 «የዜጎች ግብር የመክፈል ግዴታ በመክፈል ችሎታ መሠረት የተከፋፈለ ነው» - - - ይላል ።

የሶሻሊስት አገር ዜግነት የሌላቸው የሌላ አገሮች ሰዎች በልዩ ልዩ ምክንያት የጥገ ኝነት ፣ የንብረትና የሰውነት ጥበቃ መብት እንደሚያገኙ ሁሉ አንዳንድ ግዴታዎችም አሉባቸው ።

በአጠቃላይ እስከ ዛሬ ድረስ ያለው የመ ደባዊ ኅብረተሰብ ታሪክ በአንድ በ ኩ ል ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ ለመውጣት ፣ በሌላ በኩል የመበዝበዝና የመጨቆን «መብትን» ለማስከበርና ሌላውን ነፃነት ለመንፈግ የተ ደረገ መራራ የትግል ታሪክ ነው ።

የኅብረተሰብ እድገት ታሪክ ከመብ ትና ነፃነት እድገት ታሪክ ጋር የተያያዘ በመሆኑ አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚታይ ክስተት አይደለም ። የሰው ልጅ ባለፈባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ሁሉ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከመብትና ነፃነት ጋር የነበረው ግንኙነት በወቅቱ ሥልተ ምርት ዓይነት የተወሰነ ነው ። ሰፊው ሕዝብ ከባሪያ አሳዳሪው ሥር ዓት ይልቅ በፊውዳሉ ሥርዓት የተሻለ መብ ትና ነፃነት አይቷል ። የካፒታሊስቱ ሥር ዓት ደግሞ ከባሪያ አሳዳሪውና ከፊውዳሉ ሥርዓት የተሻለ መብትና ነፃነት አሳይቷል። ነገር ግን የሠርቶ አደሩ ሕዝብ በዓይነቱ አዲስ የሆነ ሰፊ መብትና ነፃነት ለመጐና ጸፍ የቻለው በሶሻሊስት ሥርዓት ብቻ ነው ።

ዓለም በኢምፔሪያሊስትና በሶሻሊስት ጐራዎች በተከፈለችበት በአሁኑ ጊዜ የመ ብትና የነፃነት ጥያቄና ግንዛቤው ከመደ ባዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ተፅዕኖ ነፃ ሊ ሆ ን አይችልም ። የኢምፔሪያሊዝም አፈቀላጤ ዎች የተሟላና ፍጹም የሆነ መብትና ነፃ ነት የሰፈነው በቡርዧው ዓለም (ነፃው ዓለም) ብቻ አድርገው ለማቅረብ የማያደ

Digitized by Google

ርጉት ጥሬት የለም። ኢምፔሪያሊስቶች የሚያስከብሩት ግን የጥቂት የሞኖፖል ቡርዧዎችን መብትና ነፃነት ነው ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቡርዧው ነፃነት ማለት የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ባርነት ነው ። ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከዚህ ባርነት ነፃ የሚወጣው የራሱ መለያ የሆነውን የሶሻሊስት ሥርዓት ሲገነባ ብቻ ነው ። እውነተኛ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶችና ነፃነቶች ባለቤት የሚሆነውም ያኔ ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ክፍል አንድና ሁለት ውስጥ በካፒታሊስት አገሮችና በሶሻሊስት አገሮች መብትና ነፃነት እንዴት እንደሚታዩ፣ የተሰጣቸው ሕጋዊ ዋስትና እስከምን ድረስ እንደሆነና በይበልጥም ሕጋዊ ዋስትና ያገኙትም ቢሆኑ ምን ያህል ቁሳዊ መሠረት ኖሮአቸው ተግባራዊ ሊሆኑ ወይም ላይሆኑ እንደቻሉ ለመመርመር ተሞክሯል ። የካፒታሊስቱ መብትና ነፃነት ከሶሻሊስቱ መብትና ነፃነት ጋር ሲነፃፀር ምን ያህል ኋላቀር እና የይስሙላ ብቻ እንደሆነ ለማብራራት ተሞክሯል ።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ የመብትና የነፃነት ሁኔታዎችን በተቅሉ መመርመር ቢሆንም ፣ በመጠኑ የአብዮታዊት ኢትዮጵያን የመብትና የነፃነት ሁኔታ በአጠቃላይና በአጭሩ ለማየት ተሞክሯል ። የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት አንደኛውና ዋናው ዓላማ ሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ እውነተኛ መብቶችና ነፃነቶች ባለቤት ማድረግ ነው ። ይህ ክቡር ዓላማ ተገራሪ ኃይሎችን ማለትም የኢፔሪያሊስቶችን ፣ የፊውዳሎችንና የቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስቶችን ደባና ሴራ ለማክሸፍ ከፍተኛ መሥዋዕትነት ሳይከፈልበት ግቡን አይመታም ። ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት በትክክል እንደገለጹት ፦—

. . . የሶሻሊስት አብዮቶች በተቀጣጠሉባቸው አገሮች ሁሉ ኢምፔሪያሊዝም ራሱ በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ወይም የውስጥ አድኅርት ኃይላትን በማደራጀት ያልታየበት የታሪክ አጋጣሚ የለም ። ይህም ጣልቃ ገብነቱ በሠርቶ አደሮች ያልተቀጠበ መስዋዕትነት መወገዱ የማይቀር ቢሆንም የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት ለመለወጥ የሚካሄደውን ጥረት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ገልጽ ነው ።

እውነተኛ መብት ፣ ነፃነት ፣ ከኩልነት ፍትሕና ዲሞክራሲ ሊሰፍን የሚችለው አብዮቱን ነቅቶ በመጠበቅና በመንከባከብ ሶሻሊዝምን ማገንባት ሲቻል ብቻ በመሆኑ ግንባታው በየመልኩ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት መክፈል የእያንዳንዱ ሀቀኛ እና ለፍትሕ የቆመ ዜጋ አብዮታዊ ግዴታ ነው

የግርጌ ማስታወሻ

1. Pieter N. Drost, *Human Rights as Legal Rights*, (London: 1965) p. 15.
2. Ian Brownlie (ed.), *Basic Documents on Human Rights* (London: Clarendon Press 1971), p. 113.
3. V. Kartashkin, *Human Rights and International Cooperation* (Moscow: APN Publishing House, 1977), p. 10 ff.
4. J.F. Green, *The United Nations and Human Rights*, Washington, 1966, p. 40 quoted in V. Kartashkin p. 23.
5. Ian Brownlie, *Ibid.*, p. VI and Karatshkin, *Ibid.*, p. 10 ff.
6. Ian Brownlie, *Ibid.*, p. VII-X.
7. የ.ሶ.ሪ.ኅ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ፣ የአልባኒያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17፣የቪየትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 30 እና ሌሎችም ሕገ መንግሥቶች።
8. *Socialism Theory and Practice*, No. 8, August 1981, p. 50.
9. G. Chernikov, *The Crisis of Capitalism and the Conditions of the Working People* (Moscow: Progress Publishers, 1980), p. 143 5.
10. Bulletin of Labour Statistics, International Labour Office Geneva 1980, 1984-1, p. 281-4, 45-60.
11. Bulletin of Labour Statistics.
12. ሠርቶ አደር—የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ልሳን ፣ ቅጽ 31፣ቁ- 90 ፣ ገጽ 5 ።
13. የቡልጋሪያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 74፣የሐንጋሪ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 46፣ የቪየትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 31...ይመልከቱ ።
14. የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 64/68 አንቀጽ 31 ፣ 34 ፣ 35 ።

Digitized by Google

15. A. K.H. Makhnenko, *The Star Law of the Socialist Countries* (Moscow: Progress Publishers, 1976), p. 198.
16. I· Chekharin, *The State and Social System in USSR* (Moscow: APN Publishing House, 1974), p. 70.
17. CPUSA "USA: Human Rights Denied", *Socialism Theory and Practice*, Vol. 6. (Moscow: APN Publishing House, 1978), p. 131.
18. የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ ሰነዶችና ውሳኔዎች ፣ ታኅሣሥ 1975 ፣ ገጽ 81-83 ።
19. የሶ.ሶ.ሪ.ኅ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 43 ፣ የሩማኒያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25 ... ይመልከቱ ።
20. CPUSA, loc. cit., p. 133.
21. A. Kosistyn, *op. cit.*
22. መዝገቡ ምትኬ ፣ የሕገ መንግሥት መርሆችና ጽንሰ—ሐሳቦች አጠቃላይ ማብራሪያ ፣ (አዲስ አበባ፣ ያልታተመ 1975) አ. ኢት. አ ቁ) ፣ ገጽ 150
23. ብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ፣ የአንደኛ ፣ የሁለተኛና የሦስተኛ ዙሮች የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ሂደትና ውጤት ግምገማ ፣ አዲስ አበባ
24. ሠርቶ አደር—የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ልሣን ፣ ቅጽ 7 ፣ ቁጥር 210 ፣ ገጽ 1፣6
25. K. Marx and F. Engels, *Selected Works*, Vol. I, (Moscow: Progress Publishers 1976), p· 211.
26. M. Cornforth, *Ibid.*, p. 281 ff·
27. *Ibid.*
28. S. Menshikov, "The General Crisis of Capitalism-Why it is Aggravating," *Socialism Theory and Practice*, No. 3, (Moscow: APN Publishing House, 1982), p. 108.
29. Albert Pigolkin, "All Citizens Equal Before the Law", *What The Soviet Constitution Guarantees*, (Moscow: APN Publishing House, 1978), p. 8-9.
30. *Ibid.*, p. 7.
31. የሶ. ሶ. ሪ. ኅ. ሕገ. መንግሥት አንቀጽ 34 ፣ የአልባኒያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 12፣የሩማኒያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 16 ይመልከቱ ።
32. *V. Koldayev, Soviet Citizens: Their Rights and Duties*, (Moscow: APN Publishing House, 1976), p. 41.
33. *Ibid.*, p· 42-43.
34. Geevsky, *loc. cit.*, p. 9.
35. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 29. (Moscow: Progress Publishers, 1974), p. 251-256.
36. V. Koldayev, *loc. cit.*, p· 44
37. K. Chernenko, *Soviet Democracy*: Principle and practice (Moscow: APN Publishing House, 1977), p. 73.
38. አንቀጽ 45
39. የሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ስብሰባ የሚደረግበትን ሥነ ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 243/1959
40. የኮሪያ ዲሞክራቲክ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 ፣ የአልባኒያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17 ፣ የቡልጋሪያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 78 ወዘተ ... ይመልከቱ ።
41. የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የኢሠፓአኮ መሠረታዊ ድርጅት በኢሠፓ መሥራች ስብሰባ ላይ የቀረቡ ልዩ ልዩ ሪፖርቶች ፣ አዲስ አበባ ፣ ግንቦት 1976 ፣ ገጽ 12
42. ስለሕግ መምሪያ ምክር ቤት አማካሪዎች አመራረጥ የወጣ የ1961 አዋጅ ቁጥር 264/1961 አንቀጽ 15/4
43. በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ለማ ቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 1/1966 ፡ንቀጽ 4
44. የቬየትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 23 ፣ የሞንጎሊያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 ፣ የኮሪያ ዲሞክራቲክ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 12- » ይመልከቱ ።
45. Geevsky, *Ibid.*, p. 157.
46. I· Chekharin, *loc. cit.*, p. 83 and Art. 59 of the Constitution of the USSR.
47. Art 39 of the Constitution of the People's Republic of Mongolia and the Constitutions of other socialist countries.
48. Art 59 of the Constiution of People's Republic of Hungary and Art. 93 of the Constitution of the People's Republic of Bulgaria.
49. Art. 32 of the Constitution of the People's Republic of Albania and Art. 60-61 of the Constitution of the People's Republic of Hungary.
50. A. KH. Makhnenko, *loc. cit.*, p. 204.
51. Art 64 and the following of the Constitution of the USSR.

Digitized by Google

የፖለቲካ ሥርዓትና ተግባሩ

አበበ ወርቁ

የዘመናችን የኅብረተሰብ ታሪክ ልዩ ባህርያት ከሆኑት አንዱ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የፖለቲካ ሚና እጅግ ከፍ እያለ መምጣትና መሠረታዊ የማኅበራዊ ችግሮች ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፖለቲካ ጋር ይበልጥ የተያያዙ መሆናቸው ነው። ተራማጅና የሠመረ የፖለቲካ አመራር የመሠረቱ ሀገሮች ከልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግሮች ፣ ከረሀብ ፣ በእርዛት ፣ ከድርቅ ወዘተ ተላቀው የኢኮኖሚ የባህልና የመንፈሳዊ እድገታቸውን ሲያፋጥኑ ይታያሉ። ዛሬ የሶሻሊስት ሀገሮች የሕዝቦቻቸውን ፍላጐት አርክተው ለበለጠ ድል በመታገል ላይ የሚገኙት የላቀ የፖለቲካ ሥርዓትና አመራር በመመሥረታቸው ነው።

በአንፃሩ ግን ህዝቦች በአመራር የሚጨቆኑት ፣ በኢኮኖሚ የሚበዘበዙትና በማኅበራዊ ኑሮ ለውርደትና ለጉስቁልና የተዳረጉት በዝባዦች የፖለቲካ ሥልጣንን ጠቅልለው ለመያዝ በመቻላቸው ነው።

ሰፊው ህዝብ ከልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግሮች ሊላቀቅና ፍትሕና እኩልነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ ሊገነባ የሚችለው የፖለቲካ ሥልጣንን በመያዝ ለራሱ የሚያገለግለው የፖለቲካ ሥርዓት ሲመሰረትና ይህንንም የፖለቲካ ሥልጣን በመጠቀም ምርትንና ክፍፍልን በማህበራዊ ይዞታ ሥር ሲያውል ነው።

ይኸ በኅብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው ፖለቲካ ምንድ ነው? ከሌሎች የኅብረተሰብ የኑሮ ገጽታዎች በምን ይለያል? የፖለቲካ ይዘትና ተግባራት ምንድን ናቸው? ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታትና እድገትን ለማፋጠን ፖለቲካ ከሌሎች የኅብረተሰብ የኑሮ ገጽታዎች ጉልህ ሚና አለው ሊባል የቻለው ምን ባህሪያት ስላሉት ነው? ይህ ጽሑፍ በፖለቲካ ሥርዓት ይዘትና ተግባራት ላይ በማተኮር ለእነኚህ ጥያቄዎች በተቻለ መጠን መልስ ለመስጠት ይሞክራል። ከዚያ በፊት ግን የአንዳንድ ጽንሰሃሳቦችንና የአጠናን ዘዴዎችን ማብራራት አስፈላጊ ነው።

Digitized by Google

የፖለታካን ይዘት በበለጠ ለመረዳትና ለመተንተን ከሚያስችሉን ዘዴዎች አንዱ ፖለቲካን ከኅብረተሰብ ሥርዓቶች አካልነቱ አንፃር ማጥናት ነው ። አያሌ የፖለቲካ ተመራማሪዎች ይህን የአጠናን ዘዴ ይጠቁሙበታል ። « የፖለቲካ ስርዓት የሚባለውን ፈርጅ በትክክል መተርጎምና መጠቀም---የኅብረተሰብን የፖለቲካ ሕይወት የሚገልጹትን መሠረታዊ ፈርጆችና ጽንሰ ሀሳቦችን በአንድ ሥርዓት ለማጠቃለል ያስችላል ። »[1] ይህንንም መሠረት በማድረግ ወይንም ከዚህ በመነሳት ተመራማሪዎቹ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ገጽታዎችን አንድ ባንድ ለመተንተንና ዝርዝር የፖለቲካ ጥናት ለማካሄድ ይችላሉ ።[2]

ፖለቲካን የበለጠ ለመረዳት የፖለቲካ ግንኙነትን እንደአንዱ የኅብረተሰብ ሥርዓት ማለትም ይህን ግንኙነት በፖለቲካ ሥርዓትነት መልኩ ለመመርመር ፣ የኅብረተሰብን ፣ የሥርዓትን ፣ የኅብረተሰብ ሥርዓትንና የፖለቲካ ሥርዓትን ምንነት መገንዘብ አስፈላጊ ነው ።

ኅብረተሰብ— ኅብረተሰብ የተለያዩ ፍቺዎች አሉት ።[3] ከእነዚህ ውስጥ ሦስቱ የሚከተሉት ናቸው ። 1ኛ/ ኅብረተሰብ ማለት የአንድን ማኅበራዊ ቡድን ቅንብር፣ አሠራሩን ፣ ዕድገቱን ፣ አስተሳሰቡን፣ ፍላጎቱን ፣ የአባላቱን መስተጋብር ጥምር የሚያመለክት ነው ። በዚህ መሠረት በአንድ መንግሥት ሥር የሚተዳደረውን ሕዝብ ወይም የአንድ ከተማ ወይም ቀበሌ ነዋሪዎችን ኅብረተሰብ በማለት ለመሰየም ይቻላል ። 2ኛ/ ሌላው የኅብረተሰብ ፍቺ የሰው ጅል በደረሰበት የእድገት ደረጃ ፣ ባለበት የኤኮኖሚ ግንኙነት ዓይነት ፣ ወይንም በሌሎች አንፃር ሳይከፋፈል በዓለም ያሉ ሰብዓዊ ፍጡራንን በአጠቃላይ የሚያመለክት ነው ። ለምሣሌ ፣ ኢምፔሪያሊዝም የዓለምን ኅብረተሰብ ሕልውና አደጋ ላይ እየጣለ ነው ፤ የኒኩሊየር ጦር መሣሪያ ክምችት በዓለም ኅብረተሰብ ላይ የእልቂት አደጋ እንዲያንዣብብ አድርጓል እየተባለ ሲነገር ኅብረተሰብ የሚለውን ቃል በዚህ ፍቺ በመጠቀም ነው። 3ኛ/ በመጨረሻም ኅብረተሰብ ማለት አንድን የኅብረተሰብ ዓይነት ብቻ በመሠረታዊ ባሕርይ/ በስልተምርት ላይ ተመሥርቶ/ ነጥሎ የሚያመለክት ነው። ኅብረተሰብ ይህን ትርጉም ሲይዝ የጋርዮሽ ፣ የባሪያ አሳዳሪ ፣ የፊውዳል ፣ የካፒታሊስት ፣ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ እየተባለ ይነገራል ።

ሥርዓት፡—ይህ ጽንሰሃሳብ ከሚይዛቸው ትርጉሞች አንዱ የአጠናን ዘዴ ነው ። ፖለቲካን የተለያዩ የአጠናን ዘዴዎችን በመጠቀም መመርመርና ማጥናት ይቻላል። ከነዚህ ዘዴዎች መካከል የምክንያተ ንድፈሀሳብ (Factor theory) ንጽጽራዊ የጥናት ዘዴ (Comparative analysis) ፣ የሥርዓት ዘዴ (System approach) ፣ ይገኙበታል ። በምክንያተ ንድፈሀሳብ አንፃር ፖለቲካን የማጥናት ዘዴ ልዩ ልዩ ነገሮችና ክስተቶች /ባህል ፣ ኤኮኖሚ ፣ የአመራር ችሎታ ፣ ስነምግባር ፣ ሃይማኖት ፣ የምርት ኃይሎችና የቴክኖሎጂ የእድገት ደረጃ ፣ የመልክአ ምድር አቀማመጥና የመሳሰሉት/ በፖለቲካ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ይመረምራል ። ንጽጽራዊ የጥናት ዘዴ ግንኙነት ያላቸው የፖለቲካ አካሎች /ለምሳሌ ፣ የተለያዩ የኮሚኒስት ፓርቲዎችን ፣ የሶሻሊስት መንግሥታትን ፣ በታዳጊ ሀገሮች ያሉ መንግሥታትን/ ወይንም ተቃራኒ የሆኑ የፖለቲካ አካሎችን /ለምሳሌ የሶሻሊስትና የካፒታሊስት መንግሥታትን አሠራር/ በማነፃፀር የጋራና የልዩነት ባህሪዎችን በማሳየት ጥምር ፖለቲካን ይመረምራል ።[4] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በአብዛኛው የምንጠቀምበት የአጠናን ዘዴ የሥርዓት ዘዴ ሲሆን፣ ይኸ ዘዴ የፖለቲካ ሥርዓትን ልዩ ባህሪያት መለየትን ፣ የሥርዓቱን የተለያዩ ዘርፎች መተንተን ፣ የርስ በርስ ግንኙነታቸውንና የሚያካሂዱትን ተግባር መመርመርን ያጠቃልላል ።[5]

Digitized by Google

ሥርዓት የሚለው ጽንሰሐሳብ ከአጠናን ዘዴነቱ በተጨማሪ ሌላ ትርጉም አለው። ይህ ጽንሰሐሳብ አንድ የጥናት መስከን ይመለከታል።[6] በዚህ ፍቺ መሠረት ሥርዓት የሚለው ጽንሰሐሳብ የተለያዩ ማኅበራዊና የተፈጥሮአዊ ክስተቶችን ባህርያት ለማብራራት ያገለግላል። ቀለልባለ አገላለጽ በዚህ ትርጉሙ ሥርዓት ማለት እርስ በርሳቸው የተወሳሰቡና የተዛመዱ የአንድን ክስተት ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን የሚያመለክት ነው። እነሱም «አንደኛ፣ ውስብስብ የሆኑ የርስበርስ ግንኙነት ያላቸው ነገሮችን፣ ሁለተኛ፣ እነኚህን ነገሮች አንድ ውጤት ለማምጣት በጋራ የሚሠሩ መሆናቸውን»[7] ነው።

የኅብረተሰብ ሥርዓት፣ ይህ ጽንሰ ሐሳብ «አንደኛ የማኅበራዊ ክስተትን መዋቅር፣ የአካላቱንና የነኚሁኑ አካላት የርስበርስ ግንኙነት ተግባራትና ሚና፣ ሁለተኛ የማኅበራዊ ክስተት አስተዳደግን፣ ተለዋዋጭነትን፣ የማኅበራዊ ለውጥንና የሽግግርን አዝማሚያዎችና አቅጣጫዎች ያመለክታል።»[8]

የኅብረተሰብ ሥርዓት መደቦችን፣ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችን፣ነገዶችን፣ጐሣዎችን፣ ሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶችን፣ መንግሥትን፣ የተለያዩ የአስተሳሰብ ፈርጆችንና የመሳሰሉትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። የአንድ ኅብረተሰብ አካል የሆኑ ሰዎች ወይም እነዚህ ሰዎች የተሰበሰቡባቸው የኅብረተሰብ አካሎች የአባሎቻቸውን ቁሳዊና ኅሊናዊ ፍላጐቶች ለማርካት በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊና በኅሊናዊ መስኮች እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። በዚህም እንቅስቃሴ አንዳንድ የኅብረተሰብ፣ የኑሮ ገጽታዎች /የመደብ ትግሎች፣ የፓርቲዎች መፈጠር፣ የሕዝባዊ አብዮት መቀጣጠል ወይም መክሰም፣ ወዘተ/ ይከሰታሉ። ኅብረተሰብ እነኚህንና የመሳሰሉትን ክስተቶች ያቀፈ አንድ ሥርዓት ነው።

ኅብረተሰብ አንድ ሥርዓት ቢሆንም በውስጡ በያዛቸው የተለያዩ መስኮች አንፃር ለምሳሌ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የኅሊናዊ ሥርዓት በማለት በንዑስ ሥርዓቶች ሊከፈል ይችላል። እነኚህን ንዑስ ሥርዓቶችም እንደገና በየግላቸው እንደ አንድ ሥርዓት በመውሰድ በንዑስ ሥርዓቶች ከፋፍሎ ማጥናት ይቻላል።

የፖለቲካ ሥርዓት—፣ ከማኅበራዊ ሥርዓቶች አንዱ የሆነው የፖለቲካ ሥርዓት ሲባል ፖለቲካዊ የሆኑ ወይንም ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች የርስበርስ ግንኙነት፣ ቅንብር፣ የጋራ አሠራርና ሚናዎችን የሚያጠቃልል ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ እነኚህ መደባዊ ሥልጣንን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ምንነት ይገልፃል።

ፖለቲካ

በመሠረታዊ ባህርይው ፖለቲካ በመደቦች መካከል ያለ የትግል ወይንም የትብብር ግንኙነት ነው። መደቦች ለረጅም ጊዜ ወይንም ለአንድ ወቅት መደባዊ ጥቅማቸው የሚቻቻል ሲሆን ወይንም የሚቻቻል መስሎ ሲታያቸው ትብብራቸው ጥቅም የሚያስገኝላቸው መሆኑን ሲገነዘቡ፣ ወይንም ሲመስላቸው መደባዊ ግንኙነታቸው በአመዛኙ የትብብር ይሆናል። ጥቅማቸው የማይጣጣምና ኅብረትም ሊመሠርቱ የማያስችላቸው ሲሆን መደባዊ ግንኙነታቸው በትግል ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

ሆኖም የመደቦች ግንኙነት ሁሉ ፖለቲካ ነው ለማለት አይቻልም። ፖለቲካዊ ያልሆነ የመደቦች የእርስበርስ ግንኙነት፣ ለምሳሌ የኢኮኖሚ ግንኙነት አለ። ጭቁን አርሶአደሮች በፊውዳል የሁዳድ እርሻ ላይ በማረስ ወይንም በመቆፈር፣ ለፊውዳሉ ሲሶ በማፍሰስ፣ እርቦ በመስፈር፣ የፊውዳሉን እጥር በማጠርና የመሳሰሉትን ተግባራት በማካሄድ ከፊውዳሉ

Digitized by Google

ጋር የሚፈጥሩት ግንኙነት የኢኮኖሚ ግንኙነት ነው ። እነኝህ ገበሬዎች መበዝበዝና መገበር አንገፍገኗቸው በፊውዳሉ መደብ ላይ እድመው ለመደቡ አናገለግልም ፣ ምርታችንን አንሰጥም በማለት ቢያምጹ ወይንም ከዚህ ከፍ ብለው በፊውዳሉ መደብ ላይ ጦርነት ቢያካሂዱ ጥያቄያቸውና ትግላቸው ፖለቲካዊ ይሆናል ። በሌላ አነጋገር የገበሬዎች እንቅስቃሴ መሠረታዊ ጥቅማቸውን የማስከበርን ከፊውዳሉ መደብ ጭቆናና ብዝበዛ ነፃ የመሆን ጥያቄን ያነሳና ለተግባራዊነቱም የታገለ በመሆኑ ፖለቲካ ነው። ገበሬው በመደብነቱ ኑሯውን ለይቶ በፊውዳሉ መደብ ላይ የሚያካሂደው የነፃነት ትግል ሁሉ የፖለቲካ ትግል ነው ።

ወዝአደሮች በአንድ ፋብሪካ ወይንም በአንድ ሀገር ውስጥ ጉልበታቸውን ለካፒታሊስቶች በመሸጣቸው የሚፈጠረው ግንኙነት ወይንም ወዝአደሮች ካፒታሊስቱ ደመወዝ እንዲጨምርላቸው ፣ የኑሮ ሁኔታ እንዲያሻሽልላቸው ፣ የሚያቀርቡት ጥያቄ የኢኮኖሚ ጥያቄ ነው ። ወዝአደሮቹ እነኝህን ጥያቄዎች በማንሳት ቢያምጹ ፣ ትግል ቢያካሂዱ አመጻቸውና ትግላቸው ኢኮኖሚያዊ እንጂ ፖለቲካዊ አይደለም ። ምክንያቱም የወዝአደሮች ትግል መሠረታዊ የነፃነት ጥያቄዎችን ማለትም ከካፒታሊስቱ መደብ በአጠቃላይ ነፃ የሚያደርጋቸውን ጥያቄ የሚመለከት አይደለምና ። እነኝህ ወዝአደሮች በካፒታሊስቱ መደብ ይዞታ ሥር የሆኑ ፋብሪካዎች እንዲወረሱ ፣ የምርት መገልገያዎች በማኅበራዊ ይዞታ ሥር እንዲሆኑና ካፒታሊስቶች ሥልጣናቸውን እንዲለቁ ወይንም ከሥልጣን እንዲወርዱ የሚያቀርቡት ጥያቄ ግን ፖለቲካዊ ነው ።

ከዚህ በላይ የፖለቲካ ግንኙነት ማለት የተለያዩ መደቦች መሠረታዊና መደባዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር በማሰብ የሚፈጥሩት ወይንም የሚኖራቸው የእርስ በርስ ግንኙነት መሆኑ ተመልክቷል ። ነገር ግን የፖለቲካ ግንኙነት ከመደቦች የእርስ በርስ ግንኙነት እድማስ የሰፋ ነው ።'

ፖለቲካ በመሠረቱ የመደቦች የእርስ በርስ ግንኙነት ቢሆንም የመንግሥታትና የመንግሥት አካላት (መዋቅር) የእርስ በርስ ግንኙነቶች ፣ የብሔሮች ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግንኙነቶችም የፖለቲካ ግንኙነቶች ናቸው ። ሕዝቦች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ ፣ የተለያዩ ፓርቲዎች ለቆሙለት መደብ የሚያወጡት ፕሮግራምና ደንብ ፣ የሚከተሉት ስትራቴጂና ታክቲክ፣ ለዓላማቸው ተፈጻሚነት የሚያደርጉት እንቅስቃሴም ፖለቲካዊ ነው ። ለምሳሌ አብዮታዊት ኢትዮጵያ የምትከተለውን የውጭ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ከተለያዩ መንግሥታት ፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎችና ከአርነት እንቅስቃሴዎች ጋር ያላትና የሚኖራት ግንኙነት ፖለቲካዊ ነው። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በየፈርጁ እየተደራጀ (ለምሳሌ ፣ በሠራተኛ ፣ በገበሬ፣ በሴቶች በወጣቶች ማኅበራት) የነፃነትና የመብት እድማሱን ለማስፋት የሚያካሂደው ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ፀረ ፊውዳልና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ትግል ፖለቲካዊ ነው ።

ፖለቲካ ከመደቦች የቀጥታ የእርስ በርስ ግንኙነት ባሻገር የሚያቅፋቸው የማኅበራዊ ግንኙነት ዓይነቶች ፣ ቅርጽና ደረጃ ፣ በግንኙነቱ ውስጥ የተሳታፊዎች ብዛት ፣ ለግንኙነቱ መንስኤ የሚሆኑት ጉዳዮች እጅግ የበዙና ውስብስብ ናቸው ። የፖለቲካ ግንኙነት ምን ያህል የሰፋና ውስብስብ ቢሆንም ከሌሎቹ የማኅበራዊ ግንኙነቶች (ለምሳሌ ከኢኮኖሚ ግንኙነት) የሚለይ ነው ። ይህ መለያ ፣ ይህ ፍሬ ነገር ወይንም ጽንሰ ሐሳብ ምንድን ነው ?

የፖለቲካን ምንነት ለመግለጽ መንደርደሪያ ሐሳብ ከሆኑት አንዱ ፖለቲካ መሠረታዊ የመደብ ጥቅምን ለማስከበር በሚደረግ እንቅስቃሴ አንጻር የመደቦች የእርስ በርስ ግንኙነት መሆኑን ማመልከት ነበር ። የመደቦችን መሠረታዊ ጥቅም የማስከበር ጥያቄ ደግሞ ዞር ዞር ወደ መንግሥት ሥልጣን

Digitized by Google

ጥያቄ ማለትም የመንግሥት ሥልጣንን
በቁጥጥር ሥር የማድረግን ጉዳይ የግዴታ
የሚያስነሳ ነው ። የፖለቲካም ፍሬ ሐሳብ፣
የፖለቲካ ዓይነተኛ መለያ ወይንም እምብ
ርት ጥያቄ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ
ነው ። ፖለቲካ የተለያዩ የግንኙነት ቅርጾ
ችና ዓይነቶች የሚይዝ ቢሆንም ከሌሎቹ
ማኅበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ የሚለየው በቀ
ጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከመንግሥት ሥል
ጣን ጥያቄ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው ።

ማኅበራዊ ቡድኖችና እነኚህ ቡድኖችን
ያቀፉ ድርጅቶች ሁሉ (መንግሥት ፣ የመ
ንግሥት አካላት ፣ ፓርቲዎች ፣ መደቦች ፣
ጊዜያዊም ሆኑ ቋሚ ቡድኖች ፣ ወዘተ)
የሚያደርጉት የእርስ በርስ ግንኙነትና የሚ
ያነሱት ጥያቄ ፖለቲካ ነው ሊባል የሚች
ለው ግንኙነቱ ወይንም ጥያቄው ሥልጣነ
መንግሥትን ለመያዝና ፣ ለመጠበቅ የሚ
ያስችል ፣ ወይንም ለመያዝ አመች ሁኔታ
የሚፈጥር ወይንም ሥልጣንን ተግባራዊ የ
ሚያደርግ ሲሆን ነው ። ፍዩዶር ቡርላትስኪ
የሚባለው የሶቭየት ኅብረት የፖለቲካ ሳይ
ንቲስት ይህን አስመልክቶ ሲጽፍ እንደሚ
ከተለው ብሏል ፦

በመደባዊ ክስተትነቱ የፖለቲካ ሰጠቃ
ላይ መለያ ፖለቲካ ከሥልጣንና ሥልጣ
ንን ተግባራዊ ከማድረግ እንቅስቃሴ ጋር
በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ ግንኙነት
ያለው መሆኑ ነው ። እንደሚመስለኝ ይ
ህን መሠረት በማድረግ ብቻ ነው ፖለቲ
ካንና የፖለቲካ ግንኙነቶችን ከጠቀላ
ላው የማኅበራዊ ግንኙነቶች መለየት
የሚቻለው ።[10]

በ1981 የሶቭየት ኅብረት የፖለቲካ
ሳይንቲስቶች ማኅበር ያካሔደው ስብሰባ
ለፖለቲካ ከሰጠው ፍቺም የፖለቲካን ምን
ነት ለመግለጽ ሥልጣን የሚለው ጽንሰ ሐ
ሳብ ቁልፍ መሆኑን ለመገንዘብ የሚያዳ
ግት አይደለም ። ስብሰባው የፖለቲካን
ምንነት ለመግለጽ መንደርደሪያ ያደረ
ገው ሐሳብ ፦ « ፖለቲካ የመንግሥት
ሥልጣንን ከመያዝ ፣ ከማደራጀትና ከመ
ምራት ጋር በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ
የተገናኘ በመደቦች ፣ በብሔሮችና በሌ
ሎች ማኅበራዊ ቡድኖች መካከል የሚደ
ረጉ ግንኙነቶች ቅርጽ ነው »[11] የሚል
ነበር ።

ቪ. አይ. ሌኒን ፖለቲካ «መደቦችና የኅ
ብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ከመንግሥትና ከአ
ስተዳደር ጋር የሚኖራቸው የግንኙነት መስ
ክ፣ በሁሉም መደቦች መካከል ያለው የእርስ
በርስ ግንኙነት መገለጫ ነው» ብሏል ።[12]
ፊዮዶር ቡርላትስኪ ይህንን የሌኒን በኩ
ረሐሳብ በማብራራት ሲገልጽ ፣ «ስለሆነም
የፖለቲካ እንቅስቃሴ በተቀዳሚ የፖለቲካ
ሥልጣንና የአስተዳደር ጉዳዮችን የሚያጠ
ቃልል የመደቦች የእርስ በርስ ግንኙነት መ
ስክ ነው» በማለት ጽፏል ። የፖለቲካ እን
ቅስቃሴ እምብርት የሆነው ሥልጣን ምን
ድን ነው ? መሠረቱስ ? የሥልጣን መገሪ
ያዎች ምንድን ናቸው ?

ሥልጣን

በተለምዶ አነጋገርም ሆነ በንድፈ ሐሳብ
ትንተና ውስጥ ሥልጣን (power) የሚለው
ቃል የተለያዩ ፍቺዎች አሉት ። ለም
ሳሌ ፣ እከሌ ሥልጣኑን መከታ አድርጎ
ሀብት በዘበዘ ፤ እከሌ ስለዚህ ጉዳይ ለመ
ከታተል ሥልጣን አለው ፤ የእከሌ የኅብ
ረት ሥራ ማኅበር በዚህ ጉዳይ ላይ የማ
ዘዝ ሥልጣን አለው ፤ እየተባለ ሲነገር
ይሰማል ። እነኚህ አነጋገሮች ሥልጣን የሚ
ለው ጽንሰሐሳብ ፍቺ ከችሎታ ጋር የሚመ
ሳሰል መሆኑንና ይህንንም ችሎታ መሠረት
በማድረግ አንድን ነገር ለመቆጣጠር ወይን
ም የሚፈልጉትን ነገር ለማድረግ መቻልን
ያመለክታሉ ። ማርክስና ኤንግልስም ሥል
ጣን የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ በማኅበራዊ
ግንኙነት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ሰው ከተፈ
ጥሮ ጋር በሚኖረው ግንኙነት አንጻር (ለ
ምሳሌ ፣ ሰው በሥልጣኔ እየገፋ ሲሔድ በ
ተፈጥሮ ወይንም በአካባቢው ላይ የሚና
ረው ሥልጣን (ቁጥጥር) እየሰፋ የሚሔድ
መሆኑን ለመግለጽ) ተጠቅመውበታል[13]

በፖለቲካ ፍልስፍና የንድፈ ሐሳብ ትን
ተና ውስጥ ሥልጣን የሚለው ቃል የሚ

Digitized by Google

ይዘው ፍቺ በማኅበራዊና በመደባዊ መል
ኩ የሚኖረውን ትርጉም ነው ። በዚህ አን
ጻር «ሥልጣን ማለት በማኅበራዊ ሕይወት
ውስጥ አስፈላጊ ከሆነ ሌሎችን በማስገደድ
ጭምር የራስን ፍላጐት ተግባራዊ ማድረግ
ነው» ። [14] የአጠቃላይ የማኅበራዊ ሥልጣን
አካልና ከሥልጣን ከፍተኛ መገለጫዎች
አንዱ የሆነው የፖለቲካ ሥልጣን ማለት
«አንድ መደብ፣ ቡድን ወይንም ግለሰብ በፖ
ለቲካና በሕግ ደንቦች ውስጥ የሚገለጹ
ፍላጐቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚኖረው
ተጨባጭ ችሎታ ነው ።» [15]

ሥልጣን ወይንም በተራ አነጋገር በማ
ኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ግለሰቡን ወይንም
የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አንድን
ጉዳይ እንዲፈጽሙ ፣ ወይንም ከመፈጸም
እንዲቆጠቡ የማስገደድ ጉዳይ ከፖለቲካ
ሕልውና በፊት ፣ ፖለቲካ በኅብረተሰብ ታ
ሪክ ውስጥ ከመከሰቱ በፊት የነበረና
ከፖለቲካ ውጭም ሊኖር የሚችል የማኅበ
ራዊ ግንኙነት ገጽታ ነው ። ለምሳሌ ሌኒን
«የማስገደድ ሥልጣን በማንኛውም ኅብረ
ተሰብ ውስጥ ያለ ነው ፤ በጋርዮሽ ኅብ
ረተሰብ ውስጥና በጥንቱ ሰፊ የቤተሰብ ግን
ኙነትም ውስጥ ነበር» [16] በማለት ጽፏል ።
ይሁን እንጂ በፖለቲካ ውስጥ የሥልጣን
ፍቺ የተለየ ነው ።

እላይ ከተጠቀሰው የሥልጣን ፍቺም ሆኑ
በቀን ተቀን የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ከሚታ
የው ማኅበራዊ እንቅስቃሴ መገንዘብ እንደ
ሚቻለው በፖለቲካ ውስጥ ሥልጣን ሲባል
በመሠረቱ የመደብ ጥቅምን ከማስከበርና
ከመደቦች ግንኙነት ጋር የተያያዘ ነው።ይህ
ጽንሰ ሐሳብ የፖለቲካ ግንዛቤና የፖለቲካ
ንድፈ ሐሳብ ዋናው ቁም ነገር ነው ።
«የሥልጣን መደባዊ ገጽታ የፖለቲካ አመ
ለካከታችን እምብርት ነው ።» [17]

በፖለቲካ ግንዛቤ ሥልጣን የሚለው ጽ
ንሰ ሐሳብ ከመደባዊ ገጽታው በተጨማሪ
«አንደኛ ፣ ከፖለቲካ ሥርዓት ጋር የተያያዘ
ነው ፤ ሁለተኛ ፣ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍ
ሎችና በግለሰቦች መካከል የጠቃሚ ነገር
ችን (Goods) ስርጭት በሚመለከት ለኅብ
ረተሰቡ በአጠቃላይ አስገዳጅ የሆኑ ውሳኔ
ዎችን የማውጣት ነፃነትና ችሎታ ነው» ።[18]
የፖለቲካ ሥርዓት የሚባለው የመንግሥት
አካላትን ፣ ፓርቲያዎችን ፣ የተለያዩ ማኅበ
ራዊ ቡድኖችን ለምሳሌ ፣ የመደቦችና የህ
ብረተሰብ ልዩ ልዩ ክፍሎችን ሕዝባዊና
የሙያ ማኅበራትን ፣ የፖለቲካ አስተሳሰብ
ንና የመሳሰሉትን የሚያቅፍ ነው ።

<u>የሥልጣን መሣሪያዎች</u> ፣ የፖለቲካ ሥል
ጣን ዘላቂና መሠረታዊ ምንጩ የምርት
መገልገያዎች ባለቤትነት ነው ። በማንኛ
ውም ኅብረተሰብ ውስጥ አንዱ መደብ
በሌላው መደብ ላይ የፖለቲካ የበላይነ
ቱን ሊጨብጥ ወይንም ሊያሰፍን የሚ
ችለው ይህ መደብ የምርት መገልገያች
(የመሬት ፣ የፋብሪካዎች ፣ የባንኮች ፣ የአገ
ልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ፣ ወዘተ) ባለ
ቤት ሲሆን ነው ። የፊውዳሉ መደብ
በጭሰኞቹ ወይንም በገባሮቹ ላይ የሚኖ
ረው ሥልጣን ምንጩ ይህ መደብ ያለው
የመሬት ባለቤትነት ነው ። የፊውዳሉ
መደብ አባላት የያዙት መሬት ሲወሰድባ
ቸው በአርሶ አደሮቹ ላይ የሚኖራቸው የፖ
ለቲካ ሥልጣን አብሮ ያከትማል ።

ታላላቅ የካፒታሊስት ሞኖፖሊስቶች
ባላቸው ከፍተኛ የግል ሀብት በመጠቀም
የመንግሥታቸው ፖሊሲ በፈለጉት መን
ገድ እንዲቀየስ በተለያዩ ዘዴዎች ተጽዕኖ
ያደርጋሉ ። ጥቅማቸውን የሚያስከብሩላ
ቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖች (ፕሬዚዳ
ንቶች ጭምር) በመንግሥት አመራር ውስ
ጥ ቁልፍ የሥልጣን ቦታ እንዲይዙና የሞ
ኖፖሊስቶችን ጥቅም የሚያስከብሩ እርም
ጃዎች እንዲወስዱ፣ በገንዘብ አስተዋጽኦና
በሌሎችም ዘዴዎች ይደግፏቸዋል ፤ አይጠ
ቅሙንም የሚሏቸውን ባለሥልጣናችንም
ከሥልጣን እንዲባረሩ ተጽዕኖ ያደርጋሉ ።
በእነዚህና በሌሎችም ዘዴዎች ሞኖፖሊስ
ቶች የመንግሥት ፖሊሲ በሚፈልጉት አቅ

Digitized by Google

ጣሚ እንዲቀየስ በማድረግ መደባዊ ፍላጐታቸውን ያረካሉ ፤ ወይንም ለማርካት ይጥራሉ ። ተበዝባዥ ሕዝቦችም ቢሆኑ ቁልፍ የኤኮኖሚ ዘርፎችን በይዞታቸው ሥር ካላደረጉና ካልተቆጣጠሩ የፖለቲካ ሥልጣን በዘላቂነት ሊይዙና መደባዊ ጥቅማቸውን ሊያስከብሩ አይችሉም ።

የፖለቲካ ሥልጣን መሠረታዊና ዘላቂ ምንጭ (መሣሪያ) የምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ቢሆንም ሌሎች የሥልጣን መሣሪያዎችም አሉ ። ከኤኮኖሚ ይዞታ በተጨማሪ ለአንድ መደብ የፖለቲካ ሥልጣን መሣሪያዎች ከሚሆኑት ነገሮች መካከል አንደኛ ፣ የመንግሥት ልዩ ልዩ አካላት (የጦር ኃይል ፣ ፖሊሲ ፣ ብሔራዊ ሸንጐ ፣ እሥር ቤት ፣ ወዘተ) ፤ ሁለተኛ ፣ በዜጐች (ቢያንስ በአብዛኛዎቹ) አዕምሮ ወይንም አስተሳሰብ ተደጋፊ መሆን ይገኙበታል ።[19] የገዥ መደቦች ሥልጣነ መንግሥት ይዘው የመደብ ጥቅማቸውን ለማስከበር የቻሉት በእነኝህ ልዩ ልዩ የሥልጣን መሣሪያዎች ጥምር በመጠቀም ነው ።

ጆርጊ አርባቶቭ የተባለው የሶቭየት ኅብረት ምሁር ይኸንኑ አስመልክቶ ሲጽፍ ፤

ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ለዘመናት ተጨቁኖ ተዋርዶና መብቱ ተገፎ ኖሯል ፣ ምክንያቱም ለአያሌ ምዕተ ዓመታት በኅብረተሰብ ውስጥ ሥልጣን የያዘው ይህ ሕዝብ ሳይሆን የበዝባዥ ክፍል በመሆኑ ነው ። ሥልጣኑ ሊጠበቅ የቻለው በኢኮኖሚ ፣ በአስተሳሰብ ወይንም በርዕዮተዓለም የበላይነት እና በመጨረሻም ምን ጊዜም ቢሆን የመንግሥት ሥልጣን መሰረት በሆነው በኃይል ፣ በግልጽ ለመናገር ፣ በታጠቀ ኃይል ለማካይነት ነው ብሏል ።[20]

በመደባዊ አቋሙ ምክንያት ጠቅላላውን ምዝብር ሕዝብ ነፃ የማውጣት ተልዕኮ የአለው የሠራተኛው መደብ የሚመሠረተው ሥልጣነ መንግሥትም በመንግሥት ኃይልና በሕዝባዊ ድጋፍ ጥምር የሚጠናከር ነው ። በእርግጥ የወዝአደሩ መደብና የበዝባዥ መደቦች የሥልጣን ባህርይ ይለያያል። የሠራተኛው መደብ ሥልጣንን የሚጠቀምበት እራሱንና ሌሎችን ሠርቶ አደሮችን ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ ለማውጣት ነው ። ይህ መደብ የቆመለት የሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ ሥር እየሰደደና እየተስፋፋ ሲሔድ የሠራተኛው መደብ የሥልጣን አጠቃቀምም ኅብረተሰቡን በማግባባትና በማሳተፍ ላይ የተመሠረተ ይሆናል ።

የሠራተኛው መደብ በሥልጣን ለመቆየትና የቆመለትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የመላ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ የአስተሳሰብ ድጋፍ የግዴታ ማግኘት አለበት ። ለዚህም ሕዝቡን ያነቃል ፤ ያደራጃል ፤ ያስታጥቃል። ሰፊው ሕዝብም ከሠራተኛው መደብ ጐን ይቆማል ፤ አመራሩንም ይቀበላል ።

የፖለቲካ ሥርዓት

ከዚህ በላይ ፖለቲካ የማኅበራዊ ግንኙነቶች አንዱ አካል መሆኑን ፣ ከእነዚህም ግንኙነቶች የሚለይበት ዋናው ምክንያት ከመደባዊ ሥልጣን ጋር በመያያዙ መሆኑን የፖለቲካ ሥልጣንም ዓይነተኛ ባሕርይ ምን እንደሆነ ለማመልከት ተሞክሯል። ፖለቲካን ከሌሎች የማኅበራዊ ግንኙነቶች የሚለይበትን ባሕርያት ማመልከት ብቻ የፖለቲካ ምንነትን ለመግለጽ በቂ አይደለም ። ፖለቲካ ከማኅበራዊ ግንኙነት ክፍሎች መካከል አንዱ ነው ከተባለ (ነውም) የዚህ ግንኙነት ይዘት ምንድን ነው ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል ።

ፖለቲካ የመደቦች ትግል አንድነትን የመጠናከርንና የመዳከምን ፣ የመከሰትን፣ የመክሰምንና ሌሎችም ተቃራኒ አዝማሚያዎችን የያዘ ነው። በመሆኑም የፖለቲካን ይዘት የበለጠ መረዳት ማለት የእነዚህን የማኅበራዊ ግንኙነቶች አካሎች፣ባሕርያት ተግባራቸውን ፣ ውስጣዊ ቅራኔያቸውንና አንድነታቸውን ወዘተ ---መረዳትን የሚያጠቃልል መሆን አለበት ። የፖለቲካን ይዘት በበለጠ ለመረዳትና ለመተንተን ከሚስያችሉት ዘዴዎች አንዱ ፖለቲካን ከኅብ

Digitized by Google

ረተሰብ ሥርዓቶች ከፍልነቱ አንጻር ግተናት መሆኑ ከላይ ተጠቅሷል ።

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ እንደተጠቀሰው ከኅብረተሰብ ግኅበራዊ ሥርዓቶች አንዱ የሆነው የፖለቲካ ሥርዓት ማለት ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር ግንኙነት ያላቸውን ክፍሎች (ዘርፎች) የእርስ በርስ ግንኙነት፣ ቅንብር ፣ የጋራ አሠራርና ሒናዎችን የሚያጠቃልል ነው። ፊዩዶር ቡርላትስኪ ለፖለቲካ ሥርዓት የሰጠው ፍቺ የሚከተለው ነው ።

> የፖለቲካ ሥርዓት ማለት… የዚህ (የፖለቲካ) ሥርዓት ተቋሞች ድምር (ጥርቅም) ማለት አይደለም። የፖለቲካ ሥርዓት አስገዳጅ ውሳኔዎችን የሚሰጥና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያገለግል የመደቦች ፣ የማኅበራዊ ኃይላት ፣የቡድኖችና የአካላት ፣ ለምሳሌ የመንግሥትና የፓርቲ አካላት የእርስ በርስ ቅንብር ነው።እዚህ ላይ አስገዳጅ ውሳኔዎች ስንል በኃይል ወይንም በማግባባት ወይንም በሌሎች ተጽዕኖ የማድረጊያ ዘደዎችን በመጠቀም ተግባራዊ የሚሆኑና አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍልም አስገዳጅ መሆናቸውን የሚገነዘባቸው ውሳኔዎች ናቸው ። እነኝህ ውሳኔዎች የግድታ በሕግ የተደነገጉ ላይሆኑ ይችላሉ ።[21]

ይህ ለፖለቲካ ሥርዓት የተሰጠ ፍቺ በሌላ አገላለጽ ቢቀርብ ፣ አንደኛ ፣ የሥርዓቱ አካሎች መደቦች ፣ ማኅበራዊ ኃይላት ፣ ቡድኖችና ሌሎችም ማኅበራዊ አካሎች ለምሳሌ የፖለቲካ ፓርቲ አካሎች (የፓርቲ ጉባኤ ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፣ ወዘተ) ፣ የመንግሥት አካሎች (የጦር ኃይል ፣ ፖሊሲ ፣ ፍርድ ቤት ወህኒ ቤቶች ፣ ወዘተ) እና የተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች መሆናቸው ፣ ሁለተኛ ፣ የፖለቲካ ሥርዓት የእነኚህ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ቡድኖችና ተቋሞች ድምር ወይንም ስብስብ ሳይሆን የተወሳሰበ የእርስ በርስ ግንኙነታቸው ቅንብር መሆኑን ፣ ሦስተኛ ፣ የፖለቲካ አካሎች መዋቅራዊ ይዘት ተግባራት በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ አስገዳጅ ውሳኔዎችን ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ መሆኑን ፣ አራተኛ ፣ የፖለቲካ ሥርዓት አካሎች የሚያወጧቸው ውሳኔዎች በተለያዩ ዘዴዎች (አላይ እንደተጠቀሰው በመንግሥትና በኢኮኖሚ ኃይል ፣ በሐሳብ ተቀባይነት በማግኘት ጭምር) ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉና . የኅብረተሰቡም አብዛኛው ክፍል አስገዳጅነታቸውን የሚቀበለው መሆኑን ይገልጻል ። የፖለቲካ ሥርዓት ዋና ዋና ዘርፎች ፣ ባሕርያትና ዓቢይ ተግባራት ምንድን ናቸው ?

የፖለቲካ ሥርዓት ዘርፎች

ባለንበት ዘመን ያሉ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ቡድኖችና እነኝህ ማኅበራዊ ቡድኖች የሚያከናውኗቸው ተግባራትና የሚያራምዷቸው የአስተሳሰብ ዓይነቶች ከፖለቲካ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ናቸው ። የተለያዩ የማኅበረሰብ እንቅስቃሴዎች እንደሁኔታው መሠረታዊ የመደብ ጥቅምንና የሥልጣን ጥያቄን የሚያነሱበት ጊዜ አለ ። አንዳንድ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች በተለይም «በሰላም» ወቅት ከመደብ ጥቅሞች መከበር ጋር በቀጥታ ያልተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ ። ነገር ግን አጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው ከፖለቲካ ጋር እንዳችም ግንኙነት የለውም ወይንም ምንም ዓይነት መደባዊ ባሕርይ አያሳይም ለማለት አይቻልም ።

በኢትዮጵያ ያሉ የዕድር ማኅበራትን በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል ። እነኝህ ማኅበራት በአመዛኙ የሚያተኩሩት በማኅበራዊ አገልግሎት (ሀዘንተኛን በማስተዛዘን ፣ የዕዝን በማቅረብ ፣ እንግዶችን በማስተናገድ ፣ ለቀብር ሥነ ሥርዓት የሚያስፈልጉ ነገሮች በማሟላትና በመሳሰሉት) ላይ ነው ። ውስጣዊ አሠራራቸውም በተጻፉ ወይንም በተዘረዘሩት የዕድር መተዳደሪያ ደንቦች ብቻ ሳይሆን በምግባረ ግዕዛንም ጭምር (ለምሳሌ ፣ እነከሴ ምን ይሉኛል ፣ ጐረቤት ምንይለኛል በሚል ፍራቻ ብቻና ይህን ሳያደርግ ቢቀር መጥፎ ድርጊት እንደሆነ በመቁጠር በዕድሩ ውስጥ ግዳጅን መፈጸም) የሚመራ ነው። ማኅበራቱ ከዚህ እንቅስቃሴያቸው አንጻር

Digitized by Google

ሲታዩ የፖለቲካ ባሕሪይ አላቸው ለማለት የሚቻል አይመስልም ። ነገር ግን ዕድሮቹ አንዳንድ የመንግሥት መመሪያዎችን ለአባላት ቢያሳውቁ ፣ ተግባራዊ ቢያደርጉ ፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ነፃነት መከበር በሚያስችል መንገድ ተግባር ላይ የሚውል ገንዘብ ቢያዋጡ ፣ የፖለቲካ ቅስቀሳ ሥራ ቢያካሂዱ፣ ወዘተ የፖለቲካ ሥራ መሥራታቸው ነው። ለምሳሌ በ1969 የሶማሌ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ያካሄደውን ወረራ ለመከላከል በተካሔደው የትጥቅ ትግል መጠናከር አያሌ የኢትዮጵያ ዕድሮች የድንኳኖችና የሌሎችም የቁሳቁሶች አስተዋጽኦ አድርገዋል ። የዕድሮቹ ቁሳቁስ ወረራውን ለመከላከል ለተሰበሰበው ሕዝባዊ የሚሊሺያ ጦር በመጠለያነትና በመገልገያነት ውለዋል ። በዚህ አንጻር ሲታይ ዕድሮቹ የፖለቲካ ተሳትፎ አድርገዋል ።

በተጨማሪም ፣ ዕድሮች መንግሥት በዘረጋው ማኅበራዊ ፖሊሲ ለምሳሌ ትምህርትን ለማስፋፋት ፣ የጤና ጥበቃ አገልግሎትን ለማዳረስ የወጣውን መንግሥታዊ ዕቅድ በተግባር ለመተርጐም አስተዋጽኦ ቢያደርጉ በፖለቲካ ውስጥ መሳተፋቸው ነው ።

በዓለም አቀፍ ደረጃም በቀጥታ የፖለቲካ ሥራ የማያካሂዱ ነገር ግን ስለሰላም (በኃያላን መንግሥታት መካከል ስላሉ ግንኙነቶች ጭምር) ስለኑክሌር ጦርነት አደገኛነት ፣ የጦር መሣሪያ እሽቅድምድም ስለሚያስከትለውም የገንዘብና የሰው ኃይል ብኩንነት ፣ ወዘተ የሚያስቡና መፍትሔ ነው የሚሉትን የሚያቀርቡ አያሌ ዓለም አቀፋዊ ፣ አህጉራዊ ወይንም ክፍለ አህጉራዊ ድርጅቶች ፣ ንቅናቄዎች ፣ ወዘተ አሉ ። ድርጅቶችም ሆኑ ሌሎች አካሎች ይህን አስተያየት በመስጠታቸው ፖለቲካዊ አቋም መያዛቸውና በፖለቲካ መሳተፋቸው ነው ።

በመሆኑም ላይ ላዩን ሲመለከቷቸው ከፖለቲካ የተገለሉ የሚመስሉ ሌሎች ማኅበራዊ ድርጅቶች ተቋሞችና የሐሳብ ቅንብሮች በአጠቃላይ ሲታዩ (በተለይም ባለንበት ዘመን) ከፖለቲካ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን ።

ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ የኑሮ ገጽታዎች (ነባራዊ ሆነ ኅሊናዊ ክስተቶች) ከፖለቲካ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተገናኙ ከሆነ ፣ የፖለቲካ መስክ የሚያጣቅሳቸው ማኅበራዊ ጉዳዮች ወይም አካሎች በጣም ብዙ ከሆኑ ፣ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ሥርዓት ዘርፎችን ከሌሎች የኅብረተሰብ ሥርዓት ልዩ ልዩ ዘርፎች እንዴትና በምን መስፈርት መለየት ይቻላል? የፖለቲካ ሥርዓት ዘርፎችን ከሌሎች ማኅበራዊ ዘርፎች መለያው ምንድነው ?

ባለንበት ዘመን ከፖለቲካ ጋር የማይገናኝ ፣ የፖለቲካ ጥያቄ (ለምሳሌ የዓለም የሰላም ጥያቄ) ተጽዕኖ የማያሳድርበት አካል፣ ማኅበራዊ ድርጅት፣ ተቋምና ወይንም የአስተሳሰብ ዘርፍ አለ ለማለት ያስቸግራል የሚለው አጠቃላይአ ገላለጽ ሳይዘነጋ ስለፖለቲካ ሥርዓት ዘርፎች ዓይነተኛ ባሕርይ መናገር ይቻላል። የፖለቲካ ሥርዓት ዘርፎች የሚባሉት መደባዊ ሥልጣንን ለመያዝ ወይንም ለመምራት በሚደረግ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸውና ይኸውም ተሳትፎ ከመሠረታዊ ባህርያቸው አንድ የሆኑ የኅብረተሰብ ድርጅቶች፣ ተቋሞችና የአስተሳሰብ ዓይነቶች ናቸው ። ፊዮዶር ቡርላትስኪ የፖለቲካ ሥርዓት ዘርፎችን ከሌሎች የኅብረተሰብ ሥርዓት ዘርፎች መለያን በሚመለከት እንደሚከተለው ጽፏል፤

> በዘመናችን ማኅበረሰቦች ፣ ድርጅቶች ፣ ግለሰቦች በሚያካሂዱዋቸው ተግባራት ውስጥ የፖለቲካ ገጽታዎች አሉ ። ይሁን እንጂ ከፖለቲካና ከሕዝብ አስተዳደር ጋር የጠበቀ መስተጋብር ያላቸውና ይህም ድርጊታቸው መሠረታዊ (essential) ባሕርያቸው የሆ ተቋሞች ናቸው የፖለቲካ ሥርዓት ዘርፎች የሚባሉት ። [22]

ለፖለቲካ ሥርዓት ከተሰጠው ፍቺ አንጻር የፖለቲካ ሥርዓትን (በተለይም የመደብ ትግል በየአቅጣጫው በተፋፋመበት በያዝነው ዘመን) ከተለያየ አቅጣጫ መመል

Digitized by Google

ኩት ይቻላል ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በቀረበው ትንተና የፖለቲካ ሥርዓትን በሦስት ዋና ዋና ዘርፎች ማለትም 1ኛ/ በፖለቲካ ግንኙነት ፣ 2ኛ/ በፖለቲካ አካላት ፣ (Political Organization) 3ኛ/ በፖለቲካ አስተሳሰብ መልክ ተከፋፍለው ቀርበዋል ።

የፖለቲካ ሥርዓት ዘርፎች አከፋፈል ከአንባቢ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል ። ቀደም ሲል እንደቀረበው ፖለቲካ በመደቦች ፣ በመንግሥታት ፣ በብሔሮችና በሌሎችም መሰል የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለ ግንኙነትና የዚህ ግንኙነት ዓይነተኛ ባሕርይም መደባዊ ሥልጣንን ከማደራጀት ፣ ከመያዝና ተግባራዊ ከማድረግ እንቅስቃሴ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተያያዘ መሆኑ ተገልጿል ። በአጭሩ ፖለቲካ የመደቦች ግንኙነት ነው ተብሏል ። ታዲያ ፣ ፖለቲካ ግንኙነት ነው ከተባለ እንዴት የፖለቲካ ሥርዓት አንዱ ዘርፍ የፖለቲካ ግንኙነት ነው ሊባል ይችላል ?

ጉዳዩ ከአቀራረብ ስልት ጋር የተያያዘ ነው። በመጀመሪያ የፖለቲካን ምንነት ለመረዳት መንደርደሪያ የተደረገው አቀራረብ የፖለቲካን ጽንሰ ሐሳብ ፍቺ መግለጽ ነው ። የአንድን ጽንሰ ሐሳብ ፍች መግለጽ ማለት በመጀመሪያ ደረጃ «በመሠረቱ ተገላጩን ጽንሰ ሐሳብ ይበልጥ ውስብስብ ከሆነው ጽንሰ ሐሳብ አካልነቱ አንጻር መረዳት ነው ።»[23] ይህን አገላለጽ መነሻ በማድረግ ፖለቲካ በመደቦች መካከል ያለ ግንኙነት መሆኑንና የመደቦች ግንኙነትም ቢሆን ብዙ ዓይነት ሊሆን ስለሚችል ከዚህ ውስጥ የፖለቲካ ግንኙነት የሚሆነው ከመደባዊ ሥልጣን ጋር የተያያዘው የማኅበራዊ ግንኙነት ብቻ መሆኑ ተገልጿል ። በዚህ አቀራረብ ፖለቲካ በማኅበራዊ ግንኙነት አካልነቱ ምን ዓይነተኛና ልዩ ባሕርይ እንዳለው(ሥልጣን መሆኑ ነው)ስብስብ አድርጐ ለመግለጽ ተሞክሯል።ለዚህ የአቀራረብ ዘዴ ሲባል የፖለቲካ ግንኙነትን በአንድ ወገንነቱ ለማየት እንዲያመች ከፍፍል አልተደረገም። ነገር ግን ጠለቅ ብሎ ፣ የፖለቲካን ምንነት በዝርዝር ለማጥናት ፖለቲካን (ከላይ እንደ ተገለጸው) በሥርዓትነቱ አንጻር መረዳቱ ጠቃሚ ነው ። በዚህ ዘዴ የፖለቲካን ምንነት ለመረዳት እንዲያመች ከላይ እንደተጠቀሰው የፖለቲካ ሥርዓትን በሶስት ዘርፎች(ማለትም የፖለቲካ ግንኙነት ፣ የፖለቲካ አካላት ፣ የፖለቲካ አስተሳሰብ) ከፋፈሎ ለማቅረብ ይሞከራል ።

የፖለቲካ ግንኙነት ፣—የፖለቲካ ሥርዓት አንዱ ዘርፍ የሆነው የፖለቲካ ግንኙነት መሠረቱ የኢኮኖሚው የምርት ግንኙነት ነው ። በመሆኑም የባሪያው አሳዳሪ ፣ የፊውዳል ፣ የካፒታሊስትና የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት የየራሳቸው የፖለቲካ ግንኙነቶች አሏቸው ። እነኝህ ግንኙነቶች በተለያየ የፖለቲካ አካላት መካከል በተለያዩ ቅርጾች ይከሰታሉ ። የብዝበዛ ሥርዓት በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ የመደቦች የርስ በርስ ትግል ፣ በብሔሮች ወይንም በብሔረሰቦች የጨቋኝና የተጨቋኝ ግንኙነት ፣ የሶሻሊስት ሥርዓት በሰፈነበት ሁኔታ በተራማጅ መደቦች ኅብረት ፣ የትግል አንድነት (ለምሳሌ ፣ በወዝአደሩ ፣ በአርሶ አደሩና በሌሎች ሠርቶ አደሮች የትግል አንድነት) ፣ በብሔሮች ወይንም በብሔረሰቦች ወንድማማችነትና የመረዳዳት ግንኙነት ፣ በሶሻሊስትና በካፒታሊስት መንግሥታት መካከል በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲን በመከተልና ባለመከተል መልክ ሊከሰት ይችላል ።[24]

የፖለቲካ ሥርዓት አካላት (Political Organization) የፖለቲካ አካላት መንግሥትን ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ፣ ህዝባዊ ድርጅቶችንና የሙያ ማኅበራትን ያቅፋል ። የፖለቲካ ስርዓት አካላት ከፖለቲካ ግንኙነት መፈጠር ጋር የተከሰቱ ናቸው ።

Digitized by Google

ከፖለቲካ አካላት ሁሉ በቅድሚያ የተከሰተው መንግሥት በወቅቱ የኤኮኖሚ የበላይነት የያዘው መደብ ጥቅሙን ለማስከበር የመሠረተው ተቋም ነው ። የፖለቲካ ፓርቲ በሌላ አገላለጽ የአንድ መደብ የነቁ ክፍሎች ማለትም የመደባቸውን አጠቃላይ ጥቅም የሚገነዘቡና ይህንም ለማስከበር የሚታገሉ አባላት የሚመሠርቱት ድርጅት ሲሆን ተስፋፍቶ የታየውም ከካፒሊታስት ሥርዓት መመሥረት ጋር ነው ። ባለንበት ዘመን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ግንኙነቶችና የዕድገት አቅጣጫዎችን የሚቆጣጠሩ እያሌ የፖለቲካ አካላት ተመስርተዋል ።

የፖለቲካ አካላት ዓይነተኛ ባሕርይ በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ መሠረታዊ የመደብ ጥቅምን ለማስከበር በሚካሔደው ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ መሆን ነው ። በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ የፖለቲካ አካል ማለት «በመደቦች ፣ በብሔሮችና በመንግሥታት መካከል ያሉ ፖለቲካዊ ግንኙነቶችን የሚቆጣጠሩ ተቋሞችና ድርጅቶች ቅንብር ነው።» ለምሳሌ ፣ «በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የፖለቲካ አካል ማለት ሥልጣን ለማግኘት ወይንም ለመያዝ ለዚህኛው ወይም ለዚያኛው መደብ ጥቅሞች መከበር ለመታገል ፣ የሚፈጠሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎችም ሕዝባዊ ድርጅቶች ናቸው ።»[25]

የፖለቲካ አካላት የኅብረተሰብ የላዕላይ መዋቅር ዓይነተኛ ገጽታዎች ናቸው ። የአንድ ኅብረተሰብ መሠረታዊ ፖሊሲዎች የሚነደፉት ፣ ዕቅዶችና ሕጎች የሚደነገጉት ፣ እንዲሁም ለእነኝህ ፖሊሲዎችና ድንጋጌዎች ተግባራዊነት የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች ለማሰባሰብ የሚቻለው በፖለቲካ አካል አማካይነት ነው ።[26]

<u>የፖለቲካ አስተሳሰብ</u> ፣ የተለያዩ ኅብረተሰብ ክፍሎች ፣ መንግሥታት ፣ ፓርቲዎች ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችና መሪዎች ፣ ወዘተ በፖለቲካ ግንኙነቶች ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ አስተሳሰባቸውን የሚያንጸባርቁ የፖለቲካ አቋሞች ፣ መግለጫዎችና ፕሮግራሞች ያወጣሉ ፤ ደንቦችና መርሆዎች ይነደፋሉ ፤ ስለፖለቲካ ግንኙነትና ስለፖለቲካ አካሎች የተወሰነ የአስተሳሰብ ዘይቤና ስሜት ይኖራቸዋል ። ሰዎች በፖለቲካ ውስጥ በሚሳተፉበት ጊዜ (ተሳትፎአቸው በንቃት ላይ ተመሠረተም አልተመሠረተም ፣ ተሳትፎአቸው የሚያስከትለውን ውጤት ተረዱም አልተረዱም) ሆነ ብለው የሚከተሉት የተወሰነ የትግባር መመሪያ ፣ ሥነ ሥርዓትና ፣ በአጠቃላይ ከእንቅስቃሴው ጋር የተያያዘ አስተሳሰብ አላቸው ። ይኸውም የፖለቲካ ሥርዓት አንዱ ዘርፍ የሆነው የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚባለው ነው ። የፖለቲካ አስተሳሰብ የኅብረተሰብ ልዩ ልዩ ክፍሎች ፖለቲካዊ ሕይወት ነጸብራቅ ነው ።

የፖለቲካ አስተሳሰብን በተለያዩ እንፃሮች ለመከፋፈል ይቻለል ። ለምሳሌ ተግባራዊ ለመሆን ከመቻል ወይም ካለመቻል አንጻር ሲታይ ፣ የፖለቲካ አስተሳሰብ እውን ወይንም ተምኔታዊ ሊሆን ይቻላል ። ልዩ ልዩ የፖለቲካ ከስተሳሰብ አራማጆች (የተለያዩ ግለሰቦችም ሆኑ መደቦች) ጭምር እንደየግንዛቤያቸው ደረጃ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ወይንም በስሜትና ምኞት ላይ የተመሠረቱ የፖለታካ አስተሳሰቦች ሊያቀርቡ ወይንም ሊያራምዱ ይችላሉ ።

ከስፋት አንጻር ሲታይ የፖለቲካ አስተሳሰብ 'ግለሰባዊ ፣ ቡድናዊ ፣ መደባዊና ብሔራዊ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ግለሰባዊ የፖሊቲካ አስተሳሰብ የሚገለጽበት አንዱ መልክ በአንድ ዓይነት የህብረተሰብ ሥርዓትና በአንድ ዓይነት ፓርቲ ፣ በአንድ አነስተኛ ቡድን ውስጥ ቢጋራ የፖለቲካ አመራር የሚሰጡ ግለሰቦች በየግላቸው ቡድኑ በያዘው የሥልጣን ቁንጮ ላይ ሲወጡ የሚያሳዩት የየግላቸው የፖለቲካ ሐሳብ (ለምሳሌ የማኅበረሰቡን የአመራር ዘዴ ፣ ቅድሚያ የሚሰጡት ወይንም ይበልጥ የሚያተኩሩበት ማኅበራዊ ጉዳይ) ልዩነት ያሳያል ። ለዚህ ልዩነት የየግለሰቦች የፖለቲካ አስተሳሰብ ወይንም እምነት አስተዋጽኦ አለው ። የአንድ መደ

Digitized by Google

ብ እባል በሆኑ ቡድኖች የሚያራምዱት የፖለቲካ አስተሳሰብ በመሠረቱ ለመደቡ ጥቅም የቆመ በመሆኑ አንድነት ቢኖረውም ልዩነትም ስላለው በአንድ መደብ ውስጥ ባሉ ቡድኖች መካከል የፖለቲካ ሽኩቻ ፥ ውዥንብርና መንታረክም በብዙ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይታያል ።

ከዚህ በላይ የፖለቲካ ሥርዓት የተለያዩ ዘርፎች (የፖለቲካ ግንኙነት ፥ የፖለቲካ አካላትና የፖለቲካ አስተሳሰብ) ምንነትና ባሕርያትን በተናጠል ለመዘርዘር ተሞክሯል ። ከዚህ ቀጥሎ የአጠቃላይ የኅብረተሰብ ሥርዓቶች አንድ ክፍል የሆነው የፖለቲካ ሥርዓት ከሌሎቹ ሥርዓቶች በምን ይለያል ? ዓይነተኛ የሚያደርጉት ባህሪያቱ ምንድን ናቸው ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞከራል ።

የፖለቲካ ሥርዓት ዓይነተኛ ባህርያት

በፈዩዶር ቡርላትስኪ አስተያየት የፖለቲካ ሥርዓት ከሌሎቹ ማኅበራዊ ሥርዓቶች የሚለይባቸው አራት መሠረታዊ ባህርያት አሉት ። [27] ከእነዚህም ባህርያት አንደኛው ፥ ይህ ሥርዓት ከሌሎች ማኅበራዊ ሥርዓቶች ሁሉ የበላይነት ያለው ፥ በሥልጣን የላቀ መሆኑ ነው ። የፖለቲካ ሥርዓት «በኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን አለው ። የሚያወጣቸው ውሳኔዎች ለኅብረተሰቡና ለእያንዳንዱ የኅብረተሰብ ሥርዓቶች አስገዳጆች ናቸው ። የዚህ ሥርዓት ተቀዳሚ ባሕርይ ሥልጣን ነው ።» ለምሳሌ የኢኮኖሚና የኅሊናዊ ሥርዓቶች በኅብረተሰብ ውስጥ ያላቸውን ሚና ብናይ ፥ «የኢኮኖሚ ሥርዓት ከሁሉም በላይ በዕቃዎች ምርትና በአገልግሎቶች አሰጣጥ የሚያተኩር ሲሆን ዓላማውም የኅብረተሰቡን ፍላጐቶች ማርካት ነው ።» የሕሊናዊ ሥርዓትም ተቀዳሚ ተግባር የባሕርይ ገዕዛንንና መልካም አርአያነት በማስፋፋት ግለሰቦች የኅብረተሰቡን ወግና ባህል ተቀብለውና የኅብረተሰቡ ተስማሚ አካል ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ ነው ።

የፖለቲካ ሥርዓት እንቅስቃሴ ኃይላት የሚያወጧቸው ዕቅዶች ፥ ፕሮግራሞች ፥ ውሳኔዎች ፥ የሚቀይሷቸው ግቦች ሁሉ በልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ገጽታዎች ተግባራዊ የሚሆኑና ለተግባራዊነታቸውም አስገዳጅነት ያላቸው ናቸው ። ከሌሎች የኅብረተሰብ ሥርዓቶች ጋር ሲነፃፀሩ « የፖለቲካ ሥርዓት መሠረታዊ ተግባር በመሪ የመደብ ኃይላት ለኅብረተሰቡ የታተዱ ግቦች ዕውን እንዲሆኑ የሚያስችሉ ነገሮችን (resources) ሁሉ ማሰባሰብ ነው ።

ሁለተኛው የፖለቲካ ሥርዓት ልዩ ባህ ይህ ሥርዓት ከሌሎች ንዑሳን ማኅበራዊ ሥርዓቶች ጋር የሚያደርገው መስተጋብር የአካባቢው በተለይም የኅብረተሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረት ውጤት (function) መሆኑ ነው ። የፖለቲካ ሥርዓት ፥ ምንም እንኳን በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛውን ሥልጣን (የበላይነት) የያዘ ቢሆንም በኅብረተሰብ መሠረታዊ ኢኮኖሚና የማኅበራዊ ግንኙነት የሚወሰን ላዕላይ መዋቅር ነው ።

ሦስተኛው የፖለቲካ ሥርዓት ባሕርይ ይህ ሥርዓት ካለው አንጻራዊ ነፃነት ጋር የተያያዘ ነው ። ሥርዓቱ በተለያዩ ቡድኖች ተዛምዶ ፥ ሚናዎችና ተግባራት ልዩ አሠራር ላይ የተመሠረተ አንጻራዊ ነፃነት አለው ። አንጻራዊ ነፃነቱ ከሚከስትባቸው መልኮቹ አንዱ የፖለቲካ ሥርዓት ከኅብረተሰቡ ንዑሳን ሥርዓቶች ሁሉ አሠራሩ በሕግና በግዕዝ (norm) የተደነገገ ፥ የተብራራና የተወሰነ መሆኑ ነው ። የፖለቲካ ሥርዓት ውስጣዊ ግንኙነት ብዙውን ጊዜ ሕጋዊና ፖለቲካዊ በሆኑ ልዩ ልዩ ገዕዛን የሚመራ ነው ።» ለምሳሌ የፓርቲ ወይንም የመንግሥት አሠራር በአመዛኙ በአዋጅ ፥ በአስተዳደር ደንቦችና በመሳሰሉት ሕጐች የተዘረዘረና የተገለጸ ነው ።

አራተኛው የፖለቲካ ሥርዓተ ልዩ ባሕርይ ሥርዓቱ በኅብረተሰቡ ውስጥ ሌሎች የኅብረተሰብ ንዑሳን ሥርዓቶች ካላቸው ተሰሚነት ሁሉ የበለጠ ብርቱና ጠንካራ ተሰሚነት ያለው መሆኑ ነው ። ለዚህም ምንመ

Digitized by Google

የመጀመሪያው ባሕርይው ማለትም የ ፖለቲካ ሥርዓት ከፍተኛ ሥልጣን ያለውና በኅብረተሰቡ ሀብት ላይ ለማዘዝ መቻሉ ነው ። ፖለቲካ፣እነኚህን አራት ባህርያት አካቶ የያዘ በመሆኑ ነው በኅብረተሰብ ኑሮ ውስጥ ትልህ ሚና ሊጫወት የሚችለው ።

የፖለቲካ ሥርዓት ተግባራት

ኅብረተሰብ ያድጋል ፤ በየዕድገት ደረጃውም የተለያዩ ፣ ውስብስብና ከባድ የሆኑ ማኅበራዊ ችግሮች ይገጥሙታል ፤ እንደሁኔታውም መፍትሔ ይሰጣቸዋል ወይንም ሊሰጣቸው ይታገላል ። በዚህም ድርጊቱ የዕድገት ሂደቱን ያከናውናል ።

የኅብረተሰብ ታሪክ የሰው ልጅ ከመሰሉና ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርገው የማያሰልስ ግንኙነት ውስጥ ለሚነሱ ችግሮች መፍትሔ በመስጠትና ወደላቀ የዕድገት ደረጃ በሚደረግ ሂደት የተሞላ ነው ። በዚህ አንጻር «የኅብረተሰብ ዕድገት ማለት የችግሮች መከሰትና መፍትሔ የማግኘት ሂደት ነው » [28] ለማለት ይቻላል ።

አንድ ኅብረተሰብ ሊያከናውነው የሚገባ ተግባር ፣ ፍላጐቱን ለማርካትና ሕልውናውን ለመጠበቅ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ፣ መፍትሔ የሚጠይቁ ጉዳዮችና የመሳሰሉት የኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ችግሮች ናቸው ። ማኅበራዊ ችግር ሲባል «ምንጊዜም ቢሆን በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች የሚያመለክት ነው ።» [29]

ማኅበራዊ ችግሮች በኅብረተሰቡ ውስጥ ከሚከሰቱባቸው መልኮች መካከል ፣ ሀ/ ለኅብረተሰብ ታሪካዊ ዕድገት እጅግ አስፈላጊ በሆኑት ነገሮችና እነኚህን ነገሮች ለማሟላት በመሣሪያነት የሚያገለግሉ ነገሮች በቂ ሆኖ አለመገኘት ለ/ ቁሳዊ ሀብትና የሰው ኃይል በቂ ባለመሆናቸው የኅብረተሰቡን ፍላጐት ለማሟላት የሚደረገው ጥረት አለመሳካት ሐ ኅብረተቡ የገጠሙትን ችግሮች ለመፍታት የችግር ማስወገጃ የሆኑ አዳዲስ ነገሮችን አለመገኘት ወይንም ቢገኙም በቂ አለሆናቸው ይገኙበታል ። [30] የዚህ ዓይነቱ የችግሮች መከሰት ሂደት የሚቀጥል ነው ።

የኅብረተሰብ ዕድገት ከማኅበራዊ ችግሮች መፈጠርና መፈታት ተነጥሎ አይታይም ። አንዱ ችግር ሲፈታ ሌላው ይቀጥላል ። አንድንም ችግር መፍታት ሌላ ችግርን ሊያስከትል ይችላል ። [31] ነገር ግን የኅብረተሰብ የሥልጣኔ ደረጃና የማኅበራዊ ሁኔታ ችግሮቹን በትክክል በመረዳት ችሎታ ላይና በእነኚህ ችግሮች በቁጥጥር ሥር መዋል ወይንም አለመዋል ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መሆኑ መረሳት የለበትም ።

ማኅበራዊ ችግሮች ነባራዊ ናቸው ። አንድ ኅብረተሰብ ሕልውናውን ለመጠበቅ የሚችለው የሚገጥሙትን ችግሮች እንደሁኔታው ለመፍታት ወይንም ቢያንስ ለጊዜውም ቢሆን ችግሮቹ የሚያስከትሉትን ጥፋት ለመቀነስ እስከቻለ ድረስ ነው ። በየዕድገት ደረጃው የሚገጥሙትን ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግሮች ሊፈታ ያልቻለ ኅብረተሰብ ዞር ዞር ችግሮቹ ተባብሰውና ተካረው የአደረጃጀት ቅርጹን ያፈርሱበታል ። አንድ የሶቭዬት ምሁር ማኅበራዊ ችግር በኅብረተሰብ ላይ የሚያቀርበውን አስገዳጅነት ሲገልጽ« ማኅበራዊ ችግር አንድ ኅብረተሰብን ከፊቱ ቆሞ መፍትሔ አግኝልኝ አለበለዚያ ብትንትንህን አወጣዋለሁ» [32] ከሚል ከአንድ ትልቅ ኃይል ጋር አመሳስሎታል ። በርግጥም ማኅበራዊ ችግሮች እንደየከብደት ደረጃቸው በኅብረተሰብ ኑሮ ውስጥ የግዴታ ለውጥ ያስከትላሉ ፤ አንድን የምርት ግንኙነት ማለትም የአንድን ኅብረተሰብ የአደረጃጀት ቅርጽ በሌላ ይተካሉ ፤ ወይንም ቢያንስ ለመተካቱ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ።

ማንኛውም ኅብረተሰብ ቢሆን ውድቀቱን ለማስወገድ የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታትና ለማደግ ይፈልጋል ። ነገር ግን ይህን ለማድረግ የሚፈልገው በቆመለት የመደብ ጥቅም አንጻር ነው ። ለምሳሌ የካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ የፖለቲካ ሥርዓት

Digitized by Google

የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታትና ለማደግ የሚፈልገው በመሠረቱ የካፒታሊስቱን የመደብ ጥቅም ከማስጠበቅና ከማስፋፋት አንጻር እንጂ በምንም ዓይነት የዚህ ተቃራኒ አይሆንም ። የሠራተኛው መደብ የሚያቋቁመው የፖለቲካ ሥርዓትም ማኅበራዊ ችግሮቹን የሚፈታው የሠራተኛውን መደብ ጥቅም (ከዚህም ጋር ተያይዞ የመላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅም) ከማስከበር አኳያ ነው ።

የፖለቲካ ሥርዓት የተለያዩ ተግባራትን በማከናወኑ ምክንያት በሌሎች ማኅበራዊ ወይንም የኅብረተሰብ የኑሮ ገጽታዎች ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል ። «ፖለቲካ ተጽዕኖ በሚያደርግባቸው ማኅበራዊ ግንኙነቶች መስክ አንጻር ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ ፣ ማኅበራዊ ፖሊሲ ፣ ባህላዊ ፖሊሲ ወይንም ቴክኖሎጂያዊ ፖሊሲ» እየተባለ ይከፈላል ። 33

ሌኒን እንዳለው «አንድ መደብ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ሊያስከብርለት የሚችል ትክክለኛ የፖለቲካ ፖሊሲ መንደፍ ካልቻለ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የበላይነት ቦታ እንደያዘ ለመቆየት አይችልም ። በዚህም ምክንያት ለገጠሙት የኢኮኖሚ ችግሮች እልባት ለመስጠት ይሳነዋል ።» 34

የተለያዩ የፖለቲካ ሥርዓቶች በያሉበት ኅብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የጨበጡ ፣ ከሌሎች የኅብረተሰብ የኑሮ ገጽታዎች ሁሉ የበለጠ ተሰሚነትና ንቁ ተሳታፊዎች መሆናቸው ለሚቀይሱት ግብ ዕውን መሆንና ለሚያከናውኑት ተግባር እልባት መስጠት ከሌላው የኅብረተሰብ ሥርዓቶች ሁሉ የተሻለ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል ። ነገር ግን ከነባራዊ የዕድገት ሕግጋትና ከመደባዊ የኃይል አሰላለፍ ጋር የማይጣጣም የፖለቲካ ሥርዓት አሠራሮች በአመዛኙ ተግባራዊ ለመሆን የሚሳናቸውና ቀውስ የሚጠናወታቸው መሆኑ መረሳት የለበትም ። አድኃሪ ወይንም ግራ ተስፈንጣሪ ፖሊሲ የሚያራምድ የፖለቲካ ሥርዓት በታሪክ ሂደትና ሕግጋት ላይ አለመመሥረቱና ለብዙኃኑ ጠቃሚ አለመሆኑ ግልጽ እየሆነ ሲሄድ ፣ የተጠናወተው ቀውስ እየጠናበት የኅብረተሰቡን ችግር ለመፍታት ይሳነዋል ። በመጨረሻም በመደብ ትግል አስገዳጅነት ቦታውን ለተራማጅ የፖለቲካ ሥርዓት ይለቃል ።

በኅብረተሰብ የትግል ሂደት ውስጥ የፖለቲካ ሥርዓት ተግባር ግቡን ሊመታ የሚችለው የሚወስዳቸው ልዩ ልዩ እርምጃዎች ከነባራዊ የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግጋት ጋር ሲጣጣሙ ፣ የቆመለት ዓላማ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነትን ሲያገኝ ፣ ሰፊውን ሕዝብ በትግሉ በማሰለፍ ከተጻራሪዎቹ የሚሰነዘርበትን ትግል ሲያከሽፍና በትግሉም የበለጠ ተጨባጭ ውጤት ለማስገኘት የኅብረተሰቡን ሀብት በጥቅም ላይ ሲያውል ነው ።

ፊዮዶር ቡርላትስኪ

ግቦችን መንደፍና እነሱንም ተግባራዊ ለማድረግ ሀብትን ማሰባሰብ የፖለቲካ ሥርዓት ተቀዳሚ ተግባር ሲሆን ኅብረተሰቡን ማስተባበር (Integration) እና የፖለቲካው ሥርዓት ደጋፊዎች የቀፀሙ ለተ ግብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረግ (Legitimation) የፖለቲካና የሌሎችም የኅብረተሰብ ንዑሳን ሥርዓቶች በተለይም የሕሊናዊ ሥርዓት (Intellecutal subsystems) ተግባራት ናቸው 35

እንዳለው አንድን ኅብረተሰብ በየአቅጣጫውና በየዕድገት ደረጃው የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታት ያሚስችሉ ናቸው የሚባሉትን የተለያዩ ግቦች መንደፍና ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ ፣ የፖለቲካ ሥርዓት ተግባር ብቻ አይደለም ። ነገር ግን ለአንድ ኅብረተሰብ ሕልውና መጠበቅ ወይንም ዕውን መሆን ዋና ዋና ግቦችን መንደፍና ለእነ ዚሁም ግቦች ተግባራዊነት የሚያስፈልጉትን ማኅበራዊ ኃይላት ማስተባበርና የኅብረተሰቡን ሀብት መጠቀም ከሌሎች የኅብረተሰብ ሥርዓቶች ሁሉ የፖለቲካ ሥርዓት ተቀዳሚ ተግባር ነው ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ ፤

1. Fydor Burlatsky, *The Modern State and Politics* (Moscow: Progress Publishers, 1978), p. 48.
2. *Ibid.*
3. Yu I. Semyonv, "Socio-Economic Formations in the Historical Process", an article in *Philosophy in the USSR: Problems of Historical Materialism* (Moscow: Progress Publishers, 1981), pp. 33-34.
4. Fydor Burlatsky, pp. 34-35.
5. *Ibid.*, pp. 41, 47.
6. German Gvishian, "The Philosophical Basis of Systems Studies", *Social Sciences*, Vol. XIII, No. 3, 1982, pp. 56-57.
7. V.S. Semyonov, "The Ensemble of Social Structure and the Social Structure of Society", an article in *Philosophy in the USSR: Problems of Historical Materialism*, p. 210.
8. *Ibid.*, pp. 210-211.
9. See, for example, D. Chesnokov, *Historical Materialism* (Moscow: Progress Publishers, 1969), p. 289.
10. Fydor Burlatsky, p. 16.
11. "Horizons of Soviet Political Sciences," *Social Sciences*, Vol. XIII, No. 3, 1982, p. 160.
12. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 5, p. 422, Quoted in Fydor Burlatsky, p. 17.
13. Karl Marx and Frederik Engels, *The German Ideology*, p. 42, Cited in Fydor Burlatsky, p. 15.
14. Fydor Burlatsky, p. 21.
15. *Ibid.*
16. V.I. Lenin as cited by Fydor Burlastky, p. 15.
17. *Ibid.*, p. 17.
18. *Ibid.*, p. 22.
19. See, Jack Woddis, *Armies and Politics* (London: Lowrence and Wishart, 1977), pp. 17-18.
20. Georgi Arbatov, *The War of Idea in Contemporary International Relations* (Moscow: Progress Publishers, 1975), p. 62.
21. Fydor Burlatsky, p. 22.
22. *Ibid.*, p. 49.
23. V.I. Lenin, *Col. Works*, Vol. 14, p. 146.
24. V. Afanasyev, *Social Information and Regulation of Social Development* (Moscow: Progress Publishers, 1978), p. 307.
25. *Fundamental of Marxist-Leninist Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1974), p. 407.
26. Fydor Burlatsky, p. 51.

bid., pp. 48-49.

27. *Ibid.*, pp. 48-49.
28. V.I. Kutsenko, "The Social Problems: Objective, Nature, Structure, Solution", an article in *Philosophy in The USSR: Problems of Historical Materialism*, p. 134.
29. *Ibid.*
30. *Ibid.*, p. 135.
31. *Ibid.*
32. S.G. Strumilin, as cited by V.I. Kutosenko, p. 137.
33. See, *Great Soviet Encyclopedia*, Vol. 20, 1974, p. 349, see also V. Afanasyev, p. 308.
34. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 32, p. 84, as cited in V. Afanasyev, p. 309.
35. Fydor Burlatsky, p. 49.

Digitized by Google

የአስተያየት ገፅ

መሪ ፓርቲና መሪ ዕቅድ

ሁለት የአብዮታችን አበይት ድሎች

ኢትዮጵያ ከፍተኛ ግምት ያለው የታሪክ ቅርስና ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ሀገር ናት። የሕዝቧ የኑሮ ደረጃ በአብዮቱ አማካይነት መለወጥ ቢጀምርም መነሻው እጅግ በጣም ዝቅተኛ ከሚባሉት ጥቂቶች መካከል የሚገኝ ነው። ለአያሌ ምዕተ ዓመታት ሰፊው ሕዝብ ወጥቶ ወርዶ ለፍቶ ደክሞ ያመረተውንና ያፈራውን ለገዥ መደብ አባሎችና ለአጫፋሪዎቻቸው በማስረከብ በረሃብና በሽታ፣ በድንቁርናና በጉስቁልና ኑሮ ውስጥ ፍዳውን ሲያይ ኖሯል። ብዝበዛውና ጭቆናው አንገፍግፎት በየካቲት 1966 ሰፊው ሕዝብ እንደ አንድ ሰው ሆኖ የተነሣውና የተንቀሳቀሰው፣ በዝባዦችና ጨቋኞች የሚጭኑበትን ቀንበር ሰባብሮ በመጣል የነፃነት፣ የእኩልነትና የብልጽግና ኅብረተሰብ ለመገንባት፣ በሰላምና በደስታ ለመኖር መሆኑ ግልጽ ነው።

የአዲስ ብዝበዛ-አልባ ኅብረተሰብ] ግንባታ ረዥም፣ መራራና ውስብስብ ትግልን አቋርጦ የሚደርስበት የሩቅ ጊዜ ግብ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚያ በፊት የነበረውን እንኳን ብንተው ከዛሬ አሥር ዓመታት ወዲህ አሁን የደረሰበት ምዕራፍ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ መሥዋዕትነት የጠየቁ መራራና ውስብስብ ትግሎችን በየመስኩና በየፈርጁ አካሂዷል። አድኃሪውን የገዥ መደብ በማስወገድ ሥልጣነ መንግሥትን ከመጨበጥ እንሥቶ በኢምፔሪያሊዝምና በአድኃሪ የአካባቢው መንግሥታት አስተባባሪነትና ደጋፊነት ከወደቀው የገዥ መደብ ርዝራዦች፣ ከልዩ ልዩ ጠባቦችና ትምክህተኞች፣ ከወራሪዎችና ተስፋፊዎች ጋር በፖለቲካው፣ በርዕዮተዓለሙ፣ በወታደራዊው መስኮች እጅግ ከፍተኛ የሕይወትና የንብረት መሥዋዕትነትን የጠየቁ መራራ ትግሎች ተደርገዋል። ዛሬ ከአሥር ዓመታት በኋላ አብዮታችን የበላይነቱን ቢያረጋግጥም ከኢምፔሪያሊዝምና ከቡችሎቹ ጋር የሚደረገው ውስብስብ ትግል አሁንም በየአቅጣጫውና በየፈርጁ እንደቀጠለ ነው።

Digitized by Google

ኢምፔሪያሊዝምና አድኀርት ኃይላት
ሕዝባዊ አብዮታችንን ለመቀልበስ፣የእናት
ሀገራችንን ህልውና ለመፈታተን፣በኢኮኖ
ሚውና በማኅበራዊው እንደዚሁም በሌ
ሎች ቡርቦራቸውንና ደባቸውን አካሒደ
ዋል። አሁንም ቢሆን አብዮቱ ሥር እንዳ
ይሰድና እንዳይጠናከር አሻጥሮችንና ልዩ
ልዩ መሰሪ ድርጊቶችን ከመፈጸም ወደኋላ
አይሉም። የኢትዮጵያ አብዮት ከ1966
ጀምሮ በየደረጃውና በተከታታይ ዋና ዋና
ዎቹን የምርት መገልገያዎች፣የማክፋፈያ፣
የገንዘብና የአገልግሎት ድርጅቶች የመን
ግሥትና የሕዝብ ይዞታ በማድረግ የሚከ
ተለው የዕድገት ፈለግ ሶሻሊዝም መሆኑን
በይፋና በተግባር ማረጋገጥ ከጀመረ ወዲህ
ጠላቶቹ የሥራ ማክናወኛ መሣሪያዎችንና
የምርት መገልገያዎችን በማሰናከል በመሰ
ባበርና በማውደም የሥራን እንቅስቃሴ
በመጐተትና በማንዛዛት፣የሥራ መስክ ን
በማጥበብ፤ በመቀነስ፣ማኅበራዊ ችግሮቹን
በማባባስና ውዥንብሮችን በመንዛትና በመ
ሳሰሉት ልዩ ልዩ ዘዴዎች ክፉኛ ሲፈታ
ተኑት ቆይተዋል። አሁንም ሆነ ወደፊት
ጨርሶ ድል እስኪመቱ ድረስ በዚሁ አቅ
ጣጫ ከመቀጠል ወደኋላ እንደማይሉ የወ
ቅታችን በሁለቱ ርዕዮተ ዓለሞች፣በሁለቱ
ሶሲዮ ኤኮኖሚያዊ ሥርዓቶች፣በሶሻሊዝ
ምና በካፒታሊዝም መካከል የሚካሔደው
ትግል ታሪክ በግልጽ የሚያሳየው ሀቅ ነው።

ዛሬ አሥረኛ ዓመቱን የሚያከብረው የኢ
ትዮጵያ አብዮት በመራራና ውስብስብ ትግ
ሎች ውስጥ አልፎ ከዚህ ዓቢይ ምዕራፍ
ላይ የደረሰው የአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ
መሪ የሆነውን ሀቀኛና ጠንካራ የመሪ
ፓርቲ ሳያቀዳጅ በአብዮታውያንና በሰ
ፊው ሕዝብ ተጋድሎ ነው። ከልዩ ልዩ
መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ተውጣ
ጥተው በፀረ ፊውዳል፣በፀረ ቢሮክራሲያዊ
ካፒታሊዝምና በፀረ ኢምፔሪያሊዝም መድ
ረክ ላይ በመሰባሰብና በመካከላቸውም
መራራ ትግል በማካሔድ በጊ.ወ.አ.ደ.
መሪነት እስከዚህ ድረስ የመጡት አብዮ
ታውያን ኃይሎች የአብዮቱን ድሎች በማ
ጠናከር ለሶሻሊዝም ግንባታ አስተማማኝ
መሠረት ለመጣልና ግንባታውንም ሙሉ
በሙሉ በመያያዝ ወደፊት ለመገስገስ
ይችሉ ዘንድ የመሪ ፓርቲ አማራጭ የሌ
ለው ብቸኛ ኃይል ነው።

የወዝአደሩ ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም በሰ
ፊው ካልተሠራጨበት፣ ከዘጠና በመቶ
በላይ የሆነው የኅብረተሰቡ አብዛኛው
ክፍል በማይምነት ጥቁር መጋረጃ ውስጥ
ከነበረበት እጅግ በጣም ኋላቀርና ከቆረ
ቆዘ የኤኮኖሚ ይዞታ፣በአጠቃላይ በዝቅ
ተኛነት ከጥቂት አገሮች በስተቀር ከማይ
ወዳደሩት የዕድገት ደረጃ ተነሥቶ ዛሬ ለአ
ዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ ፍቱንና አማራጭ
ከማይገኝላቸው ወሳኝና አስፈላጊ ሁኔታ
ዎች ውስጥ በመጀመሪያ የሚጠቀሱትን
መሪ ፓርቲና መሪ የልማት ዕቅድ መቀዳ
ጀት ባንድ አብዮታዊ ሂደት ውስጥ በቀ
ላሉ የሚገመት ክንዋኔ አይደለም። በአድ
ኃሪው ፊውዳል ሥርዓት ጭቆናና ብዝበዛ
እጅግ በጣም ተማሮና ተንገፍግፎ የነበረው
የኢትዮጵያ ሰፊ ሠርቶ አደር ሕዝብ የተጠ
የቀውን መሥዋዕትነት ሁሉ ያለ አንዳች
ማመንታት እየከፈለ ከአሥር ዓመታት
ውስብስብ ትግል በኋላ እነዚህን ወሳኝ የሶ
ሻሊስት ግንባታ መሣሪያዎች ለመጨበጥ
መቻሉ ከአዲስ ምዕራፍ ላይ መድረሱን
የሚያበሥር ሁኔታ ነው።

ፓርቲ ተመሳሳይ ዓላማና አመለካከት
ያላቸው ወገኖች የመደብ ጥቅማቸውን ለማ
ስከበርና ለማስጠበቅ የተሰለፉበት የተደ
ራጀ ኃይል ነው። የሠራተኛው ፓርቲ የማ
ሌን ሳይንስ የተጠቁ፣ንቃተ ኅሊናቸው ከፍ
ተኛ የሆነ፣የሠራተኛው መደብ አባላት የተ
ሰበሰቡበት ግንባር ቀደም ድርጅት ሲሆን፣
ለመራራውና ውስብስብ ትግል የሠራተኛ
ውን መደብና በአጠቃላይ ሰፊውን ሠርቶ
አደር ሕዝብ በማንሣሣትና በማሰለፍ በዝ
ባዡን ሥርዓት በመገርሰስ የጭቆናና የብ
ዝበዛ ቀንበርን በመሰባበር የወዝአደሩን
የበላይ ገዥነት የማስፈንና ለአዲሱ ብዝ
በዛ ለሌለበት ኅብረተሰብ ግንባታ አመራር

Digitized by Google

በመስጠት ከግቡ የማድረስ ታሪካዊ ኃላፊነት አለበት ። በፕሮግራሙና በደንቡ ላይ በመመሥረት ፓርቲው የአባላቱን የርዕዮተ ዓለም ግንዛቤና ተገዥነት እንደዚሁም የሠራተኛውን በአጠቃላይም የሰፊውን ሠርቶ አደር ንቃተኅሊና በማዳበር የአባላቱን ቁጥር ያሳድጋል ፤ የመከላከያና የደኅንነት ፣ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲዎችንና ዕቅዶችን በማዘጋጀትና አፈጻጸማቸውን በመከታተልና በመቆጣጠር የግንባታውን ተግባራት ደረጃ በደረጃና በቅደም ተከተል ያራምዳል ። ፓርቲ ሠራተኛው መደብ በጭቆናና ብዝበዛ ሥርዓት ፣ መቃብር ላይ እኩልነት ፣ ነፃነትና ብልጽግና የሰፈነበት አዲስ ሥርዓት ፣ አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት የሚያካሒደው ረዥምና ውስብስብ ትግል አዝማች ፣ ስትራቴጂና ታክቲክ ቀያሽ ፣ ተግባራዊነቱንም የሚቆጣጠር የሚያረጋግጥ እንደመሆኑ አብዮታችን ይህን ወሳኝ ኃይል መቀዳጀት ለግንባታ ጥረታችን መሳካት ጽኑ መሠረት ነው ።

ብዝበዛና ጭቆና የሌለበትን አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት በሳይንስ ላይ በተመሠረተ ዕቅድ ወይም ፕላን ተግባርን መምራትና ማንቀሳቀስ አስፈላጊና ወሳኝ ነው ። ፓርቲው ሥራውንና በአጠቃላይ የግንባታውን ተግባር የሚመራው የኅብረተሰብን የዕድገት ሕግጋት በሚያገናዝብ ፕላን ላይ በመመሥረት ነው ። የሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ሁለንታዊ ዕድገት ለማረጋገጥ ፕላን አማራጭ የሌለው መሆኑን የዳበረ ሶሻሊዝም በመገንባት ላይ ያሉት አንጋፋ ሶሻሊስት አገሮች ልምድ በይፋ ያረጋግጣል ።

የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾች ካርል ማርክስና ፍሬድሪክ ኤንግልስ በአያሌ ሳይንሳዊ ሥራዎቻቸው በግል ሀብትና ጥቅም የሚመራው ሥርዓተ አልባ የሆነው የካፒታሊስት ኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ማኅበራዊ ብልጽግናን ግቡ ላደረገውና በፕላን ለሚንቀሳቀሰው ሶሻሊስት ኤኮኖሚ ሥፍራውን መልቀቅ እንዳለበት ደጋግመው አብራርተዋል ። ፍሬድሪክ ኤንግልስ ፀረ ዱሪንግ በተባለው ዝነኛ መጽሐፉ «የዛሬዎቹ የምርት ኃይሎች እውነተኛ ባሕርይ ግንዛቤ ቢያንስ ሥርዓተ አልባው ማኅበራዊ አመራረት ፣ በማኅበረሰቡና በግለሱቡ ፍላጎት መሠረት በተወሰነ ፕላን ለሚመራ ፣ ደንብን ለተከተለ ማኅበራዊ አመራረት ሥፍራውን እንደሚለቅ ያመለክታል» * በማለት በሶሻሊዝም ኤኮኖሚው የሚመራው በፕላን መሆኑን አስገንዝቧል ። ታላቁ ሌኒንም የፕላንን አስፈላጊነት ሲገልጽ « ባለፉት ሥርዓተ ማኅበሮች ያልነበረው በማሽን ላይ የተመሠረተው ትልቅ ኢንዱስትሪ ምርት በሕዝብ ቁጥጥር ሥር መሆን በፕላን መመራትን የግድ ያደርገዋል» * * ብሎ ነበር ።

የካፒታሊስት ኤኮኖሚ በገበያ (በእሴት ሕግ) በግል ብልጽግናን ዘወትር ከፍተኛ ትርፍ በማሳደድ ፣ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በመበዝበዝ ሕግ የሚመራ እንደመሆኑ ሥርዓተ አልባ ነው ። እያንዳንዱ ግለሰብ ካፒታሊስት በየፊናው ከፍተኛ ትርፍና ሀብት ለማጋበስ በተለያዩ አቅጣጫዎች ይከንፋል ፤ ይሯሯጣል እንጂ የሰከነና መሥመር የያዘ በኅብረተሰቡ ጥቅምና ደኅንነት ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ አይከተልም ። በሌላ አባባል ሳይንሳዊ በሆነው ኤኮኖሚውን በዕቅድ በመምራት ሕግ አይገዛም ። በተቃራኒው ዓላማውና ግቡ የወል ብልጽግናና የሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ኑሮ ማሻሻልና ማሟላት የሆነው ሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታ ሊሰፍንና እውን ሊሆን የሚችለው በሳይንሳዊ መሠረት ላይ በተገነባ ዕቅድ ወይም ፕላን የተመራ እንደሆነ ብቻ ነው ። ዘላቂ የማኅበራዊ ዕድገት ሊገኝ የሚችለው በሌላ ዓይነት ዘዴ ወይም መንገድ ሳይሆን የኅብረተሰብ የዕድገት ሕግጋትን ተከትሎ በሚቀየሰው ዕቅድ ወይም ፕላን

---

* Frederick Engels, Anti-Duhring, pp· 320 21·

** V.I. Lenin, "The development of capitalism in Russia," Col. W., Vol. 3, p. 544.

ነው ። ፕላን ወይም ዕቅድ የኅብረተሰብ ዕድ
ገት ዓይነተኛ መሣሪያ ከመሆኑም በ ላ ይ
በአንድ ሀገር ልዩ ልዩ ክፍሎችና ሥፍራዎች
እንደዚሁም በተለያዩ ክፍላተ ኤኮኖሚዎች
መካከል የተመጣጠነ ዕድገትን እውን ለማ
ድረግ ዓቅምን ገምግሞ ፣ ጠንቅቆና አውቆ
ኃይልን አሰባስቦ ግቦችን በቅደም ተከተል
ተልሞ ተጨባጭ ውጤት ለማስገኘት የሚ
ያስችል ዘዴ ነው ። ዕቅድ በቁሳዊና ሰብአዊ
ሀብት ፣ ቴክኒካዊና አእምሮአዊ ችሎታን
አግባብ ባለው መንገድ ከፍተኛና ዘ ላ ቂ
ጠቀሜታ ሊያስገኝ በሚችልበት ሁኔታ ለሰ
ፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ኑሮ መሻሻልና
ዕድገት ለማዋል የሚያስችል ብቸኛ ዘዴ
ነው ። በዚህ መሠረት ዛሬ በ10ኛው ዓመት
የአብዮት በዓል ወቅት የአሥር ዓመቱ መሪ
ዕቅድ መዘጋጀቱ ከፍተኛ ግምት የሚሰ
ጠው ድል መሆኑ አያጠያይቅም ።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በተቀጣ
ጠለ በ10 ዓመቱ ዛሬ የግንባታው ትግል
መሪ የሆነውን የሠራተኛውን ፓርቲና የግ
ንባታ ተግባሩም ማከናወኛ ዓይነተኛ ዘዴ
የሆነው መሪ ዕቅድ መዘጋጀቱ ዓቢይ ክንዋኔ
ቢሆንም እነኝህን መሣሪያዎቹ በአግባቡ ተግ
ባራዊ ለማድረግና በመጨረሻም ግንባታ
ውን ወደፊት ለማራመድ ግን ገና ብዙ
ውጣ ውረድና ውስብስብ ትግል ይጠይ
ቃል ። አብዮታችን ከባድ መሥዋዕትነት
ተከፍሎበት በአያሌ ውጣ ውረድ ውስጥ
አልፎ እነዚህን ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸ
ውን ድሎች ይቀዳጅ እንጂ እነዚህን ፍቱ
ንና ሳይንሳዊ የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ
መሣሪያዎች በአግባቡ ለመጠቀምና በተቀ
የሰው ጐዳና ወደፊት ለመራመድ መቻል
ቀላል አይደለም ። ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ
ችን ፣ የተመጠነ ልምዳችንና ንቃታችን አሁ
ንም ልንወጣቸው የሚገቡ እክሎች ናቸው ።
የዕድገት መሣሪያዎቻችን በትክክል ሊያ
ገለግሉ የሚችሉት ሀልውናቸው በይፋ በመ
ገለጡ ብቻ አይደለም ። ዋናው ቁም ነገር
መሣሪያዎቹ ብቻ ሳይሆኑ እነዚህን መሣሪ
ያዎች የሚያንቀሳቅሱት ሰዎች ዓይነትና
ብቃት ነው ። እጅግ በጣም ዝቅተኛና ኋላ
ቀር ከሆነ የዕድገት ደረጃ ተነሥተን ረዥ
ሙንና ውስብስቡን ሂደት አቀራርጠን በአ
ጭር ወይም በመካከለኛ ጊዜ ውስጥ ከላ
ቀው የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያ
ስፈልጉት የሰው ዓይነቶች በጣም የተለዩ ፣
በርዕዮተዓለምና በሙያ በንድፈ ሐሳብና
በተግባራዊ ችሎታ የተሟላ ብቃት ያላቸው ፣
ለቆሙለት ዓላማ ከፍተኛውን መሥዋዕት
ነት ለመክፈል ዝግጁ የሆኑ ፣ በሁሉም መስክ
ግንባር ቀደም አርአያ የሚሆኑ ፣ ከለዘብተ
ኝነትና አድርባይነት ፈጽመው የጸዱ ሀቀ
ኛና እውነተኛ አብዮታውያን እጅግ በጣም
አስፈላጊና ወሳኝ ናቸው ። እነዚህን መሠረ
ታዊና አስፈላጊ ባሕርያት ያሟሉ ካድሬ
ዎችን ማግኘት ለግንባታው ተግባር ከግቡ
መድረስ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው ። ፓር
ቲም ሆነ ፕላን ያለ ብቁ ካድሬዎች ፋይዳ
ሊኖረው እንደማይችል ታሪክ በተደጋጋሚ
በልዩ ልዩ ሥፍራና ጊዜ ያሳየው ሀቅ ነው ።

በ1966 የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አሻፈ
ረኝ በማለት ለአብዮት ከዳርዳር ሲንቀሳ
ቀስ ፣ የአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ መመሪያ
የሆነው የማሌ ሳይንስ ታዋቂነቱና ተቀባ
ይነቱ ገና በጥቂቶቹ ዘንድ የተወሰነ ቢሆ
ንም ፣ ዛሬ በጥልቀትም ባይሆን በስፋቱ
በኢትዮጵያ ውስጥ ያላደረሰው አካባቢ አለ
ለማለት አያስደፍርም ። ይሁን እንጂ ይህ
ንን ሳይንስ ሙሉ በሙሉ ተገንዝቦ ንድፈ
ሐሳቦችን ከተግባር ጋር አቀናጅቶና አዋ
ሕዶ በሚገባ የግንባታው መሣሪያ ለማድ
ረግ ገና የረዥም ጊዜ የማያቋርጥ ጥረትና
ትግል ይጠይቃል ። በዚህ ወቅት ህልውና
ውን የተጐናጸፈው የኢትዮጵያ ሠራተኞች
ፓርቲ ካድሬዎቹን ከፊታቸው ለተደቀነው
ዓቢይ ተግባር ብቁ ለማድረግ ፣ በአጠቃላይ
የሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ንቃተ ኅሊና

Digitized by Google

በማዳበር ወደ ሶሻሊስት ንቃተ ኅሊና ደረጃ ለማሳደግ ከፍተኛና የማያሰልስ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል ።

በሶሻሊስት የዕድገት አቅጣጫ ዛሬ የደረስንበት ምዕራፍ በቀላሉ የማይታይ ቢሆንም ፣ በሁሉም ረገድ በተለይ በፓርቲ አሠራርና በዕቅድ አፈጻጸም በኩል ከፍተኛ ትግል እንደሚጠብቀን ግልጽ ነው ። በፓርቲም ሆነ በዕቅድ በኩል ገና ከመጀመሪያው ምዕራፍ እንጂ ከመጨረሻው ላይ አይደለንም ። የፓርቲውን የአመራር ሚና በተግባር እያጠናከርን ዕቅዱን ወደ ተሟላ ተግባራዊነት ለማሸጋገር ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል ። ተደጋግሞ እንደተገለጸው አሁን የተደረሰበት ምዕራፍ ለግንባታው ተግባር ዓይነተኛ መሣሪያዎችን አስጨብጦናል ። ከፊታችን የተደቀነው ተግባር የውጤት ማረጋገጫና ልንወጣው የሚገባን ታሪካዊ አደራ ነው ።

Digitized by Google

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google



HOOVER INSTITUTION 1985

▲ በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የሶሻሊዝም መሠረት ግንባታ

▲ ሕዝባዊ ቁጥጥርና አንዳንድ ችግሮቹ

▲ የየብስ ትራንስፖርትን ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ የተደረገ ጥረት

▲ አንድ የዓለም ቋንቋ እንዴት ይፈጠራል ?

ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 5 ቁጥር 20
ታኅሣሥ 1977

Digitized by Google

Meskerem P...

ET4704PF
9

መስከረም

ቅጽ 5 ቁጥር 20
ታኅሣሥ 1977

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ 3
- በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የሶሻሊዝም መሠረተ ግንባታ 6
  — አሰፋ ሀብቱ
  — ተክለ ብርሃን ገ/ሚካኤል
  — ታደለ ገብሬ ሕይወት
- ሕዝባዊ ቁጥጥርና አንዳንድ ችግሮቹ 34
  — ግርማ ተፈራ ዘማርያም
- የየብስ ትራንስፖርትን ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ የተደረገ ጥረት 54
- አንድ የዓለም ቋንቋ እንዴት ይፈጠራል ? 70
  — ኃይሉ አርአያ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር - [illegible]001

የስልክ ቁጥር - 113000

Digitized by Google

ወገንን ከዚህ ሰቆቃ ከማዳን የበለጠ ተቀዳሚ ተግባር የለም ።

በመልሶ መቋቋም አዲስ ሕይወት ምስረታ ።

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

የወቅቱ ጥሪ

ተግባራዊ አኩልነትና የጋራ ብልፅግና የማናቸውም ሠርተአደር ሕዝብ ፍላጐት ነው ። ይህን ይቀዳጅ ዘንድም በተቀዳሚ የፖለቲካ ልዕልናውን ማረጋገጥ እንዳለበት የታወቀ ነው ። ሆናም የፖለቲካ ልዕልና ማግኘት ብቻ ከድህነት ነፃ ለመውጣትና ፍላጐተቹን ሁሉ ለማሟላት አያበቃውም ። በፖለቲካ ረገድ ያገኘው ድል በፈጠረለት ለመቾ ሁኔታ በመጠቀም በኢኮኖሚው አደረጃጀትና ውጤት የበላይነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል ። አዲስ ማኅበራዊ ግንኙነት መመሥረት ፣ አዲስ የሥራ ዲሲፕሊንና የሥራ አደረጃጀት ማስፈን ደግሞ የፖለቲካ ሥልጣንን ከበዝባዥና ጨቋኝ መደቦች ከመንጠቅ የበለጠ ከባድ ነው ። ምክንያቱም ፍትሀ የሚያስገኝ አዲስ ስልተምርትና የላቀ ማኅበራዊ ሥርዓት መገንባት ውስብስብ ተግባር በመሆኑ ነው ።

እዚህ ላይ መጤን ያለበት አንዱ መሠረታዊ ቁም ነገር ሕዝብ ታሪክን የሚሠራው እራሱ በመረጠው ሁኔታ ሳይሆን በነባራዊ የእድገት ህግጋት እየተገዛና በውስብስብ ተፈጥሯዊና ማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ነው ። ሁኔታው የተመቻቸ ወይም እንቅፋት የበዛበት ሊሆን ይችላል ። ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ አብዮት ያለፈበት ጉዳና መለስ ተብሎ ሲታይ ሠርተአደሩ ሕዝብ የአብዮቱ ጠላቶች ሽንፈታቸውን ላለመቀበል በየጊዜው የሚሰነዝሩብትን ጥቃት ለመመከትና ለማክሸፍ በሕይወትና በንብረት ከፍተኛ መስዋዕትነት ሲከፍል የቀየና ብዙ አስቸጋሪ የትግል ምዕራፎችን ያሳለፈ መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም ። ትግሉ ምንም ያህል መራራ ቢሆን በአጠቃላይ ሲታይ ሠርተአደሩ ሕዝብ ከድል ወደ ድል እየተረማመደ በመምጣት ላይ ነው ። በአሁኑ ጊዜም ፀረ-አብዮተኞች የሚፈጽሙበት ደባ ፍፁም ተወግዶለታል ባይባልም የዕድገት እንቅፋቶችን በማስወገድ ወሳኙን የፓርቲ አመራር በመቀዳጀት እርምጃውን ለማፋጠን በይበልጥ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል ። ይሁን እንጂ በአየር ንብረት መዛባት ምክንያት የተከሰተው ድርቅ ያስከተለውን አስከፊ ችግር መቋቋም ላይ እንዲያተኩር በመገደዱ እጅግ ከባድ የሆነ ተጨማሪ የመስዋዕትነት ዋጋ የሚጠይቅ ሁኔታ አጋጥሞታል ።

በስፋቱና በአደገኛነቱ በአገራችን አቻ እንደማይገኝለት የሚገመተው የድርቅ ሁኔታ ያስከተለውን ከፍተኛ ጥፋት መግታት በቀላሉ የሚቻል ሆኖ ባለመገኘቱ የተቀነባበረ ብሔራዊ ጥረትና የጐላ ዓለምአቀፋዊ ዕርዳታ የሚያሻው ሆኗል ። በዚሁ መሠረት የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የፖለቲካ ቢሮ የነደፈውን የድርጊት ፕሮግራም በተግባር ለመተርጐም ሰፊ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል ። በየአቀጣጫው በተደረገው ጥረትም የእያሌ ዜጐችን ሕይወት ለማትረፍና ይደርስ የነበረውን ጥፋት ለመቀነስ

የተቻለ ሲሆን ችግሩን ደረጃ በደረጃ ለማስወገድ፣ ደግሞ ትግሉ በተጠናከረ መልክ መቀጠል ያለበት ነው ።

እጅግ አደገኛ በሆነ መልክ በአገራችን የተከሰተው ድርቅ ሌሎች ከዛያ የሚበልጡ የአፍሪካ አገሮችንም ጉዳት ላይ ጥሏቸዋል ። ይሁን እንጂ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ላይ ያስከተለው አደጋ ስፋትና ክብደት ያለው በመሆኑ የአያሌ ሕዝቦችን ፣ መንግሥታትንና ልዩ ልዩ ድርጅቶችን ትኩረት ሊስብ ችሏል ። ይህም ከአጋሮቻችንና በሰብአዊነት መንፈስ ሊረዱን ከሚፈልጉ ወገኖች ችግሩን ለመቋቋም የሚያግዝ ዕርዳታ ለማግኘት አስችሎናል ። በተፃራሪው ጠላቶቻችን አዛኝ መስለው ስውር የፖለቲካ ዓላማቸውን በይበልጥ ለማራመድና የሁኔታው ተጠቃሚ ለመሆን እንዲመኙ ሳያደፋፍራቸው አልቀረም ። ድርቁ ያስከተለውን አደጋ ለመቋቋም ተቀዳሚ ትኩረት መስጠትና ለሚደረግልን ዕርዳታ ሁሉ ምስጋና ማቅረብ እንዳለብን አጠያያቂ ባይሆንም ሁኔታው ከመደብ ጥቅም ነፃ በሆነ መልክ ይታያል ወይም ሁሉም ወገን በበጐ መንፈስ ችግሩን ከማቃለል አኳያ ብቻ ይመለከተዋል ብሎ ማመን የዋህነት ነው ።

ከሠርቶአደሩ ሕዝብ ጋር በዓላማ አንድነት የቆሙ ወገኖች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም አደገኛ የሆነውን ድርቅና እሱም ያስከተለውን ጥፋት ለማስወገድ የሚረዳ የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል ። የፊተኞቹ ፍላጐትና ጥረት ችግሩ ተወግዶና አብዮቱ ተጠናክሮ የሠርቶአደሩ ሕዝብ የዕድገት እርምጃ እንዲፋጠን ነው ። በአንፃሩ የኋለኞቹ ምኞት ችግሩ ብቻ ሳይሆን አብዮቱም ጭምር እንዲወገድላቸውና ሠርቶአደሩን ሕዝብ መልሰው በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ነው ። ይህ ሁኔታ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል ።

ጠላቶቻችን ፣ አብዮታችን ተቀልብሶ በሀገራችን የበላይነታቸውን ለመመለስ ከመመኘትና ከማድባት ወደኋላ ያሉበት ጊዜ የለም ። እድኀሪ ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ባመቻቸው ዘዴ ሁሉ ከመጠቀም እንደማይቆጠቡም የታወቀ ነው ። በዚሁ መሠረት ካለፈው ተሞክሮ ለተረክብነውና ለመለወጥ ለምንታገለው እጅግ አሳፋሪና አሳዛኝ ሁኔታ ፣ እንዲሁም እራሳቸው ለሚፈጥሩትም ሆነ ለማናቸውም ችግር አብዮቱን ተጠያቂ ማድረግ የተለመደ ዘዴያቸው ነው ። ዛሬ ደግሞ የአደጋው መጠን ቢለያይም በሌሎች በርካታ የአፍሪካ አገሮች ጭምር ለተከሰተው ድርቅ አብዮታችንን ተጠያቂ አድርገው ለማቅረብ ጊዜ አልወሰደባቸውም ።

ጠላቶቻችን በአገራችን የደረሰውን ድርቅ አብዮታችንን መውጊያ መሣሪያ አድርገው ለመጠቀም በሚያው ጠነጥኑት ሴራ በርከት ያሉ የአሉባልታ ነጥቦችን የሚደረድሩ ሲሆን ከነዚህም አንዱ «የምግብ እጥረት ሊደርስ የቻለው አብዮቱ በግብርና ረገድ የሚከተለው ፖሊሲ ትክክል ስላልሆነ ነው» በማለት የሚያቀርቡት ምክንያት ነው ። አብዮቱ

Digitized by Google

ያንብርና ረገድ የወሰደው እርምጃና የቀየሰው ስልት ገበሬውን ከገባርነት ለማላቀቅና የመሬት ባለመብት ለመሆን ያስቻለው መሆኑን ማንም ሊክድ አይችልም። ዛሬ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ መሬትም ሆነ ሌሎች ከፍተኛ የኢኮኖሚ ለውታርች የሠርተአደሩ ሕዝብ ንብረት በመሆናቸው ለሕዝብ መበደል ዋንኛ ምክንያቶች የነበሩት ሁኔታዎች ተወግደዋል። እርገጥ በተረከብነው የኋላቀርነት ጠንቅና የአብዮቱ ጠላቶች በሚፈጥሩት ችግር ምክንያት የተፈለገውን ያህል ለመራመድ አልተቻለም። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በድርቅ ምክንያት ሀድገትን የሚፈታተን ሌላ እንቅፋት መፈጠሩ ገልጽ ነው። ነገር ግን ለብዮቱ የእነዚህ ዕድገትን የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች ሁሉ ምንጭ ሳይሆን ይልቁንም የሚያስወግድና ለሠርተአደሩ ሕዝብ እኩልነትና ብልጽግና መረጋገጥ የቆመ ነው።

በገሐድ እንደሚታየው ሠርተአደሩ ሕዝብ ከኋላቀርነት ማጥ ውስጥ ለመውጣት የሚያስችለውን ንቃትና ድርጅታዊ ብቃት እያዳበረ እንዲመጣ ለብዮቱምቹ ሁኔታ ፈጥርለታል። ከበዝባዦችና ከጨቋኞች የግፍ ቀንበር በማላቀቅ የአገሩ ባለቤትና የራሱ ዕድል ወሳኝ የመሆን መብት አቀዳጅቶታል። ይህ ባይሆን ኖር ዛሬ በድርቅ ምክንያት ለከፋ ሁኔታ የተጋለጡትን ወገኖቻችንን ለመርዳት ብሔራዊ አቅማችን ሁሉ ወደዚያ እንዲያተኩር ለማድረግ ባልተቻለ ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ በድርቁ የተጉዱ ዜጎቻችንን ከሚገኙበት ሥፍራ አንቀሳቀሶ ለም ወደሆኑ የአገራችን ክፍሎች በማዛዋወር መልሶ ለማቋቋም ፍፁም ባልተሞከረ ነበር። እነዚህ ተጨባጭ ሁኔታዎች እንደሚመሰክሩት የአብዮቱ ተልዕኮ ያለጥርጥር ሕዝባዊ ልዕልናንና ዕድገትን ማስገኘት ነው። በዚሁ ዓላማ መሠረት ባካሄድነው ትግል ዛሬ ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ዕውን የምትሆንበት ዋዜማ ላይ እንገኛለን።

ቀንደኛ ኢምፔሪያሊስቶች፣ አድኅርትና ምንደኞቻቸው ሁካታ የሚያበዙትና ለጥፋት ድርጊት የሚሯሯጡት ይህንን ታሪካዊ ክንውን ለማደናቀፍ በመሻት መሆኑ ገልጽ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሠርተአደር ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣንን ሙሉ በሙሉ በእጁ አድርጉ በማናቸውም የማኅበራዊ ሕይወት መስክ የዕድሉ ወሳኝ የሚሆንበትን ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን ለማየት የሚሻ ዜጋ ሁሉ ለጊዜያዊ ችግር ሳይበገር ወሳኙን ምዕራፍ በአሸናፊነት ለማለፍ ጠንክር መታገል ይኖርበታል። ያለትግልና ያለመስዋዕትነት የተቀዳጀነው ድል እንዳለመኖሩ ሁሉ ለወደፊቱም በምኞት ብቻ የምናገኘው ነገር ይኖራል ብለን ልንጠብቅ አንችልም። ይልቁንም እስከዛሬ ከፍተኛ የመስዋዕትነት ዋጋ የከፈልንባቸው ድሎቻችን ፍፁም የጸና መሠረት የሚይዙበት ዋዜማ ላይ የምንገኝ እንደመሆናችን ከመቼውም ይልቅ በርትተን መታገል ይኖርብናል። በሁሉም መስክ የፓርቲያችንን ፕሮግራምና መመሪያዎች በተግባር ለመተርጉም ያልተቀጠበ ጥረት እስካደረግን ድረስ ጊዜያዊ ችግሮችን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰባችን ከኋላቀርነት ጨርሶ መላቀቅና የዕድገት እርምጃውም መፋጠን ዋስትና ይኖረዋል። ስለዚህ ጊዜያዊ ችግርን የመቋቋም እንቅስቃሴያችንን የዘልቄታ ዓላማችንን በተግባር ከመተርጉም ነጥለን ሳናይ ለአጥጋቢ ውጤት የጋራ ጥረትን ከፍ ማድረግ የወቅቱ የአብዮታችን ጥሪ ነው።

Digitized by Google

በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የሶሻሊዝም መሠረት ግንባታ

— አሰፋ ሀብቴ
— ተክለ ብርሃን ገ/ሚካኤል
— ታደለ ገብረ ሕይወት

የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ በሽግግር ወቅት

የሽግግር ወቅት ባሕርይ

ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ወዲህ በ1917 (እ.አ.አ) በሶቪየት ኅብረት ሶሻሊዝም እስከ ተመሠረተበት ጊዜ ድረስ በኅብረተሰቡ ዕድገት ታሪክ በተከሰቱት የመደብ ሥርዓት ማኅበራትና በተለይ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ካፒታሊዝምን በሚያራምዱ ሀገሮች ያለው ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ያሉት ማኅበራዊ ግንኙነቶች በብዙኃኑ ጭቁኖች ተበዝባዥነትና በጥቂቶቹ ጨቋኞች በዝባዥነት ላይ የተዋቀሩ ናቸው ። ይህ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት እስካለ ድረስ የሰው ልጅ የተሟላ መብትና ነፃነት ሊያገኝ አይችልም ። የብዝበዛው ምንጭ የምርት መገልገያዎች በግል ንብረትነት መያዝ ሲሆን ፣ የይዞታው ማስከበሪያና የመጨቆኛው መሣሪያ ደግሞ የበዝባዥ መደብ መንግሥት ነው ። ስለዚህ ብዙኃኑ ከብዝበዛና ከጭቆና ቀንበር ሊላቀቁ የሚችሉት የምርት መገልገያዎች የግል ንብረትነት ሲወገድና የመንግሥት ሥልጣን በሠራተኛው መደብ እጅ ሲገባ ብቻ ነው ። ይህ ደግሞ በአንድ ጊዜና በቀላሉ ሊገኝ የሚችል ሳይሆን ከፍተኛ ትግል ፣ መስዋዕትነትና የሽግግር ጊዜን የሚጠይቅ ነው ። በዚህ የሽግግር ወቅት የኢኮኖሚው መስክ አንዱና ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ የትግል ዘርፍ ነው ።

በመሠረቱ የሽግግር ወቅት ኢኮኖሚ የምርት ኃይሎች የግል ይዞታ ወደ ማኅበራዊ ይዞታ የሚለወጥበትን የትግል ወቅት ያመለክታል ። ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር በመራራ የመደብ ትግል የሚታለፍ ሲሆን ፣ በአጠቃላይ ጭቁኑ የሠራተኛና የአርሶ አደሩ መደብ በጨቋኝና በዝባዥ መደቦች ላይ በሶሻሊስት አብዮት ድል የሚቀዳጁበት ሂደት ነው ። በሽግግሩ ወቅት የግል ይዞታን የሕዝብ የማድረግና አነስተኛ አምራቾችን በኅብረት ሥራ ማኅበራት የማደራጀት ሂደት ይጠናቀቃል ።

Digitized by Google

ሽግግሩ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት እንደየሀገሩ ነባራዊ ሁኔታ ይለያል ። [1] አንድ ሀገር ሶሻሊዝምን ለመገንባት ሲጀምር የወቅቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ። ከእነዚህም ነባራዊ ሁኔታዎች ውስጥ የምርት ኃይሎች ያሉበት የእድገት ደረጃ ፣ የተፈጥሮ ሀብት ሁኔታና ሥራ አጥነትን ለማስወገድ ያለው ሁኔታ በተለይ የሚጠቀሱ ናቸው ። እንደዚሁም የሽግግሩ ወቅት አቢይ የኢኮኖሚ መመሪያ የግል ካፒታልን መውረስ፣ የሶሻሊስት ሥርዓትን መሠረት መጣልና መገንባት በመሆኑ ፣ በአጠቃላይ የዓለም አቀፍ ሁኔታ ፣ በተለይም የሶሻሊስት ሥርዓት ፣ ዓለምአቀፋዊ ሁኔታ ፣ በተፃራሪ ሥርዓቶች መሀከል ያለው ቅራኔ እና የትግል ፍልሚያ ሁኔታ ፣ የሽግግሩን ወቅት የትግል ስልት ከመቀየስ አኳያ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። እየከሰመ የሚሔደውን የካፒታሊስት ይዞታ በማስወገድ በአብዮቱ መጀመሪያ ጊዜ የሽግግሩ ኢኮኖሚ በሁለት መሠረቶች ላይ ይቆማል። ባንድ በኩል የሶሻሊስት ይዞታ ሲኖር በሌላ በኩል የአነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች በተለይም የገበሬዎች የግል ይዞታ ይኖራል ። በዚህ የሽግግር ወቅት ከሚቀየሰው የትግል ሥልት አኳያ የአነስተኛው አምራች ዘርፍ የግል ንብረት የማይወረስ ስለሆነ በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር እየተደራጀ ሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነትን ያዳብራል ።

በመሆኑም በግብርናው ዘርፍ የተሠማራው አርሶ አደር በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ይደራጃል ። ገበሬው እየነቃ በፈቃደኝነት በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር እስኪደራጁ ድረስ የግል ይዞታውን እንደያዘ ይቆያል ። ስለሆነም አብዮታዊ መንግሥት ከሽግግር ወቅት ኢኮኖሚ መመሪያው ጋር በሠመረ ድርጅታዊ አሠራር እየተጠቀመ ገበሬውን በማንቃት በዘመናዊ የእርሻ ዘዴ እንዲጠቀም እያደረገ በገዛ ፈቃዱ የኅብረት ሥራ ሕዝባዊ እንቅስቃሴው የነቃና የበቃ ተሳታፊ እንዲሆን ያደርገዋል ። የግብርናውን ዘርፍ ግንባታ ለማፋጠን አብዮታዊ መንግሥት የኢኮኖሚ ድጋፍ መስጫ ሥልት ይቀይሳል ። ይኸም ግብር በመቀነስ ፣ ለድጉማ የሚሆን ገንዘብ በመመደብ ወዘተ ነው ። በዚህ አኳያ መንግሥት ሁለት ዓይነት የዋጋ ተመን ያወጣል። ይኸውም ባንድ በኩል የገበሬ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የማምረቻ መሣሪያዎችን በቅናሽ ዋጋ እንዲገዙ ሲያደርግ ፣ በሌላ በኩል አምራች ማኅበራቱ ለመንግሥት ለሚሸጡት የእርሻ ምርት ለአፈሰሱበት ጉልበት ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲከፈላቸው አርሶ አደሩን በኅብረት ከማደራጀት ጎን ያገሪቱን ታኅታይ መዋቅር ለመገንባት ፣ ለግብርና ምርት ሥርጭት አስፈላጊ የሆኑትን ቴክኒካዊ መሠረቶች ዘመናዊ ለማድረግና በአጠቃላይም የግብርናና የኢንዱስትሪ ግንባታ ሂደትን ለማፋጠን አብዮታዊ መንግሥት ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ ይመድባል። ባጭሩ በሽግግሩ ወቅት እንዱስትሪንና ሰፋፊ እርሻዎችን የመንግሥት ማድረግ፣ አነስተኛ አምራቾችን በኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጀት ፣ ኢኮኖሚውን በእቅድ መምራት ዓይነተኛ ስልቶች ናቸው ።

በዚህ ጽሑፍ ወደፊት እንደሚገለጸው አብዮታዊት ኢትዮጵያም እስካሁን ድረስ የተከተለችው ስልት ከሞላ ጎደል ከዚህ በላይ የተመለከተውን የሽግግር ወቅትን ሂደት የሚያንጸባርቅ ነው ። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያሉ ዋና ዋናዎቹ የኢኮኖሚ ይዞታዎች የመንግሥት ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበር ፣ የአነስተኛ ካፒታሊስት ፣ የአነስተኛ ሸቀጥ አምራቾችና ከእጅ ወደአፍ የሆነ ኑሮ ለመኖር ብቻ የሚያስችል ኋላቀር ተፈጥሮአዊ የኢኮኖሚ ይዞታ ናቸው ። በዚህ ሁኔታ መስፋፋትና መዳበር ያለባቸው መንግሥታዊና ማኅበራዊ ወይም ሕዝባዊ ይዞታዎች ናቸው ። በመሆኑ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የመንግሥት ሰፋፊ እርሻዎችና የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን በስፋትና በጥራት የማደራጀቱ ተግባር ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሠረታዊ ጉዳይ ነው ።

Digitized by Google

የግብርና ዘርፍ ሁኔታ

በኢትዮጵያ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በሀገሪቱ የሶሻሊስት ኢኮኖሚን መሠረት ለመጣልና ብሎም ለመገንባት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ዘርፍ ነው ። ታዲያ ይህ ወሳኝ ቦታ የያዘን የኢኮኖሚ ዘርፍ ኢትዮጵያ ካላት ሰፊና ለም መሬት አንፃር ምን ያህል ተንቀ ሳቅሷል ? ምን ያህልስ ይቀረዋል ? የሚለው ጥያቄ ሊነሣ ይገባል ።

የኢትዮጵያ ጠቅላላ የመሬት ስፋት 122.4 ሚሊዮን ሄክታር ይሆናል ። ከዚህ ውስጥ 13.8 ሚሊዮን ሄክታር ወይም 11.3% ለቋሚና ዓመታዊ ሰብሎች ፣ 65.2 ሚሊዮን ሄክታር ወይም 53.3% ለግጦሽ ፣ 8.9 ሚሊ ዮን ሄክታር ወይም 7.3% ለደንና ቁጥቋጦ የሚውል ፣ 12.1 ሚሊዮን ሄክታር ወይም 9.9% በሐይቆችና ወንዞች የተሸፈነና ረግ ረግማ መሬት ሲሆን ፣ በጠቅላላው 23.3 [2] ሚሊዮን ሄክታር ወይም 18.2% ለአንዳችም ዓይነት ጥቅም እንደማይውል ይገመታል። በአጠቃላይም ካለው 122.4 ሚሊዮን ሄክ ታር ውስጥ ቢያንስ 84 ሚሊዮን ሄክታር የሚሆነው ለግብርና ሥራ ተስማሚ እንደሆ ነና ከዚህም ውስጥ በእሁኑ ወቅት 13.8 ሚ ሊዮን ሄክታር የሚሆነው ብቻ ለልዩ ልዩ አዝርእት የዋለ መሆኑ ይገመታል ። ማለት ም ከ70 ሚሊዮን ሄክታር በላይ የሆነ ለእ ርሻ የሚስማማ መሬት ገና አልተነካም ። ለእርሻ ከሚውለው መሬት ውስጥ በተለ ያየ ምክንያት 3.5 ሚሊዮን ሄክታር ጦም የሚያድር ነው ። በመሆኑም በየዓመቱ ልዩ ልዩ እህል ለማምረት የሚታረሰው መሬት ስፋት ከ5.4 እስከ 5.6 ሚሊዮን ሄክታር ድረስ ብቻ ነው ።[3] እንዲሁም በተለያዩ የኢ ትዮጵያ ሸለቆዎች አካባቢ 3 ሚሊዮን ሄክ ታር የሚገመት ለመስኖ እርሻ የሚሆን መሬት ያለ ሲሆን ከዚሁ የለማው 100ሺ ሄክታር ያህሉ ነው ።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የእንስሳት ሃብት ያላት ሀገር እንደመሆኗ 27 ሚሊዮን የዳልጋ ከብት ፣ 42 ሚሊዮን በግና ፍየል በአጠ ቃላይ ብዛቱ 70 ሚሊዮን ያህል የእንስሳት ሃብት እንዳላት ይገመታል ። ኢትዮጵያ በዓለም በእንስሳት ሀብት ቀዳሚ ከሆኑት 10 አገሮች ውስጥ አንዷ ስትሆን በአፍሪቃ አንደኛ ናት ። በሀገሪቱ ያለው የእንስሳት ሀብት በአብዛኛው የገበሬው ይዞታ ነው ለማለት ይቻላል ።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የዓሣ ሀብትም ያላት ሀገር ናት ። በቀይ ባሕር ፣ በሐይቆችና ወን ዞች ከሚገኘው የዓሣ ሀብት ክምችት ብቻ በዓመት ከ92 እስከ 120 ሺህ ቶን ሊመረት እንደሚችል ይገመታል ። በተለይም በቀይ ባሕር ውስጥ ለእንዱስትሪና ለገበያ የሚ ሆኑ ዓሣዎች በብዛት እንደሚገኙ ይታወ ቃል ።

የዘላኑ ክፍል በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከፍ ተኛ ሚና አለው ። ሁለተኛው የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኳሚቴ መደበኛ ስብሰባ ዘላኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሀገሪቱ ብሔራዊ ኢኮ ኖሚ ጋር መዋሐድ እንዳለበት በወሰነው መሠረት አብዮታዊው መንግሥት የዘላኑን ዘርፍ በማስጠናት ላይ ይገኛል ። እስካሁን ከተገኘው ጥናት መረዳት እንደሚቻለው የዘላኑ ሕዝብ ብዛት ሦስት ሚሊዮን ያህል እንደሚሆን ይገመታል ። የዚህ የዘላኑ ሕዝ ብ ኑሮ በጎሳ የተሳሰረ ጥንታዊ የጋርዮሻዊ የምርት ግንኙነት ባህርያት የሚያንጸባርቅ በመሆኑ ከግላዊ ይልቅስ ማኅበራዊ ባህሪው ያመዝናል። ስለሆነም ማርክስና ኤንግልስ የ ጥንቱ የገበሬው ጋርዮሻዊ ማኅበር (peasant commune) ከመፍረሱ በፊት የሶሻሊስት አብዮት የተከሰተ እንደሆነ እነዚህ ጋርዮ ሻዊ ባህሎች ለአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር መቋቋምና ለዲሞክራሲያዊ አስተ ዳደር አመቺ ይሆናሉ [4] ያሉትን ከሀገራችን ዘላን ሕዝብ ኑሮ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማገ ናዘብ ተገቢ ይሆናል ። እንደዚህ የመሳሰሉ የጋራተኝነት ባህሎችና ድርጅታዊ ገጽታ ዎች ማለትም መሬት የጋራ መሆን ፣ በጎ ሳው ከፍተኛ የትብብር ባህል መኖር ወዘተ ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የሚረዱ አመቺ ገጽታ አላቸው ። [5]

Digitized by Google

ዘላኑ ሕዝብ ከሀገሪቱ የከብት ሀብት ርቢ ከግማሽ በላይ ወይም 52% ያህል ያረባል ። በመሆኑም ዘላኑ ለግብርናው ዘርፍ ኤኮኖሚ የእርሻ በሬ በብዛት የሚያቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በአጠቃላይ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ከ60% እስከ 70% ድረስ ከብት እንደሚያቀርብ ይገመታል ። የዘላኑ ዘርፍ በአብዛኛው በጠረፍ አካባቢ የሚገኝ እንደመሆኑ በሀገር ውስጥ ከሚሸጠው ይልቅስ በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ የጠረፍ ገበያዎች የሚጉርፈው ከብት እንደሚበዛ ይታወቃል ። ይህም ሀገሪቱ በዚህ ዘርፍ ልታገኝ የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ ምን ያህል ሊጎዳ እንደሚችል በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል ።

ዘላኑ ሕዝብ ዘመናዊ ሥልጣኔ ከሚያስገኘው ጥቅም ተገልሎ ስለሚኖርና በተለይም በዘመናዊ እንስሳትን የማዳቀል ርቢ ስለማ ይጠቀም የከብት እርባታው ውጤት ዝቅተኛ ነው ። እንዲሁም የከብት ሕክምና ፣ የገበያ፣ የመገናኛ የጤናና የትምህርት አገልግሎት የተፈለገውን ያህል አለመስፋፋት ፣ የግጦሽና የውኃ ሁኔታ አስተማማኝ አለመሆን ፣ በአጠቃላይም የዘላኑ ሕዝብ ከሀገሪቱ ኤኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ኑሮ ጋር በሚገባ አለመዋሐዱ ብዙ ጊዜ ለተፈጥሮና ለሰው ሠራሽ ችግሮች እንዲጋለጥ አድርጐታል ።

የተደረጉ ጥረቶችና የተከሰቱ ችግሮች

ከዚህ በላይ የቀረበው የግብርናው ዘርፍ ያለበትን ሁኔታ ባጭሩ ያመለክታል ። ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ ለሶሻሊስት ስልተ ምርት ምሥረታና ግንባታ የሚበጁና መሠረት የሚሆኑ ልዩ ልዩ አዋጆችና ደንቦች ወጥተዋል ፤ መመሪያዎች ተቀይሰዋል ፤ ውሳኔዎች ተላልፈዋል ፤ ለዚህም ተግባራዊነት የሚያግዙ መዋቅሮች በየዘርፉ ተዘርግተው ተግባራዊ በመሆን ላይ ናቸው ።

ከነዚህ አብዮታዊ እርምጃዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል ።

—የገጠርን መሬት የሕዝብ ያደረገው አዋጅ ቁጥር 31/1967 ፣

—የቀበሌ ገበሬ ማኅበራትን ማደራጃና ማጠናከሪያ አዋጆች ቁጥር 71/1968 ፣ 130 እና 141/1970 ፣ 223/1974 ፣

—የሚያዝያ ወሯ 1968 የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መመሪያ ፤

—የከብት ገጠሽ ልማት እቅድ አዋጅ ቁጥር 83/1968 ፣

—የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 138/1970 እና በሰኔ ወር 1971 የወጣው የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መመሪያ ፣

—የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 156/1971 ፣

—የመንግሥት እርሻ ልማት በሚኒስቴር ደረጃ በ1971 መቋቋም ፣

—የሁለተኛው መለስተኛ የእርሻ ልማት ፕሮግራምና ማስፈጸሚያ አዋጆች ቁጥር 204 እና 205/1973 ፣

—የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 226/1972 ፣

—የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች ፣ የካቲት 1973 ፣

—የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ውሳኔዎች ፣ ታኅሣሥ 1975

—ከ1971 ጀምሮ በመካሔድ ላይ ያለው የመሠረተ ትምህርትና የባህል ዘመቻ ፕሮግራም ።

እነዚህም እስካሁን ድረስ የተከናወነውን ሲያመለክቱ ወደፊት ለሚካሔደውም የተግባር አቅጣጫ የሚቀይሱ ናቸው ።

ከዚህም በመነሳት ባሁኑ ወቅት የአሥር ዓመት እቅድን ለመዘርጋት በተግባር ለመተርጐም ቅድመ ሁኔታዎች በመመቻቸት ላይ ናቸው ።

Digitized by Google

በሽግግሩ ወቅት የግብርናው ዘርፍ ኢኮኖሚ ዋና ዓላማዎች

—የምግብ እጥረትን ማስወገድ ፣ ለአገር ውስጥ እንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ማቅረብና ለውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ምርት በብዛትና በጥራት ማምረት ፣

—በተበታተነ ቁርስራሽ የግል ይዞታ ላይ ያለውን ሰፊ አርሶ አደር በፈቃደኝነት በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ማደ ራጀት ፣

—ለገበሬ የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ምርት ማሳደጊያዎችንና ለፍ ጆታ የሚውሉ መሠረታዊ ሸቀጦችን ለገ በሬው በትክክል እንዲደርሰው ፣ ገበሬው ምርቱን ለገበያ እንዲያቀርብ የሚያስች ሉት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣

—ለኢኮኖሚ ግንባታው የሚያስፈልገውን ክምችት ማዳበር ፣

—ገበሬው በተሻሻለ የምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ማድረግ ፣

—የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት ለመንከባከ ብና ለማዳበር ለገበሬው የሚሰጠውን ትምህርትና ድጋፍ ማጠናከር ፣

—የመንግሥት እርሻ ምርታማነትን ከፍ ለማድረግ በሚያግዝ መልክ አደረጃጀ ታቸውና አመራራቸው ጥራት እንዲኖ ረው ማድረግ ፣

—የምርት ኃይሎችን ለማዳበርና በሳይን ስና ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሚያግዙ የምርምር ሥራዎችን ማስፋፋት፣

—የዘላኑ ኅብረተሰብ የልማት እንቅስቃሴ ከሀገሪቱ አጠቃላይ የልማት እቅድ ጋር ማቀናጀት ፣ በተለይም ለዘላኑ ሕዝብና ለከብቱ የውሃና የግጦሽ ሃብቱን መጠ በቅና ማልማት ፣

—የሀገሪቱን የደን ፣ የዱር አራዊት ፣ የአ ፈርና የውሀ ሀብት ልማት መንከባከብና ማዳበር ፣

—የእንስሳትና ዓሣ ሃብት ልማትን ማዳበር፣

—ሥራን በእቅድ መምራትና የመሳሰሉት ናቸው ።

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ኢትዮጵያ ከፍተኛና የተለያየ የተፈጥሮ ሀብት ያላት አገር ነች ። ግን በአንፃሩ መሬትና እንጨት ለእርሻ ፣ ለግጦሽና ለቤት ሥራ እየተመነ ጠረ ያገሪቱ ደንና የተፈጥሮ ሀብት በመራ ቆቱ ፣ የዱር አራዊቶቻችን ከመጠጊያ እጦት የተነሳ ወደ ጐረቤት አገሮች እንዲፈልሱ ፣ አፈርዋ በዝናብ ውሃ እንዲታጠብና ለም ነቷ እንዲቀነስ ፣ የግጦሽ እጥረት እንዲደር ስና የእንስሳት ሀብታችን እንዲመነምን እየተደረገ ነው ። በመሆኑም ጥቅም ሳይሰጥ የቆየ መሬትን ማልማት ያገሪቱን የእንስሳትና የዓሣ ሀብት ማዳበር፣እየመነመነ የመጣውን የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት መጠበቅና ማል ማት የወቅቱ ጥያቄ ነው ።

ኢትዮጵያ በአብዛኛው የቅድመ ካፒታ ሊስት ስልተምርት የሰፈነባት ሀገር ነች ። ይኸም ሁኔታ ለጥሪት ክምችት አለመዳበ በርና ለሕዝቡም የኑሮ ደረጃ መቀጨጭ እንዱና አቢይ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል ። የምርት ኃይሎች እድገት ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለሚገኝ ምርቱ ከእጅ ወደ አፍ ሆኖ በዚህ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ተወስኖ ይገ ኛል ። ከየካቲት 66 ወዲህም እንኳ አብዮቱ አርሶ አደሩን የቤቱና የመሬቱ ባለቤት ቢያ ደርገውም ሠርቶ አደሩ በአብዛኛው የዘል

Digitized by Google

ግድ አሠራሩን ገና አልለወጠም ። ከዚሁም የተነሳ በነፍስ ወከፍም ሆነ በኅብረት የሚ ያገኘው የምርት መጠን በጣም ዝቅ ተኛ ነው ። በዓመት የአንድ ገበሬ ቤተ ሰብ አማካይ የምርት ውጤት 11 ኩንታል ያህል ብቻ ሲሆን ፣ አማካይ የመሬት ይዞታ ስፋት 1.14 ሄክታር ገደማ ነው ።[6] የተቆራረጠ የመሬት ይዞት እንቅፋት ሆኖ የቆየ ነው ። በነዚህና በሌሎችም የእርሻ ክፍለ ኤኮኖሚ ችግሮች የኢትዮ ጵያ ገበሬ እስካሁን ድረስ ራሱን ፣ ቤተሰቡንና ካጠቃላይ የሀገሪቱ ሕዝብ 11.3 ያህል የሆነውን የከተማ ነዋሪ ሕዝብ በበቂ ለመመገብ አልቻለም ።

ለምግብ እጥረት የገበሬው የፍጆታ መጠን ከፍ ማለትና የመሬት ጦም ማደር በየፊና ቸው አስተዋጽኦ አድርገዋል ። በተጨማ ሪም ባለበት ዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን አርሶ አደሩ አንዳንድ ነገር ገና ስላልተሟላለት ምርቱን ለማሳደግ አልቻለም ። ይኸውም ለምሳሌ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክ ቱት ከሀገሪቱ ገበሬዎች ውስጥ 35% የሚ ሆኑት ምንም የእርሻ በሬ የሌላቸው ሲሆኑ, 30%የሚሆኑት ደግሞ አንድ በሬ ብቻ ያላቸ ው እንደሆኑ ይገመታል ።[7] ይህም ለምርት ዕጥረት አንዱ ምክንያት መሆኑ መገመት አያዳግትም ።

በሌላ በኩል ባለፉት አስር ዓመታት የሕዝቡ ቁጥር ባጣም እየጨመረ መምጣቱ ይገመታል ። ከዚህ የሕዝብ እድገት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የምርት እድገት ግን አይታይም ። በአማካይ የሕዝብ ዕድ ገት በዓመት 2.9% እንደሆነ ሲገመት[8] የም ርት ዕድገት ግን ይኸንን እንደማይመጥን ጥናቶቹ ይጠቁማሉ ።

በተጨማሪም ባሁኑ ወቅት የገበሬው ፍጆታ በማደጉ ለገበያ የሚቀርበው ምርት 14 ሚሊዮን ኩንታል ያህል ብቻ እን ደሆነ ይገመታል ።

በአጠቃላይ ሲታይ የምርት ኃይሎችን ዕድገት ከሚገቱ ችግሮች ዋናው እስካሁን ድረስ ያለው የተበታተነ የግል እርሻ ይዞታ ነው ። ይህም በተለይ ለእቅድ አሠ ራር ሆነ ለምርት እድገት እንቅፋት ነው ። በዚህ ሁኔታ ላይ ካለው አርሶ አደር የምርት እድገትና ክምችት መጠበቅ አስተማማኝ ነት ስለማይኖረው አስቸኳይና ዘላቂ መፍ ትሔ በመፈለግ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጆችና መመሪያዎች ወጥ ተው ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛሉ ።

ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠ ፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በየካቲት ወር 1973 ባቀረቡት ሪፖርት ፦

«. . . የሀገራችን ኤኮኖሚ ዛሬ በሚገኝ በት የእድገት ደረጃ ሶሻሊስት እንዱስትሪን ለማስፋፋት የሚያስፈልገው የጥሪት ክም ችት በአብዛኛው ከእርሻው ክፍለ ኤኮኖሚ ውጭ ማመንጨት እንደማይቻል ግልጽ ነው ። ስለዚህ እንዱስትሪን ለመገንባትም ሆነ በአጠቃላይ የምርት ኃይሎችን ለማዳ በር ለእርሻው ዘርፍ ዕድገት ቅድሚያ ትኩ ረት መስጠት እንዳለብን አያጠያይቅም ። ሆኖም እርሻችን ዛሬ በሚገኝበት የተበታተ ነና ኋላቀር ሁኔታ ዕድገቱን ለማፋጠንና የእንዱስትሪ ግንባታ የሚጠይቀውን የጥሪ ት ክምችት ለማፍራት እንደማይችል ግልጽ ነው ። ገበሬው በነፍስ ወከፍ በያዘው ማሳ የግብርናውን ክፍለ ኤኮኖሚ ለማዳበር ይች ላል ማለት ዘበት ነው ።

Digitized by Google

«በተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎች በመጠቀምና ቴክኖሎጂን በገጠር በማስፋፋት የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ የምርት ውጤት ለማሳደግ በመጀመሪያ የገበሬው ይዞታ ለከፍተኛ ምርት ከንዋኔ በሚያመች መልክ መመደራጀት አለበት ። ...ይህንንም ለማድረግ የምርት ግንኙነቱ መለወጥ አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው ። ሰፊ የሆነውን የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ወደ ከፍተኛ የምርት ደረጃ ለማሸጋገርና በገጠርም ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚቻለው የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማስፋፋት ብቻ ነው ። የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚያስገነዝበን የዕድገታችን መፋጠን የሚወሰነው በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋት እንደመሆኑ ፣ ከእንግዲህ ዋንኛው የልማት ስትራቴጂያችን ቅድሚያ ትኩረት በገበሬዎችና የዕደጥበብ ባለሙያዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ላይ መሆን ይኖርበታል ።»[9]

ሲሉ የገለጹት በግብርናው ዘርፍ በተለይ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ዐበይ ነጥቦችን የሚያስገነዝብ እጅግ ወቅታዊ መመሪያ ነው ።

የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ የግብርናው ዘርፍ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ምርት የ46.7% ከጠቅላላው የውጭ ንግድ 90% ድርሻ ያለውና ከሀገሪቱ አምራች የሰው ኃይል ውስጥ ለ85% ያህል የመተዳደሪያ ምንጭ በመሆኑ ባለፉት የአብዮት ዓመታት የተካሔደው የልማት ተግባር በገጠር ግንባታ ላይ ያተኮረ መሆኑን ይገልጣል ። [10]

ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ የዕቅድ አሠራር እስከተዘረጋበት እስከ 1971 ድረስ ካለው የግል ይዞታና ከነበረው የከረረ የመደብ ትግል የተነሳ ምርት ዝቅ እያለ መጥቶ እንደነበረ ይታወሳል ። ለምሳሌ የዋና ዋና ሰብሎች ምርት ፣

በ1968	55	ሚሊዮን	ኩንታል
በ1969	53	»	»
በ1970	47	»	»

ነበር ። አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ከተቋቋመ ወዲህ ግን ፣ በተለይም አጣዳፊና አንገብጋቢ ችግሮችን በዘመቻ መልክ ለማስወገድ በርካታ እርምጃዎች በመወሰዳቸው ፣ በአጠቃላይ መጠነኛ የምርት ዕድገት ታይቷል ። ጠቃሚ የዕቅድ አሠራር ልምድም ተገኝቷል ። ከዘመቻ አንድ ጀምሮ እስከ ዘመቻ አምስት ማለትም ከ1971/1972 እስከ 1975/1976 ድረስ የተገኘው ውጤት የተጠበቀውን ያህል ባይሆንም የወደፊቱ እቅዶች የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኙ ያስተማምናል ። የግል ይዞታ የሰፈነበትን የግብርና ኢኮኖሚ በእቅድ መሥራት በጣም አስቸጋሪ ነው ። ቢተለይም ለገበሬው አስፈላጊ የሆኑትን የልማት አገልግሎቶች ለእያንዳንዱ ገበሬ ማዳረስና ምርቱን እንዲጨምር ማስቻል ቀላል አይደለም ። በግል ከሚያመርተው አርሶአደር በተጨማሪ የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር እና የመንግሥት እርሻዎች እየተስፋፉ ከዓመት ዓመት ምርትና የሥራ ልምድ እያዳበሩ ነው ። ይኸውም ሲባል ከታቀደውና ከተጠበቀው አኳያ ያስገኙት ውጤት አነስተኛ መሆኑን መረዳት ይገባል ። ስለሆነም ከ1971 ጀምሮ እስከ 1975 ድረስ የነበረው የይዞታ ሁኔታ ቀጥሎ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል ። [11]

Digitized by Google

ከ1971 – 1975 የታረሰው መሬት በዓይነቱ ይዞታ

መጠን /በሺህ ሄክታር/ የተገኘው ምርት መጠን/ በሺህ ኩንታል

ተራ ቁ.	ይዞታ	1971		1972		1973		1974		1975	
		የዘራ መሬት/ ሄ./	የተገኘ ምርት /ኩ./	የዘራ መሬት/ ሄ./	የተገኘ ምርት /ኩ./	የዘራ መሬት/ ሄ./	የተገኘ ምርት /ኩ./	የዘራ መሬት/ ሄ./	የተገኘ ምርት /ኩ./	የዘራ መሬት/ ሄ./	የተገኘ ምርት /ኩ./
1	የግል እርሻ	5,927.21 97.4%	47.482.93 96.7%	6,187.25 97.2%	74,726.42 /96.7%	6,004.92 95.4%	65,254.54 94.1%	5,918.89 93.9%	62,093.96 93.2%	6,200 95.4%	68,800 94.2%
2	መንግሥት እርሻ	158.59 2.6%	1,600.52 3.3%	148.85 2.3%	2,370.11 3.1%	238.28 3.8%	3,555.21 5.1%	247.66 4.[illegible]%	3,733.05 5.6%	212.7 3.3%	3,406.7 4.7%
3	የኅብረት ሥራ ማኅበራት እርሻ	–	–	–	–	7.44 0.1%	196.97 0.3%	26.43 0.4%	412.94 0.6%	42.1 0.6%	499.1 0.7%
4	የሠፈራ እርሻ	–	–	27.79 0.4%	146.71 0.2%	44.07 0.7%	317.31 0.5%	46.29 0.7%	359.98 0.5%	35.8 0.6%	335.5 0.6%
	ጠቅላላ ድምር	6,085.80	49,083.45	6,363.89	77,243.24	6,294.71	69,324.03	6,239.27	66,654.93	6,495.6	73,041.3

Digitized by Google

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የመ
ንግሥት እርሻ ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትና
የሠፈራ እርሻ ይዞታ አሁንም ገና በዝቅ
ተኛ ደረጃ ላይ ናቸው ። ይሁን እንጂ በአጠ
ቃላይ መጠነኛ እድገት እያሳዩ እንደመጡ
ግን መረዳት ይቻላል ። በ1971 ከጠቅላላው
የእርሻ መሬት ይዞታ ውስጥ የመንግሥታዊ
ይዞታ 2.6% ሲሆን የግል ይዞታ 97.4%
ነበር ። በ1975 ግን የመንግሥታዊ ፣ የኅብ
ረት ሥራ ማኅበራትና የሠፈራ ይዞታ በአ
ንድ ላይ ወደ 4.6% ከፍ ሲል የግል ይዞታው
ደግሞ ወደ 95.4% ዝቅ ሊል ችሏል ።

ምርትን በሚመለከት በ1971 የመንግ
ሥት እርሻ ምርት ከጠቅላላው ምርት 3.3%
የነበረ ቢሆን የግል እርሻ ምርት ግን 96.7%
ነበር ። ይሁን እንጂ በ1975 የመንግሥት
እርሻ ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትና የሠፈራ
ምርት በአንድነት 5.8% ሲሆን የግል
እርሻ ምርት ድርሻ ወደ 94.2% ዝቅ ሊል
ችሏል ።

በአብዮቱ የተደራጁና በግብርናው ዘርፍ
ለሶሻሊስት ግንባታ አመቺ ሁኔታ የፈጠሩ
የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት፣የአገልግሎትና የአ
ምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሲሆኑ፣
ሌሎቹ የመንግሥት እርሻዎች ይገኙበታል።

በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተደ
ራጁና የተጠናከሩ 19,867 የቀበሌ ገበሬ
ማኅበራት ሲኖሩ በነዚህ ውስጥ 5.5 ሚሊ
ዮን አባል ገበሬዎች ታቅፈዋል ። የቀበሌ
ገበሬ ማኅበራት በአስተዳደር ፣ በአብዮት
ጥበቃ ፣ በፍትህ ፣ በድርጅታዊና ፖለቲካ
ሥራ ከማሳተፍም ሌላ ለአባል ገበሬዎች
ከባንክ የሚሰጥ ብድርን እንዲሁም ከመን
ግሥታዊ ድርጅቶች የሚሰጡ የምርት ማሳ
ደጊያዎች ለአባል ገበሬዎች በማሠራጨት
ከኢኮኖሚ ልማት ሥራ ጋር የተያያዙ ተግ
ባሮችን ያከናውናሉ ። እነዚህ ማኅበራት
በግል የሚያርሰውን ገበሬ በአምራቾች
ኅብረት ሥራ ማኅበር እንዲደራጁ ለማድ
ረግ ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ
ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ።

በሌላ በኩል በአሁኑ ጊዜ 17,204 የቀ
በሌ ገበሬ ማኅበራትን ያቀፉና ለ4.5 ሚሊ
ዮን አባል ገበሬዎች ግልጋሎት የሚሰጡ
156 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያላቸው 3,913
የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ
ማኅበራት ሲኖሩ ከነዚህም 1,040 ሕጋዊ
ሰውነት ያገኙ ናቸው ። እነዚህ ማኅበራት
በ1975 አንድ ሚሊዮን ብር፣ በ1976 ደግሞ
873,000 ብር ለአምራቾች ኅብረት ሥራ
ማኅበራት ያበደሩ ሲሆኑ በተለይም የንግ
ዱን ዘርፍ ሶሻሊስታዊ ለማድረግና በገጠርና
በከተማ የተስተካከለ የሸቀጥ ልውውጥና
ሥርጭት እንዲኖር የሚረዱ ተቋማት
ናቸው ። በመሆኑም በ1974፣105 ሚሊዮን
ብር እንዲሁም በ1975፣112 ሚሊዮን ብር
የሚያወጣ ሸቀጥ ገዝተው ለአባሎቻቸው
አከፋፍለዋል ። ማኅበራቱ በተለይ ለአባሎ
ቻቸው የገበያ አገልግሎት በመስጠት
ሸቀጣሸቀጥና የምርት ማሳደጊያዎችን በግ
ቅረብ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። ሆኖም
አሁንም ቢሆን በአገልግሎት ኅብረት
ሥራ ማኅበራት አንዳንድ ችግሮች ይታያሉ።
ለምሳሌ ለገበሬው የሚቀርብ የመሠረታዊ
ዕቃዎችና የሌሎች ሸቀጦች እጥረት አለ።
ሌላው ችግር ፣ ገበሬው ምርቱን ለአገልግ
ሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት በዱቤ ከሰጠ
በኋላ የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት በወቅቱ
ገንዘቡን ከፍሎ እህሉን ስለማይረከብ ባንድ
በኩል በገበሬውና በአገልግሎት ማኅበራቱ፣
በሌላ በኩል በአገልግሎት ማኅበራቱና በእ
ርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት መሃል የአሠራር
ችግር ሲፈጠር ይታያል ። ለዚህ የክፍያ
ስምምነቶችን ማክበርና የሚፈለገውን ክፍ
ያ ሳይዘገዩ በወቅቱ እንዲከናወኑ ማድረግ
ችግሩን ለማቃለል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደ
ርጋሉ ።

የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅ
በራትን በሚመለከት መመሪያው ከወጣ
ጀምሮ እስካሁን ድረስ 992 በማልባ ፣ 497
በወልባ ደረጃ የተደራጁ በድምሩ 1,489 አም
ራች ማኅበራት ተቋቁመዋል ። እነዚህም

Digitized by Google

94,368 አባላት ፣ 213,085 ሄክታር የመሬት ይዞታ ያላቸው ሲሆን ከዚሁ የሰማው መሬት 165,407 ሄክታር እንደሆነ ይገመታል። ማኅበራቱ በ82,166 በሬዎች በ960 ፈረሶችና በ76 ትራክተሮች ይጠቀማሉ ። ይህም በተደራጁ የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ውስጥ 74% አምራች ማኅበራት እንዳሉና፣ ይሽም 1.7% የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት አባላትን እንደያዘ ያሳያል ።[12] የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተለይ በሥራ አመራርና ሂሳብ አያያዝ ችግር ይገጥማቸዋል ። ለምሳሌ እያንዳንዱ አባል በሬውን ጠምዶ መሰማራቱን እንጂ በውል የሚያርሰው አባል ከማያርሰው ጋር ተነጻጽሮ ነጥብ ለመስጠት ለቡድን መሪዎች አስቸጋሪ በመሆኑ የነጥብ አሰጣጡ በአብዛኛው በሰዓት ላይ ያተመረኰዘ ነው ። ይህም አንድ ቡሥራ ለቆየበት ሰዓት በደፈና ነጥብ የሚሰጥ በመሆኑ ጉበዝና ሰነፉን በግልጽ በነጥብ መለየትን አስቸጋሪ ያደርገዋል ። በመሆኑም ትጉህና ታታሪ የሆኑ አባሎችን ስለማይገፋፋ ምርታማነት አይዳብርም ። ሥራዎችን እንደየ ባሕርያቸው በመከፋፈል ለማቀናጀትና ለማዳደራጀት የእርሻ መሬት ተሸንሽኖ መታወቅ ይኖርበታል ። ስለሆነም ለተደራጁት የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የመሬትን መጠን መለካትና የመሸንሸን ሥራ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ከማኅበራት መደራጀት ጋር አብሮ ሊራመድ አለመቻሉ ችግር ሆኖ ይገኛል ።

የማኅበራት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ባለመያዙ ምክንያት ሂሳባቸው የተመረመረ ማኅበራት ሁሉ የገንዘብ ጉድለት ይታይባቸዋል ። ለዚህ ጉድለት የተለያየ ምክንያት ቢኖርም ዋናው ግን ሥርዓት ያለው የሂሳብ አያያዝ ዘዴ ካለመከተል የሚመጣ ነው ። የሂሣብና ንብረት ጉዳይ በዘልማድ የሚሠራ በመሆኑ ለገንዘብ ጉድለትና ለንብረት መዝረክረክ መንገድ ከፍቷል ። ማኅበራት የሠለጠኑ ሙያተኞችን ቀጥሮ ለማሠራት አቅማቸው ውሱን በመሆኑ፣ የገበሬ ተወካዮችንም በቅርብ ሆኖ ድጋፍ ለመስጠት ከማኅበራት ቁጥር ጋር የተጣመደ በቂ የሰው ኃይል ካለመኖሩ የተነሳ የማኅበራት አመራርና ሂሳብ አያያዝ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ።

ከ70 ሚሊዮን ሂክታር በላይ የሆነ ጨርሶ ያልተነካ ድንግል መሬት ያላት ሀገራችን ራስዋን ሙሉ በሙሉ ለመመገብ ስላልበቃች በዕርዳታም ሆነ በግዥ እህል ከውጭ ማስመጣት ተገዳለች ። ሌላው ቀርቶ በዓመት ሁለት ሶስት ጊዜ ሊመረትበት የሚችል ለም መሬት የሚገኝባቸው አንዳንድ ክፍላተ ሀገር እንኳ ራሳቸውን መቻል እያቃታቸው እህል ከሌላ ሥፍራ እንዲቀርብላቸው እየተደረገ ነው ። ሀገራችን ሰፊ ላም መሬትና ከፍተኛ የሰው ኃይል ያላት ብትሆንም የድርቅ መስፋፋት፣ የሀገሪቱ የቴክኖሎጂ ደረጃ ዝቅተኛ መሆን ፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ፣ የሥራ ምርታማነትና የምርት አደረጃጀት ዝቅተኛነት ራስዋን አላስቻላትም ።

እዚህ ላይ ስለምርታማነት በመጠኑ ማብራራት ተገቢ ይሆናል ። ምርታማነት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚመረተውን ምርት ከተሰማራው የሰው ኃይል ወይም ካፒታል ወይም ከታረሰው መሬት ጋር በማዛመድ የሚገኝ የውጤታማነት መለኪያ ነው ።[13] በዚህም መሠረት ለምሳሌ በአንድ አምራች ድርጅት በቀን 8 ሰዓት እየሠራ የሚመረተው ጠቅላላ ምርት በሠራተኞች ቁጥር ሲከፈል እያንዳንዱ ሠራተኛ በቀን በነፍስ ወከፍ የሚያመርተው የምርት መጠን የሠራተኛ ምርታማነትን ያመለክታል ። በተመሳሳይ መንገድ በተወሰነ የሰብል ወቅት ከአንድ ሄክታር መሬት የሚገኘው ምርት የመሬት ምርታማነትን ይጠቁማል ። ምርታማነትን ከሚወስኑት መካከል የሰው ኃይል ፣ የትምህርትና ሥልጠና ደረጃ የማምረቻ መሣሪያዎችና የምርት ማስፋፊያዎች መጠን የቴክኖሎጂ ደረጃና የአስተዳደርና የአሠራር ሥልቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።[14]

ስለሆነም ባሁኑ ጊዜ ዘመናዊ የእርሻ ቴክኖሎጂን ለገበሬው በተግባር ለማሳየትና

Digitized by Google

ለማስተማር እንዲቻል በሠርቶ ማሳያ ጣቢ
ያዎችና በገበሬ ማሳዎች ላይ ብዙ ሙከራ
የተደረገ ቢሆንም ከንውኑ አሁንም ገና በዝ
ቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ። በተለይም ለአ
ብዛኛዎቹ ሠርቶ ማሳያ ቅርብ ወይም አዋ
ሳኝ በሆኑ የገበሬ ማሳዎች ላይ እንኳ በተሻ
ለ የእርሻ ዘዴ የመጠቀም ሁኔታ ጉልቶ
አይታይም ። የአዝርዕት ምርትን ለማሳደግ
በቀላሉ በአገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ
የምርት ማሳደጊያዎች የማዳበሪያ ፣ ምርጥ
ዘር ፣ ፀረ-ተባይ ወዘተ --- አጠቃቀም
ገና ዝቅተኛ ነው ። እንዲያውም ለምሳሌ
ለልዩ ልዩ አዝርዕት ከሚውለው መሬት
ውስጥ ማዳበሪያ የሚያገኘ 7% ብቻ ሲሆን፣
ምርጥ ዘር የሚያገኘ ደግሞ 1% ብቻ እንደ
ሆነ አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ ።[15]

ከሚመረተው ምርጥ ዘር ከፍተኛው ድር
ሻ የሚደለደለው ለመንግሥት እርሻ ሲሆን
ከሀገሪቱ የእርሻ ምርት ከፍተኛውን ድርሻ
ይዞ ለሚገኘው አርሶ አደር ሲቀርብ የቆየው
የምርጥ ዘር ድርሻ ግን ከሚመርተው ከ2%
በልጦ አያውቅም ። ገበሬው በየዓመቱ 2.3
ሚሊዮን ኩንታል በሚገመት ዘር ይጠቀ
ማል ። በዚህ ውስጥ እላይ እንደተመለከተው
የምርጥ ዘር መጠን 1% ብቻ ነው ።

በአብዛኛው ከውጪ እየተገዛ የሚመ
ጣው የማዳበሪያ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ
በመምጣቱ በአሁኑ ወቅት ኢኮኖሚያዊ
በሆነ መንገድ በማዳበሪያ ለመጠቀም የሚ
ቻለው ከምርጥ ዘር ጋር ተቀናጅቶ ሲቀርብ
ነው ። በመሆኑም የገበሬው የማዳበሪያና የም
ርጥ ዘር አጠቃቀም እጅግ ከፍ ማለት አለበ
በት ። እዚህ ላይ የምርጥ ዘር አልፎ አልፎ
በገበሬው ተቀባይነት የማያገኝበት ሁኔታ
አለ ። ይኸውም አንዳንዱ የምርጥ ዘር ጥራት
ገበሬው ከሚያመርተው እህል ያልተሻለ
ሆኖ ሲገኝ ነው ።

ገበሬው በሄክታር በአማካይ የሚያገኘው
የምርት መጠን የአገዳና የብር እህል 9.8
ኩንታል ፣ ጥራ ጥሬ 7 ኩንታል ፣ የቅባት
እህል 3.3 ኩንታል እንደሆነ ይገመታል ።
ይህ አማካይ የምርት ደረጃ በተመሳሳይ የዕ
ድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙ ሀገሮች ጋር ሲወ
ዳደር ዝቅተኛ ነው ። በምርምርና በግብርና
ሳይንስ የትምህርት ተቋሞች ከተካሄደው
የረዥም ጊዜ ጥናት በመጠቀም በአሁኑ ጊዜ
የሚገኘውን ዝቅተኛ የአመራረትና የአስ
ተራረስ ዘዴን አሻሽሎ በምርጥ ዘርና በማ
ዳበሪያ በመጠቀም በእጥፍና ከዚያም በ
ላይ ለማሳደግ እንደሚቻል ይታወቃል ።[16]

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የግብርናውን
ክፍለ ኢኮኖሚ ለመገንባት ብዙ ጥረት እየተ
ደረገ ነው ። ለምሳሌ አንደኛ መለስተኛ የእ
ርሻ ልማት ፕሮግራም በመባል የሚጠራው
ፕሮጀክት በ1966/67 የሰብል ዘመን ሥራ
ውን በጥቂት ወረዳዎች ጀምሮ እያደር በ285
ወረዳዎችና 35 ጣቢያዎች ሊያስፋፋ ችሎ
አል ። ፕሮጀክቱ የመንገድ መገናኛ ባለባ
ቸው አካባቢዎች ለሚገኙ ገበሬዎች የም
ርት ማሳደጊያዎችን ማለትም ማዳበሪያና
ምርጥ ዘር በማስተዋወቅ ረድቷል ። ቀጥ
ሎም ሁለተኛ መለስተኛ ፕሮግራም የተባ
ለው ፕሮጀክት ከመጀመሪያው ፕሮግራም
ከተገኘው ጥናትና የሥራ ልምድ በመነሳ
ትና ጥረቱን ሰፋ በማድረግ በድርጅታዊ
ስልት ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማስተዋወቅ
ሥራውን ጀምሮ ከ1972 ወዲህ በ80 አው
ራጃዎች ውስጥ በሚገኙ 440 ወረዳዎች
ፕሮግራሙን አስፋፍቶ በመሥራት ዕቅ
ዱን በ1976 አጠናቋል ። ለፕሮግራሙም
ግብ በክፍለ ሀገር ደረጃ አምስት ቡድኖች
ማለትም ፣ የአዝርዕት ልማትና ጥበቃ ቡድ
ን ፣ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ቡድን ፣
የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ቡድን ፣
የኅብረት ሥራ ማደራጃ ቡድን፣ የኑሮ ዘዴ
ቡድን በመባል በጋራ ሠርተዋል። ቡድኖቹ
በአውራጃና በወረዳ ደረጃ ያለውን ሥራ
ሁሉ ይመራሉ፤ያካሂዳሉም። በመሆኑም የመ
ስክ ሠራተኞች ሰፊውን አርሶአደር በቀበሌ
ገበሬ ማኅበር ፣ በአምራቾችና በአገልግሎት
ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲሰባሰብና እን
ዲደራጅ በማድረግ ከፍተኛና ውጤታማ
ሥራ ፈጽመዋል ። በተለይም ምርት ማሳ

Digitized by Google

ዶጊያዎችንና ዘመናዊ የእርሻ ዘዴዎችን አጠቃቀምና የሚያስገኙትን ጥቅም በሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎችና በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እርሻዎች ላይ ማሳየቱ ከፍተኛ ውጤት እያስገኘ ነው ።

የመንግሥት እርሻ ዘርፍ ከ1968 ጀምሮ መጠነኛ አስተዋጽኦ እያደረገ መጥቷል ። ዘርፉ የቅርብ ጊዜ ክስተት በመሆኑ ለእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ያበረከተው አስተዋጽኦ ገና ጉልቶ አይታይም ። ባሁኑ ጊዜ የመንግሥት እርሻ ግብ የእህል እጥረትን አስወግዶ በቂ ምግብ በማቅረብ ፣ ከዚያም ባሻገር ከምርትን ለማዳበርና ለአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት የሰፋፊ እርሻ ልማትና አመራርን በሶሻሊስታዊ ባህል በማዳበር አርአያ መሆን ነው ። በተለይም ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ በማቅረብና የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ዘርፍ ነው። ከዚህም አልፎ ለእርሻ-ኢንዱስትሪ ግንባታ መሠረት ከመሆኑም ሌላ ሥራ አጥነትን በማስወገድ ጭምር ይረዳል ። ለምሳሌ በ1974 የመንግሥት እርሻ ለ27,000 ቋሚና ለ76,000 ጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ ዕድል አስገኝቷል ። [17]

የመንግሥት እርሻዎች በአሁኑ ጊዜ ከጠቅላላው የግብርና ምርት ውስጥ ያላቸው ድርሻ ከ5% አይበልጥም ። ይሁንና አሁን የሚታዩባቸው የአመራርና ሌሎች ድክመቶች ከተወገዱ ለግብርና ምርታማነት ዕድገት አርአያ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል ። በርካታ የመንግሥት እርሻዎች በበቂ ጥናት ላይ ተመሥርተው ባለመቋቋማቸው ድርቅ ወይም የዝናም መብዛት ፣ የመሬት አቀማመጥና የአፈር ባሕርይ ጉድለቶችና የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሁኔታዎች ለምርታማነታቸው ዝቅተኛነት ምክንያት ሆነዋል ። በተጨማሪም የሰብልና የእንስሳት ዝርያዎች ጥራት ዝቅተኛነት በግብርና ምርምር ላይ የተመሠረቱ የእርሻ ዘዴዎች አለመጠቀም ፣ የእርሻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች እጥረት ፣ የጥገና አገልግሎትና የቴክኒክ እውቀት አለመዳበርና የሥራ አመራርና የአስተዳደር ድክመቶች በተመሳሳይ መንገድ ለምርታማነት እንቅፋት ሆነዋል ። በዚህም ምክንያት በሄክታር የሚገኘው የሰብል መጠን ምርታማነቱ በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲታይ አነስተኛ ነው ። ለምሳሌ ከመንግሥት እርሻዎች በሄክታር የሚገኘው የስንዴ ምርት መጠን ከ10 እስከ 20 ኩንታል ይቀያየራል። የበቆሎ ምርትም በአብዛኛው በሄክታር ከ30 ኩንታል በታች ነው ። ከላይ የተጠቀሙና የመሳሰሉ ድክመቶችን ለማረምና ምርታማነትን ለማሳደግ ብዙ ጥረት በመደረግ ላይ ነው ። ለምሳሌ ምርጥ ዘር አምርቶ ለገባሬዎች የማከፋፈል ሥራ ማካሄጃ ተጀምሯል ። የቴክኒክ ግልጋሎትንም በሚመለከት በ56,000 ሄክታር የእርሻ ጋራዦች እንዲቋቋሙ ከመደረጉም ሌላ የተማና ጋራዦች ጥናት ተጠናቆ ፣ የማዕከላዊ ጋራዥ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ። [18]

የባንክ አገልግሎት

የእርሻን ክፍለ ኢኮኖሚ ዘመናዊና ምርታማ ለማድረግ የባንክ አገልግሎትና የሠለጠነ የሰው ኃይል ከፍተኛ ሚና አላቸው ። በመሆኑም የባንክ አገልግሎት ለግብርናው ልማት በሚያግዝ መልክ እንዲቀየስ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ። ከባንኩ የሚበደሩት የኅብረት ሥራ ማኅበራትና የመንግሥት እርሻዎች ናቸው ። አርሶ አደሩ እስካሁን ያገኘው የባንክ አገልግሎት ዝቅተኛ ነው ። ለዚህም ዋና ምክንያት አርሶ አደሩ በተበታተነ የግል ይዞታ ሁኔታ መሆንና በተለይም በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ገና ባለመደራጀቱ ነው ። ከዚህም ሌላ ብድር ሊያገኙ የሚችሉት ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ማኅበራት ብቻ ሲሆን ሕጋዊ ሰውነት ያገኙትም ቢሆን በተለይ በሥራ አመራርና በሂሳብ አያያዝ ብቃት ስለሚጎድላቸው የሚሰጠው ብድር በሚገባ በሥራ ላይ አልዋለም ይህም ሆኖ ግን የሚሰጠው ብድር ተንጿል ማለት አይደለም ።

የእርሻና ኢንዱስትሪ ባንክ በ1968/69 [19] ጀምሮ እስከ 1974/75 የሰብል

ዘመን ለገበሬዎች አምራቾችና አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ያበደረው ጠቅላላ ገንዘብ 271.2 ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዚሁ ውስጥ 14.1 ሚሊዮን ለመዋዕለ ንዋይ፣ 168.7 ሚሊዮን ብር ለምርት ማሳደጊያ፣ 88.3 ሚሊዮን ብር ለሥራ ማስኬጃ ውሎ አል ። እንዲሁም ባንኩ ለመንግሥት እርሻ ልማት ከ1967/68 እስከ 1974/75 ድረስ በጠቅላላው 1.1 ቢሊዮን ብር ያበደረ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ 310 ሚሊዮን ብር ለመዋዕለ ንዋይ ፣ 806.4 ሚሊዮን ብር ለሥራ ማስኬጃ ውሎአል ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የባንክ ቅድሚያ ተገልጋዮች የመንግሥት እርሻና የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሲሆኑ ፣ ሁለቱም ዘርፎች ሲነጻጸሩ ከተገኘው ጠቅላላ ብድር የመንግሥት እርሻ ልማት 80% ሲበደር የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ 20%ተበድረዋል ማለት ነው ። ይህም ከሀገሪቱ የግብርና ምርት ከ90% በላይ የሚያመርተው አርሶ አደር ድርሻ በጣም አነስተኛ መሆኑን ያሳያል ። ብድሩን ከፍ ለማድረግ ከሚረዱት እርምጃዎች መካከል የኅብረት ሥራ ማኅበራት ብዛትና ጥራት ማሳደግ ይገኙበታል ።

የተማረ የሰው ኃይል መኖር ለማንኛውም ዕድገትና ልማት ወሳኝ ነው ። የሀገራችንን የእርሻ ኢኮኖሚ ዘርፍ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ለመጠቀምና የዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ የተማረ የሰው ኃይል እጅግ አስፈላጊ ነው ።

የሰው ኃይል ሥልጠናን በሚመለከት ባጭሩ ሁኔታው የሚከተለውን ይመስላል ። በአጠቃላይ ዘመናዊ የእርሻ ቴክኖሎጂን በሚገባ በሥራ ላይ በማዋልና በመጠገን ችግር አለ ። ለዚህም ችግር ምክንያቱ በሙያው የተካነ የሰው ኃይል እጥረትና የአጠቃቀም መረጃና መመሪያ አለመኖር ነው። ከማዳበሪያ አንስቶ እስከ ሰብል ጥበቃ መድኃኒት አጠቃቀምን ፣ በሞተር የሚንቀሳቀሱ የእርሻ መሣሪያዎች አያይዘን ፣ የላቦራቶር ዕቃዎች አጠቃቀምን ፣ ወዘተ . . . በሚመለከት ድክመቶች በብዛት ይታያሉ። ስለዚህ በአጠቃላይ የእርሻ ቴክኖሎጂን በተገቢው ለመጠቀም ያለው ብቃት በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው ።

ባሁኑ ወቅት በሀገራችን ለግብርናው ዘርፍ የሰው ኃይል በከፍተኛ ደረጃ የሚያሰለጥን የዓለማያ ኮሌጅ ነው ። [20] ኮሌጁ ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ በዕፀዋትና በእንስሳት ሳይንስ የድኅረ—ምረቃ ፕሮግራም ዘርግቶ በማካሄድ ላይ ይገኛል ። በመካከለኛ ደረጃም የግብርና ባለሙያዎች በደብረ ዘይትና በአዋሳ መለስተኛ ኮሌጆች ይሰለጥናሉ ። ባተጨማሪ የግብርና ቴክኒሽያኖች በአምቦና በጅማ የእርሻ ተቋሞች ፣ በወንዶ ገነት የደን ትምህርት ተቋምና በደብረ ዘይት መለስተኛ የእንስሳት ሕክምና ማሠልጠኛ ተቋም እየሰለጠኑ ይወጣሉ ። ከዚህም ሌላ በግብርና ልማት የተሰማሩ ድርጅቶች የተለያዩ የአጫጭር ጊዜ ትምህርቶች (ኮርሶች) እንዲዘጋጁ እያደረጉ የሠራተኞቻቸውን ችሎታ ለማሻሻል የሥልጠና ፕሮግራሞች ያካሂዳሉ ።

ሆኖም ግብርና የአገሪቱ የጀርባ አጥንት እንደመሆኑ የዘርፉን ምርት ለማሳደግ አሁንም ገና በርካታ የተማረ የሰው ኃይል ያስፈልጋል። ለዚህም ያሉትን ተቋሞች ከማስፋፋትና ከማጠናከር ባሻገር በተጨማሪ ሌሎች የማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶችን በጥራትና በስፋት ማቋቋም ያስፈልጋል ። በ1976 ውስጥ 700 የሚሆኑ የኮሌጅና የዩኒቨርሲቲ የግብርና ምሩቃን በየሙያቸው ስለተሰማሩ ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት የሚያቃልል ይሆናል ። እንዲሁም በተለይ በግብርና ምርምርና ሥርፀት ተግባር የተሰማራው የሰው ኃይል ብዛትና ጥራት እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ባሁኑ ጊዜ በዚሁ ተግባር ላይ የተሰማራው በከፍተኛና መለስተኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል ብዛት 900 ያህል እንደሆነ ይገመታል ።በአጠቃላይ ከምርምር የተገኙ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ውጤቶች ብዛትና ጥራት በመስክ የተሠማሩት ሠራተኞች ብዛትና ጥራት

Digitized by Google

እስከ አሠራር ዘዴአቸው ጭምር አጥጋቢ ካለመሆኑም ሌላ በአጠቃላይ በምርምርና በውጤቱ ስርጭት መካከል ያለው ግንኙነት በቂ ባለመሆኑ የአርሶ አደሩ የኑሮ ደረጃ በተፋጠነ ሁኔታ ሊሻሻልና የግብርናውም ክፍለ ኢኮኖሚ የሚጠበቅበትን ያህል ዕድገት ሊያሳይ አልቻለም ። የገበሬዎችና የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ዕድገት ከማስፋፋትና ከማዳበር አኳያ በአርሲ ክፍለ ሀገር አርዳኢታ በተባለ ሥፍራ የኅብረት ሥራ ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት በኮሌጅ ደረጃ ተቋቁሞ መለስተኛ ትምህርት መስጠት ጀምሯል ።

እንደዚሁም ሰፊው አርሶ አደር በዘመናዊ መማሪያና ቴክኖሎጂ በመጠቀም ምርታማነቱን እንዲያሳድግ አብዮታዊው መንግሥት ልዩ ልዩ የትምህርት መስጫ ተቋሞችን በአማካይ ቦታዎች በመከፈት ላይ ይገኛል።በተለይም በባሌ ክፍለ ሀገር ለስድስት ወር የሚያሰለጥን የአጋርፋ የገበሬዎች ማሠልጠኛ ማዕከል በየካቲት ወር 1975 ሥራውን ጀምሮ በዓመቱ መጨረሻ ከአሥራ አራቱ ክፍላተ ሀገር የተውጣጡ 1,045 ገበሬዎች አሠልጥኖ አስመርቋል ። እንዲሁም ይኸው ማዕከል ከመስከረም ወር 1976 ጀምሮ በየስድስት ወር 2000 ያህል ገበሬዎችን እየተቀበለ በማሠልጠን ላይ ነው ።[21]

እንዲሁም በዓላማውና በአሠራሩ ከአጋርፋ የገበሬዎች ሁለገብ ማሠልጠኛ ማዕከል የሚመሳሰል በጐንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በወረታ አካባቢ ሊሠራ ታቅዶአል።ይህ የሰሜን ኢትዮጵያ ከፍተኛ ሁለገብ የገበሬዎች ማሠልጠኛ ማዕከል አጠቃላይ የግብርና ቴክኖሎጂ ፣ የእንስሳት እርባታ ፣ የአዝርዕት ፣ የምርምርና ሌሎችም ተቋማት እንደሚገኙበትና ከዚህም ጋር የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር በሞዴልነት ተቋቁሞ የአካባቢውን ገበሬ እንዲያገለግል ይጠበቃል ።

የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረትን ለማስወገድና ሙያን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት አኳያ የኅብረት ሥራ ማኅበር አባላትን እውቀት ከፍ ለማድረግ እርምጃ ተወስዶአል ። ለምሳሌ በዘመቻ አምስት ብቻ በተከታታይ 5,674 እና 5,655 የአምራቾችና የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት በኅብረት ሥራ አመራር ሰልጥነዋል ። እንደዚሁም በነዚሁ ክፍሎች በተከታታይ 2,149 እና 1512 አባላት በማኅበራት ሂሳብ አያያዝ ሠልጥነዋል ።[22] ይህ ሁሉ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ምርታማነት ለማሳደግና ለማፋጠን የተደረገውን ጥረት ያስገነዝባል።

ከዚህም ሌላ ከ1971 ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው የመሠረተ ትምህርትና የባህል ዘመቻ ፣ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማይምነት አላቆ ወደ ብሩህ ሕይወት የሚያሸጋግር በመሆኑ በአጠቃላይ ለምርት ኃይሎች ዕድገት አስተማማኝና ወሳኝ ሚና የሚጫወት ነው ። አብዮቱ እንደፈነዳ ማንበብና መጻፍ የሚችለው ሕዝብ 7% ያህል ብቻ ነበር ። እስካሁን በተካሄዱት የመሠረተ ትምህርት ዘመቻዎች አማካይነት ባሁኑ ወቅት 62.5% የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማይምነት ቀንበር ሊላቀቅ ችሏል ። ይህም ሰፊው ሕዝብ እየተማረና እያወቀ በራሱ አነሳሽነት በግብርናው ዘርፍ የሚኖረውን ተሳትፎ ለማሳደግ አስተዋጽኦ አለው ።

የወደፊቱ የጥረት አቅጣጫ

በገጠር ሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶች የሚፈጠሩት ፣ የሚስፋፉትና የሚጠናከሩት በገበሬ ማኅበራት በተለይም በገበሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትና በመንግሥት እርሻዎች አማካይነት ነው ።

የብሔራዊ ኢኳኖሚያችን ዋልታ በሆነው በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የምርት ግንኙነቶችን ማኅበራዊ ማድረግና እንዲሁም የምርት ኃይሎችን በማሻሻልና በማዳበር ምርታማነትን ማሳደግ ፣ ለኅብረተሰቡ የኑሮ ደረጃ መሻሻልና እንዲሁም በአጠቃላይ ለኢኮኖሚውና ለሶሻል ልማትና

Digitized by Google

የካቲት ፳፩ የኅብረት ሥራ ኢንስቲትዩት
(አርሲ ክፍለ ሀገር)



አጋርፋ የገበሬዎች ሁለገብ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት
(ባሌ ክፍለ ሀገር)

Digitized by Google

ዕድገት ወሳኝ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደ ለም ። ይህም በመሆኑ ታሪካዊው የኢሠፓ አኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብ ሰባ በዚህ ላይ የማያወላውል አቋም በመ ውሰድ ሶሻሊዝምን በገጠር ለመገንባት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለመፍጠርና ለማ ጠናከር የሚከተሉትን የፖሊሲ ውሳኔዎች አሳልፎአል ።[23]

1ኛ/ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለሻሶ ሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ የማቴሪያ ልና የቴክኒክ መሠረት ለመፍጠር የሚያስችለውን የጥሪት ክምችት ለማዳበር ምንጫችን የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ቢሆንም ፣ ዘርፉ ባለበት የተበታተነና አነስተኛ የምርት አደረ ጃጀት ሁኔታ ይህንን እውን ማድረግ ስለማይቻል የግብርናውን ክፍለ ኢኮ ኖሚ በከፍተኛ ምርት ዕድገት ለማደ ራጀት ፣ በገጠር ሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ለመገንባትና የካፒታሊዝ ዝምን ግቆጥቆጥ ለመከላከልና የሶሻ ሊዝምን ድል አድራጊነት ለማረጋገጥ ለአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋትና መጠናከር ትኩረት እን ዲሰጥ ፣

2ኛ/የሀገሪቱ የልማት ስልት መሠረት የአምራቾች ኅብረት ሥራ መስፋ ፋት እንደመሆኑ ፣ ይህን በአስተማማኝ በተግባር ለመተርጐምና የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የምርት ውጤት በከ ፍተኛ ደረጃ እየዳበረ መሄዱን ለማረ ጋገጥ ፣

ሀ/ በየዘመኑ ለልማት የሚመደበው መዋዕለ ንዋይ ከምንጊዜውም በበ ለጠ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ላይ እንዲያተኩር ፣

ለ/ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የም ርት ውጤት በከፍተኛ ደረጃ ለማ ዳበር የተሻሻሉ መሣሪያዎችና አገልግሎቶች በማቅረብ ረገድ ቅድ ሚያ እንዲሰጣቸው ።

ሐ/ ማኅበራቱን ለማስፋፋትና ለማ ጠናከር የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት የሚሠለ ጥንበት የማሠልጠኛ ተቋሞች እን ዲጠናከሩና እንዲቋቋሙ ፣

መ/ አብዮታውያን ሁሉ በያሉበት የኅ ብረት ሥራ ማኅበራትን ለማስፋ ፋት የሚደረገውን ጥረት በከፍ ተኛ ደረጃ እንዲያራምዱ ።

እንዲሁም የኢሠፓአ ሁለተኛ ጉባኤም ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ይህንኑ የልማት ፖሊሲ አቋም የሚያጠናክሩና ለተግባራዊ ነቱ ሥልቶችን የሚቀይሱ ከመሆናቸውም በላይ የመንግሥት እርሻዎችንም በሚመለ ከት መወሰድ የሚገባቸውን አጠቃላይ እር ምጃዎች የሚጠቀሙ ናቸው ። ውሳኔዎቹ እንደሚከተሉት ተገልጸዋል[24]

1ኛ/ አግባብ ያላቸው መንግሥታዊ ድርጅቶች በአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበር ከተደራጁ ገበሬዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር እንደየአ ካባቢያቸው ልዩ ጠባይ እየታየ የገ በሬ ማኅበራቱ የተወሰኑ ምርቶችን እንዲያመርቱ እንዲደረግ ፣ ምርታ ቸውንም ለገበያ እንዲያቀርቡና ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ፣ በተ ቀነባበረ መልክ የብድር ፣ የሸቀጥ አቅርቦትና ሌሎችም አገልግሎቶች የሚያገኙበት ሁኔታ በበለጠ እን ዲጠናከር ፣

2ኛ/በአጠቃላይ ገበሬው በተሻሻሉ የምርት መገልገያዎችና ዘዴዎች እንዲጠቀምና ምርታማነቱን በማ ማሳደግ የራሱን ሕይወት እየለ ወጠ ለኅብረተሰቡም የሚያበረክ ተውን አስተዋጾኦ ለማሳደግ እን ዲችል በተገቢው ሥልት ላይ የተመሠረተና የተቀነባበረ ድጋፍ እንዲሰጠው ፣

3ኛ/የመንግሥት እርሻዎች ምርታማ ነታቸውን ከፍ ለማድረግ እንዲ

Digitized by Google



የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት በምርት ክፍፍሉም አኩሪ ሚና አላቸው ።

Digitized by Google

ችሉ የአደረጃጀታቸውንና የማኔጅመንታቸውን ጥራት ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡትና እንዲሁም ገበሬው በተሻለ ቴክኖሎጂና የእርሻ ዘዴ እየተጠቀመ የተሻለ ውጤት እንዲያስገኝ በተግባራዊ አርአያነት ለማስተማር የሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ጥረት እንዲደረግ ፤

እነዚህ ውሳኔዎች በአጠቃላይ በግብርናው ክፍለ ኢኳኖሚ ወደፊት የምንከተለውን የልማት አቅጣጫ የሚተልሙ ሲሆን ውሳኔዎቹንም በሥራ በመተርጐም የግብርናውን ክፍለ ኢኳኖሚ ወደ ከፍተኛ የምርት የአደረጃጀትና የቴክኖሎጂ ደረጃ ማድረስ የሚቻለው በተለይ በተነደፈው የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ አማካይነት ዝርዝር መርሃ ግብሮችንና የድርጊት ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ በተመደበላቸው የጊዜ ገደብ በቁጠባና በቅልጥፍና በተግባር በማስፈጸም ብቻ ነው ። ለግብርናው ክፍለ ኢኳኖሚ የተቀየሰው የልማት ስትራቴጂ በአጠቃላይ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ልማት ሂደት መሪ ሃሳብ በሆነው «ዕድገት በእኩልነት » በሚለው መሠረታዊ መርህ ላይ የተመረኰዘ በመሆኑ ፤ ሁለት ጥምር ዓላማዎችን የያዘና እነዚህን የሚያሟላ ነው ። እነዚህም አንደኛ በገጠር ሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ማስፋፋትና ማጠናከር ፤ ሁለተኛ የግብርና ምርትንና ምርታማነትን ማሳደግ ናቸው ። የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማጠናከር በተለይ ምርታማነታቸውን በብቃት በማሳደግ የመገልገያ መሣሪያዎችና የአሠራር ሥልታቸው በዘመናዊ መልክ መደራጀት እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው ። እዚህ ላይ ማርክስና ኤንግልስ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኢኮኖሚ በማሽነሪና በሌሎች የምርት ኃይሎች እድት ካልተደገፈ የንድፈሀሳብ ሕልም ብቻ ሆኖ ይቀራል ያሉትን ማስታወስ ጠቃሚ ነው ።[25]

እስካሁን ያለው ፍቱን የልማት ስትራቴጂ በመላ ኢትዮጵያ የገበሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማደራጀትና ማስፋፋትና ማጠናከር በመሆኑ ፤ የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ዓይነተኛ ዓላማም በየጊዜው የሚያድገውን ገበሬ በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር እንዲደራጅ ማዘጋጀት ነው ። በዚህ ረገድና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለን ብንሆንም የጀመርነው ሙከራ ግን እጅግ የሚያበረታታ ነው ።

ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓ መሥራች ጉባኤ ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ላይ ይህን አበረታች ጅምር እንደሚከተለው ገልጸውታል ፤

«የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የማስፋፋቱ ዓላማችን በገበሬ ፍጹም ዲሞክራሲያዊ ውሳኔና ለማኅበራቱ መመሥረት ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን በማረጋገጥ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ባለፉት ዓመታት ጥረታችን ያፈራናቸው ማኅበራት ብዛት የተመጠነ ነው ። ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም የተቋቋሙት ማኅበራት ጥንካሬ ግን ለወደፊቱ ጥረታችን ፍሬያማነት የሚያበረታታ ነው ። በታሪካችን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ገበሬዎች የትራክተር ፤ የኮምባይንና የጭነት መኪናዎችም ባለቤት ለመሆን የበቁት በመደራጀታቸው መሆኑ ማኅበራቱን ለማስፋፋት ለምናደርገው እንቅስቃሴ አርአያነት ያለው ነው ።»[26]

በመሆኑም ማኅበራት ገና ባልተቋቋሙባቸው ሥፍራዎችና (አካባቢዎች) እንደሁኔታው ከሕዝቡ ኑሮ ጋር ከተጣጣመ የሠፈራና ሌሎች የገጠር ልማት ፕሮግራም ጋር በማጣመር የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ቀደም ሲል እንደተመለከተው የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን በሚመለከት በርካታ ችግሮች አሉ ። በተለይም ትክክለኛና የተቀናጀ የሥራ ክፍፍል ፤ የሥራ ሥርዓትና ደንብ አለመኖር ፤ የሂሣብ ሰነዶችና መዛግብት በትክክል አለመያዝ ፤ የገንዘብና የንብረት መባከን ፤ ልአ

Digitized by Google

ባላት እንደ ሥራቸው መጠንና ጥራት ሊመ ክፈል አለመቻሉ ፣ የምርት መገልገያዎች በተለይም በበሬ-እጥረት ፣ በምርጥ ዘር ፣ በማዳበሪያና በመሳሰሉት የምርት ማሳደጊ ያዎች በብቃት ለመጠቀም አለመቻሉ በአ ሁኑ ወቅት ጐልተው ከሚታዩት ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ። [27] ከዚሁ በመነሣት የወደፊቱ ጥረት የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊያጠቃልል ይገባል ።

—አዋጆችንና መመሪያዎችን በመከተል የገበሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በየክፍለ ሀገሩ በጥራት ማደራጀት የሚችሉ ሰዎችን ከሙያው ጋር በተዛመደ መልክ ማሠልጠን ፣

—ከብሔራዊ እስከ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ደረጃ ድረስ በሴሚናር ፣ በአብዮታዊ ኪነት ፣ በጽሑፍ፣ በሥዕላዊ መገለጫና በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ትምህርት አዘል ቅስቀሳ በማካሄድ የአርሶ አደ ሩን ንቃት ከፍ ማድረግና በአምራች ማኅበራት እንዲደራጅ ማድረግ ፣

—የኅብረት ሥራ ማኅበራት ራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ በመንግሥት ድጋፍ በማኅበራቱ አስተዳደር ውስጥ በቁል ፍ ቦታዎች (ለምሳሌ በሂሣብና በሥራ አመራር ፣ በልማት ወዘተ —) በተለይ ሂሣብ ነክና የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎችን በቋሚነት መመደብ ፣

—አምራች ማኅበራቱ በተለይ በሬ ፣ ምርጥ ዘር ፣ ምርጥ ኮርማ ፣ ማዳበሪያ ፣ ፀረተባይ ፣ ፀረአረም ፣ የተሻሉ የም ርት መገልገያዎች ፣ ወዘተ - - - በተ መጣጣኝ ዋጋ እንዲገኙ ማድድረግ ፣

—ሁለገብ የገበሬዎች ማሠልጠኛ ማዕ ከሉችን በቀሩት አራት ቀጠናዎች (ማለትም በኢጋርፉ ከተቋቋመው ሌላ) ማቋቋም ።

—ለአምራች ማኅበራቱ የተሻሻሉ የእ ርሻ መሣሪያዎችና የትራክተር ኪራይ አገልግሎት እንዲያገኙ ስልት መቀየ ስና ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል ።

የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓላማ የአባላትን ምርት ለገበያ ማቅረብ ፣ በአጸፋው ለአባላት የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችንና ምርት ማሳደጊያዎ ችን እንዲሁም የፍጆታ ሸቀጦችን ማቅ ረብ ሲሆን በተለይም ለአምራቾች የኅብ ረት ሥራ ማኅበራት የገንዘብና ሌላ ድጋፍ መስጠት እንዲሁም አገልግሎቶችን ማስ ፋፋት ይጨምራል ። [28] የገበሬዎች አገ ልግሎት ማኅበራት ለገበሬው በተለይ መሠ ረታዊ የፍጆታ ሸቀጦችን በማቅረብ ረገድ በቀላሉ የማይገመት አገልግሎት የሰጡ ቢሆንም ፣ በርካታ ድክመቶች አሳይተዋል። በተለይም በገንዘብ አለአግባብ መጠቀም፣ የአመራር ፣ የሂሣብና የንብረት አያያዝ ጉድ ለቶች በማኅበራቱ ውስጥ ፣ ተከስተዋል ።

ከማኅበራቱ ውስጣዊ ድክመቶች በተጨ ማሪ እድገታቸውን ከገቱት ችግሮች መካከል የገንዘብ እጥረት ፣ የትራንስፖርትና የመገ ናኛ ችግሮችና በቂ የመንግሥት ሰብል መረከቢያ ጣቢያዎች አለመኖር ይገኙ በታል ።

የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በከፍተኛ ደረጃ(በወላ ንድ) መቋቋም እንደመሸጋገሪያ ድልድይ ሆነው የሚያገለግሉ ከመሆናቸውም በላይ በሽግግሩ ወቅትም አያሌ የልማት አገልግ ሎቶችን ለማበርከት የሚችሉ በመሆናቸው በአሁኑ ጊዜ የሚታዩባቸውን ድክመቶች ለማረም የወደፊቱ ጥረታችን በተለይ በሚ ከተሉት ላይ ማተኮር ይኖርበታል ፣

—በተበጣጠሰና በተበታተነ መሬት ላይ የማረስና ኋላ ቀር የግብርና አሠራር ባሕልን በማስቀረት ገበሬው በተለየ በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅብ ራት አማካይነት በመንደሮች ተሰባ ስቦ የተሻሻሉ የእርሻ ምርት መገልገ

Digitized by Google



በዝናብ ብቻ ከመተማመን በመስኖም ወደ መገልገል
(ሐረርጌ ክፍለ ሀገር)

Digitized by Google

ያዎችና የአሠራር ስልቶች ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ እንዲደራጅ የተጀመረውን ጥረት በተጠናከር መንገድ መቀጠል ፤

—ልዩ ልዩ የምርት ማስፋፊያዎችን(ማዳበሪያ ምርጥ ዘርን ፣ ኳርማን ፣ ፀረተባይን ፣ የተሻሻሉ የግብርና መሣሪያዎችን ፣ ወዘተ --- ለገበሬዎች በብዛትና በወቅቱ ለማቅረብ እንዲቻል በዚህ የልማት ሥራ ላይ የተሠማሩ የመንግሥት መ/ቤቶችንና ተቋሞችን ማጠናከርና እንዲሁም በገርብና ምርት ማስፋፊያዎች የሚውለውን የልማት ወጪ ማሳደግ ፤

—የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ የበለጠ ስልጣንና ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ፤

—በገበሬዎች አገልግሎት ኅብረትሥራ ማኅበራት አመራር ውስጥ ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች ባለሙያዎች እንዲሠማሩ ማድረግ ፤

—በተለይ በአሁኑ ጊዜ ጉልተው የሚታዩትን ችግሮች ማለትም የመጋዘን፣ የሚዛንና ጆንያ እጥረት ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ችግሮች ወዘተ ማቃለል ፤

—መንግሥታዊ ድርጅቶች የገበሬወን ምርት ለመግዛትና እንዲሁም ለገበሬው መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችንና የምርት መገልገያዎችን ለማቅረብ ከገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር በበለጠ ሰፊ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ማድረግና የሚያጋጥሙ ዕንቅፋቶችንም ለማስወገድ ያልተቀጠበ ጥረት ማድረግ ፤

—በተጨማሪም በአንድ ወረዳ በአማካይ 11ሺህ የገበሬ ቤተሰብ ወይም 40 የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ስለመኖራቸው አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ ። [29] እንዳሁኑ በወረዳ ደረጃ ከሦስት እስከ አምስት የሚሆኑ ባለሙያዎችን ብቻ መመደብ ከፍተኛ ብዛት ላለው አርሶ አደር አገልግሎት ለመስጠት ስለማያስችል የልማት ፕሮግራም በሚካሄድበትና ገበሬው በቅርብ አገልግሎት በሚፈልግበት አካባቢ የባለሙያዎች የሰው ኃይል በበቂ መጠን እንዲሠማራ ያስፈልጋል ።

—ሌላው መታወስ ያለበት ጉዳይ የመንደር ምሥረታ ጥያቄ ነው ። የመንደር ምሥረታ በጥናት ላይ የተመሠረተ ሆኖ አስፈላጊነቱና ወቅታዊነቱ እየታየ መሆን አለበት ።

ለመንደር ምሥረታ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችና መሠረተ ልማቶች መሟላትም አለባቸው ።

የመንግሥት እርሻዎች ከገበሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ጐን ለጐን ሆነው በገርብናው ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶችን በማስፋፋትና በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። ይሁን እንጂ እላይ እንደተጠቀሰው የመንግሥት እርሻዎች ባሁኑ ወቅት በርካታ ድክመቶች ይታይባቸዋል ። ከነዚህም በተለይ በቂ የመሬት ጥናት አለመኖርና የአንዳንድ እርሻዎች ያለበቂ ጥናት መቋቋም ፣ በእርሻ መሣሪያዎች በኩል የአጠቃቀም፣ የጥገናና የመለዋወጫ ችግሮች መኖር፣ የምርት ማሳደጊያዎች አቀራረብና አጠቃቀም በኩል ችግሮች መኖር፣የገበያ የመጋዘንና የትራንስፖርት ችግሮች መኖር፣ የምርታማነት ዝቅተኛ መሆን ፣ የእርሻ መሠረተ ልማቶች አለመስፋፋት ወዘተ—ናቸው።

የመንግሥት እርሻዎችን በማስተዳደርና በማምረት ያለው ተግባራዊ ልምድ በጣም አነስተኛ በመሆኑ የችግሮች መከሰት ባያስገርምም የመንግሥት እርሻዎች በተለይ ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የልማት መሠረት ስለሚሆኑ ለዚህ ግብ ተግባራዊነት በሚከተሉት ላይ ማተኮር ተገቢ ይሆናል ።

Digitized by Google

—አክሳሪ የሆኑትን እርሻዎች በሚመለከት ተገቢ ውሳኔዎችን መውሰድና ወደፊትም የመንግሥት እርሻ ዎች ሲቋቋሙ ጥልቅና ሰፊ የእርሻ ፕሮጀክት ጥናት ከተደረገ በኋላ ብቻ እንዲሆን ማድረግ ፣

—የመንግሥት እርሻዎች በሠለጠነ የሰው ኃይል በኩል ያለባቸውን ችግር ለማቃለል በመደበኛው የትምህርት ሥርዓትና ከዚያም ውጪ በልዩ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች አማካኝነት በተለይም እጥረት በሚታዩባቸው ሙያዎች (ማኔጀሮች ፣ አካውንታንቶች ፣ አግሮኖሚስቶች ፣ የእርሻመሣሪያ መሃንዲሶችና መካኒኮች) በብቃት እንዲኖሩ ማድረግ ።

—የመንግሥት እርሻዎች በመስኖ ልማት ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግና ለዚህም ተስማሚ አካባቢዎችን በስፋትና በጥልቀት አጥንቶ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት ፣

—የእርሻ ምርምር ተግባር በተጨባጭ ችግሮች ላይ የሚያተኩር ሆኖ በተለይም በመንግሥት እርሻዎችና በምርምር ጣቢያዎች መካከል የተቀራረበ ዘወትራዊ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግና ወዘተ - - - -

—እስካሁን በመንግሥት እርሻ ድርጅታዊ መዋቅርና አስተዳደር ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ፣ ያስገኙትን ውጤቶች በመገምገም የእርሻ ድርጅቶችን የውስጥ ኃላፊነትን ሥልጣን ለማስፋት ፣ የሂሳብ አያያዝ ፣ የዕቃግዥ ፣ የሰው ኃይል፣ የምርትና የቴክኒክ አመራርና አስተዳደር ስልቶች ተመሳሳይና ቀልጣፋ ለማድረግና በአጠቃላይም የመንግሥት እርሻዎችን ድርጅታዊ መዋቅርን ማኔጅመንትን ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ፣

—የዕቃ ጥራትን ፣ የዋጋ ተመጣጣኝነትን ፣ የአቅርቦት አስተማማኝነትን ፣ የመለዋወጫ ዕቃ በቀላሉ መገኘትንና የመሳሰሉትን መመዘኛዎች መሠረት በማድረግ ከውጭ የሚመጡ የእርሻ መሣሪያዎችን የዓይነት ብዛት መቀነስና የጥገና አገልግሎቶችን በሰው ኃይልና በድርጅት ማጠናከር ፣

—የመንግሥት እርሻዎች የሚጠቀሙባቸውን የሰብልና የእንስሳት ዝርያዎችን ማሻሻል ፣

በአጠቃላይም ተለዋዋጭ የአየር ሁኔታ በተለይም ድርቅ በእርሻ የኢኮኖሚ ላይ ከሚያስከትለው ተደጋጋሚ ችግር ደረጃ በደረጃ ለመላቀቅ በግልና በማኅበር ፣ የግብርና ክፍሉ አነስተኛና መለስተኛ የመስኖ ልማት ሥራዎችን ማቋቋምና ማስፋፋት እንዲሁም እንደገጠር መንገዶች ፣ መጋዘኖች ፣ የገበያ ሥፍራዎችና የመሳሰሉት የግብርና መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት ያስፈልጋል ።

እዚህ ላይ የኢሠፓ የፖለቲካ ቢሮ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባውን ባካሔደበት በከፍተኛ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ አመራር በሰጠበት ወቅት በወቅቱ የተከሰተውን ድርቅ ለመቋቋም በተለይ የግብርናው ዘርፍ ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን በመጠቆም፣ « - - - ከዚህ አንጻር የውሃ ግድቦችንና የጉርፍ መከተሪያዎችን መሥራት፣ ድርቅን መቋቋም የሚችሉና ቶሎ የሚደርሱ የሰብል ዓይነቶችን ማብዛት ፣ የአካባቢውን የአየር ሚዛን የሚያናጉ አጥፊ ተግባሮችን በተለይም የደን ጭፍጨፋ እንዲታቀብ መደረግና የመሳሰሉት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ናቸው » [30] በማለት የሰጠውን መመሪያ እያንዳንዱ ገበሬ በአጠቃላይም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በጥብቅ ሊገነዘበውና በሚወስዳቸው የአስቸኳይና የአጭር ጊዜ እርምጃዎች ሁሉ ከልብ ሊሳተፍበት የሚገባ ዐቢይ ቁም ነገር ነው ።

Digitized by Google



በ9 ቀን ብቻ የ98 ኪሎ ሜትር የመኪና መንገድ ሥራ
(መንዝና ግሼ-ሸዋ ክፍለ ሀገር)

Digitized by Google

የአስቸኳይና የአጭር ጊዜ እርምጃዎች

የኢትዮጵያ ሕዝብ የገጠመውን የረሀብ አደጋ ፣ የድርቅ መስፋፋትና የምግብ እጥረትን ፣ ወዘተ --- ለመቋቋም የሚያስችሉ አስቸኳይ መፍትሔዎችን ለመፈለግና እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ከኅዳር 13—14/1977 የግብርና ባለሙያዎች ሴሚናር መክፈቻ ላይ ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም እንደሚከተለው ተናግረው ነበር ።

> ከማንኛውም ዓይነት ብዝበዛ ነጻ የሆነ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ መመሥረታችን የሚወሰነው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እድገት ተፋጥኖ ለግባችን ተጨባጭነት የሚያስፈልገውን ቁሳዊ መሠረት ለመፍጠር ወደሚያስችለን የዕድገት ደረጃ ሊያንደረድረን ስንችል ብቻ ነው ።
>
> ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ግን ከዚህ አርቀን ከምናየው ከሩቅ ግብ በፊት ለማንኛውም ኅብረተሰብ ሕልውና መሠረት የሆነውን የምግብ እህል አቅርቦት የማሟላት የሞት የሽረት ትግል ላይ ነው ። 31

ዛሬ ከመቸውም የበለጠ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ለረሀብ ፣ ለእርዛትና ለስደት አደጋ ተጋልጧል ። በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በአንድ በኩል የሀገሪቷ ለምለም ሀብት ለጥቂት የሀገር ውስጥ ሀብታሞች ጥቅምና ለውጭ በዝባዦች እንዲጋለጥ ፣ በሌላ በኩል ሠርቶአደሩ ሕዝብ ነቅቶና ታሪካዊ ኃላፊነቱን ተገንዝቦ የተፈጥሮ ክስተት ከሚያደርስበት አደጋ ለመዳን እራሱን እንዲያዘጋጅ ፣ የተፈጥሮ ሀብቱን በትክክል እንዲጠቀም ስላልተደረገ ድርቅ ያስከተለው ችግር የሕዝቡን ሕልውና እየተፈታተነው ነው ።

በ1976 በበልግ ወቅት ዝናብ አለመጣሉ ፣ የክረምት ወቅትም እንደተጠበቀው ሳይሆን ቀደም ብሎ የጀመረና ቀደም ብሎ የወጣ ፣ የጣለው ዝናብም ቢሆን ከመደብኛው የክረምት ዝናብ ጋር ሲነጻጸር እስከ 95% የቀነሰ መሆኑ ፣ በ1977 የምግብ እህል ፣ ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ ምርቶች (የግጦሽ ሣር ጭምር) ፣ የውሃ ፣ እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ በጥሬ ሀብትነት የሚውሉ፤ ወደውጭ ገበያ ተልከው ለሀገሪቱ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ጭምር ለመግዛት የሚያስችል የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ የእርሻ ምርቶች (ለምሳሌ ቡና ፣ ሌጦ ፣ ወዘተ ---)እጥረት እንደሚኖር ይገመታል ።

በ1977 በድርቅ የተጐዳው ሕዝብ ቁጥር 9 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን በአጠቃላይ በድርቁ ምክንያት አስቸኳይ የምግብ እርዳታ የሚፈልገው ሕዝብ ቁጥር 6.5 ሚሊዮን ያህል ነው። አሁንም ቢሆን ድርቁ ያስከተለው ችግር በብዙ ሺህ ለሚቆጠር ሕዝብ ሕይወት መጥፋት ምክንያት እየሆነው ነው።እያሌ የሀገራችን የቤትና የዱር እንስሳት እያለቁ ናቸው ። በመሆኑም ከችግሩ ከባድነት አንጻር ሲታይ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ መስኮች ከኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ፊት ለፊት የተጋረጡት ተቀዳሚ ተግባሮች ፣ በሚቻለው መንገድ ሁሉ የምግብ አቅርቦትን መጨመርና ድርቁን መቋቋም ናቸው ። ችግሩን ለመቋቋም ፣ ለማቃለልና እንዲሁም ዘላቂ መፍትሔ ለማግኘት ኢሠፓና የኢትዮጵያ መንግሥት የድርጊት ፕሮግራሞች ቀይሰዋል ። የፕሮግራሙ ይዘት የሚያጠቃልላቸው መሠረታዊ ሐሳቦች ፦

ሀ/ በድርቅ ለተጐዱት የኅብረተሰብ ክፍሎች ምግብና ሌላም እርዳታ በመስጠት ነፍሳቸውን ማዳን ፣ ከዚሁም አጣምሮ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ በማጠናከር ለዘለቄታው ችግራችን ለመፍታት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብለው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች ከአጣዳፊና ከአስቸኳይ ተግባራት ጋር በተጓዳኝነት እንደሁኔታው ማካሄድ ፣

ለ/ ማንኛውንም ስፋትና ጥልቀት ያለውን ችግር ለመፍታት ወሳኝ የሆነውን

Digitized by Google

ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ማስተባበርና ንቁ ተሳታፊ ማድረግ ናቸው ።

ከነዚህ መሠረታዊ ሐሳቦች አንጻር በ1977 የደረሰውን ችግር ለመቋቋም የሚያስችሉ የአስቸኳይና የአጭር ጊዜ እርምጃዎች ተዘርዝረው ተግባራዊ እየሆኑ ነው።

የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች [32]

የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች የተለያዩ እጅግ አንገብጋቢ እርምጃዎችን የሚያጠቃልሉ ሲሆን ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

[illegible] ውስጥ የሚታየውን የእህል [illegible]ትና ልውውጥ ችግር ለማቃለል ከፍተኛ የምርት ክምችት ያላቸውን ገበሬዎች ይህን ምርታቸውን ወደ [illegible]ያቀርቡ አስፈላጊውን ቅስ[illegible] ሁሉ ማድረግ ፣ የቀረበውንም እህል በእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን አማካይነት ሰብስቦ ማሠራጨት ፣ [illegible] ነዋሪዎች ለምግብ የሚሆናቸውን የእርሻ ምርት በተለያዩ መንገዶች ለመግዛት እንዲችሉ መፍቀድ፣

ለ/ የንግዱን እንቅስቃሴ ለማጠናከር የሚያስችሉ እርምጃዎች ለምሳሌ ለእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት የሚቀርበውን የእህል መጠን ለመጨመር የሚረዳ ኢኮኖሚያዊ የማበረታቻ ዘዴ መፍጠር ፣ የድርጅቱን ድክመቶች ማስወገድ ፣ የገበሬውም ሆነ የከተማ ነጋዴዎች ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት በማሰብ የሚፈጥሩትን የእህል ክምችት ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ፤

ሐ/ ባለው ዝቅተኛ የውጭ ምንዛሬ አቅም የተቻለውን ያህል ከውጭ አገር መጠነኛ እህል በአነስተኛ ዋጋና በረጅም ጊዜ የሚከፈልበትን መንገድ በመፈለግ በአስቸኳይ መግዛት ፣ ከውጭ የሚገኘውን ዕርዳታ መጠን ከፍ ለማድረግ መጣር ፣

መ/ ሕይወትን ለማዳንና በረሀብ የተጐዳውን ሕዝብ እንዲያገግም ለማድረግ የዕለት እርዳታን ማጠናከር ።

ያጭር ጊዜ እርምጃዎች

በዚህ ርዕስ ሥር የሚጠቃለሉት እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ በዕለት ደራሽ ዕርዳታ ሥር ከሚገኙት እርሶ አደሮች መካከል ፣ በምርት ተባር ውስጥ ሊሰማሩ የሚችሉትን ተረጂዎች የዝናብ መጠናቸው ፣ የአየርና የአፈር ሁኔታቸው አስተማማኝ በሆነባቸው የሀገሪቷ ክፍሎች በማስፈር ማቋቋም ፣ እያንዳንዱንም ሰፋሪ ገበሬ ከመንግሥት መጠነኛ እርዳታ አግኝቶ ኑሮውን በአመዛኙ በራሱ ጥረት እንዲመሠረት የሚያስችሉ የተለያዩ የማቋቋም ሥልቶች መከተል ፣

ለ/ በ1977 ይደርሳል ተብሎ የተገመተውን የምግብ እህል እጥረት ለመቋቋም አስተዋጽኦ እንዲያደርግ በከተሞችና በገጠር ያሉ ሕዝባዊ ፤ መንግሥታዊና ሌሎችም ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች አመች በሆነው ቦታ ሁሉ የጓሮ አትክልት ልማት እንዲያካሂዱ ማድረግ ፣

ሐ/ እላይ ከተጠቀሱትና ከሌሎችም እስከ እስከ አሁን ከተገኙ መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የ1977 ምግብ የእህል አቅርቦት እጥረትና በድርቁ ምክንያት በእንስሳት ሀብት ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ እጅግ አሳሳቢ ሆኗል ። ችግሩን በተቻለ መጠን ለመቋቋም የተለያዩ እርምጃዎች ይወሰዳሉ ። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

የ1977 የበልግና የመኸር ለዘመራ የተሟላ ለማድረግ ልዩ ልዩ የምርት ማሳደጊያዎችና አገልግሎቶች በወቅቱና በሚፈለገው መጠን ለገበሬው እንዲቀርቡ ይደረጋል ። በተጨማሪም የምርት ማሳደጊያዎች በተለይ ዘር ፣ ማዳበሪያ ፣ ፀረ ሰብል ተባዮች ፣ መከ

ላከያ መድኃኒቶችንና በድርቅ ምክንያት በሬ ለሞተባቸው አካባቢዎች የእርሻ በሬ፣ አነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች እንደአስፈላጊነታቸው ይሰጣሉ ። በተለይ ከፍጆታ በላይ አምራች በሆኑ አካባቢዎች የትራክተር አገልግሎትና እንዲሁም የተጠናከረ የእርሻ ዘዴ አገልግሎት ይሰጣል ።

ከዚህም ሌላ በእንስሳት ላይ ሊደርስ የሚችለውን እልቂት ለመቋቋም የመኖ፣ የጤና፣ የውሀ፣ የግጦሽና ጊዜያዊ የከብት ማቆያ ግልጋሎቶች ይሰጣሉ ።

መ/ በሀገሪቷ ውስጥ የደረሰውን የምግብና የዘር እጥረት ለመቋቋም የመንግሥት እርሻዎች ከመደበኛው የግብርና ተግባራቸው በተጨማሪ ሁለት ፕሮግራሞች ማለትም የበልግና የመኸር ፕሮግራሞች በመንደፍ የግብርና ሥራቸውን ከፍ በማድረግና በማስፋፋት የተለያዩ ምርቶች እንዲያመርቱ ተወስኗል ። አስፈላጊው ቅስቀሳና የሥራ ዝግጅትም እየተደረገ ነው።

ሠ/ ድርቁ በእንስሳት ላይ የሚያደርሰውን እልቂትና ጉዳት ከዚህም ተያይዞ የሚመጣውን ችግር በተለይም የእርሻ በሬ እጥረት ችግርን ለመቋቋም የእንስሳት ጤና አገልግሎት በተቻለ መጠን ይስፋፋል። በተጨማሪም የእንስሳት መኖ ይቀርባል ። በድርቁ የተጎዱትና ሊጎዱ የሚችሉት እንስሶችን በጥቅም ላይ ለማዋል ወይም ወደሌላ ቦታ አዛውሮ ለማቆየት ወይም ለመሸጥ የሚያስችል የእንስሳትስ ግዥ ዘመቻ ፕሮግራም ይወጣል ።

ረ/ ድርቁን ለመቋቋም የሚያስችል ከፍተኛ የውሀ ክምችት መፍጠር የሚያስፈልግ መሆኑ አጠያያቂ ስላይደለ እንደሁኔታው በተቻለ መጠን አያሌ ኩሬዎችን ለመቆፈር ግድቦችን ለመሥራት ፣ ወንዞችን ለመጥለፍና ውሃውን ለሰብል ምርትና ለእንስሳት መኖ ለመጠቀም አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል ። (በዚህ አኳያ በአንዳንድ ቦታዎች ለምሳሌ በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ገበሬዎች ያካሔዱት የራስ አገዝ የወንዝ ጠለፋ ሥራ ለሌሎች አካባቢዎች አርአያነት ያለውና አበረታች ነው ።)

ድርቁ ያስከተለውን ችግር ፣መቋቋምና ራስን የመቻል ጥያቄ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመኖር ወይም ያለመኖር ፣ ካለበት ችግር ውስጥ የመውጣት ወይም ያለመውጣት ፣ የብሔራዊ ሕልውናውን ማስከበር ወይም አለማስከበር ጥያቄ ስለሆነ ፍጹም ቸል ሊባል የሚችል አይደለም ። ጓድ መንግሥቱ ይህን አስመልክው ሲናገሩ ፣ «ምግብ ተመጽዋች ከመሆን በላይ ብሔራዊ ሕልውናን ዝቅ የሚያደርግ ነገር ከቶ የለም ። እራሳችንን መመገብ አቅቶን ወገኖቻችን ሲረግፉ ከማየት የበለጠ አሳዛኝ ወቅትና ሁኔታ አይኖርም ። ይህንንም ሁኔታ መለወጥ አለብን ። ይህ ሁኔታ ደግሞ የሚለወጠው በሥራ ነው። ችግሩም የመነጨው የሥራ ባህላችን ካለመዳበሩ ነው።»[33]

ብለዋል ። የሀገራችን ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነውን የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ዛሬ ከገጠመው ችግር አላቆ ከወደቀበት አዘቅት አንስቶ ምርታማና የበለጸገ የሚያደርገው ይኸው ሥራ ነው ። ሥራውም ውጤት እንዲሰጥ በረጅምና በአጭር ጊዜ የሚወሰዱት እርምጃዎች ተጣጥመውና ድርጊታቸው ተቀነባብሮ እንዲሄድ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው ። የዚህ ቅንብር የተጣጣመና ውጤታማ መሆን አሁን የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከገጠመው አንገብጋቢ ችግር ለመላቀቅና ሊገነባው ላቀደው ሶሻሊስት ኅብረተሰብ መሠረት ለመጣል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. Csiko's Nagy, Socialist Economic Policy (Budapest: Akademiai Kiado, 1973), pp. 70-74, and Paul Baran, The Political Economy of Growth (London: Penguin Books Ltd., 1973) pp. 428-43.
2. የግብርና ሚኒስቴር መዋቅራዊ ጥናት መስከረም, 1976, ጥራዝ 1 ፣ ገጽ 1 (ያልታተመ) ።
3. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ።
4. Mark Und Engels, Werke, Bd. 19, 5. 391 cited by I.L. Andreyeu The Non Capitalist way, (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 140 and E. Terray, Marxism & Primitive Societies (New York: Monthly Review Press, 1972), pp. 105-138, 117, 138.
5. Tama's Szentes, The Political Economy of Under-Development, Third Edition (Budapest: Akademiai Kiado, 1976), p. 272.
6. የገበሬ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አዝርእትና ቋሚ ሰብል እርሻ ልማት ፣ የግብርና ልማት 10 ዓመት መሪ ዕቅድ, ክፍል 1, ገጽ 23 (ያልታተመ)
7. የግብርና ሚኒስቴር መዋቅራዊ ጥናት ጥራዝ 1 መስከረም 1976 ፣ ገጽ 8 (ያልታተመ) ።
8. ሠርቶ አደር ፣ ቁጥር ኅዳር 27 ፣ 1977 ገጽ 2
9. ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ያቀረቡት ሪፖርት, ፣ የካቲት 1973 ፣ ገጽ 34—35 (ያልታተመ ።)
10. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ሰነዶችና ውሳኔዎች ፣ ታኅሣሥ 1975 ፣ አዲስ አበባ ፣ ገጽ 46 ።
11. እስከ 1974 ያለው ከ10 ዓመት ጠቋሚ ዕቅዶች የተውጣጣ ሲሆን በተለይ የ1975 ግን ከ5ኛው ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ፣ ኅዳር 1976 ገጽ 10 እና 44 ነው (ያልታተመ)
12. የግብርና ሚኒስቴር፡ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃ መምሪያ መረጃ ፣ ጥቅምት 1976 (ያልታተመ) ።
13. See for example, Graham Bannocketal, The Penguin Dictionary of Economics, pp. 360-61.
14. See for example, Encyclopaedia Britanica, Vol. 7 p. 931.
15. የግብርና ሚኒስቴር መዋቅራዊ ጥናት ፣ መስከረም 1976 ፣ ገጽ 15 (ያልታተመ) ።
16. የዘመቻ አምስት ግምገማ ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ ኅዳር 1976 ገጽ 25—27 (ያልታተመ) ።
17. ብ· አ· ም· ዘ· ማ· ፕ· ጠ·መ የግብርና ምርትን በአጭር ጊዜ ለማሳደግ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች በተደረገው አገርአቀፍ ሴሚናር መጋቢት 30 እና ሚያዝያ 1 ቀን 1975 ፣ አዲስ አበባ ፣ ልዩ እትም ፣ ቁጥር 8 ገጽ 2 ።
18. የመንግሥት እርሻዎች አመሠራረት የተከናወኑ ተግባሮች ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የወደፊት አቅጣጫ ፤ የመንግሥት እርሻ ልማት ሚኒስቴር ፤ ሐምሌ 1975 ፣ ገጽ 5 ፣ 8፤11 ፣ 15—22 (ያልታተመ) ።
19. ከእርሻና ልማት ባንክ የተገኘ መረጃ (ያልታተመ) ።
20. የሳይንስና ቴክኖሎጂ የ10 ዓመት መሪ እቅድ ፣ የግብርና ቴክኖሎጂ ግምገማ ፣ ሚያዝያ 1975 ፣ ገጽ 13—14 ፤ 17 ። (ያልታተመ) ።

Digitized by Google

21. ብ.አ.ዎ.ግ.ፕ.ጠ.መ. የዘመቻ አምስት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ኅዳር 1976 ፥ ገጽ 28 ።

22. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 27 ።

23. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች ፥ የካቲት 1973 አዲስ አበባ

24. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ሰነዶችና ውሳኔዎች፥ ታህሣሥ ፥ 1975 ፥ አዲስ አበባ ፥ ገጽ 130 ።

25. Marx und Uber Feuerback, Marx-Engels Archio (Frankfurt, N.D.) Rol. I, p. 284. as cited by Paul Baran, p. 434.

26. ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓ መሥራች ጉባኤ ያቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ፥ ጳጉሜ 1976 ፥ አዲስ አበባ ።

27. የገበሬ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አዝርዕትና ቋሚ ሰብል እርሻ ልማት ፥ የግብርና ልማት 10 ዓመት መሪ ዕቅድ ብ-አ-ዘ- ግ-ፕ-ጠ-መ ፥ ሐምሌ 1974 ፥ ገጽ 70—81 (ያልታተመ ።)

28. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 47 — 63

29. የግብርና ሚኒስቴር መዋቅራዊ ጥናት፥ ጥራዝ 1 መስከረም 1976 ፥ ገጽ 4

30. ሠርቶአደር ፥ ቁጥር 225 ገጽ ? (መስከረም 24 1977 ።)

31. ሠርቶአደር ቁጥር 232 ኅዳር 13 1977 ገጽ 6 ።

32. ስለአስቸኳይና የአጭር ጊዜ እርምጃዎች የተዘረዘረው ሐሳብ የተቀነባበረው በድርቅ ምክንያት ችግሮችን ለመቋቋም ከተዘጋጀው የድርጊት ፕሮግራም አጠቃላይ ሐሳቦች ጥቅምት 1977 አዲስ አበባ (ያልታተመ) ነው ።

33. ሠርቶአደር ቁጥር 232 ኅዳር 13 1977 ገጽ 7 ።

Digitized by Google

ሕዝባዊ ቁጥጥርና አንዳንድ ችግሮቹ

—ግርማ ተፈራ ዘማርያም

የሠራተኛው መደብ ጨቋኝና በዝባዥ መደቦችን በማንበርከክ የፖለቲካ ሥልጣኑን በእጁ ከጨበጠ በኋላ በዚህ ሥልጣን አማካኝነት ተሳትፎውን ከፍ በማድረግ የራሱን መንግሥት ፣ አስተዳደርና አመራር የሚያጠናክርበት አንዱ መሳሪያ ሕዝባዊ ቁጥጥር ነው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ይኸው የሕዝብ መገልገያ ያለውን አብዮታዊ አስተዋጽኦና ከሌሎች አንጋፋ ሶሻሊስት አገሮች አብዮታዊ እንቅስቃሴ የተቀሰሙ ልምዶችን በመጠቀምና በየደረጃው ያጋጠሙ ችግሮችን በመመርመር በኢትዮጵያ የሕዝባዊ ቁጥጥር መድረክ እስከአሁን ያደረገውን አጠቃላይ እንቅስቃሴና ያጋጠሙትን አንዳንድ ችግሮች ለማውሳት ይሞከራል ።

የሶሻሊስት አብዮት በድል አድራጊነት መውጣት ፣ ሠራተኛው ሕዝብ ከማንኛውም ዓይነት ጭቆናና ብዝበዛ ተላቆ ፍትሕ የተስተካከለበትን ኅብረተሰብ ለመገንባት የሚያስችለው መሆኑ ዕውቅ ነው ። ይህ ብቻም አይደለም ። ለዘመናት ሲጨቆን የነበረው ሰፋፊ ሰፊ ሕዝብ ራሱንና መንግሥትን በመምራት ተግባር ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ ለማድረግ ያስችለዋል ። በታሪክ ውስጥ የሠራተኛውን ሕዝብ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ልዕልና አረጋግጦ በሕዝባዊና በመንግሥታዊ አስተዳደር ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲያደርግ አስፈላጊውን አመቺ ሁኔታ የሚፈጥረው ሶሻሊዝም ብቻ ነው ።[1]

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የብዝበዛና የጭቆና ምንጭ የሆነው የምርት መሳሪያዎች የግል ባለቤትነት ስለሚወገድ ሠርቶአደሩ ሕዝብ ያለምንም አድልዎና ልዩነት በግንባታው ተግባር ውስጥ እንዲሳተፍ ይደረጋል ። ሶሻሊዝም ሕዝቡ በተለያዩ መስኮች በመሳተፍ የዲሞክራሲ መብቱን እንዲያዳብር የሚያስችሉትን ሁኔታዎች የሚያመቻችለት ሲሆን ፣ ከነዚህም ዋነኛው የትግል መድረኮች መካከል አንዱ የሕዝባዊ ቁጥጥር ሥርዓት ነው ። ኅብረተሰቡ በዚህ አካል ውስጥ በንቃት በመሳተፍ የመንግሥትና

Digitized by Google

የሕዝብ ኑብረት በሚገባ ተጠብቆ ጥቅም ላይ መዋሉን ከማረጋገጥ አንስቶ ፥ የሶሻሊስት ዲሞክራሲን እስከማዳበር ድረስ አስፈላጊውን የትግል ልምድና ማኅበራዊ ተግባሮችን በብቃት መምራት ይማራል ።

ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በኋላ አዲሱ የሶቭየት መንግሥት ትልቅ ትኩረት ካደረገባቸው ጉዳዮች መካከል የሕዝባዊ ቁጥጥር ሥርዓትን በማጠናከር የአድኃሪ ኃይሎችን ፀረ—አብዮት ተግባር መቆጣጠርና የሶሻሊስት ኢኮኖሚን መሠረት ማጠናከር ይገኙበታል ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የግንባታ ሂደት ውስጥ የቁጥጥር ተቀዳሚ ተግባር ሠራተኛው ሕዝብ በግንባታው ጥረት ውስጥ የሚኖረው ተሳትፎ እንዲጐላና በራሱም ጠቅላላ ጥረት እራሱን ለመቆጣጠርና ለመምራት እንዲችል ማድረግ ነው ። የቦልሼቪክ ፓርቲ መሪና የሶቭየት መንግሥት መሥራች የነበረው ሌኒን ሶሻሊዝምን በመገንባት ረገድ በሚነሱ የንድፈ ሐሳብና የተግባር ጥያቄዎች ውስጥ በመላ ሀገሪቷ ውስጥ የሕዝባዊ ቁጥጥርን ሥርዓት የማደራጀቱንና ትክክለኛ አሠራሩንም የማረጋገጡን ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠው ነበር ። ይህም ያለ ምክንያት አይደለም ፤ በአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ውስጥ የቁጥጥር ሥርዓት በቅርጹም ሆነ በይዘቱ ተጠናክር በአብዮቱ ውስጥ የተገኙትን ድሎች ለመጠበቅና የበለጠም ለማጠናከር ብሎም የሕዝቡን መሠረታዊ ፍላጐት ለማሟላት የሚያስችለው መሣሪያ ጭምር በመሆኑ ነው ።

ሶሻሊዝምን ለመገንባት ጥረት በሚደረግበት ወቅት ሁሉ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊነት የሚመነጨው ከአዲሱ ሥርዓት ባሕርይና በተለይም ደግሞ የሚኖረው የኢኮኖሚ ግንኙነት በማኅበራዊ ይዞታ ላይ ከመመሥረቱ አኳያ ነው ። በሶሻሊዝም ሠራተኛው ሕዝብ ከማንኛውም ዓይነት ጭቆና ነፃ ስለሚሆን የራሱን መንግሥትና የሕዝባዊ አካሎችን እንቅስቃሴ በሚገባ ለመከታተል እንዲችል በራሱ የሚመረጡና ለርሱ መሠረታዊ ጥቅሞች የቆሙ ተወካዮች የሚሳተፉበትን አካላት ያዋቅራል ። ይህም ጠቅላላ ሥርዓቱን በዕቅድ ከመምራትና የኢኮኖሚ ዕድገቱንም በተመጣጠነ መልክ ከማንቀሳቀስ ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው ። በሶሻሊስት ሥርዓት ሕዝባዊ ቁጥጥር በማኅበራዊ ጠባዩ ኢኮኖሚውን በተመጣጠነና በዕቅድ እንዲመራ ከማድረግ ተነጥሎ የማይታይ ነው ።

የሠራተኛውን ሕዝብ ጠቅላላ የግንባታ ጥረት የመምራትና ለዘላቂ ግብ የማብቃት ግንባር ቀደም ተልዕኮ ባለበት በኮሚኒስት ፓርቲው አስተያየት የሕዝባዊ ቁጥጥር አደረጃጀትና አወቃቀር የሶሻሊስት ኢኮኖሚ አመራርን ለማጠናከር ከፍተኛ አጋዥ ኃይል ነው ። ፓርቲው ሕዝባዊ ቁጥጥር ሶሻሊስት ዲሞክራሲን ለማዳበርና የሕዝብን የፈጠራ ችሎታ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑንም ይገነዘባል ። ምክንያቱም የዚህ ዓይነቱ የቁጥጥር ሥርዓት ጥፋተኛን (በአካል) በማጥፋት ላይ የተመሠረተ አይደለም ። እንዲያውም የአስተማሪነትና ስህተቶችን በቀና መንገድ የማረሙ ባሕርይው ጐልቶ የሚታይበት ነው።[2] ስለዚህ የሕዝባዊ ቁጥጥር አሠራርና አመራር የፓርቲውን ፖሊሲ ተከትሎ የሠራተኛውን ሕዝብ መንግሥት በማጠናከር መልክ የሚተለም ነው ።

ከዚህም ሌላ ሕዝባዊ ቁጥጥር የዜጐችን በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የኃላፊነት ድርሻ በማጐልበት በተለያዩ የግንባታ ዘርፎች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉም የሚያስችል ሥርዓት ነው ። በመሆኑም የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች በአዲሱ የሠራተኛ መንግሥትና በሠራተኛው ሕዝብ መካከል እንደ ድልድዮች ሆነው የሚሠሩ ናቸው ። ለሶሻሊዝም ግንባታ በጋራ መታገላቸውም አንድነታቸውን ያጠናክረዋል ። የመንግሥትን ትልሞች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥና በሌላ በኩል ደግሞ ሕ

Digitized by Google

ዝቡ በየተሰማራበት የሥራ ቦታ ምርታማ
ነትንና ለሀገሩና ለሶሻሊዝም የሚኖረውን
ፍቅር በማሳደግ የላቀ ሚና ይጫወታሉ ።
በዚሀ መልኩ የሚዋቀሩ የቁጥጥር አካላት
ተጨባጭ የሆነ የኅብረተሰቡን ፍላጐት የ
ሚያንጸባርቁና ለዚህም ዓላማ በተግባር የ
ቆሙ ናቸው ። በተጨማሪም ሕዝባዊ የቁ
ጥጥር አውታሮች ኅብረተሰቡ የራሱንና
የመንግሥትን ንብረት የመንከባከብ ፣ ሶሻ
ሊስት ሕጐችን የመጠበቅና የአስተዳደር
ጥበብን የመማር ልምድ የሚያካብትበት
ትምህርት በመሆን ያገለግላሉ ።

የሕዝባዊ ቁጥጥር ሥርዓት መስፈንና
በዚህም ላይ ተመስርቶ የሶሻሊስት ኢኮ
ኖሚ አመራር መጠናከር ሠራተኛው ሕ
ዝብ አዲስ ዓይነት የሥራ ዲስፕሊን እንዲ
ያዳብር ፣ የማኅበራዊ ይዞታ ስሜት በአዕ
ምሮው ውስጥ እንዲሰርጽ ፣ የጋራ ዕድገት
ፍላጐትንና አስተሳሰብን በጥልቀት እንዲ
ረዳ በተለይም ደግሞ ብኩንነትን ፣ ምዝበ
በራን ፣ ጉቦኝነትንና ሌሎችም ለማኅበራዊ
ዕድገት ዕንቅፋት የሆኑ አዝማሚያዎችን
በብርቱ እንዲዋጋ ያስችሉታል ።

የሶሻሊዝምን ግንባታ ለማፋጠን በብዙ
ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦችን በፈቃደኝ
ነትና በአብዮታዊ ስሜት በቁጥጥሩ ተግባር
ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ የሠራተኛውና የገ
በሬው መንግሥት ቅድሚያ ተግባር ይሆ
ናል ። ነገር ግን የመንግሥታዊና የሕዝባዊ
ቁጥጥርን ጽንሰሐሳብ በትክክል በኅብረ
ተሰብ ውስጥ ግንዛቤ እንዲያገኝ የማድረግ
ተግባር ቀላል አይደለም ። ስለሆነም ማን
ኛውም የሶሻሊስት አብዮት በቅድሚያ ከ
ሚያጋጥሙት ችግሮች አንዱ የሠራተኛ
ውን ሕዝብ ሥልጣን ለማጠናከር አዳዲስ

ስልቶችንና ዘዴዎችን ቀይሶ በተግባር የመ
ተርጐም ጥያቄ ነው ።

የሕዝብ ጠላቶች ሕዝብ በመንግሥት ፣
በሕዝባዊ አስተዳደርና አመራር ውስጥ በ
ብቃት እንዳይሳተፍ በየወቅቱ የቲሊያዩ አዘ
ናጊና አድኃሪ መፈክሮችን ይዘው ከመነሳት
እንደማይቆጠቡ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ።
እነዚህን የሶሻሊዝምን ጠላቶች ለመደምሰ
ስ ፣ የምርት አመራርንና ክፍፍልን ትክክ
ለኛ ፈር ለማስያዝ ሠራተኛው ሕዝብ
በቁጥጥር ጉዳዮች ላይ ጠንክሮ መገኘት
ይኖርበታል።ሠራተኛው ሕዝብ በራሱ መን
ግሥት አማካይነት የሕዝባዊ ቁጥጥርን ሥር
ዓት በብሔራዊ ደረጃ በማደራጀት ራሱንና
ሶሻሊዝምን ከተቀናቃኞች መከላከል አለ
በት ።

በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ
የሚነሳ ሕዝባዊ አብዮት ሠራተኛውን ሕ
ዝብ የፖለቲካ ሥልጣን በማስያዝ ብቻ የሚ
ጋሰን አይሆንም ። በአንድ በኩል የሠራተ
ኛውን ሕዝብ የፖለቲካ የበላይነት የሚታ
ገው አድኃሪ መደቦችን መደምሰስ ፣ በሌ
ላ በኩል ደግሞ አዲሱን ሥርዓተ ማኅበር
ዕውን ለማድረግ የግንባታውን ተግባር በየ
ዘርፉ ማጠናከር ትልቁ ተግባር ነው ። ይህ
ን ተግባሩን በትክክል ከተወጣው ፣ ከካፒ
ታሊዝም የላቀውንና በሁለንተናዊ መልኩ
ብልጫ ያለውን አዲሱን ማኅበራዊ ሥር
ዓት ዕውን ማድረጉ የማያጠራጥር ነው ።

«ሶሻሊዝም ከካፒታሊዝም የላቀ መሆኑን
ከሚያሳይባቸው መስኮች መካከል ይህ ሥር
ዓተ ማኅበር የግንባታ ተግባር ውስጥ መላው
ን ኅብረተሰብ ለማሳተፍ የሚያስችሉ አመቺ
ሁኔታዎችን የሚፈጥር መሆኑና በተለይም
ማኅበራዊ ምርትን በማደራጀት ፣ በዕቅድ
በመምራትና በተለያዩ መስኮች የላቁ ድሉ
ችን ለማስገኘት መቻሉ ነው ።»[3] የምርት

Digitized by Google

ማፍሬያ መሣሪያዎች ባለቤትነቱም በማኅበ
ራዊ ይዞታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የም
ርት ኃይሎችን ዕድገት በማፋጠንና ግንኙ
ነቱንም ሶሻሊስታዊ ፈር በማስያዝ የተመጣ
ጠነ ሁለንተናዊ ዕድገትን ያስገኛል ።

ሕዝባዊ ቁጥጥር በሶቭየት ኅብረት

ሕዝባዊ የቁጥጥር ሥርዓትን በማስፈን
ረገድ የሶቭየት ኅብረት ልምድ እንደሚያስ
ረዳን ከጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት መባቻ
ጀምሮ በሌኒን ይመራ የነበረው የቦልሼቪክ
ፓርቲና የሶቭየት ኅብረት መንግሥት የሕ
ዝባዊ ቁጥጥር አውታርን በመዘርጋቱ ሠራ
ተኛው ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅሞቹንና
መብቶቹን እንዲቀዳጅና እንዲያስጠብቅ
ብርቱ መሣሪያ በመሆን ያገለግሉታል ።

የሶቭየት ሥልጣን ከተመሠረተ ጀምሮ
የቁጥጥር አካሎች ቅርጽና የሥራ ዘዴያቸው
ብዙ ለውጥ ተደርጉባቸዋል ። ስያሚው አያሌ
ጊዜ ቢለዋወጥ ማለትም የሠርተአደሩ ቁጥ
ጥር ፣ የሠርተአደሩና የገበሬው ቁጥጥር ኮሚ
ሽን ፣ የሶቭየት ቁጥጥር ኮሚቴ ፣ ሕዝባዊ ቁጥ
ጥር በመባል የተለያየ ስም ይሰጠው እንጂ
ተግባራዊ ይዘቱ አንድ ነው ። የሁሉም ተግ
ባር መንግሥታዊ ቁጥጥር ከማኅበራዊ ቁጥ
ጥር ጋር በአንድነት የምርትን ሥራ ለማሻ
ሻልና ለሥራው ትክክለኛውን አመራር ለመ
ስጠት ፣ በሀገሪቱ የአመራር ተግባር መላው
ሕዝብ እንዲሳተፍ ለማድረግ የሚያስችሉ
ትን ሁኔታዎች ለመፍጠር የሚያስችል ነው ።[4]

በሶቭየት ኅብረት ሕገ መንግሥት መሠ
ረት የቁጥጥር ሥርዓት አካሎች በየደረጃው
ከታች ጀምሮ እስከመላው (ብሔራዊ) የሶ
ቭየት ኅብረት የቁጥጥር አካል ድረስ የሚ
የቀሩት በሕዝባዊ ተወካዮች ምክር ቤቶች
ነው ። ለሶቭየት ኅብረት የሕዝባዊ ቁጥጥር
ኮሚቴ አመራር የሚሰጡት ሸንጐ የሶቭየት
ኅብረት ከፍተኛ ምክር ቤት (የብሔራዊሸን
ጐ) ፕሬዚዲየምና የሶቭየት ኅብረት የሚኒስት
ሮች ምክር ቤት ናቸው ። የሕዝባዊ ቁጥጥር
ኮሚቴ ስለሚያካሂደው ሥራ ለከፍተኛው
ምክር ቤት ፕሬዚዲየምና ለሚኒስትሮች
ምክር ቤት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል ።
በቁጥጥር ሥራዎች የተገኙትን መረጃዎች
መሠረት በማድረግ የቁጥጥር ኮሚቴው
ለከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዲየምና ለሶቭ
የት ኅብረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አዲ
ስ ሐሳቦችን ያቀርባል ።

የኅብረት ሪፐብሊኮችና የአውቶኖመስ
ሪፐብሊኮች የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች
ከመንግሥት ሥልጣንና የአመራር አካሎች
ጋር ያላቸው ግንኙነት ተመሳሳይ ነው ።
በየአካባቢው ያሉት የክልል የቁጥጥር ኮሚ
ቴዎች ተግባራቸውን የሚያካሂዱት በአካ
ባቢው የሕዝባዊ ተወካይ ምክር ቤት መሪ
ነት ሲሆን ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱና
ለበላይ የሕዝባዊ ቁጥጥር አካሎች ነው ።
የሕዝባዊ ቁጥጥር አሠራርም በዲሞክራሲ
መርሆዎች ላይ ተመስርቶ የተዋቀረ በመ
ሆኑ ሕዝባዊ አስተዳደርና ሥልጣን እንዲ
ጠናከር ረድቷል ።

የሠርቶአደሩና የገበሬው ቁጥጥር ኮሚ
ሽኖች ከሠርቶአደሩ ሕዝብ ለተውጣጡ
አስተዳዳሪዎች ተግባራዊ ግሰልጠኛ ሆነው
ሰፋ ያለ የሥራ ልምድ መስጠት ችለዋል ።
በቁጥጥር ሥርዓት ከተካፈሉት ሠርቶአደ
ሮች መካከል ብዙዎቹ የፋብሪካ ፣ የማዕድን ፣
የባንክና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥራ
መሪ (ዲሬክተሮች) ለመሆን በቅተዋል ።
ሀገሪቱ በተለይ በወቅቱ የደረሱባትን ችግ

Digitized by Google

ሮች ለመፍታት የቻለችው በነሱ ተሳትፎ
በተገኘው ውጤት ጭምር ነው ። ኢንዱስ
ትሪን የመገንባትና የማጠናከር ተግባር ማካ
ሄድ የቀጠለችውም በነዚህ ዜጎች ከፍ
ተኛ አስተዋጽኦ ነው ።

በሶቪየት ኅብረት ውስጥ የሕዝባዊ ቁጥ
ጥርን ዓላማ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ
የተቻለው በተለይ በመንግሥታዊና በሕዝ
ባዊ ድርጅቶች ውስጥ ነው ። በሀገሪቷ ውስ
ጥ በየትኛውም መስክ ወይም በማንኛውም
የመንግሥትም ሆነ ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስ
ጥ የቁጥጥሩ አሠራር ዲሞክራሲያዊ ባህርይ
ያለው ነው ። ይህም ከማዕከላዊነት አስተሳ
ሰቡ ጋር የተጣጣመ ከመሆኑም በላይ እንደ
ተጨባጭ ሁኔታ አንዱ ከሌላው ጐልቶ ሊ
ታይ ይችላል ። በመሠረተ ዓላማው ግን የሕ
ዝባዊ ቁጥጥር አደረጃጀትና አሠራር ዲሞ
ክራሲያዊ ጠባይ ያለው ነው። እነዚሁ በመ
ንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ውስጥ
የሚቋቋሙት የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች
በአሠራር ቅርጻቸው የተለያዩ መንገዶችን
ቢከተሉም በይዘትና ዓላማ አንድ ናቸው ።
ሁሉም ለአንድ ዓላማ የቆሙ ናቸው።ስለ
ዚህም በማንኛውም ሥፍራ የሕዝባዊ ቁጥ
ጥር አካላት ሥራና ጠቅላላ እንቅስቃሴያ
ቸው ሁሉ የፖለቲካ አመራር የሚሰጠውን
የኮሚኒስት ፓርቲውን ፖሊሲና አመራር
ተግባራዊ የሚያደርጉ ናቸው ።

በሶቭየት ኅብረት የቁጥጥር ኮሚቴዎች
ሥራ በአብዛኛው የሚከናወነው በሰፊው
ሕዝብ ተሳትፎ ነው ። በኮሚቴዎቹ ውስጥ
ደመወዝ የሚከፈላቸው ቋሚ ሠራተኞች
ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው ። ለምሳሌ ከ6
ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በሚገኙባት በሞስኮ
ከተማ የተቋቋሙት 43 የከተማና የወረዳ
የቁጥጥር ኮሚቴዎች በብዙ መቶ ሺህ የሚ
ቆጠሩ የሕዝባዊ ቁጥጥር አባላትን ሥራ የሚ
ያቀነባብሩ 80 ብቻ ደመወዝ የሚከፈላቸው
ቋሚ ሠራተኞች አሏቸው ።[5]

ሕዝባዊ ቁጥጥር በሶቪየት ኅብረት ውስ
ጥ መጠናከር በጀመረበትና አገሪቱ የእርስ
በርሱና የውጭ አድኃሪ ኃይላት ከፍተው
ባት በነበረው ጦርነት የደቀቀው ኢኮኖሚ
ማንሠራራት በጀመረበት በዚያ ወሳኝ ወቅ
ት የሕዝባዊ ቁጥጥር አባላት መከተል ስላለ
ባቸው ዘዴ ብላድሚር ኢሊች ሌኒን ሲናገር
«የሠርቶ አደሩና የገበሬው ቁጥጥር ከፍተኛ
ተግባር ጥፋተኛውን መያዝና ማጋለጥ ሳይ
ሆን ጉድለት የሚታረምበትን መንገድ መ
ቀየስ ነው ።[6] » በማለት እንደገለጸው ከብ
ሔራዊ ጀምር እስከታች የተዋቀሩት
የእነዚህ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች
አባላት ስለቁጥጥር ምንነት ለሠራተ
ኛው ሕዝብ የማስረዳት ፣ የማስተማርና
የማሳመንን አሠራር ስልቶች አጥብቀው
የሚከታተሉ ናቸው ። በተለይም በጠቅላ
ላው እንቅስቃሴያቸው በትክክልለኛ መረጃ
ላይ የተመሠረቱ ፈጣን ውሳኔዎችን በመስ
ጠትና በማሳመን የሚያከናውኑት ተግባር
በሕዝቡ ዘንድ ታማኝነትንና ተወዳጅነትን
ሊያተርፍላቸው ችሏል ። ማሳመን በኮሚ
ኒስት ፓርቲው አበይት መርሆዎች ውስጥ
አንዱ ተፈላጊ የአሠራር መርህ ነው።ይህ
የአሠራር ስልት በሁሉም የመንግሥትና
ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የዜጎች ዲሞክ
ራሲያዊ መብት እንዲዳብር ከመርዳቱም
ባሻገር ማንኛውም ተግባርና በተለይ በግ
ንባር ቀደሙ የፖለቲካ ድርጅት የሚተላለ
ፉት ውሳኔዎች ያለማወላወል በትክክል
በሥራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ነው ።

Digitized by Google

በሶቭየት ኅብረት የሕዝባዊ ቁጥጥር አካሎች አወቃቀር *



* « ዩ.ሪ ዛክሬቭስኪይ፣ ሕዝባዊ ቁጥጥር በሶቭየት ኅብረት» ሞስኮ የኖቮስቲ አገልግሎት ማሳተሚያ ቤት፣ 1983 ከገጽ 22 የተወሰደ ።

በሶቪየት ኅብረት ውስጥ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴ አወቃቀር

1. የሶቪየት ኅብረት የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴ ፣
2. የኅብረት ሪፐብሊኮች የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች፣
3. የአውቶኖሚያዊ ሪፐብሊክ ፣ የአካባቢ ፣ የአውራጃ ፣ የአውቶኖሚ ግዛት የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች ፣
4. የአውቶኖሚያዊ አካባቢ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች፣
5. በወረዳ በሚከፈሉት ከተማዎች ያሉት የከተማ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች፣
6. የከተማ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች፣
7. በከተማ ክልል ውስጥ የወረዳ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች፣
8. የምርት ተቋሞች ፣ የትንጅቶች ፣ የመሥሪያ ቤቶች የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች
9. የወረዳ ፣ በገጠር ውስጥ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች ፣
10. በሠፈራ ቦታዎችና በገጠር መንደሮች የሕዝቦች እንደራሴዎች ሥር ያሉ እንዲሁም በምርት ተቋሞች ፣ በኅብረት እርሻ ማኅበሮች ፣ በመሥሪያ ቤቶች የሚገኙ የሕዝባዊ ቁጥጥር ቡድኖች፣
11. በሥራ ክፍሎችና በዎርክ ሾፖች ያሉ የሕዝባዊ ቁጥጥር ቡድኖችና ንዑስ ቡድኖች፣

በሶቪየት ኅብረት ውስጥ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች በሶሻሊስት አመራረትና አስተዳደር ላይ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ መብታቸው በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ውስጥ የተደነገገ ነው ። በሁሉም መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ላይ ሁሉ ጉዳዮችን የመከታተል መብት አላቸው። «የሕዝባዊ ቁጥጥር አካሎች የመንግሥት ዕቅድና ውጥኖች መሟላታቸውን ይቆጣጠራሉ ፤ መንግሥታዊ ሥነ ሥርዓት የሚጥሱትን ፣ የብሔረተኝነት ዝንባሌ አስተሳሰቦችን ፣ ሁሉን እኔ ልሥራ ባዮችን ፣ ትክክል ያልሆነ አሠራርን ፣ ንብረት አባካኝነትን ፣ ጉዳይ ወዛፊነትንና የቢሮክራሲ ግንቆን ያጋልጣሉ ። እንደዚሁም የመንግሥት መ/ቤቶች ሥራዎች በሚገባ መካሔዳቸውን ያረጋግጣሉ »[7]

በሶቪየት ኅብረት የተለያየ ሙያ ያላቸው 10 ሚሊዮን የሚሆኑ ሠራተኞች መሠረታዊ በሆኑት የቁጥጥር አካሎች ውስጥ በበጐ ፈቃደኝነት ይሳተፋሉ ። በየሁለት ዓመት ከስድስት ወር ተሰሚነትና ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሐቀኛ ጓዶች በቁጥጥሩ ተግባር እንዲካፈሉ በግልጽ ስብሰባ በይፋ ይመረጣሉ። እ. ኤ. አ እስከ 1983 ባለው ጊዜ ውስጥ በሶቪየት ኅብረት «762 ሺ የሕዝባዊ ቁጥጥር ቡድኖች ፣ 504 ሺ የቁጥጥር ንዑስ ቡድኖች ተቋቁመው ሥራውን ያካሂዱ ሲሆን ፣ በነዚህም ቡድኖች ውስጥ ካሉት ተመራጮች መካከል 4.7 ሚሊዮን ሠራተኞች ፣ 15 ሚሊዮን ገበሬዎች ፣ 3.5 ሚሊዮን የመሥሪያ ቤት ባልደረቦች ፣ 45.6ሺ ተማሪዎች፣ 178.5 ሺ ጡረተኞችና አዛውንቶች»[8] እንደተሳተፉ ተረጋግጧል ።

በአጠቃላይ ሶቪየት ኅብረት ከታላቁ የጥቅምት አብዮት በኋላ በኮሚኒስት ፓርቲው አመራር ፣ በሠርቶ አደሩ ያልተቆጠበ ተሳትፎና በየደረጃው በተዘረጉት ሕዝባዊና መንግሥታዊ የቁጥጥር አውታሮች ያላሰለሰ የአፈጻጸም ክትትል ባካሔደችው የግንባታ ተግባር ለሌሎች የሶሻሊዝምን ፈለግ በመከተል ላይ ላሉ ሀገሮች አርአያነት ያላቸው አያሌ ውጤቶችን ለማስመዝገብ ችላለች ። በሳይንሳዊ ዕቅድ ላይ የተመሠረተው ይህ ጠንካራ ሶሻሊስት ኢኮኖሚዋም ግናቸውንም የሥራ ትልም በተግባር ለመተርጐምና ጊዜና የዕድገት ደረጃ ለሚያቀርባቸው

Digitized by Google

ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ችሎታና አቅም ያለው መሆኑን በተጨባጭ አስመስክሯል ።

በሶቭየት ኅብረት ልምድ አንጻር የሕዝባዊ ቁጥጥር አንዳንድ ችግሮች

የሶሻሊስት አብዮት ድል ከተቀዳጀና ሠራተኛው ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣንን በእጁ ካስገባ በኋላ በብሔራዊ ኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካና በማኅበራዊ ኑሮ መስኮች ላይ የሚያካሂደው ቁጥጥር የዚሁ ሥልጣን ከፍተኛው ተግባር መሆኑ በተደጋጋሚ ተወስቷል ። ታላቁ ምሁር ቭላድሚር ኢሊች ሌኒን በጥቅምቱ አብዮት መባቻ ላይ «እነዚህ ደም መጣጭ መዥገሮች በሶሻሊስቱ ኅብረተሰብ ንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ አብዮታዊ ወኔ የሰፈነበት ሠርቶአደሮችና ፈቃደኛ፣ነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞችና ገበሬዎች የሚሳተፉበት የቁጥጥርና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ማቋቋም አለብን [9] » በማለት የተናገረውም የሕዝባዊ ቁጥጥርን አስፈላጊነት በሚገባ የሚያስገነዝብ ነው። ሆኖም ሕዝባዊ ቁጥጥር ስሙ በትክክል እንደሚያመለክተው በራሱ በሰፊው ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ እንጂ የተለየ ዕውቀትና ሙያ ባላቸው ጥቂት ምሁራን ብቻ የሚካሔድ አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ። ስለሆነም ሥልጣን የያዘውና ለአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ የተዘጋጀው ሰፊው ሕዝብ ይህን ልምድና ዕውቀት እንዴት ሊያገኝና ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል ? ከዚህም ባሻገር ባለፈው ጊዜ (በወደቀው ኋላቀር ሥርዓት) በቁጥጥር ዘርፍ የተገኘው ልምድ ለአሁኑ ማለትም ለአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ ሙሉ በሙሉ ሊያገለግል ይችላል ? የሚሉትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም ።

አንዳንድ የቡርዧ ምሁራንና ከላሾች የቁጥጥር ዘዴዎችን የተወሳሰቡ ፣ አስቸጋሪዎችና በቀላሉ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ ተግባሮች ናቸው በማለት ንቃተ ሕሊናው ያልዳበረውን የኅብረተሰብ ክፍል ለማወናበድና እጁን አጣጥፎ እንዲቀመጥ ለማድረግ ሞክረዋል ። እውነቱ ግን «ሌላው ቀርቶ አርጌው የዛሩ አገዛዝ ሳይቀር ሰፊውን ሕዝብ በሚሠራው ሥራ ፣ ፀባይና በሙያው አንጻር በማስተባበር ቁጥጥርን ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚቻል ጠንቅቆ ያውቅ እንደነበር ታሪክ ያረጋግጥልናል ። ይሁን እንጂ ሕዝቡን በዚህ መልክ ማስተባበሩና ራሱን የራሱ ንብረትና ሀብት ተቆጣጣሪ ማድረጉ የአድኃሪው አገዛዝ ሕልውና የሚያናጋው በመሆኑ ዓላማውን ተግባራዊ ሳያደርገው ቀርቷል ።» [10] ስለዚህ ሌኒን « ... ማናቸውም ማንበብና መጻፍ የሚችል ፣ ስለአራቱ የሂሳብ መደቦች ዕውቀት ያለውና በደረሰኝ ላይ በትክክል ለማስፈር የሚችል ሰው የመቆጣጠርና መዝገብ የመያዝ ተግባርን ሊያከናውን ይችላል [11]» በማለት እንደአስገነዘበውና በተግባርም እንደተረጋገጠው ቁጥጥር ውስብስብ እንዳልሆነና በሰፊው ሕዝብ ተሳትፎና በመሠረታዊ የሂሳብ ዕውቀት ደረጃም ጭምር ሊከናወን እንደሚችል ግልጽ ሊሆን ይገባል ። በመሆኑም ከማይምነት የተላቀቀ ማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል የቁጥጥሩ ተግባር ሙሉ ተሳታፊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያሻል ።

ሰፊው ሕዝብ ለዚህ ዓይነቱ ተሳትፎ አዲስ በመሆኑ በእርግጥም በመጀመሪያው የተግባራዊ እንቅስቃሴ ወቅት መጠነኛ ስህተቶች ሊፈጠሩና ለፀረ ሕዝብ ኃይላት አድኃሪ ቅስቀሳ በር ሊከፍቱ ይችላሉ ። «ከዚህም በላይ ደግሞ ባለፈው ጊዜ የተገኘው የአመራር ልምድ ለአሁኑ ሁኔታ ሊያገለግል አይችልም ። የመንግሥትን ሥልጣን በእጁ የያዘው አዲስ መደብ ስለሆነ የአርጌውን መንግሥት አካሎች ማፍረሱና አዲስ የአመራር ዘዴዎችን መፍጠሩ የማይቀር መሆኑ ግልጽ ነው ። ለራሳቸው አዲስና ያልተለመደውን ሥራ መሥራት የጀመሩት ጓዶች በሙሉ ድፍረት አለማሳየታቸውና ስህተት ማድረጋቸው የማይቀር ነው ። [12] ይሁን እንጂ ይህ ችግር ከልምድ ማካበትና በአጠቃላይም ከንቃተ ሕሊናና ከሕዝባዊ ተሳትፎ መጎልበት ጋር የተቆራኘና ከዚህ

Digitized by Google

ጋር የሚፈታ መሆኑን የአንጋፋዎቹ የሶቪ
የት ኅብረት ሕዝብ የቁጥጥር አውታሮች
እንቅስቃሴና ውጤት ሊያረጋግጡልን ችሏል።

በሶቪየት ኅብረት ልምድ እንኳር በሕዝ
ባዊ ቁጥጥር ዘርፍ ከተከሰቱት ችግሮች መ
ካከል ሌላው ደግሞ በሕዝባዊ ቁጥጥር ተመ
ራጮችና በአንዳንድ የአስተዳደር ኃላፊዎች
መካከል ተገቢው የሥራ ትብብር አለመ
ኖሩ ነበር ። ይህም ችግር የሚመነጨው አ
ንዳንዱ ስለሕዝባዊ ቁጥጥር ዓላማና ተግ
ባር ጠንቅቆ ካለመረዳትና ብዙውን ጊዜ
ደግሞ ከግዴለሽነትና ከሥልጣን ትምክህ
ተኝነት እንደሆነ በአንዳንድ ተጨባጭ ክስ
ተቶች ለማረጋገጥ ተችሏል ።

ለሕዝባዊ ተቆጣጣሪዎች የተሰጡት መብ
ቶች የተረጋገጡ ናቸው ። ግን መብቶቻቸ
ውን የሚያስጠብቁ ደጋፊዎች ያስፈልጉዋ
ቸዋል ። ያቀረቡዋቸውንም አሳሳቢ ጥቆማ
ዎች የምርት ተቋም አስተዳዳሪዎች በሚገባ
ካልተመለከቱአቸው ምንም ውጤት ሊያስ
ከትሉ ለይችሉም ። የቁጥጥር መረጃዎች
ካልተመረመሩ በተቆጣጣሪዎችና በአስተዳ
ዳሪዎች መካከል የሥራ ግንኙነት ሊመሠ
ረት ለይችልም ። የሚያሳዝነው ነገር ፣ ሕዝ
ባዊ ተቆጣጣሪዎች ሊረዱን የሚችሉ የሥ
ራችን ተባባሪዎች ናቸው የማይሉ ለያሌ አስ
ተዳዳሪዎች መኖራቸው ነው ። ተቆጣጣሪ
ዎቹ የሥራ ጉድለት በማየት ሂስ ሲያቀርቡና
የሚታረምበትን መንገድ ሲጠቀሙ አስተ
ዳዳሪዎቹ ቀር የሚሰኙበት ጊዜ ይኖራል።[15]

በነዚህና በመሳሰሉት ችግሮች የተነሳ
የሕዝባዊ ቁጥጥር አካሎች የሚያስተላል
ፉቸው ገንቢ አስተያየቶችና ጥቆማዎች ዋጋ
ቢስ እንዳይሆኑ የሶቪየት መንግሥት አንድ
ተጨማሪ ሕግ ማውጣት የተገደደበት ጊዜ
ነበር ። በዚህም ምክንያት «ሕዝባዊ ቁጥ
ጥር በሶቪየት ኅብረት» በተባለው ሕግ ላይ
«ባለሥልጣኖች ትክክለኛ ያልሆነ ሥራ
በመሥራት ወይም ለሌሎች ትዕዛዝ ባለመ
ስጠት በመንግሥት ፣ በኅብረት እርሻ ፣ በ
መረዳጃ ማኅበሮች ፣ በማኅበራዊ ተቋሞ
ችና ድርጅቶች ላይ ጉዳት ያደረሱ እንደ
ሆነ ኪሣራውን ለማሟላት ባለሥልጣ

ናቹ ገንዘብ እንዲከፍሉ የሕዝባዊ ቁጥጥር
ኮሚቴዎች ሊያስገድዱ ይችላሉ[14]» የሚለው
ድንጋጌ ወጣ ። ይህ እንግዲህ አሻፈረኝ በ
ሚሉ አንዳንድ የሥራ ኃላፊዎች ላይ የሚ
ወሰድ እርምጃ ሲሆን ለአጠቃላዩ ውጤ
ትና መፍትሔ ግን ሕዝባዊ ቁጥጥር አካላት
የሚያቀርቧቸውን ተጨባጭ ሐሳቦች ተግ
ባራዊ በማድረግና በማስደረግ እንጻር የፓ
ርቲ መዋቅሮች ፣ የሙያ ማኅበራትና የሕ
ዝባዊ ድርጅቶች ድጋፍ ወሳኝነት ያለው
ነው ።

በሕዝባዊ የቁጥጥር አካላት እንቅስቃሴ
ላይ የተደቀነው ሌላው ችግር በአንዳንድ
ግለሰቦች ፣ ቡድኖች ወይም የኅብረተሰብ
ክፍሎች ዘንድ በቂ ግንዛቤ አለመኖርና የተ
ሳትፎ መቀነስ ሁኔታ ነው ። የሕዝባዊ ቁጥ
ጥር መሠረታዊና ዓቢይ ዓላማ ሁሉንም
ዜጎች በፍላጎት በማሳተፍ ዲሞክራሲያዊ
ጠባይ ያለው መሆኑን በመዘንጋት አንዳን
ድ ግለሰቦች የቁጥጥር ዓላማ በኃይልና በማ
ስገደድ ላይ የተመሠረተ አድርገው ይወስ
ዱታል ። ይሁን እንጂ በዚህ ገጽታው በዲ
ሞክራሲ ጠባዩና በማዕከላዊነት መካከል
ሊኖር የሚገባውን ዳያሌክቲካዊ ግንኙነት
በውል ማጤን የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ መ
ሆን ይኖርበታል ። በተጨማሪም ሌኒን
«የሠርቶ አደሩና የገበሬው ቁጥጥር ከፍ
ተኛ ተግባር ጥፋተኛውን መያዝና ማጋ
ለጥ ሳይሆን ጉድለት የሚታረምበትን መን
ገድ መቀየስ ነው[15]» በማለት እንደጠቆመው
የተፈጸመንና ችግር ያስከተለ ስህተትን ከመ
ንስኤው ነጥሎ ለማረም መሞከር ዘላቂ መፍ
ትሔ እንደማያስገኝ የተረጋገጠ ነው ። በመሆ
ኑም ለስህተት መንስኤ የሚሆኑትን ምክንያ
ቶች እየገመገሙ የማያዳግም መፍትሔ መስ
ጠት በሶቪየት ኅብረት የሕዝባዊ ቁጥጥር አካ
ላት ዘንድ ከዕለት ወደ ዕለት እየዳበረ በመ
ሔድ ላይ ነው ። በበጐ ፈቃደኝነት የሚ
ሠሩ ተቆጣጣሪዎችና የንዑስ ቡድን አባ
ላት ሊሠራ ዕንቅፋት የሚሆኑትን ጉድለ
ቶች በማጋለጥና የሚታረሙበትን መንገድ
በመጠቆም የቁጥጥር ሥራቸውን ያካሂዳሉ።

Digitized by Google

የተገኘውን የቁጥጥር ውጤትና ተቆጣጣሪዎች ያቀረቧቸውን ሐሳቦች ለምርት ድርጅቶች መሪዎች በማቅራራት የኅብረቱ ባለቤት የሆነው ሠራተኛ ተሰብስቦ እንዲወያይባቸውና ድክመቶችን ብማረም ጠንካራ አዝማሚያዎችን እንዲያዳብራቸው ይደረጋል ።

ሕዝቡ ስለራሱ ንብረትና ሀብት እንክብካቤና አጠቃቀም ያለው ግንዛቤ ከፍ እንዲልና ምዝበራና ብኩንነት ከሥሩ እንዲመነገል ለማድረግ የሕዝባዊ ቁጥጥር አካሎች የተለያዩ የስብሰባ መድረኮችንና አጋጣሚዎችን ሁሉ ይጠቀማሉ ። በተለይም የተለያዩ የዜና ማሰራጫዎችን እንደዓይነተኛ የማስተማሪያ ፣ የመቀስቀሻና ከሕዝቡ ጋር የመገናኛ መሣሪያዎች አድርገው ይገለገሉባቸዋል ። የሶቭየት ሕዝብ ትክክለኛ ጥቆማውንና አስተያየቱን በነዚሁ የመገናኛ ዘዴዎች ሲያቀርብ በየደረጃው የተዋቀሩት የቁጥጥር አካላትም ስለሕዝባዊ ቁጥጥር ዓላማና በእንቅስቃሴው ስለተገኘው ውጤት ለሕዝቡ በማቅረብ ተሳትፎው በየዕለቱ እየጐለበተ እንዲሔድ ያደርጋሉ ። እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ያከማቸው ልምድ በሀገሪቱ ውስጥ በየደረጃው ላሉት ሕዝባዊ ተቆጣጣሪዎች ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር ተቀናጅቶ እንዲያገለግል ለማድረግ የቴሌቪዥን ልዩ ፕሮግራሞች ፣ የጋዜጣ ዓምዶች ፣ መጽሔቶችና የሬዲዮ ፕሮግራሞች የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ ። የኮሚኒስት ፓርቲው ልሣን የሆነው የፕራቭዳ ጋዜጣ ሳይቀር ለሕዝባዊ ቁጥጥር ሳምንታዊ ዓምድ በመስጠት ፓርቲው ለሕዝባዊ ቁጥጥር የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት አረጋግጧል ።

ሕዝባዊ ቁጥጥር በኢትዮጵያ ።

የሶሻሊዝምን ፈለግ በመከተል ላይ የምትገኘው አብዮታዊት ኢትዮጵያ የኋላቀሩን ፊውዳላዊ አገዛዝ አሽቀንጥራ በጣለች ማግስት ከገጠር መሬት ጀምሮ የተለያዩ ትላልቅ የማምረቻ ፣ የማከፋፈያና አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በማዋል የምርት ግንኙነት ለውጥ አድርጋለች ። ያሏት መንግሥታዊ የቁጥጥር አካላትም አቅም እስከፈቀደ ድረስ በነዚህ ተቋሞች ላይ ተገቢውን አስተዳደርና ቁጥጥር በማድረግ የግንባታው ተግባር ፈር እንዳይስትና እንዳይቀዘቅዝ ሲታገሉ ቆይተዋል ።

ይሁን እንጂ ሥልጣናቸውን ያጡት የአሮጌው ሥርዓት አራማጆች ፣ ተስፋፊዎች ገንጣዮችና በአጠቃላይም የውስጥና የውጭ አድኃሪ ኃይላት አብዮታዊት ኢትዮጵያ የምትከተለው የዕድገት አቅጣጫ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅማቸውን እንደሚያነጥፍባቸው ስለተረዱ በየአቅጣጫው የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በጥሞና ሊመለከቱት አልቻሉም ። መሣሪያ መዘው ሰላም ለማናጋት ፣ ሀገር ለመቁረስና ሥልጣን ለመጨበጥ እንደታገሉ ሁሉ የምርት ተቋሞችን የአገልግሎት መስጫ ፣ የመገናኛ ወዘተ... ተቋሞችን በማፈራረስ ፣ ምዝበራና ብኩንነትን በማስፋፋት ፣ ምርትን በመቀነስና በመሳሰለው ሁሉ የግንባታውን ትግል ለማኮላሸትና አብዮቱን ለፀረ—ሕዝብ ዓላማቸው ለማመቻቸት በከፍተኛ ደረጃ ታግለውናል ! እየታገሉንም ናቸው ። ይህን አሳሳቢ ሁኔታ በሚገባ ያጤኑት አብዮታዊው መሪያችን ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መስከረም 2 ቀን 1973 ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባቀረቡት ጥሪና የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ በዚሁ ላይ ተመስርቶ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ሁሉ ከተሟላ በኋላ ጥቅምት 26 ቀን 1974 የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴና የልዩ ፍ/ ቤት ማቋቋሚያ አዋጆች ወጥተዋል ።

ከዚያም «ብሔራዊ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴን ምርጫ በበላይነት የሚመራ ፣ የሚያስፈጽምና በተግባር ላይ መዋሉን የሚቆጣጠር አንድ ከፍተኛ ማዕከላዊ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ መጋቢት 7 ፣ 1974 ተቋቁሞ ሥራውን እንዲጀምር ተደረገ ። ለብሔራዊውም ሆነ በየደረጃው ለሚመሠረ

Digitized by Google

ቱት የቁጥጥር ኮሚቴዎች አባላት የሚመ
ረጡት በአዋጅ ቁጥር 213 አንቀጽ 8 እን
ደተደነገገው በሕዝባዊ ድርጅቶች መድረ
ክነት በመሆኑ በአገር አቀፍ ደረጃ ከተጻጻ
ሙት የተውጣጡ 200 አባላት ማለትም እያ
ንዳንዱን ድርጅት ካቀፈው የአባላት ብዛ
ትና ስርጭት ፡ ከአብዮታዊ ሚናና ከሌሎች
ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች በመገምገም በተሰ
ጠው ኮታ መሠረት መኢሠማ 50 ፡ መኢገማ
40 ፡ አኢወማ 35 ፡ አኢሴማ 35 ፡ አ-አ-
ከነማ 20 ፡ ልዩ ልዩ የሙያ ማኅበራት ባን
ድነት 20 ተወካዮች እንዲልኩ ተደርጐ መ
ራጭ አካሉ እንዲጻጻም ተደረገ ። አካሉ
በተሰጠው መመሪያ መሠረት በልዩ ልዩ
ንዑሳን ኮሚቴዎች ራሱን ከፋፍሎ ከሰፊው
ሕዝብ የሚቀርቡለትን ጥቆማዎችና አስተ
ያየቶች እየመዘገበና እየመረመረ ፡ እንዲ
ሁም ዕጩዎችን በተሰጠው መመዘኛ እያ
ነጻጸረ «በመጀመሪያ ደረጃ ከተጠቆሙት
187 ዕጩዎች መካከል የመጀመሪያውን
የማጣሪያ ዙር ያለፉትን 75 ዕጩዎች ስም
ዝርዝር ለሕዝብ በማሳወቅ የድምጽ አሰጣ
ጡን ሥነ ሥርዓት መጋቢት 29 ቀን 1974
አጠናቆ መጋቢት 30 ቀን 1974 ለብሔ
ራዊ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ አባ
ልነት የተመረጡትን አባላት ስም ዝርዝር
በይፋ በመግለጥ ተግባሩን አጠናቀቀ» [16]
በተመሳሳይ ሁኔታና እንደአካባቢው ኢኮ
ኖሚያዊ ፡ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ እንቅስ
ቃሴ እየታየ የክ/ሀገር ፡ የአውራጃ ፡ የወረ
ዳና የመሠረታዊ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር
ኮሚቴዎች ምርጫም ተካሒዷል ። እስከ
ነሐሴ 30 ቀን 1976 ባለው ጊዜ ውስጥም
የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ መዋቅር በ7
ክፍላተ ሀገር ፡ በ8 አውራጃዎች ፡ በ2 ወረ
ዳዎችና በ520 መንግሥታዊ ድርጅቶች
ውስጥ ተዘረጋ ።

እነዚህ ከብሔራዊ እስከ መሠረታዊ ደ
ረጃ ድረስ የተጻጻሙት የሠርቶአደሩ የቁ
ጥጥር ኮሚቴዎችም ባለፉት ሁለት ዓመ
ታት ባካሔዱት እንቅስቃሴ ጥቂት ግለሰ
ቦችና ራስ ወዳዶች በተለያዩ ዘዴዎች አጭ
በርብረው ሊያስተፉት የነበረውን በብዙ
ሚሊዮን ብር የሚገመት ንብር ፡ የመንግ
ሥት ንብረትና ገንዘብ አስመልሰዋል። ጉዳ
ዩ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸ
ውን መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች
በማስተባበር የኮንትሮባንድ ንግድ ቀስ በ
ቀስ የሚወገድበትን ዘዴ በመተለም ፡ የተ
ለያዩ የመንግሥት ንብረቶችና የአገልግሎት
ክፍያዎች በተገቢው ጊዜና በትክክል እን
ዲሰበሰቡ በማድረግ የመንግሥት ተሽከር
ካሪ አጠቃቀምና ንብረት አያያዝ ተገቢ
ውን መመሪያ እንዲከተል በማድረግ ፡ የተ
ፈጥሮ ሀብቶቻችን በሚገባ ተጠብቀው በተ
ገቢው መንገድ በአገልግሎት ላይ እንዲ
ውሉ መመሪያ በመስጠትና በመደገፍ ፡ ምር
ታማነት እንዲጨምር አስፈላጊውን ግብ
ረታታት በማድረግ ወዘተ . . . ከፍተኛ ጥ
ረት ያደረጉ ሲሆን ፡ ሰፊው ሠርቶአደር
ስለሕዝባዊ ቁጥጥር ያለው ግንዛቤ ከፍ እን
ዲልና ተሳትፎውን እንዲጨምር በተለያዩ
የዜና ማሰራጫዎች በየጊዜው የሚያስተላ
ልፏቸው መልእክቶችና የምርመራ ውጤ
ቶችም የተጨባጭ ሥራቸው ፍሬያማነት
ማስረጃ ናቸው ።

የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ ችግሮች

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የሠርቶ አደሩ
ቁጥጥር አሠራር ውስጥ የተከሰቱ አያሌ ችግ
ሮች ቢኖሩም በጥቅሉ ሲታዩ ዋና ዋናዎቹ
ሀ/የግንዛቤ ዝቅተኛነትና የአድኃሪዎች ሴራ
ለ/የግንኙነት አለመጣጣም ፡ ሐ/ የኃላፊ
ነት መደራረብ ፡ መ/ የቁጥጥር ኮሚቴ አባ
ላት ዝውውር ናቸው ለማለት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አብዮት ማካሄድ
ከጀመረ ገና 10 ዓመቱ ነው። ከእነዚህ ዓመ
ታት ውስጥም ከፊሎቹ የሕዝቡን አንድነ
ትና ዳር ድንበር በማስከበር እንዲሁም አብ
ዮቱን ከቅልበሳ ለማዳን በተካሔደው መራ
ርና ወሳኝ ትግል የተገባደዱ በመሆናቸው
ለንቃተ ሕሊና መጐልበትና ለድርጅት ጥ
ንካሬ የዋለው ጊዜ እጅግ አነስተኛው እን
ደሆነ ግልጽ ነው ። በተጨማሪም አብዛ
ኛው ገጽታው ፊውዳላዊ የሆነው ኋታችና

Digitized by Google

ኋላቀር ሥርዓት አመለካከቶች ለብዙ ዓመታት ተንሰራፍተው የቆዩ በመሆናቸው በቀላሉና በጥቂት ዓመታት ከነስንኮፋቸው ነቅሎ ለመጣል የማይቻልና አስቸጋሪ መሆኑ አይካድም ። ለንቃት መዳበር የዋለው ጊዜ ማጠርና አሮጌው ሥርዓት የተወው አድኃሪ አመለካከት ጠንካራ መሆን ሰፊው ሕዝብ ለጥቂት ፀረ አብዮተኞች አድኃሪ ቅስቀሳ እንዲጋለጥ አድርገውታል ።

ድል የሰፊው ሕዝብና የአብዮታውያን ኃይሎች ቢሆንም ቀድሞ የጥቂቶች ሀብት ማካበቻ የነበሩትና ዛሬ የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት በመሆናቸው ኪሳራ የሚያሳዩት የተለያዩ የማምረቻ ፣ የማከፋፈያና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሁኔታና የመሳሰለው ሁሉ በሰፊው ሕዝብ ንቃተ ሕሊና ዝቅተኛነትና በአንጻሩም በፀረ—አብዮት ኃይላት ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ተጽዕኖ የመጣ ለመሆኑ አሉ የማይባል ነው ።

አብዮታዊው መሪያችን ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሕዝባዊ ቁጥጥር አስፈላጊነት ገና ማስገንዘብ እንደጀመሩ በቁጥጥሩ ሂደት ዕርቃናቸውን እንደሚቀሩና የብዝበዛ ጥቅማቸውን እንደሚያጡ የተረዱት እነዚሁ አድኃሪ ኃይላት ቁጥጥሩ ፍሬን ከገለባ የማይለይ እንደደራሽ የክረምት ውሃ ሁሉንም ጠራርጎ የሚወስድ አድርገው በማቅረብ የቁጥጥሩ ባለቤት የሆነውና የጋራ ሀብቱ የተመዘበረበት ሰፊው ሕዝብ ከጐናቸው እንዲሰለፍ ለማድረግ ብዙ ጥረዋል ። ይህም አልሳካ ሲላቸውና የቁጥጥሩ ሕልውና የማይቀር መሆኑን ሲረዱት ደግሞ መስሎቻቸውን በመዋቅሩ ውስጥ ለማስረግና የቁጥጥሩን ዓላማ ፈር ለማሳት ሞክረዋል ። ሆኖም ፍላጐታቸው ስላልተሳካላቸው የትግል አቅጣጫቸውን መቀየር ግዴታ ሆኖባቸዋል ።

ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ኃይላት ቀጥሎ የተጠቀሙበት ዘዴ ንቃተ ሕሊናቸው ዝቅተኛ የሆነውን የኅብረተሰቡን ክፍሎች በመገፋፋት ተራ ወይም ግላዊ ጥቅምን ብቻ የሚመለከቱ እንዳንዶም ሐሰተኛ የሆኑ ጥቆማዎችን ለኮሚቴዎቹ እንዲያቀርቡና ኮሚቴዎቹም በነዚህ ርካሽ ጥቆማዎች ተተብትበው ሥራቸው እንዲጐተት ፣ ዓላማቸውን እንዲስቱና በየአጋጣሚውም አድኃሪያኑ ጊዜያዊ ፋታን እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ነበር ። ለምሳሌ ከብሔራዊ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በ1976 በተለያየ ደረጃ ለተቋቋሙት የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴዎች በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ከቀረቡት 2577 ጥቆማዎች መካከል 616 ጥቆማዎችን የኮሚቴውን ዓላማ የማይመለከቱና አንዳንዶቹም በተጨባጭ ማስረጃዎች ላይ ያልተመሠረቱ በመሆናቸው ሊዘጉ ችለዋል ። በዚህ መሠረት እነዚህን ጥቆማዎች ለመመዝገብና ምንነታቸውን ለማጣራት የሚፈጀው ጊዜ ፣ ማቴሪያልና የሰው ኃይል ምን ያህል እንደሆነ መገመቱ አያስቸግርም ።

በሰፊው ሠርቶአደር የንቃተሕሊና ደረጃ ዝቅተኛነት ላይ የተመሠረተው ሌላው ችግር ደግሞ አንዳንድ ዜጐች በሰፊው ሕዝብ ንብረትና ገንዘብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ስህተቶችን በሊጋንታቸው ከመጠቆም ይልቅ ጥፋቱ ከደረሰ ወይም ከተፈጸመ በኋላ መጠቆማቸውና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አይቶ እንዳላየ በመሆንና በግዴለሽነት ምንም ይሁን ምን ጥቆማ ለማቅረብ ፈቃደኝነት ያለማሳየታቸው ሁኔታ ነው።እዚህ ላይ ሰፊው ሕዝብ ሊያጤን የሚገባው ዓቢይ ነገር ፣ የመንግሥት ሀብት ማለት የራሱ የሰፊው ሕዝብ ሀብት ማለት መሆኑንና የሚደርሰው ጥፋትና ኪሳራ በእሱና በቤተሰቦቹ ዕድገትና ብልጽግና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያስከትል መቻሉን ነው ። አይቶ ዝም ማለቱ (ጥቆማ አለማድረጉ) ለተደጋጋሚ ጥፋቶች መከሰት በር ይከፍታል ። ከደረሰ በኋላ መጠቆሙ ደግሞ ወደፊት ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይደገም ርምጃ ለመውሰድ ያግዛል ። ከሁሉም ይልቅ ጥፋት ከመድረሱ ወይም ከመፈ

Digitized by Google

ከ«ሠርቶአደር» ቁጥር 202 ግንቦት 2 ቀን 1976 የተወሰደ ።

Digitized by Google

ጸሙ በሬት መጠቆሙ ግን የአሁኑንና የወደፊቱንም ችግር ለማስወገድ ይረዳል። ይህ በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባዋል። በአጠቃላይም በጥቅምቱ አብዮት መባቻ ላይ ሌኒን ፦—

ጓዶች ሠርተ አደሮች ፣ የሀገሪቱ መሪዎች እናንተ መሆናችሁን አስታውሱ ። በተመረቱ ዕቃዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ምዝገባ መደረጉን አረጋግጡ ። በምርት ላይ ሻጥር የሚፈጽሙ ማለትም የሚያበላሹ ፣ የሚያዘገዩ ፣ እህል የሚደብቁ ፣ ጭነት የሚያዘገዩ ፣ የአውራ ጐዳናን ፣ የፖስታን ፣ የቴሌግራፍንና የቴሌፎንን አገልግሎት የሚያደናቅፉ በአጠቃላይ ሰላምን በማደፍረስ ደህው ገበሬ መሬቱን እንዳይረከብ ወዝ አደሩም በምርትና በሥርጭቱ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዳያደርግ የሚያውኩትን ሁሉ ማጅራታቸውን እየያዛችሁ ለአብዮቱ ፍርድ አቅርቡ ፤ በተጠንቀቀ ቆማችሁ መሬታችሁን እህላችሁን ፣ ፋብሪካዎቻችሁን ፣ መሣሪያዎቻችን ፣ ምርትንና ውጤቱን ፣ የትራንስፖርት መገልገያዎችን እንደ ዐይናችሁ ብሌን ጠብቁ ። ካሁን ጀምሮ እነዚህ ሁሉ የእያንዳንዳችሁ ብሎም የሕዝብ ንብረት መሆናቸውን ለተዘንጉ ። [17]

በማለት ለሰፊው የሩስያ ሕዝብ እንዳስገነዘበው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም ስለኃብቱና ንብረት በቂ ግንዛቤ ኖሮት ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያደርግ የመቀስቀሱና የማስተማሩ ተግባር ወሳኝ ነው ። ይህ ደግሞ ከአንጋፋ ሶሻሊስት ሀገሮች ልምድ አንጻር እንደሚታየው በሥርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ብቻ ሳይሆን በአብዮታዊ ምሁራን ፣ በደራስያን ፣ በኪነት ባለሙያዎች ፣ በዜና ማሠራጫ ባለሙያዎች ወዘተ - - - ትብብር ጭምር መከናወን ያለበት ነው ።

ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓ መሥራች ጉባኤ ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ላይ

ስለሕዝባዊ ድርጅቶች ሚና እያደገ መሔዱ አስፈላጊነት ካነሳን ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነጥብ አለ ። ይኸውም በሕዝባዊ ድርጅቶችና በመንግሥታዊ አካላት መካከል መኖር ያለበት የግንኙነት ሁኔታ ነው ። ስለዚህ ጉዳይ በተደጋጋሚ የተወሳ ቢሆንም አሁንም የግንዛቤ ጉድለት መኖሩ ከተግባር ይታያል ። ሕዝባዊ ድርጅቶች በመንግሥታዊ ተግባራት ውስጥ የመሳተፋቸው ጉዳይ ሊታለፍ እንደሚችል ለማራጭ የሚያዩ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች አሁንም ጥቂት አይደሉም ። እንደእውነቱ ከሆነ የሕዝባዊ ድርጅቶች ተሳትፎ ለስትራተጂያዊ የዕድገት ጉዞአችን ዋስትና የሚያስገኝ ከመሆኑም ሌላ በአጭር ጊዜ የተሻለ ውጤት ከማስገኘት አኳያም ያለው ጠቀሜታ በጥሞና ላስተዋለው ግልጽ ነው ። የተዋሐደ አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት የምንሻ እስከሆነ ድረስ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በመንግሥታዊ አካላት መካከል ያለው ግንኙነት በይበልጥ መሻሻል ይኖርበታል ። ይህን ቻል ብሎ ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንገነባለን ማለት የማይሆን ነው ።

በማለት እንደገለጡት የአብዮቱ ለጋ ፍሬ በሆነው በሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴና በአንዳንድ መንግሥታዊ ተቋሞች መካከል ያለው የሥራ ግንኙነት የሚጠበቀውን ያህል የተጣጣመና አመርቂ አይደለም ። በእርግጥ በሠርቶአደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ ማቋቋሚያ አዋጅ ውስጥ የሠርቶአደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት ለማስከበር በሚያካሂደው ማንኛውም እንቅስቃሴ ግለሰቦች ፣ የግል ድርጅቶች ፣ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሁሉ ተገቢውን ትብብር እንዲያደርጉ ተደንግጓል ።

ይሁን እንጂ በራሳቸው የማይተማመኑ ጥቂት የሥራ ኃላፊዎች ዓላማውን በመጻረር ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የአዲሱን ሥርዓት አዲስ የአሠራር ስልት በውል ካለመገንዘብ የተነሳ ኃላፊነታቸውን የተቀሙ ወይ

Digitized by Google

ም በኃላፊነት የሚሠሩበት መ/ቤት ተግባር
በኮሚቴው የተነጠቀ (የተተካ) እየመሰላ
ቸው ፣ በመቀናቀን አልፎ አልፎም በምን
ቸገረኝነት ከሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ
ዎችና የኮሚቴ አባላት ጋር መኖር የሚገባ
ውን ጥብቅ ግንኙነቶች ሲያላሉትና ለሥ
ራው ዕንቅፋት ሲፈጥሩ መታየታቸው አል
ቀረም ። በአጭር ጊዜ መጠናቀቅ የሚገ
ባው ምርመራ በየምክንያቱ ይጓተታል ።
ጠቃሚ የሆኑ ማስረጃዎችን በወቅቱና በት
ክክል መላክ ሲገባቸው ይደብቃሉ ፤ አንዳ
ንዶም እምቢተኛ ይሆናሉ ። የመንግሥ
ትና የሕዝብ ንብረት ዘራፊዎችን ያሸሻሉ
ወይም ሽፋን ይሰጣሉ ። በአጥፊው ላይ የአ
ስተዳደር እርምጃ እንዲወስዱ ሲጠየቁ አሻ
ፈረኝ ይላሉ ። በአጠቃላይ የኮሚቴዎቹን
ዕሊታዊ እንቅስቃሴ ራሳቸው እያጓተቱ ለ
ሚደርሰው ድክመት ተጠያቂዎቹ ኮሚቴ
ዎቹ እንዲሆኑ ይጥራሉ ።

ሆኖም እነዚህ ክፍሎችና ግለሰቦች በሚ
ገባ ሊያጤኑት የሚገባው ዓቢይ ነገር ዛሬ
በደረስንበት የዕድገት ደረጃና ከምንከተ
ለው ርዕዮተ ዓለም አንጻር የእያንዳንዱ
መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅት እንቅስ
ቃሴ በአብዮቱ ዓላማና ግብ ላይ እንጂ በግ
ለሰቦች ፍላጐትና የተበታተነ ዕቅድ ላይ
የተመሠረተ እንዳልሆነ ነው ። ለአንድ ትክ
ክለኛ ዓላማ. የተቋቋሙትና የተጠናከሩት
ድርጅቶች ሁሉ ጉዞአቸው በአንድ አቅጣ
ጫ መሆን ሲገባው አንዱ የሌላውን ሥራ
የሚያደናቅፍና የሚያጓትት ከሆነ ለሰፊው
ሕዝብ የጋራ ዕድገትና ብልጽግና ቆሚአ
ለሁ ብሎ መናገሩ አስመሳይነት ነው ።

ስለዚህ በተለያዩ ሕዝባዊና መንግሥ
ታዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ የኢሠፓ
አካላት፣የሙያ ማኅበራት ፣ የቁጥጥር ኮሚ
ቴዎችና ወዘተ ... የየአካባቢአቸው እንቅ
ስቃሴና አስተዳደር ትክክለኛው ፈር መከ
ተሉን ከሌሎች ተቋሞች ጋር በሚኖረው ግን
ኙነት ተገቢውን አቅጣጫ መያዙንና የሚ
ጠበቀው ያህል መሆኑን በየጊዜው የመገምገ
ምና የማስተግበር ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮጵያ ዛሬ ያሏት ባለሙያዎች ቁጥር
እጅግ አነስተኛ በመሆኑ በሀገሪቱ በስፋ
ትና በየአቅጣጫው በሚካሔደው የአዲስ
ሥርዓት ግንባታ ትግል ውስጥ የባለሙያ
ዎች እጥረት እንደሚታይ የማይካድ ሐቅ
ነው ። ለምሳሌ ፡–

በ1971 የዘመቻ ወቅት በልዩ ልዩ ክፍላተ
ክፍላተ ኢኮኖሚ የተጠየቀውን የሰው ኃይል
ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም በሰለ
ጠነ የሰው ኃይል ረገድ የተፈለገውን ያህል
ለማሟላት አልተቻለም ። በየመሥሪያ ቤቱ
የሚገኘው የሰለጠነ የባለሙያ ቁጥር በጣም
አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ከዚያ አዲስ ባለ
ሙያ ለማግኘት አልተቻለም ። በእርሻ ፣
በኢንዱስትሪ ፣ በንግድና ፣ እንዲሁም በሌ
ሎች ክፍላተ ኢኮኖሚ ውስጥ የባለሙያዎች
እጥረት ከፍተኛ በመሆኑ በሀገሪቱ ውስጥ የሚ
ገኙት የማሰልጠኛ ተቋሞች በየጊዜው የሚ
ያስመርቋቸው ባለሙያዎች ፍላጐታቸውን
ሊያሟሉ አልቻሉም ከዚህም ሌላ ባለሙያ
ዎች ያለሙያቸው መሠማራት የተፈጠረውን
እጥረት አባብሶታል ።[18]

በሌላ በኩል ደግሞ ሀገሪቱ ካፈራቻቸው
ከእነዚሀ እጅግ አነስተኛ ባለሙያዎች መካ
ከል ስንቶቹ ለሰፊው ሕዝብ የጋራ ዕድገ
ትና ብልጽግና በአጠቃላይም ለአብዮቱ
ዓላማ መሳካት ቆመዋል፤ የሚለውን ጥያቄ
ማጤኑ ተገቢ ይሆናል ። የየትኛውም አብ
ዮት ሂደት እንደሚመሰክረው የመደብ ት
ግል እስካለ ድረስ ምሁሩም እንደተረው
የኅብረተሰቡ ክፍል ተሰልፎ ይበጀኛል
ለሚለው መደብ መታገሉ የማይቀር ነው።
በኢትዮጵያም የተከሰተው ይኸው ሐቅ
ነው ። ይህም በሃገሪቱ ያሉትን አነስተኛ
ባለሙያዎች ቁጥር በመጠኑም ቢሆን እን
ደቀነሰው ይታመናል ።

በነዚሁና በመሳሰሉት ምክንያቶች
ብዙ ሥራ በጥቂት አብዮታውያን ላይ
መጫኑ የማይቀር ነው ። ለምሳሌ አንድ

Digitized by Google

«ቁጥጥር» ከተባለው መጽሔት መስከረም 2 ቀን 1977 ልዩ እትም የተወሰደ ።

Digitized by Google

ጓድ ከመደበኛው ሥራ ባሻገር በከነማ ፣ በቁጥጥር ኮሚቴ ፣ በኢሠማጉና በተለያዩ ኮሚቴዎችና ገብረ ኃይሎች ውስጥ የአመራር አባል ሆኖ ሲያገለግል የሚታይበት ሁኔታ አለ ። ታዲያ የአንዳንዶቹ ሕዝባዊ ድርጅቶች የአገልግሎት መስጫ ጊዜ ተመሳሳይ በመሆኑ በጊዜ እጥረትና በሥራ መደራረብ የአንድ ወይም የሁለቱ አካሎች ሥራ ይበደላል፤ እንቅስቃሴአቸውም ይጓተታል። ከሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት መካከል አንዳንዶቹ ጓዶችም ተመሳሳይ የሆነ ተደራራቢ ኃላፊነት ስላለባቸው ሁኔታው በኮሚቴዎቹ እንቅስቃሴ ላይ የማይናቅ ተጽዕኖ እንዳስከተለ ለመገንዘብ ተችሏል ።

የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ አንዱና ልዩ ጠባዩ ሥራው በአብዛኛው በኮሚቴ የሚከናወን መሆኑ ነው ። በተለይም ከብሄራዊ እስከ ወረዳ የተቋቋሙት ኮሚቴዎች እያንዳንዳቸው አሥራ አንድ አባላት ያሉአቸው ሲሆን ፣ ከነዚህ መካከል ሶስቱ በኮሚቴው ውስጥ በቋሚነት የሚያገለግሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ፣ የቀሩት ስምንቱ ደግሞ በተወሰነና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ኮሚቴውን በሚመለከቱ አበይት ጉዳዮች ላይ ለመወያየትና ውሳኔ ለመስጠት የሚሰበሰቡ የኮሚቴው አባላት ናቸው ። ከእነዚህ ማለትም ከስምንቱ አባላት መካከል ከላይ እንደተጠቀሰው አንዳንዶቹ በመደበኛ ሥራቸውና በሌሎች ግል ጋሎቶች ላይ የተሰማሩ እንደመሆናቸው ብዙውን ጊዜ በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ለመገኘት ይሳናቸዋል ። በዚህም የተነሳ አልፎ አልፎ የጉዳዮችና የውሳኔዎች መጓተት መታየቱ አልቀረም ።

አንዳንድ ኮሚቴዎች ይህን ችግር ያስወገዱ እየመሰላቸው በኮሚቴው ውስጥ በቋሚነት ለሚሠሩት ሶስቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የተወሰነ የውሳኔ ሥልጣን ሲሰጧቸው ይታያሉ። ሆኖም ይህ ዘዴ በአንድ በኩል ለሥራ መቀላጠፍ አመቺ ሆኖ ቢታይም በሌላ ጉኑ የአፍራሽነት አዝማሚያ እንደሚኖረው መገመቱ አያዳግትም።

በመጀመሪያ ደረጃ የዚህ ዓይነት አሠራር የኮሚቴውን ሕዝባዊነት ደረጃ ዝቅ የሚያደርግና ዲሞክራሲያዊነቱንም የሚያጠብ ነው ።

በተጨማሪም ለፀረ ሕዝብ ሴራ መክፈቻ በር የሚከፍት ነው።ለምሳሌ ከሕዝብ የሚቀርቡ ጥቆማዎች በሶስቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ብቻ እየታዩ አስፈላጊው ማጣራት የሚደረግባቸው ወይም የማይደረግባቸው ከሆነ ፣ በሌላ አነጋገር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ስለሆነ ከሶስቱ አባላት መካከል ሁለቱ ተስማምተው ማንኛውንም ዓይነት ውሳኔ ቢያሳልፉ በሀገሪቱ ብሎም በሕዝቡ ሀብትና ገንዘብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከመድረሱም ባሻገር ጉዳዩ በመዝገብ ላይ የማይሰፍር በመሆኑና ከራሱ ከጠቋሚው ግለሰብ ወይም ድርጅት በቀር ጉዳዩን የሚገመግም አካል ወይም የኮሚቴ አባል ባለመኖሩ አሻጥር ሊሠራ ከታሰበ ከአሥራ አንዱ አባላት መካከል በሁለቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ድምጽ ብቻ የፀረ—ሕዝብ ኃይላት ደባ ግብ ሊመታ ይችላል ማለት ነው ። ስለዚህ ይህንና የመሳሰለውን በኮሚቴው እንቅስቃሴና ትክክለኛ አሠራር ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ችግሮች ለማስወገድ ፣ የኮሚቴው አባላት በሙሉ ፣ በሚፈለገበት ጊዜና ቦታ ሁሉ ፣ የመገኘት ግዴታ ሊኖርባቸው ይገባል ።

ለዚህ ደግሞ በአጭር ጊዜ መፍትሄ አንጻር ከሁሉም በፊት የሚቻል ከሆነና የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ከፈቀደ ለአንድ ዜጋ የሚሰጠው ኃላፊነት ተደራራቢ እንዳይሆን ተገቢውን ድልድል ማድረግ አስፈላጊ ነው ። በረዥም ጊዜ መፍትሄ አንጻር ለአብዮቱ የቆሙ ባለሙያዎችን ለሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ ሥራ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሥራ መስኮች ደረጃ በደረጃ በማፍራት ረገድ የሚወሰድ ብሄራዊ እርምጃ ወሳኝነት ይኖረዋል ።

ኢሠፓ እና አብዮታዊው መንግሥት በሚካሄደው የአዲሱ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ

ዎችን ወሳኝ ሚና በሚገባ በመገንዘብ የኮሚቴዎቹ መዋቅር የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን በመላ ሀገሪቱ ውስጥ እንዲዘረጋ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው ። አብዮታዊው መሪያችን ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሠርቶ አደሩን ቁጥጥር በሚመለከት ፤

የሠርቶአደሩ ቁጥጥር ሥርዓት አንድከፍተኛ ሥፍራ የሚይዝ ቁም ነገር ነው ። የዚህ መዋቅር በመላው ኅብረተሰብ ውስጥ መዘርጋትና ተገባራዊ መሆን ለአብዮቱ አላታዎች ከግብ መድረስ ዋስትና በማስገኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ።

የሠርቶአደሩ ቁጥጥር አውታር ሠርቶአደሩ ሕዝብ የራሱንና የመንግሥትን ሀብትና ንብረት ለመጠበቅና ለመንከባከብ ፣ እንዲሁም የሥራና የኑሮ ዲስፕሊን በተሟላ መልክ እንዲከበር ለማድረግ የሚያግዝና በአጠቃላይ ሠርቶአደሩ ሕዝብ የፖለቲካ ልዕልናውን የሚያረጋግጥበት አንዱ መሣሪያ በመሆኑ በአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ተገቢ ትኩረት የሚሻ ነው ።

ስለዚህ አስፈላጊው አካባቢዎችን ሁሉ በመዳሰስና የተቀላጠፈ እንቅስቃሴ በማድረግ የተሻለ ውጤት እንዲያሳዩ ኢሠፓ አስፈላጊውን አመራር ድጋፍና ትብብር እንዲያገኙ ያደርጋል ። ...[19]

በማለት የገለጡት ኢሠፓ ለዚህ መዋቅር በመላ ሀገሪቱ ውስጥ መዘርጋት የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት የሚያረጋግጥልን መሪ ቃል ነው ።

ይሁን እንጂ በአንድ በኩል ኢሠፓና አብዮታዊው መንግሥት ይህን ጥረት ሲያደርጉ በሌላ በኩል ደግሞ በአንዳንድ ቁልፍ በሆኑና የማያሰለስ ቁጥጥር በሚያሻቸው ተቋሞች ውስጥ በሥራ ፣ በዕድገትና በመሳሰለው እየተመካኘ በርከት ያሉ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ከቦታቸው ስለሚዛወሩ የቁጥጥሩ መዋቅር ከላይ ሲገነባ ከታች እንዳይዳከም በጥብቅ የሚታሰብበት ነውና ለምሳሌ በመስከረም 20፥ 1977 ከብሔራዊ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ የተገኘው አንድ መረጃ እንደሚጠቁመን

በየደረጃው ከተቋቋሙት የሠርቶአደሩ ቁጥጥር ኮሚቴዎች አባላት በተለይም ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱት ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል ሰማንያ አንድ በልዩ ምክንያት ከቁጥጥሩ ተግባራቸው ላይ በመፈናቀላቸው የ64 ቁጥጥር ኮሚቴዎች ሥራ ሙሉ በሙሉና በከፊል የተቋረጠ መሆኑ ተረጋግጧል ።

እዚህ ላይ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በቁጥጥሩ ተግባር ላይ ተሰማርተው የበለጠ አገልግሎት በመስጠታቸው ወይም የኮሚቴ አባል በመሆናቸው ብቻ ተገቢ ጥቅምና ዕድገት ሊሰጣቸው አይገባም ለማለት አይደለም ። ይሁን እንጂ በአካባቢው የሚካሔደውን ጠንካራ የቁጥጥር ተግባር ለማደናቀፍ ሲባል የሚሰጠው ዕድገትና ዝውውር መገታት ይኖርበታል ። ተገቢ ዕድገትን መስጠት ወይም ለበለጠ ወሳኝና አስቸኳይ ተግባር ማንንም የሀገሪቱን ዜጋ ማዛወር ይቻላል ። ሆኖም በሌላ በኩል የቁጥጥሩ ተግባር እንዳይደናቀፍ በቅድሚያ ከሚመለከተው የበላይ አካል ጋር በጉዳዩ ላይ መወያየቱና ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ ችግሩን ለማስወገድ ዓይነተኛ ዘዴ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል መገንዘብ ያሻል ።

ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲገመገም በሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ እንቅስቃሴ ላይ የተከሰቱና ከላይ የሠፈሩት አንዳንድ ችግሮች በአንድ አብዮቱ አጠቃላይ ችግር ውስጥ የሚቃዩ ናቸው ። ሆኖም እነኝህ ችግሮች ኢሠፓ በየትግል ዘርፉ የተደቀኑትን ዕንቅፋቶች ሁሉ ደረጃ በደረጃ በማስወገድና ትክክለኛ አመራር በመስጠት የሚጫወተው ወሳኝ ሚና ፣ በአብዮታውያን ያልተቆጠበ ተሳትፎና መስዋዕትነት በአጠቃላይ በአብዮቱ ዕድገትና ጥንካሬ ሊፈቱ የሚችሉ መሆናቸው አያጠራጥርም ።

Digitized by Google



ከ«ሠርቶአደር» ቁጥር 217 ነሐሴ 1976 የተወሰደ ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. Victor Turovtsev, People's Control in Socialist Society (Moscow: Progress Publishers, 1973), p. 7.
2. *Ibid*, p. 14.
3. G.S. Sarkisyants, Soviet Economy Results and Prospect (Moscow: Progress Publishers, 1971). p. 220.
4. Soviet Monthly Digest, Socialism, Theory and Practice, No. 12, (Moscow: Novosti Press Agency, 1978), p. 68.
5. *Ibid*, p. 69.
6. ዩሪ ዛክሬቭስኪ ፣ ሕዝባዊ ቁጥጥር በሶሺየት ኅብረት ፣ (ሞስኮ ፣ የኖቮስቲ አገልግሎት ማተሚያ ቤት 1983) ገጽ 12
7. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 18
8. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 24
9. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 26, pp. 411-412.
10. V.I. Lenin, On Socialist Economic Organisation (Moscow: Progress Publishers 1971), p. 16.
11. V.I. Lenin, The State and Revolution (Peking: Foreign Languages Press, 1973), pp. 120-21.
12, ዩሪ ዛክሬቭስኪይ ገጽ 9
13. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 65—66
14. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 41
15. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 12
16. ብሔራዊ የሠርቶአደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ ፣ ቁጥጥር ልዩ ዕትም ፣ አዲስ አበባ (መስከረም 2 ቀን 1977) ገጽ 12
17. የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር አስተባባሪዎ አደራጅ ኮሚቴ ፣ የሌሎች ሶሻሊስት አገሮች የሂሳብ አያያዝና የቁጥጥር ሥርዓት ፣ ኅዳር 1973 ፣ ገጽ 15 (ያልታተመ)
18. የ2ኛ ዓመት 1972 ዕቅድ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕዘላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ አዲስ አበባ፣ 1972 ፣ ገጽ 328
19. የኢሠፓ መሥራች ጉባኤ ማዕከላዊ ሪፖርት ፣ ሠርቶ አደር ቅጽ 5 ቁጥር 220, ጳጉሜ 1 ቀን 1976 ገጽ 7

Digitized by Google

የየብስ ትራንስፖርትን ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ የተደረገ ጥረት*

*በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሕዝብ ግንኙነትና በመስከረም መጽሔት ዝግጅት ክፍል ትብብር የተዘጋጀ ።

«ትራንስፖርት የአንድ ኅብረተሰብ ኢኮኖሚ የደም ስር ነው።» የሚለው አባባል የዚህን ክፍለ ኢኮኖሚ አቢይ ሚና በትክክል ይገልጸዋል ። በተለይም ዛሬ ዓለማችን በደረሰችበት የእድገት ደረጃ በአገሮችና በልዩ ልዩ ሥፍራዎች መካከል ከፍተኛ የሰዎችና የቁሳቁሶች እንቅስቃሴ ይደረጋል ። የዓለምንም ሆነ የአንድን አገር ኢኮኖሚ የሚያስተሳስረውንና የሚያቀራኘውን ፤ ሰዎችንና ሸቀጦችን ከሥፍራ ሥፍራ የሚያጓጉዘውና የሚያመላልሰው በየብስ ፤ (መንገድና ሀዲድ) በባህርና በአየር ላይ የተዘረጋው የትራንስፖርት ሥርዓት ነው ። ትራንስፖርት ከሰው ልጅ እድገትና ሥልጣኔ ጋር የተያያዘ ፤ አብሮ እየዳበረና እየተስፋፋ የመጣ እንደመሆኑ ዛሬ በካፒታሊስቱም ሆነ በሶሻሊስቱ ዓለም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ። የኋላቀር ወይም የታዳጊ አገሮች ጉልህ የኢኮኖሚ ችግሮች ከሆኑት አንዱ የትራንስፖርት አለመስፋፋት ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር እንደማናቸውም የኢኮኖሚ ዘርፍ ትራንስፖርትም በግል የተያዘና ለግል ብልጽግና የሚውል ሲሆን ፤ የግንባታ ዓላማውም ከግል ጥቅም ጋር የተያያዘ ነው ። በአንፃሩ በሶሻሊስት ሥርዓተ ትራንስፖርት ለወል ጥቅም የሚውልና ለኅብረተሰቡ የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥ ነው ።

ከዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ተነስተው ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር ትግል የሚያካሂዱ አገሮች በማናቸውም የኢኮኖሚ ዘርፍ እንደሚያጋጥማቸው ሁሉ በትራንስፖርትም በኩል ማለትም በመንገዶችና በአውሮፕላን ማረፊያዎች አለመስፋፋት ፤ በሀዲዶች በስፋት አለመዘርጋት ፤ በወደቦች ተሟልቶ አለመደራጀትና ፤ ይበልጡኑ በማጓጓዣዎቹ (መጓሪያዎች)እጥረትና ተሟልቶ አለመገኘት ፤ ወዘተ ... ውስብስብ ች

Digitized by Google

ገሮ ይገጥማቸዋል ። በተጨማሪም የአድኃሪዎች ደባ ፣ ጥገኛነት ፣ የድርጅትና የአመራር ልምድ ማነስና የመሳሰሉት በሽግግር ወቅት በትራንስፖርት መስክ የሚከሰቱ ሌሎች ችግሮች ናቸው ። የዚህን ክፍለ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሚና በመገንዘብ አድኃሪያን ሰፊውን ሕዝብ ለማሸበርና አብዮትን ለመቀልበስ በመሣሪያነት እንደሚገለገሉበት በቺሊ እ.ኤ.አ.በ1973 በተጨባጭ ታይቷል። በአገራችንም የውስጥ ቦርቧሪዎች ፣ የውጭ ወራሪዎች፣ ፀረ-አብዮተኞችና ፀረ-አንድነት ኃይሎች ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ በልዩ ልዩ ጊዜና በተደጋጋሚ የትራንስፖርት መስመሮችን በመቁረጥና በመዝጋት ግባቸውንም ለማስናከል ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ይህም የአጭር ጊዜ ታሪክ ያለውንና ያልተስፋፋውን የአገራችንን የትራንስፖርት እንቅስቃሴ እንዲደክምና ችግሩም ከባድ እንዲሆን አድርጎታል ።

የዘመናዊ ትራንስፖርት አመጣጥና እድገት

በዘመናዊ ትራንስፖርት ግንባታ ቀደምትነት ያለው ከጂቡቲ አዲስ አበባ ድረስ የተዘረጋው የምድር ባቡር ነው።የምድር ባቡር በሀገራችን እንዲዘረጋ የመጀመሪያው ሀሳብ የተወሰነው እ-ኤ-አ- መጋቢት 4 ቀን 1884 ነበር ። የምድር ባቡር መዘርጋት እቅድ ሲወጣ በሦስት አቅጣጫ ማለትም ከጅቡቲ ሐረር ፣ ከሐረር እንጦጦ፣ ከእንጦጦ ከፋ ክ/ሀገርን አቋርጦ እስከ ነጭ ዓባይ እንዲሰራ ነበር ።

ተሽከርካሪ መኪና ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በ1889 ነበር ። እያደርም የመንገድ ትራንስፖርት እድገት ከመንገድ ሥራ ጋር እየተስፋፋና እያደገ መጣ ።

የአየር ትራንስፖርትን በሚመለከት የመጀመሪያው አይሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ የገባው እ.ኤ.አ. በ1921 ሲሆን በፋሺስት ጣሊያን ወረራ ምክንያት ከ1928 እስከ 1932 ሊቋረጥ ችሎአል። በአገራችን በ1937 የሲቪል አቪየሽን አስተዳደር እንደተቋቋመ ፣ ኢትዮጵያም ከዚሁ ጊዜ አንስታ የዓለምአቀፍ የሲቪል አቪየሽን ድርጅት አባል ሆነች ። የሲቪል አቪየሽን አስተዳደር በ1945 እና በ1963 የበለጠ ተጠናክሮ እንዲሠራ ተደረገ ።

የአየር ትራንስፖርት ባለሥልጣን በ1969 በአዋጅ ቁጥር 111/1969 ተጠናክሮ ሲቋቋም አበይት ተግባራቱ ፣ ዓለምአቀፍ የአየር ትራንስፖርት ሕጎችንና ደንቦችን፣በትራንስፖርት ጉዳይ ኢትዮጵያ ያደረገቻቸውን ስምምነቶችና ዓለምአቀፍ ውሎችን ማስከበር ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳዎችን ከነሙሉ ድርጅታቸው ማቋቋም ፣ ማስተዳደርና የአየር ማመላለሻ አገልግሎት ከፍተኛ ጥንቃቄና ደህንነት እንዲኖረው ማረጋገጥ መሆናቸው ተገልጿል ።

በዚሁ አኳያ የባህር ትራንስፖርት አገልግሎት በ1970 በአዋጅ ቁጥር 139/1970 «የባህር ትራንስፖርት ባለሥልጣን»ተብሎ እስከተቋቋመ ጊዜ ድረስ «የባህር ክፍል» ተብሎ በ1945 በኤርትራ ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪ (በዚያን ጊዜ ገዥ) የበላይነት ሥር ቢውልም ፣ በሚቀጥለው ዓመት እንደገና በባህር አዋጅ መሠረት በመከላከያ ሚኒስቴር ሥራ እንዲውል ተደርጎ ነበር ። ሆኖም በድርጅቱ የሥራ ጠባይና የአገልግሎት ዓይነት ምክንያት ድርጅቱ በ1958 በመገናኛ ሚኒስቴር ቁጥጥር ሥር ሆኖ « የባህር ማመላለሻ አስተዳደር » የሚል ስም ተሰጥቶት አገልግሎቱን ቀጠለ።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያን የትራንስፖርት ዘርፍ ታሪካዊ አጀማመር ለመንደርደሪያ ያህል ጠቀስነው እንጂ የዚህ ጽሑፍ ትኩረት በሀገራችን የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ድርሻ ባለው በየብስ (ማለትም የምድር ባቡርና የመንገድ) ትራንስፖርት ላይ ነው።ጽሑፉ ባለፉት የአብዮት ዓመታት፣ በአንድ በኩል የአብዮት ቦርቧሪዎችና ወራሪዎች ይህን የትራንስፖርት ዘርፍ ምን ጉዳት እንዳደረሱበት፣ በሌላ በኩል የአብዮቱ ኃይላት ዘርፉን መልሶ ለመጠገን፣ለማጠናከርና ለማስፋፋት ያደረጉትን ጥረት በአጭሩም

Digitized by Google

ቢሆን ለመዳሰስ ይሞከራል ። አቀራረቡም ዘርፉ በቅድመና በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የነበረበትንና ያለበትን ሁኔታ በመለየት ይሆናል ። በመጀመሪያ የምድር ባቡርን እንመልከት ።

የምድር ባቡር ትራንስፖርት በቅድመ አብዮት

እላይ እንደተጠቀሰው የምድር ባቡር በሀገራችን የዘመናዊ ትራንስፖርት ግንባታ ቀደምትነት ያለው ዘርፍ ነው። የምድር ባቡርን ለመዘርጋት በወጣው እቅድ መሠረት እ-ኤ-አ- በጥቅምት ፣ 1897 የሀዲድ መዘርጋት ሥራ ከጂቡቲ ወደብ ተጀመረ። ከአምስት ዓመታት በኋላ እ-ኤ-አ- በታህሣሥ 1902 የሀዲድ መዘርጋት ሥራ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ተጠናቀቀ ። የመዘርጋቱ ሥራ ወደ መሀል ሀገር ቀጥሎ በ1915 አቃቂ በመድረስ በኢትዮጵያ የዓለምአቀፍ ግንኙነት ፣ በተለይ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሁኔታ ላይ በወቅቱ ከፍተኛ ሊባል የሚችል ለውጥ አመጣ ።

ይህ መስመር በመዘርጋቱ ለአያሌ ዘመናት ከውጪው ዓለም በቂ የመገናኛ መስመር ያልነበራትን ኢትዮጵያን መጠነኛ የመገናኛ አውታር ከፈተላት ። መስመሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከውጪው ዓለም ፣ የውጭውንም ዓለም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የበለጠ ለማስተዋወቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ። የባቡር ሀዲድ መዘርጋቱ በኢኮኖሚው ዘርፍ ኢትዮጵያ ወደ ውጪ የምትልካቸው የተለያዩ ሸቀጦች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለዓለም ገበያ እንዲቀርቡ ፣ የሀገር ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴም የበለጠ እንዲስፋፋ ፣ እንዲዳብርና የሸቀጥ ንግድ እንዲጠናከር ረድቷል ። በማኅበራዊ መስክ ከሃዲድ መስመር መዘርጋት ጋር አያሌ ሠራተኞች በመቀጠራቸው በሀገራችን የሠራተኛ መደብ ቁጥር እንዲበረከት፣ መስመሩን በመከተል አያሌ ከተሞች እንዲቆረቆሩና እንዲስፋፉ ፣ ሱቆች እንዲከፈቱ ፣ ብዙ ሕዝብ ከቦታ ወደቦታ እንዲዘዋወር፣ እርስ በርሱም እንዲተዋወቅና እንዲቀራረብ ረድቷል ።

ነገር ግን የምድር ባቡር የተጠበቀውን ያህል የሀገሪቱን እድገት ለማፋጠንና ለማበልፀግ በሚቻልበት ሁኔታ ሊቀጥል አልቻለም ። ኩባንያው በፋሽስት ወረራ ጊዜ በኢጣሊያን መንግሥት ቁጥጥር ሥር በመዋሉ ከሥራው እንቅስቃሴ የተገኘው ዐብት ሁሉ ለኢጣሊያን መንግሥት ጥቅም እንዲውል ተደረገ ። ከጦርነቱም በኋላ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር እ-ኤ-አ- 1944 ባደረገው ስምምነት መሠረት የሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስኪያልቅ ድረስ በሚል ሽፋን ኩባንያው በእንግሊዝ መንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነ። ጦርነቱ እንዳለቀና ኢትዮጵያም ከእንግሊዝ መንግሥት ተፅዕኖ ቀስ በቀስ እየተላቀቀች ስትመጣ በኢትዮጵያና በፈረንሳይ መንግሥታት መካከል ስለባቡሩ መስመር በ1945 ውል ተፈረመ ። በውሉ መሠረት ኩባንያው የኢትዮጵያና የፈረንሳይ መንግሥት ንብረት በመሆን (ማለትም ከወረራው በፊት የነበረውን አቋም በመያዝ) እንደገና ሥራውን ጀመረ።

የምድር ባቡር እ-ኤ-አ- እስከ 1952 ድረስ የኢትዮጵያ አብዛኛው የውጭ ንግድ የመተላለፊያ መስመር በመሆን አገልግሏል ። ነገር ግን በዚሁ ዓመት ኤርትራ ከእናት ሀገሯ ከኢትዮጵያ ጋር በመቀላቀሏ የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ በአሰብና በምጽዋ ወደቦች መንቀሳቀሱ የዚህን የምድር ባቡር በብቸኝነት ይዞት የነበረውን የንግድ እንቅስቃሴ ተጋራው ። በዚህ ውድድር ምክንያት ከ1954—1957 ባሉት ዓመታት መካከል ድርጅቱ ኪሣራ ላይ ወደቀ ።

የፈረንሳይ መንግሥት ኩባንያው ተወዳዳሪ የገጠመው መሆኑንና በኪሣራ መሥራቱ ስላሳሰበው ችግሩን ለማስወገድ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር አዲስ ውል ለመፈራረም ጠየቀ ። ዘጥያቄውም መሠረት ውሉ እ-ኤ-አ- በ1959 ተፈረመ ። ውሉ ከያዛቸው በርካታ ግዴታዎች መካከል፣ ሀ/ ከአዲስ አበባ ጂቡቲ «የተዘረጋውን የምድር ባቡር የሚወዳደር ሌላ የባቡር መስመር እንዳይዘረጋ የሚከለክል ›› ለ/ እስከ 1959

Digitized by Google

ድረስ የፈረንሳይ ወገን ይዞት የነበረውን 75% የአክሲዮን ድርሻ በማስቀረት እያንዳንዳቸው የጠቅላላውን 50% እንዲይዙ የሚደነግግ ፣ ሐ/ ኩባንያው ከተቋቋመ ጀምሮ ፓሪስ ላይ የነበረው የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ላይ እንዲሆን የሚያትቱ ይገኙበታል ።

በአዲሱ ስምምነት መሠረት ሥራውን የቀጠለው ኩባንያ ተገልጋዮችን ለመሳብ ታሪፉን ቀነሰ፤ አገልግሎቱን ለማሻሻል አዳዲስ ሎኮሞቲቮችን ፣ ጋሪዎችን ፣ የሕዝብ ማመላለሻ ሊቶሪናዎችን ገዝቶ በሥራ ላይ አዋለ። በአጠቃላይ በቴክኒክ አንፃር ሲታይ ኩባንያው መጠነኛ መሻሻል አደረገ። ነገር ግን ስለሠራተኛው መብትና ነፃነት ምንም ዓይነት አጥጋቢ እርምጃ ባለመወሰዱ የተፈለገውን ያህል ትርፍ ለማግኘት አልተቻለም ። እያደርም የሠራተኛው ብሶት የበለጠ እየጨመረ መጥቶ ፣ የሠራተኛውን አመጽና ትግል ኩባንያውን የተጠናወተው ባህርይ ሆነ ። ትግሉ አንዳንዴ ቦግ ሲል አልፎ አልፎም የተዳፈነ ሲመስል በአጠቃላይ ሲታይ ግን እየተጠናከረ በመምጣት በአንድ በኩል ሠራተኛው በማኅበር ተደራጅቶ መብቱን ለማስከበር ሲጣጣር ፣ በሌላ በኩል ኩባንያውም በቅራኔ ተወጥሮ ሥራውን ሲያካሂድ የ1966 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ተቀጣጠለ ።

የምድር ባቡር በድህረ አብዮት

በኢትዮጵያ አብዮት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የአዲስ አበባ ጂቡቲ የምድር ባቡር ኩባንያ ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴ አሳይቷል ።

> በዚህ ወቅት የሠራተኛው ቁጥር ከመጨመሩና የኩባንያው የሥራ አመራር ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን መካሄድ ከመጀመሩ ሌላ በድርጅቱም ገቢ በኩል የሚያስደስት አዝማሚያ መታየት ጀምሮ ነበር።እ.ኢ.ለ. በ1975/76 የበጀት ዓመት ከመቼውምጊዜ የበለጠ የሥራ እንቅስቃሴ በመታየቱ ከ25·5 ሚሊዮን ብር በላይ ትርፍ ከመገኘቱም ሌላ ወደ 4 ሚሊዮን የሚጠጋ ብር ወደ መጠባበቂያ ሂሣብ ሊዞር ችሏል ።

ይሁን እንጂ ይህ መልካም የሥራ አዝማሚያ ሊቀጥል አልቻለም ። በጐረቤት አድሃሪ መንግሥታትና በዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም አደፋፋሪነትና እርዳታ በምሥራቅ እና በደቡብ ሀገራችንን የወረረው የሱማሌ መንግሥት በባቡሩ መስመር ላይ የተደጋገመ ጉዳት ማድረስ ጀመረ ። በተለይም በግንቦት ወር 1969 ባደረሰው ጉዳት የባቡሩ መስመር ለአንድ ዓመት ያህል አገልግሎቱን አቋርጦ በኢትዮጵያ ላይ ከፉኛ የኢኮኖሚ ጉዳት አደረሰ ። በዚህ ወረራ የባቡር አገልግሎት መስጫ ሞተሮች ልዩ ልዩ ክፍሎች ለምሳሌ ፣ ሎሪ ሞተሮች ፣ ጐታች ማሽኖች ፣ የዕቃ መጫኛ ጋሪዎች 24 የተለያዩ ርዝመት ያላቸው ድልድዮች፣ የተለያዩ የሠራተኛ መኖሪያዎች ፣ የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶችና ሌሎች ንብረቶች ወድመዋል ። ሌሎች አያሌ ንብረቶችም በወራሪው ተዘርፈዋል ። በአጠቃላይ ወረራው «በመጠነኛ ግምት በኩባንያው ላይ ያደረሰው ጉዳት ወደ 54 ሚሊዮን ብር እንደሚጠጋ ተገምቷል ።» [2]

ድርጅቱ የተሟላ አገልግሎት የመስጠት ሥራውን ለአንድ ዓመት ያህል ለማቋረጥ በተገደደበት ወቅት አብዮታዊው መንግሥት የ6 ሚሊዮን ብር ኦቨር ድራፍት ብድር በመፍቀዱ የኩባንያው ሠራተኞች ደመወዛቸው እንዳይቋረጥባቸው አድርጓል። የወራሪው ጦር በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የተባበረ ትግል ከተደመሰሰና የተረፈውም ወደመጣበት እንዲመለስ ከተደረገ በኋላ የባቡሩ መስመር የወትሮ አገልግሎቱን እንዲጀምር በድርጅቱ ሠራተኞችና በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ጥረት ተደረገ ።

በወረራው የወደመውን ኤኮኖሚ መልሶ እንዲያንሰራራ የበለጠ ትኩረት ሲደረግ የምድር ባቡርን ለማጠናከርና አገልግሎቱንም ከፍ ለማድረግ አያሌ እርምጃዎች ተወሰዱ ። ልዩ ልዩ የመንግሥት ድርጅቶች ፣ መለዮ ለባሾችና ሚሊሺያዎች ከኩባንያው ሠራተኞች ጋር በመተባበር የፈራረሱ ድልድዮች እንዲሰሩና የወደሙ አያሌ ንብረቶች እንዲ

Digitized by Google

ተኩ በማድረግ ኩባንያው አገልግሎቱን እንዲጀምር ተደረገ። በሌላ በኩልም እንደ ትዮጵያ አቆጣጠር በ1969 ከፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ነፃ የወጣችው ጅቡቲ ለባቡሩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መስፋፋት ከፍተኛ ፍላጐት ያላት ሀገር መሆኗ ተገለፀ ። ሁለቱም ሀገሮች ለኩባንያው ሥራ መሻሻልና መስፋፋት ያላቸውን በጐ አስተሳሰብ ተግባራዊ ለማድረግ በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል መጋቢት 12 ፣ 1973 አንድ ስምምነት ተፈረመ ። በዚህ ስምምነት መሠረት ኩባንያው«የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት» በመባል ከመሰየሙ በተጨማሪ አዲስ አበባንና ጅቡቲን የሚያገናኘውን የምድር ባቡር የጋራ በማድረግ ኪሣራን በማያስከትልና አስተማማኝ በሆነ መሠረት ላይ እንዲቋቋምና ለሁለቱ ሕዝቦች ጥቅም እንዲውል፣ ባቡሩ የሚሰጠውም አገልግሎት ለሁለቱ ሀገሮች ብቻ ሳይሆን ለሚገኙበትም አካባቢ ጭምር የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እድገት አመች ሁኔታዎችን እንዲፈጥር የሚደረግ መሆኑም ተገለፀ። በተጨማሪም ድርጅቱን የሚመራው የአስተዳደር አካል ከኢትዮጵያና ከጅቡቲ በእኩል ቁጥር የተውጣጡ አባላት ያለው የአስተዳደር ምክር ቤት እንዲሆን ተደረገ ።

ይህ አዲስ ስምምነት ከተፈረመ በኋላ የድርጅቱን የቴክኒክ ሁኔታ (የአገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችን ጭምር) እንዲሁም የውስጥ አሠራርና አስተዳደር ለማሻሻልና ለማጠናከር አያሌ እርምጃዎች ተወስደዋል። ኩባንያው የሚጠቀምባቸው የአገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች የባቡሩ ሃዲድ ከዛሬ 80 ዓመት በፊት በአበካባቢው ሲዘረጋ የተሠሩ መሣሪያዎች በመሆናቸው ኋላቀር፣ ያረጁና በተለይም የመለዋወጫ ዕቃ የማይገኝላቸው ናቸው።ይህን ሁኔታ ለማሻሻል ከውጪ በተገኘና ወደፊት በሚገኝ እርዳታ የተለያዩ አዳዲስ የአገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች እየተገዙና ሊገዙም እየታቀዱ ነው ። ለምሣሌ 10 የመንገድ ጋሪዎች፣ 1 ሊቶሪና 2 ሎኮሞቲቮች፣ 6 የመፈተሻ ጋሪዎችና ልዩ የመለዋወጫ ዕቃዎች ተገዝተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው ። [3]

የድርጅቱን የሥራ አመራርና የአሠራር ዘይቤም ለማሻሻልና የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው።በዚህ መሠረት የሥራ አመራሩን ለማሻሻል ልዩ ጥናት ተካሂዶ ተግባራዊ እንዲሆን ሃሳቡ ቀርቧል ። የቴክኒክ ባለሙያዎችን ለማሰልጠንም በጅቡቲ ከተማ አንድ የማሰልጠኛ ማዕከል ለማቋቋም ታቅዷል። ከዚህም ሌላ በሀገራችን ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በመሄድ ላይ ያለውን የየብስ ትራንስፖርት ፍላጐት ለማርካት ያለውን የምድር ባቡር መስመር አሠራርና የቴክኒክ ሁኔታ ማሻሻል ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ የባቡር ሃዲድ መስመሮችን ለመዘርጋት እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ሆኗል።በዚህም ምክንያት፣

1. ከአሰብ አዲስ አበባ የባቡር መስመር ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት ለማድረግ የሚያስፈልገው የሥራ መመሪያ (Terms of Reference) ከሕንድ የምድር ባቡር ድርጅት ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ተጠናቆ በቅርቡ ጥናቱ እንደሚጀመር ይጠበቃል ፤
2. በአገሪቱ ውስጥ ሌሎች የባቡር መስመሮችንም ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመጀመር ዝግጅት በመደረግ ላይ ነው።

በአጠቃላይ በ1973 በተደረገው ስምምነት የኩባንያውን የውስጥ አሠራርና አስተዳደር ለማሻሻል በተወሰደው እርምጃና በሠራተኞች ጥረት ድርጅቱ ዛሬ ከአክሳሪነት ወደ አትራፊነት ተሸጋግሯል ። በተለይ በ1975 የበጀት ዓመት ከኪሣራ ወጥቶ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ትርፍ አግኝቷል። መሻሻሉ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ለመገመት ከሚያስችሉት መለኪያዎች አንዱ በ1975 የተጠቀሰውን ታሪፍ ያገኘ ከመሆኑ አንጻር በ1974 ይኸው ድርጅት 1,207,400 ኪሣራ ደርሶበት የነበረ መሆኑ ነው። ወደፊትም የምድር ባቡርን በታቀደው መሠረት የበለጠ ማስፋፋትና ማሻሻል በብዙ መኪ

Digitized by Google

ናዎች፣ በአያሌ ምልልስና በከፍተኛ ወጪ የሚጓጓዙ ጭነቶችን በቀላሉ፣ በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ወጪ ለማንሳት፣ እንዲሁም ይህን የትራንስፖርት ዘርፍ ከሌሎች የትራንስፖርት ዘርፎች ጋር የበለጠ ለማቀናጀትና ሥራውን ለመምራት ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል ።

የመንገድ ትራንስፖርት

እላይ እንደተጠቀሰው ተሽከርካሪ መኪና ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ1899 ነበር።ሆኖም እስከ 1928 ማለትም በቅድመ ፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ድረስ የመንገድ ትራንስፖርት ይህ ነው የሚባል ጉልህ እድገት አሳይቷል ለማለት አያስደፍርም። ስለዚህም የመንገድ ሥራ በሀገራችን በሰፊው የተካሄደው ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በ1928 ከወረረች በኋላ ነው ማለት ይቻላል። በዚሁ የወረራ ወቅት የትራንስፖርት ሥራ ይካሄድ የነበረው በኢጣሊያ መንግሥትና በአንዳንድ የውጪ አገር ዜጐች አማካይነት ነበር ። ወራሪዋ ኢጣሊያ በቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች ትግል ድል ሆና ስትባረር በእጅዋ የነበሩትን የንግድ ተሽከርካሪዎች የኢትዮጵያ መንግሥት ተረክቦ የትራንስፖርት ሥራ ማካሄድ ጀመረ ። ይህ የኢኮኖሚ ዘርፍ በሀገሪቱ ገና አዲስና ታዳጊ ስለነበረ በዚሁ መስክ ለተሰማሩት የሀገር ውስጥና የውጭ ሃብታሞች ከፍተኛ ጥቅም ማጋበሻ በመሆኑ በኢትዮጵያውያንና በውጪ ከበርቴዎች መካከል የጥቅም ቅራኔ ተፈጠረ ። ቅራኔው እየጐላ በመምጣቱ ለረጅም ጊዜ ትግል ከተደረገ በኋላ ኢትዮጵያውያን የመንገድ ትራንስፖርትን ክፍለ ኢኮኖሚ ሊቆጣጠሩት ቻሉ ።

ይሁን እንጂ የውጪ በዝባዦች በሀገሪቱ ከበርቴዎች መተካታቸው የሰፊውን ሕዝብ የትራንስፖርት ፍላጐት ሊያሟላ አልቻለም ። እንዲያውም የእነዚህ ስግብግብ ከበርቴዎች ቁጥር እየበረከተ መሄድ በመካከላቸው ፉክክርን በመፍጠሩ የትራንስፖርትን እድገት ይበልጥ እየገታው መጣ ። ከዚሁ ጋር አዳዲስ ችግሮች እየተፈጠሩ የትራንስፖርት ሥራ ስርዓተ አልባና የሕዝቡም የትራንስፖርት ፍላጐት እንዳይሟላ ሆነ ።

በመንገድ ትራንስፖርት ሥራ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች መካከል የተፈጠረው የጥቅም ግጭት ካስከተላቸው መሠረታዊ ችግሮች መካከል ጥቂቶቹ ፡—

1. ወደ ትራንስፖርት የሥራ መስክ ለመግባት የሚፈልጉ በርካታ የሀገሪቱ ዜጐች የመስመር ፈቃድ ለማውጣት ባለመቻላቸው በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት ሹማምንትን ደጅ በመጥናትና እጅ በመንሳት በርካታ ዓመታት እንዲያሳልፉ መደረጉ ፤

2. የመስመር ፈቃድ ካገኙ በኋላም ከበርቴ ነጋዴዎች መስመሩን በከፍተኛ ዋጋ ስለሚሸጡ አነስተኛ ነጋዴዎች የጥቅሙ ተካፋይና የክፍለ ኢኮኖሚው አጋዥ ሊሆኑ አለመቻላቸው፣

3. ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ተገልጋዩ ሕዝብ በሚፈለግበት ሰዓት ወደ ፈለገው ሥፍራ ሊጓጓዝ አለመቻሉና ሥራው የሚመለከተው ክፍልም ታሪፍን ባለመወሰኑ ተገልጋዩ ሕዝብ ለከባድ ብዝበዛ መጋለጡ ፤ የመንገድ ትራንስፖርት መስመሮችን በሞኖፖል የያዙትና የግል ተሽከርካሪዎች ባለቤት የሆኑት ጥቂት ከበርቴዎች የመንግሥት ታክስንና ግብርን በትክክልና በወቅቱ አለመክፈላቸው ነበር ።

ይሁንና የወደቀው የፊውዳል መንግሥት ከየአቅጣጫው የተነሱት የትራንስፖርት ችግሮች እየተባባሱ በመምጣታቸው በ1952 የሕዝብ ማመላለሻን ታሪፍ ለመወሰን ተገደደ ። የተወሰነው ታሪፍ ከፍተኛውንና ዝቅተኛውን የሚያመለክት እንጂ ታሪፉ በተግባር ስለመተርጐሙ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ መንግሥታዊ አካል አልተቋቋመም ነበር።በዚህና በሌሎች ምክንያቶች የትራንስፖርትን አሰራር መስመር ለማስያዝና ችግሩን ለማቃለል ባለመቻሉ በጥናት የተደገፈ ነው የተባለ ሌላ የመንገድ ማመላለሻ አዋጅ በ1960 ወጥቶ በዚሁ አዋጅ መሠረት የመንገድ ማመላለሻ አስተዳደር ተቋቋመ ።

Digitized by Google

የአስተዳደሩ ተቀዳሚ ተግባር የመስመር ፈቃድና የጉዞ ቁጥጥር ማድረግ ነበር። ይሁን እንጂ አዋጁ ከታወጀ በኋላም አስተዳደሩ ሥራውን ወዲያውኑ ሊጀምር ባለመቻሉ ለሁለት ዓመታት ያህል ሲጓተት ቆይቶ በ1962 ሰባት ሠራተኞችን ይዞ ሥራውን ጀመረ። የ1960 የመንገድ ማመላለሻ አስተዳደር አዋጅ ዓላማ የመስመር ፈቃድና የጉዞ ቁጥጥር ለማድረግ መሆኑ ቢታወቅም ከአዋጁ በስተጀርባ የነበረው ፍላጐት በአመዛኙ ለከፍተኛ የትራንስፖርት ባለንብረቶች የበላይነት ሥልጣን ለመስጠት ነበር ።

በመሆኑም አዋጁ ፦

1. ባለንብረቶች ማኅበር እንዲያቋቁሙና ሥራቸውን ፊት ከነበረው ይበልጥ አጠናክረው፤የማያቋርጥ ትርፍ ለማካበት እንዲችሉ በር ከፈተላቸው ።
2. የድምጽ አሰጣጥ ለአንድ ሰው አንድ ድምጽ የሚለው ሳይሆን ፣ አንድ ሰው የመኪናዎቹን ወንበሮች ብዛት ያህል ድምጽ እንዲኖረው ስለተደረገ በዚህ ሁኔታ በተቋቋመው ማኅበር ውስጥ ከፍተኛ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች የማኅበር መሪዎች ለመሆን አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው።
3. በማኅበሩ ውስጥ የአመራር ሥፍራ የያዙ ከበርቴዎች ከማኅበሩ አባላት የሚሰበሰቡትን ገንዘብ በጋራ ጋራዥ ፣ የመለዋወጫ እቃ መጋዘንና የነዳጅ ማደያ የመሳሰሉ አስፈላጊ ድርጅቶችን ሊያቋቁሙበት ሲገባ ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው እንዲያውሉት አስቻላቸው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ባለተሽከርካሪዎች በመንግሥት ፖሊሲ አውጪ ቦርድ ውስጥ የ40.6% ድምጽ ሲኖራቸው በመቻሉ የመንገድ ማመላለሻ አስተዳደር የተገልጋዩን ሕዝብ መብት ለማስከበር ደንቦችንና መመሪያዎችን አውጥቶ ተግባራዊ ለማድረግ አልቻለም። በ1962 ሥራውን የጀመረው የመንገድ ማመላለሻ አስተዳደር የሥራ ማስኬጃ በጀቱ ብር 276,896.08 ብቻ ነበር ። በ1965 የአስተዳደሩ ሠራተኞች ቁጥር ወደ 58 ከፍ ሲል በዚህ ዓመት ከኢትዮጵያ ትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የከብደት መጠን ቁጥጥር ሥራ ወደ መንገድ ማመላለሻው በመዛወሩና ይህን ሥራ ያከናውኑ የነበሩት 29 ሠራተኞችም አብረው በመዛወራቸው የሠራተኛው ብዛት 87 ደርሷል።

የመንገድ ትራንስፖርት በድኅረ አብዮት

አብዮታችን በ1966 ሲፈነዳ የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ እንደቀሩት የኢኮኖሚ ክፍሎች በአጠቃላይ ሲታይ ኋላቀርና ደካማ ነበር። በተለይም የመንገድ ትራንስፖርት በጣም አዝጋሚ በመሆኑ በሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚ ላይ የነበረው ተጽዕኖ ቀላል አልነበረም። እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ የተሰራው የመንገድ ርዝማኔ 1,750 ኪ.ሜ አስፋልትና 4,888 ኪ.ሜ ጠጠር መንገድ ሲሆን በድምሩም 6,638 ኪ.ሜ ነበር ። በተለያዩ የትራንስፖርት ዘርፎች መካከል የነበረው የእድገት ደረጃም በጣም የተራራቀና የተዛባ ነበር። በትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው የመንገድ ትራንስፖርት ከሌሎች የትራንስፖርት ዘርፎች ያነሰ ድርጅት የነበረው መሆኑ የችግሩ ዓይነተኛ ገጽታ ነው ።

በአብዮቱ ሂደት የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚያችን ካጋጠሙት መሠረታዊ ችግሮች መካከል የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በአመዛኙ የአገልግሎት ዘመናቸውን ያገባደዱ በመሆናቸው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ለማጠናከር ያለው አቅም ዝቅተኛነት መሆኑ ነው።ለምሳሌም ያህል የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ከከፍተኛ አውቶቡሶች 64% ከመለስተኞች 80% እና ከአነስተኞች ደግሞ 60% የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ ሲሆኑ፣ እነዚህን ሁሉ ለመለወጥና የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማሻሻል አቅምና ጊዜን ጠይቋል ።

ከእነዚህ የትራንስፖርት መሣሪያዎች እርጅና ጋር ተያይዞ መገምገምና መታየት

Digitized by Google

ያለበት ሌላው ችግር የመለዋወጫ እቃ ጉዳይ ነው።የአገልግሎት ዘመናቸውን ለጨረሱ ተሸከርካሪዎች አስፈላጊውን ጥገና እድሳት እያደረጉ ከመገልገል ሌላ የተሻለ አማራጭ ባልተገኘበት ሁኔታ የመለዋወጫ እቃዎች በተፈለገው ዓይነትና ወቅት አለመገኘት ፣ ቢገኙም ዋጋቸው በየጊዜው እየናረ መሄድ ችግሩን የበለጠ አባብሶታል ።

በዚህ ዘርፍ የተከሰተው ሌላው ችግር ደግሞ መናኸሪያዎችና መንገዶች የተፈለገውን ያህል ተጠናክረውና ተስፋፍተው አለመገኘታቸው ነው ።

በየትኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ እንደሚታየው በትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚም የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር አለ። በተለይ በመንገድ ማመላለሻው ዘርፍ ይሠሩ የነበሩት ሠራተኞች ድርጅቶች በግለሰቦች እጅ በነበሩበት ጊዜ የተቀጠሩ በመሆናቸውና በአብዛኛውም የሙያው ልምድ እንጂ የሥራው መስክ የሚጠይቀው በቂ እውቀት የሌላቸው መሆን እንዲሁም ይኸው ችግር ታውቆ አስፈላጊውና በቂ የሙያ ማሻሻያ ትምህርት አለመስጠቱ አገልግሎቱን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ላይ ተጽእኖ አሳድሯል ።

በማንኛውም ክፍለ ኢኮኖሚ የሰለጠነ የሰው ኃይል ወሳኝነት ያለውን ያህል የመንገድ ትራንስፖርትም የማይዳሰሰው የኅብረተሰብ ክፍል ስለሌለ ለሥራው የሰለጠነ የሰው ኃይል አስፈላጊነትን ከዚሁ ሁሉ ጋር አጣምሮ መመልከት ተገቢ ነው ። በትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰማሩ ሠርቶ አደሮች የእርሻውም ሆነ የኢንዱስትሪ ወዝ አደሮችን በቅርብ የሚያገናኙ ፣ የእርሻውን ምርት ለከተማው ፣ የኢንዱስትሪውን ውጤት ለገጠሩ ሕዝብ የሚያደርሱ ፣ የአንድ ሀገር ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ የደም ሥር በመሆናቸው ለሥራው የሚኖራቸው ብቁነት ከዚህ ሁሉ ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት ።

ከመገልገያ መሣሪያዎች እርጅና ፣ ከመለዋወጫ እቃዎች እጥረትና ከዋጋ መናር ፣ ከመናኸሪያዎች አለመስፋፋትና ከሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ጋር የሚከሰተው ሌላው መሠረታዊ ችግር የስምሪትና የቁጥጥር ተግባር በትክክል አለመገኘት ነው ። የመገልገያ መሣሪያዎች አርጌ በመሆናቸው ባልተጠበቀ ጊዜ አገልግሎታቸውን ሊያቋርጡ ይችላሉ ። የመለዋወጫ እቃዎች በሚፈለጉበት ዓይነትና ወቅት ስለማይገኙ የተበላሸው መገልገያ ቶሎ ተጠግኖ አገልግሎቱን አይጀምርም። በዚህ ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ተጨምሮበት የስምሪትና የቁጥጥር ተግባርችን ከንዋኔ ችግር ላይ ጥሎታል ። ከጥቅምት 24—25 ቀን 1976 በትራንስፖርት መገናኛ ሚኒስቴር ንመታዊ ሴሚናር ላይ ከተነሱት መሠረታዊ ችግሮች መካከል ትክክለኛ የስምሪትና የቁጥጥር እቅድ መንደፍ አለመቻሉና ይህም በትራንስፖርት እንቅስቃሴ ላይ ያስከተለው ችግር ይገኙበታል ።[4]

በዚህም ረገድ ቢሆን ከፍተኛው ችግር የሚታየው በመንገድ ማመላለሻ ዘርፍ ነው። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉት ። ከሁሉ በፊት የመገልገያ መሣሪያዎች አሁንም ቢሆን በአመዛኙ በግለሰቦች ይዞታ ሥር ናቸው።አብዛኛዎቹ ግለሰቦች የመንገድ ማመላለሻ ዘርፍን የሚመለከቱት የግል ጥቅም ማጋበሻ መሣሪያ አድርገው እንጂ ኅብረተሰቡን የማገልገል ኃላፊነታቸውን አይረዱም፤የአገልግሎት ዘመኑን የጨረሰ ተሽርካሪ በግለሰቦች እስተያየት ቢበዛ መጠገን እንጂ መለወጥ አያሻውም። ትክክለኛ አገልግሎት ለመስጠት የሰለጠነ የሰው ኃይል አስፈላጊነት አይታያቸውም ወይም አይፈልጉም ።

በሌላ በኩል የስምሪትና የቁጥጥር ተግባሮች በሚገባ እንዳይከናወኑ እንቅፋት የሚሆነው የተገልጋዩ ክፍል (የመንግሥት ድርጅቶችን ጨምሮ) ወእትድ የመሥራት ልምድ አለመዳበር ነው። አገልግሎቱን ጠያቂው ኅብረተሰብ በተቀናጀ መልክ የመሥ

Digitized by Google



ከአሰብ ወደብ ወደ መሐል አገር ዕቃዎች ሲጫኑ



የባቡር ትራንስፖርት እንቅስቃሴ (ከጅቡቲ አዲስ አበባ)

Digitized by Google

ራት ባህሉ ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።
በዚህ አንፃር በተለይም በጭነት ማመላለሻ
ውና በወደቦች አካባቢ የሥራ ቅንጅት
ጉድለት በጉልህ ይታያል ። ከሀገራችን ከፍ
ተኛውን ቁጥር የያዘው ሕዝብ በግብርና
የሚተዳደር እንደመሆኑ የእርሻ ውጤቶች
በአንድ ወቅት ስለሚደርሱና የተመረተው
ሁሉ ወዲያውኑ እንዲጓጓዝ ስለሚጠ
ይቅ ፣ የተላኪና የተመላሽ ጭነት ቅንጅት
ጉድለት በየጊዜው የሚከሰት አቢይ ችግር
ሆኗል ።

በአብዮቱ የተወሰዱ እርምጃዎች

ከእድገት ደረጃችን ዝቅተኝነትና ከወረስ
ነው ኋላቀር ኢኮኖሚ ምክንያት እንዲሁም
በአብዮቱ ሂደት ውስጥ የተከሰቱትን ዓበይት
የትራንስፖርት ችግሮች ለሚቃለል ብሎም
ለማስወገድ ሕዝባዊው አብዮት ባለፉት
አሥር ዓመታት የምድር ባቡርን አገልግ
ሎትለማሻሻል እንደወሰደው ሁሉ የመንገድ
ትራንስፖርትም ለማሻሻል ልዩ ልዩ እር
ምጃዎች ወስዷል። በመዋቅር ፣ በተግባር ፣
በአደረጃጀት ፣ በሰው ኃይል ፣ በመሣሪያ ፣
ወዘተ...በኩል የተወሰዱትን ዋና ዋናዎቹን
እርምጃዎች የሚናቁ አይደሉም ።

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ከሚሳፈረው
መንገደኛ ዘጠና ሰባት በመቶና ከሚጓጓዘው
ጭነት ዘጠና በመቶው የሚካሄደው በመን
ገድ ትራንስፖርት ነው ። [5] በአንድ በኩል የ
መንገድ ትራንስፖርት ከፍተኛውን ሥፍራ
የያዘ መሆኑና በሌላ ወገን ደግሞ ይህ ዘርፍ
በአብዛኛው ከግለሰቦች እጅ ሳይወጣ መን
ግሥት የኅብረተሰቡን ጥቅም ለማስከበር
አስፈላጊውን ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት
ምን ያህል ውስብስብ ችግሮችን ሊያስከትል
እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም ። በኅብ
ረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መመ
ሪያ እንደተገለፀው «የከባድና የቀላል የጭ
ነት መኪናዎችና አገልግሎት ፣ በከተሞች
መካከል የሚደረገው የማመላለሻ አገልግ
ሎት ... በግል ይዞታ እጅ እንዳለ ሆኖ መን
ግሥት የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ለማስከበር
አስፈላጊ ቁጥጥር [6] እያደረገ ቢሆንም በዚህ
ዘርፍ የግል ይዞታ በብዛት የሚገኝ በመሆኑ
ችግሮች መከሰታቸው አልቀረም ።

የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በ1967
በተከታታይ ያወጣቸውን የኢኮኖሚ መመሪ
ያና የማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት አዋጆች
ን በሚገባ በመረዳትና በ1968 የወጣውን የ
ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም
ዓላማዎችን በመገንዘብ የግል ተሽከርካሪ
ባለንብረቶች የባለንብረትነት መብታቸው
ሳይነካ ሕዝቡን የማገልገል ኃላፊነታቸውን
መወጣት ሲገባቸው ፣ አንዳንድ አወናባጆች
ከላይ የተሰጠውን ግልጽ የመንግሥት ፖሊሲ
ችላ በማለት «ትራንስፖርት ሊወረስ ነው»
እያሉ በሚያናፍሱ ወረኞች በመወናበድ ፣
ብዙዎች መኪናዎቻቸውን ለማደስ ከመቆጠ
ባቸውም ሌላ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥ
ት ኢኮኖሚ መመሪያ ለግል ባለሀብቶች በተ
ፈቀደው የሥራ መስክ መሠረት አዳዲስ የን
ግድ ተሽከርካሪዎችን በሚፈለገው መጠን
ባለመግዛታቸው የተሽከርካሪ እጥረት ሊፈ
ጠር ችሏል ። ይሁንና አብዮታዊው መንግ
ሥት የኅብረተሰቡን የትራንስፖርት ፍላ
ጎት ለማሟላት ከፍተኛውንና ተቀዳሚውን
ኃላፊነት በመውሰድ እስከ አሁን 100 የከ
ፍለ ሀገርና 50 የከተማ ከፍተኛ አውቶቡስ
ችን ፣ በ1976 የበጀት ዘመን 640 የደረቅ ጭ
ነት ከባድ መኪናዎችን ፣ 157 የፈሳሽ ጭነት
ተሽከርካሪዎችን ለኅብረተሰቡ አገልግሎት
እንዲሰጡ በማድረግ ችግርን ለመቋቋም
ጥረት አድርጓል ።

ባጭሩ በዚህ ክፍለ ትራንስፖርት የታየ
ውን ዕድገት በንጽጽር መልክ ከሚከተለው
ሰንጠረዥ በቀላሉ መረዳት ይቻላል ።

Digitized by Google

<u>የመንገድ ትራንስፖርት ዕድገት*</u>

	1975	1976
1. የመንገድ ርዝመት (በኪ/ሜ)	6,638	15,941
2. የተሽከርካሪ ብዛት	47,678	56,994
3. የሕዝብ ንግድ ተሽከርካሪ		
የዕቃ	6,791	7,775
የነዳጅ	428	611
የመንገደኛ	2,134	4,408
ድምር	9,353	12,794
4. <u>የመንግሥት ንግድ ተሽከርካሪ</u>		
(የዕቃ የነዳጅና የመንገደኛ)	—	1,579
የናትራኮር	4,554	5,222
የሌሎች	4,554	6,801
5. <u>የመንገደኛ አገልግሎት</u> (ክ/ሀገር) **		
ተሳፋሪ (በሺህ)	2,787	43,412
ተሳፋሪ (በኪ/ሜ) በሚሊየን	595.7	2,887.6

በለውጡ ሂደት ውስጥ እየነቁ የመጡት ሠርቶአደሮች በማናቸውም ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስክ የተከሰቱትን ችግሮች ከመንግሥት ጋር በመተባበር በቆራጥነት እንደተወጡት ሁሉ በትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ የተከሰቱት ችግሮችም በየደረጃው መፍትሔ እንዲያገኙ ጥረት አድርገዋል ። በሠርቶአደሮችና በሀቀኛ ታጋዮች መስዋዕትነት የትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚውን መልክ ለማስያዝ ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል አንዱ በህዳር ወር 1969 የወጣው የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ነው ።

አዋጁ በሀገሪቱ የመንገድ ትራንስፖርት ሥርዓት ላይ በቀላሉ የማይታይ ለውጥ አምጥቷል ። የዚህ አዋጅ መውጣት የመንገድ ማመላለሻ አስተዳደር ይባል የነበረው መ/ቤት ትጠናክሮና ሰፊ ኃላፊነት ተሰጥቶት «የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን» እንዲባል ከማስቻሉም በላይ በጭነትና በሕዝብ ማመላለሻ ዘርፍ የተሰማሩትን የግልና የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና ቁጥጥር የሚከታተል አዲስ ድርጅት እንዲፈጠር አድርጓል ። ይህም አዲስ ተቋም «ብሔራዊ የመንገድ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን» የሚባለው ነው ።

ብሔራዊ የመንገድ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን በሥሩ የተለያዩ ድርጅቶችን ያስተዳድራል ። እነዚህም ድርጅቶች በሕዝብ ማመላለስ ተግባር የተሰማሩትን የመንግሥትና የግል ከፍተኛ ፣ መለስተኛና አነስተኛ አውቶቡሶችን የሚያጠቃልለው የሕዝብ ማመላለሻ ዘርፍ፣ የጭነት ማመላለሻ ድርጅቶችን የሚያቅፈው የጭነት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና ቁጥጥር ዋና መምሪያ (ከ6 ቀጠናዎች

* ትራንስፖርትና መገናኛ ፤ ልዩ እትም ፤ መስከረም 1977 ገጽ 11

* * የመለስተኛ ተሽከርካሪዎችን መንገደኞችን አይጨምርም ።

Digitized by Google

ጋር)፣ የጭነት ማመላለሻ ድርጅት (ጭግድ) እንዲሁም አገልግሎት ሰጪ የሆኑ ድርጅቶችን የያዘው የመለዋወጫ እቃ አስመጪና አከፋፋይ ድርጅት፣ የንዳጅ ማደያዎች አገልግሎት ድርጅት ናቸው ።

የ1969 የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣንን ከማጠናከሩና ብሔራዊ የመንገድ ማመላለሻ ኮርፖሬሽንን ከመፍጠሩም ባሻገር በእነዚህ ሁለት መንግሥታዊ ተቋሞች አማካይነት የመንገድ ማመላለሻው ተግባር ሥርዓት እንዲይዝ አድርጓል ። የሁለቱ መንግሥታዊ ተቋሞች መፈጠር እስከዚህ አዋጅ መውጣት ድረስ ማዕከላዊ አመራርና አሠራር ጉድኳቸው የነበሩት መሠረታዊ የሆኑት የመንገድ ማመላለሻ ድርጅቶች መልክ እንዲይዙ ረድቷል ።

የ1969 የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ካስገኛቸው ድሎች መካከል አንዱና ዋነኛው በሀገሪቱ የመንገድ ማመላለሻ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ችግር ሆና ለቆየው የታሪፍ ተመን መፍትሔ ማስገኘቱ ነው።በዚህ አዋጅ መሠረት የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ተግባራዊ ሊሆን የቻለ የመንገድ ማመላለሻ የታሪፍ ደንብ አውጥቷል ።

የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ታሪፍ ደንብ የሕዝብና የጭነት ማመላለሻዎችን ይመለከታል ። የሕዝብ ማመላለሻን በሚመለከት ሁለት ዓይነት ታሪፎች አሉ ። የመጀመሪያው የመቀመጫው ልክ 50 እና ከ56 በላይ ለሆኑት ከፍተኛ ክፍለ ሀገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች የሚያገለግል ታሪፍ ሲሆን ይኸውም በሰው በኪሎ ሜትር 3.155 ሣንቲም ነው ። ሁለተኛው የታሪፍ ዓይነት ደግሞ እስከ 200 ኪሎ ሜትር ክልል ውስጥ ለሚሠሩ አንስተኛና መለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የተመደበ ታሪፍ ሲሆን በሰው በኪሎ ሜትር 3.385 ሣንቲም ያስከፍላል ።

የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች ስማቸው እንደሚያመለክተው ሕዝብ ከአንድ ሥፍራ ወደሌላው የሚጓዝባቸው ቢሆንም እቃ ወይም ጓዝ አይጓጓዝባቸውም ማለት አይደለም ። በሀገራችን የትራንስፖርት አገልግሎት ባለመስፋፋቱና ኅብረተሰቡም ከጓዙ ተለይቶ የመሄድ ባህሉ ገና ያልዳበረ በመሆኑ መንገደኛው የተወሰነ ጓዝ ይዞ መንቀሳቀስ የግድ ነው ። በዚህም መሠረት አንድ መንገደኛ እስከ 25 ኪሎ ግራም የሚመዝን ጓዝ በከፍተኛ ክፍለ ሀገር አቋራጭ አውቶቡሶች በነፃ የማጓጓዝ መብት የተሰጠው ሲሆን ከዚህ በላይ ጓዝ ይዞ ከመጣ ከ25 ኪሎ ግራም እስከ 50 ኪሎ ግራም ለእያንዳንዱ ኪሎ ግራም በኪሎ ሜትር ብር 0.001፣ ከ50 ኪሎ ግራም እስከ 75 ኪሎ ግራም ለእያንዳንዱ ኪሎ ግራም በኪሎ ሜትር ብር 0.002፣ እንዲሁም ከ75 ኪሎ ግራም በላይ ለእያንዳንዱ ኪሎ ግራም በኪሎ ሜትር ብር 0.003 እንዲከፍል መመሪያ ወጥቷል ።

አጠቃላይ የሕዝብ ማመላለሻው ታሪፍ ይህን ቢመስልም እንደተጨባጭ ሁኔታዎች አስገዳጅነት የሚለዋወጡ ጉዳዮችም አሉ። በተለይ ጓዝን በሚመለከት ሁሉም ተጓዦች ብዙ ጓዝ ይዞ ቢመጣ ምናልባት ከአውቶቡሱ የመሸከም አቅም በላይ ሊሆን ይችላል ። በሌላ በኩል ደግሞ በአጠቃላይ ገጽታው አንድ መንገደኛ ከ50 ኪሎ ግራም የበለጠ ጓዝ እንደማይዝ ቢታመን በትም ገደቡ የማይመለከታቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን መዘንጋት አያሻም ። ገደቡ የማይመለከታቸው፣

ሀ. በገዳጅ ላይ ቆይተው በፈቃድ ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ ትውልድ ቦታቸው የሚሄዱትን ወይም ከትውልድ ቦታቸው ወደ ግዳጅ የሚመለሱትን ወታደሮች ፣

ለ. የምርት መግሪያን ለመጠገን የቴክኒክና የጤና ባለሙያዎች የሚይዟቸው የቴክኒክ መግሪያዎችንና ለአጣዳፊ የምርት ሥራ የሚላኩትን ዶክሜንቶች ፣

ሐ. ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች ሁኔታዎችም

Digitized by Google

በሚያጋጥመው ጊዜ ችግር እንዳይፈጥር አግባብ ባለው ማዕከላዊ ክፍል እየተጣራ ገደቡ እንዳይመለከታቸው ይደረጋል ።

አጠቃላይ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶችን በሚመለከት የታሪፉ ተመን ይህን የመሰለ ቢሆንም ጓዝን በሚመለከት ለአነስተኛና ለመለስተኛ ተሽከርካሪዎች ታሪፍ የተወሰነ ባለመሆኑ ፣ ከዚህም በላይ እነዚህ ተሽከርካሪዎች ከሞላ ጐደል በግለሰቦችና በግል ድርጅቶች ይዞታ ሥር በመሆናቸው፣ ባለተሽከርካሪዎችም በተቻላቸው ዘዴ ሁሉ ብዙ ገንዘብ የማጋበስ ፍላጐት ስላላቸው ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ ። ይሁን እንጂ የስምሪትና የቁጥጥር ተግባሩን የሚከታተለው የሕዝብ ማመላለሻ ዘርፍ ችግሮች በተከሰቱ፡ ጊዜ ሁሉ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል ።

የታሪፍ ደንብ የሚመለከተው ሌላው የጭነት ማመላለሻን ነው ። የጭነት ማመላለሻው ታሪፍም እንደ ሕዝብ ማመላለሻው ሁሉ በሁለት የተከፈለ ነው ። የመጀመሪያው የጭነት ታሪፍ ዓይነት ተሳቢ ለሌለው ተሽከርካሪ በኩንታል በኪሎ ሜትር 2.49 ሣንቲም ሲሆን ለባለ ተሳቢ ተሽከርካሪ ደግሞ የተለየ ታሪፍ አለ ።

የባለተሳቢ ተሽከርካሪ ታሪፍ ራሱ በሁለት የተከፈለ ነው ። አንደኛው ከአዲስ አበባ አሰብ መስመር ላይ ያለውን የሚመለከት ሲሆን ሌላው ደግሞ ከአዲስ አበባ አሰብ መስመር ውጪ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚሠሩትን ይመለከታል ። ከአዲስ አበባ አሰብ መስመር ውጪ ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ለሚሠሩ በ1.25 ሣንቲም በኩንታል በኪሎ ሜትር ሆኖ ተሽከርካሪው ጭነት እንዲያነሳ በሚደረግበት ጊዜ ያለጭነት ለመሄድ ወይም ለሚመለስበት በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 48/1967 የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ታሪፍ ደንብ መሠረት 35% አስጫኙ ለጫኙ ይከፍላል ። አዲስ አበባ- አሰብ መስመር ላይ ለሚሠሩ ግን በ1·25 ሣንቲም በኩንታል በኪሎ ሜትር ሆኖ ተሽከርካሪው ያለ ጭነት ለሚሄድበት ተጨማሪ ክፍያ አይደረግም ።

የ1969 የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ከሰጠው ሥልጣንና ተግባራት መካከል አንዱ «ለመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት የመነሻና የመድረሻ ተርሚናሎችን ለማዘጋጀት ለመጠበቅ ፣ ለማከራየትና ለማካሄድ» ስለሆነ በዚሁ መሠረት ጥረት እየተደረገ ነው ። በአዲስ አበባ ከተማ ለከፍተኛና መለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሁለት መናኸሪያዎች ከነቢሮአቸው ተሰርተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው ። ከዚህም በተጨማሪ በጅማ ከተማ ለሕዝብና ለጭነት ተሽከርካሪዎች ፣ በጐንደር ከተማ ለጭነት ማመላለሻዎች ፣ በደብረ ማርቆስ ደግሞ ለሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች ዘመናዊ መናኸሪያዎች በመሠራት ላይ ናቸው ።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ከመንገድ ማመላለሻ ተግባር ጋር አብሮ የሚሄድ ጋራዥና የመለዋወጫ ዕቃዎች ጉዳይ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር ። ጋራዦች የሚከፈቱት በንግድ ድርጅትነታቸው ገቢ እንዲያስገኙ እንጂ በአገልግሎት ሰጪነታቸው የትራንስፖርቱን ክፍለ ኢኮኖሚ ያግዛሉ በሚል አልነበረም ። የ1969 የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ መውጣት ግን በዚህም ረገድ መለስተኛ ቢሆንም ለችግሮች መፍትሔ ሊሰጥ ችሏል ። በአንድ በኩል የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን የሹፌሮችና የመካኒኮች ማሠልጠኛ ማዕከል በ1973 በማቋቋምና በማጠናከር ፣ ኩብልሽት በሬት ለተሽከርካሪዎች አስፈላጊውን እንክብካቤ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ እያመቻቸ ከመሆኑም በላይ ፣ በሕዝብም ሆነ በጭነት ማመላለሻ ዘርፍ የተመዘገቡ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በጋራዥና በጥገና ስም እንደፈለጋቸው ሊቆሙ አይችሉም ። ይህም የትራንስፖርቱን ሕገወጥ አጥረት ለመቋቋም መጠነኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በብሔራዊ የመንገድ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን ሥር የተቋቋመው

Digitized by Google

የመለዋወጫ እቃዎች አስመጪና አከፋፋይ
ድርጅት ለሕዝቡም ሆነ ለጭነት ተሽከርካ
ሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የመለዋወጫ እቃዎ
ችን በማስመጣትና በማከፋፈል የተፈጠረ
ውን ችግር በማቃለል ላይ ይገኛል ።

ዛሬ ሀገሪቷ በአለችበት የእድገት ደረጃ
ጋራዦችን ሁሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር
ለማድረግ የማይቻል ቢሆንም፣ቢያንስ የመ
ንግሥት ተሽከርካሪዎችን ጥገና እና እድሳት
በሚመለከት አንዳንድ እርምጃዎች እየተወ
ሰዱ ናቸው። ለምሳሌ ለኢትዮጵያ ተሽከርካ
ሪ መኪናዎች አገልግሎት ድርጅት (አንበሳ)
ሾገሴ ሜዳና ዲያባኮ አጠገብ ከተሠሩት ሁ
ለት ዴፖዎች በተጨማሪ ከፍተኛ 17 ውስጥ
በመሠራት ላይ የሚገኘው የጋራዥ ኮምፕ
ሌክስ ችግሩን የሚቀንስ ለመሆኑ አያጠራ
ጥርም ። እንዲሁም መንግሥት ለችግሩ ከፍ
ተኛ ትኩረት በመስጠቱ አራት የመለስተኛ
ጥገና አገልግሎት የሚሰጡ ጋራዦችና አንድ
ማዕከላዊ ጋራዥ አቋቁሞአል ። ይልቁንም
ከፍተኛ ገምት የሚሰጠውና ችግሩንም ከ
ሞላ ጐደል ለመወጣት ያስችላል ተብሎ የታ
መነበት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች
የጋራዥ ኮምፕሌክስ ሥራ በመጣደፍ ላይ
ሲሆን የሚገኘውም ቢቃሊቲ አካባቢ (በአ
ቃቂ ከተማ) ነው። በትንሿ አዋሽ ላይም ለከ
ባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች መለስተኛ ጥገና
የሚሰጥ ጋራዥና የሾፌሮች መዝናኛና ማረ
ፊያ ቦታ በመሠራት ላይ ነው ።

የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ማ
ቋቋሚያ አዋጅ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ የመ
ንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ስምሪትና
ቁጥጥር አልባ ሆኖ ቆይቶ እንደነበር የሚታ
ወቅ ነው ። በዚህ አዋጅ መውጣት ምክን
ያት ግን የተስተካከለ የስምሪት መርሐ ግብር
ተነድፎ ሁሉም ተሽከርካሪዎች በተመደበ
ላቸው የስምሪት ድልድል መሠረት ኅብረተ
ሰቡን እንዲያገለግሉ ለማድረግ የሚደረገው
ጥረት የሚያበረታታ ነው ። ከስምሪቱ ድል
ድል ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት የቁጥጥር
ጉዳይ ነው ። ማናቸውም የሕዝብም ሆነ የጭ
ነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብሔራዊ የመን
ገድ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን በሚያወጣው
የስምሪት ድልድል መሠረት ኃላፊነቱን እን
ዲወጣ ያላሰለሰ ቁጥጥር ይደረጋል ። ይሁን
እንጂ የሀገሪቱ የእድገት ደረጃ በወሰነው
መሠረት የስምሪት ድልድል በተለያዩ ጊዜ
ያት ችግሮች ያጋጥሙታል ። በተለይ የጭ
ነት ተሽከርካሪዎች የእርሻ ውጤቶች በአ
ንድ ወቅት ስለሚደርሱና የተመረተው ሁሉ
ወዲያውኑ እንዲጓጓዝ የትራንስፖርት ጥያቄ
ስለሚቀርብ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተላኪና
የተመላሽ ጭነት ቅንጅት በተፈለገው መ
ጠን አለመሟላት ከሚያጋጥሙት ችግሮች
መካከል አንዳንዶቹ ናቸው ።

የስምሪትና የዲስፕሊን መመሪያን በሚ
ተላለፉ አስጫኝ ድርጅቶችና ግለሰቦች
ላይ ቅጣት ሲወሰንባቸው አስጫኝ ድርጅ
ቶችም ልዩ ልዩ ምክንያቶችን በማቅረብ የ
ተወሰነባቸውን ቅጣት ለመክፈል ፈቃደኛ
የማይሆኑባቸው በርካታ ሁኔታዎች መፍጠ
ራቸው አልቀረም ። በአፈጻጸም ረገድ በየወ
ቅቱ ለሚከሰቱት ልዩ ልዩ ችግሮች የመፍ
ትሔ ሀሳቦች የሚቀርቡ ቢሆንም በአጠቃ
ላይ በመንገድ ማመላለሻ የተግባር ክንዋኔ
ላይ አሁንም ልዩ ልዩ ድክመቶች መንፀባረ
ቃቸው እውን ነው ።

የትራንስፖርትን ማኅበራዊ ይዞታና አሠራር የበለጠ ለማጠናከር

የትራንስፖርትን ማኅበራዊ ይዞታና አሠ
ራር በበለጠ ለማጠናከር ያለው መሠረታዊ
መፍትሔ ከምንከተለው የእድገት አቅጣጫ
አንፃር ግልጽ ሆኖ የሚታይ ነው ። በአንድ
ማዕከላዊ ፕላን ሥር የሚደራጀው የሶሻሊ
ስት ኤኮኖሚ ለዚህ መሠረታዊ ችግር መፍ
ትሔ ይሰጣል ። ዛሬ ከጅምሩ በግልጽ እን
ደሚታየው የመንግሥትና የኅብረት ሥራ
ማኅበራት ፣ የሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶች
መጠናከር ለአጠቃላይ ማኅበራዊ እንቅስ
ቃሴ ወሳኝ ሥፍራ ያላቸውን ያህል የትራን
ስፖርትን ማኅበራዊ ይዞታና አሠራር በበ
ለጠ ለማጠናከር ሚናቸው ከፍተኛ ነው ።

Digitized by Google

በኢትዮጵያ የኤኮኖሚ ፖሊሲና በኢሠፓ ፕሮግራም በግልጽ እንደተቀመጠው በተያያዘነው የግንባታ ምዕራፍ የትራንስፖርትን ክፍለ ኤኮኖሚ ካለበት ዝቅተኛ የእድገት ደረጃና ከአበይት ችግሮቹ በመጠኑም ቢሆን ለማላቀቅ የመንግሥትን ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶችንና የባለ ግል ንብረቶችን ተሳትፎና ትብብር ይጠይቃል ። ይሁንና ለዘለቄታው ሶሻሊዝምን ለመገንባት በዚህ ክፍለ ኤኮኖሚ የመንግሥትንና የሕዝብ ይዞታን ከፍ ማድረግና ቀስ በቀስም የግል ይዞታን በሕዝባዊ ይዞታ መተካት አስፈላጊ ነው ። ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ባለፉት ዓመታት የመንግሥት ይዞታን ለማሳደግ ፣ የኅብረተሰቡን የትራንስፖርት ፍላጐት ለማርካትና የማኅበራዊ ይዞታን ለማሳደግ የሚረዱ እርምጃዎች ተወስደዋል ። በአሁኑ ወቅት በመንገድ ትራንስፖርት የመንግሥት ይዞታ በሕዝብ ማመላለሻና በጭነት 25% ሲሆን በሚቀጥሉት ዓመታት እነዚህ አሀዞች ከፍ እንደሚሉ ይታመናል ።

የትፉንስፖርት አገልግሎት አደረጃጀትንና አስተዳደርን ሕዝባዊ ለማረግ ልዩ ልዩ እርምጃዎች ተወስደዋል ። የብሔራዊ የመንገድ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን በአዋጅ መቋቋም የትራንስፖርት አገልግሎት አደረጃጀትና አስተዳደር ማሻሻልና የአሠራሩን ህዝባዊ ባህሪ ለማጠናከር የተወሰነ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የትራንስፖርትን (የመንገድና የምድ ባቡርን ጭምር) አገልግሎት ፣ አደረጃጀትና አስተዳደር ሕዝባዊ ለማድረግ በዚህ መስክ የተሰማራው የሠራተኛው ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ ንቃቱንና የሙያ ችሎታውን ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ነው ። በትራንስፖርት ክፍለ ኤኮኖሚ የተሰማራው ሠርቶአደር በትራንስፖርት አገልግሎት አደረጃጀትና አስተዳደር አንጻር ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲኖረው በአስተዳደር፣በስምሪትና በበጀት ዝግጅት ፣ በእቅድ አወጣጥና በአፈጻጸም ወዘተ...መስኮች ልምምዱን ደረጃ በደረጃ እያሳደገ ነው ። አልፍ አልፍ የመደብ ባህርያቸው እያየለባቸው ፣ የሠራተኛውን መደብ ሕልውና ውስጥ ውስጡን የሚፈታተኑ ኃይሎች ቢኖሩም በአመዛኙ ሠራተኛው በፖለቲካ ድርጅቱ ፣ በሙያ ማበሩና በሌሎች ሕጋዊ መድረኮች አማካይነት በትራንስፖርት አገልግሎት አደረጃጀትና አስተዳደር አንፃር ተሳትፎውን እንዲያጠናክር ጥረት እየተደረገ ነው ። የአስተዳደሩንና የአጠቃቀሙን ሕዝባዊ ባህርይ ይበልጥ በማጠናከሩ አንፃር ተገልጋዩ ኅብረተሰብ በልዩ ልዩ ማኅበራቱና ድርጅቶቹ አማካይነት ተሳትፎውንና ትብብሩን ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች በመመቻቸት ላይ ናቸው ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

ለማንኛውም ሕዝብ ፣ በተለይም እድገቱን ለማፋጠንና ከብዝበዛ ነፃ የሆነ ኅብረተሰብ ለመገንባት ቆርጦ ለተነሳ ሕዝብ፣ የትራንስፖርት ክፍለ ኤኮኖሚ መስፋፋት ከፍተኛ የእድገት አፋጣኝነት ሚና አለው።ትራንስፖርት ባልተስፋፋበት ሁኔታ ለልዩ ልዩ የኤኮኖሚ አውታሮች ጤናማ አሠራር ወይም እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑትን ጥሬ እቃዎችንና ምርቶችን ወደ ሚፈለጉበት ሥፍራ ለማዘዋወር፣ምርትን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማካሄድና ሕዝቡንም በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ለማዘዋወር አይቻልም ።

በመሆኑም የትራንስፖርት ክፍለ ኤኮኖሚ ለአጠቃላይ የኤኮኖሚ እድገት እንደ ደም ሥር የሚያገለግልና ለተሟላ ማኅበራዊ እድገት አመቺ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ዘርፍ ነው ። ይህንን ሐቅ በመገንዘብ ነው አብዮቱ ለየብስ ትራንስፖርት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የቻለው ።

የትራንስፖርትን ክፍለ ኤኮኖሚ ዘመናዊ ለማድረግና ለማስፋፋት እስካሁን ከተወሰዱት እርምጃዎች በተጨማሪ በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ይህን የኤኮኖሚ ዘርፍ የበለጠ ለማጠናከር ሊሠሩ ከታቀዱት አበይት ተግባራት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል ።

Digitized by Google

1ኛ/ ለዚህ ክፍለ ኤኮኖሚ ማለትም ፣ ለየብስ (መንገድ ፣ ሀዲድ)የባህርና ለአየር ትራንስፖርት መስፋፋት አስፈላጊ የሆኑትን መሠረተ ልማቶች (ኢንፍራስትራክቸሮች)ማጠናከርና መዘርጋት ፤

2ኛ/ የትራንስፖርት አገልግሎት አስተማማኝና በተሟላ ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችሉ ሌሎች ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፤

3ኛ/ እንደአስፈላጊነቱ ክፍለ ኤኮኖሚውንበዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማጠናከርና በማስፋፋት የውጭምንዛሪን ለማዳንና ለማፍራት ጥረት ማድረግ ፤

4ኛ/ የትራንስፖርት ማኀበራዊ ይዘታንና አሠራርን የበለጠማጠናከርና የሚሰጠውን አገልግሎት የተሟላ ማድረግ ፤

5ኛ/ በክፍለ ኤኮኖሚ የግል ይዞታን ቀስበቀስ በመንግሥትና በሕዝባዊ ይዞታ መተካት ፤በአሁኑም ወቅት በግል ይዞታላይ የላቀና የተቀነባበረ ቁጥጥር ማድረግ ፤

6ኛ/ የአስተዳደሩን አወቃቀርና አመራር የበለጠውጤታማና ሕዝባዊ ማድረግ ፤

7ኛ/ ዝርክርክነትን፣ ብኩንነትን ፣ ቀልጌነትን ፣ወዘተ... ማስወገድና በእቅድ መሥራትን ማጠናከር ።

እነኚህንና የመሳሰሉትን ተግባራት በእቅድ በማከናወን ዛሬ በሀገሪቷ ውስጥ የሚታዩትን የየብስና እንዲሁም በአጠቃላይ የትራንስፖርት ችግሮች ደረጃ በደረጃ በመፍታት የአዲሱን ኅብረተሰብ ግንባታ በአስተማማኝ ለማራመድ ይቻላል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. ትራንስፖርትና መገናኛ ለፓርቲ ምሥረታና ለ10ኛው ዓመት የአብዮት በዓል በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የተዘጋጀ ልዩ እትም ፣ መስከረም 1977 ገጽ 18 ።
2. ከላይ የተጠቀሰው ፤
3. ከላይ የተጠቀሰው ፤
4. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ክፍለ ኢኮኖሚ የ1975 የበጀት ዓመት የሥራ ክንውን ግምገማና የ1976 የበጀት ዓመት 1976 ፣ ገጽ 26
5. የመንገድ ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ኅዳር 1969 ፣ ገጽ 5
6. የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መመሪያ 1969 ፣ ገጽ 11 ።

Digitized by Google

አንድ የዓለም ቋንቋ እንዴት ይፈጠራል?

ኃይሉ አርአያ

ቋንቋ ሰዎች ሐሳባቸውን የሚገልጹበትና እርስ በርሳቸው የሚግባቡበት መግሪያ ነው። ቋንቋ መሠረቱ ትርጉም ያለው የድምፅ ቅንብር ሲሆን ፣ የቅንብሩ ትርጉም የሚወሰነው በማኅበራዊ የዕድገት ሂደት ነው። ድምጾቹ በምልክቶች ሲወከሉ ቋንቋው የሚጻፍ ወይም ፊደል ያለው ነው እንላለን።

ቋንቋ የተፈጥሮ ግንዛቤ ነጸብራቅ ነው። በዚህ ግንዛቤ መሠረት ረቂቅ ጽንሰሐሳብ የሚቀረጸው ፣ ቁሳዊ ሕልውና የሚኖረውና ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችለው በቋንቋ አማካይነት ነው። ቋንቋ ለሰው የውስጥ ስሜቱ መግለጫና የዕለት ተዕለት ኑሮው ማከናወኛ መሣሪያ ከመሆኑም በላይ ባህሉን ፣ ታሪኩን ፣ ክንዋኔውን ፣ የዕውቀቱንና የልምድ ክምችቱን ፣ በአጠቃላይ ማንነቱንና ምንነቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍበት መሣሪያ ነው።

ቋንቋ መጀመሪያ በሰው የተፈጠረ ቢሆንም ተመልሶ ሰውን ይፈጥራል። ኅብረተሰብ የአባላቱን አስተሳሰብ የሚቀርጸውና በአማኅበር (ሶሻላይዜሽን) ሂደት ውስጥ የሚመራቸው በቋንቋ አማካይነት ነው።

እያንዳንዱ ግለሰብም ሕልውናውን ከአካባቢው ጋር አገናዝቦ እሱነቱን የሚገልጸው በቋንቋ አማካይነት ነው። ግለሰቡና ቋንቋው በጥብቅ የተሳሰሩ ስለሆኑ ለቋንቋው የሚሰጠው ማኅበራዊ አመለካከት ለተናጋሪው ከሚሰጠው ማኅበራዊ አመለካከት ተነጥሎ ሊታይ አይችልም።

ቋንቋ በማኅበር የመኖርና በጋራ የመሥራት ውጤት ነው። የሰው ልጅ በረጅሙ የአዝጋሚ ሂደት ታሪኩ በተለይ በመነሻው ክፍል የነበረው ተጨባጭ ሁኔታ የተቀነባበረ የቋንቋ መኖርን አልጠየቀም። ቀስ በቀስ አካላዊና ሕሊናዊ ባህሪያቱ ከማኅበራዊ ሥራ ጋር በተጣመረ ሁኔታ እያደጉ መጡ። ማኅበራዊ ሕይወቱም እየተጠናከረና ለኅብረተሰቡም ሆነ ለግለሰቡ ሕልውና መረጋገጥ የሚያስገኘው ጥቅም ጉልህ እየ

Digitized by Google

ሆን መጣ ። በማኅበር መኖር ፣ በጋራ መሥራትና ማምረት ፣ መግባባትንና የአሠራር ቅንብርን ይጠይቃል ። ቋንቋም የነዚህ ግፊት ውጤት ነው ።

የተቀነባበረ የሰው ንግግር (*Articulated human Speech*) ሊዳብር የቻለው በሥራ ሂደት ነው።የተቀነባበረ የሰው ንግግር ከመፈጠሩ በፊት ሰዎች በሥራ ሂደት በጫጫታና ጩኸት ሐሳብ ይለዋወጡ ነበር ። ከጊዜ በኋላ ጫጫታና ጩኸቱ በሰውነት አካል ክፍሎች በጉሮሮ ላይ ጭምር ለውጥን ፈጠሩ። ጉሮሮም ቀስ በቀስ ለተቀነባበረ ንግግር መፈጠር ምቹ ሆነ። የተቀነባበረው ንግግርም የሐሳብ መለዋወጫ ቋንቋ (መግሪያ) ሆነ ። ቋንቋ ሰዎችን በሥራ ሂደትም ሆነ ከዚያ ውጭ የሚያገናኝ መግሪያ ለመሆን በቃ ።

እያንዳንዱ ቋንቋ ለተናጋሪው ማኅበረሰብ የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥ መግሪያ ነው ። ቋንቋዎች ሁሉ ሊያሉበት ኅብረተሰብ የሚመጥን አገልግሎት የሚሰጡ እስከሆኑ ድረስ በባሕርያቸው ተመሳሳይ ናቸው። ቋንቋዎች ሁሉ የተሟላ ሰጥሰው አላቸው ። ሆኖም ኅብረተሰቦች በዕድገት ደረጃ ስለሚለያዩ ይህ ልዩነት ከቋንቋ አንጻር የሚንጸባረቀው በያንዳንዱ ቋንቋ የቃላት ብዛትና ጥልቅ ጽንሰሐሳብ የመግለጽ ችሎታ ነው።

በቋንቋ መግባባት የሥራ ቅንብርንና የዓላማ መሳካትን ያስከትላል ። በቋንቋ የሚጠቀሙና የሚግባቡ ሰዎች ተፈጥሮን ለመቆጣጠርና መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት አመች ሁኔታ አላቸው ። ፍላጎታቸውን ለማርካት በመቻላቸው ደግሞ ለአካላቸውና ለአዕምሮአቸው መዳበር እንዲሁም ለሕልውናቸው መረጋገጥ አመች ሁኔታ ይፈጥራል ። ስታሊን እንዳለው የሐሳብ ልውውጥ የማይቋረጥ ወሳኝ ሂደት ነው ። ያለሐሳብ ልውውጥ ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርጉትን የጋራ ትግል ለማቀነባበር ያዳግታል።ያለሐሳብ ልውውጥ ኅብረተሰብ ለሕልውናው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊ እሴቶችን ለማምረት የሚያደርገው ጥረት መሳካቱን ለማረጋገጥ አይቻልም ። ያለሐሳብ ልውውጥ ማኅበራዊ ምርት ለማካሄድ አይቻልም ። ከዚህም የተነሣ አንድ ኅብረተሰብ አባላቱ ሁሉ የሚያውቁትና የተቀበሉት የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ከሌለው ማምረት ያቆማል።ከዚያም ተፍረክርኮ ኅብረተሰብ መሆኑ ያከትማል ማለት ነው ።[1]

የሰው ልጅ በተፈጥሮ ግፊት መሥራትን ሲማር መሥራት ደግሞ በተራው በሰውነቱ ክፍሎች ቅርጽና ተግባር ላይ ለውጥን እያስከተለ መጣ ። የሰው ልጅ ቀደምት ዝርያዎች የሚንቀሳቀሱት ዛሬ በዝንጀሮና ፀጦጣ እንደምናየው በአራት እግራቸው እንደነበሩ ታሪክ ይመሰክራል ። የዛፍ ላይ ኑሮን በመተው በሜዳ መሬት ላይ መኖር ሲያዘወትሩና የመሥራት ምልክትም እያሳዩ ሲሄዱ ቀደም ሲል ለመንቀሳቀሻ ያገለግሏቸው የነበሩ ሁለት የፊት እግሮች ቀስበቀስ ወደ እጅነት እየተለወጡ መጡ። በኋላ እግሮቻቸው ተደላድለው እየቆሙ የያኔ የፊት እግሮች የአሁን እጆች የመሥራት ችሎታቸው እያደገ መጣ ። የእግሮችም ሆኑ የእጅ አጥንቶችና ጡንቻዎችም ለሚያከናውኑት ተግባር በሚስማማ ሁኔታ እየዳበሩ (እየሰለጠኑ) መጡ ።

ማወቅ፣በማኅበር መሥራትና በቋንቋ መጠቀም መጀመር ለውጥ ያስከተሉት በእጅና በእግር ተፈጥሮ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የሰው አካል ክፍሎች ላይ ነው።ለምሳሌ ቋንቋን የሚመለከቱ ዋና ዋና ክፍሎችን ብቻ እንመልከት ።

የቋንቋ ድምጽ ሲፈጠር የሚሳተፉ የሰውነት ክፍሎች ከንፈር፣ ጥርስ፣ የውስጥ ድድ ፣ ምላስ ፣ ትናጋ ፣ የአፍ በዓት፣ የአፍንጫ በዓት ፣ ጉሮሮ ፣ ሥረድምጽ (ቮካል ኮርድ) እንዲሁም ሳምባ ናቸው ። እነዚህ የሰውነት ክፍሎች መጀመሪያ ሲፈጠሩ ከቋንቋ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አልነበራቸውም። ማለትም የሰው ልጅ በቋንቋ ለመጠቀም እንዲያስችሉት ተብለው አይደለም የተፈጠሩት። አፈጣጠራቸው ከምግብ አጠ

Digitized by Google

ታቀምና ከሌሎች መሠረታዊ የሕልውና
(ሰርቫይቫል)ተግባራት ጋር በተያያዘ ሁኔታ
ነው ። ቀስበቀስ ግን የሰው ልጅ በሕልው
ና ትግል አስገዳጅነት በቋንቋ መጠቀም ሲጀ
ምር እነዚህ የሰውነት ክፍሎች መሠረታዊ
የሕልውና ተግባራትን እያከናወኑ በተጨ
ማሪ ቋንቋ የመቅረጽ ሥራንም ማከናወን ጀ
መሩ።ለምሳሌ ምላስ ከመሠረታዊ ሥራዎቹ
አንዱ አፍ ውስጥ የገባን ምግብ በጥርስ ወ
ፍጮ በሚገባ እንዲፈጭ ኢየገላበጠ ማከ
ፋፈልና ሲደቅ እንዲዋጥ ለጉሮሮ ማቀ
በል ነው ። በቋንቋ የመጠቀም ተግባር ሲ
መጣ ደግሞ ወደ ጥርስና ወደ ውስጥ ድድ
እየተወነጨፈ ፣ ጭብጥ ዘርጋ በማለት ከት
ናጋ ጋር እየተገናኘ የተለያዩ ድምጾች እንዲ
ፈጠሩ ይረዳል ። ሌሎችም ክፍሎች እንደ
ዚሁ በቀድሞ ሥራቸው ላይ ተጨማሪ አዲስ
ሞያ አፍርተዋል ። ሳምባ ከሥር አየር ሲስ
ብና እየመጠነ ሲገፋ ሥረድምጽ (ቮካል
ኮርድ) ሲርገበገብ ጉሮሮ አጠር ረዘም፣ ጠበ
ብ ሰፋ እያለ የሰው ልጅ የተለያየ ትርጉም
ያላቸውን ድምጾች ለመፍጠር ያስችሉታል።
እነዚህ የሰውነት ክፍሎች በዚህ ድምጽ የመ
ፍጠር ተግባር ይበልጥ በቀጠሉ መጠን
የውስጥ ተፈጥሮአቸውም ለዚሁ ተግባራ
ቸው በሚስማማ ሁኔታ እየተደራጀና እየ
ሰለጠነ ይሄዳል ።

በኅብረተሰብ ውስጥ የሚወለድ ሕፃ
ንም እነዚህን የሠለጠኑ የድምጽ መፍ
ጠሪያ የሰውነት ክፍሎች ስላሉት ውስ
ጣዊ የመናገር ችሎታን ይዞ ይወለዳል።
ሆኖም ይህ ውስጣዊ ችሎታ ሕጻኑ ከማኅበ
ራዊ አካባቢው ጋር በሚኖረው መስተጋብራ
ዊ ግንኙነት በቋንቋ ግብአት (ኢንፑት) ካል
ተቀሰቀሰ በስተቀር ለንግግር አያበቃውም ።
ተዳፍኖ ይቀራል ። ይህም ማለት አንድ ሕ
ጻን በአካባቢው ቋንቋን ካልሰማና ካላየ (የቋ
ንቋ ግብአት ካላገኘ) ውስጣዊ የመናገር ች
ሎታ ይዞ ቢወለድም ሊናገር አይችልም ማ
ለት ነው ። እዚህ ላይ ሕጻናት ከመጀመሪያ
ጀምሮ ለቋንቋ መጋለጥ ወይም አለመጋለጥ
ወይም የመጋለጣቸው መጠን በኋላ በቋንቋ
ችሎታው ላይ ወሳኝ የሆነ ተጽዕና እንደሚ
ኖረው ለማየት አያዳግትም ።

በዓለም ላይ የነበሩ ሰው መሰል ዝርያዎች
ከምድር ገጽ እንዲጠፉ ካደረጓቸው ምክን
ያቶች አንዱ አካላዊና ሕሊናዊ ዕድገታቸው
ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር አብሮ አለመሔድና
በዚህም ምክንያት ቋንቋ መፍጠር አለመቻ
ላቸው ፣ በቋንቋ በመጠቀም መሠረታዊ ፍላ
ጐታቸውን በሚገባ ለማሟላት አለመቻላ
ቸው ፣ ደግሞ መልሶ በአካላዊና በአዕምሮ
ኣዊ ዕድገታቸው ላይ ተጽዕኖ በማሳደሩ መ
ሆኑ ይታመናል ።

ቋንቋ ሁለት ዓይነት ነው ። አንደኛው
የተፈጥሮ ቋንቋ ሲሆን ፣ ሁለተኛው ሰው
ሠራሽ (አርትፍሻል)ነው ። የተፈጥሮ ቋንቋ
በኅብረተሰብ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ፣
ማኅበራዊና ባህላዊ ሕይወት ላይ ተመስ
ርቶ ለብዙ ሺህ ዘመናት የዳበረ ፣ የሕዝቡ
ሁለንታዊ ባህሪ ነጸብራቅና የዕለት ተዕለት
ኑሮው ማካሔጃ መሣሪያ ነው ። የተፈጥሮ
ቋንቋ የተናጋሪዎቹን ባሕርያት የሚያንጸባ
ርቅ በመሆኑ አንድን ሕዝብ ከሌላው ለመለ
የት የምንጠቀምበት ዓይነተኛ መሣሪያ
ነው።ሰው ሰራሽ ቋንቋ የረጅም ታሪክ ሂደትና
የአንድ ማኅበረሰብ የጋራ መግባቢያ ውጤ
ት ሳይሆን በአንድ ሰው ወይም በአንድ ቡ
ድን ለተወሰነ አገልግሎት በአጭር ጊዜ
ውስጥ የሚፈጠር ነው ። በአንድ ኅብረተ
ሰብ ሕይወት ውስጥ ሥር የሰደደና ዕድገ
ቱም ከኅብረተሰቡ ዕድገት ጋር የተያያዘ
አይደለም ። በመሠረቱ ሁለቱም ዓይነት
ቋንቋዎች ሰው የፈጠራቸው ናቸው ። ልዩ
ነቱ አንዱ ከኅብረተሰቡ ጋር እያደገ የመጣ
የታሪክ ሂደትና የጠቅላላው ኅብረተሰብ
ስምምነት ውጤት ሲሆን ሌላው በአንድ
ሰው ወይም ቡድን ሜካኒካዊ በሆነ መን
ገድ ለአንድ የተወሰነ ዓላማ በአጭር ጊዜ
ውስጥ የተፈጠረ መሆኑ ነው ።

ሰው ሠራሽ ቋንቋ እንደገና በሁለት ሊከ
ፈል ይችላል ። አንደኛው በጣም ጠባብና
ለአንድ የተወሰነ ጉዳይ ወይም መስክ የሚ
ፈጠር ነው ። ለምሳሌ የሂሳብ መስክ ለስ
ሌት ተግባር የሚረዱ ምልክቶች ያሉት የ
ራሱ የሆነ ቋንቋ አለው። የሬዲዮ መገናኛም
በነጥብና በሰረዝ ላይ የተመሠረተ ውሱን
ቋንቋ አለው ። ቦይ ስካውቶችና መርከበ
ኞች በቁራጭ እንጨት ላይ የታሠረ ጨርቅ
በማወዛወዝ ወይም መብራት ብልጭ ድር
ግም በማድረግ የሚፈጥሩት የመገናኛ ዘዴ
የውሱን ሰው ሠራሽ ቋንቋ ሌላው ምሳሌ
ነው። ሁለተኛው ዓይነት ሰው ሠራሽ ቋንቋ

Digitized by Google

የተፈጥሮ ቋንቋን በማስመሰል ለዓለም ሕዝቦች መግባቢያ እንዲያገለግል ተብሎ የሚፈጠር ቋንቋ ነው ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ሰው ሠራሽ ቋንቋ ስንል ይህን ዓይነት ማለታችን ነው ።

ሰዎች ሰው ሠራሽ ቋንቋን መፍጠር የጀመሩት ከዛሬ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ዓመታት በፊት ጀምሮ እንደሆነ ይታመናል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ 500 ያህል የዚህ ዓይነት ቋንቋዎች ተፈጥረዋል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተለይም የዚህ ድርጅት አንዱ አካል የሆነው የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት ፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ለዓለም ሕዝቦች መግባቢያ የሚሆን አንድ ሰው ሠራሽ ቋንቋ የመፍጠሩን ጉዳይ እንዲያስብበትና በዚህም አቅጣጫ ተጨባጭ ርምጃዎችን እንዲወስድ ኢያሌ ጥያቄዎች ቀርበዋል ።

ሰው ሠራሽ ቋንቋዎች የዓለም ሕዝቦች በአንድ ቋንቋ እንዲናገሩና የበለጠ እንዲግባቡ ከማድረግ ምኞት የመነጩ ሙከራዎች ናቸው ። የሰው ሠራሽ ቋንቋ ፈጠራ ከዛሬ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ዓመት በፊት የተሞከረ ቢሆንም ለጊዜው በጥንታዊነቱ ለመጥቀስ የሚቻለው በአሥራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ቅድስት ሂልደጋርድ በተባለችውና በምሁርነቷ በታወቀችው አንዲት የገዳም እመምኔት የተፈጠረውንና «ሊንገዋ ኢግኖታ» የተባለውን ነው ። እ-ኤ-አ- በ1629 የፈረንሣዩ ፈላስፋ ዴካርት ለአንድ የታወቀ የገዳም መሪ በጻፈው ደብዳቤ ለመፍጠር ስለአሰበው ቋንቋ አብራርቶ ጽፏል ። ላይብኒትዝ የተባለው የጀርመን ፈላስፋ «የሃሳብ አልጀብራ» የሚሆን ቋንቋ ለመፍጠር ሞክሯል ። በ1880 ጂ- ሽለየር የተባለ ጀርመናዊ «ቮላፕዩክ» የተባለውን ፣ በ1887 ጉስታብ ዛመንሆፍ (በብዕር ስሙ ዶክተር ኤስፔራንቶ የተባለና በሞያው የዓይን ሐኪም የነበረ የፖላንድ ዜጋ) «ኤስፔራንቶ» የተባለውን ፣ በ1903 ደግሞ ፒና የተባለ ኢጣሊያዊ ከሌሎች ምሁራን ጋር በመሆን « ኢንተርሊንገዋ » የተባለውን ቋንቋ ፈጥረዋል ። እንዲሁም በ1922 ኢ. ደ.ዎል የተባለ ኤስቶኒያዊ «ኦክሲደንታል» የተባለውን ፣ በ1928 ኦቶ የስፐርሰን የተባለው ዴንማርካዊ «ኖቪያል» የተባሉትን ቋንቋዎች ፈጥረዋል ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው እስከአሁን ድረስ ከተፈጠሩት 500 ያህል ቋንቋዎች ይበልጥ ተቀባይነትን አግኝቶ ሊስፋፋ ችሎ የነበረና አሁንም ቢሆን በመጠኑ በመነገር ላይ ያለ ኤስፔራንቶ ብቻ ይመስላል ። ይህ ቋንቋ የዛሬ ሐያ ዓመት ስምንት ሚሊዮን ያህል ተናጋሪዎች እንደነበሩት ታውቋል ። ዛሬ ግን ተናጋሪዎቹ አንድ ሚሊዮን ያህል እንደሆኑ ይገመታል ።

ሰዎች ሰው ሠራሽ ቋንቋ ሲፈጥሩ ትልቁ ጥረታቸው ቋንቋውን በተቻለ መጠን የወገናዊነት ባህሪ የሌለበትና ፍጹም ሥርዓታዊ ማለትም ሰዋስዋዊ ሕግጋቱ የተጠበቁና «ኤክስፐሽን» የሌለባቸው እንዲሆኑ ለማድረግ ነበር ። ማንኛውም የተፈጥሮ ቋንቋ ይብዛ ይነስ እንጂ በአነባበብ ፣ በቃላት አፈጣጠር ፣ በሰዋስዋዊ አገባብ ኢሥርዓታዊነት አለበት ። ይህንም ሁኔታ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የተለየ ሌላ ቋንቋ ለመማር የሞከሩ ሰዎች ሁሉ በሚገባ ያውቁታል ።

የኤስፔራንቶ ቃላት ከዋና ዋናዎቹ የአውሮፓ ቋንቋዎች የተውጣጡ ግን መልካቸውን ለወጥ አድርገው የቀረቡ ናቸው።የልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ባህሪያት ማመልከቻ የሆኑ ቅጥያዎችም ከእነዚሁ ቋንቋዎች የተወሰዱ ሲሆኑ አልፎ አልፎ የፈጠራ ውጤቶችም አሉባቸው ። የቅጥያዎቹ አገባብ ግን ፍጹም ሥርዓታዊ ነው ። የኤስፔራንቶ ሰዋስው ጠቅላላ ሕጎች አሥራ ስድስት ብቻ ሲሆኑ ምንም ሕገወጥነት (ኤክስፐሽን) የለባቸውም ። ሥርዓተ ድምጹም ፍጹም ሥርዓታዊ ነው ። እንደሚጻፍ ይነበባል ። እንደ እንደሚነበብ ይጻፋል ። መመሪያው ሁል ጊዜ «አንድ ምልክት አንድ ድምጽ»ነው።

ኤስፔራንቶ ፍጹም ሥርዓታዊ ከመሆኑ የተነሳ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመማር እንደሚቻል ታውቋል ። በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተደረጉ የተለያዩ ሙከራዎች ኤስፔራንቶን ለመማር የሚወስደው ጊዜ መደበኛ ቋንቋን ለመማር ከሚወስደው ጊዜ አንድ አምስተኛ እንደሆነ አሳይተዋል ። በአጠቃላይ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ አስተሳሰቦች ኤስፔራንቶ ከተፈጥሮ ቋንቋ ከ5—15 ጊዜ እንደሚቀልና ለመማርም የሚወስደው ጊዜ የዚያኑ ያህል እንደሚቀንስ

Digitized by Google

ይጠቀማሉ ። የኤስፔራንቶ ቋንቋን ባሕሪ በማየት የሰው ልጅ ከብዙ ሙከራዎች በኋላ ፍጹም ሥርዓታዊ የሆነ ቋንቋ የመፍጠር ጥረቱ ከሞላ ጎደል ተሳክቶለታል ለማለት ይቻላል። ሆኖም ሰው ሠራሽ ቋንቋዎች በአጠቃላይ የታሰበውን ያህል አልተስፋፉም። ለምን ? ቢያንስ ሶስት ዋና ምክንያቶች አሉ።

አንደኛው ምክንያት የሰው ሠራሽ ቋንቋዎች ሕያውነት ማጣት ነው ። እያንዳንዱ የተፈጥሮ ቋንቋ እንደዛፍ ሥሩን በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰድዶ ከታሪኩ ፣ ከባህሉ ፣ ከልዩ እምነቶቹ ፣ ከሕዝቡ ቅንብር፣በውስጡ ከተካሔዱት ትግሎች ፣ ወዘተ . . . እየተመገበ ከሕዝቡ ጋር አብሮ ያደገ ሕያው መግሪያ ነው ። የሕዝቡ እሱነት አንዱ መገለጫ ቋንቋው ነው ። እያንዳንዱ ሰው ሠራሽ ቋንቋ እነዚህ ባህሪያት የሉትም ። «የእኔ ነው » የሚለውና የሚንከባከበው ተፈጥሮዊ ወገን የለውም ። የተዘጋጀው መካኒካዊ በሆነ መንገድ ነው ። መካኒካዊነቱ የረቀቀ ቢሆንም ሕያውነት ሊያስገኝለት አልቻለም፣

ሁለተኛው ምክንያት ሰው ሠራሽ ቋንቋዎች ብዙ የቋንቋ ተናጋሪዎችን የማያረካ የከፊል ወገናዊነት ጠባይ ነው ። ለምሳሌ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ኤስፔራንቶ ቃላቱን ያጠናቀረው ከዋናዎቹ የአውሮፓ ቋንቋዎች ነው ። ከየቋንቋው የተወሰዱ ቃላት ቍጥራቸው የተወሰኑ ከመሆናቸውም በላይ አዲሱ ቋንቋ ውስጥ ሲገቡ ለሥርዓታዊነት ሲባል መልካቸውን ይለውጣሉ።እያንዳንዱ ቃል ከየት እንደመጣ መገመት የሚያስችል መልክ ይኖረው ይሆናል ። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ የናት ቋንቋው መልክ የለውም ። ስለዚህ የቋንቋው ወገናዊነት አስተዋጽኦ ከአደረጉለት ቋንቋዎች ለማንኛቸውም አጥጋቢ የወገናዊነት ስሜት አይሰጥም ። ይህ ደግሞ ከመጀመሪያው ምክንያት ጋር የተያያዘውን በአያሌ ሕዝቦች ዘንድ «የእኔ ነው » ባይነትን ያሰጣል ።

ይኸው የአስተዋጽኦ አድራጊ ቋንቋዎች ባለቤቶችን ያላረካ ከፊል ወገናዊነት ቋንቋቸው ያልተወከለላቸው ሌሎች ሕዝቦችን ያስኮርፋል ። በዓለም ላይ ስንት ቋንቋዎች እንዳሉ በእርግጥ አይታወቅም ። ነገር ግን የፈረንሳይ አካዳሚ በአዘጋጀው ዝርዝር መሠረት 2790 ያህል ቋንቋዎች መኖራቸውን ያመለክታል።[2]ይህን ቁጥር እንደመነሻ አድርገን ብንወስድ ኤስፔራንቶየተውጣጣው ካውሮፓ ዋና ዋና ቋንቋዎች በተለይም ከላቲን ነው።የሌሎችም ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ኤስፔራንቶን የሚመለከቱት እንደ ባዕድ ቋንቋ ነው ማለት ነው ። አሁን ካሉት ዓለም አቀፍ ነባራዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎች አንጻር የዓለም ሕዝቦች አንድን ቋንቋ በመግሪያነቱ ለዓለም ሕዝቦች መግባባት ከሚሰጠው ጥቅም አኳያ ብቻ በማየት ሊቀበሉ በሚችሉበት የንቃተሕሊና ደረጃ ላይ አይደሉም ።

ሶስተኛው ምክንያት ሰው ሠራሽ ቋንቋዎች ከተፈጥሮ ቋንቋዎች ጋር ሊወዳደሩ አለመቻላቸው ነው። የዓለም ሕዝቦች አንድ የመግባቢያ ቋንቋ ቢኖራቸው ይጠቅማል በሚለው ሐሳብ ላይ ምንም ያህል መሊያየት የለም። ችግሩ የሚፈጠረው የማን ቋንቋ ይሁን በሚባልበት ጊዜ ነው ። ከዚህ ጥያቄና ከሚያስከትለው ችግር ለማምለጥ ነበር ወገናዊ ያልሆነ አርትፍሻል ቋንቋ ለመፍጠር የተሞከረው ። ነገር ግን መፍትሔ ተብሎ የታሰበው ኢወገናዊነት ግዳከሚያውም ሆኖ ተገኘ ።

በአንድ በኩል አንድ የዓለም ቋንቋ ለመፍጠር ሲሞከር በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ አገሮች ቋንቋቸው ለዓለም ቋንቋነት አመቺ ሁና እንዲገኝ ወይም ደግሞ በውስጣዊ ባህሪዩና በተናጋሪዎቹም ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ባህሪያት ገፊት ፈንቅሉ ወጥቶ የዓለም ቋንቋ እንዲሆን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።በተለይ እንግሊዝና ፈረንሣይ በአሁኑም ወቅት ቢሆን ለቋንቋቸው መስፋፋትና በዓለም ላይ የበላይነቱን ማግኘት ከፍተኛ ትግል ያካሂዳሉ ። በአሁኑ ጊዜ ፈረንሣዮች «አሊያንስ ፍራንሴዝ» እንግሊዞች ደግሞ « ብሪቲሽ ካውንስል » ተብለው በሚጠሩ ድርጅቶቻቸው አማካይነት በዓለም ታላላቅ ከተሞች የየራሳቸውን

Digitized by Google

ቋንቋ በተሻለ ሊግስተግርና ባህላቸውንም እግረመንገዱን ለማሰራጨት የሚያደርጉት ጥረት በግልጽ የሚታይ ነው ። ሰው ሠራሽ ቋንቋዎች በዚህ ትግል ሊወዳደሩ አልቻሉም።የኢኮኖሚው አቅምም ሆነ የማኅበራዊ ኑሮ የላቸውም ።

ሰው ሠራሽ ቋንቋዎች ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት የሌላቸው በመሆናቸው የተፈለገውን ውጤት ሊያስገኙ አልቻሉም ። በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች አንድ ቋንቋ ስለተናገሩ ይግባባሉ ፣ በሰላም ይኖራሉ ፣ አንድነታቸው ይጠነክራል ማለት አይደለም። አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች እርስ በርሳቸው ሲተላለቁ ታሪክ ደጋግሞ አሳይቶናል። ስለዚህ የዓለም ሕዝቦች ተግባብተው በሰላም እንዲኖሩ ከተፈለገ ዋናው ትኩረት ቋንቋ ላይ አይደለም ። የቋንቋ መግባባት ግን አያስፈልግም ማለት አይደለም ። ።

የዓለም ሕዝቦች በአንድ ቋንቋ መናገር ለሕዝቦች የበለጠ ለመግባባት አስተዋጽኦ ያደርጋል። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የዓለም ሕዝቦች በአንድ ቋንቋ ለመናገር የሚችሉበት ሁኔታ የሚፈጠረው እንዴት ነው? የሚለው ነው። ይህ ጥያቄ ደግሞ ሌላ ጥያቄን ያስከትላል።ይኸውም መጀመሪያውኑስ ቢሆን የቋንቋ ልዩነት እንዴት ተፈጠረ ? የሚለው ነው ። ሁለተኛውን ጥያቄ በቅድሚያ መመለስ የመጀመሪያውን ጥያቄ በበለጠ ግንዛቤ ለመመለስ ይረዳናል ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ዛሬ በዓለም ላይ ከ2,500 በላይ የሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎች እንዳሉ ይገመታል። የቋንቋዎች መለያየት ከሰው ዘር አመጣጥና ስርጭት ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው።ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የሰው ዘር አመጣጥንና ስርጭትን በሚመለከት ሁለት አቋሞች አሉ ። እነዚህም «ብዙ ማዕከል» (ፖሊሰንትሪዝም)እና «አንድ ማዕከል» (ሞኖሰንትሪዝም) የሚሉት ናቸው።[3] ብዙ ማዕከል የሚለው አቋም የሰው ዘር በተለያዩና በተራራቁ ብዙ ማዕከሎች ማለትም በአፍሪካ ፣ በእስያና በአውሮፓ አህጉራት ልዩ ልዩ አካባቢዎች በአዝጋሚ ለውጥ ሂደት እያደገ መጥቶ በኋላ ከእነዚህ ማዕከሎች በየአቅጣጫው እንደተሰራጨ የሚያመለክት ነው።አንድ ማዕከል የሚለው አቋቋም ደግሞ የሰው ዘር የመነጨው በአንድ ማዕከል ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ሲሆን አሁን ያለውን ቅርጹን ከያዘ በኋላ በየአቅጣጫው ተበተነ የሚል ነው ። የተባለው አንድ ማዕከል የሜዲትራኒያን አካባቢ ሲሆን በውስጡ የሚገኙት የሰው መፍለቂያ አካባቢዎች ደግሞ ደቡባዊ አውሮፓ ፣ ሰሜናዊና ምዕራባዊ አፍሪካ እንዲሁም ምዕራባዊ እስያ ናቸው።ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሊቃውንት በእነዚህ ሁለት አቋሞች ተከፍለዋል ።

ከላይ ከተመለከቱት ከሁለቱም አቋሞች የምንረዳው የምንጩ ማዕከል አንድም ይሁን ብዙ የተለያዩ ማኅበረሰቦች በተለያዩ አካባቢዎች ተመስርተው እያደጉ መምጣታቸውን ነው። ለምሳሌ በሁለተኛው አቋም ማለትም የሰው ዘር ምንጭ የሜዲትራኒያን ማዕከል ነው በሚለው ቢኬድም እንኳን በዚህ ማዕከል ውስጥ የተለያዩ አካባቢዎች ማለትም የሰሜናዊና ምዕራባዊ አፍሪካ ፣ የደቡባዊ አውሮፓ ፣ እንዲሁም የምዕራባዊ እስያ ክፍሎች እንዳሉት ተጠቅሷል ። እነዚህም አካባቢዎች ሰፋፊ በመሆናቸው በውስጣቸው ንዑሳን አካባቢዎች አሏቸው ።

በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ለአካባቢያቸው ሁኔታ በሚስማማ መሠረት የራሳቸውን ቋንቋዎች ይፈጥራሉ። «የጥንታዊ ኅብረተሰብ ታሪክ የተለያዩ ማኅበረሰቦች ታሪክ በመሆኑ የየአንዳንዱ ማኅበረሰብ ቋንቋ ራሱን ችሎ እያደገ መጣ ። ስለዚህም የየአንዳንዱ ማኅበረሰብ ቋንቋ ከሌላው ማኅበረሰብ ቋንቋ የተለየ ሆነ » ። ይህም የሚሆነው በተጨባጭ ሁኔታዎች ምክንያት ነው ። የአንድን ማኅበረሰብ የሕይወት ስልት የሚወስነው የአካባቢው የተፈጥሮ ሁኔታ ነው ። የአካባቢው የአየር ጠባይ ፣ የመሬቱ ገጽታና (ምድራዊ አቀማመጥ) በውስጡ የሚገኙ የተፈጥሮ ሁኔታዎች በግለሰቦች አካላዊና ሥነልቦናዊ ባህሪያት ላይ ተጽዕኖ ከማሳደ

Digitized by Google

ራቸውም በላይ የማኅበረሰቡን የአደረጃጀት፣ የአመራረት ፣ የምርት መሣሪያ አዘገጃጀት፣ የአመጋገብ ፣ የአለባበስ ፣ የቤት አሠራርና የቤት ውስጥ አኗኗር በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ በአካባቢው የተፈጥሮ ሁኔታ ውስጥ ሕልውናውን ለማረጋገጥ የሚያደርገውን የትግል ስልት ዓይነት ይወስናሉ ። ቋንቋም የእነዚህ የአካባቢ ሁኔታዎች ሁሉ መግንዘቢያ ፣ የዚያ ግንዛቤ ማንጸባረቂያና የመግባቢያ መሣሪያ በመሆኑ የተለያዩ ባህሪያት ባሏቸው አካባቢዎች የሠፈሩ ማኅበረሰቦች የተለያዩ ቋንቋዎችን ፈጥረዋል ።

ስለቋንቋዎች መለያየት መጠነኛ ግንዛቤ እንዳገኘን በማመን ወደ መጀመሪያው ጥያቄአችን ማለትም በዓለም ላይ አንድ የመግባቢያ ቋንቋ ሊኖር የሚችለው እንዴት ነው? ወደሚለው እንመለስ ።

በአሁኑ ጊዜ ለዓለም አንድ ቋንቋ ለማስገኘት የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ ብዙ ዓለምአቀፍ ሂደቶች አሉ።ከእነዚህ ሶስቱና ዋናዎቹ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማደግና መስፋፋት፣የብሔረሰብና ዘር ዘለል ጋብቻዎች እየበረከቱ መሔድና የሶሻሊዝም መስፋፋት ናቸው ። ከእነዚህ መሠረታዊና ዋናው ሂደት ሶስተኛው ነው።

ዛሬ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ በፋብሪካና በኅትመት ውጤቶች አማካይነት ዓለምአቀፍ የቋንቋዎች መስተጋብርና መወራረስ እየተካሄደ ነው ። ለዚህ መወራረስ ያልተጋለጠ ቋንቋ የለም ። በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት ምክንያት የዓለም ሕዝቦች በይበልጥ እየተቀራረቡ ነው ። የዓለም ቋንቋዎች መዛግብተ ቃላት ይዘቶችም ተመሳሳይ እየሆኑ በመሄድ ላይ ናቸው ። ሳይንስና ቴክኖሎጂ ይበልጥ በአደጉና በተስፋፉ ቁጥር የሕዝቦች መቀራረብና የቋንቋቸው መመሳሰል እያደገ ይሔዳል ።

የዓለም ሕዝቦች የተለያየ ቋንቋ በሚናገሩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች፣ጐሣዎችና ከዚያም ባነሰ ደረጃ ባሉ ማኅበረሰቦች ተከፋፍለዋል።ዛሬ በዓለም ላይ የብሔረሰብና የዘር ዘለል ጋብቻዎች በስፋት እየተካሄዱ ናቸው። የኢትዮጵያን ሁኔታ እንደምሳሌ ብንወስድ በጋብቻ ከሌላ ብሔረሰብ ያልተቀላቀለ ብሔረሰብ አይገኝም ። የብሔረሰብ መቀራረብ በቋንቋም መቀራረብ ነው ። የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች በመጋባትም ሆነ ተቀራርቦ በመኖር በቋንቋ እየተመሳሰሉ በመሄድ ላይ ናቸው ። የዚህ ዓይነት ሂደት ብዙ ብሔረሰቦች በአሏቸው ሌሎች አገሮች ሁሉ በሀፋት እየተካሔደ ነው ። ለምሳሌ ከ100 ብሔረሰቦች በላይ በሚገኙባት በሶቪየት ኅብረትም ተመሳሳይ ሂደት አለ ።

> በሶቪዬት ኅብረት ቅልቅል ጋብቻዎች በሚሊዮን ይቆጠራሉ።በአማካይ ግምት ከሀገሪቱ አጠቃላይ ተወላጆች 20% ወላጆቻቸው ከተለያዩ ብሔረሰቦች ናቸው ። ለምሳሌ በዩክሬይን፣በማልዳቪያና በቢሎሩሲያ ይህ ሚዛን 25%፣ በካዛኽስታን ውስጥ በሚገኙ ብዙ አካባቢዎች 33% ፣በአንዳንድ የሉተዊንያ ከተሞች 55% ይሆናል ።[4]

ሌላው ጉልቶ የሚታየው የጋብቻ ሂደት በተለያዩ ዘሮች መካከል የሚካሔደው ነው። እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ዘር አጥኚዎች የዓለምን ሕዝቦች ጥቁር፣ነጭ፣ቢጫ ፣ ወዘተ ብለው ከፋፍለውታል ። በዘር ደረጃም የዓለም ሕዝቦች መመሳሰል በተፋጠነ ሁኔታ እየተካሔደ ነው።ለምሳሌ የጥቁሮችና የነጮች ጋብቻዎች እየበረከቱ መጥተዋል።የሰው ልጅ ዘር ባህሪያት አጥኚዎች እንደሚገምቱት በጋብቻና በሌሎችም ታሪካዊ ሂደቶች ምክንያት ከጥቁር ዘር ጂኖች 30 በመቶ የነጭ ዘር ጂኖች ናቸው ።[5]

ይህ የዘር መመሳሰል ለቋንቋ መመሳሰል አመች ሁኔታን ይፈጥራል ። ወይንም መመሳሰሉን ያስከትላል ። እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ግን የዓለም ሕዝቦች አንድ ቋንቋ ስለተናገሩ ብቻ የዓለም ሰላም እንደማይኖር ሁሉ አንድ ዓይነት ዘር ስለሆኑ ብቻም የዓለም ሰላም እንደማይኖር ነው ። ምክንያቱም አንድ ዓይነት ዘር የሆኑም ሕዝቦች ሲተላለቁ አይተናል ። ከቋንቋና ከዘር አንድነት ብቻ ሰላም አይወለድም ። የዓለም ሰላም የሚወለደው ከሶሻሊዝም ብሎም ከኮሚኒዝም ዕውን መሆን ነው ።

Digitized by Google

የሶሻሊዝም ግንባታ ሂደት የዓለም ጭቁን ሕዝቦችን በትግል የማቀራረብ ሂደት ነው። የዓለም ጭቁን ሕዝቦች የአንድነት እንቅስቃሴ የተጠነሰሰው ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለ በኋላ ተገኘው መደብ ከጭቆናና ከብዝበዛ ነፃ ለመውጣት ትግሉን ከተያያዘበት ጊዜ ጀምሮ ነው። የዓለም ጭቁን ሕዝቦች በጂኦግራፊያዊ አሰፋፈራቸው ፣ በታሪካቸው ፣ በባህላቸው ፣ በንቃተሕሊና ደረጃቸውና በትግል ስልታቸው የተለያዩ ስለነበሩ ትግላቸው በአንድ ጊዜ የተጀመረና በአንድ ወጥነት የተካሔደ አልነበረም ። በብዙ ሁኔታዎች ይለያዩ እንጂ በዓላማቸው ፣ ማለትም ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ ለመውጣትና እኩልነትና ፍትሕ የሰፈነበት ዓለም ለመፍጠር በመፈለጋቸው ያኔም እንደ ዛሬው አንድ ነበሩ።ካርል ማርክስ ይሁ የተበታተነ የጭቁኖች ኃይል ቢሰባሰብና ትክክለኛ አመራር ቢያገኝ ዓለምን እንደሚለውጥ በመገንዘብ ነው « የዓለም ወዛደሮች ተባበሩ » የሚለውን ጥሪ ያስተጋባው ።

በየቦታው ተበታትኖ የጀመረው የጭቁኖች ትግል በአያሌ ኮሚኒስት ፓርቲዎችና በሺ በሚቆጠሩ ካድሬዎች ትግል ተሰባስቦና ተጠናክር በዓለም ላይ አንድ ታላቅ ኃይል እየሆነ መጣ ። ይህ ኃይል በ1871 በፓሪስ ያሳየው የድል ብልጭታ በ1917 የፊውዶ ካፒታልን ጨለማ ሰንጥቆ በሩሲያ ምድር ከዳር እስከዳር አበራ ። ጭቁን ሕዝቦች የመንግሥት ሥልጣን ጨብጠው የመጀመሪያውን ዘላቂ ሶሻሊስት ሥርዓት መሠረቱ ። ከዚያ ወዲህ ፣ በስልሳ ያህል ዓመታት ውስጥ ከሰላሳ የማያንሱ የሶሻሊዝምን ፈለግ የሚከተሉ መንግሥታት ተመስርተዋል ። በእነዚህ አገሮች ውስጥ የሚገኙ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ለዓለም ሕዝቦች መቀራረብና ብሎም ለአንድነት ጽኑ መሠረት ጥለዋል ።

የዓለም ሕዝብን በመጀመሪያ በተጽዕኖ (በቅኝ አገዛዝ ጭምር) አሰባስቦ በኋላ ደግሞ ከፋፋይ ፣ ጨቋኝና በዝባዥ የሆነው ካፒታሊዝም እየተሸነፈና ግዛቱም እየጠበበ ፣ በሙሉ ፈቃደኝነትና በመግባባት መንፈስ በዕውን አሰባሳቢ የሆነው የሶሻሊስት ሥርዓት እየሰፋ የሚሔድ በመሆኑ ከጊዜ በኋላ ካፒታሊዝም ጠፍቶ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በሶሺያሊስት ሥርዓት ታቅፈው ዓለም የሠራተኞች ትሆናለች። የዓለም ሕዝቦች በጋራ ርዕዮተ ዓለም እየተመሩ በምድር ላይ የሰው በሰው መበዝበዝ የሌለበት ፣ ነፃነት፣እኩልነትና ፍትህ የሰፈነበት ሥርዓት መሥርተው ሊጋራ ዓላማ ማለትም ሊጋራ ደኅንነትና ብልጽግና በኅብረት ይታገላሉ ። የሕዝቦች በአንድ ርዕዮተዓለም መመራትና ለጋራ ዓላማ በኅብረት መታገል በመካከላቸው የበለጠ መቀራረብና መመሳሰልን ያስከትላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ቀስ በቀስ በቋንቋም መቀራረብና መመሳሰልን ስለሚያስከትል ለአንድ ዓለም አቀፍ ቋንቋ መወለድ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ።

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፣ የብሔረሰብና የዘር ዘለል ጋብቻዎች እንዲሁም የሶሻሊዝም ርዕዮተዓለም መስፋፋት ሕዝቦችን እንዴት እንደሚያቀራርብና ለአንድ የጋራ ቋንቋ መውጣትም አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥር ሀገራችንን በምሳሌነት በመውሰድ በአጭሩ ለማሳየት ይቻላል ። የዛሬ መቶ ዓመት አካባቢ ኢትዮጵያውያን ብንወስድ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤት የሆነው የምድር፣ የባሕርና የአየር ትራንስፖርት ባልነበረበት ፣ ሬዲዮ፣ቴሌፎንና ቴሌቪዥን ባልታወቀበት ፣ የዘመናዊ ዕውቀት ማስፋፊያ የሆኑት ትምህርት ቤቶች ባልተከፈቱበት ጊዜ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ይካሔድ የነበረው ግንኙነት በጣም ውሱን ነበር ። ብሔረሰቦች እንደ እንቅስቃሴአቸው ፣ አስተሳሰባቸውም በአብዛኛው በአካባቢያቸው የተወሰነ ነበር ።

የብሔረሰቦቹ የዕድገት ደረጃም ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነበር ። በዚህም ምክንያት ከቋንቋዎችም መካከል ይበልጥ በመዳቡሩ ምክንያት ከወሰኑ አልፎ የመስፋፋት አዝማሚያ የያዘና የጎላ የጋራ መግባቢያነት ጠባይ ያሳየ ቋንቋ አልነበረም። እማርኛም ቢሆን በዚያን ጊዜ ግዕዝን እየተካ መጥቶ በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ የሚነገር ጠባብ ቋንቋ ነበር ለማለት ይቻላል ።

እንደዚህ ባለ ሁኔታ በሥራ ምክንያት የተለያዩ ቋንቋዎች ወደሚነገሩባቸው አካባቢዎች የሚዘዋወር ሰው ብዙ ቋንቋዎች ማወቅ

Digitized by Google

ወይም እስተርጓሚ መፈለግ እንደነበረበት ይገመታል ። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በብሔረሰቦች መካከል ያለው ግንኙነት ውስን ስለነበር ለጋራ መግባቢያነት የደረሰ ቋንቋ ለጊዜው ባለመኖሩ ነው ። ለምሳሌ የተለያዩ ብሔረሰቦች የሚኖሩባቸውን አካባቢዎች አቋርጦ የሚሔድ የጥንት ሲራራ ነጋዴ ከሚያጋጥሙት ቋንቋዎች በልውውጥ ጊዜ ሊረዳው የሚችል ያህል ማወቅ እንደነበረበት ይገመታል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ይበልጥ እየተማከለና እየተጠናከረ ከውጭውም ዓለም ግንኙነቱን እያሰፋ በመምጣቱ ለዘመናዊ እስተሳሰቦች በር ተከፈተ ። ቀስ በቀስ የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎት እየተስፋፋ፣ የብሔረሰቦችም ከቦታ ወደቦታ የመዘዋወር ችሎታቸው እያደገ መጣ ። በኅትመት ፣ በሬዲዮ ፣ በቴሌፎን ፣ በቅርቡም በቴሌቪዥን አማካይነት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ይበልጥ እየተቀራረቡና እየተዋወቁ ሲመጡ እንዲሁም ትምህርት ቤቶች ሲስፋፉ ፣ ለጋራ አመለካከት መስፋፋት ፣ ለብሔረሰብ ዘለል ጋብቻና ለአንድነት ስሜት መዳበር ከምንጊዜውም ይበልጥ አመች ሁኔታ እየተፈጠረ መጣ ። በመጨረሻም በየካቲት 1966 የተቀጣጠለው ታላቁ አብዮታችን በረጂም ጊዜ ታሪካቸው እየተቀራረቡና አንድነታቸውን እያጠናከሩ የመጡትን የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች በተራማጅ ርዕዮተዓለምና በጋራ ዓላማ በማስተሳሰር ከምንጊዜውም ወደላቀ የኅብረት ደረጃ አሸጋግሯቸዋል ።

ዛሬ በሀገራችን የሚታየው ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ዕድገት ለሕዝቦች በቋንቋ መቀራረብ አመች ሁኔታ እየፈጠረ ነው ። በአሁን ጊዜ በአንድ በኩል አማርኛ በተጨባጭ የታሪክ ሂደት ምክንያት ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጥ የመዳበር ዕድል በማግኘቱ በተለይ ከአብዮታችን መቀጣጠል ወዲህ የሰፊው ሕዝብ ያለምንም ተጽዕኖና በሙሉ ፈቃደኝነት የጋራ መግባቢያው እያደረገው መጥቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ከአብዮታችን ዋና ዓላማዎች አንዱ የብሔረሰቦችን እኩልነት ማረጋገጥ በመሆኑና የዚህም እኩልነት አንዱ መከሰቻ የቋንቋዎች እኩልነት መረጋገጥ በመሆኑ እኩልነት ዕውን ሆኖ ቋንቋዎች እንዲዳብሩ ጥረት እየተደረገ ነው ። እንደሚታወቀው ዛሬ መሠረተ ትምህርት በ15 ቋንቋዎች በመካሄድ ላይ ነው ። በእነዚህ ቋንቋዎች ልዩ ልዩ የማስተማሪያ መጻሕፍት ተዘጋጅተዋል ። በሰባት ቋንቋዎች የሬዲዮ ፕሮግራም ይሠራጫል ። አዋጆችና ሌሎች አበይት የመንግሥት መግለጫዎች በአያሌ ቋንቋዎች ይሰራጫሉ ። በሶስት ቋንቋዎች ጋዜጦች ይታተማሉ ። በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ በተለያዩ ቋንቋዎች መዝገበ ቃላት በመዘጋጀት ላይ ከመሆናቸውም በላይ ሌሎች የብሔረሰቦች ቋንቋዎችን የሚያዳብሩ ጥናቶችና ዝግጅቶች ይካሄዳሉ ። አካዳሚው በአሥር ዓመት ዕቅዱ የቋንቋዎች ማዳበርያ ፕሮግራም ዘርግቷል ። በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ኢንስቲትዩት የብሔረሰቦች ቋንቋዎችን ለማዳበር የሚረዳ ልዩ የጥናትና ምርምር ፕሮግራም ያካሂዳል ። እነዚህንም ቋንቋዎች ለማዳበር የሚረዱ ጥረቶች ምሳሌዎች ናቸው ።

ቋንቋን በሚመለከት ዛሬ በሀገራችን (እንዲሁም በሌሎች አገሮች) የሚታየው ሂደት ከልሣነ ብዙነት ወደ ልሳነ ክልኤነት (ሁለት ልሣን) የመሰባሰብ ሂደት ነው ። ይህም ማለት ከዚህ በፊት ከተለያዩ ብሔረሰቦች አባላት ጋር ለመግባባት ይብዛም ይነስ የግዴታ ቋንቋቸውን ማወቅ ያስፈልግ ነበር ። ዛሬ ግን አንድ ሰው ከራሱ ቋንቋ ሌላ አማርኛን ካወቀ በአብዛኛው ከብዙ ብሔሰቦች አባላት ጋር ሊግባባ ይችላል ማለት ነው ። ይህ ደግሞ ዛሬ በኢትዮጵያ በየቦታውና በየዕለቱ የሚታይ ሁኔታ ነው ። ያ ቀደም ሲል የተጠቀሰው ሲራራ ነጋዴም ዛሬ ቢኖርና ከራሱ ቋንቋ በተጨማሪ አማርኛ የሚያውቅ ቢሆን የዚያን ጊዜ ማወቅ የነበረበትን ቋንቋዎች የግዴታ ማወቅ አይኖርበትም ። አማርኛ ቋንቋ በማወቁ ከብዙ ብሔረሰቦች አባላት ጋር ያለብዙ ችግር ሊግባባ ይችላል ።

ከልሣነ ብዙነት ወደ ልሣነ ክልኤነት የመሰባሰቡ ሂደት ሲገባበድ የሚከተለው ሂደት ከልሣነ ክልኤነት ወደ ልሣነ አንድነት መጠቃለል ይሆናል። ይህም ማለት

Digitized by Google

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ቀስ በቀስና በማኅበራዊ ሕጎች መሠረት ወደ አንድ ቋንቋ ያመራል ማለት ነው ። የቋንቋዎች መጠቃለልና የቋንቋዎች መዳበር የሚቃረኑ ሂደቶች አይደሉም ። ጎን ለጎን የሚከናወኑና ሊደጋገፉ የሚችሉ ሂደቶች ናቸው ። የቋንቋዎች መዳበር የቋንቋዎች መጠቃለልን አያግደውም ።

በየአንዳንዱ አገር የሚገኙ የተለያዩ ቋንቋዎች ውስብስብ በሆነ ማኅበራዊ ሂደት በየአገሩ ወደ አንድ ቋንቋ የመጠቃለሉ ሂደት ዛሬ በግልጽ ይታያል ። ለምሳሌ በብሪታኒያ በአሜሪካ ፣ በካናዳ ፣ በአውስትራሊያ ፣ በኒውዚላንድ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ቋንቋዎች ወደ እንግሊዝኛ እየተጠቃለሉ ነው። ፈቬየትናም የሃምሳ አራት ብሔረሰቦች ቋንቋዎች አሉ ። ቀስ በቀስ ወደ ክን ቋንቋ እየተሰባሰቡ ነው ። በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ አርባ ሺህ ያህል ሰዎች የሚናገሩት የሶርብ ብሔረሰብ ቋንቋ አለ። ነገር ግን ወደ ጀርመንኛ እየተጠቃለለ ነው ። በሶቪዬት ኅብረት ከመቶ በላይ የብሔረሰብ ቋንቋዎች አሉ ። ነገር ግን የሩሲያ ቋንቋ በሚያስደንቅ ፍጥነት እየተስፋፋ ነው ። በዚህም ታላቅ አገር አሁንም በተፈጥሮ ሂደት የቋንቋዎች ወደ አንድ ቋንቋ መሰባሰብ ሂደት የማይቀር ነው ። በምሥራቅ አፍሪካ የስዋህሊ ቋንቋ እየተስፋፋ በመምጣት ላይ ነው ። የባንቱ ሕዝቦች ቋንቋዎች ወደዚህ ቋንቋ በመጠቃለል ላይ ናቸው ። ለእነዚህ ዓይነት የቋንቋዎች መጠቃለል ሂደት አያሌ ተጨማሪ ምሳሌዎች መዘርዘር ይቻላል ። ይህ የየአገሩ ቋንቋዎች ወደ አንድ ቋንቋ የመሰባሰብ ሂደት የአንድ የዓለም ቋንቋ መፈጠር ሂደት አካል ነው ። በየአገሩ ከቋንቋዎች መጠቃለል ሂደት ጎን ለጎን በዓለምአቀፍ ደረጃም የቋንቋ መቀራረብ ብሎም የመጠቃለል ሂደት እየታየ ነው ። ይህ ሂደት በአሁኑ ወቅት ለምሳሌ በቋንቋዎች መወራረስና በቃላት መመሳሰል እየተከሰተ ነው ።

ወደፊት የሚኖረው አንድ የዓለም ቋንቋ ምን ዓይነት ይሆናል ? አሁን ካሉት ቋንቋዎች አንዱ ነው የዓለም ቋንቋ የሚሆነው ወይስ አሁን ያሉት ቋንቋዎች በመዋሃድ ተመሳስለው የዓለም ቋንቋው ከሁሉም የተውጣጣ ይሆናል ? ወይስ ሌላ አማራጭ ይኖር ይሆን ? በየአንዳንዱ አገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው የቋንቋዎች መሰባሰብ ሂደት እጅግ በጣም ውስብስብ ስለሆነ ከአሁኑ ይህ ይሆናል ብሎ ለመተንበይ አይቻልም ። የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማደግና የሕዝቦች በይበልጥ መቀራረብ ፣ የብሔረሰብና የዘር ዘለል ጋብቻዎች መስፋፋት ፣ ከሁሉም በላይ ግን በሶሻሊስት ርዕዮተዓለም የመመራትና ለጋራ ዓላማ የመታገል እንዲሁም የሌሎች ማኅበራዊ ሁኔታዎች ዲያሌክቲካዊ ሂደት ውጤት እንደሚሆን ግን ግልጽ ነው ። ቋንቋው በወቅቱ ሰዎች ያለአንዳች ማኅበራዊ ተጽዕኖ ፈቃደኝነትና በተጨባጭ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ብቻ መሆን ያለበት ነው ብለው የሚቀበሉት ይሆናል።

ዛሬ በዓለም ላይ የሚታየው ውጥረትና ግጭት ምንጩ በቋንቋ አለመግባባት ላይ ሆን በጥቅምና በዓላማ አለመግባባት ነው። ይህን እውነታ በሶሻሊስትና በካፒታሊስት ጎራዎች ያለውን ሁኔታ በማየት ማረጋገጥ ይቻላል ። የሶሻሊስት አገሮች ሕዝቦች በጥቅም ተግባብተው በጋራ ርዕዮተዓለም እየተመሩ ለጋራ ደኅንነትና ብልጽግና በኅብረት ይታገላሉ ። ይህንንም በማድረጋቸው ለሰላም በዓለም ላይ መስፈን መሠረት ጥለዋል ። ለዓለም ቋንቋም አንድ የመሆን ሂደት አመቺ ሁኔታ ፈጥረዋል ። የካፒታሊስት አገሮች ሕዝቦች ግን ብዙዎቹ በቋንቋ ቢግባቡም በጥቅምና በዓላማ ባለመግባባታቸው የተካረረ የመደብ ትራኔ መድረኮችና የዓለም ሰላም ጠንቅ ሆነዋል ። ከዚህ ሁኔታ በግልጽ እንደሚታየው በዓለም ሕዝቦች ዘንድ መግባባት የሚኖረው ፣ አንድነታቸው የሚጠናከረውና የዓለም ሰላም የሚሰፍነው ፣ የዓለም አንድ ቋንቋም የሚወለደው ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሲስፋፋ ፣ የምርት ኃይሎች ዕድገት የሰውን ልጅ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ሲችልና የሶሻሊዝም ብሎም የኮሚኒዝም ሥርዓት በመላው ዓለም ላይ ሲሰፍን ብቻ ነው ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. J.V. Stalin, *Marxism and the Problem of Linguistics* (Peking: Foreign Languages Press, 1972), p. 21.
2. George Alan Connor and others, *Esperanto: the World Interlanguage* (New York: Sagamore Press Inc., 1959), p. 6.
3. Great Soviet Encyclopaedia, Volume 25, 1976, p. 587.
4. Alexander Gorbovsky, "Coalescence of Nations: What's Next?" *Socialism: Theory and Practice* (Moscow: Novosti Press Agency Publishing House, July 1982), p. 26.
5. *Ibid.*

እርማት

በመስከረም ወር 1977 በወጣው ቅጽ 5 ቁጥር 19 «መስከረም መጽሔት» ቅደም ተከተላቸው የተዛባ ገጾች እንደሚከተለው ታርመዋል ።

የቀድሞ ገጽ 31 32

» » 32 33

» » 33 .... 31 ተብለው ይነበቡ ።

Digitized by Google

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

መስከረም

HOOVER
OCT 31 1985
INSTITUTION

- የሠራተኛ መደብ ዕድገት በአፍሪካ
- በሽግግር ወቅት የሕግ ሚና
- ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚደረገው ትግል

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 5 ቁጥር 21
መጋቢት 1977

Digitized by Google

ቅጽ 5 ቁጥር 21
መጋቢት 1977

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ 3
- የሠራተኛ መደብ ዕድገት በአፍሪካ 9
  — አብዱልአዚዝ ጁኔይዲ
- በሽግግር ወቅት የሕግ ሚና 33
  — ፈለቀ ዋኑ
- ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚደረገው ትግል 47
  — ዮሐንስ ገ/ሥላሴ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001

የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google



ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

የፓርቲውን የመሪነት ሚና ማሳደግ

የኢሠፓ ፕሮግራምና በአጠቃላይ የመሥራች ጉባኤው ልዩ ልዩ ሠነዶች የአገራችን አብዮታዊ ሂደት የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ በጥልቀት በመገምገም ወቅቱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ እየተገባደደ ለሶሻሊዝም መሠረት የሚጣልበት መሆኑን አመልክቷል ። ይህ የምንገኝበት የዕድገት ደረጃ አጠቃላይ ባሕርይ ሲሆን ያቀድነውን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረ ዝርዝር ሁኔታዎችን ማገናዘብና የአፈጻጸም ቅደም ተከተልን መቀየስ አስፈላጊ ነው።በዚህ መሠረት በአሁኑ ጊዜ የተፈጥሮ ችግር ያደረሰብንን የከፋ አደጋ መቋቋምና ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎቻችንን መልሶ ማቋቋም ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው አቢይ ጉዳይ ነው ። ሕዝባችን ዕድገቱን በአስተማማኝ ለማራመድ የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጥርለትን አዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት ለማሟላት ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን ማዋቀርም ሌላው የወቅቱ አቢይ የትኩረት ነጥብ ነው ። በተጨማሪም በየትኛውም መስክ የተያያዝነው ትግል እንዳይደናቀፍ አብዮቱንና እናት አገርን መጠበቅም ለአፍታም ቸል ሊባል የማይችል ግዳጅ ነው ።

በተደጋጋሚ እንደተገለጸው በማናቸውም ረገድ የተቀየሰው የትግል ስልት ትክክለኛነቱ አያጠያይቅም ። ፈታኝ ሁኔታ የሚያጋጥመው በተግባር በመተርጎሙ ሂደት ላይ ነው ። ሆኖም አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ ከተገኘ የሚገድ አይደለም ። ይህም ቅድመ ሁኔታ ድርጅታዊ ብቃት ነው ። ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ፣ ከአብዮታዊ ትግሎች ልምድና ባለፉት አሥር ዓመታት ከተጓዝንበት የትግል ጉዳና ላይ በተግባር የተማርነው ቁምነገር የጠንካራ ድርጅትን አስፈላጊነት ነው ። በተለይ ከፊታችን ከተደቀነው የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ውስብስብ ትግል የሚጠበቁ መልካም ውጤቶች ሁሉ መገኘት አለመገኘት በድርጅታዊ ብቃት ይወሰናል ።

ለኢሠፓ መመሥረት የሚሰጠው ግምት ከፍተኛነት የሚወሰነው በምሥረታው በራሱ ሳይሆን ይልቁንም ከእንግዲህ ለሚጠብቀን ትግል ስምረት የፓርቲው አመራር በሚያስገኘው ውጤት ነው ። ስለዚህ የፓርቲያችን ጥንካሬና የአመራር ብቃት፣ ፓርቲያችን በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዘንድ የሚኖረው ተሰሚነትና ተወዳጅነት ከመመሥረቱ ወይም ከፕሮግራሙ ጥራትና ካዘጋጃቸው መመሪያዎች ትክክለኛነት ብቻ ሳይሆን ከሚያደርጋቸው ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችና ከሚያስገኛቸው ተጨባጭ ውጤቶች የሚመነጭ ነው ። በደንቡ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው፣ “ኢሠፓ በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ዘልቆ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ እውነተኛ ግንባር ቀደም መሪነቱን የሚያረጋግጠውና የሚኖረውም ተቀባይነት የሚመነጨው ስለራሱ ከሚናገረው ሳይሆን ይልቁንም ምንነቱን ከሚያረጋግጥበት ተግባሩ ነው ። ”

Digitized by Google

የፓርቲው መገኘት ፣ ፓርቲው የነደፈው ትክክለኛ መሥመርና የመሥመሩም ተግባራዊነት ለአብዮቱ ወደፊት መራመድ ያላቸው አስተዋጽኦ ምትክ የለውም ። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ላይ የሕዝብ ተሳትፎ ከተውነም ሊታለፍ የሚችል አይደለም ። ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም መሠረታዊ አስተምህሮ እንደምንረዳው ፣ ከሌሎች ሀገሮች ታሪክና በተለይም ከአብዮታችን ሂደት በተጨባጭ እንደተገነዘብነው በማኅበራዊ ዕድገት ሂደት ውስጥ ወሳኙ ኃይል ሕዝብ ነው ። በዚህም መሠረት ፓርቲያችን በሕዝቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ያካሔድ ዘንድ ተፈላጊውን ብቃት ለማጐናጸፍ የሚደረግ ጥረት ለአንድ አፍታ እንኳን ቸል መባል የለበትም ።

በተለያዩ አጋጣሚዎችና መድረኮች በተደጋጋሚ እንደተነገረው ድርጅት ከግብ ለመድረስ የሚያገለግል መሣሪያ እንጂ በራሱ ግብ ያለመሆን ከንድፈ ሐሳባዊ ገንዛቤ ባሻገር በተግባር መታየቱ ከምንጊዜውም ይበልጥ ዛሬ በምንገኝበት ወቅት የተለየ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ። ዛሬ በምንገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃርም የተደራጀ ትግልና አሠራር ከፓርቲው ጋር ብቻ ተቀራኝቶ መታየት ያለበት ሳይሆን የፖለቲካ ሥርዓቱን አካላት ሁሉ የተቀነባበረ እንቅስቃሴን ያጠቃልላል ።

እንደሚታወቀው አብዮታዊው መንግሥት የኢሠፓን አመራር ለመቀበል ባወጣው አዋጅ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሥልጣኑን ለሕዝብ ተወካዮች ሸንጎ እስኪያስረክብና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በሕገ መንግሥቱ መሠረት እስኪቋቋም ድረስ የኢትዮጵያን ሠራተኞች ፓርቲ አመራርን በመቀበል መንግሥታዊ ተግባሩን እንደሚያከናውን በግልጽ ተመልክቷል ። "መንግሥታዊ ተግባር" ሲባል ደግሞ በኢሠፓ ፕሮግራም ውስጥ ከተመለከቱት ፣ በኅብረተሰባችን ፖለቲካዊ ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ርዕዮተዓለማዊ ተግባሮች ውጭ እንዳልሆነ ግልጽ ነው ።

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ኢሠፓ የኅብረተሰቡ በአጠቃላይና በተለይም የፖለቲካ ሥርዓቱ መሪ ማዕከል መሆኑን ስለተቀበለ የአብዮታዊው መንግሥት አውታሮች የኢሠፓን ፕሮግራምና መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ያለባቸው ግዴታ ሕጋዊ መሠረት አለው ። ሕዝባዊ ድርጅቶችም ከተቋቋሙባቸው መሠረታዊ ዓላማዎች አኳያ የፓርቲውን አመራር ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ከዚሁ ውጭ የሚታዩ አይደሉም ።

የሠርተአደሩን ሕዝብ ፍላጐትና ምኞት ለሚወክለው ለኢሠፓ አመራር የተሟላ ተግባራዊነት ከሁሉ በፊት አስፈጻሚዎች ለፓርቲው መስመር ያላቸውን ተገዥነት ይጠይቃል ። የግለሰቦችን ከእምነት የመነጨ ተሳትፎ ፣ የሚፈጽሙትን ተግባር ከራሳቸው እንደመነጨ ቆጥረው በይዘቱ ጥራትና በአፈጻጸም ስልቱም ሙሉ በሙሉ ማመናቸውን ይሻል ። እነዚህን የመሳሰሉ ርዕዮተዓለማዊና መንፈሳዊ ዝግጅቶችን በመመሪያዎችና በደንቦች አማካይነት ብቻ ማሟላት እንደማይቻል ግልጽ ነው ። እነዚህ ካልተሟሉ ደግሞ የፓርቲውን አመራር ከርሱ ውጭ ባሉት አካላት አማካይነት በኅብረተሰቡ ውስጥ በሚፈለገው ጥራት ፣ ቀልጥፍናና ስፋት ማስፈን ያዳግታል።

Digitized by Google

የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግ መመሪያ ብቻ ማውጣት በቂ አይደለም ። ተገቢ ትኩረት በመስጠት አገዛ ፣ ክትትልና እርምት ማድረግን ይጠይቃል ። በዚሁ መሠረት ፓርቲው የትግል መሥመርና መመሪያዎችን በጥንቃቄ መቀየስ መሠረታዊ ተግባሩ ቢሆንም ይህ የተልዕኮው አንድ ክፍል ብቻ ሲሆን ይልቁንም ከባዱ ጉዳይ ተከታተሎ በትክክል መፈጸማቸውን ማረጋገጡ ነው ።

ፓርቲው ይህንንም ሊያደርግ የሚችለው በካድሬዎቹ አማካይነት ነው ። የካድሬዎች ብቁነትም በአንድ ወቅት በሚያሳዩት አጥጋቢ ውጤት ብቻ የሚለካ ሳይሆን ከሚለዋወጡና በአዲስ ከሚከሰቱ ሁኔታዎች ጋር እርምጃዎቻቸውን ለማስተካከል ከመቻላቸውና አጠቃላይ መመሪያዎችን ፈጠራ በተሞላበት መልክ ተፈጻሚ አድርገው በሚያስገኙት ውጤት ጭምር ነው ።

የመምራትና የማስተዳደር ተግባር ሳይንስንና ጥበብን የሚጠይቅ ሲሆን ፣ በተለይ ደግሞ የጥበብነት ባሕርዩ ልዩ ትኩረት የሚጠይቅ በመሆኑ ለእያንዳንዱና ለሁሉም ሁኔታ ተስማሚ የሚሆን ስልት (ፎርሙላ) ሊቀረጽ አይቻልም ። ይህ ሐቅ በተለይ በማኅበራዊ ሂደቶች ውስጥ ከሚታየው ውስብስብ ሁኔታ አንፃር በግልጽ የሚታይ በመሆኑ ሰፊ ማብራሪያ የሚያሻው አይደለም ። በአንድ ወቅት ፍሬያማ የነበረ የአመራር ስልት በሌላ ጊዜ በዚያው መልኩ ሥራ ላይ መዋል ያለበት ሳይሆን ለወቅቱ እንዲስማማ መደረግ ያለበት ነው ። ስለዚህም የአመራር ስልቶቻችንን በየደረጃው ከሁኔታዎች ጋር በአግባቡ ለማጣጣም መቻል እንደሚኖርብን ልንገነዘብ ይገባል ።

ኢሠፓ ላወጣው ፕሮግራምና በአጠቃላይ ለአመራሩ ተግባራዊነት የካድሬዎቹን ግንባር ቀደምትነትና የኅብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎ ይሻል ። ለየትግል መስኩ የቀየሰው መስመር ፍሬያማነት የሚለካው በሚያሳድረው ጠቀላላ ግምት ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ እንደተገለጸው በተግባር ነውና የጠቀላላውን የፖለቲካ ሥርዓቱን አካላት እንቅስቃሴ ይጠይቃል ።

ለኢሠፓ የአመራር ሚና ከፍ እያለ መሔድና ለዓላማውም ተግባራዊነት እራሱ እንደአንድ ወጥ ውሑድ ድርጅትነቱ የሚያደርገው እንቅስቃሴ መሠረታዊ ጉዳይ ሲሆን ፣ ለዚህም ጤናማ ውስጣዊ ሕይወቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ።

የፓርቲውን አመራር ጥራት በሚመለከት ከግለሰብ ካድሬዎቹ ብቃት ባሻገር የአካላቱ አሠራር ቀልጥፍና አብሮ የሚታይ ነው ። ይልቁንም ለግለሰብ ካድሬዎቹ ብቃትና ውጤታማ እንቅስቃሴ አካላቱ የአመራር ሰጪነት ኃላፊነታቸውን የሚወጡበት ሁኔታና ስልት ወሳኝ ተጽዕና አለው ። ግለሰብ ካድሬዎችና መሪዎች በጋራ አመራር ውስጥ የግል ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚጠበቅባቸውን እንደመሆናቸው ከፓርቲ አመራር ጥራትና ጥንካሬ አኳያ የአካላት ሚና ጉልህ ሥፍራ ይይዛል። የግለሰቦች ጥንካሬ ለአካሉ ጥንካሬ መሠረት እንደመሆኑ በየአካላቱ ውስጥ ያለው የአሠራር ሥርዓት በአባላቱ ዕውቀትና ሙያ በስፋት ለመጠቀም የሚያስችል መሆን ይኖርበታል ። ስለዚህም በመመሪያዎች ላይ የተመሠረተ የኢሠፓ አካላት የተቀላጠፈ አሠራር የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ ከመቻሉ አኳያ ብቻ ሳይሆን የፓርቲውን ውስጣዊ ዲሞክራሲ በማሳደግ መሪዎችን በብዛት ለማፍራት የሚያስችል ከመሆኑም አንፃር መታየት ያለበት ነው ።

Digitized by Google

በአጠቃላይ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አሠራር በፓርቲያችን ውስጥ እየዳበረ መሄድ የጋራ አሠራርንና የግል ኃላፊነትን በሚገባ የመወጣት ልምድ እንዲሰፍን ያደርጋል ። ከዚህ ውጭ የሚሠራ ከሆነ ግን በደሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህዎች ላይ ለተመሠረተ ፓርቲ ፍጹም ባዕድ የሆነ ቢሮክራሲያዊነትና የግለሰቦች ኃላፊነታቸውን በተገቢው መንገድ ያለመወጣት ልምድ ሥር ይሰዳል ። ስለዚህ የመርሁ መጣስ የሚያስከትለው ጉድለት ከተነሳንለት ግብ እንዳንደርስ የሚያደናቅፈን መሆኑን በመረዳት በመርህ ላይ የተመሠረቱና በውጤታማነታቸው በተግባር የተፈተኑ የአሠራር ስልቶችን ያለማወላወል ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል ።

የኢሠፓን የመሪነት ሚና በማሳደግ የአብዮታችንን ዓላማ ዳር ለማድረስ የድርጅታዊ ሥራችን ጥራትና ቀልጥፍና ወሳኝ እንደሆነ ተመልክተናል ። ለዚህ ወሳኝ ተግባር የምንሰጠው ግምትም ከሁሉ አስቀድሞ የድርጅታዊ ሥራን ምንነት በሰፊው ከመረዳት የሚጀምር መሆን አለበት ። ድርጅታዊ ሥራን ከምልመላና ከፓርቲ ውስጣዊ ሕይወትና ከመሳሰሉት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ መልክ ብቻ መወሰን ቁንጽል አቀራረብ ነው ። ስለዚህ ጉዳዩን በተገቢው ስፋት በመረዳት ድርጅታዊ ሥራችንን ለማጠናከር ያልተቀጠበ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል ። ድርጅታዊ ሥራ ስንል አዲሱን ሥርዓት ለመገንባት የተያያዝነውን ትግል ሁሉ የሚመለከት ሲሆን የሚጠይቀን ትኩረትም የዚያኑ ያህል ጥልቅ ነው ። በአንድ ወቀት በተመሳሳይ አብዮታዊ ሁኔታ ውስጥ የነበረችውን ሩሲያን በማስተዋል ሌኒን እንዳስገነዘበው ፣

«… አገሪቱን በተሳካ ሁኔታ ማስተዳደር እንችል ዘንድ ተጨባጭ ድርጅታዊ ሥራ የመሥራት ችሎታ ሊኖረን እንደሚገባ ማወቅ ይኖርብናል ። ይህም ሥራ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት ኢኮኖሚያዊ መሠረት በአዲስ መንገድና በጥልቀት ማደራጀትን የሚመለከት በመሆኑ እጅግ ከባድ ሥራ ነው ።»

ከዚህ አንፃር የአገራችንን ኅብረተሰብ በአዲስ መሠረት ላይ ለመገንባት በየትኛውም መስክ የሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ ከድርጅታዊ ሥራ ተለይቶ የሚታይ አይደለም ። ስለዚህ ድርጅታዊ ሥራ የጥቂቶች ተግባር ብቻ ሳይሆን የብዙኃንን የተቀነባበረ እንቅስቃሴ ይጠይቃል ። በፓርቲያችን ውስጥ በማንኛውም ደርጃና የሥራ ዘርፍ እንዲሁም በፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት የሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ፍሬያማነት መለኪያ ድርጅታዊ ሥራችን ሲሆን ለዚሁ ውጤት መገኘት የዚያኑ ያህል የማያሰልስ ትኩረት ሊደረግበትና በተግባር ሊገለጥ ይገባል ።

የኢሠፓን የመሪነት ሚና ለማሳደግ በምናደርገው ጥረት ሁሉ መመሪያዎችን በሚፈለገው መልክ ተግባራዊ እያደረግን ፣ ከተግባርም በምናገኘው ልምድ እያሻሻልንና እያዳበርን ለሌላ ተጨማሪ ተግባር ከተዘጋጀን ፣ አሠራራችንን ለማቀላጠፍ የሚያበቃን ችሎታ እንዳለን ካረጋገጥን ፣ ትግላችን እንደሚሰምር ቀንጣት ታህል አንጠራጠርም ። በፈታኝ ወቀቶች ሁሉ የተሰጠውን አመራር ያለማመንታት እየተቀበለ

Digitized by Google

ታሪክ ሠሪነቱን በተግባር ያስመሰከረውና በማስመስከር ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በኢሠፓ አመራር ሌሎች ታላላቅ የታሪክ ፋይዳ ያላቸው ተግባሮችን እን ደሚያከናውን እሙን ነው፤። በአንፃሩም ይህን የሠርቶአደሩን ሕዝብ ዝግጁነት ለበለጠ ፍሬ ለማብቃት በየመስኩ የተሠማሩት የፓርቲው ካድሬዎች ምን ያህል ከባድ ኃላ ፊነት እንዳለባቸው ግልጽ ነው ። የአብዮታችንን ዓላማ ለግብ ለማብቃት ብቸኛው መተማመኛችን የፓርቲውን ትክክለኛ አመራር ከሠርቶአደሩ ሕዝብ ጥረት ጋር ማቀ ናጀት እንደመሆኑ ይኸው በአግባቡ መፈጸሙን ማረጋገጥ ለነገ ሊባል የማይቻል ኃላፊነት ነው ። ለትልሞቻችን ሁሉ ዕውን መሆን ቀስትና የሆነው የኢሠፓ የአመ ራር ሚና አያደገ መሔድ ማረጋገጫም ከዚህ አንፃር የምናሳየው ተጨባጭ ውጤት ነው ።

Digitized by Google

ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ
ኢትዮጵያን እንመሠርታለን!

Digitized by Google

የሠራተኛ መደብ ዕድገት በአፍሪካ

አብዱልአዚዝ ጁነይዲ

የአፍሪካ ሠራተኛ መደብ ኢምፔሪያሊዝምን ፣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ፣ ዘረኝነትን ፣ ወዘተ እየታገለ ነው ። በዚህ ትግሉ የሚጐናጸፈው ድል ለዓለም አብዮታዊ ሂደት መፋጠን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደርጋል ። ይህ የሠራተኛ መደብ ፣ በብሔራዊ አርነት ንቅናቄ ውስጥ ሰፊ ተሳትፎ ቢያደርግም የንቅናቄው መሪ አልነበረም። በቁጥር ፣ በክምችት ፣ በንቃትና በድርጅት የደረሰበት የዕድገት ደረጃ ይህንን ሚና ለመጫወት አላበቃውም ። ሆኖም የሠራተኛው መደብ በንቅናቄው ውስጥ የመሪነት ሚና ለመጫወት አለመቻሉ ወይም ተመሪ መሆኑ ጊዜያዊ ነው ። ዋናው ነገር መደቡ ካለው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕርይ ወይም አቋም (ማለትም መሠረታዊ ጥቅሙ ሊከበር የሚችለው በአጠቃላይ የሰው በሰው መበዝበዝ ሲወገድ በመሆኑ) እና ከዚህም ባሕርይ የሚመነጨው ንቃቱና ቆራጥ ታጋይነቱ ነው ። ለዚህ ነው ማርክስና ኤንግልስ ዋናው ጉዳይ ፦ ይኸ ወይም ያኛው ወዛደር ሊላው ቀርቶ መላው ወዝአደር በወቀቱ ዓላማው አድርጎ የሚመለከተው ጉዳይ የቱ ነው የሚለው ጥያቄ አይደለም ። ጥያቄው ወዛደሩ ምን እንደሆነና ከዚህ ሕልውናው የሚመነጨው ታሪካዊ ተግባሩ ነው ፤ ያሉት ።

በአፍሪካ አህጉር የሠራተኛው መደብ ከማኅበራዊ ሕልውናው አንፃር ሲታይ ፡ በማኅበራዊና በብሔራዊ ትግል እያደገ የሚሔድ ሚና ለመጫወት የሚችልና እንደሌሎቹ ዓለምአቀፍ የሠራተኛ መደብ አካላት ሁሉ ታሪካዊ ተልዕኮ ለመፈጸም የሚችል ነው ። እንዲያውም በአፍሪካ የተሟላ ነፃነት የመጐናጸፍ ጉዳይ በአህጉሩ ኢምፔሪያሊዝምን በመቃወም ፣ ማኅበራዊ ችግርችን ለማስወገድና ዕድገትን ለማፋጠን በሚካሔደው ትግል የሠራተኛው መደብ በሚኖረው ቆራጥ የተሳትፎ ደረጃና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎችንና ሌሎችንም ሠርቶአደሮች በዙሪያው አሰልፎ ለመታገል በሚኖረው ብቃትና ችሎታ ይወሰናል ።

ታዳጊው የአፍሪካ ሠራተኛ መደብ እያቆጠቆጠና እየተጠናከረ በመሔድ ላይ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል የሚካሔደው ትግል እየተፋፋመ ፣ ሶሻሊዝም በዓለም አብዮታዊ ሂደት ውስጥ የሚጫወተውም ወሳኝ ሚና እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ነው ።

Digitized by Google

ስለዚህ የወቅቱ ዓለምአቀፍ ሁኔታ ፣ ለፖለቲካ ንቃቱ ፣ ለድርጅታዊ ጥንካሬውና ለውጊያ ብቃቱ መዳበር አመቺ ሁኔታን ፈጥሮለታል ። ይህም መደቡ ለሚጫወተው ሚና በተቀጠነ ሁኔታ መጕልበት የሚረዳ ነው ። በተጨማሪም አያሌ የአፍሪካ አገሮች ከአርነት በኋላ ያካሔዱት መጠነኛ የኤኮኖሚ ዕድገት በአህጉሩ ለሠራተኛው መደብ ቁጥር መበራከት፣ በኅብረተሰቡ ውስጥም ለሚጫወተው ሚና ከፍ እያለ መሔድ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

በዚህ ጽሑፍ የአፍሪካን የሠራተኛ መደብ አመጣጥና አስተዳደግ በመመርመር ከምዕራብ አውሮፓው ሠራተኛ መደብ አነሳስና ዕድገት የሚለይባቸውን ባሕርያት ለማመልከትና የአስተዳደጉን ለየት ያለ መልክ ፣ ሚናውንና የዕድገቱን ሁኔታ በአጠቃላይ ለመዳሰስ ጥረት ይደረጋል ።

የመደቡ አፈጣጠር

በቅድመ ሞኖፖል ጕልተው ከሚታዩት የካፒታሊዝም ባሕርያት መካከል አንዱ ነፃ ውድድር ነበር ። በካፒታሊስቶች መካከል የሚካሔደው ውድድር ከፍተኛ የምርትና የካፒታል መከማቸትንና መማከልን አስከተለ ። ከቴክኒክ ዕድገት ጋር የካፒታል ጥንቅር እያደገ መሔዱ አማካይ የትርፍ መጠን ለማግኘት የሚያስፈልገው የካፒታል መጠን እንዲጨምር አደረገው ። በውድድሩ ሂደት በአሸናፊነት ለመውጣት የበቁት ድርጅቶች የቴክኒክ ዕድገትን ለማስፋፋት የሚያስችላቸው ብዙ ገንዘብ የነበራቸውና የካፒታል ጥንቅራቸውም ከፍተኛ የሆኑ ድርጅቶች ነበሩ።ማሸነፍ የተሳናቸው ካፒታሊስቶች ግን ከሰረው ከገበያ ውጭ በመሆን ከንብረታቸው ተፈናቀሉ ። ጥቂት ድርጅቶች ኅብረት በመፍጠር ወደ ትልልቅ የሞኖፖል ድርጅቶች አደጉ ።

እነዚህ ትልልቅ ድርጅቶች በውድድር ሂደት የበላይነታቸውን ከጨበጡ በኋላ በአመዛኙ ዋጋን ለመቆጣጠርና ከፍ ያለ የሞኖፖል ትርፍ ለመዛቅ የሚያበቃ ጥንካሬ አገኙ ። የተፈጠሩት የሞኖፖል ኅብረቶችና ድርጅቶች ነፃ ውድድርን እየተኩ በሔዱ መጠን በኢንዱስትሪ በበለፀጉ አገሮች ውስጥ የካፒታል መትረፍረፍና የመዋዕለ ንዋይ መስክ መጣበብ ተፈጠረ።የሀገሮቻቸው ሠራተኛ ሕዝቦች በድኅነት የቆረቆዙ በመሆናቸው የኢንዱስትሪ ውጤቶቻቸውን በመግዛት አስተማማኝ ገበያ ሊፈጥሩላቸው አልቻሉም ። ስለዚህም አዳዲስ ገበያ ማፈላለግ ግድ ሆነ ።

እንዲሁም ትላልቅ የሞኖፖል ኢንዱስትሪዎቻቸው የሚያስፈልጋቸውን የማዕድንና የእርሻ ጥሬ ዕቃ በአገር ውስጥ አቅርቦት ብቻ ለማርካትና ከኢንዱስትሪ ዕድገት ጋር በከተሞች የተከማቹትን ሕዝቦች በአገር ውስጥ በሚመረት የምግብ እርሻ ውጤት ብቻ ለመመገብ አልተቻለም። ስለዚህ መስፋፋት በካፒታሊስት ሀገሮች የሚታየውን የትርፍ መጠን የማሽቆልቆል ዝንባሌን ለመቋቋም ለሞኖፖሊስቶች ጠቃሚ መሆኑ ግልጽ ሆነ ። እነዚህ ምክንያቶች ተዳምረው ካፒታሊዝምን ወደ ቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ለማሸጋገር አስተዋጽኦ አደረጉ ።

ካፒታሊስት ሀገሮች በጦር መሣሪያ የበላይነታቸውና በዘመናዊ የሚሊተሪ ዘዴያቸው በመታገዝ በርካታ የእስያና የአፍሪካ አገሮችን በቀጥተኛ የቅኝ አገዛዝ መዳፍ ውስጥ በማስገባት ፣ ጥቂቶችንም ከፊል ቅኝና ጥገኛ አገሮች በማድረግ የኢምፔሪያሊዝም የቅኝ አገዛዝ ሥርዓትን መሠረቱ። [2]

ቅኝ አገዛዝ ከሰፈነ በኋላ አፍሪካና ሌሎች ቅኝና ጥገኛ አገሮች በዓለም ካፒታሊስት ገበያና የሥራ ክፍፍል ውስጥ ደካማና ተቀጥላ ሥፍራ ያዙ ። በዚህም ምክንያት አፍሪካና እነኚህ አገሮች ለቅኝ ገዢ አገሮች የእርሻና የማዕድን ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ፣ የሸቀጥ ማራገፊያና ትርፍ ማፈሻ ሆኑ ።

Digitized by Google

በቅኝ አገዛዝ አማካይነት ካፒታሊዝም ወደአፍሪካ መግባቱ የነዚህ ሀገሮች የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መዋቅር ለቅኝ ገዥዎች ጥቅም በሚያመች መንገድ እንዲደራጅ አድርጐታል ። ኢኮኖሚያቸውም ከቅኝ ገዥዎች ፍላጐት ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ ለባዕድ ፍላጐት የሚቀርቡ የእርሻና የማዕድን ጥሬ ዕቃዎችን እንዲያመርት የተዋቀረ ነው ። በተጨማሪም በአንዳንድ ኢኮኖሚያዊ መስኮች ዘመናዊ የአመራረት ሁኔታ ውሱን በሆነ ደረጃ መዳበሩ ፣ ከፊውዳልና ከቅድመ ፊውዳል የምርት አደረጃጀት ጋር መዳቀሉ በአህጉሩ የተዛባና እርስ በርስ ያልተያያዘ ኢኮኖሚያዊና መደባዊ መዋቅር እንዲፈጠር አድርጓል ። በአንድ በኩል አሮጌው የኢኮኖሚና የመደብ መዋቅር ሙሉ በሙሉ አልጠፋም ። በሌላ በኩል አዲሱ የኢኮኖሚና የመደብ መዋቅር ተስፋፍቶ አሮጌውን መዋቅር ለማስወገድ እንዲችል አመቺ ሁኔታ አልተፈጠረለትም። በመሆኑም አሮጌውና አዲሱ ሥርዓትጐን ለጐን የሚኖሩበት ሁኔታ ሊቆይ ችሏል ። ነገር ግን ይኸው ውሱን የካፒታሊዝም መስፋፋት በአህጉሩ መጠነኛ የጥሬ ዕቃዎችና የሸቀጥ ምርት እንዲያድግ ብቻም የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት (በገብ ርና ዘርፍ ጭምር) እንዲፈጠር ፣ የአፍሪካ ገበሬዎች ወደ ሠራተኛነት እንዲለወጡና[3] በመጠኑም ቢሆን የአፍሪካ የቡርዧ መደብ እንዲፈጠር አግዟል ። ይህ ሁኔታ በአፍሪካ አህጉር የሠራተኛውን መደብ አፈጣጠርና የትግል ባሕርይ ለየት ያለ መልክ እንዲይዝ አድርጐታል ። ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ ገፅታዎች ፣

1. በቅኝ አገዛዝ መስፋፋት ምክንያት የሠራተኛው መደብ መፈጠሩ ፣
2. መደቡ በአመዛኙ የሚበዘበዘው በቅኝ ገዥዎች መሆኑና የመጀመሪያው የትግል እንቅስቃሴው ብዙውን ጊዜ ፀረ ቅኝ አገዛዝ (ፖለቲካዊ) ይዘት ያለው መሆኑ ፣
3. መደቡ ከቅድመ ካፒታሊስት የኢኮኖሚ መዋቅሮች የተላቀቀበት (የተፈናቀለበት) መንገዶች (ዘዴዎች) ፣ ናቸው ።

ስለዚህ የአፍሪካ ሠራተኛ መደብ ከምዕራብ አውሮፓ ሠራተኛ መደብ ከሚለይባቸው መልኮች አንዱ መደቡ በአመዛኙ የሚበዘበዘው በቅኝ ገዥዎች መሆኑ ነው ። በዚህ ምክንያት አፍሪካውያን ሠራተኞች ያካሄዱዋቸው ቀደምት የሥራ ማቆም እንቅስቃሴዎችና ሌሎች የተቃውሞ እርምጃዎች ፀረ ቅኝ አገዛዝ ፖለቲካዊ ይዘት ነበራቸው ። በርግጥ አፍሪካውያን በመጀመሪያ ያካሄዱት እንቅስቃሴ የምንዳ ጭማሪንና የሥራ ሁኔታን መሻሻልን የሚመለከቱ ነበሩ። ይሁንና ቅኝ ገዥው መንግሥት ወታደሮቹን አሰማርቶ የሥራ ማቆም እንቅስቃሴ ተካፋዮችን ማሰሩና መግደሉ ፣ የሥራ ማቆም እንቅስቃሴንም መንግሥቱን ለመጣል እንደሚያካሂድ ትግል አድርጐ መቁጠሩ ፣ የሠራተኞቹን ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ንቃት በማዳበር የሚያካሂዱዋቸው የሥራ ማቆም እንቅስቃሴዎች ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ ባህሪም ያላቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ አስተዋጽኦ አድርጓል። በአፍሪካ የሠራተኛ መደብና በባእዳን ሞኖፖሊስቶች መካከል በተፈጠረው የብዝበዛ ግንኙነት ሠራተኞች የሚያሳዩት ተቃውሞ የኢምፔሪያሊዝምን ተፅዕኖ ፣ የሥራና የኑሮ ሁኔታዎችን አስከፊነት ለማስወገድ እንዲነሳሱ በማድረጉ ትግሉ ጣምራ ባህርይ እንዲይዝ (ማለትም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንዲሆን) አድርጐታል ።

በአህጉሩ ቅኝ ግዛት ተስፋፍቶ በነበረበት ወቅት ቅኝ ገዥ መንግሥታት ዋነኛው ቀጣሪና አሰሪ መሆናቸውም ለአፍሪካ ሠራተኞች እንቅስቃሴ ፖለቲካዊ ገጽታ መጉላት ተጨማሪ መንስኤ ሆኗል ። መንግሥታቱ በሚያካሂዷቸው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች(ለምሳሌ ፣ በመንገድና በሕንፃ ሥራ፣ በባቡር ሃዲድ መዘርጋት ወዘተ)

Digitized by Google

እያሌ ሠራተኞችን ቀጥረው ነበር ። ሠራተኞቹ ሲሠራ ሂደት የሚፈጸምባቸውን ጭቆና ለመቋቋምና የኑሮ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ያካሄዱት ትግል በቀጥታ ከመንግሥት ጋር አጋጭቷቸዋል ።

በቅድመ ቅኝ አገዛዝ አፍሪካ ውስጥ አልፎ አልፎ ከሚታዩ የቅጥር ሁኔታዎች በስተቀር [4] በሰፊው የተለመደ የምንዳ ሠራተኛነት አልነበረም ። የአገሬዎቹ ጉሣዎች ከእጅ ወያአፍ ለሆነ ኑሮ በሚመረትበት ኢኮኖሚ በመሠማራት ከሞላ ጎደል ለራሳቸው የሚበቃ ምግብና ሌሎችንም አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በማምረት የተወሰኑ ነበሩ ። በዚህም ምክንያት ቅኝ አገዛዝ ሲጀመር የአገሬዎቹ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች በቅጥር ጉልበት የመሠማራት ፍላጐት ሊኖራቸው አልቻለም ። በመሆኑም በቅኝ አገዛዝ ሞኖፖሊስቶች የተቋቋሙት የማዕድን ፣ የእርሻና የኢንዱስትሪ ድርጅቶች የቅጥር ሠራተኞች ዕጥረት አጋጥሟቸዋል ።

ቅኝ ገዥዎች የገጠማቸውን የሠራተኛ እጥረት ለማስወገድ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል ። ከነኝህ እርምጃዎች መካከል ፣ ሀ/ ገበሬዎችን በፖለቲካ ኃይል (በመንግሥት አማካይነት)በቀጥታ አስገድዶ በካፒታሊስታዊ ይዞታ ውስጥ በቅጥር እንዲሰሩ ማድረግ፣ለ/ገበሬዎች በጉልበት ሥራ እንዲሰማሩ በተዘዋወሪ መንገድ ለማስገደድ በጥሬ ገንዘብ ታክስ እንዲከፍሉ መወሰን፣ሐ/የእርሻ ምርት እንዳይዳብር የተለያዩ እንቅፋቶች መፍጠርና ፣ መ/የመሬት ይዞታቸውን መቀነስ ይገኙበታል ። በተለይ የቅኝ አገዛዝ መስፋፋት በመጀመሪያው ደረጃ ላይ በነበረበት ወቅት የቅጥር ጉልበትን ለማስገኘት ከኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ይልቅ ፖለቲካዊ ምክንያቶች ጉልህ ሚና ተጫውተዋል ። ቅኝ ገዥዎች በነበራቸው የፖለቲካ የበላይነትና ኃይል በመጠቀም አፍሪካውያን ገበሬዎችን በሕንፃ ፣ በመንገድና በድልድይ ሥራ ፣ እንዲሁም በማዕድንና በእርሻ የሥራ መስክ እንዲሠማሩ አድርገዋቸዋል ። ሠርቶ አደሮቹ በእነዚህ መስኮች ለቅኝ ገዥዎች ጥቅም ለመሥራት የተገደዱት የምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ስለሌላቸውና የመሥራት ኃይላቸውን ለመሸጥ ተገፋፍተው አልነበረም ። ይልቁንም ፣ በዚሁ ወቅት በተግባር የዋለው የግዳጅ ሥራ አፍሪካውያንን በቅጥር ሠራተኛነት እንዲሰማሩ አስገድዷቸዋል። ለምሳሌ አንድ ፀሐፊ እንደሚለው «የሠራተኛን እጥረት ማቃለያው ጉልህ ዘዴ ግዴታዊ የሆነ የምንዳ ሠራተኛነት በመሆኑ በመጀመሪያ ቅኝ ገዥዎች በሮዴሺያ ሲሰፍሩ በሰፊው ሥራ ላይ ውሏል ።» [5]

ቅኝ ገዥዎች የግዳጅ ሥራን በሮዴሺያ ብቻ ሳይሆን በሌሎች አካባቢዎችም ተጠቅመውበታል ። ለምሳሌ ቤልጅግ ኮንጐ (ዛየር) እየተባለ በሚጠራው አገር ከ1889 * ጀምሮ የግዳጅ ሥራ አስከፊ በሆነ ሁኔታ ሲካሄድ የቆየ ከመሆኑም በላይ የተለያየ አስተዳደራዊ ቅርጽ በመያዝ እስከ 1954 እንዳልተወገደ በጉዳዩ ላይ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ገልጠዋል ። የግዳጅ ሥራ በእንግሊዝ የቅኝ አገዛዝ ሥር በነበሩት ምእራባዊ የአፍሪካ ክፍሎችም ሥራ ላይ ውሏል። ፍሬዴሪክ ሉግ የተባለ አንድ የእንግሊዝ ባለሥልጣን ናይጀሪያን አስመልክቶ የግዳጅ ሥራን አስፈላጊነት ሲናገር «ከጐሳዎች አባላት መካከል ለባቡር ሃዲድና ለሌሎች አስፈላጊ ሥራዎች ክንፃኔ የሚጠቅሙ ሠራተኞች ለማግኘት በጐሳ መሪዎቻቸው አማካይነት በግዴታ ምልመላ ማካሄድ አስፈላጊ ነበር ።» [6] ብሏል ።

ቅኝ ገዥዎች በብዙ የአፍሪካ ቅኝ ግዛቶቻቸው የተፈጠረውን የምንዳ ሠራተኞች

* በዚህ መጽሔት ውስጥ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የዘመን አቆጣጠር እ. ኤ. አ. ነው ።

Digitized by Google



ቅኝ ገዢዎች በኩንጐ የባቡር ሐዲድ ሲያሠሩ
ከ"The Growth of African Civilization Vol. 2" የተወሰደ

Digitized by Google

እጥረት ለማቃለል ሲሉ በወቅቱ በነበራቸው ኃይል ተጠቅመው በተግባር ላይ የዋሉት የግዳጅ ሥራ አፈፃፀም እንደሚከተለው ነበር ።

የተወለሱ ወንደርተኞች የምንዳቸው መነሻ ሊዜር ሽልንገ ሆኖ እንዲሁም ምግብና መኝታ ቀርቦላቸው ለነጮች እንዲሠሩ የአገሬዎቹ ኮሚሽነሮች ወይም የፖሊስ ኢንስፔክተሮች ለወንደረተኞች እንዲተላለፍ ለጉሣ አለቆችና ለባላባቶች ትዕዛዝ ይሰጡ ። ትዕዛዞቹ ብዙውን ጊዜ ከሥልጣን ክልላቸው በላይ ለማስፈጸም በሚተጉ ከአፍሪካውያን መካከል በተመለመሉ ፖሊሶች አማካይነት ሥራ ላይ ይውሉ ነበር ። [7]

ይህ በአገሬዎቹ የጉሣ አለቆችና ባላባቶች አማካይነት የቅኝ ገዢዎች በተዘዋዋሪ የማዘዝ ስልት በይበልጥ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች በነበሩ የአፍሪካ አገሮች ተገባራዊ ሆኗል ። በዚህ ዓይነት በኃይል ላይ በተመሠረተ ዘዴ በመጠቀም አገሬው ለቅኝ ገዢዎች በግዴታ እንዲሠራ ምዝገባና ምልመላ ይካሔድ ነበር ።

በቀጥታ በቅኝ ገዢ ባለሥልጣኖች ወይም በተዘዋዋሪም ቢሆን በጉሣ መሪዎች አማካይነት ሠራተኞችን መልምሎ በግዴታ ማሠራት እያደር ወደተታውጥና ወደ አመፅ ሊያመራ በመቻሉ ፣ አመጹን ለማፈንም ከፍተኛ ወጭና ጦር ማዘጋጀት በመጠየቁ የዚህን ዘዴ ጉጂ ገጽታ ለመቀነስ ከቀጥታ የግዳጅ ሥራ መቆጠብና ሌሎች አማራጭ ስልቶችን መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ ።

አፍሪካውያንን ወደ ቅጥር የጉልበት ሥራ ለማስገባት ከተጠቀሱት ዘዴዎች አንዱ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈል የታክስ ደንብ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ነበር ። እንዲከፍሉ የተጣለባቸውን የታክስ ዕዳ ለመክፈል አፍሪካውያኑ ገንዘብ የማገኛ ዘዴዎችን መቀየስ ነበረባቸው ። ከቅኝ አገዛዝ በፊት ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው የሚበቃ ምርት በማምረት ፍላጐታቸውን ስለሚያሟሉ በንግድና በልውውጥ የሚሠማሩት አልፎ አልፎ ነበር ። ስለዚህም ጥሬ ገንዘብ አላስፈለጋቸውም ። ኋላ ግን ቅኝ ገዥዎቹ ታክስ በገንዘብ እንዲከፍሉ ስላስገደዱዋቸው በቅኝ ገዢዎቹ ድርጅቶች ተቀጥረው በመሥራት በገንዘብ ከሚከፈላቸው ምንዳ ላይ ገብራቸውን ከመክፈል ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም ።

በተጨማሪ ይህ ያልዳበረ የሸቀጥ ልውውጥ የሚታይበት የአፍሪካውያን ኢኮኖሚ እንዲሟሟም ሆን ተብሎ በቅኝ ገዢ መንግሥታት የተወሰዱት እርምጃዎች የአፍሪካውያን የሸቀጥ ምርት እንዳይዳብር የሚጉትቱ ከዚህ ይልቅ በቅጥር ጉልበት መሠማራታቸውን የሚያበረታቱ ነበሩ ። ለምሳሌ በሮዴሽያ የሰፈሩት ቅኝ ገዢዎች አፍሪካውያን ገበሬዎችን ከባቡር ሐዲድ መስመርና ከመንገድ አካባቢ ርቀው እንዲሰፍሩ አድርገዋቸዋል። ይህ ርቀት የትራንስፖርት ወጭን በመጨመሩ (ብሎም የትርፍ መጠንን በመቀነሱ) አፍሪካውያን ምርታቸውን ወደ ገበያ አቅርበው እንዳይሸጡ እንቅፋት ሆኖባቸዋል ። ከዚህም በላይ ቅኝ ገዢዎቹ ሆን ብለው መጋቢ የገጠር መንገዶችን ከማስፋፋት ታቅበዋል ። በተጨማሪም የቅኝ ገዢዎቹ ቡርዧዎች ከመንግሥታቸው ድጐማና ብድር እያገኙ የሸቀጥ ምርታቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ሲደረግ አፍሪካውያን ገበሬዎች ግን እንኳንስ ድጎማ ሊያገኙ ቀርቶ የሚያመርቱትንም ሸቀጥ በዝቅተኛ ተመን እንዲሸጡ በመገደዳቸው የሸቀጥ ምርታቸው እንዳይጠናከር ተደርጓል ። [8] ምክንያቱም አፍሪካውያን የሸቀጥ ምርታቸው በዳበረና የእርሻ ውጤቶቻቸው ዕድገት ባሳየ ጊዜ እራሳቸውን የሚችሉና የምንዳ ሠራተኛነት ፍላጐታቸው የሚቀንስ መሆኑ በመረጋገጡ ነው ።

አፍሪካውያን ሠራተኞች ወደቅጥር ጉልበት እንዲሠማሩ በማድረግ ውጤት ያስገኘው ሌላው የቅኝ ገዢዎች እርምጃ የአፍሪካውያን ገበሬዎችን የመሬት ይዞታ መጠን

Digitized by Google

የሚቀንስ ፖሊሲ መቀየስ ነበር ። ቅኝ ገዢዎችና ወኪሎቻቸው በሚያወጡዋቸው ፖሊሲዎች መሠረት ለእርሻ የሚውል ፣ ወይም ሊውል የሚችል ለም መሬትን ለደን ልማት መከለል ፣ በዚህ አቅጣጫ ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል አንዱ ነው ። የአፍሪካውያን የመሬት ይዞታ መጠን መቀነስ አንዱ ዓቢይ ዓላማ አገሬውን በእርሻና በማዕድን ቁፋሮ ሥራ ላይ በቅጥር ሠራተኛነት እንዲሠማራ ለማድረግ ነበር ።በዚህ ዓይነት የመሬታቸው መጠን መቀነሱ የዕለት ጉርሳቸውን የሚያመርቱበትንና ቤተሰባቸውን የሚመግቡበትን ማሳና የምርታቸውን መጠን ቀንሷል ። አፍሪካውያን በተቀነሰው ማሳቸው ቤተሰባቸውን መመገብ ባለመቻላቸው ከእርሻ ከሚያገኙት ገቢ ሌላ ተጨማሪ መደጐሚያ እንዲፈልጉ ገፋፍቷቸዋል ። መደጐሚያ ለማግኘት የነበረው ጉልህ አማራጭ ደግሞ ከትንሿ ማሳቸው በሚተርፈው ተጨማሪ የሥራ ጊዜ በአውሮፓውያን የማዕድንና የእርሻ ድርጅቶች ተቀጥሮ መሥራት ነበር ።

በተጨማሪም በአፍሪካውያን ይዞታ ሥር የነበረው ለም መሬት በቀጥታ ለነጭ ሰፋሪዎችና ለውጭ ኩባንያዎች መታደሉ አያሌ አፍሪካውያን በቅጥር ጉልበት ሥራ እንዲሠማሩ አስገደዳቸው ። ለምሳሌ ፣ ከ1898—1899 በሰሜንና በደቡብ ካሜሩን የጀርመን ኩባንያዎች ከ40% በላይ የሚሆነውን መሬት በ[illegible]ጥራቸው ሥር አድርገዋል ። በኮንጐ ብራ[illegible]1899 በውጭ ኩባንያዎች ኮንሴሲዮን እጅ የ[illegible]ው የመሬት ስፋት 780,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን ይህም ከጠቅላላው የፈረንሳይ የግዛት ክልል ይበልጣል ።[9]

በ1931 በሮዴሺያ (በዛሬዋ ዚምባብዌ) በወጣው ሕግ መሠረት በዘረኛ ፖሊሲ ላይ የተመረኮዘ የመሬት ሽንሸና እንዲካሔድ ተደርጓል ። ሽንሸናው ፣ ሀ/ በወል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተውን የአፍሪካውያንን የቀበሌ ክልልን ፣ ለ/ በመጠኑም ቢሆን አፍሪካዊ ቡርዧን ለመፍጠር ተብሎ ለአፍሪካውያን መሬት መግዛትና መሸጥ የተፈቀደበት ቀበሌን ፣ ሐ/ አብዛኛው ለም መሬት የሚገኝበትንና ለአውሮፓውያን የተከለሉ አካባቢዎችን ፣ መ/ የደን ልማት ክልልንና ለማንም ያልተመደቡ መሬቶችን ይይዛል ።[10]

ከላይ በዝርዝር ለማመልከት እንደተሞከረው በአፍሪካ የቅጥር ጉልበት ለማስገኘት የተወሰዱት እርምጃዎች በመንግሥት ጣልቃ ገብነት በመከናወናቸው በአህጉሩ ውስጥ በመጀመሪያ ላይ በአመዛኙ ፖለቲካዊ እንጂ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የቅጥር ጉልበት እንዳላስገኙ መረዳት ይቻላል።እነዚህ እርምጃዎች ባይወሰዱ ኖሮ በኮኝ አገዛዝ ዘመን [illegible]በ[illegible]ው ማሳውን[illegible] መንደሩን ለቆ ወደ ቅጥር ሠራተኛነት ለመሰማራት እምብዛም ፍላጐት ባልኖረው ነበር ። ሸርን እስቲቼር የተባለች ጸሐፊ ስለ ኬንያ ሠራተኛ መደብ አመጣጥ እንደገለጸችው «የሠራተኛ ጉልበት ጥያቄ መጠን በፍላጐት ላይ ከተመሠረተ አቅርቦት ጋር ሲነጻጸር እጅጉን የሚልቅ በመሆኑ በጉልበት ገቢያ ውስጥ የመንግሥት ጣልቃ መግባት አስፈላጊ ሆኗል ።» ስለዚህም «ሠራተኞች ለበለጠ ቅጥር ሥራ እንዲተርቡ ለማድረግ መንግሥት የነፍስ ወከፍ ግብርና ሌሎችንም በጥሬ ገንዘብ የሚከፈሉ የግብር ዓይነቶችን[11] ጠይቋል ።

ቅኝ ገዥዎች የሠራተኛ ጉልበት ፍላጐታቸውን ለማርካት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ሳይወሰኑ በፊውዳል ዘዴዎችም ተጠቅመዋል ። ይህም የጉልበት አገልግሎት በመባል የሚታወቀው ነው ። በፊውዳሊዝም ዘመን በጭሰኝነት የሚተዳደሩት ገበሬዎች የሚያርሱትና የሠፈሩበት መሬት የመሬት ከበርቴን ንብረት ስለነበረ የተወሰነ የጉልበት አገልግሎት እንዲያበረክቱለት መጠየቅ ይችል ነበር ። ጭሰኞቹም የሚያርሱትን መሬት እንዳይቀሙና እንዳይባረሩ ለባለመሬቱ እርቦ ወይም ሲሶ የመሳሰሉትን የዓይነት ክፍያዎች ከማበርከት ሌላ

Digitized by Google

የጉልበት አገልግሎት መስጠት አንዱ የክፍያ ግዴታቸው መወጫ መንገድ ሆኖ ቆይቷል ።

በቅኝ አገዛዝ ዘመን የአገሬው ገበሬዎች የሚያርሱት ማሳና መኖሪያ ቤታቸውን የሚሠሩበት ቦታ ወደቅኝ ገዥ መንግሥታት ወይም ወደ ኩባንያዎቻቸው ንብረትነት ተዛወረ ። አፍሪካውያኑ በመሬቱ ለመጠቀም እንዲፈቀድላቸው ላዲሶቹ የመሬት ባለንብረቶች የጉልበት አገልግሎት ማበርከት ግዴታቸው መሆኑ ተገለጸ ። ለምሳሌ በሮዴሺያ ውስጥ አፍሪካውያን በሳምንት ለተወሰኑ ቀናት በሰፋሪዎች እርሻ ላይ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ነበረባቸው ።[12]

የጉልበት አገልግሎት የሚጠየቅበት ይህ ዓይነቱ የሠራተኛ ጭሰኝነት ቀድሞ ፊውዳሎች ከገበሬው ከሚጠይቁት አገልግሎት አስከፊ የሚሆንበትም ምክንያት አለው ። ፊውዳሎች ከገበሬው የሚፈልጉት የጉልበት አገልግሎት በአብዛኛው የፊውዳሎችን የፍጆታ ፍላጐት ለማርካት የሚውል ነበር ። ሆኖም ቅኝ ገዥዎች የጉልበት አገልግሎት እንዲሰጣቸው የሚፈልጉት ትርፍ ለማካበት እንደመሆኑ መጠንና ይህ የትርፍ ፍላጐታቸው ደግሞ የእርካታ ገደብ ስለሌለው አፍሪካውያን ገበሬዎችን ሲበዘብዙ የቆዩት ከፊውዳሎች በላቀ ደረጃ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል ።[13] የጉልበት አገልግሎት ሥራ ላይ መዋል ለጊዜው የቅኝ ገዥ ኩባንያዎችና አሠሪዎች የሠራተኛን ፍላጐት በማርካት በኩል መጠነኛ ውጤት በማስከተል ብቻ አላበቃም ። በዚህ መነሻ ፣ ገበሬዎቹ አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለቅኝ ገዥዎቹ የጉልበት አገልግሎት እንዲያውሉ በመገደዳቸው በራሳቸው መሬት ላይ ለመሥራት የሚያበቃቸው ጊዜ እያነሰ ሄደ ። በዚህም ምክንያት ከማሳቸው ለመሰብሰብ የሚችሉት የምርት መጠንም እያቆለቆለ ፣ ከእለት ወደ እለት ወደድህነት አዘቅት ስለገቡ አያሌ ገበሬዎች ከመሬታቸው መፈናቀል ግድ ሆኖባቸዋል ።

አውሮፓውያን ቅኝ ገዥዎች የተፈጠረውን የሠራተኛ እጥረት ለመቋቋም የተጠቀሙበት ሌላው ዘዴ እስያውያንን መልምሎ ወደ አፍሪካ ምድር በማምጣት ማሠራት ነበር ። ይህን በሚመለከት አንድ ጸሐፊ ሲያትት እንደሚከተለው ብሏል ።

ወደ አህጉሩ ይገቡ በነበሩና በአመዛኙ በእርሻ ሥራ እንዲሰማሩ በሚዳረጉ እስያውያን / በአብዛኛው ሕንዶች / ነበሩ ። በ1904 የእንግሊዝ መንግሥት በቅኝ ግዛት ባለሥልጣኖች ገፊት 40,000 የሚሆኑ ቻይናውያን የጉልበት ሠራተኞች ወደ ደቡብ አፍሪካ እንዲገቡ አድርጓል ። የሥራ ሁኔታቸውም ከአፍሪካውያን የከፋና ምንዳቸውም ያነሰ ነው ።[14]

ቅኝ ገዥዎች ፣ በዚህ ዓይነት እስያውያን ሠራተኞችን መበዝበዛቸው ፣ ከሚያስገኝላቸውም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ የአፍሪካውያንን ምንዳ በተቻለ መጠን ዝቅ እንዲል ለማድረግ የበለጠ ጠቅምኦቸዋል ።[15]

ከላይ እንደተጠቀሰው ፣ አሠሪዎች የገጠማቸውን የምንዳ ሠራተኞች እቅርቦት እነስተኛነት ለማስወገድ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ተጠቅመዋል ። አፍሪካውያን ታክስ በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍሉ መወሰኑ ፣ የእርሻ መሬታቸው በተለያዩ ዘዴዎች መቀነሱ ፣ በተወሰኑ አካባቢዎች እንዲኖሩ መከለሉ ፣ እንዲሁም ሌሎች መሰል እርምጃዎች መወሰዳቸው አያሌ አፍሪካውያን ገበሬዎችን በምንዳ ሥራ እንዲሠማሩ አስገድዷቸዋል ።

የጊዜያዊ ሠራተኛነት መስፋፋት

በአፍሪካ ለረጅም ጊዜያት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች በጊዜያዊ ሠራተኛነት ተቀጥረው እንዲሠሩ ተገደዋል ። እነዚህ ጊዜያዊ ሠራተኞች ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በምንዳ ሠራተኛነት ተቀጥረው የሚሠሩና የተቀረውን ጊዜ በገጠር የሚኖሩ ገበሬዎች ናቸው ። አውሮፓውያን አሠሪዎች ፣ ኩባንያዎቻቸውና

Digitized by Google

መንግሥቶቻቸው በወቅቱ ገጥሞአቸው
የነበረውን የሠራተኛ አቅርቦት ችግር
ለማስወገድ ከላይ የተጠቀሱትን በርካታ
እርምጃዎች መውሰዳቸው ለጊዜያዊ ሠራተ
ኛነት መስፋፋት መንስኤ ሆነዋል ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አፍሪካው
ያንን ወደምንዳ ሠራተኛ ለማሰማራት
ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል አንዱ
የመሬታቸውን ይዞታ መቀነስ ነበር ። ይሁን
እንጂ እርምጃው አፍሪካውያንን ሙሉ
በሙሉ ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት
አላላቀቃቸውም ። ምክንያቱም የእርሻ መሬ
ታቸው እንዲጠብና ለሙን መሬት ለአውሮ
ፓውያን እንዲለቁ ቢደረግም ጠፉን መሬት
በባለቤትነት ይዘው ነበር ። ምንም እንኳ
ኋላቀር ቢሆኑም የራሳቸው ማረሻና ሌላም
የእርሻ መሣሪያም ነበራቸው ።

በምእራብ አውሮፓ ግን (በተለይ በእን
ግሊዝ ውስጥ የሱፍ ምርት ተፈላጊነት ከማ
ደጉ ጋር ባለመሬቶች ሰፊ መሬት ለበግ
ርቢ ሲከልሉ) በርካታ ገበሬዎች በባለመሬ
ቶች አስገዳጅነት ከመሬታቸው ተነቅለው
ወደከተሞች በመጉረፍ በኢንዱስትሪዎች
ውስጥ በቅጥር ሠራተኞችነት መሠማራታ
ቸው ይታወሳል። እነዚህ ገበሬዎች ከግል እር
ሻቸው ከተፈናቀሉ በኋላ ወደዚህ ሥራቸው
ሊመለሱ የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም ።
የ አፍሪካው ገበሬ ግን በማሳው ወይም ከንብ
ረቱ ሙሉ በሙሉ በመፈናቀሉ ሳይሆን ከማ
ሳው አነስተኛነትና ከመሬቱ ጠፍነት የተ
ነሳ የሚያገኘው የምርት መጠን ማነሱ ለቤ
ተሰብ የሚበቃ ምርት አምርቶ መመገብ
ስለተሳነው ተጨማሪ ገቢ ለመሻት ወደ
ከተሞች ፣ ወደማዕድንና የእርሻ አካባቢ
ዎች የቅጥር ሥራ ለመፈለግ ተሰደደ ።

የቅኝ ገዢ መንግሥታት የገንዘብ ታክስ
ክፍያ ደንብ ማውጣትም ጊዜያዊ ሠራተ
ኛነትን የሚያበረታታ ሆኗል ። አፍሪካው
ያን ሠርቶ አደሮች አህጉሩን ለወረሩት
ቅኝ ገዥዎች በምንዳ ሠራተኛነት እንዲ
ሠሩ' የሚገፋፋቸውም ምክንያት እንዳል
ነበረ ከላይ ተጠቅሷል ። ሆኖም መንግ
ሥታት የገጠማቸውን የሠራተኛ እጥረት
ለማቃለል አፍሪካውያን ሠርቶ አደሮች በገ
ንዘብ መልክ ግብር እንዲከፍሉ መወሰና
ቸው እነኝህ ሠርቶ አደሮች ለክፍያው ገን
ዘብ ሊያስገኝላቸው በሚችለው በምንዳ
ሥራ እንዲሰማሩ አስገደዳቸው ። ምክን
ያቱም አንደኛ ፣ የአፍሪካውያን የግብርና
ሥራ ለራስና ለቤተሰብ የሚበቃ ምርት የሚ
መረትበት እንጂ ከሸቀጥ አመራረት ጋር
ያልተያያዘ በመሆኑ ጥሬ ገንዘብ ሊያስገኝ
አልቻለም ። ሁለተኛ ፣ ለም መሬታቸው
በአውሮፓውያን ስለተወሰደ በያዙት ጠፍ
መሬት ላይ ዘመናዊ ባልሆነ አስተራረስ
ከቤተሰባቸው የሚተርፍ ምርት አምር
ተው ለገበያ በማቅረብ የተጠየቁትን ጥሬ
ገንዘብ ለማግኘት አልቻሉም ። ሶስተኛ ፣
የቅኝ ገዥዎች የአፍሪካውያን የሸቀጥ
ምርት እንዳይዳብርና ጥሬ ገንዘብ እንዳያ
ስገኝላቸው እንቅፋት ፈጠሩ ። ስለዚህ
ግብር ለመክፈል የሚያስችል ገንዘብ ለማግ
ኘት በጊዜያዊ ሠራተኛነት መሠማራቱ
ዓይነተኛው አማራጭ ሆኖ ተገኘ ።

አፍሪካውያን በምንዳ ሠራተኛነት ከተሰ
ማሩ በኋላ በቋሚ ሠራተኛነት ሳይቆዩ ወደ
ገጠር እንዲመለሱ የሚያደርጋቸው ምን
ድነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት በአ
ፍሪካ የጊዜያዊ ሠራተኛነትን መንስኤ
ለመረዳት ያስችላል ።

አፍሪካውያን ገበሬዎች በቅጥር ሠራተ
ኛነት ተሰማርተው የሚያገኙትን የምንዳ መ
ጠን ከፍተኛ ቢሆን ኖሮ ቤተሰባቸውን ለማኖ
ርም ሆነ የመንግሥቱን ግብር ለመሸፈን ስለ
ሚያስችላቸው የገጠሩን ኑሮ ሙሉ ለሙሉ
በመተው በከተሞች፣በኢንዱስትሪዎችና በሰ
ፋፊ እርሻዎች አካባቢ በቋሚ ሠራተኛነት
ተቀጥረው እንዲሠሩ ይገፋፉቸው ነበር ።[16]

ቅኝ ገዥ አሠሪዎች ፣ አፍሪካውያ
ንን በጊዜያዊ ሠራተኛነት ማሠራት ከፍ
ተኛ ትርፍ የሚያስገኝ በመሆኑ ጊዜያዊ
ነቱ እንዲቀጥል ፈላጊዎች ነበሩ። [17] ስለ
ዚሁ ጉዳይ ጥናት ባካሄደ አንድ ምሑር
አስተያየት ቅኝ ገዥዎች በአፍሪካውያን

Digitized by Google

ገበሬዎች መካከል በሚፈጠር የመደብ መሸ ጋሸግ ምክንያት ከፊሎቹ ወደ ወዛአደር ነትና ሌሎችም ወደቡርዧነት መቀየራቸ ውን ያልወደዱበት ምክንያት የዚህ ዓይ ነቱ ሂደት ተፎካካሪ የሆነ የአፍሪካ ቡርዧ እንዲፈጠር የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገ ፡፡

ምናልባትም የበለጠ ግምት ሊሰጠው የሚገ ባው ለማዳዊን የመሬት ይዞታ ሥርዓት አለ ማፍረሱ የሠራተኞችን ምንዳ ዝቅ አድ ርጐ ለማቆየት እንደሚረዳ በመገመታቸው ነው ምክንያቱም የጊዜያዊ ሠራተኛ ቤተሰብ የሚያስፈልገውን ወጭ በገበሬዎች የሚሸፍን በመሆኑ ነው ። [18]

አብዛኛዎቹ በጊዜያዊ ሠራተኛነት ለመ ሠማራት የተሰደዱ ገበሬዎች ለሥራ ብቁ በሆነ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ጐልማሶች እንዲሁም ወጣቶች ነበሩ ። በገጠሩ ማሳ ቸው የሚቀሩት በአብዛኛው ሴቶች ፣ ሕፃ ናትና ሽማግሌዎች ናቸው ። ለሁለት ወይም ለሦስት ዓመት ለሚሆን ጊዜ አያሌ ጐል ማሶች ከግብርና ተለይተው በቅጥር ሥራ በሚሰማሩበት ጊዜ የግብርናው ሥራ በሴ ቶችና በሽማግሌዎች ጉልበት ይከናወናል ። ሴቶችም ለሥራ እንዲመለመሉ ቢደረግ የእርሻ ምርት ስለሚቋረጥ የጊዜያዊ ሠራ ተኛ ኃይልን አቅርቦት ያፈልሰው ነበር። [19]

በዚህ ሁኔታ ርካሽ የጊዜያዊ ሠራተኞች ጉልበት የሚፈለገውን ያህል አይኖርም ። በሌላ አነጋገር የሠራተኛውን ቤተሰብ በገ ጠር በማቆየት ዝቅተኛ ምንዳ ለመክፈል ይቻላል ። ቤተሰቡ በገጠር ካልኖረ ግን የሠራተኛውን ምንዳ በጣም ዝቅ ማድረግ አይቻልም ።

በጊዜያዊ ሠራተኛነት መስፋፋት ምክ ንያት ጠንካራ አምራች ኃይል ከገጠር በመ ሰደዱ በአፍሪካውያን የሚካሄደው ሰፊ የግ ብርና ሥራ በሰው ኃይል እጥረት እንዲዳ ከም ፣ በዚህም ምክንያት በመስኩ ምርታ ማነት እንዲቀነስ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ከቅኝ አገዛዝ በፊት ፣ የአፍሪካውያን የእ ርሻ መሬት በተደጋጋሚ በመታረሱ ምክ ንያት ልምላሜውን ከቀነሰ እዳሪ በማው ጣት አዳዲስ ያለሙ ነበር ። ሆኖም ፣ ከቅኝ አገዛዝ በኋላ የይዞታቸው መጠን በመቀ ነሱ ፣ በተለይም ለሙን ክፍል አውሮፓው ያን በመውሰዳቸው የማሳ ማለዋወጥ ዘዴ እንደቀድሞው ሥራ ላይ እንዳይውል እን ቅፋት ሆኗል ። ከዚህም በላይ ፣ የጊዜያዊ ሠራተኛነት ስምሪት መስፋፋቱም በገጠር የወንዱን አምራች ኃይል በከፍተኛ ደረጃ በመቀነሱ አዳዲስ ማሳ የማልማቱን ሥራ አዳከመው ። በመንደሮቹ አካባቢ የሚቀ ሩት ሴቶችና ሽማግሌዎች ይህን ዓይነት የጉልበት ሥራ ለማከናወን አቅም ስለሚ ያጡ ያለማቋረጥ አሮጌውን ማሳ በተደጋ ጋሚ ለማረስ ተገደዋል ። ይህ የአስተራረስ ዘደም የአፈሩ ልምላሜ እንዲቀንስ ፣ የም ርት ውጤት እንዲያሽቆለቁልና የአፍሪካ ውያን ድኅነትም በበለጠ እንዲባባስ አድ ርጓል ። [20]

እዚህ ላይ አንድ መታወስ ያለበት ጉዳይ በጊዜያዊ ሠራተኛነት ባል ከሚስት ተለ ይቶ እስከ ሁለትና ሦስት ዓመት የሚቆይ ስለነበር የአፍሪካውያንን ትዳር ማናጋቱና በተለይም በሴቶች ላይ ችግር ማስከተሉ ነው ። ከጊዜያዊ ሠራተኛነት መስፋፋት በፊት በባልና ሚስት መካከል አለመግባ ባት ሲነሳ በአፍሪካውያን ባህል መሠረት በቤተ ዘመድ ግፊት አማካይነት ጭቅጭቁ ጋብቻ እንዲጠናከር ይደረግ ነበር ። ጊዜ ያዊ ሠራተኛነት ከተስፋፋ በኋላ ሚስት እንደቀድሞው በቤተዘመድ አካባቢ የም ትኖር በመሆኗ ባልዋን በታማኝነት እንድ ትጠብቅ በርሷ ላይ ባህላዊ ተፅዕኖ መደረጉ ያላቋረጠ ቢሆንም ባል ግን ከሚስቱ ተለ ይቶ ሁለትና ሦስት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከቤተዘመድ አካባቢ በመራቁ የገ ጠር ሚስቱን ባይደግፋት ወይም ጭራሽ ቢተዋት ወዲያውኑ ባህላዊ ተግሳጽ ለመ ስጠት አልተቻለም ። ይህ ችግር ለቤተሰብ ብሶት መባባስና ቀድሞ በአፍሪካውያን ዘንድ ብዙ ላልተለመደው ፍቺም መስ ፋፋት አስተዋጽኦ አድርጓል ። [21]

Digitized by Google

አብዛኛዎቹ አፍሪካውያን ሠራተኞች የሙያ ሥልጠና የሌላቸው መሆኑም ከጊዜያዊ ሠራተኛነት ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነው ። ይኸውም አፍሪካውያን ሠራተኞች ለጊዜው የሚቀጠሩና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ ገጠሩ ሥራቸው ስለሚመለሱ አንደኛ፣ መጠነኛ ዕውቀት ለመቅሰም ቢችሉም እንኳን እንደገና ወደከተማ ሲመለሱ ወደቀድሞ ሥራቸው ሳይሆን ወደሌላ መስክ የመሰማራት አጋጣሚ በሰፊው በመኖሩ በፊተኛው ሥራቸው ላይ የቀሰሙትን መጠነኛ ዕውቀት ይዘነጉታል። ሁለተኛ፣ ወደቀድሞው ሥራቸው የሚመለሱበት አንዳንድ አጋጣሚ ቢኖር ቢችልም ሥራው በየጊዜው የሚደረግ በመሆኑ ሙያን በተከታታይ ለማዳበር አያስችልም ። በመሆኑም ጊዜያዊ ሠራተኛነት በሥራ ልምድ አማካይነት ሙያ ለመቅሰም የሚያመች አይደለም ። ይህን ችግር በሚመለከት አንድ ስለጉዳዩ ጥናት ያካሄደ ምሁር እንደሚከተለው ጽፏል ።

አፍሪካ ሠራተኛ ኃይል ቋሚ ያለመሆኑ ራሱ ሙያ ማዳበርን ያዳክማል ። ሠራተኞች ከአጭር ጊዜ በኋላ ከተሞችን እየለቀቁ የሚሄዱ በመሆናቸው ከፍ ያለ የሙያ ዕውቀት ይባክናል።(ሠራተኛው) ዳግመኛ እንኳን ወደ ከተማ ቢመለስ ያገኘውን አብዛኛውን ዕውቀት ይዘነጋዋል ። [23]

እዚህ ላይ በሙያ መካንና ያለመካን የሚያስከትለውን ውጤት ማጤኑ ጠቃሚ ነው። ከሙያ ባለቤትነት ወይም ሥልጠና አንፃር የሚከተሉት አራት አበይት የሥራ እርከኖች መኖራቸውን ምሁራን ያስገነዝባሉ ።

1. ሙያ አልባ (Unskilled) በተለያዩ ሙያ በማይጠይቁ መስኮችና የሥራ ሂደቶች ካስፈለገም በነዚህ ዓይነት ሥራዎች ላይ ካለአንዳች ችግር እየተዘዋወረ መሥራት የሚችል ፣ ነገር ግን ከቅጥር ሠራተኛነት ዲሲፕሊን ጋር ያልተለማመደ ነው ።

2. ከፊል ባለሙያ (Semiskilled) ሠራተኛ ልዩ የሥራ ክፍል(መስክ) ያለው፣ በተደጋጋሚ ይህንኑ ሥራ የሚያከናውንና ከሥራው ጋር የተለማመደ ፣

3. ባለሙያ (Skilled) ሠራተኛ ውስብስብ የሆነ የእጅ ሙያ ዕውቀት ያለው ነው ። ለምሳሌ አናጢ ፣ መካኒክ ፣ ወዘተ . . .

4. የሠለጠነ የሰው ኃይል (high level manpower) በሥራው ላይ ከተገኘ ዕውቀት ባሻገር የተወሰነ መደበኛ የትምህርት ደረጃና የሙያ ትምህርት ያላቸውን ሠራተኞች የሚይዝ ፣ ለምሳሌ መሐንዲስ፣ የዕቃ ግዥና ሽያጭ ኤክስፐርት ወዘተ . . . [24]

በቅኝ አገዛዝ ወቅት የነበረው የአመራረት ዘዴ በተራ ቁጥር 1 እና 3 የተጠቀሱት ሠራተኞች ተጣምረው የሚሰሩበት ነበር ። [25] አፍሪካውያን ጊዜያዊ ሠራተኞች በተራ ቁጥር 3 በተጠቀሰው የሙያ ሥልጠና በማይጠይቀው መስክ ሲሰማሩ ፣ አብዛኛውን ጊዜ አውሮፓውያንና መጠነኛ እስያውያን በተራ ቁጥር 3 በተጠቀሰው የሙያ ዓይነት ተቀጥረው ይሠሩ ነበር ። ከሠራተኞቹ መካከል ከፍተኛውን የሙያ አልባ ሠራተኞች ቁጥር የሚይዙት አፍሪካውያን ጊዜያዊ ሠራተኞች ነበሩ ።

በቅኝ አገዛዝ ጊዜ የነበረው የአመራረት ቴክኒክና ይህ ዓይነቱ አመራረት የጠየቀው የሠራተኛ ኃይል ባሕርይ በአፍሪካ የሠራተኛ መደብ መዋቅር ውስጥ ለሙያ አልባ ጊዜያዊ ሠራተኞች መበርከት ሊጠቀሱ ከሚገባቸው መንስኤዎች መካከል አንዱ ነው ። የዚያን ጊዜ አሠሪዎች ከፍተኛ ካፒታል ያልነበራቸው በመሆኑ ከትልቅ ካፒታል ባለንብረትነት የሚመነጭ ጥንካሬም አልነበራቸውም ። ለሥራቸው ስምረት የበለጠ የጠቀማቸው ከመንግሥታቸው የሚያገኙት ድጋፍ ነበር ። እነዚህ አሠሪዎች ከፍተኛ ምንዳ ቢከፍሉ የሚስገበገቡለትን ትርፍ ስለሚቀንስባቸው በተቻለ መጠን ዝቅተኛ ክፍያ መስጠት ፍላጐታቸው ነበር ። ሠራተኛው የሙያ ሥልጠና

Digitized by Google

እንዲያገኝ የሚሹና የሚገፋፉም አልነበሩም ። የሙያ ሥልጠና ያገኘ ሠራተኛ የሚከፈለው ምንዳ ከፍ ስለሚል ወይም ሠራተኛውን ማሠልጠኑ ራሱ ለጊዜው ወጪ ስለሚያስከትል ከማሠልጠን ተቆጥበዋል ። በጊዜው የነበሩት የአፍሪካ ጊዜያዊ ሠራተኞች የሚከፈላቸው ምንዳ በገጠሩ የሚደጐም ስለነበር አሠሪው ለሠራተኛው የሚከፍለው ከሥራ ኃይል እሴት በታች ሆኖ ቆይቷል ። አሠሪዎቹ ከእሴት በታች ለመክፈል መቻላቸው የአፍሪካውያን ሠራተኞችን ጉልበት በመበዝበዝ ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስ ጠቅሟቸዋል።የዚህ ዓይነት የሠራተኛ ኃይል አቅርቦት የሚሟላው ደግሞ ከገጠር ጋር ግንኙነት ባላቋረጠ ከፊል ሠራተኛ ከፊል ገበሬ በሆነ ጊዜያዊ ሠራተኛ አማካይነት ነበር ። ስለሆነም ካፒታሊስቶቹ ሙያ አልባ የሆኑ ጊዜያዊ ሠራተኞች መኖርና የሠራተኛ ኃይል አወቃቀር አለመለወጥ የሚበጃቸው ሆኖ አግኝተውታል ። እነዚህ ምክንያቶች በአንድነት ተዳምረው ለአብዛኛው የአፍሪካ ሠራተኛ ሙያ አልባ መሆንና ቋሚነት ማጣት ምክንያት ሆነዋል ። ይህም ምክንያት በተራው በአፍሪካ የተደላደለና ባለሙያ የሠራተኛ መደብ እንዳይፈጠር እንቅፋት ሆኗል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በወቅቱ የነበረው የሠራተኛ ኃይል አወቃቀር በገጠር ቤተሰብና አነስተኛ ማሳ ያላቸውን በርካታ ሙያ አልባ ጊዜያዊ ሠራተኞችን ብቻ ሳይሆን ጥቂት ቋሚ የሆኑ በከተማ የሚኖሩ ባለሙያ ሠራተኞችንም ያካትታል ። ባለሙያ ሠራተኞች ይበልጡኑ አውሮፓውያን ነበሩ ። አውሮፓውያኑ የተሰማሩበት የሙያ ዕውቀትን የሚጠይቀው የሥራ መስክ ከፍ ያለ ክፍያ የሚሰጥበት ሲሆን የሙያ ሥልጠና የሌላቸው ጊዜያዊ አፍሪካውያን ሠራተኞች የተሰማሩበት መስክ ግን ዝቅተኛ ምንዳ የሚከፈልበት ነበር ።[25] ይህ ሁኔታ ሠራተኞችን በቀለምና በዘር ለመከፋፈል አመቺ በመሆኑ ሞኖፖሊስቶችና ቅኝ ገዥ መንግሥታት መከፋፈሉን ለአድሃሪ አላማቸው በከፍተኛ ደረጃ ተጠቅመውበታል ።

በአፍሪካ የሠራተኛ መደብ እንድነትና የጊዜያዊ ሠራተኛነት መስፋፋትን እንደሚቀጥለው ማጠቃለል ይቻላል ። በቅኝ አገዛዝ ወቅት የባዕድ ካፒታል ወደ አፍሪካ መግባትና የአፍሪካ ገበሬዎች በምንዳ ሠራተኛነት እንዲሰማሩ የማድረጉ ተግባር ግዴታ በሆነ ዘዴ የተከናወነ ነበር ። የቅኝ ገዥ መንግሥታት በቀጥታ በማስገደድም ሆነ በተዘዋዋሪ በባላባቶች እየታገዙ አፍሪካውያንን ወደ ቅጥር ጉልበት ለማስገባት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ። አፍሪካውያን ለዘለቄታው በምንዳ ሠራተኛነት እንዲሰማሩ ለማድረግ ሲባል የተወሰዱት አስገዳጅ እርምጃዎች አፍሪካውያንን አደህይተዋቸዋል። የጥሬ ገንዘብ ፍላጐታቸውን በማሳደግ እያደር ያለመንግሥት አስገዳጅነት ምንዳ የሚከፈልበት የቅጥር ሥራ እንዲፈልጉ አድርጓቸዋል ። ሆኖም የመጀመሪያው የአፍሪካ የሠራተኛ መደብ ሙሉ ለሙሉ ከመሬትና ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት «ነፃ» አለመሆኑ አመጣጡ ከምዕራብ አውሮፓ የሠራተኛ መደብ አመጣጥ የተለየ እንዲሆን አድርጐታል ። በምዕራብ አውሮፓ ለካፒታሊዝም ዕድገት አስፈላጊ የሆነው የምንዳ ሠራተኛ የተገኘው ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ደህይቶ ሙሉ ለሙሉ የምርት መገልገያ ባለቤትነት በማጣቱና ይህም እጦት የመሥራት ኃይሉን ብቻ በመሸጥ ለመተዳደር ስላስገደደው ነበር ። በአፍሪካ ግን ሠርቶአደሩ ከምርት መገልገያዎች በተለይም ከመሬት ባለቤትነት ሙሉ ለሙሉ ሳይላቀቅ በምንዳ ሠራተኛነትም ለመሰማራት የሚችልበት ለየት ያለ ሁኔታ ተፈጠረ። ይህ የንብረት ባለቤትነት በቅኝ አገዛዝ ወቅት ጐልቶ ለታየው የጊዜያዊ ሠራተኛነት ሥርዓት መንሰራፋት ምክንያት ከሆኑት መካከል አንዱ ነው ። ሌላው ምክንያት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የምንዳ ዝቅተኛነት ነበር ።

Digitized by Google

በአፍሪካ ዛሬም ቢሆን ጊዜያዊ ሠራተኛነት ያልቀረ ቢሆንም እየተዳከመና ከጊዜያዊ ሠራተኛነት ወደቋሚ ሠራተኛነት ሽግግር እየተደረገ ነው ። በሚቀጥለው ክፍል የዚህን መዳከምና የሽግግሩን መንስኤዎች እንመለከታለን ።

የቋሚ ሠራተኛነት ዕድገት

በብዙዎች የአፍሪካ አገሮች በተለይም በሐሩሩ ቀጣና ውስጥ አብዛኛው ሕዝብ በግብርና የኢኮኖሚ መስክ የተሰማራና በገጠር የሚኖር ነው ። በሠራተኛው መደብ መካከል በርካታ ሙያ አልባ ሠራተኞች አሉ ። እንዲሁም ብዙዎች ዛሬም ቢሆን ከገጠር ጋር ግንኙነት አላቸው ። ሪቻርድ ሳንድብሩክ የተባለ ጸሐፊ ስለ ኬንያ ሠራተኞች ባካሄደው ጥናት እንደሚያስረዳው ፤ «ምንም እንኳን በምሥራቅ አፍሪካ ደረጃ ሲታይ ኬንያ የበለጠ የተራመደ የኢንዱስትሪና የንግድ መሠረት ያላት ብትሆንም ዛሬም አብዛኛው የኅብረተሰቡ ክፍል ገበሬ ነው ። ከሞላ ጐደል ዘጠኝ አሥረኛ የሚሆነው ሕዝቧ በገጠር ነዋሪ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አብዛኛው ገበሬ ነው ።» [26]

በርካታ ሥራ አጥ ሠራተኞችና የከተማ ድሆች ከገጠሩ ኑሮ ሙሉ ለሙሉ አልተላቀቁም ። በገጠሩ ገበሬና ፈልሰው በከተማ በሚኖሩ ሠርቶ አደሮች መካከል በልዩ ልዩ መንገድ ግንኙነት ይካሄዳል ። አያሌ ሠራተኞች በቅጥር ከሚያገኙት ምንዳ በተጨማሪ የራሳቸው አነስተኛ ማሳ አላቸው ። ለምሳሌ በኬንያ ውስጥ «ብዙ አውሮፓውያን አሠሪዎች ለእርሻ ሠራተኞቻቸው አነስተኛ የሆነች ማሳ ይደለድላሉ ። ስለዚህ እነዚህ ሠራተኞች የምንዳ ሠራተኛ የመሆናቸውን ያህል ገበሬዎችም ናቸው ።» [27] በከተሞች በትላልቅ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በእርሻ ከተሰማሩት የበለጠ ቋሚ ናቸው ። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ከሥራው ባሕርይ የተነሳ የእርሻ የሥራ እንቅስቃሴ የሚካሄደው በወቅት በመከፋፈል እንጂ ዘወትር ባለማቋረጥ የሚከናወን አለመሆኑ ነው ።በእርሻ ሥራ ላይ ብዙ ሠራተኞች የሚፈለጉት በመኸር ወቅት ነው ። እንደሚታወቀው የመኸር ወቅት በዓመት አንድ ጊዜ ፤ ግፋ ቢልም ሁለት ጊዜ ቢደርስ ነው ። ይህ የእርሻ ሥራ ባሕርይና አሠሪዎች የሚከተሉት ፖሊሲ በየጊዜው በዚህ ውስጥ የሚሰማሩት ሠራተኞች ቋሚ እንዳይሆኑና በሠራተኛነት እንዳይደላደሉ እንቅፋት ሆነዋል ።

ምንም እንኳን ዛሬም በቁጥሩ አነስተኛ ቢሆንም ከፖለቲካ ነፃነት በኋላ (በተለይም ከ1960ዎቹ መባቻ ጀምሮ) የአፍሪካ የሠራተኛ መደብ የቋሚነት ዝንባሌ እየተጠናከረ መጥቷል ። በቋሚ ሠራተኛነት ተቀጥረው የሚሠሩ አፍሪካውያን ሠራተኞች መበራከትና እንዲሁም በቅኝ አገዛዝ ወቅት ለነበረው ጊዜያዊ ሠራተኛነት ሥርዓት መዳከም አያሌ ምክንያቶች አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ከእነዚህ ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ በአፍሪካ አህጉር፤—

1. በ1950ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የታየው የምንዳ ጭማሪ፤
2. በአንፃራዊ አነጋገር ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የትላልቅ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና የአመራረት ቴክኒክ ለውጥ፤
3. የፖለቲካ ነፃነት መገኘትና የሠራተኞቹ ትግል መጠናከር ናቸው ።

ከ1950ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የአፍሪካውያን ምንዳ በገንዘብም ሆነ በመግዛት አቅሙ ጭማሪ እንደታየበት በርካታ ምሁራን ባካሄዱት ጥናት አረጋግጠዋል ። [28] ቋሚ የሆነና በሥራ ላይ የተደላደለ ወዝአደር እንዳይፈጠርና ጊዜያዊ ሠራተኛነት እንዳይቋረጥ እንቅፋት ከሆኑት ዐበይት ምክንያቶች አንደኛው በቅኝ አገዛዝ ወቅት የነበረው የምንዳ ዝቅተኛነት መሆኑ የሚታወስ ሲሆን ፤ በተጠቀሰው ወቅት የምንዳ ጭማሪ መደረግ ለተደላደለ የሠራተኛ ኃይል መፈጠር ድርሻውን አበርክቷል ። ምክንያቱም

Digitized by Google

በዚያ ወቅት የነበረው ሠራተኛ በገጠር የእርሻ ማሳ ያለውና ከቅኝ ገዥዎቹ የሚከፈለውም ዝቅተኛ ምንዳ (ለሥራ ኃይል እርባታ ከሚያስፈልገው በታች ስለነበር) ቤተሰቡን ወደከተማ አዛውር ለማስተዳደር የማያስችለው ነበር ። ይህ ሁኔታ በጊዜያዊ ሠራተኛነት ተሰማርቶ በተረፈው ጊዜ ወደ እርሻው እንዲመለስ ሲያስገድደው ቆይቷል ። ቤተሰቡንም ጭምር ሊቀልብ የሚችልበትን የምንዳ መጠን ቢያገኝ ኖሮ ዳግመኛ ወደ ገጠር እንዲመለስ የሚገፋፋው ምክንያት እስከዚህም ጉልቶ የሚታይ አይመስልም ። በመሆኑም «ከ1960 በኋላ የታየው የዕውነተኛ ምንዳ ዕድገትና ይህንኑ የተከተለው የከተማ ተቀጣሪነት ከፍ ማለት የከተማውን የቅጥር ሥራ ትቶ ወደ እርሻ መመለስ የሚያስከትለው ኪሣራ መጨመሩን ያሳያል ። »[29]

ሥራ አገኝተው የተቀጠሩት ሠራተኞች ይህንን ዕድል ካገኙ በጊዜያዊ ሠራተኛነት ወቅት በነበረው አኳኋን ወደገጠር አይሄዱም ። ምክንያቱም ሥራቸውን ትተው ወደገጠር ሄደው እስኪመለሱ ድረስ ሥራው የማይቆያቸው በመሆኑና ወደገጠር በመሄዳቸው የሚያገኙት የተሻለ ነገር ስለሌለ ከተማውን ለቀው መሄድ አይፈልጉም ። ስለዚህ ሠራተኛው ሥራ ካገኘ በኋላ ወደ ገጠር ለመሄድ ብሎ ከሥራ መሰናበት ወይም ከሥራ መቅረት ጉዳትነቱ እንደሚብስ ስለሚገነዘብ በቋሚ ሠራተኛነት መቆየቱን ይመርጣል ።

አፍሪካውያን ሠራተኞች በቋሚ ሠራተኛነት የሚሰማሩበት ሁኔታ ከተፈጠረ በኋላ እንደቀድሞው ከፊል የሥራ ስምሪታቸው በገጠር ከፊሉ ደግሞ በከተማ መሆኑ ተወገደ ። ከዚህ በኋላ ወደ ገጠር የሚሄዱት ለዓመት በዓል ወይም በጡረታ ወቅት ብቻ ሆነ ። በተረፈ ዕድሜያቸውን በሙሉ በወዛደርነት ተቀጥረው ይሠሩ ጀመር ።

ይሁን እንጂ ቋሚ ሠራተኛነት እየጎለበተ በሄደበት ወቅትም ቢሆን ብዙዎቹ አፍሪካውያን ሠራተኞች በገጠር ውስጥ መሬት የላቸውም ወይም ከገጠሩ ጋር ያላቸው ግንኙነት ፈጽሞ ተቋርጧል ማለት አይደለም ። የሠራተኞች ምንዳ መጨመርና ለረጅም ጊዜ ሥራ ላይ መቆየት የመሬት ባለቤትነት ሊያሳጣ ይችላል ። ምክንያቱም ቀድሞውኑም የአፍሪካን ጊዜያዊ ሠራተኞች ወደቅጥር ጉልበት እንዲሰማሩ ያደረገው አንዱ ችግር የመሬቱ መጠን አነስተኛነት ሲሆን በተቀጠሩበት ሥራ ላይ እንዳይቆዩ የሚያገደው ደግሞ የሚከፈለው ምንዳ ዝቅተኛነት ነበር ። ስለዚህም ምንም እንኳን መጠነኛ መሬት ቢኖራቸውም የምንዳቸው መጠን ከፍ ሲል በቋሚ ሠራተኛነት መሰማራቱ የበለጠ ጥቅም ስላለው በዚሁ ሥራ ይሰማራሉ ። ሆኖም ሚስቶቻቸው ለተወሰነ ጊዜ በከተማ ውስጥ ከባሎቻቸው ጋር ቆይተው በዘርና በመኸር ጊዜ ወደ ገጠር ሊሄዱ ይችላሉ ። በአንዳንድ ሁኔታ አንደኛዋ ሚስት ገጠሩ ማሳቸው ላይ ስትቆይ ሌላኛዋ ደግሞ ከተማ ውስጥ ከባል ጋር ትቆያለች ።[30]

ከአፍሪካ የሠራተኛ መደብ አመጣጥ ልዩ ባሕርይ የተነሳ ገበሬው ወይም ሌላው ሠርቶአደር ምን ያህል ወደ ሠራተኛነት እንደተለወጠ (level of proletarisation) ከገጠር ጋር ካለው ግንኙነት ወይም ከመሬት ባለቤትነቱ በመነሳት ብቻ መለካት አይቻልም ። የመሬት ባለቤትነቱን ብቻ እንደመለኪያ ከወሰድን የአፍሪካን ሠራተኛ ዕድገት ከሚገባው በታች ዝቅ አድርገን እንድንገምት ያደርገናል ። ይህ ድርጊት ወደተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ያደርሳል ።

ምንም እንኳን የቋሚ ሠራተኛነት ሥርዓት እየተጠናከረ ከመጣና የተደላደለ የሠራተኛ ኃይል ከተፈጠረ በኋላም ከገጠር ጋር ግንኙነት ሊኖረው ቢችልም ፣ በዚህ ወቅት የከተማው ገቢ የገጠሩን ገቢ ይደጉም እንደሆነ እንጂ አብዛኛውን ጊዜ ገጠሩ ከተማውን ይደጉማል ማለት ጉልቶ የሚታይ እውነታን አያንፀባርቅም ። በምንዳ

Digitized by Google

መልክ የሚገኘው ገቢ ዋነኛው መተዳደሪያቸው ወደ መሆን በማምራትና በአሀጉሩም የተደላደለ የሠራተኛ መደብም * በመፍጠር ላይ ነው ። [31]

ይህ ሲባል ሠራተኛው ከገጠሩ ጋር ያለው ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ እንደተቋረጠ ወይም በተሳሉም ሊቋረጥ እንደሚችል ተደርጐ መታየት የለበትም ። ዛሬም ቢሆን ገንዘብ ፣ ልብስና የመሳሰሉት ዕቃዎች ከከተማ በገጠር ለሚገኝ ዘመድና ወዳጅ ሲላኩ ፣ እህል፣ ዶሮና ዕንቁላል የመሳሰሉት ደግሞ ከገጠር ወደ ከተማ ይላካሉ ። የከተማው ሠራተኛ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ገጠሩን ሊጐበኝ ይችላል ። ለምሳሌ ፣ በአገር ልማድና ወግ መሠረት ቤተሰብ በጠቅላላው ሊገኝበት የሚገባ ሥነ ሥርዓት ካለ በዚህ ዓይነት ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘት ከከተማ ወደ ገጠር ይሄዳል። አለበለዚያም በዘመድ ቀብር ወይም ተዝካር ላይ እንዲገኝ ጥሪ ይደረግለታል ። በአንዳንድ አካባቢ ከተሜው ሠራተኛ ሲሞት አስከሬኑ ወደተወለደበት አካባቢ ተመልሶ እንዲቀበር ይደረጋል ። በወግና ልማዳቸው መሠረት ከሩቅ አካባቢ ወይም ከሌላ ጐሳ ጋር ጋብቻ መፈጸም ክልክል ስለሆነ ተመልሰው ከመንደራቸው አካባቢ የትዳር ጓደኛ መፈለግ ግዴታ የሚሆንበትም ሁኔታ አለ ። በተጨማሪም ሚስቱ በእነርሱ አስተሳሰብ ከሚናቁት የተብረተሰብ ክፍሎች ወይም ጐሣዎች ወገን የምትወለድ እንዳትሆን የሚፈራ ስለሆነ ከሚታወቁ ጐሣዎችና ቤተሰቦች አካባቢ ሚስት ለመፈለግም ሲል ወደገጠር ሊመለስ ይችላል ። [32]

ከዚህም በላይ በየጊዜው ዘመዶቹ ከገጠር ለሥራ ፍለጋ ወይም ሠራተኛውን ለመጐበኘት በሚል ሰበብ ወደከተማ ሲመጡ ምግብና መኝታ በማቅረብ የማስተናገድ ማኅበራዊ ግዴታ አለበት ። አንዳንድ ጊዜ ሥራ ለመፈለግ ከገጠር የመጡት ከተማ ውስጥ በሚገኙት ዘመዶቻቸው አማካይነት ሥራ ስለሚያገኙ ከተመሳሳይ አካባቢ የመጡ ሰዎች በአንድ ድርጅት ውስጥ ሊበረከቱ ይችላሉ ። አልፎም በከተማው ውስጥ አሰፋፈራቸው የጐሣና የቤተዘመድ መልክ ሊይዝ ይችላል ። ለምሳሌ ፣ በአንድ ከተማ ውስጥ «የእነከሌ ሠፈር» የሚባለው የጐሣ ወይም የአካባቢ አሰፋፈር ከዚህ ዓይነት ግንኙነት ሊመጣ ይችላል ። ምንም እንኳን ከቋሚ ሠራተኛነት እየተጠናከረ መሄድ ጋር ከገጠር ጋር ያለው ግንኙነት እየቀነሰ ቢሄድም ረዘም ላለ ጊዜ በልዩ ልዩ መልክ እንደሚቀጥል ከተጠቀሱትና ከሌሎችም የተለያየ የግንኙነት ቅርጾች ስፋትና ጥልቀት መገንዘብ ይቻላል ።

---

* በልዩ ልዩ ሥፍራዎች የአፍሪካ ሠራተኞች ምንጻ ማደግ የሠራተኛውን ኃይል ወደጸሚነት ለመለወጥና ለማደላደል ከፍ ያለ ሚና መጫወቱን ተመልክተናል ። ሆኖም ይህ ሁኔታ ቀደም ሲል በጊዜያዊ ሠራተኛነት ተሰማርቶ የቆየውን የሠራተኛ ኃይል በሙሉ ወደቋሚ ሠራተኛነት የለወጠው አለመሆኑ መታወቅ አለበት ። ከዚህ ጋር ከፍተኛ ሥራ አጥነትም ተከሥቷል ። አነስተኛ ጠፍ መሬት ብቻ ተትቶላቸውና ዋነኛ መተዳደሪያቸውን የተነፈጉ አፍሪካውያን የተሰጣቸው መሬት እያደር እየተሸረሸረና ልምላሜው እየተሟጠጠ ሄደ ። የሕዝብ ብዛትም እየጨመረ መሄድ የሚሰበሰቡትን ሰብል የነፍስ ወከፍ ምርት ውጤት ተነሰባቸው ። በዚህ ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ የቅጥር ሥራ የሚፈልጉ አፍሪካውያን ገበሬዎች ቁጥር እየጨረመ ሄደ። በተጨማሪ በኢንዱስትሪና በአመራረት ጠዋቅሩ ላይ የታየው ለውጥም የሙያ አልባ ሠራተኞችን ሥራ ተፈላጊነት ቀንሶታል ። ስለዚህ ከጦርነቱ በኋላ ባሉት ወቅቶች የምንጻ ጭማሪ ማግኘት የቻሉት በአብዛኛው ሁኔታ ከፈል ባለሙያና ባለሙያ ሠራተኞች ነበሩ ። በእነዚህ ወቅቶች አያሌ ደሀ ገበሬዎችና ሙያ አልባ ሠራተኞች ሥራአጥ ለመሆን ተደገዋል ።

Digitized by Google

ለተደላደለ የሠራተኛ መደብ መፈጠር መንስኤዎች ከሆኑት አንዱ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አካባቢና ከጦርነቱም በኋላ በኢንዱስትሪ መዋቅር ላይ የተከሰተው ጉልህ ለውጥ መሆኑ ከላይ ተጠቅሷል ። ይኸውም አንደኛ ፣ በንሊም የንግድ መሥመር የተቃና ክንዋኔ ላይ ጦርነቱ የፈጠረው ችግር ቀድሞ ከውጭ ወደ አፍሪካ በሚገቡት የተለያዩ የፍጆታ ሸቀጦች በአህጉሩ ውስጥ እንዲመረቱ ሁኔታዎች ማስገደዳቸው፤ ሁለተኛ ፣ በጦርነቱ ምክንያት የዓለም የሸቀጦች ምርት አቅርቦት መቀነሱና ከውጭ ወደ አፍሪካ አህጉር ይመጡ የነበሩትን ምርቶች በዚህ አህጉሩ በሰፊው ለማምረትና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ጠቃሚ ሆኖ መገኘት ፤ ሶስተኛ ፣ ለውጭ ገበያ ሸቀጥ ለማምረት የተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎች ቁጥር ከጦርነቱ በኋላ መበርከታቸውና ማደጋቸው ፤ እነዚህ ምክንያቶች በመደመር ኢንዱስትሪዎች በአህጉሩ እንዲስፋፉ ፣ የጊዜያዊ ሠራተኞች ፍላጐት እንዲቀነስ ፣ የከፊል ባለሙያ ሠራተኞች ፍላጐት እንዲጨምርና የተደላደለ የሠራተኛ መደብ እንዲፈጠር መንስኤ[33] በመሆናቸው ነው ። ይህ ሁኔታ ዘርዘር ብሎ ሲታይ እያሌ ምክንያቶችን ያጠቃልላል ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በቅኝ አገዛዝ ወቅት የነበሩ የአነስተኛ ድርጅቶች ሚና ቀንሶ የትልልቅ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ሚና አድጓል ። ከላይ እንደተመለከተው በቅኝ አገዛዝ ወቅት የነበሩ ትንንሽ ድርጅቶች በርካታ ሙያ አልባ ሠራተኞችን ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ ባለሙያ ሠራተኞች ጋር በማቀናጀት የሚያመርቱ ነበሩ ። በዚያ ወቅት ካፒታሊስቶች የነበራቸው የካፒታል መጠን ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቁ የተወሳሰቡ ማሽኖች ለመጠቀምና ምርታማነትን ለማሳደግ የካፒታል አቅም አልነበራቸውም ። የካፒታላቸው መጠን የሚጠቀሙበት ማሽንና የሥራ አደረጃጀታቸው ሲታይ ከፍተኛ የምንዳ መጠን ለመክፈል የሚያበቃ አልነበረም ። ይልቁንም እጅግ ዝቅተኛ ምንዳ ከፍለው ሙያ አልባ የሆኑ ጊዜያዊ ሠራተኞችን በማሠማራት ከፍተኛ ትርፍ ማግኘት የበለጠ ጥቅም የሚሰጣቸው ድርጅቶች ነበሩ ። በዚህ ምክንያት የተሻለ ምንዳ ከፍለው ጊዜያዊ ሠራተኛነት እንዲቋረጥና የሠራተኛውን ኃይል ማደላደል የሚሹ ሊሆኑ አልቻሉም፡የሙያ ላይ ሥልጠና (on the job training) የሙያ ማሻሻያ ትምህርት እንዲከተሉ የሚያስችሉና ሌሎችም የተደላደለ የሠራተኛ ኃይል ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልነበሩም ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እየተጠናከሩ የሄዱና ትንንሽ የማምረቻ ድርጅቶችን የተኩት ከፍተኛ የካፒታል ጥንቅር (Organic Composition) ያላቸው ትላልቅ ኩባንያዎች ናቸው ። እነዚህ ኩባንያዎች ያላቸው የካፒታል ኃይልና የሚጠቀሙበት የአመራረት ቴክኒክም ከዚሁ የካፒታል አቅማቸው ጋር የሚመጣጠን እንደሚሆን አያጠያይቅም ። ይህም ባላቸው የገንዘብ አቅም ምክንያት ከፍ ያለ የማሽን ኃይል በመጠቀም በአነስተኛ የሠራተኛ ኃይል ማምረት እንደሚችሉ ያመለክታል ። እያንዳንዱ የምርት ውጤት በአነስተኛ የሠራተኛ ኃይል መመረት የሚቻልበት ቴክኒክ የሚፈለገው የሥራ ዓይነትም የተለየ ነው። ውስብስብ የሆኑ ቀድሞ በባለሙያ ሠራተኞች የሚከናወኑ ሥራዎች በሥራው ሂደት በተለያየ ደረጃ ላይ እንዲበታተኑ አሠራራቸው እንዲቀልና አስቸጋሪ እንዳይሆኑ በማድረግ በከፊል ባለሙያ ሠራተኞች ሊከናወኑ የሚያስችል የአመራረት ቴክኒክ ነው ።[34]

በዚህ ምክንያት በቅኝ አገዛዝ ወቅት የነበረው በርካታ ሙያ አልባ የሆኑ አፍሪካውያን ጊዜያዊ ሠራተኞችን ከጥቂት አውሮፓውያን ጋር በማቀናጀት የሚመረትበት ቴክኒክ በመጠኑም ቢሆን ተቀየረ ። የተወሰኑ ከፊል ባለሙያ ሠራተኞችና የሠለጠኑ ሠራተኞች በአንድነት

Digitized by Google

ተጣምረው በሚያመርቱበት (Capital Intensive) ቴክኒክም ተስፋፋ ።

ስለዚህም ፥ ሀ/ ትላልቅ ኩባንያዎች በቅኝ አገዛዝ ወቅት እንደነበረው ባለሙያ ሠራተኞችን ከውጭ በማስመጣት ከማምረት ይልቅ በዚሁ በአፍሪካ ውስጥ በከፊል ባለ ሙያ ሠራተኛነት ሊሠሩ የሚችሉ ሠራተኞችን ማሠልጠንና በሠራተኛነት ለመደላደል የሚያስፈልገውን የምንዳ መጠን መክፈል የበለጠ የሚጠቅማቸው መሆኑን ተገነዘቡ ። ምክንያቱም የሚከፍሉት የምንዳ መጠን ከጠቅላላው ወጪያቸው ውስጥ በጣም አነስተኛ ስለሆነ በቅኝ አገዛዝ ወቅት እንደነበሩ አሠሪዎች ትርፋቸውን ብዙም የሚጐዳባቸው አልሆነም ።[35] ለ/ ኩባንያዎች የኋላቀር አገሮችን ርካሽ የሰው ጉልበት ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ሀብታቸውን መበዝበዝና በእነዚህ አገሮች ገቢያ ማግኘታቸው የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ በመሆኑ የበለጠ ምንዳ በመክፈል የሠራተኛውን ኃይል ከማደላደል እንዲቆጠቡ የሚገፋፋቸው ምክንያት የለም ።[36] ሐ/ ትላልቅ ኩባንያዎች የሸቀጦችን ተመን ለመወሰን ባላቸው የሞኖፖል ችሎታ ምክንያት ለሠራተኛው ያወጡትን ወጭ ወደ ሸማቾች ለማዛወር ስለሚችሉ ለሠራተኞች መደላደል አስፈላጊ የሆነ ምንዳ መጠን መክፈል አይሳናቸውም ። መ/ትላልቅ ኩባንያዎች የሚያስተላልፉት ውሳኔ ወይም የሚያወጡት ዕቅድ ፥ የሚከተሉት የመዋዕለ ንዋይና የቅጥር ፖሊሲ በረጅም ጊዜ ውስጥ የሚያስከትሉትን ውጤትና የሚያስገኙትን ጥቅም በመገመት ስለሆነ በእቅዳቸው መሠረት ለሠራተኛው የተሻለ ምንዳ ለመክፈል ይችላሉ ። በቅኝ አገዛዝ ወቅት የነበሩ ትንንሽ ድርጅቶች በዚህ ዓይነት የተነደፈ የረጅም ጊዜ ፖሊሲ ማውጣት ስለማይችሉ የሠራተኛውን ኃይል ማደላደሉ ወይም የተሻለ ምንዳ መክፈሉ ለጊዜው የሚያስከትለውን ወጭ ብቻ በመመልከት የምንዳ መጠንን ከፍ ለማድረግም ሆነ ሠራተኛው ሙያ እንዲቀስም እርምጃ ከመውሰድ ተቆጥበዋል ።

በአፍሪካ የፖለቲካ ነፃነት መገኘት በአሁጉሩ የተደላደለ የሠራተኛ መደብ ለመፍጠር አስተዋጽኦ አድርጓል ። ከአስተዋጽኦው አንዱ አዳዲሶቹ መንግሥታት የተከተሉት ፖሊሲ መጠነኛ የሠራተኞች ምንዳ ማደግን የሚደግፍ መሆኑ ነው ። ምክንያቱም ለፖለቲካ አርነት ትግል በሚካሄድበት ወቅት ሠራተኞችና የሠራተኛ ማኅበራት ለአርነቱ የታገሉትን የተለያዩ የአርበኞች እንቅስቃሴዎች የደገፉና ከጐናቸውም ተሰልፈው የተዋጉ በመሆናቸው እንዲሁም ይኸው ተሳትፎዋቸው ከነፃነት በኋላም በመንግሥታቱ ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ ለማሳደር እንዲችሉ አመቺ ሁኔታዎችን (ለምሳሌ የተደራጀ ኃይልና የትግል ልምድን)የፈጠረላቸው በመሆኑ ነው ። አዳዲሶቹ መንግሥታትም ቢሆኑ ከሠራተኞች አካባቢ ተቃውሞ ቢመጣባቸው የፖለቲካ መናጋትን የሚያስከትልባቸው መሆኑን ስለሚገነዘቡ ሠራተኞቹ የሚያቀርቡትን ጥያቄ በቸልታ መመልከት አይችሉም ። በዚህ ምክንያት በብዙ አገሮች መንግሥታት የሠራተኞችን የምንዳ መጠን/ዝቅተኛ ወለል/ወስነዋል ። በመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ምንዳም ከፍ እንዲል አድርገዋል ። እነዚህ እርምጃዎች ለምንዳ ዕድገት ተጨማሪ ምክንያት ሆነዋል ።

የሠራተኞች ምንዳ ከፍ እንዲል ያደረገው ሌላው ዓቢይ ምክንያት የሠራተኛው ትግል ራሱ ነው ። የአፍሪካ ሠራተኞች ለምንዳ ጭማሪና ለኑሮ ሁኔታ መሻሻል ያካሄዱት ትግል ለብሔራዊ አርነት ከሚደረገው ትግል ጋር በመቀናጀቱ ከሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችም ድጋፍ አግኝቷል ። ይህ ድጋፍ ለሠራተኞቹ ትግል ተጨማሪ ጥንካሬ በመስጠት አሠሪዎች የሠራተኞችን ምንዳ ከፍ እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል ። ለምሳሌ በ1955 የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት በነበሩ የምዕራብ አፍሪካ አገሮች ውስጥ ሠራተኞች ሥራ ባቆሙ ጊዜ

Digitized by Google

ገበሬዎችም በበኩላቸው ሥራ ላቆሙት ሠራ ተኞች ምግብ በማቅረብ የትግል አንድነታ ቸውን በተግባር አሳይተዋል ። [37] ይህ ዓይ ነቱ የትግል አንድነት አሠሪዎችን ስላሰጋ ቸው የምንዳ ጭማሪ በማድረግ እንቅስቃሴ ያቸውን ለጊዜው ለማብረድ እንዲጥሩ አስ ገድዷቸዋል ።

በአጠቃላይ ከ1950ዎቹ መጨረሻና 1960 ዎቹ መባቻ አካባቢ ጀምሮ የታየው የም ንዳ ጭማሪ የሠራተኛውን ኃይል መጐልበ ትና ቋሚ የሆነ የሠራተኛ ኃይል ለመፍጠር ያስቻለ ዋነኛው ምክንያት ሲሆን፣ለምንዳው ጭማሪ መንስዔና ከዚህም ጋር ተያያዘ ለተባለው የሠራተኛ ኃይል መፈጠር አስተ ዋጽኦ ያደረጉት ምክንያቶች ደግሞ ከሁለተ ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የታየው የኢን ዱስትሪ አደረጃጀትና የአመራረት ቴክኒክ ለውጥ ፣ የሠራተኞች ትግል ዕድገትና የፖ ለቲካ ነፃነት መገኘት ናቸው ።

በቅኝ አገዛዝ ወቅት የነበረው የምንዳ መጠን ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሠራተኛ ውን ከነቤተሰቡ ለማኖር የማይችል በመ ሆኑ ጊዜያዊ ሠራተኛነትን እንዳጠናከረ ቀደም ሲል ተጠቅሷል ። ጊዜያዊ ሠራተኛ ነት ከተዳከመና የምንዳ መጠን ካደገ በኋላ ከነቤተሰቦቻቸው ወደ ከተማ ፈልሰው የሚ ኖሩ ሠራተኞች ቁጥር እንዲበራከት ማድረ ጉን በመመልከት የሠራተኛው ኃይል ምን ያህል እንደጐለበተ ለመገመት ይቻላል ። ለምሳሌ፣ በካምፓላ (ኡጋንዳ) ውስጥ ሙያ አልባ የሆኑ ሠራተኞችን ገቢና ወጭ አስመ ልክቶ የተካሄደ አንድ ጥናት እንደሚያመለከ ተው ከቤተሰቦቻቸው ጋር በከተማ የሚኖሩ ሠራተኞች ቁጥር በ1957፣27 በመቶ የነበረው በ1964 ወደ 43 በመቶ ከፍ ማለቱ [38] የሠ ራተኛው ኃይል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠና ከረ መሄዱን ያመለክታል ።

ይህም ብቻ ሳይሆን በሌሎች ዘዴዎች የሠራተኛው ኃይል ምን ያህል ወደ ቋሚነ ትና ወደ መደላደል እንዳመራ ለማጤን ይቻ ላል ። ለምሳሌ ፣ ለረጅም ዓመታት በሥራ ቸው ላይ የሚቆዩት ሠራተኞች እየበረከቱ መሄዳቸውን በግልጽ ጠቃሚ ግንዛቤ ማግ ኘት ይቻላል ። ምክንያቱም ጊዜያዊ ሠራ ተኛነት ሰፍና በነበረበት ወቅት ሠራተኞች ለረጅም ጊዜ ሥራቸው ላይ የማይቆዩ ስለ ነበር ረዘም ላለ ጊዜ ሥራ ላይ መቆየት የጊዜያዊ ሠራተኛነትን መዳከም ያመለ ክታል ።

ስለሆነም ከ10 ዓመታትና ከዚያም በላይ ለሚሆን ጊዜ በሥራቸው ላይ የቆዩ ሠራተ ኞች ከጊዜ ወደ ጊዜ ምን ያህል ዕድገት እን ዳሳዩ ማጥናት የቋሚ ሠራተኛነትን ዕድገት ለመገመት ያስችላል ። በዚህ መሠረት ከ 1965—66 ድረስ 1,300 በሚሆኑ ኬንያው ያንና ኡጋንዳውያን የኢንዱስትሪ ሠራተ ኞች መካከል የተካሄደ አንድ ጥናት 21 በ መቶ የሚሆኑት ለአሥር ዓመትና ከዚያም በላይ በሥራቸው ላይ መቆየታቸውን አረ ጋግጧል ። በ1953 ግን ለተጠቀሰው ጊዜ ያህል በሥራቸው ላይ የቆዩት ሠራተኞች 3 በመቶ ብቻ መሆኑ ዕድገቱን በግልጽ ያመ ለክታል ። በተጨማሪም በ1953 ከሠራ ተኞቹ 80 በመቶ የሚሆኑት ከ3ዓመት ላነሰ ጊዜ ሥራ ላይ የቆዩ ነበሩ ። ከ1965—1966 ባለው ጊዜ ውስጥ ግን ከ3ዓመት በታች በሥራቸው ላይ የቆዩት ሠራተኞች መጠን 32 በመቶ ብቻ ነበር ። [39] ከ1960ዎቹ በ ኋላ ለረጅም ጊዜ በሠራተኛነት ተቀጥረው የቆዩ ሠራተኞች ቁጥር እየበረከተ መሄዱ በቋሚ የምንዳ ሠራተኛነት ተሰማርተው የሚተዳደሩ ሠራተኞች እየጨመሩ መሄዳቸ ውን ያስረዳል ።

ከዚህ በላይ ለአፍሪካ የሠራተኛ መደብ እነሳስ ፣ በአፍሪካ ጐልቶ ለታየው ጊዜያዊ ሠራተኛነትና ቋሚ ለሆነ የሠራተኛ መደብ ዕድገትን መንስዔ ዋና ዋና ምክንያቶችን ለመመርመር ተሞክሯል ። ይሁን እንጂ በአ ጠቃላይ ከምንመለከታቸው የጋራ ባሕር ያት ባሻገር በተለያዩ አገሮችም መካከል ታሪካዊ የአመጣጥና የዕድገት ልዩነቶች እን ዳሉ መገንዘብ ያሻል ። ለምሳሌ ፣ ሰሜናዊ አፍሪካ ከሐሩሩ የአፍሪካ ክፍል ፣ ሐሩራ ዊውክፍልደግሞ ከደቡባዊውአፍሪካ የተለዩ

Digitized by Google

ባሕርያት አሉት ። ዝርዝሩ ሰፊ ቢሆንም አንዳንድ ልዩነቶችን ብቻ በአጭሩ እንጥቀስ ።

በሰሜን አፍሪካ የጊዜያዊ ሠራተኛነት መጠን ከሐሩሩ የአፍሪካ ክፍል ያነሰ ነበር ። ሰሜን አፍሪካ ከአውሮፓውያን መምጣት አስቀድሞ የበለጠ የዳበረ ፊውዳላዊ ሥርዓትን ፣ ግላዊ የመሬት ባለቤትነትና መጠነኛ ስፋት ያላቸው ከተሞች የነበሩት በመሆኑ የአካባቢው የሠራተኛው መደብ አስተዳደግ ለየት ይላል ። በዚህ አካባቢ የቅጥር ጉልበት ፣ በገዳጅ ዘዴዎች ብቻ ሳይሆን በኤኮናሚያዊ ምክንያቶች ከሐሩሩ የአፍሪካ ክፍል ቀደም ብሎ ታይቷል ። በቅኝ አገዛዝ ጊዜ መሬት በሞኖፖሊስቶችና በአገሬዎቹ ፊውዳሎች እጅ እየገባ በሄደ መጠን ወደ ድህነት ማጥ ውስጥ የገቡት ገበሬዎች በተፋጠነ ሁኔታ ወደ ምንዳ ሠራተኛነት በመቀየራቸው ምክንያት ጊዜያዊ ሠራተኛነት ከመጀመሪያውም ውሱን መጠን እንዲኖረው አድርጓል ። ስለዚህም በአብዛኛው በሰሜን አፍሪካ ለሠራተኛው መደብ ዕድገት እንቅፋት የሆነው ሠራተኛው ከገጠር ጋር የነበረው ግንኙነት አለመቋረጥ አልነበረም ። ይልቁንም ለሠራተኛው መደብ ዕድገት እንቅፋት ሆኖ የቆየው የሞኖፖሊስቶች የበላይነት ነው ።

በደቡባዊ አፍሪካም የሠራተኛው መደብ ዕድገት ለየት ያለ መልክ ታይቶበታል። በአካባቢው ከ1870ዎቹ ጀምሮ በዓለም ከፍተኛው የወርቅና ያልማዝ ክምችት መገኘቱ የማዕድን ቁፋሮ እንዲስፋፋና ከመቼውም ጊዜ የበለጠ እንዲፋጠን አድርጓል።ለሥራው መካሄድ ከፍተኛ የሰው ጉልበት ማግኘት አንገብጋቢ ጥያቄ ሆኖ ቀረበ ። ችግሩን በአውሮፓውያን ስደተኞች ብቻ መወጣት አልተቻለም ። በዚህ ምክንያት አፍሪካውያንን በቅጥር ጉልበት ለማሠማራት ቅኝ ገዥዎች እርምጃ መውሰድ ነበረባቸው ።

የነፃ መንግሥታት ፖሊሲና የሠራተኛ መደብ እድገት

ከዚህ በላይ በአፍሪካ አህጉር የፖለቲካ ነፃነት መገኘት ለሠራተኛው ምንዳ እድገት ብሎም ለመደቡ መደላደል አስተዋጽኦ ያደረገ መሆኑ ተመልክቷል ። ሆኖም የፖለቲካ ነፃነት መገኘት ለአፍሪካ የሠራተኛ መደብ መጠናከር አስተዋጽኦ ያደረገው በቀጥታ ለምንዳ ጭማሪ መንስኤ በመሆን ብቻ ሳይሆን ለኢንዱስትሪ እድገት መፋጠንና መስፋፋት፣ ለትምህርት መሻሻል አንፃራዊ አመች ሁኔታን በመፍጠርም ጭምር ነው ።

የአፍሪካ ነፃ መንግሥታት የቅኝ አገዛዝን የኢኮኖሚ አወቃቀር በተለያዩ መንገዶች ለመለወጥ ያደረጉት ጥረት ኢንዱስትሪ በመጠንና በዓይነት እንዲያድግ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ለምሳሌ ፣ በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገሮች ከ1960 እስከ 1975 ባለው ጊዜ በብሔራዊ ምርታቸው ውስጥ እርሻ ነክ ያልሆኑ ውጤቶች ከ20 በመቶ ወደ 30 በመቶ አድገዋል ።

በኢኮኖሚው መስክ በተለይም በኢንዱስትሪው የታየው ዕድገት ማኅበራዊ መስክ ባስከተለው ለውጥ ምክንያት ከ1960 እስከ 1975 ባለው ጊዜ በአፍሪካ አህጉር የምንዳና የደመወዝ ሠራተኞች ቁጥር ከ20 ሚሊዮን ወደ 30 ሚሊዮን ከፍ ብሏል ። በዚህ ወቅት ፣ የሠራተኛው ቁጥር በሰሜን አፍሪካ አገሮች በግምት 11 ሚሊዮን ፣ በሀሩሩ ቀጣና 11 ሚሊዮን ፣ በደቡባዊ አፍሪካ ከምላ ጉደል 10 ሚሊዮን ያህል እንደሚሆን ተገምቷል ።[41] በ1970ዎቹ ውስጥም የምንዳ ሠራተኞች ቁጥር በ11 ሚሊዮን ጭማሪ አሳይቷል ። በአጠቃላይ በ1980ዎቹ መባቻ ላይ 33 ሚሊዮን የምንዳ ሠራተኞች የነበሩ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 4 ሚሊዮን የሚሆኑት በኢንዱስትሪና በትራንስፖርት መስክ የተሰማሩ ነበሩ ።

ነፃ የአፍሪካ መንግሥታት ከ1960ዎቹ ወዲህ ለኢንዱስትሪ እድገት ፣ በተለይም ለመፈብረኪያ ኢንዱስትሪዎች ትኩረት

Digitized by Google

በመስጠታቸው ምክንያት ከፍ ያለ ዕውቀቅ
ና ሙያ ያላቸው ሠራተኞች አስፈላጊነት እየ
ጨመረ መጥቷል። በዚህም ምክንያት በዘመ
ናዊ የመፈብረኪያ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ
የሚሠማሩ ሠራተኞች የሙያ ዕውቀት ፥
ልዩ ሥልጠናና የመደበኛ ትምህርት ደረጃ
እያደገ መሄዱ የሠራተኛውን መደብ የአ
ወቃቀርና የባህል ደረጃም ለውጦታል ።

በሐሩሩ የአፍሪካ ክፍል (በሰሜን አፍ
ሪካ ካሉት እንደግብፅ ከመሳሰሉት አገሮች
ጋር ሲነፃርር) ዘመናዊ የመፈብረኪያ ኢን
ዱስትሪዎች መስፋፋት የጀመሩት በቅርቡ
ቢሆንም ፥ ከ1960ዎቹ በኋላ በነዚህ አካባ
ቢዎችም የመፈብረኪያ ኢንዱስትሪዎች
እያደጉ የመሄድ ዝንባሌ አሳይተዋል። «በ
ሙያ የሰለጠኑ በርካታ ሠራተኞች የሚገ
ኙት በማፈብረኪያ ኢንዱስትሪዎቻቸው
አንፃራዊ ዕድገት በሚታወቁት እንደ ናይ
ጀሪያ ፥ ዚምባብዌና ኬንያ በመሳሰሉት አገ
ሮች ነው ።»[42] በሌሎች የአፍሪካ ሐሩር
ቀጣና ውስጥ ባሉ ሀገሮችም በሠራተኛው
ሙያ በኩል ግልጽ የሆነ ለውጥና መሻሻል
ታይቷል ። ለምሳሌ ከፍተኛ የሆነ የመፈብ
ረኪያ ኢንዱስትሪዎች (አንጻራዊ) ክምችት
ባላት በሴኔጋል ውስጥ የሠለጠኑ ሠራተኞች
ቁጥር ከ35 እስከ 40 በመቶ ሲሆን በአይቮሪ
ኮስት ውስጥ ከ35 እስከ 37 በመቶ የሚ
ሆኑት የኢንዱስትሪ ሠራተኞች የችሎታ
መመዘኛ ፈተና ያለፉና የኢንዱስትሪ ሙያ
ያላቸው ናቸው ።

«ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር
መሣሪያዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል
የሙያ ብቃትና ሥልጠና ብቻ ሳይሆን ተፈ
ላጊው መደበኛ የትምህርት ደረጃም በየጊ
ዜው በማደግ ላይ ይገኛል ።[43] ከነፃነት
በኋላ በቅኝ አገዛዝ ወቅት አፍሪካውያን
መደበኛ ትምህርት እንዳያገኙ የተዘረጋው
የትምህርት ሥርዓት መወገዱ ፥ በተጨማ
ሪም ፥ የዘመኑ የኢንዱስትሪ መዋቅር በቅኝ
አገዛዝ ወቅት ከነበረው የተለየና የላቀ የት
ምህርትና የሥልጠና ደረጃ መጠየቁ አፍሪ
ካውያን ሠራተኞች ለትምህርት የበለጠ እን
ዲተጉ ገፋፍቶአቸዋል ። በዚህ ምክንያት ፥
ወደ ት/ቤት የሚሄዱት ወጣቶች ቁጥር እየ
ጨመረ ፥ በኢንዱስትሪው የወዛደር መደብ
አባልነት የሚቀላቀሉት መሠረተ ትምህር
ትና አጠቃላይ ትምህርት የተማሩ ሰዎች
ቁጥር ከፍ እያለና የማይማን ቁጥር እየቀነሰ
በመሄድ ላይ ይገኛል ። በ1970ዎቹ ግብፅና
ቱኒዝያን በመሳሰሉት አገሮች ወደ ሠራተኛ
ው መደብ የተቀላቀሉት አዳዲስ ሠራተኞች
በአብዛኛው የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ያጠና
ቀቁ ነበሩ ። በተለይም ከ1960ዎቹ በኋላ
ባሉት ወቅቶች ኢንዱስትሪዎች እየተስ
ፋፉ በሄዱባቸው የሐሩሩ ቀጣና አገሮችም
ቢሆኑ በ1940ዎቹ መጨረሻ ላይ አብዛኛ
ዎቹ የኢንዱስትሪ ወዛደሮች ቢያንስ የማን
በብና የመጻፍ ችሎታ ያላቸው ነበሩ ።[44]

የተማሩ ሠራተኞች በሠራተኛው መደብ
ውስጥ መበራከታቸው ስለመደባቸው ታሪ
ካዊ ተልዕኮ ፥ መደባቸው በማኅበራዊ አመ
ራረት ውስጥ ስለሚጫወተው ሚና ፥ ከሌ
ሎች መደቦች ጋርም ስላላቸው ግንኙነት
በኅብረተሰቡ ውስጥ መጫወት ስለሚገባ
ቸው ፖለቲካዊ ተልዕኮ ወዘተ . በሚገባ
ለመገንዘብና መደባዊ ንቃታቸውን ለማዳ
በር ፥ ለሠራተኛው መደብ መደባዊ ጥንካ
ሬና አንድነት መጉልበት እንቅፋት የሆኑ
ልዩ ልዩ ኋላቀር እምነቶችን ለምሳሌ ብሔ
ረተኝነትን ፥ ዘረኝነትን ፥ ወዘተ . . . ለማስ
ወገድ ይጠቅማቸዋል ። ከጐሣ ፥ ከዝምድ
ናና ከአካባቢ ግንኙነቶች ይልቅ በመደብ
አንድነት ላይ የበለጠ ትኩረት እንዲያደ
ርጉ ይረዳቸዋል ።

በአፍሪካ አህጉር ለሠራተኛው መደብ
ዕድገት በአህጉሩ የኢካፒታሊስት የዕድገት
ጐዳና የሚከተሉ ሀገሮች ከፍተኛ አስተዋ
ጽኦ እያደረጉ ነው። የእነኝህ ሀገሮች ፖሊሲ
የብሔራዊ ኢንዱስትሪ ዕድገትን የሚያፈ
ጥን ፥ የቀጥተኛና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን
ኢኮኖሚያዊ ፥ ፖለቲካዊ ፥ ባህላዊና ርዕዮ
ተዓለማዊ ተፅዕና የሚቀንስ ነው ። በነዚህ

Digitized by Google

ዚህ ሀገሮች ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ለማስፋፋትና የሠራተኛውን ትግል ከዓለም ሶሻሊስትና ተራማጅ ኃይላት ጋር ለማስተባበር አመቺ ሁኔታ አለ ።

ለዚህም የኢትዮጵያን ሁኔታ እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ። በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት የሠራተኛውን መደብ ሚና ለማጠናከር ከተወሰዱት አብዮታዊ እርምጃዎች መካከል የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 64/68 እና አዋጁ ቁጥ 222/74 ይገኙበታል ። በአብዮታዊ መንግሥት ፖሊሲ መሠረት የሠራተኛው በማኅበር የመደራጀት መብት ተገቢውን የሕግ ድጋፍ ያገኘው በ1968ቱ የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሲሆን ፣ ከዚያም ወዲህ የተከሰቱት ጉልህ የአደረጃጀትና የአሠራር ድክመቶች በሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 222/74 ተወገደዋል ።

በአዋጁም መሠረት የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ በአገሪቱ በሚካሔደው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ለማጠናቀቅና ለሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ መሠረት ለመጣል በሚደረገው ትግል ውስጥ ድርጅታዊ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊና አስተዳደራዊ ተግባሮች ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆን፣በብሔራዊም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከትግል አጋሮቹ ጋር ግንኙነቱን እንዲያጠናክር ፣ ደረጃ በደረጃም በኢሠፓ አመራር አማካይነት የመሪነት ሚናውን እንዲይዝ አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮለታል ። እነዚህ አዋጆች የጣሉት መሠረትም በኢሠፓ ፕሮግራም ይበልጥ ተጠናክረዋል ። ይህ ፕሮግራም የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የርዕዮተዓለም ፖሊሲ ቀይሷል ። በፖለቲካ ፖሊሲው ከሚተኮርባቸው ነጥቦች መካከል ፣ በአገሪቷ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የፓርቲውን የመሪነት ሚና ማጠናከር ፣ የመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ መብት የሚከበርበት ፣ የብሔረሰቦች እኩልነት ዋስትና የሚገኝበት ፣ የሠራተኛው መደብና የገበሬው የበላይነት የሚሰፍንበት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ማቋቋም ፣ እንደትግሉ የዕድገት ደረጃ የሕዝባዊ ድርጅቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያለማሰለስ ማሳደግና የቢሮክራሲያዊ አሠራርንና ዝባሌን መበጣጠስ ይገኙበታል ። ለዚህም ግብ ተግባራዊነት ሕዝባዊ ድርጅቶች በየፈርጁ ተደራጅተው የበለጠ እየተጠናከሩና ሕዝባዊ መንግሥትም ለመመሥረት የሚያስችሉ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ነው ።

የፓርቲው የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት ፖሊሲ በሚያተኩሩባቸው ነጥቦች መካከል ፣ በየኢኳኖሚ መስኩ ለምርት ኃይሎች ዕድገት አመቺ ሁኔታ በመፍጠርና በማሳደግ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ማጠናቀቅና ለሶሻሊስት ግንባታ ተፈላጊውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት መጣል እንዲሁም በአገሪቷ ውስጥ በመዋቀር ላይ ያለውን የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት የበላጠ ማጠናከር ፣ በማኅበራዊ መስክ የሥራን ክቡርነት ተግባራዊ የሚያደርጉ ፣ ሥራ አጥነትን የሚያስወግዱና የሠርቶ አደሩን ማኅበራዊ ፍላጎት ለማርካት የሚያስችሉ አገልግሎቶችን (ለምሳሌ ፣ የጤና ፣ የትምህርት) አቅም በፈቀደ መጠን ማስፋፋት ይገኙበታል ። የፓርቲውን የኢኳኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ ተነድፎ ከ1977 ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ነው ።

በርዕዮተ ዓለምም መስክ የፓርቲው ፖሊሲ የሠራተኛውን መደብና የሌሎች ሠርቶ አደሮችን ንቃተሕሊና የሚያዳብር ፣ ንቁ ታሪክ ሰሪ የሚያደርግና ሳይንሳዊ ርዕዮተ ዓለምን የሚያስፋፋ ነው ። በኢሠፓ ፕሮግራም ውስጥ እንደተጠቀሰው ።

«ወደ ሶሻሊዝም የሚመራ አብዮትና በተለይም ይህን አብዮት በግንባር ቀደምትነት የሚመራ ፓርቲ ለዓላማው መሳካት ዋስትና ትልሙንና ተግባራቱን በማርክሲዝም ሳይንስ ላይ መመሥረቱ ነው ።» ፕሮግራም ገጽ114

ስለዚህም ኢሠፓ ለዓላማው ተግባራዊነት ዋስትና የሆነውን የርዕዮተ ዓለም ሥራ

Digitized by Google

ለሰፊው ያካሂዳል ። የርዕዮተ ዓለም ሥራ ዓላማ ሳይንሳዊ አስተሳሰብን ማዳበር ፣ ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት አስተዋጽኦ ማድረግና ምርትን ማሳደግ ብሎም በሕሊናዊም ሆነ በቁሳዊ መስኮች የሠርቶ አደሩን የበላይነት ማስፈን ይሆናል ። ይህን ዓላማ በሚመለከት ጓድ ዋና ጸሐፊው ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ላይ እንደሚከተለው ተናግረው ነበር ፦

የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራችን ከአጠቃላይ ጽንሰሃሳቦች ፣ መርሆዎችና ንድፈሳቦች አልፎ ከሕይወት ጋር እየተገናዘበ ራስንና አካባቢን የማወቁና የመመርመሪያ ፣ የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስገኛ ፣ የፈጠራ ችሎታ ማዳበሪያና በአካባቢ የሰው ኃይልና የተፈጥሮ ሀብትን በማቀናጀት የማህበራዊ ችግሮች መፍቻ መሣሪያ ሊሆን ይገባል ። ከዚህ በመለስ አጠቃላይ መፈክሮችን ደጋግሞ በማንሳት ብቻ ሁልጊዜ ሕዝቡን ማንቀሳቀስና መምራት አይቻልም ።

ኢትዮጵያና ሌሎችም መሰል የኢካፒታሊስት የእድገት ጎዳና የሚከተሉ የአፍሪካ አህጉር አገሮች የሠራተኛ መደብ ቆራጥና ንቁ ታሪክ ሰሪነት ትልሙን የጀመረባቸውና ወደፊትም የበለጠ ለመጠናከር ከፍተኛ ተጋድሎ የሚያካሂድባቸው ጉልህ መድረኮች ናቸው ። የእነኝህ አገሮች ሠራተኞችና አጋሮቻቸው የሆኑት ሌሎች ሠርቶ አደሮች በከፋና በመራራ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለተጫነባቸው ለሌሎች የአፍሪካ አገሮች የትግል ሠርቶ አደሮች አርአያነታቸውና የተስፋ ምንጭነታቸው የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም ። የኢካፒታሊስት የእድገት ጎዳና የሚከተሉ የአፍሪካ አገሮች ወደፊት በታሪክ መድረክ መላው የአፍሪካ የሠራተኛ መደብ የሚጫወተውንና መጫወት የሚገባውን ሚና የሚያሳዩ መድረኮች ናቸው ።

ነገር ግን ሁሉም የኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ጎዳና ተከታይ የአፍሪካ ሀገሮች ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ያለአንዳች ክለሳ ያስፋፋሉ ለማለት አያስደፍርም ። ለምሳሌ አንዳንዶቹ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ከብሔረተኝነትና ከሃይማኖታዊ ርዕዮተዓለም ጋር አጣምረው ወይም በርዘው ያስፋፋሉ ። ይህ ጉዳይ አዝማሚያ ቢሆንም እነዚህ ሀገሮች የሚከተሉት ፖሊሲ በአጠቃላይ ሲታይ ለሠራተኛው መደብ የመጠን ዕድገትና የዓይነት ለውጥ (ለምሳሌ በንቃት ከፍግለትና በአንድ አካባቢ በብዛት በመሰብሰብና በተሻለ ሁኔታ መደራጀት ፣ ወዘተ) ለማምጣት የሚረዳ ነው ።

በአፍሪካ አህጉር ከነፃነት በኋላ በኢንዱስትሪና በመሠረተ ልማት በኩል የታየው ዕድገት ሠራተኞች በቁጥር እንዲጨምሩ ከማድረጉም ባሻገር በከተሞችና በትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለሠራተኞች ከምችት መጨመር ከፈጠረው አመች ሁኔታም አኳያ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው ይገባል ። የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ቁጥር ከዚህ ውስጥም በሠራተኛነት የሚሰማራው ቁጥር እየጨመረ በሄደ መጠን የሥራ ኃይል አርባታም ከከተሞች ጋር እየተያያዘ ስለሚሄድ የገጠሩ የሠራተኛ መደብ አዳዲስ አባላት ምንጭነት እየቀነሰ ይሄዳል ። የከተማው ሠራተኛ ልጆች ራሳቸው በሠራተኛነት የሚሰማሩበት ሁኔታ ስለሚጨምር የቤተሰብ አመጣጣቸውም ከሠራተኛው መደብ ይሆናል ።

Digitized by Google

ምንም እንኳን ከኢኮኖሚያዊ ኋላቀርነትና ከዚህም ከሚመነጨው አዝጋሚ የኢንዱስትሪና የሠራተኛ መደብ ዕድገት የተነሳ የአፍሪካ የሠራተኛ መደብ ዛሬም ከጠቅላላው ሕዝብና ዕድሜያቸው ለሥራ ከደረሱ ሰዎች መካከል አነስተኛውን ቁጥር የያዘ ቢሆንም ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሚናው ከቁጥሩ አንፃር ብቻ መታየት የለበትም ። የሠራተኛውን መደብ ጥንካሬ በማሳደግ ላይ የሚገኙት ሌሎች ምክንያቶች ለምሳሌ ፣ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መስፋፋት ፣ የሠራተኛ ማኅበራት ድርጅታዊ ጥንካሬ መጨመር ፣ የሠራተኞች መጠን ማደግና ሌሎች ሠርቶአደሮችንም አስተባብሮ ከጐኑ ለማሰለፍ አመች ሁኔታ የሚፈጥሩለት መሆኑም መታወቅ አለበት ።

የግርጌ ማስታዎሻ

1. Marx and Engles, "The Holy Family of Critique of Critical Criticism," in Marx and Engels *Collected Works*, Vol. 4, New York, 1976, p. 36.
2. Tomas Szentes, *The Political Economy of Underdevelopment*, Third Edition (Budapest: Akademia, 1976), p. 36.
3. *Ibid*.. p. 36.
4. Richard Sand Brook and Robin Co hen, "Introduction" in *The Development of an African Working Class*, (London: Longman Group Limited, 1975), p. 13.
5. Ükandi G. Ðamachi and others, Industrial Relations in Africa (London: The McMillan 1979), pp. 4-5.
6. *Ibid.*
7. Arrighi and Soul.
8. Luke Malaba "Supply, Control and organization of African Labour in Rhodesia," *In A Review of African Political Economy*, Vol. XVIII, (May-August 1980), p. 9.
9. Zagladin and others, *The International Working Class Movement Problems of History and Theory*, Vol. 2, (Moscow: Progress Publishers, 1976), p. 523.
10. Malaba, p. 10.
11. R. Sand Brook and R. Cohen, "Introduction" in *The Development of an African Working Class in Class Formation* and acion, (London: Longman Group Limited, 1975), pp. 14-16.
12. Sharen Sticher, "The Development of Working Class, "in *The Development of an African Working Class in Formation and Action*, R. Sand Brook an and Cohen, ed., p. 24.
13. *Ibid.*
14. Y.M. Ivanov, p. 14.
15. Zaglandin and others, p. 619.
16. *Ibid.*
17. Deboraha Bryceson, "Proletarinization of Tanzanian Women" in *A Review of African Political Economy*, No. XVII, (January-April 1980), p. 13.
18. *Ibid.*
19. G. Arrighi, p. 34.
20. D. Bryceson, pp. 13-14.
21. Y.M. Ivanov, pp. 13-14.
22. D. Bryseson, pp. 15-16.
23. R.S. and Sofer, "Jinja Transformed a Social Servey of Multilateral Township, "p. 4, Quoted in Y.M. Ivanov, *Agrarian Reforms and Hired Labour in Africa*, (Moscow: Progress Publishers, 1978), p. 24.
24. G. Arrighi, "International Corporations Labour Aristocracies and Economic Development in Tropical Africa," In Imperialism and Underdevelopment (Monthly Review Press, 1973), p. 228.
25. *Ibid.*, p. 229.

Digitized by Google

26. Sharon Sticher, *Migrait Labour in ..enya: Capitalism and African Response*, 1895-1975 (*London*: Longman Group Ltd. 1982), p. 26.

27. Sharon Sticher, p. 15.

28. See, for example, Richard Sand Brooke, *Proletarians and African Capitalism*: The Kenyan Case 1960-1975 (London; Cambridge University, Press, 1975), p. 11.

29. *Ibid.*, p. 15.

30. See Giovanni Arrighi, p. 231-232.

31. R. Sand Brook, p. 125.

32. Sharon Sticher, p. 125.

33. R.D. Grillo, *African Railway Men* (London: Cambridge University, 1973), p. 51.

34. Sharon Sticher, p. 133-139.

35. G. Arrighi, p. 133-139.

36. *Ibid.*

37. *Ibid.*

38. Y.M. Ivanon.

39. *Ibid.*

40. R. Sand Brook, p. 17.

41. *Documents of Communist Parties and the National Revolutionary Movement of Asian and African Countries*, Statni Pedagogicke Naklada Telsrvi, Prague, p. 180.

42. Leonid Fridman and Sergei Vernin, "Industrialisation and the Proletariat of the Newly-Free Countries Today" *Asia and Africa Today*, Vol. 1, January-February, 1981, p. 5.

43. *Ibid.*, p. 6.

44. *Ibid.*

45. *Ibid.*, p. 7.

46. *Ibid.*, p. 7.

Digitized by Google

በሽግግር ወቅት የሕግ ሚና

ፈለቀ ዋጉ

የሽግግር ወቅት ሁለት ትርጉሞች አሉት ። 1ኛ/ የሠራተኛ መደብ የፖለቲካ ሥልጣኑን ከጨበጠ በኋላ ለሶሻሊስት ግንባታ መሠረት የሚጥልበትን ጊዜ ያመለክታል ። 2ኛ/ የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር የመጀመሪያው ደረጃ የሆነው ሶሻሊዝምም የሽግግር ወቅት ይባላል ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሽግግር ወቅት ሲባል እንደአገባቡ ሁለቱንም ትርጉሞች የሚያቅፍ ቢሆንም በአብዛኛው ሁለተኛውን ትርጉም ይይዛል ።

የሽግግር ወቅት ማንኛውም ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሚመሰርት አገር በውስጡ ማለፍ ያለበት ወቅት ነው ። በመሆኑም ይህ ወቅት አስፈላጊ የሚሆነው በካፒታሊስት ዕድገት ደረጃ ይላ ላሉት አገሮች ብቻ ሳይሆን ቅድመ ካፒታሊስት ወይም ከፊል ካፒታሊስት ዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙትም ነው ። ሌኒን የዘመነ ኢምፔሪያሊዝምን ነባራዊ ሁኔታ በማርክሳዊ ሳይንስ ተንትኖ በማጥናት ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር ባንድ ወይም ካንድ በሚበልጡ አገሮች ሊካሄድ ይችላል ብሏል ። ኬ ዛራዶቭ የሚባለው የሶቭየት ኅብረት ምሁር የሽግግር ወቅት ምን እንደሚያቅፍ ሲገልጽ፣ «ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው የሽግግር ወቅት ከካፒታሊስት ወይም እንዲያውም ከቅድመ ካፒታሊስት አገሮች እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ሶሻሊዝምን የገነቡትን ሁሉ የሚያጠቃልል ዓለምአቀፋዊ የታሪክ ክፍለ ጊዜ ነው»[1] ብሏል ።

የሽግግር ወቅት ዕድገት አጠቃላይ በሆኑ ሕጐች የሚመራ በመሆኑ በእያንዳንዱ አገር ነባራዊ ሁኔታዎች ምክንያት በነገሮች አመጣጥ ቅደም ተከተል ወይም ቅርጽ ልዩነት ሊኖር ቢችልም በመሠረታዊ ይዘቱ ተመሳሳይነት አለው ። በዚህ ምክንያት ነው የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ዕድገት መሠረታዊ ሁኔታዎችና አቅጣጫዎች በሁሉም አገሮች

Digitized by Google

በአጠቃላይ ተመሳሳይ ናቸው የሚባለው ።

የማይለወጡና በሁሉም አገሮች የሚከሰቱ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ያእድገት ሁኔታዎችና አቅጣጫዎች ውስጥ የሚገኙት ሉት ይገኙባቸዋል ።

1. ወደሶሻሊዝም ለመድረስ በሚደረጉ የትግል ደረጃዎች ሁሉ የሠራተኛው መደብና የርሱ ፓርቲ የመሪነት ሚና መጫወት ፤
2. በወዛደሩና በገበሬው እንዲሁም በሌሎች የኅብረተሰቡ ሥርተአደር ክፍሎች መካከል የተጠበቀ አንድነት መፍጠር ፤
3. የካፒታሊዝምን የመንግሥት መዋቅር ደምስሶ በምትኩ የወዛደሩን የበላይ ገዥነት መንግሥት ማቋቋም ፤
4. የዋና ዋና የምርት ማከናወኛ መሣሪያዎችን በግል ንብረትነት መያዝን አስወግዶ በምትኩ ማኅበራዊ ባለቤትነትን ማጠናከር ። [2]

የሽግግር ወቅት በሶስት ደረጃዎች ማለትም የመጀመሪያው ፤ የመካከለኛውና የመጨረሻው በማለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል ።

—የመጀመሪያው የሽግግር ክፍለ ጊዜ በኢኮኖሚው ውስጥ የመንግሥት ይዞታ ፤ የግልና የጥቃቅን ሸቀጥ አምራቾች ይዞታ የሚገኝበት ጊዜ ሲሆን ይህም ብሔራዊ ወይም አዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እስከሚገባደድበት ጊዜ ድረስ ያለው ነው ። ይህ ጊዜ አሮጌው ሥርዓት ጠንካራ ሆኖ የሚታይበት ነው ።

—የመካከለኛው የሽግግር ወቅት ሶሻሊስት አብዮት የሚካሄድበት ክፍለ ጊዜ ነው ። በዚህን ጊዜ ኢኮኖሚው በመንግሥትና በኅብረት ይዞታዎች ብቻ ተጠቃልሎ የሚገኝበት በመሆኑ በአሮጌው ሥርዓት ገጽታዎች ላይ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ገጽታዎች የበላይነት የሚያገኙበት ነው ።

—የመጨረሻው የሽግግር ወቅት ክፍለ ጊዜ የሽግግሩ ወቅት የሚያበቃበትና የዳበረ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ተገንብቶ የሚገኝበት ነው ። በዚህ ጊዜ ኢኮኖሚው የመንግሥት ይዞታዎች በከፍተኛ ደረጃ ዳብረው የሚገኙበትና ዘመናዊ የወልአርሻ ይዞታዎች ተስፋፍተው የሚታዩበት ጊዜ ነው ። በዚህም ምክንያት ሶሻሊስት ባህል ፖለቲካና ርዕዮተ ዓለም በሚገባ ይሰፍናሉ ።

ሕግና መንግሥት

መንግሥትና በመንግሥት የሚወጣ ሕግ በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ክስተቶች ናቸው ። መንግሥትና ሕግ ከመደብና ከመደብ ትግል ውጭ ሊሆኑ አይችሉም ። የመደብ ትግል ባለበት ኅብረተሰብ ሁሉ የማን መንግሥት? የማን ሕግ ? መባሉ ግድ ነው ። ስለዚህ መንግሥትና ሕግ መጠናት ያለባቸው ካሉበት ሥርዓተ ማኅበርና ከሚያገለግሉት መደብ አንፃር ነው ።

በኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ ስለመንግሥት ምንነት ሳይንሳዊ ትንተና ለማቅረብ የቻለው ማርክሲዝም ሌኒንዝም ነው ። ፍሬደሪክ ኤንግልስ የቤተሰብ ፤ የግል ንብረትና የመንግሥት አመጣጥ በሚለው መጽሐፉ ስለመንግሥት ያደረገውን ሳይንሳዊ ትንተና ሲያጠቃልል ፦—

ስለዚህ መንግሥት በኅብረተሰቡ ላይ ከውጭ የተጫነ ነገር አይደለም ። ... ይልቁንም በተወሰነ የዕድገት ደረጃ ከኅብረተሰቡ የሚመነጭ ነው ። የመንግሥት መኖር ኅብረተሰቡ ሊያስወግዳቸው በማይችሉና በማይፈቱ ቅራኔዎች መተብተቡን ፤ በማይታረቁ ተቃራኒ ኃይሎች መከፈሉን ያረጋግጣል ። ነገር ግን እነዚህ በኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ምክንያት የተፈጠሩ የማይታረቁ መደቦች እርስ በርሳቸው እንዳይጠፋፉ ፤ በመካከላቸው ያለውን ግጭት ለማቀዝቀዝና ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ የሚችል ከኅብረተሰቡ በላይ ያለ የሚመስል ኃይል መኖርን አስፈላጊ አደረገው ። ይህም ከኅብረተሰብ ወጥቶ ራሱን ከኅብረተሰቡ በላይ ያስቀመጠውና በየጊዜው ከኅብረተሰቡ እየራቀ የሚሄደው ኃይል መንግሥት ነው [3] ብሏል ።

Digitized by Google

መንግሥት በኅብረተሰብ ውስጥ የማይታረቁ ትራኔዎች በመኖራቸው ምክንያት የተከሰተ ሲሆን ዓላማውም የገዥውን መደብ ጥቅም እየጠበቀ ትራኔው እንዳይባባስ ማድረግ ነው ። መንግሥት ገዥው መደብ ተገዳሪውን መደብ የሚገዛበት፣ የሚጨቁንበትና ፍላጐቱንና ፈቃዱን በማስገደጃ ኃይል አማካይነት የሚያስፈጽምበት ድርጅት ነው ። ይህንንም ለመፈፀም ያስችለው ዘንድ መንግሥት የታጠቀ ቋሚ ሠራዊትና ፖሊስ ፣ ለገዥው መደብ ፍላጐትና ፈቃድ ግለት ለሕጉ የማይገዙትን መቅጫ ፍርድ ቤቶች ፣ ማሠሪያ ወህኒ ቤቶችና ሌሎችም መዋቅሮች አሉት ። መንግሥት የመደብ ትግል ውጤት የሆነ ከኅብረተሰብ ተወልዶ ራሱን ከኅብረተሰብ ያገለለ ፣ አንዱ መደብ ሌላውን የሚጨቁን የተደራጀ አካል ነው ።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ኅብረተሰቡ የውጭ ጥቃትን የሚከላከለው ሁሉም በአንድነት ሆኖ እንጂ የተለየ እንደመንግሥት የተደራጀ አካል አልነበረውም።«የምርት መገልገያዎች በጋራ ባለቤትነት ሥር በነበሩበትና የምርት ውጤትም የኅብረተሰብ የጋራ ሀብት በነበሩበት በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሰው ልጅ «መንግሥት» የሚባል አካል ሳያስፈልገው ኑሮውን መምራት ይችል እንደነበረ በታሪክ ጥናት የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ዛሬም ቢሆን የዚህ ሥርዓት ቅሪቶች በሚገኙበት አካባቢ ይህ ሁኔታ በግልጽ ይንፀባረቃል ።» [4] በተጨማሪም የግል ማምረቻ መሣሪያዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ኅብረተሰቡ ንብረትነት ሲዛወሩ ፣ የምርት ግንኙነትም ሙሉ በሙሉ ማኅበራዊ ሲሆን መደቦች ይከስማሉ ። የመደቦች መከሰምም የመንግሥት መከሰምን ያስከትላል ። ስለዚህ መንግሥት በግል ንብረትና በመደቦች መኖር ምክንያት እንደተፈጠረ ሁሉ የግል ንብረትና መደቦች ሲከስሙ አብሮ የሚከስም ማኅበራዊ ክስተት ነው ።

ሃሳባውያን መንግሥት ዘላለማዊ ነው ብለው ያምናሉ ። እነርሱም መንግሥት የሚፈጠርበት ሁኔታ አይገነዘቡትም ወይም ለመገንዘብ አይፈልጉም ። ከዚህም እምነታቸው በመነሳት ያለመንግሥት ኅብረተሰብ ሊኖር አይችልም ወደሚለው መደምደሚያ ይደርሳሉ ። ይህንን መደምደሚያ መሠረት በማድረግ እስካሁን ድረስ ያሉትን የመንግሥታት ዓይነቶችን በዓይነትና በይዘት የሚለዩ ሳይሆን በቅርፅ ብቻ እንደሚለዩ አድርገው ያቀርባሉ ።

የሶሻሊዝም ደጋፊዎች ነን የሚሉ የ«ግራ» እና የቀኝ አድርባዮችም ለመንግሥት የሚሰጡት ትርጉም ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ትርጉም ጋር የሚቃረን ነው ። የቀኝ አድርባዮች መንግሥት የገዥው መደብ ሌሎችን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለመጨቆን የሚገለገልበት መሣሪያ መሆኑን በመካድ በመደቦች መካከል የተፈጠረውን የማይጣጣም ቅራኔ ለመፍታት ወይም ለማስታረቅ የሚጠቅም መሣሪያ ነው ይላሉ ። የ«ግራ» አድርባዮችም የሠራተኛው መደብ አሮጌውን መንግሥት ከደመሰሰ በኋላ የራሱን መንግሥት ማቋቋም አያስፈልገውም የሚል አስተያየት አላቸው ።

ሃሳባውያንም ሆኑ የ«ግራ»ና የቀኝ አድርባዮች ስለመንግሥት የሚሰጡት ትርጉም በሳይንሳዊ ትንተና ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በስሜት ፣ በምኞትና ጥቅማቸውን በሚያንፀባርቅ ፍላጐት ላይ የተመሰረተ ነው ። የሠራተኛው መደብ የቡርዧውን

Digitized by Google

መንግሥት በአብዮታዊ አመፅ ካስወገደ በኋላ የሰውን ዘር በሙሉ ነፃ ለማውጣት የሚያስችለውን ትግሉን ለመቀጠል የወዛደሩን የበላይ ገዥነት መንግሥት ያቋቁማል ። ይህ ወዛደሩ ራሱን እንደ ገዥ መደብ አደራጅቶ የሚያቋቁመው መንግሥት በቡርዧው ከየአቅጣጫው የሚቀርብበትን ተቃውሞ ለመቋቋምና የቡርዧውን መደብ ለመደምሰስ የሚገለልበት አዲሱን ሶሻሊስት ሥርዓት ለመገንባት የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው ።

የወዛደሩ መደብ መንግሥት የብዙኃኑን ሕዝብ ጥቅም በማስከበር የሰውን ልጅ ከብዝበዛ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነፃ ለማውጣት በቡርዧው መደብ ላይ የሚያካሂደው ጭቆና ከቀደምት መንግሥታት ልዩ ያደርገዋል ። ይህ መንግሥት የግል ባለሀብትነትን ደምስሶ ፣ ሰውን በሰው መበዝበዝ አስወግዶ ፣ በአጠቃላይ የሰውን ዘር ነፃ የማውጣት ተልዕኮውን የሚፈጽም ሲሆን በመጨረሻም ከመደቦች መክሰም ጋር የሚከስም ነው ።

ሕ ግ

ሕግ ነባራዊና በመንግሥት የሚወጣ ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል ። በሁለቱም መካከል ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት አለ ። መንግሥት የሚያወጣው ሕግ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ከነባራዊ (ከተፈጥሮና ከማኅበራዊ ሳይንስ) ሕግ ጋር መጣጣም አለበት ። በመንግሥት የሚወጣው ሕግ ሳይንሳዊ ሕግን በሚገባ አውቆና ተረድቶ በማይቃረን ሁኔታ ከተቀረፀ በነባራዊው ሕግ ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል ።

ይህ በሁለቱ መካከል ያለውን ተዛምዶ ያሳያል ።

ነባራዊ ሕጎች በሙሉ የነባራዊ እውነታና ክስተቶች ነፀብራቅ እንደመሆናቸው ከሰው ፍላጐት ውጭ የሚኖሩና የሚሠሩ ናቸው ። ሰው እነዚህን ነባራዊ ሕጎች ለማግኘት ፣ ለማወቅ ፣ ለማጥናት ፣ ለኅብረተሰብ በሚያገለግሉት ሁኔታ ለመጠቀም ይችላል እንጂ ሊለውጣቸው ፣ እንደ ፍላጐቱ ሊቀርጻቸው ወይም ሊፈጥራቸው አይችልም ። [5] ለምሳሌ በካፒታሊስት ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ውስጥ የዋጋ ሕግ ከሸቀጥ ምርት ጋር የተያያዘና የሸቀጥ ምርት እስካለ ድረስ ከሰዎች ፍላጐት ውጭ የሚኖርና የሚሰራ ሕግ ነው ። ነገር ግን ይህን ሕግ ሰው በሚገባ አውቆት፣ማለትም ሕጉን እንዲኖርና እንዲሠራ የሚያደርገው የሸቀጥ ምርት መሆኑን በመረዳት የሸቀጥ ምርት በማኅበራዊ ምርት እንዲተካ እያደረገ የሸቀጥ ምርት እንዲወገድና የኮሚኒስት ሥርዓት እንዲመሠረት በማድረግ የዋጋ ሕግ እንዳይሠራ ለማድረግ ይችላል ።ይህን ለማድረግ በመንግሥት የሚወጣው ሕግን ጠቃሚ መሳሪያ ነው ። በዚህ ሁኔታ ነባራዊ ሕግ በመንግሥት በሚወጣ ሕግ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያደርግ ሁሉ በመንግሥት የሚወጣው ሕግም ነባራዊ ሕግ ለኅብረተሰቡ በሚጠቅም ሁኔታ ታስቦ የወጣ ከሆነ በነባራዊው ሕግ ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል ። ለምሳሌ ለቡርዧው መንግሥት ሕጎች መሠረቱ የቡርዧውን ሥርዓተ ማኅበር የምርት ግንኙነት የሚቆጣጠረው ነባራዊ ሕግ ነው ። ሆኖም በቡርዧው መንግሥት የወጣው ሕግ የቡርዧ የምርት ግንኙነት ስፋትና ጥልቀት እንዲኖረው በማድረግ በነባራዊ ሕግ ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል ። እነዚህ ሁኔታዎች በነባራዊ ሕግና በመንግሥት በሚወጡ ሕጎች መካከል ያለውን ግንኙነትና መተሳሰር መረዳት ይቻላል ።

እዚህ ላይ የነባራዊ ሕግ ሁኔታ የተነሳው በመንግሥት ከሚወጣው ሕግ ጋር ያለውን ግንኙነት በማሳየት የሕግን ትርጉም አስፍቶ ለማሳየት ያህል እንጂ ስለነባራዊ ሕጎች ሁኔታ በዝርዝር ለማስረዳት አይደለም ። እንዲያውም በስፋት ለመግለጽ የተፈለገውና የሚፈለገው በመንግሥት

Digitized by Google

የሚወጣውን ሕግ ነው ። ስለሆነም በመንግሥት የሚወጣው ሕግ ትርጉም ምን እንደሆነ ዘርዘር አድርገን እንመለከት ።

መንግሥት ኅብረተሰብ በመደብ በመከፋፈሉ ምክንያት እንደተፈጠረ ሁሉ ሕግም የግል ባለሀብቶችን መደብ ፍላጐትና ፈቃድ ለማሟላት ከመንግሥት ጋር አብሮ የመጣ ነው ። ሕግ የገዥው መደብ ፍላጐትና ፈቃድ ምን እንደሆነ በመንግሥት አማካይነት ለኅብረተሰቡ የሚገለጽበት ስልት ነው። «ሕግ ... ከመደቦችና ከመንግሥት ጋር አብሮ ተከሰተ ። ሕግ የገዥውን መደብ ፍላጐት በሕግ ቅርጽ የሚገለጽ ነው ። በመሆኑም የገዥውን መደብ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ፍላጐቶች የሚያንፀባርቅ ነው ።»[6]

ሕግ በየትኛውም ሥርዓተ ማኅበር ቢሆን የገዥውን መደብ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጐቶች የሚገልጽ በመሆኑ በእያንዳንዱ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ባሉት ወይም በነበሩት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ላይ ተመሥርቶ የሚወጣ የገዥው መደብ ፍላጐትና ፈቃድ መግለጫ ነው ። የኅብረተሰቡ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦች በሕግም ላይ ለውጦችን ያስከትላሉ ። ሕግ ከላዕላይ መዋቅሮች ማለትም ከፖለቲካ፣ ከርዕዮተ ዓለም ፣ ከባህል ወዘተ... ጋር ያለ እንደመሆኑ ከኤኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ዕድገት ጋር የተያያዘና አብሮ የሚያድግ ነው ።

የሕግ ትክክለኛ ትርጉም ግልጽ ሊሆን የሚችለው ራሱን ከፈጠረው ከመደብ አንፃር ሲታይ ነው ። ሕግን ከመደብና ከመደብ ትግል ውጭ ራሱን የቻለ አድርጐ በመውሰድ ማጥናቱና መመርመሩ ኢሳይንሳዊ ነው ። ስለዚህ ፡-

ሕግ የበላይነት የያዘውን መደብ ፈቃድ የሚገልጽና በመንግሥት ሥልጣን የተቋቋሙ ወይም የፀደቁ ፣ ለተፈጻሚነታቸውም ዋስትና መንግሥት ያለው የአስገዳጅነት ኃይል የሆነ፣ የበላይነትን ለያዘው መደብ ተስማሚና ጠቃሚ የሆኑ ማኅበራዊ ግንኙነቶችንና ቅንጅቶችን ለመጠበቅ ፣ ለማረጋገጥና ለማዳበር የታቀዱ የምግባር ደንቦች/ገዕዛት/ስብስብ ነው።[8]

ከዚህ በላይ ሕግና መንግሥት ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለበት ጊዜ ጀምሮ ባንድነት የተከሰቱ መሆናቸው ተመልክቷል ። ሁለቱም የገዥው መደብ ጥቅም ማስከበሪያ ናቸው ። ለሕግ ተፈፃሚነት መንግሥት መኖር አለበት ። እንደዚሁም መንግሥት ለመኖርና የገዥውን መደብ ጥቅም ለማስከበር በሕግ መጠቀም አለበት። ስለዚህ አንዱ ያለሌላው ሊኖር አይችልም ።

እስካሁን ድረስ በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ የተለያዩ መንግሥታትና ሕጎች ታይተዋል ። የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበር የባሪያ አሳዳሪ መንግሥትና ሕግ ነበረው ። የፊውዳሉና የቡርዧው ሥርዓተ ማኅበራትም የየራሳቸው መንግሥትና ሕግጋት ነበራቸው ። ሶሻሊስት ኅብረተሰብም ሶሻሊስት መንግሥትና ሕግ አሉት ። እነዚህ መንግሥታትና ሕግጋት እንደየሥርዓተ ማኅበሩ ይዘታቸው የተለያየ ነው ። በአጠቃላይ ግን መንግሥትና ሕግ የመደብ መጨቆኛ ሁለት ገጽታዎች ሆነው ቆይተዋል ።

በሽግግር ወቅት የሕግ ሚና

በሽግግር ወቅት የሚኖረው ዋንኛው ቅራኔ በመወገድ ላይ ባለው ካፒታሊዝምና በሚያደገው ሶሻሊዝም መካከል ነው ።ካፒታሊዝም የራሱ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ርዕዮተዓለማዊ ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ያሉት ሲሆን ፣ አዳጊው ሶሻሊዝም ደግሞ በተቃራኒነት የራሱ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊ ፣ ርእዮተዓለማዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ይኖሩታል ። ካፒታሊዝም እየተሸነፈና እየተዳከመ የሚሄድ ሲሆን ሶሻሊዝም ደግሞ በተቃራኒው እያደገ ፣ እየተጠናከረና እያሸነፈ የሚሄድ ነው ። በዚህ ሂደት ውስጥ ሕግ የሚኖረው የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው ?

Digitized by Google

በሽግግር ወቅት በሕግ መስክ የሚኖሩት ቅራኔዎች በአዲስና በአሮጌ ሕጎች መካከል በሚካሄደው ትግል ይንፀባረቃሉ። በአሮጌና በአዲስ ሕጎች መካከል ያለው ጊዜያዊ ጐን ለጐን መኖር በሽግግር ወቅት በሚኖሩት ታህታይ መዋቅሮች መካከል ያለውን አንድነትና ቅራኔ የሚያንፀባርቅ ነው ። በእነዚህ በሁለቱ ተቃራኒ ገጽታዎች መካከል የሚካሄደው ትግል ለካፒታሊዝም መወገድና ለሶሻሊዝም መመሥረት የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል ። በአንፃሩም የሽግግር ወቅት የሕግ ሚና በግልጽ ሊታይና ሊታወቅ የሚችለው የሽግግሩ ወቅት ታህታይና ላዕላይ መዋቅሮች ሁኔታ ግልጽ ሲሆን ነው ።

ለአንድ ኅብረተሰብ መሠረትና የእድገት መንስኤ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው አንድነትና ትግል ነው ። የኅብረተሰቡ ታህታይ መዋቅሮች የሚባሉትም የምርት ኃይሎችንና የምርት ግንኙነቶችን የሚመለከቱ መዋቅሮች ናቸው። የእነዚህ መዋቅሮች ሁኔታ ነው በላዕላይ መዋቅሮች የሚንፀባረቀው ። ላዕላይ መዋቅሮች የሚባሉት ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉት የሕግ ፣ የፖለቲካ ፣ የርዕዮተ ዓለም ፣ የባሕልና የማኅበራዊ ኑሮ ሥርዓቶች ናቸው ።

ሕግ ከላዕላይ መዋቅሮች አንዱ እንደመሆኑ ለመከሰቱ ታህታይ መዋቅር ምክንያት ቢሆንም የታህታይ መዋቅሮችን ዕድገት የመርዳት ወይም የመቃረንም ፣ የማፋጠን ወይም የመግታት ሚና ይጫወታል። በዚህም ምክንያት በላዕላይ መዋቅሮችም ለውጥ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ ይችላል። እዚህ ላይ አንድ መታወስ ያለበት ነገር «ነባራዊ ሁኔታዎች አዲስ ማኅበራዊ ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ ለማድረግ የተመቻቹ ካልሆነ በቀር ሕግ ምንም ዓይነት ማኅበራዊ ግንኙነቶች መፍጠር»[9] አለመቻሉ ነው ።

አንድ ኅብረተሰብ ከካፒታሊዝም ተነስቶ በቀጥታ ሶሻሊስት አብዮትን በማካሄድ የሚመሠርተው መንግሥት የወዛደሩ የበላይ ገዢነት እምባገነን መንግሥት ነው ። ነገር ግን ኅብረተሰቡ ትግሉን በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የጀመረ ከሆነ መጀመሪያ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን ከዚያም ሶሻሊስት አብዮትን ማካሄድ ስላለበት የሚያቋቁመው መንግሥት ቅርጽና ይዘት እንደ አብዮቱ የእድገት ደረጃ ይወሰናል። ይህም ማለት በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጊዜ የኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ ቅድመ ካፒታሊስት ወይም ከፊል ካፒታሊስት ስለሚሆን የወዛደሩ መደብ ብቻውን የበላይ ገዥነት መንግሥት ማቋቋም አይችልም ። ስለሆነም የወዛደሩ መደብ ከገበሬው ጋር ግንባር በመፍጠርና ሌሎች ጭቁን የኅብረተሰቡን ክፍሎች በማስተባበር የወዝአደሩንና የገበሬውን ወይም ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዢነት የሽግግሩ ወቅት የሶሻሊስት አብዮትን በማካሄድ የተጀመረ ከሆነ ጭቁኑን የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበር የወዛደሩ የበላይ ገዢነት መንግሥት ይቋቋማል ።

የሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትና የወዛደሩ የበላይ ገዥነት መንግሥት የሚያወጧቸው ሕጎች ተመሳሳይ ሊሆኑ አይችሉም ። ምክንያቱም ማንኛውም መንግሥት የሚያወጣው ህግ በመንግሥቱ ውስጥ የሥልጣን ባለቤት የሆኑትን መደቦች መሠረታዊ ጥቅም የሚያፀባርቅ[10] በመሆኑ ነው ። ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሚያወጣው ሕግ ያቀፉቸውን መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም የማይቃረን መሆን ሲገባው የወዛደሩ የበላይ ገዥነት መንግሥት ደግሞ የሚያወጣው ህግ የወዛደሩን መደብ ዓላማና ተልእኮ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ነው ። ስለሆነም በዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅትና በሶሻሊስት

አብዮት ወቅት የሚወሰዱት ርምጃዎችና
የሚቋቋሙት መንግሥታት የተለያዩ እንደ
መሆናቸው ሕጎቹም እንደዚያው የተለያዩ
መሆናቸው መዘንጋት የለበትም ።

ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወደ ሶሻሊስት
አብዮት ለመድረስ የሚቀየስ አብዮት እን
ደመሆኑ በዚያን ወቅት የሚወጡት ሕጎች
ዲሞክራሲያዊ አሠራር እንዲሰፍንና እንዲ
ለመድ ፣ እንዲሁም ለሶሻሊስት አብዮት ኢኮ
ኖሚያዊ ፣ ባህላዊ ፣ ቴክኒካዊና ፖለቲካዊ
መሠረት እንዲጣል የሚረዱ መሆን አለባ
ቸው። በዲሞክራሲያዊ አብዮት ጊዜ በተላይ
ወሳኝ በሆነው ኢኮኖሚ ረገድ በመንግ
ሥት ፣ በኅብረትና በግል ይዞታ ሥር የሚ
ገኙትን የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን የሚመለ
ከቱ ይሆናሉ ማለት ነው ።

ይሁንና በሶሻሊስት አብዮት ጊዜ በኢኮ
ኖሚ በኩል የመንግሥትና የኅብረት ይዞታ
ዎች ብቻ እንዲኖሩ የሚደረግበት፣ በፖለቲካ
የወዛደሩ የበላይ ገዥነት ሙሉ በሙሉ የሚ
ረጋገጥበት፣ የወዛደሩ ባህልና ርእዮተ ዓለም
ሙሉ ልዕልና እንዲያገኝ የሚደረግበት በመ
ሆኑ በወቅቱ የሚወጡ ሕጐች ይህንን ትግ
ል የሚያግዙ መሆን ያለባቸው ናቸው ።

ወደ ሶሻሊዝም በሚደረግ ሽግግር ወቅት
የሚቋቋመው መንግሥት የሚመራው በሠ
ራተኛው መደብ ፓርቲ ነው ። ፓርቲ
ውም ኢኮኖሚን ፣ ፖለቲካን ፣ ባህልን ፣ ርእ
ዮተ ዓለምንና ማኅበራዊ ሕይወትን በሚመለ
ለከት በማርክሲዝም ሌኒንዝም ሳይንስ ላይ
በመመሥረት የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ
ፕሮግራም ያወጣል ። ለኅብረተሰቡ ዓላማ
ውን አሳውቆ እንደየወቅቱ ሁኔታ መውጣት
የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ፣ የሚወገ
ዱትንና የሚጠናከሩትን ፣ ዕድገት ጐታ
ችና አራማጅ አሠራሮችንና አዝማሚያ
ዎችን በመለየት አብዮቱን የሚያራምዱት
ንና የሚያጠናክሩትን በሕግ እንዲታገዙና
ሌሎቹም እንዲወገዱ ያደርጋል ።

በአጠቃላይ በሽግግር ወቅት የሠራተኛው
መደብ ፓርቲ ሕዝባዊ ድርጅቶች ከመንግ
ሥት ጋር በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ የሚና
ራቸውን ሚና ዘርዝር የሚያመለክተው
በወቅቱ መኖር የሚገባቸውን የኢኮኖሚ ፣
የባህል ፣ የማኅበራዊ ሕይወት ፣ የርዕዮተ
ዓለም ፣ የመከላከያና የፖለቲካ መመሪያ
ዎችን የሚገልፀውና መመሪያዎችንም የኅ
ብረተሰቡ አባል ተግባራዊ እንዲያደርግ
የሚያስገድደው በሕግ ነው ። ይህን በበ
ለጠ ለመረዳት በሽግግር ወቅት ሕግ በኢ
ኮኖሚ ፣ በፖለቲካ ፣ በባህል ፣ በማኅበራዊ
ሕይወት በርዕዮተ ዓለምና አንፃር የሚጫወ
ተውን ሚና ዘርዝር በማድረግ ለመመልከት
እንሞክር ።

<u>በኢኮኖሚ፣</u> የገዥ መደብን ኢኮኖሚያዊ
ጥቅም ለመጠበቅ የወጡ ሕጎች በሽግግር
ወቅት የሠራተኛውን መደብና የሌሎች የተ
ጨቆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ኢኮኖሚያዊ
ጥቅም ለመጠበቅ ከሚወጡ ሕጎች ጋር ይቃ
ረናሉ ። ይህም ቅራኔ በሽግግሩ ወቅት የሚ
ኖሩትን ኢኮኖሚያዊ ቅራኔዎች ያመለ
ክታል ። ይህን ሐቅ በማስመልከት ኬ-ዛር
ዶሽ ሲጽፍ ፣ «በማደግ ላይ ባለው ሶሻሊ
ዝምና በመወገድ ላይ ባለው ካፒታሊዝም
መካከል ያለው ቅራኔ የሽግግር ወቅት ኢኮ
ኖሚ ዋንኛው ቅራኔ ነው ። ቅራኔውም የሚ
ፈታውም ካፒታሊዝምን ጨርሶ በመደም
ሰስና በሶሻሊዝም በመተካት፣ ማለትም የም
ርት ኃይሎችን ፣ ምርትንና የምርት ክፍፍ
ልን ማኅበራዊ በማድረግ ነው።» [11]

በሽግግር ወቅት የሚኖረው የኢኮኖሚ
ቅራኔ የሚመነጨው በወልና በግል ይዞታ
ዎች መካከል ካለው ቅራኔ ነው ። በሽግግር
ወቅት የሠራተኛው ፓርቲ ፣ መንግሥትና

Digitized by Google

ሕዝባዊ ድርጅቶች የወል (የመንግሥትና የኅብረት) ኢኮኖሚያዊ ይዞታዎች እንዲያድጉና እንዲዉምሩ የግል የኢኮኖሚ ይዞታዎች እያደር እንዲያንሱና እንዲወገዱ ለማድረግ የሚያስችላቸው እቅድ ያወጣሉ። ይህን እቅድ ወይም ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚወስዷቸውንም እርምጃዎች በሕግ መልክ ይገልፃሉ ። ለምሳሌ መንግሥት የሚያወጣው ፕላን በአግባቡ መፈፀም አለመፈፀሙን ለመቆጣጠር ፣ ባልፈፀመው ክፍል ላይም ሕጋዊ ርምጃ ለመውሰድ ያስችለው ዘንድ ፕላኑ በሕግ መልክ እንዲወጣ ያደርጋል ። ይህም ሁኔታ ፕላኑን በተግባር ለመተርጐም የሚደረገው ርብርብ ከፍተኛ እንዲሆን ያደርገዋል ። ስለሆነም ሕጉ ሶሻሊስት ይዞታን ለማጠናከር ብሎም ሶሻስሊት ሥርዓትን ለመመሥረትና በምሥረታውም ሂደት ከጥቃት ለመከላከል ዋንኛ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል ። ሕጉ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓትን መጠበቅ ፣ መከላከልና ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ለሠራተኛው የሚከፋፈለውን ምርት መጠን መለኪያ ነው ።

የ ሶሻሊስት ሕግ ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው በሚለው መርህ መሠረት ማኅበራዊ ምርትን ለሕብረተሰቡ አባላት ለማከፋፈል ይጠቀማል ። እንደሥራው ምርትን ማከፋፈል ሁልጊዜ በሥራ መለኪያና በክፍያ ምጣኔ መካከል የሚኖረውን የተወሰነ ግንኙነት መመሥረትን ይጠይቃል ። ይህም ማኅበራዊ ምርትን ለማከፋፈል የሚረዳ ዘዴ ነው ። ሕግም እንደዚህ ዓይነቱ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል ።[12]

« ሕግ የሥራ ክፍያን ሲመጥን ማኅበራዊ ሀብት ከሚፈቅደው ደረጃ ማለፍ አይችልም ። ይሁን እንጂ ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ሲኖሩ ሕግ አውጪው እንዲኖሩ የሚፈልጋቸውን ማኅበራዊ ግንኙነቶች ለመፍጠር ሕግ ጠንካራ መሣሪያ ነው ። »[13]

ሕግ በሽግግሩ ወቅት የሚሰጠው ሌላው አገልግሎት የምርት ኃይሎች ዕድገት ከምርት ግንኙነት ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ነው ። የሽግግሩ ወቅት መንግሥት የምርት ኃይሎችን ዕድገት እያፋጠነ ከእነሱ ጋር የሚጣጣም የምርት ግንኙነት መኖሩን ከሚያረጋግጥባቸው መሣሪያዎች አንዱ ሕግ ነው ። የሕግ አወጣጥ እንደኤኮኖሚው ዕድገት ደረጃ እየተገናዘበ የሚፈጸም በንታት ላይ የተመሠረተ ርምጃ ነው ። በሽግግር ወቅት በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል በየደረጃው የሚኖረው ሁኔታ በሕግ መሻሻል ይንፀባረቃል ። የሕጉም መሻሻል ተራማጁን የኢኮኖሚ ገጽታ የበለጠ ለማዳበር አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

ከዚህ በላይ በተገለጹት ሁኔታዎች ኢኮኖሚን በሚመለከት ሕግ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ለመገንዘብ ይቻላል ። በአጠቃላይ ይህ በሽግግር ወቅት አሮጌውን የኤኮኖሚ ይዞታ በሚደግፈው አሮጌ ሕግና አዲሱን የኤኮኖሚ ይዞታ በሚያራምደው አብዮታዊ ሕግ መካከል ቅራኔዎች ይኖራሉ ። አሮጌው ሕግና አዲሱ ሕግ በሽግግር ወቅት ለተወሰነ ጊዜ ጐን ለጐን የሚኖሩ ቢሆንም አሮጌው የኤኮኖሚ ሥርዓት በአዲሱ ሶሻሊስት ኤኮኖሚ ሥርዓት በሕግ አጋዥነት እንዲተካ ሲደረግ አሮጌው ሕግ ይወገዳል ። በዚህ ሂደት ማኅበራዊ ምርትና ማኅበራዊ የምርት ግንኙነት እያደጉ ኋላቀር የምርት ግንኙነቶች ደብዛቸው እየጠፉ ይሄዳል ። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የኤኮኖሚው ዕድገት ሁኔታ እየታየ አሮጌውን ሕግ በአዲሱ መተካት ግዴታ ነው ። በሽግግር ወቅት በኢኮኖሚ ግንባታ ረገድ የሕግ ሚና ጐልቶ የሚታየው በዚህ ምክንያት ነው ።

<u>በፖለቲካ፣</u> የሽግግር ወቅት ፖለቲካ የሽግግር ወቅት የመደብ ትግል ነው። የሽግግር ወቅት የመደብ ትግል በተለይም በመጀመሪያዎቹ የእድገት ደረጃዎች የመደቦች ሹም ሽር የሚከናወንበት ፣ የገዥና የተገዥ መደቦች

Digitized by Google

የሚፋለሙበት ፣ ተገዥው መደብ እንደቀድሞው ላለመገዛት ፣ የገዥውም መደብ እንደቀድሞው የመግዛት ሥልጣኑን ወይም የበላይነቱን ላለማጣት የሞት ሽረት ውጊያ የሚያደርጉበት ወቅት ነው ።

በሽግግር ወቅት የሚካሄደው አብዮትና የሚቋቋመው መንግሥት ዓይነት ለፖለቲካ ትግሉ ጠቃሚ የሆኑትን ሕጎች አቀራረጽ ይወስናል ። አብዮቱ ገና በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የእድገት ደረጃ ላይ ከሆነ የሚቋቋመው መንግሥት ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሲሆን የአብዮቱ ዋና ጠላቶች ፊውዳሊዝም ፣ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ናቸው ። የመደብ አሰላለፉም ኢምፔሪያሊስቶች ፣ ፊውዳሎችና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስቶች ባንድ በኩል ፣ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ ሌሎች ሠርቶ አደር በሌላ በኩል ሆነው የሚፋለሙበት ይሆናል ። በዚህ ወቅት ታዳጊ ሀገሮች የአብዮቱ ኃይሎች የጥቅም ማስከበሪያ ሕጐች ያወጣሉ ።

የሚካሄደው አብዮት ሶሻሊስት አብዮት ከሆነ የመደብ ትግሉ ይዘትና ቅርጽ የተለየ ስለሆነ የፖለቲካ ትግሉ ይዘትና ቅርጽም የተለየ ነው ። በዚህ ወቅት የመደብ ትግል የሚካሄደው ቡርዧ ፣ ሀብታም ገበሬና ንዑስ ከበርቴ ባንድ በኩል ፣ ወዝ አደሩ ፣ ድሀና መካከለኛ ገበሬና ሌሎች ጭቁን የኅብረተሰብ ክፍሎች በሌላ በኩል ሆነው ነው ። ለዚህ ወቅት አብዮታዊ ትግል አጋዥ የሚሆነውን ሕግ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም ። የሽግግር ወቅት የመደብ ትግል ማለትም የፖለቲካ ትግል በዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅትና በሶሻሊስት አብዮት ወቅት ምን እንደሚመስል ሲያስረዳ ፦

. . . በመጀመሪያ ከመላ ገበሬዎች (ጋር) በፀረ ዘውድ አገዛዝ ፣ በፀረ የመሬት ከበርቴ ፣ በፀረ ፊውዳል ፣ በፀረ ኋላቀር አስተሰቡ (እስከዚህ ድረስ አብዮት የቡርዧ ዲሞክራቲክ ይሆናል) መሰለፍ ። ከዚያ በኋላ ደሀ ገበሬዎችን ፣ ከፊል ወዝአደሮችን የተበዘበዙትን ሁሉ በካፒታሊዝም በገጠር ሀብታሞች ፣ በኩላኮች ፣ በአትራፊዎች ላይ ዉምር ማስነሳት ነው ። በዚህ ደረጃ ላይ አብዮቱ ሶሻሊስት አብዮት ይሆናል ። በመጀመሪያውና በኋለኛው መካከል ሰው ሠራሽ የቻይና ግንብ ለማቆም መሞከር ፣ እነዚህን ሁለቱን ክፍሎች ከወዝ አደሩ ዝግጅትና ብቃት ከወዝ አደሩና ከድሀ ገበሬው መተባበር መጠን ውጭ በማናቸውም ሁኔታ ለማለያየት መሞከር ማርክሲዝምን ክፉኛ መውጋት ፣ ማደብዘዝ ፣ ለዘብተኛነትን በማርክሲዝም ቦታ መተካት ማለት ነው ። [15]

ብሏል ።

የሽግግር ወቅት ሕግ የወቅቱ የፖለቲካ ሥርዓት ፈር እንዲይዝና ለትግሉ አመች እንዲሆን ያደርጋል ። አብዮታዊ ሁኔታ ሲኖር አብዮቱን የሚመራ ፓርቲ ፣ አብዮታዊ መንግሥትና የአብዮቱ ውጤት የሆኑና የፖለቲካ ተግባር የሚፈጽሙ ሕዝባዊ ድርጅቶች ይኖራሉ ። የእነዚህ የእያንዳንዳቸው የፖለቲካ ትግል ድርሻ ፣ በአብዮቱ ውስጥ ያላቸውን ቦታና በመካከላቸው የሚኖረው ግንኙነት የሚወሰነው በሕግ ነው። ስለዚህ ሕግ በሽግግር ወቅት የፖለቲካ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ።

ከፖለቲካ ዘርፎች አንዱ የመከላከያ ኃይል ነው ። በሽግግር ወቅት አሮጌ የመከላከያ ኃይል ፈርሶ አዲስ የመከላከያ ኃይል መቋቋር እንዳለበት የማርክሲዝም ሌኒንዝም ሣይንስ ያስተምረናል። አሮጌው የመከላከያ ኃይል ለአሮጌው በዝባዥ መደብ እንዲያገለግል በቀድሞ መንግሥት የተቋቋመ በመሆኑ ከሽግግሩ ወቅት ሁኔታዎች ጋር ይቃረናል። ይህን ቅራኔ ለማስወገድ በሽግግር ወቅት የሚቋቋመው መከላከያ በሠራተኛው መደብ መሪነት የሚደራጅ፣ከሠራተኛውና ከገበሬው

Digitized by Google

የሚውጣጣ ወገናዊነቱን አውቆ ለሶሻ ዝም ግንባታ የቆመ መሆን አለበት ። ይህ እውኑ እንዲሆን ባሽግግሩ ወቅት ባለው አብዮታዊ መንግሥት አማካይነት የሚወ ጣው ሕግ ከፍተኛ ሚና አለው ።

የሽግግር ወቅት መከላከያ ኃይል ማኅበ ራዊመሠረት እንዲኖረው ለማድረግ የብሔ ራዊ ውትድርና አገልግሎት ፥ የአካባቢ ሕዝ ባዊ ሠራዊትና የመሳሰሉት የመከላከያ ኃይ ላት መቋቋም አስፈላጊ ነው ። ይህም ተግባ ራዊ እንዲሆን አብዮታዊ ሕግ ሊኖር ይገ ባል ። የሠራተኛው መደብ ፍላጐትና ፈቃድ በሕግ መልክ ተቀርጾ መውጣት ከፍተኛ አስ ተዋጽኦ አለው ። በዚህ ሁኔታ ነው በሽግግር ወቅት የሚገኙ የአብዮቱ ድ ሎ ች ከጥቃት ሊድኑ የሚችሉት ። ጥቃቱ በሁለት አቅጣ ጫዎች ማለትም ከውስጥና ከውጭ ሊመጣ ይችላል ። በማንኛውም አቅጣጫ በአብዮቱ ላይ የሚሰነዘረውን ጥቃት ለመከላከል የሕ ዝባዊነት መሠረትና ባሕርይ ያለው አብዮ ታዊ መከላከያ ኃይል ሊኖር ይገባል ። የዚህ ዓይነት መከላከያ በአስተማማኝ ደግሞ ለመ ገንባት የሕግ አስፈላጊነትና መሣሪያነት አጠያያቂ አይሆንም ።

ይሁን እንጂ የቀድሞው የገዥ መደብ መከላከያ መዋቅር ባንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ በአብዮታዊ ጦር ሊተካና ሊለወጥ አይቻ ልም ። ስለዚህ እያደገ በሚሄደው አብዮታዊ የመከላከያ መዋቅርና እየቀረ በሚሄደው የቀ ድሞ የገዥው መደብ የመከላከያ መዋቅር መካከል ቅራኔ በመኖሩ የመደብ ትግል ይካሄ ዳል ። ቅራኔውን በሣይንሳዊ ሁኔታ ተንትኖ በመረዳት በሚወሰዱ ርምጃዎችና በሌሎች ዘርፎች አብዮቱ በሚጐናፀፋቸው ድሎች እየታገዘ በትግል የተፈተነ አብዮታዊ የመ ከላከያ ኃይል በመጨረሻ ሙሉ ሀልውና ያገኛል ። የዚህ ዓይነቱን ጦር ለመመሥ ረትና በየደረጃው እንዲያድግ ለማድረግ ሕግ አስፈላጊ መሣሪያ ነው ።

በአጠቃላይ በሽግግር ወቅት በአብዮቱ ኃይሎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመደ ንገግና ፥ የአብዮቱን ኃይሎች (የመከላከያ ኃይልን ጭምር) ለማሰባሰብና ለአብ ዮቱ ግብ መምታት በጋራ እንዲታገሉ ለማ ድረግ አብዮታዊ ሕግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ። ብዙኃን ሠርቶ አደሪዎች በአሸ ናፊነት እንዲወጣ ለማድረግ አዲሱ ሕግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የትግል መሣ ሪያ ነው ።

<u>በ ባ ሕ ል</u> ፥

የሶሻሊስት ባሕል ግንባታ በቡርዧ ሥርዓ ትም ሆነ ከዚያ በፊት የሰው ልጅ በመላው ታሪኩ ውስጥ በማኅበራዊ ተግባሩ አማካይነት ያከማቻቸውን የባ ሕል ቅርሶች ሙሉ በሙሉ የሚደመስስ ሂደት ሳይሆን ዲሞክራሲያዊና ተ ራማጅ ይዘቶቻቸውን በሙሉ በመውሰድ አጣጥሞ በማዋሀድ ወደ ከፍተኛ ባሕላዊ የዕ ድገት ደረጃ የማያሸጋግር ሂደት ነው ። [16]

በባሕል ዘርፍ የሚደረገው የመደብ ትግል በአንድ በኩል የወደቀውን የገዥ መደብ ጥቅም በሚያስከብሩና የባሕልን ዕድገት በሚቃረኑ ፥ በሌላ በኩል የሠርቶአደሩን ጥቅም በሚያራምዱና እድገትን በሚያፋ ጥኑ ባሕሎች መካከል ባለው ቅራኔ ይከሰ ታል ። አዲሱ ባሕል በአሮጌው ባሕል ላይ የበላይነቱን የሚያረጋግጠው በሕግ ጭምር በመረዳት ነው ። ሕግ በሽግግሩ ወቅት በባ ሕል መስክ በየጊዜው የሚገኙትን አብዮ ታዊ ድሎች እንዲጠበቁ ስለሚያደርግ አዲሱን ሕዝባዊና ሶሻሊስት ባሕል የማዳ በርና የማሳደግ ሚና ይጫወታል ። አሮጌ ውን ባሕል በሚመለከት ሕግና አዲሱን ባሕል የበለጠ ለማጠናከርና ለማሳደግ በወጣ ሕ ግ መካከል ቅራኔ ወይም ትግል ቢኖርም አሮጌው ባሕል በአዲሱ የባሕል ሕግ ባለመደገፉና በሌሎችም አብዮታዊ

Digitized by Google

ትግሎች መጠናከር እየጠቁና እየቀረ ሲሄድ አዲሱ ባሕል እያደር እያደገና እየደ ረጀ ይሄዳል ። ስለዚህ ሕግ የሶሻሊስት ባሕ ልን በአሮጌው ባሕል መቃብር ላይ እንዲያ ድግ ማድረጊያ መሣሪያ ነው ።

<u>በማኅበራዊ ሕይወት ፤</u> በሽግግር ወቅት የኤኮኖሚ ፤ የፖለቲካ የባሕል ፤ የርዕዮተ ዓለምና ሌሎች ለውጦች ስለሚኖሩ በእነ ዚህ ሁኔታዎች ላይ የሚመሠረተው የኅብ ረተሰቡ ማኅበራዊ ሕይወትም ይለወጣል ። በቀድሞውና በአዲሱ ማኅበራዊ ኑሮ መካ ከል ልዩነት ይኖራል ። ይህንኑ ልዩነት አጉ ልተው የሚያሳዩ ሕግጋትም ይኖራሉ ።

በሽታ፣ እርዛት ፣ ማይምነት ፣ የማኅበራዊ ዋስትና አለመኖር ፣ በዘኔነት ፣ ዝሙት አዳሪ ነት ፣ የወጣት አጥፊነት ፣ ልማደኛ ወንጀለ ኛነት ፣ ብኩንነት ፣ ዋልጌነትና ሌሎች የኅብ ረተሰቡ ዕድገትና ሰላማዊ ኑሮ ጠንቆች ከአ ሮጌው ሥርዓት የተወረሱ የሽግግር ወቅት ማኅበራዊ ሕይወት ገጽታዎች ናቸው ። እነ ዚህን ሁኔታዎች የሽግግሩ ወቅት መንግ ሥት ከሠራተኛው ወይም ከኮሚኒስት ፓር ቲው በሚሰጠው ሁለገብ አብዮታዊ አመ ራር ሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶች በሚያ ደርጉት ጥረት እየታገለ መፍትሔ ይሰ ጣል ። ጤናን ፣ ትምህርትንና ማኅበራዊ ዋስትናን በየደረጃው ለኅብረተሰቡ አባ ላት ለማዳረስ የሚያስችሉ ርምጃዎችን ለመውሰድ በሕግ ይጠቀማል ።

የማኅበራዊ ሕይወት ኑሮ ለውጥ የሕጎ ችንም ለውጥ ያስከትላል ። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኋላቀር ማኅበራዊ ሕይወት ምንጭ የሆኑት ሕጎች ይሻራሉ ። በምትካ ቸው ለተስተካከለና ሰብአዊነት ለሰፈነበት ኅብረተሰብ ግንባታ የሚረዱ ሕጎች ይወ ጣሉ ። እነኝህ ሕጎች ከሌሎች አብዮታዊ ርምጃዎች ጋር በመጣመር ለአዲስ ኅብረ ተሰብ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደር ጋሉ ።

<u>በርዕዮተዓለም ፤</u> በሽግግር ወቅት በመ ንግሥት የሚወጡትን ሕጎች ለማክበርና ለመፈጸም ማወቅ ይኖርባቸዋል ። ከዚህ አንጻር የሚደረገው ጥረትም የኅረተሰቡን አባላት የንቃተ ኅሊና ደረጃ ከፍ ስለ ሚያደርግ በማሌ ርዕዮተዓለም እንዲታ ነጹ አስተዋጽኦ ያደርጋል ። «ማኅበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች ሁኔታ ዎች በሕግ አውጪው ንቃተኅሊና ግን ዛቤ አግኝተውና ርዕዮተዓለማዊ ዓላማ ለማራመድ በሕግ» መልክ የሚገለጹ ቢሆ ንም መልሰው «በሰዎች ንቃተ ኅሊናና ሥነ ምግባር ላይ ተጽእኖ» ያሳድራሉ ። ስለሆ ነም «ሕግ በኅብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ርዕዮተዓለማዊ ወይም አንዳንድ ጊዜ እንደሚባለው ትምህርታዊ ሚና ይጫወታል ።» [17]

በሽግግር ወቅት የሚወጡት ሕጎች የብዙ ኃኑን ጥቅምና መብት የሚጠብቁና የጥቂት የቀድሞ ገዥ መደብ አባላትን በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ጥቅምና መብትየሚገቱ ናቸው። በዚህም ምክንያት የሽግግር ወቅት ሕጎች ባሕርይ ሕዝባዊ ነው ። በየጊዜው የሚ ወጡ አብዮታዊ ሕጎች ለሕዝብ ይገለጻሉ ወይም በተለያዩ ዘዴዎች ሕዝቡ እንዲ ያውቃቸውና የትግሉ መሣሪያ እንዲያደ ርጋቸው ጥረት ይደረጋል ።

አንድ አብዮታዊ መንግሥት የማርክሲ ዝም ሌኒኒዝም ፖለቲካዊ ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ባሕ ላዊና ማኅበራዊ መርሆዎችን በኅብረተሰቡ

Digitized by Google

እንዲከበሩና የተግባር መመሪያ እንዲሆኑ በመግለጽ ይደነግጋል ። ለተፈጻሚነታቸውም ያስገድዳል ። የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መርህዎች በዚህ መልክ ሕግ ሆነው በመውጣታቸው የሚጫወቱት ርዕዮተዓለማዊና ትምህርታዊ ሚና ከፍተኛ ነው ። ከዚህ እንፃር ሕግ የሠራተኛው መደብ ርዕዮተዓለም በሰፊው ሕዝብ ውስጥ እንዲሰራጭ ፥ እንዲታወቅና በኅብረተሰቡም አእምሮ እንዲሰርጽ ለማድረግ ድርሻ ያበረክታል ማለት ይቻላል ።

ዲሞክራሲን በማስከበር ፥ በሽግግር ወቅት በመንግሥት የሚወጡ ሕጎች የብዙኃኑ ዲሞክራሲ ተግባራዊ ማድረጊያ መሣሪያ ሲሆኑ የቀድሞውን የገዥውን መደብ ሕጎች የሚሽሩ ናቸው ። በአዲሱና በአሮጌው ሕጎች መካከል የሚኖረው ቅራኔ በተራማጅና በአድኃሪ የኅብረተሰቡ ክፍሎች መካከል የሚካሄደውን ትግል ያንፀባርቃል ።

አዲሱ ሕግ ለቆመለት ብዙኃን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት ሲያጐናፅፍ ለጥቂቶች የቀድሞ የገዥ መደብ አባላት ግን የዲሞክራሲን መብት ይነፍጋቸዋል ። ይህ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ በተወሰዱት ዲሞክራሲያዊ ርምጃዎችና በወጡት ዲሞክራሲያዊ ሕጎች በግልጽ ታይቷል ። ከነዚህም መካከል የገጠርን መሬት የሕዝብ ያደረገው የየካቲት 1967 አዋጅ ፥ ባንኮችን፥ ኢንሹራንሶችንና የገንዘብ ድርጅቶችን የመንግሥት ያደረገው የጥር 1967 አዋጅ፥ የከተማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው የሐምሌ 1967 አዋጅ ፥ የከነማት ፥ የኢኢሴማ ፥ የኢኢወማ ፥ የመኢገማ እና የመኢሠ ማማቋቋሚያና የማጠናከሪያ አዋጆች ይገኛሉ ። በእነዚህ ሕጎች ውስጥ የብዙኃኑ ዲሞክራሲ ተግባራዊ መሆኑ ሲረጋገጥ ለቀድሞው የገዥ መደብ አባላት ግን የዲሞክራሲ መብት ተነፍጓቸዋል ።

የብዙኃኑ ዲሞክራሲ እውን ከሚሆንባቸው ብዙ ዘርፎች አንዱ የሽግግር ወቅት መንግሥት የፖለቲካ አወቃቀር ሥርዓት አንዱ ነው ። በዚህ ሁኔታ ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት ሲዘረጋ ለብዙኃኑ የኅብረተሰብ አባላት ዲሞክራሲያዊ መብት ተረጋግጦለት በዚህም መብቱ ተጠቅሞ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት አካላት ይመሠረታል። ይህ መብት የሚገለጸውና በመብቱ መሠረትም የአፈጻጸሙ ሥርዓት የሚወጣው በሽግግር ወቅት በሚኖረው መንግሥት አማካይነት በሕግ ነው ።

ሶሻሊስት ሕግ የብዙኃኑ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የሚያደርገው በፖለቲካ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ ፥ በባሕልና በማኅበራዊ ሕይወትም ዘርፎች ጥምር ነው ።

ሶሻሊዝም በባሕርዩ ጥልቅና ሰፊ ዲሞክራሲ ያለበት ሥርዓት ነው ። በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለእውነተኛ ዲሞክራሲያዊነት ማኅበረ ፥ ኢኮኖሚያዊ መሠረት የተጣለው በሶሻሊዝም ነው ። ይህ በፖለቲካ የሕዝብ ሥልጣንና አስተዳደር በሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች ማኅበራዊ እውነተኛ እኩልነትና የግለሰብ ነጻነት የተረጋገጠበት በመሆኑ ነው ። በዚህ መርህ መሠረት ያለዲሞክራሲ ሶሻሊዝም ፈጽሞ ሊታሰብ አይችልም ። በሌላ አነጋገር ዲሞክራሲ የሌለበት ኅብረተሰብ ሶሻሊዝም አይደለም ።[18]

ስለዚህ ወደዚህ ሥርዓት ለመድረስ የሚያስችለውን የሽግግር ወቅት የተያያዘው ኅብረተሰብ በሶሻሊዝም መንደርደሪያ ላይ እንደመሆኑ የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሕግ ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው። ሰፊው ሕዝብ ሕይወቱንና ኑሮውን በሁሉም የኑሮ ዘርፎች ለማሻሻል በሕግ በታወቀለትን የዲሞክራሲ መብት በመጠቀም ዕድገ ያፋጥናል ፤ የመደብ ጠላቶቹን ይዋጋል ፤ ይደመስሳቸዋል ፤ እኩልነት ፥ ፍትህ ፥ ሰላም ብልጽግና የተመላበት ኅብረተሰብ ይገነባል ። ስለዚህ ሕግ የሠራተኛው መደብና የጭቁን ኅብረተሰብ ክፍሎች ዲሞክራሲ እውን ማድረጊያ መሣሪያ ነው ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

የሽግግር ወቅት በመደቦች መካከል የሞት ሽረት ትግል የሚደረግበት ክፍለ ጊዜ ነው።

Digitized by Google

ሕግ የመደቦች መፋለሚያ ከሆኑት ሕሊናዊ መስኮች (የኅብረተሰቡ ላዕላይ መዋቅር) አንዱ ነው። ሕግ ኢኮኖሚን ለማሳደግ፣ ማኅበራዊ ሕይወትን ለመለወጥ ፣ ርዕዮተዓለምን ለማሠራጨት ፣ የፖለቲካ ሥልጣን ለማጠናከር ያገለግላል ።

የሽግግር ወቅት ሕግ የሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ ጥልቀትና ስፋት እያገኘ እንዲሄድ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

የሕግ ድርሻ በሽግግሩ ወቅት እየጨመረ መሄዱ ከሚታወቅበት ዘርፍ አንዱ ቢሮክራሲያዊ አሠራርን በዲሞክራሲያዊ አሠራር በመተካቱ ሂደት ነው ። የሽግግሩ ወቅት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ እያደገ ሲሄድ ዲሞክራሲያዊ አሠራርም እንደዚሁ ዕድገት እያሳየ ፣ ቢሮክራሲያዊ አሠራርን በሕዝባዊ አስተዳደር እየተተካ ይሄዳል ። ለዚህም ዕውን እየሆነ መሄድ ኋላ በቀላሉ የማይታይ አስተዋፅዖ ያደርጋል ።

ሶሻሊስት ሕግ ከሶሻሊስት ኅብረተሰብ ዕድገት ጋር እየተለወጠ ስለሚሄድ ተግባራዊነቱም እያደረ ከሕጋዊ አስገዳጅነት ወደ ምግባራዊ አስገዳጅነት ወይም ምግባራዊ ልማድ እየሆነ ከመደብና ከመንግሥት ጋር አብሮ ይከስማል።እዚህ ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት ግን በየወቅቱ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚናረው የመደብ ትግል ነፀብራቅ ከሆነው መንግሥት ዓይነትና ቅርጽ ጋር ራሱን እየለዋወጠ ያድጋል ። በመጨረሻም የሠራተኛው መደብ ሕግ የሁሉም ኅብረተሰብ ሥነ ምግባርና ባሕላዊ ደንብ ይሆናል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. K. Zarodov, *Leninism and Today's Problems of the Transition to Socialism* (Moscow: Progress Publishers, 1983), p. 204.

2. *Ibid.*, p. 9.

3. F. Engels, The Origin of Family Private Property and the State, As quoted by V.I. Lenin, *The State and Revolution*, Selected Works, Vol. 2, (Moscow: Progress Publishers, 1976), p. 241.

4 ግሀሉ ወልደጊዮርጊስ ፣ ሕግ በሽግግር ወቅት ፣ መስከረም ፣ ቅጽ 4 ፣ ቁ-17 መጋቢት 1976 ፣ ገጽ 63 ።

5. J.V. Stalin, *Economic Problems of Socialism in the USSR* (Peking: Foreign Language Press, 1972), p. 2.

6 መስከረም ፣ ቅጽ 4 ፣ ቁ- 17 ፣ ገጽ 64 ።

7 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 63 ።

8 ኤሳ - ኤ- ጉሌንስኪና ኤም ኤስ ስትሮጉቢች ፣ በዮሐንስ ኅሩይና በመንግሥቱ ኃይለማርያም እንደተተረጐመ ፣ የመንግሥትና የሕግ ጽንሰ ሐሳቦች ፣ ሕግና ፍርድ ቅጽ 1 ፣ ቁጥር 1 ፣ ኅዳር 1976፣ ገጽ 10 ።

Digitized by Google

9. S.A. Golunsky, "The Creative Revolutionary Role of Socialist Law in the Period of the Comprehensive Building of Communism", *Soviet Law and Government Journal*, Vol. 1, No. 1, (Moscow: Progress Publishers, 1969), p. 14.

10. V.M. Chkhikvadze, The Soviet State and Law (Moscow: Progress Publishers, 1969), p. 197.

11 በቪ.ኬሌ. እና ኤም.ኮቫልሰን ፡ ታሪካዊ ቁስአካልነት የኅብረተሰብን ድፌሐሳብ እስተዋጽኦ (አዲስ አበባ ፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት 1972) ፡ ገጽ 165—166 (ትርጉም) ።

12. V.M. Chkhikvadze, p. 206.

13. V.M Chkhikvadze, p. 205.

14. V.M. Chkhikvadze, pp. 202-203.

15. K. Zarodov, p. 206.

16 ፋሲል ተፈራ ፡ ከበደ ትኩና ዘውዴ ሰር ባር፡ የባህልና የቴክኒክ መሠረት ግንባታ በአብዮት ሂደት ፡ መስከረም ፡ ቅጽ ፡ 3 ቁ-12 ፡ መጋቢት 1975 ፡ ገጽ 52 ።

17. V.M. Chkhikvadze.

18. K. Zarodov, p. 248.

Digitized by Google

ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚደረገው ትግል

ዮሐንስ ገብረ ሥላሴ

የተመዘገበው የዓለም ሕዝብ ታሪክ አብዛኛው የተሞላው በጦርነቶች ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ ሙሉ ሰላም ያገኘበት በጣም አጭር ነው። በተለያዩ ወቅቶች በተደረጉ ጦርነቶች ያለቀው ሕዝብ ብዛት አራት ቢሊዮን እንደሚሆን የታሪክ ተመራማሪዎች ይናገራሉ። ይህ አኃዝ ባሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ከሚኖረው ሕዝብ ቁጥር ጋር የሚቀራረብ ነው።[1]

ከፍተኛ ጥፋት ካደረሱትና 14,500 ይሆናሉ ከሚባሉት ጦርነቶች መካከል በአስከፊነታቸው እስካሁን ወደር የሌላቸውና በኢምፔሪያሊስት ኃይሎች የተቀሰቀሱት አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ጦርነቶች ከ70 ሚሊዮን በላይ ለሚገመት ሕዝብ ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆነዋል። በሁለቱ ጦርነቶች ምክንያት ይህን ያህል ሕይወት ሊጠፋ የቻለው ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ የዓይነትና የመጠን ለውጥ እያሳዩ የመጡት የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች የሰውን ልጅ በማጥፋት ተግባር ላይ በመዋላቸው ነው።

የዚህ ዓይነቱ ከፍተኛና አሳዛኝ እልቂት እንዳይደርስ የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለምአቀፋዊ ድርጅቶች በየበኩላቸው በዓለም ላይ ሰላምና ጸጥታ እንዲሰፍን ለጦር መሳሪያ ቅነሳና ለሰላም መከበር የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርጉ ይታያሉ። በዚህ ጽሑፍ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ-መ-)፣ የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄና የዓለም ሰላም ምክር ቤት ለሰላምና ለጦር መሳሪያ ቅነሳ የሚያደርጉትን ትግል፣ በትግሉ የገጠማቸውን ችግርና የትግሉን አቅጣጫ ለማሳየት ይሞክራል።

Digitized by Google

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥሪት

ሰኔ 26 ቀን 1944 በዩናይትድ ስቴትስ በሳንፍራንሲስኮ የተሰበሰቡት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሥራች ሀገሮች ያፀደቁት ቻርተር እንደሚያስረዳው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ዓላማ የዓለምን ሰላምና ጸጥታ ማስከበርና የሰውን ልጅ ከጦርነት ዕልቂት ማዳን ነው ። ይህንንም ዓላማ ለማስፈፀም ኃላፊነት የተሰጣቸው የድርጅቱ አካሎች የጸጥታው ምክር ቤትና የጠቅላላው ጉባኤ ናቸው ።[2]

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ከተፈረመ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዩናይትድ ስቴትስ በሄሮሽማና በናጋሳኪ ከተሞች ላይ የአቶሚክ ቦምብ ማፈንዳቷና ይህ አደገኛ ቦምብ እንደገና በተግባር ላይ ቢውል የሚያመጣውን ጥፋትና እልቂት ለመገመት መቻሉ ተ-መ ለጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉዳይ ተጨማሪ ትኩረት እንዲሰጥ ገፋፋት ። በመሆኑም በ1946 የተላለፈው የጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የአቶሚክ ኃይል የሚያመጣውን ውጤት ፣ የአቶሚክ ጦር መሳሪያዎችና ሌሎችም አሰቃቂ ዕልቂት ሊያደርሱ የሚችሉ መሳሪያዎች ከብሔራዊ የጦር ኃይሎች የሚወገዱበትን መንገድ የሚያጠናና ሃሳብ የሚያቀርብ የአቶሚክ ኃይል ኮሚሽን በመባል የሚታወቅ አካል እንዲቋቋም ተደረገ ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ ደህንነትና የጦር መሳሪያ ቅነሳ የማይነጣጠሉ ጉዳዮች መሆናቸውን በመገንዘብ ጠቅላላ የጦር መሳሪያ ቅነሳ እንዲደረግ በኅዳር 1946 ሃሳብ አቀረበ ።[3] ሃሳቡን ተግባራዊ ለማድረግ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉዳይ በፀጥታው ምክር ቤት ፣ በጠቅላላ ጉባኤውና በሌሎችም ዓለም አቀፍ የስብሰባ አጀንዳዎች ላይ ዋንኛ የመወያያ ነጥብ ሆኗል ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በ1947 የመደበኛ ጦር መሳሪያዎች ኮሚሽንን (Commission for Conventional Armaments) አቋቋመ ። በ1952 ቀደም ብሎ የተቋቋመው የአቶሚክ ኃይልና የመደበኛ ጦር መሳሪያዎች ኮሚሽኖች ተዋህደው የጦር መሳሪያዎች ቅነሳ ኮሚሽን (Disarmament Commission) ተመሠረተ ።[4] ይህ ኮሚሽን የጸጥታው ምክር ቤት አባላትንና ካናዳን ያቀፈ ነበር ። በ1957 የድርጅቱ አባላት ቁጥር ከ51 ወደ 82 ከፍ ባለበት ወቅት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የጦር መሳሪያዎች ቅነሳ ኮሚሽን ውስጥ 14 አባላት እንዲጨመሩ ፣ በኋላም በ1958 የድርጅቱ አባላት በሙሉ የኮሚሽኑ አባል እንዲሆኑ ወሰነ ። ሆኖም ኮሚሽኑ ቀስ በቀስ እየተዳከመ በመምጣቱ ከ1958-1965 ባለው ጊዜ ያካሄዳቸው ስብሰባዎች ሁለት ብቻ ነበሩ ። በ1978 በጠቅላላው ጉባኤ በተደረገው የጦር መሳሪያ ቅነሳ ልዩ ጉባኤ የኮሚሽኑ ሥራ እንደገና ተንቀሳቀሶ የጠቅላላው ጉባኤ በማይሰበሰብበት ወቅት የጦር መሳሪያ ቅነሳ መወያያ መድረክ እንዲሆን ተወሰነ ። ከ1978 ወዲህ የጦር መሳሪያ ልዩ ጉባኤዎች ያስተላለፉትን ውሳኔዎች መከታተል በጦር መሳሪያ ቅነሳ በኩልም ሃሳቦችን ማቅረብ ከኮሚሽኑ ተግባሮች አንዳንዶቹ ናቸው ።[5]

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ጠቅላላ ጉባኤው የጦር መሳሪያን በሚመለከት ዋና መወያያ መድረክ ሆኖ ቆይቷል ። ጉባኤው እያንዳንዱ አባል ሀገር በጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉዳይ ላይ ያለውን ኦፊሴላዊ አቋም ለመግለጽ በጦር መሳሪያ ቅነሳ በኩል አዳዲስ ሃሳቦችን ለማቅረብ ውይይት ለማካሄድ ሰፊ መድረክ ከፍቷል ።

ጠቅላላ ጉባኤው የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች የአስገዳጅነት ኃይል ባይኖራቸውም

Digitized by Google

በጦር መሳሪያ ቅነሳ ድርድሮች ላይ የተወሰነ የፖለቲካና የሞራል ተጽዕና ያደርጋሉ ። እስከ አሁን ድረስ የጦር መሳሪያ ቅነሳን በሚመለከት ከ450 በላይ ውሳኔዎች በጠቅላላ ጉባኤው ተላልፈዋል ።[6] ከነዚህም መካከል በ1946 የአቶሚክ ኃይል ለሰላማዊ ተግባሮች እንዲውል ፣ በ1959 አጠቃላይ የጦር መሳሪያ ቅነሳ እንዲደረግ ፣ በ1961 የኒኩለር ጦር መሳሪያዎች እንዳይስፋፉና በ1971 የኒኩሌር ጦር መሳሪያዎች ሙከራን የሚያወግዙ ውሳኔዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

ጠቅላላ ጉባኤው ለጦር መሳሪያ ቅነሳና ለሰላም መጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስዱ አያሌ ሰላም ፈላጊ ሀገሮች ፣ የእርነት ንቅናቄዎች ፣ ቡድኖችና ሌሎችም መሰል ኃይላት የተደጋገመ ሙከራ አድርገዋል ። ለምሳሌ በ1961 በጦር መሳሪያ ቅነሳ ላይ ብቻ የሚያተኩር አንድ ልዩ የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ እንዲደረግ ቤልግሬድ ላይ ተደርጎ የነበረው የገለልተኛ ሀገሮች ስብሰባ ጥሪ አቅርቦ ነበር ። እነዚሁ ገለልተኛ ሀገሮች አንድ አጠቃላይ የዓለም አቀፍ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ስብሰባ (World Disarmament Conferenee) ከ1978 ከመካሄድ በፊት ልዩ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ስብሰባ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ አማካይነት እንዲደረግ አሳሰቡ ። ግፊቱ ተቀባይነት በማግኘቱ ከግንቦት እስከ ሰኔ 1978 ባለው ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት አባላትን ያጠቃለለ ልዩ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉባኤ እንዲደረግ ጠቅላላ ጉባኤው በኅዳር 1976 ውሳኔ አሳለፈ ። አዲስ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ስትራተጂ መቀየስ በጊዜው የነበሩትን የጦር መሳሪያ ቅነሳ መወያያና መደራደሪያ መድረኮች ማጠናከርና የዓለም ኅብረተሰብ አስተያየት በጦር መሳሪያ ቅነሳ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ከስብሰባው ዓላማዎች ዋና ዋናዎቹ ነበሩ ።

ከግንቦት 23 እስከ ሐምሌ 1 ቀን 1978 በተካሄደው በዚህ ስብሰባ 126 ሀገሮች በጦር መሳሪያው ቅነሳ ጥረት ላይ ያላቸውን አስተያየት ሲገልጹ 25 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና 6 የምርምር ተቋሞች በድርጅቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ አሳሳቢ ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን ለመግለጽ ችለዋል ።[7] ጉባኤው እነዚህ ተቋሞች የዓለም ኅብረተሰብ በጦር መሳሪያ ቅነሳ ላይ ያለውን ተሳትፎ በማዳበር ፣ ስለጦር መሳሪያ ቅነሳ ሳይንሳዊ ጥናቶችን በማካሄድ በኩል ያላቸውን ከፍተኛ ሚና በሚገባ አጢኖታል ። ከዚህም በተጨማሪ ጉባኤው የገለልተኛ ሀገሮችና ሌሎች ትናንሽ ሀገሮች በጦር መሳሪያ ቅነሳና በሌሎች ዓለምአቀፍ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ተሳታፊነትና ተሰሚነት አሳድጓል ።

የጦር መሳሪያ ቅነሳ መወያያና መደራደሪያ አካሎችን በማጠናከር በኩል ሁሉም የተባበሩት መንግሥታት አባሎች የሚሳተፉበት የጦር መሳሪያ ቅነሳ ኮሚሽንና የተ. መ. የተወሰኑ አባላት የሚወከሉበት ሆና የድርድር ኮሚቴው በአዲስ መልክ እንዲደራጁ ተወሰነ ። በውሳኔው መሰረት የውድድር ኮሚቴው ተደራጅቶ ሥራውን በ1979 በአዲስ መልክ ሲጀምር የኮሚቴው አባላት ቁጥር ከ26 ወደ 40 ከፍ ተደርጎ ከአምስቱ የኒኩሊየር ኃይል ባለቤቶች ጋር 21 ከገለልተኛ ሀገሮች ፣ 14 ከሁለቱ (ከሰሜንና ከዋርሶ) የጦር ቃል ኪዳን ሀገሮች የተውጣጡ አባላት በኮሚቴው ውስጥ እንዲሰሩ ተወሰነ ።[8] እስከ 1978 ድረስ ከኮሚቴው ውጪ የነበረችው ፈረንሳይ በኮሚቴው ሥራ መሳተፍ ስትጀምር ቻይናም በ1979 በተደረገው ስብሰባ መልእክተኞችዋን በተመልካችነት ልካለች ። የኮሚቴው የሊቀ መንበርነት ቦታ በአሜሪካና በሶቭየት ኅብረት በቋሚነት መያዙ ቀርቶ በየወሩ በአባሎች መካከል የሚዞር እንዲሆን ፣ አባል ያልሆኑ ሀገሮችም ሃሳባቸውን የመግለጽ መብት እንዲኖራቸውና የኮሚቴውን ሥራ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጋር የበለጠ ለማቀራረብ የኮሚቴው ጸሐፊ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የሚሾሙት ተወካይ እንዲሆን ተወሰነ ።[9]

Digitized by Google

የጦር መሳሪያው ቅነሳ ልዩ ጉባኤ የጦር መሳሪያ ቅነሳን በሚመለከት ዋናው የመወያያ መድረክ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ መሆኑን ጠቅሶ ሌላ በጦር መሳሪያ ቅነሳ ብቻ ላይ የሚያተኩር 2ኛ ጉባኤ እንዲደረግ ፣ በተጨማሪም ዓለምአቀፍ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉባኤ (World Disarmament Conference) እንዲካሄድ ጥሪ አቀረበ ። [10]

በጉባኤው መጨረሻ ላይ የወጣው ዘገባ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ዓላማዎችን ፣ በአስቸኳይ ሥራ ላይ መዋል ያለባቸውን እርምጃዎችንና ለሉችም በጦር መሳሪያ ቅነሳ በኩል መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በዝርዝር የያዘ መርሐ-ግብር አውጥቷል ። የስብሰባው መሳካት የጦር መሳሪያ እሽቅድምድምን የሚገታበት ጊዜን የተቃረበ አስመሉት ነበር ። ሆኖም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የስብሰባው ዓላማዎች በሥራ እንዳይተረጎሙ ማሴር የጀመረው ገና ስብሰባው በመካሄድ ላይ እንዳለ ነበር ። በግንቦት 1978 መጨረሻ የኔቶ ቃል ኪዳን ሀገሮች በአሜሪካ መሪነት በዋሽንግተን ተሰብስበው የድርጅቱን ወታደራዊ ተቋሞች የሚያጠናክር ውሳኔ አፀደቁ ። [11] ይህም ውሳኔያቸው የመሳሪያ እሽቅድምድምን ከመገፋፋቱም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ግንኙነቶችም ላይ ውጥረት እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል ።

የመጀመሪያው የተባበሩት መንግሥታት ልዩ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉባኤ መጨረሻ ላይ የወጣው ዘገባ ባሳሰበው መሠረት ሁለተኛው የተባበሩት መንግሥታት ልዩ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉባኤ ከሰኔ 7 እስከ ሐምሌ 9 ቀን 1982 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት ተካሄደ ። የስብሰባው መነጋገሪያ ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ ። [12]

1. የጦር መሣሪያ እሽቅድድም በዓለም ሰላም ላይ ያሳደረውን ስጋት በመገምገም የጦር መሳሪያዎች በተለይም የኒኩሊየር ጦር መሳሪያ እሽቅድድም የሚገታበትን መንገድ መፈለግ ፣ የሰው ልጆችን በተለይም የታዳጊ ሀገሮችን ሕዝቦች ኑሮ ማሻሻል ፣
2. የመጀመሪያው ልዩ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉባኤ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ምንያህሉ ሥራ ላይ እንደዋሉ መገምገም ፣
3. አጠቃላይ የሆነ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ፕሮግራምን ማጽደቅ ፣
4. ኅዳር 11 ቀን 1978 ጠቅላላው ጉባኤ 1980ዎቹ ሁለተኛው የጦር መሳሪያ ቅነሳ ዓመታት እንዲሆኑ ባሳሰበው መሠረት ለዚሁ ጥሪት ድጋፍ የሚገኝበትን መንገድ መመርመር ፣
5. ያሉትን የጦር መሳሪያ ቅነሳ የመወያየና የመደራደሪያ መድረኮችንና በጦር መሳሪያ ቅነሳ በኩል የተባበሩት መንግሥታት የሚጫወተውን ሚና ማጠናከር ፣ ዓለምአቀፍ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ስብሰባ ፣(World Disarmament Conference) ሊደረግ የሚችልበትን ሁኔታ መፈለግ ፣
6. የዓለም ኅብረተሰብ አስተያየት በጦር መሳሪያ እሽቅድድም አስጊነትና በጦር መሳሪያ ቅነሳ አስፈላጊነት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ።

ሆኖም ለአምስት ሳምንታት ያህል የተካሄደው ስብሰባ እንደታሰበው አጠቃላይ የሆነ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ፕሮግራም ማጽደቅ አልቻለም ። የመጀመሪያው ስብሰባ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ምን ያህሉ በተግባር ላይ መዋላቸውንም የሚገመግም ዘገባ አላወጣም ።

ለስብሰባው አለመሳካት የተለያዩ ምክንያቶች ተሰጥተዋል። ሁለተኛው የተባበሩት መንግሥታት የጦር መሳሪያ ቅነሳ ልዩ ጉባኤ የተደረገው በዓለም አካባቢ ብዙ ግጭቶች በሚካሄዱበት ፣ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ውይይቶች በቀዘቀዙበትና የጦር መሳሪያው እሽቅድድም በተጧጧፈበት ወቅት ነበር ። በዚህም ምክንያት በማይግባቡ መንግሥታት መካከልያለው አለመተማመንና ጥርጣሬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑ ስብሰባው በዚህ ዓይነት መንፈስ ባይካሄድ ይሻል ነበር የሚሉ ታዛቢዎች ሲኖሩ ፣ ሌሎች ደግሞ

Digitized by Google

በነበረው አሳሳቢ ሁኔታ የስብሰባው መደረግ አስፈላጊ ነበር የሚል አቋም ይዞዋል ። [13] እንደ አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች አባባል ስብሰባው ፍሬያማ እንዳይሆን ያደረገው ዋናው ምክንያት ብዙ አከራካሪና ስምምነት ያልተደረሰባቸውን ነጥቦች የያዘውን አጠቃላይ የሆነ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ፕሮግራም (Comprehensive Programme Disarmament) ይጽደቅ የሚል ክርክር በመነሳቱ ነበር ። በዚሁ ፋንታ እንደ ኒውክሊየር ጦር መሳሪያና የኬሚካል ጦር መሳሪያ እገዳን የመሳሰሉ አሳሳቢና አስቸኳይ ነጥቦች ላይ በተናጠል ንግግር ቢደረግ ስብሰባው ፍሬያማ ውጤት ላይ ይደርስ ነበር የሚልም ፡ አስተያየት ተሰጥቷል ።[14] በተጨማሪም የመጀመሪያው ልዩ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ስብሰባ ባወጣው ዘገባ ላይ የተላለፉት ውሳኔዎች ምን ያህሉ ሥራ ላይ ውለዋል በሚለው ጥያቄ በክርክርና በመወቃቀስ ብዙ ጊዜ ጠፍቷል የሚልም አስተያየት አለ ። [15] ኒውደልሂ ላይ የተሰበሰበው 7ኛው የገለልተኛ መንግሥታት ንቅናቄ ስብሰባ ደግሞ ጉባኤውን ፍሬቢስ ያደረገው የአንዳንድ ኃያላን መንግሥታት ግትር አቋም ነው በማለት ጠቁሟል ። [16] ይሁንና ለስብሰባው አለመሳካት አስተዋጽኦ ያደረጉ በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩ አያሌ ምክንያቶችን መደርደር የሚቻል ቢሆንም ዋናው ችግር በዓለም ውጥረት መስፈን ፣ በሰላም መናጋትና በጦር መሳሪያ እሽቅድድም ኢኮኖሚያዊ ትርፍ የሚያጋብሱና ፖለቲካዊ ጥቅም የሚያገኙ የተንደኛ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ተደራዳሪዎች እውነተኛ ሰላም ፈላጊ ሆነው አለመገኘት ነው ።

በሁለተኛው የጦር መሳሪያ ቅነሳ ልዩ, ጉባኤ ሶቭየት ኅብረትና ሌሎች የሶሻሊስት ሀገሮች የጦር መሳሪያ እሽቅድድምን የሚገቱና በአጠቃላይ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ጥረቶችን የሚያግዙ ተጨባጭ የሆኑ ሃሳቦችን አቅርበው ነበር ። በተለይም ሶቭየት ኅብረት የኒኩለር ጦር መሳሪያ ለመጠቀም የመጀመሪያዋ እንደማትሆን ቃል የገባች ሲሆን ፣[17] የእርምጃዋም አቅድ አስከፊውን የኒኩለር ጦርነት ለማስወገድ ፣ በመንግሥታት መካከል መተማመንን ለመፍጠርና የተሻለ ዓለምአቀፍ ግንኙነትን ለመመሥረት ነበር ።

ይህ የሶቭየት ኅብረት አቋም የኒውክሊየር ጦርነትን ለማስወገድ የመጀመሪያው እርምጃ እንደመሆኑ የስብሰባው ተካፋዮችና የዓለም ሰላም ፈላጊ ሕዝብ በደስታ ተቀብለውታል ። ሆኖም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም «ሶቭየቶች በመደበኛ የጦር መሳሪያ ስለሚበልጡን የኒውክሊየር ኃይል በመጀመሪያ ለመጠቀም ያለንን መብት መተው የለብንም» [18] በሚል ሰበብ ሶቭየት ኅብረት ያቀረበችውን ሃሳብ ለመደገፍ አልፈቀደም ። ይህም የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም ፀረ ሰላም አቋም በገልጽ አሳይቷል ።

በሌላ በኩል ሁለተኛው ልዩ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ስብሰባ አያሌ ሰላም ወዳድ መንግሥታት የጦር መሳሪያ ቅነሳ ፖሊሲያቸውን እንዲያጠናክሩና ይህንኑ ፖሊሲያቸውን ለዓለም ኅብረተሰብ እንዲያስተዋውቁ ዕድል ሰጥቷቸዋል ። በስብሰባው የተካፈሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ ለሰላምና ለጦር መሳሪያ ቅነሳ የቆሙ የጥናትና የምርምር ተቋሞችም በጦር መሳሪያ ቅነሳ በኩል ያላቸው ከፍተኛ ሚና በድጋሚ ተረጋግጦአል ። በተጨማሪም ስብሰባው የዓለም ሕዝብ አስተያየት በጦር መሳሪያ ቅነሳ ጥረት ላይ እንዲያተኩር አድርጓል ። ሰኔ 12 ቀን 1982 በኒውዮርክ ወደ 750,000 የሚጠጉ ሰዎች የተካፈሉበት ሰላማዊ ሰልፍና ከዚያም በኋላ በዓለም አካባቢ የጦር መሳሪያ እሽቅድምድም በመቃወም የተደረጉ ትእይንተ ሕዝቦች በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ ። ዓለም አቀፍ የጦር መሳሪያ ቅነሳ (World Disarmament Campaign) እንዲጀመር፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በጦር መሳሪያ ቅነሳ ጥረት ላይ የሚያተኩሩ ጥናቶችንና ምርምሮችን የበለጠ እንዲደግፍ የተደረጉት ስምምነቶች [19] የሁለተኛው የጦር መሳሪያ ቅነሳ ልዩ ስብሰባ ውጤቶች ናቸው።

Digitized by Google

ከተ-መ ድርጅት ጋር የተያያዙ የጦር መሳሪያ ቅነሳ መደራደሪያ መድረኮች

በ1950ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ኃያላን መንግሥታት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውጪ የሆነ የመወያያና የመደራደሪያ መድረክ ለመክፈት ተስማሙ ። የአሜሪካና የሶቭየት ኅብረት መሪዎች በተስማሙት መሠረት በ1958 ባንድ በኩል የአሜሪካ ፣ የእንግሊዝ ፣ የፈረንሳይና የካናዳ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሶቭየት ኅብረት የቼኮዝሎባኪያ ፣ የፖላንድና የሩማንያ ኤክስፐርቶች የተገኙበት ስብሰባ የኒኩለር ጦር መሳሪያ ሙከራ ቢታገድ ይህንኑ እገዳ የሚያፈርሱ ተግባሮችን ወይም ሙከራዎችን ለማወቅ እንዴት እንደሚቻል የደረሱበትን ስምምነት ለየሀገሮቻቸው መንግሥታትና ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አቀረቡ ።[20] በኋላም በሶቭየት ኅብረት ፣ በአሜሪካና በእንግሊዝ መካከል የኒኩለር ጦር መሳሪያዎችን ሙከራን ለማገድ ከሚያስችል ስምምነት ለመድረስ ከ1962-1963 ባለው ጊዜ ውስጥ ተከታታይ ጉባኤዎች ተካሄደው ነበር ።

በ1958 ጀኔቭ ላይ በተደረገው ስብሰባ አምስት የምስራቅና አምስት የምእራብ አውሮፓ ሀገሮች የድንገተኛ ግጥታት እርምጃን ለማስቀረት የሚቻልበትን መንገድ መርምረው የስብሰባው ውጤት ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቀርቦ ነበር ። በሁለት የተከፈለው ይህ አሥር ሀገሮች የሚገኙበት መድረክ በየጊዜው ስብሰባ ማድረጉን ቀጥሎ በ1961 የሶቭየት ኅብረትና የአሜሪካ መንግሥታት ባደረጉት ስምምነትና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ባፀደቀው መሠረት በአሥሩ ሀገሮች የመወያያና የመደራደሪያ መድረክ ላይ ስምንት ገለልተኛ ሀገሮች በአባልነት እንዲታከሉበት ተወሰነ ።[21] እነዚህም ሀገሮች ብራዚል ፣ በርማ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሕንድ ፣ ሜክሲኮ ፣ ናይጀሪያ ፣ ስዊድንና ግብጽ ሲሆኑ መድረኩም የአሥራ ስምንቱ ሀገሮች የጦር መሳሪያ ቅነሳ ኮሚቴ (Eighteen Nation Committee on Disarmament) (ENCD) የሚል ስም ተሰጠው ። በ1969 ሶቭየት ኅብረትና አሜሪካ በተስማሙት መሠረት ፣ ጃፓን ፣ ሞንጎሊያ ፣ አርጀንቲና፣ሀንጋሪ ፣ ሞሮኮ ፣ ኔዘርላንድስ ፣ ፓኪስታንና ዩጎዝላቪያን በመጨመር የኮሚቴው አባላት ቁጥር ወደ26 ከፍ ብሎ ስሙም የጦር መሳሪያ ቅነሳ ኮሚቴ ኮንፈራንስ (Conference of the Committee on Disarmament) ተባለ ። ሁለቱ ሊቃነ መናብርት ፣ አሜሪካና ሶቭየት ኅብረት ኮሚቴው በተመሰረተበት ጊዜ የአባላት ጭማሪ ከማድረጋቸውም በፊት ጠቅላላ ጉባኤውን ባለማማከራቸው በሀገሮች ምርጫ በኩልም ከሰሀራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገሮች መልክአምድራዊ የሆነ ሚዛን አልተጠበቀም በማለታቸው ቅሬታ ተፈጥሮ ነበር ።[22] ሆኖም ጠቅላላ ጉባኤ ኅዳር 1968 ባስተላለፈው ውሳኔ ለወደፊት በኮሚቴው አዲስ ለውጥ ሲደረግ ጠቅላላ ጉባኤው ቀደም ብሎ እንዲያውቀው ይደረግ ብሎ በማሳሰብ በኮሚቴው አባላት ቁጥር ላይ የተደረገውን ለውጥ አጽድቆታል ።

በ1978 የተካሄደው የተባበሩት መንግሥታት የጦር መሳሪያ ቅነሳ ልዩ ጉባኤ የድርድር ኮሚቴውን አባሎች ወደ 40 ከፍ በማድረግ የኮሚቴው አባላት ከተለያዩ የዓለም አከፍሎችና የፖለቲካ ቡድኖች የተውጣጡ እንዲሆኑ ሲስማማ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመደራደሪያው መድረክ ሥራውን በተቀላጠፈ መንገድ እንዲካሄድ የአባላቱን ቁጥር አነስተኛ የማድረግ አስፈላጊነትን አምኖበታል ። የመደራደሪያው መድረክ አዲስ ስም የጦር መሳሪያ ቅነሳ ኮሚቴ (Disarmament Committee) እንዲሆን ተወሰነ ።[23]

ጀኔቭ የሚገኘው ይህ የጦር መሳሪያ ቅነሳ የድርድር ኮሚቴ አመሰራረት ከተባበሩት

Digitized by Google

መንግሥታት መድረክ ውጪ ቢሆንም ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት አለው ። የመደራደሪያ አጀንዳውን በሚያዘጋጁበት ወቅት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ላሳለፋቸው ውሳኔዎች ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን ፣ የሥራውንም ሪፖርት በየጊዜው ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል ።[24] በተጨማሪም የ1978ቱ ልዩ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት የድርድሩ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የሚሾሙት ተወካይ ሆነ ።

የድርድሩ ኮሚቴ በተመሰረተበት ወቅት ያተኮረው በአጠቃላይ የጦር መሳሪያ ቅነሳ (General and Complete Disarmament) ላይ ነበር። በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ ግን በከፊላዊ እርምጃዎች (Partial Measures) ላይ ማተኮር ጀመረ ። ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች ኃያላን መንግሥታት የበለጠ ውስብስብና የረቀቀ አገዳኝ የጦር መሳሪያዎች መሥራታቸውና ይህም መሳሪያ በጦር መሳሪያ ቅነሳ ድርድሮች ላይ ያስከተለውን ለውጥ ናቸው ።

በድርድሩ ኮሚቴ አማካይነት የተደረሱት ስምምነቶች የሚከተሉት ናቸው ።[25]

—በ1963 የተፈረመው የኑክሊየር ጦር መሳሪያን ሙከራ በከፊል የሚያግደው ስምምነት (Partial Nuclear Test Ban Treaty)

(ይህ በ1963 በእንግሊዝ ፣ በአሜሪካና በሶቭየት ኅብረት መካከል የተፈረመ ስምምነት ቀደም ሲል በድርድሩ ኮሚቴ የተደረጉ ውይይቶች ውጤት ነው ።)

—በ 1968 የተፈረመው የኒኩለር ጦር መሳሪያዎች መስፋፋትን የሚያግደው ስምምነት

—በ 1971 የተፈረመው የኒኩለር ጦር መሳሪያዎች በባህር ውስጥ እንዳይጠመዱ የሚያግደው ስምምነት ፣

—በ1972 ስምምነት ላይ የተደረሰበት ፀረ ሕይወት ጦር መሳሪያዎችን የሚያግደው ውል (Convention Banning Biological Weapon)

—በ1977 ስምምነት ላይ የተደረሰበት ሊጦርነት ተግባሮች የተፈጥሮ አካባቢ መለወጥን የሚያግደው ውል ፣

ኮሚቴው ባሁኑ ወቅት ከሚያተኩርባቸው ዋና ዋና የአጀንዳ ነጥቦች መካከል[26] «የኒኩለር ጦር መሳሪያዎች ባጠቃላይ የኬሚካል ጦር መሳሪያዎች ፣ ሌሎች የገፍ እልቂትን የሚያስከትሉ መሳሪያዎች ፣ መደበኛ የጦር መሳሪያዎች ፣ የጦር መሳሪያ በጀት ቅነሳ ፣ የጦር ኃይሎች ቅነሳ ፣ የጦር መሳሪያ ቅነሳና ልማት ፣ የጦር መሳሪያ ቅነሳና ዓለም አቀፍ ደህንነት ፣ ከጦር መሳሪያ ቅነሳ ጥረት ጋር የተያያዙ ሌሎች እርምጃዎች ፣ መተማመንን የመፍጠር ፣ የቁጥጥር ዘዴዎች መዘርጋት ፣ ወደ ጠቅላላ የጦር መሳሪያ ቅነሳ የሚመራ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ፕሮግራም መቀየስ» ይገኙበታል ።

ከ1980 ወዲህ የኮሚቴው ንኡስ አካሎች በኬሚካል ጦር መሳሪያዎች ፣ የኒክሌር ጦር መሳሪያ ባለቤት ላልሆኑ ሀገሮች ስለሚሰጠው ዋስትናና አጠቃላይ የጦር መሳሪያ ቅነሳ ላይ[27] ሰፊ ውይይት አካሂደዋል ። በ1982 ና 1983 የተካሄዱት የድርድር ኮሚቴው ስብሰባዎችም የኬሚካል ጦር መሳሪያዎችን ፣ የኒኩለር ጦር መሳሪያን ሙከራ በአጠቃላይ በዚህ መሳሪያ ሊካሄዱ የሚችሉ ጦርነትንና የጦር መሳሪያዎችን ከሕዋው ስለማገድ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ተወያይቷል ።[28]

የድርድሩ ኮሚቴ በዋና ዋና የጦር መሳሪያ ቅነሳ አርእስት ላይ ለምሳሌ እንደ ኒኩሌር ጦር መሣሪያ ሙከራን በአጠቃላይ ወይም የኬሚካል ጦር መሳሪያዎችን ስለማገድ ጉዳይ የራሱን ውይይት በሚያካሄደበት ወቅት፣ኃያላን ሀገሮች ደግሞ በግላቸው ሌላ ድርድር ስለሚያካሂዱ ኮሚቴው በአሠራሩ ላይ ችግር ስለገጠመው በ1979 የገለልተኛ ሀገሮች ሁሉም የኮሚቴ አባሎች በድርድሮቹ ላይ የሚገኙበት አዲስ ዘዴ እንዲቀየስ

Digitized by Google

አሳስበው ነበር ። በጊዜው የኮሚቴው ዋና ፀሐፊ የነበሩት የአልጀሪያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም በተናጠል የሚደረጉ ንግግሮችና ድርድሮች የሚደገፉ ቢሆንም የኮሚቴውን ሥራ መተካት እንደማይችሉ ጠቁመዋል ።[29]

የተቋቋመበት ቻርተር እንደሚያሳየው የዓለምን ሰላምና ጸጥታ ማስከበር ፣ የሰው ልጆችን ከጦርነት ዕልቂት ማዳን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ኃላፊነት ነው ። የተ.መ. ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የጦር መሳሪያ እሽቅድድም እንዲቆም ፣ ለጦር መሳሪያ የሚውለው ከፍተኛ ወጪም ለልማት ተግባሮች እንዲውል ጥረት ቢያደርግም በጦር መሳሪያ ቅነሳ በኩል የተወሰዱ ተጨባጭ እርምጃዎች ጥቂት ናቸው ።

በ1975 የተካሄደው 30ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ድርጅቱ በጦር መሳሪያ ቅነሳ በኩል የሚጫወተው ሚና የሚያጠናክርበት ዘዴን የሚያጠና አንድ ኮሚቴ አቋቁሞ 1976 የተደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ኮሚቴው ያቀረባቸውን ሃሳቦች ሙሉ በሙሉ አጽድቋል ።

ይህንኑ በሚመለከትም ከተገኙት ውጤቶች መካከል የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ለጦር መሳሪያ ቅነሳ ተግባሮች የሚሰጠውን አገልግሎት ለማጠናከር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጦር መሳሪያዎች ቅነሳ ማዕከል (UN Centre for Disarmament) መመሥረት አንዱ ነበር ። ከማዕከሉ ተግባሮች መካከል ፣ የዓለም ኅብረተሰብ የጦር መሳሪያ እሽቅድድም የሚያስከትለውን ጉዳት በሚገባ እንዲገነዘብ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን ማውጣት ፣ ስለ የጦር መሳሪያ ቅነሳ የሚካሄድ ጥናቶችንና ምርምሮችን መደገፍ ፣ ለጦር መሳሪያ ቅነሳ ከቆሙ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ማጠናከርና በጦር መሳሪያ ቅነሳ አርእስት ላይ የሚደረጉ ጉባኤዎችን ማስተናገድ[31] ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

በተጨማሪም በጦር መሳሪያ እሽቅድድም አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ለመወያየት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በ1978ና በ1982 ልዩ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ጉባኤዎች አካሂዶ ነበር ። ድርጅቱ በኅዳር 1969 ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ 1970ዎቹ የመጀመሪያው የጦር መሳሪያ ቅነሳ ዓመታት እንዲሆኑ አውጆ እንደነበር የሚታወስ ነው ። ይሁን እንጂ በ1970ዎቹ መጨረሻ የጦር መሳሪያ እሽቅድድም ከመግታት ይልቅ የበለጠ እየተባባሰ ስለሄደ 1980ዎቹ ሁለተኛው የጦር መሳሪያ ቅነሳ ዓመታት እንዲሆኑ ተ.መ በድጋሚ ጥሪ አስተላልፏል ።[33]

ሆኖም የጦር መሳሪያው ቅነሳ ጥረት በአብዛኛው ያልተሳካው በድርጅቱ መዋቅራዊ ድክመት ሳይሆን በኢምፔሪያሊስት መንግሥታት በኩል የጦር መሳሪያ ቅነሳን ተግባራዊ ለማድረግ የፖለቲካ ፈቃደኝነት በመታጣቱ ነው ። እዚህ ላይ የጦር መሳሪያ ቅነሳን በሚመለከት በተባበሩት መንግሥታት ልዩ ልዩ መድረኮችም ሆነ በሌሎች ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች አብዛኛዎቹን ሃሳቦች ያቀረቡት ሶቭየት ኅብረትና ሌሎች የሶሻሊስት ሀገሮች መሆናቸው የሚታወስ ነው ።[34] ይሁን እንጂ ኢምፔሪያሊስቶች የበላይነትን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረትና ከዚህም ጋር በተያያዘው ፀረ ሰላም አቋማቸው ምክንያት ብዙዎቹ የተባበሩት መንግሥታት ጥሪዎችና ውሳኔዎች ሥራ ላይ አልዋሉም ።

የገለልተኛ ሀገሮችና የጦር መሣሪያ ቅ ነ ሳ

የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ካተኮረባቸው ዓለም አቀፍ ጉዳዮች መካከል የጦር መሳሪያ ቅነሳ ዋነኛው ነው ። ሌላ የዓለም ጦርነት ቢነሳ የኒኩለር ጦር መሳሪያዎች ተግባር ላይ መዋላቸው

Digitized by Google

እንደማይቀርና ይህም የሰውን ልጅ ከምድረገጽ ሊያጠፋ እንደሚችል የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ያምናል ። ስለሆነም ንቅናቄው የጦር መሳሪያ ቅነሳን አጥብቆ የሚደግፈው ሰውንና የሰውን ልጅ ሥልጣኔ ከጥፋት ለማዳን ነው ።

በዚህም መሠረት በ1961 ቤልግሬድላይ የተካሔደው የመጀመሪያው የገለልተኛ ሀገሮች ስብሰባ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ለሰው ልጆች ደኅንነት ዋነኛውና ባስቸኳይ ሥራ ላይ መዋል ያለበት ጥያቄ መሆኑን አበክሮ አስገንዝቧል ። ጉባኤው ለጦር መሣሪያ የሚወጣው ወጭ ልማት ነክ በሆኑ ሥራዎች ላይ ቢውል ስለሚያስገኘው ጥቅም ጭምር ከተወያየ በኋላ የኑክለየርና የቴርሞ ኑክሊየር መሣሪያዎች እገዳ እንዲደረግ አጥብቆ አሳስቧል ። [33] በተጨማሪም ከላይ እንደተጠቀሰው ይኸው የቤልግሬድ ስብሰባ የተባበሩት መንግሥታት በጦር መሣሪያ ቅነሳ ላይ ልዩ ስብሰባ እንዲያደርግ ሐሳብ አቅርቦ ነበር ።

የኑክሊየር ጦርነት የሚያስከትለውን ጥፋት በማጤን የቤልግሬድ ስብሰባ ተካፋዮች ኃያላን ሀገሮች ጠቅላላ የጦር መሣሪያዎች ቅነሳ እንዲያደርጉና ለዘላቂ ሰላም እንዲጥሩ በጊዜው በነበሩት ለዩናይትድ ስቴትስና ለሶቭየት ኅብረት መሪዎች መልእክት አስተላልፈው ነበር ። [36]

ሆኖም ባለፉት 23 ዓመታት እንደታየው ከላይ የተጠቀሱት ጥሪዎችና ማሳሰቢያዎች የሚፈለገውን ውጤት አላስገኙም ። እንዲያውም የበለጠ አስከፊና አጥፊ መሣሪያዎች በብዛት እየተመረቱ ነው ። በጦር መሣሪያው ቅነሳ በኩል መጠነኛ መሻሻልና እርምጃዎች አስገኝተዋል የሚባሉት ስምምነቶችና ስብሰባዎች ጭምር ፍሬያማነታቸው አጠራጣሪ ሆኗል ። እነዚህ እርምጃዎች የ1963ቱ የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ሙከራን በከፊል የሚያግደው ስምምነት ፣ የ1968ቱ የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎችን ለሌሎች ሀገሮች ማስተላለፍን የሚያግደው ስምምነት ፣ የመጀመሪያው ስትራተጂያዊ ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ ንግግርና በ1978ና በ1982 የጦር መሣሪያን ቅነሳን በሚመለከት የተደረጉት የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ስብሰባዎች ናቸው ። [37]

ይሁን እንጂ የተደረጉትን መሻሻሎች አጠራጣሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ይታያሉ። ከነዚህም ሁኔታዎች መካከል ፣ የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ሙከራዎችን በከፊል የሚያግደውን ስምምነት ያልፈረሙት ሀገሮች ሙከራቸውን የቀጠሉ መሆኑ ፣ ሌሎች ውሉን የፈረሙት ሀገሮችም ስምምነቱ በመሬት ውስጥ የሚደረጉ የኑክሊየር መሣሪያ ሙከራዎችን አይከለክልም በማለት በከርሰ ምድር ሙከራ ከማድረግ አለመቆጠባቸው ፣ የኑክሊየር ኃይል ያልነበራቸው ሀገሮችም የኑክሊየር ጦር መሣሪያ መስፋፋት የሚያግደውን ስምምነት ከፈረሙ አንዳንድ የምዕራብ ሀገሮች በተዘዋዋሪ መንገድ የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ቴክኖሎጂን ማግኘታቸው ጥቂቶቹ ናቸው ። በተጨማሪም ከገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ አባላትም መካከል የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ሙከራን በከፊል የሚያግደውን ስምምነት ያልፈረሙ ሲኖሩ ብዙ ታዳጊ ሀገሮች ባሁኑ ጊዜ ከውጭ በሚያስገቡት ፣ እንዳንድ ጊዜም ሀገራቸው ውስጥ በሚሠሩት መደበኛ (ኑክሊየር ያልሆነ)ጦር መሣሪያ ራሳቸውን እያስታጠቁ ናቸው ። [38]

ይህ አስጊ የሆነ የጦር መሣሪያ እሽቅድድም የዓለም ሰላምን እንደሚያናጋና የተባባሰ የጦርነት አደጋን እንደሚፈጥር ግልጽ ነው።

የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ አባላት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አማካይነት ዓለም አቀፍ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ጉባኤ እንዲደረግ በተደጋጋሚ በጠየቁት መሠረት የመጀመሪያው ስብሰባ በ1978 ተደርጎ ነበር። በ1979 በሀቫና የተካሄደው 6ኛው የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ስብሰባ የ1978ቱን የተባበሩት መንግሥታት የጦር መሣሪያ ቅነሳ ጉባኤ ሰነድ «የሰውን ልጅ ከጦርነት

Digitized by Google

ዕልቂት ለማዳን ለሚደረግ ጥረት መሠረት የጣለ ነው » በማለት ለሰነዱ ያለውን አድ ናቆት ገልጿል ። በ1982 የተካሄደው ሁለተኛው የተባበሩት መንግሥታት የጦር መሣሪያ ቅነሳ ልዩ ስብሰባ ፍሬ ቢስ መሆን ግን እጅግ ያሳዘነው መሆኑን ኒውዴልሂ ላይ የተደረገው የ7ኛው የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ጉባኤ ጠቅሶ ለስብሰባው ውጤት አልባ መሆን ዋናው ምክንያት ደግሞ «የአንዳንድ ኃያላን ሀገሮች ግትር አቋም »[39] መሆኑን አጋልጧል ።

7ኛው ጉባኤ አንዳንድ ኃያላን መንግሥታት (በተለይ ዩናይትድ ስቴትስን የሚመለከት ነው) የሚያራምዱትን «የኑክሊየር ጦርነትን በተወሰነ ቦታ ማካሔድ ይቻላል» የሚለውን ሐሳብ አደገኛነት በጥብቅ አውግዞ ለእነኝሁ ሀገሮች «ደኅንነትና ጥበቃ»[40] ሲባል የሰው ልጅ በኑክሊየር ጦር መሣሪያ አማካይነት ለሚመጣው ዕልቂት መጋለጥ አሳዛኝና ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት አስገንዝቧል ። በተጨማሪም ጉባኤው ሰላምና ደኅንነት የሚገኘው በአጠቃላይና ሙሉ ተፈጻሚነት ባለው በዓለም አቀፍ የቁጥጥር ሥርዓት አማካይነት በሚደረግ የጦር መሣሪያ ቅነሳ መሆኑን ጠቅሶ የኑክሊየር ኃይል ባለቤት ሀገሮች የኑክሊየር ጦር መሣሪያ እሽቅድድም እንዲያቆሙና አጠቃላይ የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ሙከራን የሚያግድ ስምምነት እንዲደረግ ጥሪ አስተላልፏል ።

ሶቭየት ኅብረት ገለልተኛ ሀገሮችና ሌሎች ለሰላም የቆሙ ድርጅቶች ለጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚያደርጉትን ጥረት የምትደግፍ መሆኗን በተደጋጋሚ አሳይታለች። የጦር መሣሪያዎችን ፣ በተለይም የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ቅነሳን በሚመለከት ብዙ ሐሳቦችንም አቅርባለች ። የኑክሊየር ጦር መሣሪያን ለመጠቀም የመጀመሪያዋ አገር እንደማትሆን በመግለጽ ሌሎች የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ባለቤቶችም ይህንኑ እንዲከተሉ ጠይቃለች ። በተጨማሪም በሁለቱም ወገኖች መካከል ያሉት የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲቀነሱ [41] በማለት ያቀረበችው ሃሳብ በቀኝ አክራሪ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ዘንድ እስከዛሬ ድረስ ተቀባይነት አላገኘም ። በ7ኛው የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ስብሰባ ላይ የተገኙት መሪዎች ሶቭየት ኅብረት ከላይ የተጠቀሱትንና የጦር መሣሪያ ቅነሳን በሚመለከት የወሰደቻቸውን ሌሎች እርምጃዎችም አድንቀዋል ።

የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ለጦር መሣሪያ ቅነሳ ከኑክሊየር ጦር መሣሪያ ነፃ የሆኑ አካባቢዎች መፈጠር ወይም መወሰን አንዱ ዘዴ ነው የሚል አስተያየት አለው። የነዚህ አካባቢዎች በየቦታው መከለል ዓለም ቀስ በቀስ ከኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ነፃ ለማድረግ ያግዛል በሚል እምነት በዚህ አኳያ ጥረት ንንዲደረግ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ተደጋጋሚ ጥሪዎችን አስተላልፏል ። [42]

እስካሁን ግን ከኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ነፃ እንዲሆን ስምምነት የተደረሰበት አካባቢ ላቲን አሜሪካ ብቻ ነው ። በተለያዩ ወቅቶች እንደ ደቡብ እስያ ያሉ አካባቢዎች ከኑክሊየር ጦር መሣሪያ ነፃ እንዲሆኑ ሐሳብ ቢቀርብም ባካባቢው ባሉ ሀገሮች (ለምሳሌ በፓኪስታንና ሕንድ መካከል ባለው አለመተማመን) ሐሳቡ ሥራ ላይ አልዋለም ። የሕንድ ውቅያኖስ የሰላም ቀጣና እንዲሆን በ1970 ሉሳካ (ዛምቢያ) ላይ በተደረገው የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ሐሳቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀርቦ በ1971 በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ድጋፍ አግኝቶ ነበር ። ሆኖም ባካባቢው ባሉ የኃያላን መንግሥታት ወታደራዊ ይዞታዎች ምክንያት በሥራ ላይ ሊውል አልቻለም ። 7ኛው የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ስብሰባ የሕንድ ውቅያኖስ የሰላም ቀጣና እንዲሆን ፣ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ወደ ጦር መሣሪያ ሰፈር የለወጣት ደሴት ዲያጎ ጋርሲያም

Digitized by Google

ለሞሪሽስ እንዳትመለስ ጠይቆ በተጨማሪም በ1984 የሕንድ ውቅያኖስን የሰላም ቀጣና ስለማድረግ ጉዳይ የሚነጋገር ስብሰባ እንዲካሔድ አሳስቧል ። [43]

ኒውዴልሂ ላይ የተደረገው የገለልተኛ ሀገሮች ስብሰባ የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ ቅድሚያ የሚሰጠው ችግር ቢሆንም የኬሚካል ጦር መሣሪያዎች እገዳ ፣ ጠፈርን (ሕዋውን) ለሰላማዊ ተግባሮች ብቻ የማዋል ጉዳይና የመደበኛ ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ አስፈላጊና ባፋጣኝ ሥራ ላይ መዋል ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው በማለት አስገንዝቧል ።

የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ በመንግሥታት መካከል ለሚደረገው የጦር መሣሪያ እሽቅድድምና በየቦታው የሚቋቋሙት የጦርነት ስትራተጂያዊ ቡድኖችና የጦር ሠፈሮች የዓለምን ሰላም አደጋ ላይ ጥለውታል የሚል እምነት አለው ። የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ኃያላን መንግሥታት«በሰላም አብሮ መኖር»የሚለውን መርሕ እንዲከተሉና ወደ ጠቅላላ ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ የሚመሩ እርምጃዎችን እንዲወስዱ በ«ኒውዴልሂው መልእክት» [44] ጥሪ አስተላልፈዋል ። በዚህ መስከ ሶቭየት ኅብረት የወታደራዊ ቡድኖችን መስፋፋት በተደጋጋሚ ተቃውማለች ። የኔቶና የዋርሶ ጦር ቃል ኪዳኖችም በአንድ ጊዜና በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲፈርሱ ሐሳብ አቅርባ በኔቶ አባላት በኩል ግን ተቀባይነት አላገኘም ። [45] በዚህም ተስፋ ባለመቁረጥ የኔቶና የዋርሶ የጦር ቃል ኪዳን ክልሎች ወደ ሌላው የዓለም ክፍል እንዳይስፋፉ ስምምነት እንዲደረግ ያቀረበችው ጥያቄም በኢምፔሪያሊስቱ ካምፕ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል ።

በሌላ በኩል የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ለጠብ አጫሪነት ተግባሩ እንዲመቸው በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ወታደራዊ ሰፈሮችን ማስፋፋቱን ተያይዞታል ። በአፍሪካና በእስያ ሀገሮች ላይ ለሚደረግ ወታደራዊ የማጥቃት እርምጃ እንዲመቸው የሕንድ ውቅያኖስን መነሻ አድርጓል ። በተጨማሪም የአሥራ ዘጠኝ ሀገሮች ግዛትን ፣ የሕንድ ውቅያኖስንና የፋርስን (ፐርሺያን) ባሕረ ሰላጤ የሚያቅፍ ማዕከላዊ ወታደራዊ ዕዝ (CENTCOM) በመመሥረት ፣ ከደቡብ አፍሪካ እስከ ፓስፊክ ባለው አካባቢ የጦር ሰፈሮች ቀጣና ከልሎ [46] የመስፋፋት ዓላማውን በከፍተኛ ደረጃ ሥራ ላይ እያዋለ ነው ።

የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ የተባበሩት መንግሥታት ለዓለምአቀፍ ችግሮች መፍቻ ዋነኛው መድረክ መሆኑን በተደጋጋሚ አስታውቋል ። የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስጠባቂነት ኃይል እንዲጠናከር የሚደረጉ ጥረቶችን ይደግፋል ። እንደሌሎቹ የንቅናቄው ስብሰባዎች 7ኛውም ጉባኤ የተባበሩት መንግሥታት በጦር መሣሪያ ቅነሳ በኩል ያለውን ትልቅ ኃላፊነትና ሚና ጠቅሷል ። እንዲያውም የመጀመሪያዎቹ የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ስብሰባዎች የተባበሩት መንግሥታት የጦር መሣሪያ ቅነሳ ንግግር የሚደረግበት ብቸኛ መድረክ እንዲሆን አሳስበው ነበር ። [47] በኋላ ግን የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ወደ ሌሎች እንዳይሰራጩና የሚያግድ ስምምነት የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ሙከራን በከፊል የሚያግደው ስምምነትና እንዲሁም የስትራተጂያዊ ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ ውይይቶች የተደረጉት ከተባበሩት መንግሥታት መድረክ ውጭ በኃያላን መንግሥታት መካከል በመሆኑና እነዚህም ስምምነቶች በጦር መሣሪያው እሽቅድድም ላይ መጠነኛ መገታትን በማስከተላቸው 7ኛው የገለልተኛ ሀገችር ንቅናቄ ጉባኤ የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ባለቤቶች በድርድራቸው እንዲገፉበት ጠይቆ በውይይታቸው ላይ የደረሱበትን ውጤት ሁሉ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በየጊዜው እንዲያስታውቁ አሳስቧል ።

የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ የጦር መሣሪያ እሽቅድድምን መቃወም ከተመሠረተ

Digitized by Google



የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ፍላጎት
« NeWs » ከተባለ የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ መጽሔት ቁጥር 5/83 የተወሰደ

ቤት መርሆዎች አንዱ ነው ። ከዚህ በተጨማሪ ለጦር መሣሪያ የሚውለውን ከፍተኛ ወጭ ለልማት የማዋሉ አስፈላጊነት የጦር መሣሪያ ቅነሳን አንገብጋቢነት ጉልህ አድርጉታል ። ስለዚህ የጦር መሣሪያ እሽቅድድም ባንድ በኩል የገለልተኛነትን መርሕ የሚፃረር በሌላ በኩል ደግሞ የኢኮኖሚ ዕድገትን ወደኋላ የሚያጓትት መሆኑ የገለልተኛ ሀገሮች ለጦር መሣሪያ ቅነሳ ትግል ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡት አድርጓቸዋል ።

የዓለም ሰላም ምክር ቤት

ባሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ በሚደረገው ትግል መንግሥታዊ ያልሆኑ ብሔራዊ፣ ዓለምአቀፋዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። ይህም ድርሻቸው በ1978 እና በ1982 በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ አማካይነት በተካሔዱት ልዩ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ጉባኤዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል ። ከነዚህም ለሰላም ከቆሙ ድርጅቶች መካከል ለዓለም ሰላም ምክር ቤት፣ የአፍሮ ኤሲያ ሕዝቦች የትግል አንድነት ድርጅት የአፍሪካ፣ የእሲያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች የትግል አንድነት ድርጅት ጥቂቶቹ ናቸው ። ከነዚህ ድርጅቶች መካከል የዓለም ሰላም ምክር ቤት ለዓለም ሰላም መከበርና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ ያደረጋቸውን ትግሎች ባጭሩ ለማየት እንሞክራለን ።

የዓለም ሰላም ምክር ቤት መመሥረት መንስኤው የሆነው ርክሉ በምትባል የፖላንድ ከተማ ለሰላም ተቆርቋሪ የሆኑ ምሁራን «ዓለም አቀፍ የምሁራን ስብሰባ» በተሰኙው ጉባኤ ላይ የዓለም ጦርነት እንዳይነግ በማሳሰብ ጥሪ ያስተላለፉበት ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል ። ይኸው ጥሪያቸው ሚያዝያ 1949 በፓሪስና ፕራግ የ72 ሀገሮች ልኡካን የተገኙበት የመጀመሪያ «ዓለም አቀፍ የሰላም ጠባቂዎች» ጉባኤ እንዲካሔድ ምክንያት ሆነ ። የዚህን ታሪካዊ ተልዕኮና መንፈስ የታወቁት የፈረንሳይ ሳይንቲስት ፣ የኖቤል ተሸላሚና በኋላም የዓለም ሰላም ምክር ቤት የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ፍሬዴሪክ በተናገሩት የመክፈቻ ንግግር ማጠቃለል ይቻላል ። « - - ከእንግዲህ ወዲህ ሰላም ማስከበር የሁሉም ሰው ተግባር ይሆናል ። አንድ ሰው ወይም ሀገር ሰላምን ለብቻው መጠበቅ ወይም ማስከበር አይችልም ። »[49]

በፓሪስና ፕራግ ስብሰባዎች ላይ የተጀመረውን ሥራ የሚቀጥል ዓለም አቀፍ ኮሚቴ ወዲያው ተቋቋመ ። በ1949 እጋማሽ ላይ በሁሉም ክፍለ ዓለማት በሚገኙ 70 ሀገሮች ብሔራዊ የሰላም ኮሚቴዎች ተመሠረቱ ። ሁለተኛው የንቅናቄው ዓለምአቀፍ ስብሰባ ኅዳር 1950 በፖላንድ ዋና ከተማ ዋርሶ ላይ ተካሂዶ የዓለም ሰላም ምክር ቤት ሕልውናውን አገኘ ።

ምክር ቤቱ ሥራውን ለማካሔድ የሚያስችሉት አራት መዋቅራዊ አካላት አሉት ፤ እነዚህም የምክር ቤቱ ካውንስል ፣ ፕሬዚደንሻል ኮሚቴ ፣ ቢሮና ጽሕፈት ቤት በመባል ይታወቃሉ ። የድርጅቱ ዋና ጽሕፈት ቤት ፊንላንድ ዋና ከተማ ሄልሲንኪ ሲሆን ከናዋው ጽሕፈት ቤት ሌላ ሦስት የአህጉራት ወይም የአካባቢ ተወካዮች ይገኙበታል ።

የዓለም ሰላም ምክር ቤት በአሁኑ ጊዜ ከ137 አገሮች የተውጣጡ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ንቅናቄዎች፣ ፓርቲዎች፣ ወዘተ . . . የሚሳተፉበት ለሰላም፣ ለአርነትና ለፍትሕ የቆመ ዓለምአቀፋዊ ድርጅት ሲሆን በየሀገሩ የሚገኙት ብሔራዊ የሰላም ንቅናቄዎችን ፣ የሙያ ማኅበራትን ፣ የሃይማኖት ፣ የፖለቲካ፣ የሴቶችና የወጣቶች ድርጅቶችን ያቅፋል ።

የዚህ ምክር ቤት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ።[50]

—እሠቃቂ እልቂትን የሚያስከትሉ መሣሪያዎችና የጦር መሣሪያ እሽቅድድም

Digitized by Google

ማቆም ፣ የባዕድ ወታደራዊ ጦር ሰፈሮች መዝጋትና አጠቃላይ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ማድረግ ፣

—ማንኛውም ዓይነት የዘር መድልዎና ቅኝ አገዛዝን ማስወገድ ፣

—የሕዝቦችን የነፃነትና የልዕልና መብት ማስከበር ፣

—የሀገሮችን የግዛት አንድነት ማስከበር ፣

—በሀገሮች መካከል በእኩልነትና በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ የባህልና የንግድ ግንኙነቶች እንዲመሠረት ማድረግ ፣

—የተለያዩ ርዕዮተ ዓለም በሚከተሉ ሕዝቦች መካከል የሰላም አብሮ መኖር መርሕን በተግባር መተርጐም ፣

—በመንግሥታት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በኃይል ሳይሆን በሰላም እንዲፈቱ አስተዋጽኦ ማድረግ ።

የዓለም ሰላም ምክር ቤት ዓላማዎችንና ተግባሮችን የሚያስተዋውቅበት ኒው ፔርስፔክቲቭ (New Respective) እና ፒስ ኩሪየር (Peace Courier) የተባሉ መጽሔቶችና ምክር ቤቱ በአሳሳቢ ሁኔታዎች ላይ የተወያየባቸውንና የስብሰባ ነጥቦችን የያዙ ሌሎች ጽሑፎች በእንግሊዝኛ ፣ በፈረንሳይና ፣ በጀርመንኛና በእስፓንኛ ቋንቋዎች በየጊዜው ያወጣል ።

ምክር ቤቱ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ ከሚጠቀምባቸው መድረኮች መካከል በተናጠልም ሆነ ከሌሎች ብሔራዊ ወይም ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሚያካሂዳቸው ስብሰባዎችና ቅስቀሳዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ። የዓለም ሰላም ምክር ቤት የተቋቋመላቸውን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ባለፉት 34 ዓመታት በላምን ፣ የጦር መሣሪያ ቅነሳን ፣ ብሔራዊ ነፃነትን የሚያራምዱና የሚያጠናክሩ ፣ በዘር መድልዎ ፣ በቅኝ አገዛዝና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ላይ የሚካሄዱ ትግሎችን የሚያግዙ አያሌ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል ። በተለይም የጦር መሣሪያው እሽቅድድም በአደገኛ ሁኔታ ከተባባሰበት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ምክር ቤቱ በጦር መሣሪያ ቅነሳ ፣ በተለይም የኑክሊየር ጦርነትን ለማስወገድ በሚደረጉ ጥረቶች ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው ። በየሀገሩ የሰላም ኮሚቴዎች የታቀፉት የሙያ ማኅበራት ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ የሴቶች ፣ የወጣቶችና የሃይማኖት ድርጅቶች ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚያደርጉትን ጥረት በመደገፍና በማጠናከር፣ የዓለም ሕዝብ የኑክሊየር ጦርነት የሚያስከትለውን እልቂት በትክክል እንዲረዳ ፣ በብሔራዊ ፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች ስብሰባዎችና ውይይቶችን በማካሄድ ፣ ከተባበሩት መንግሥታትና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ለሰላም ከቆሙ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የዓለም ሰላም ምክር ቤት ለጦር መሣሪያ ቅነሳና ለሰላም መከበር በሚደረጉ ትግሎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ፤ እያደረገም ነው ።

ምክር ቤቱና ሌሎች የሰላም ኃይሎች በሚያደርጉት ጥረት የዓለም ሕዝብ ፀረ ጦርነት አቋም እየጠነከረ የመጣ ለመሆኑ አያሌ መረጃዎች አሉ ። በ1982 በግንቦትና ሰኔ በተካሄደው ሁለተኛው የተባበሩት መንግሥታት ልዩ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ጉባኤንና በየዓመቱ በጥቅምት ወር የሚታሰበውን የተባበሩት መንግሥታት «የጦር መሣሪያ ቅነሳ ሳምንትን» በመደገፍ ፣ በቦን (በምዕራብ ጀርመን) የተደረገውን የኔቶ ስብሰባና ፕሬዚዳንት ሬጋን በምዕራብ አውሮፓ ያደረጉትን ጉብኝት በመቃወም፣ በተለይም በ1983 በሰሜን አሜሪካ ፣ በአውሮፓና በእስያ (በተለይ በሕንድ) አህጉራት በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች የተካፈሉባቸው ፀረ ጦርነት ትዕይንተ ሕዝቦችና እንቅስቃሴዎች [51] የዓለም ሕዝብ ለጦር መሣሪያ እሽቅድድምና ለጦር መሣሪያዎች ክምችት ያለውን ተቃውሞ በግልጽ አሳይተዋል ። ፀረ ጦርነት ንቅናቄ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካም እየተስፋፉ መሆኑን አያሌ መረጃዎች ይጠቁማሉ ።

Digitized by Google

ባሁኑ ጊዜ የሚካሔደው ፀረ ጦርነት እንቅስቃሴ የማያቅፈው የኅብረተሰብ ክፍል የለም ። ሴቶችና ወጣቶች ፣ የተለያዩ የሃይማኖት ቡድኖች ፣ የሕክምና አዋቂዎች፣ ሳይንቲስቶች ፣ የሕግ አዋቂዎች ፣ ጋዜጠኞች ፣ መምህራን ፣ ከያኒያን ፣ ወዘተ . . . ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ ከቆሙ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ታላቅ የሰላም ኃይል ሆነዋል ።

እነዚህ ፀረ ጦርነት ቡድኖች በመካከላቸው ያለውን ትብብር ለማጠናከርና ኢምፔሪያሊስቶች በሰላም ኃይሎች መካከል መከፋፈል እንዲኖር የሚሸርቡትን ደባ ለመቋቋም ከሰኔ 14—19 ቀን 1983 በዓለም ሰላም ምክር ቤት ትብብር በፕራግ አንድ ዓለም አቀፍ የሰላም ስብሰባ አካሂደው ነበር ። የዚህ ስብሰባ ተካፋዮች በብሔራዊ ፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሰላም በሚደረገው ጥረት በተለይም የኑክሊየር ጦርነትን ለማስወገድ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ፣ የጦር መሣሪያ እሽቅድድም በኤኮኖሚና በማኅበራዊ መስኮች ስለሚያስከትላቸው ችግሮች ፣ በአፍሪካ በእስያ ፣ በላቲን አሜሪካና በካሪቢያን አካባቢ ለሰላም ፣ ለፍትሕና ለብሔራዊ አርነት የሚደረጉ ትግሎች ላይ ፣ በአውሮፓ ስላለው የኑክሊየር ጦርነት ሥጋት ፣ የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሰላማዊ የማምረቻ ተቋሞች ቢለወጡ ስለሚያገኙት ጥቅምና [52] ሌሎች ተመሳሳይ አርእስትላይ ተወያይተዋል ።

በተጨማሪም በ1983 የዓለም ሰላም ምክር ቤት የኑክሊየርን ጦርነት ለማስወገድና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ በብሔራዊ ደረጃ የሚደረጉ ስብሰባዎች ፣ የሰላም ጥሪዎች፣ ሰልፎችንና ሌሎች ቅስቀሳዎችን በማስተባበርና ድጋፍ በመስጠት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ። ሁለተኛው የተባበሩት መንግሥታት ልዩ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ጉባኤ ዓለም አቀፍ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ቅስቀሳ እንዲደረግ ፣ ጠቅላላው ጉባኤም 1980ዎቹ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ሁለተኛ ዘመን እንዲሆን [53] ያሳሰበው ተግባራዊና የተሳኩ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ግን የዓለምን ሕዝብ ከፍተኛ የሰላም ፍላጐት በመፃረር አዳዲስና አደገኛ የጦር መሣሪያዎች ማምረታቸውን ፣ የዓለምንም አካባቢ በጦር መሣሪያቸው ማጥለቅለቃቸውን በሰፊው ተያይዘውታል ። ስለዚህ የዓለም ሰላም ምክር ቤት ለሰላም የቆሙ ኃይሎችን እያስተባበረ ትግሉን ለመቀጠል የ1984 መርሐ ግብሩን በሚከተሉት ነጥቦች ላይ አርቅቋል ። [54]

—አዳዲስ የአሜሪካ ሚሳይሎች በአውሮፓ እንዳይተከሉ ፣ የተተከሉትም እንዲነሱ፣ በምዕራብና በምሥራቅ አውሮፓ የተተከሉት የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች እንዲነሱ ጥረት ማድረግ ፣

—ሁሉም የኑክሊየር ኃይል ባለቤቶች በተናጠልም ሆነ በጋራ የኑክሊየር ጦር መሣሪያን ለመጠቀም የመጀመሪያዎቹ እንደማይሆኑ ቃል እንዲገቡ መጠየቅ ፣

—የኒውትሮን ቦምብ ፣ የኬሚካልና የባክቴሮሎጂካል ጦር መሣሪያዎች እንዲታገዱ መጣር ፣

—ሕዋው ለጦርነት አገልግሎት እንዳይውል ጥረት ማድረግ ፣

—የስቶክሆልሙ ጉባኤ ወደ ጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚያመሩ ፣ መተማመንን የሚያሳድሩና ዓለምአቀፍ ውጥረትን የሚቀንሱ እርምጃዎች እንዲወሰድ መጠየቅ፣

—በዋርሶና በኔቶ የጦር ቃል ኪዳን ሀገሮች መካከል ጦርነት እንዳይነሳና ሰላማዊ ግንኙነቶችን የሚፈጥሩ ስምምነቶች እንዲደረጉ የሚጠይቁ ሐሳቦችን መደገፍ ፣

—የመካከለኛው አውሮፓ ፣ የባልካንና የኖርዲክ ሀገሮች ከኑክሊየር ጦር መሣሪያ ነፃ እንዲሆኑ መጣር ፣

—ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትን መቃወም ፣ ለብሔራዊ ነፃነት የሚደረገውን ትግል መደገፍ ፣

Digitized by Google

—በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ፣ በገለልተኛ ሀገሮችና በአፍሪካ አንድነት ድርጅት መርሆዎች መሠረት ለችግሮች መፍትሔ መፈለግ ፣

—አፍሪካ ፣ መካከለኛው ምሥራቅ ፣ የሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ ፣ ሩቅ ምሥራቅ፣ ላቲን አሜሪካና የካሪቢያን አካባቢ ከኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ፣ ከባዕዳን የጦር ሰፈሮችና ወታደራዊ ቡድኖች ነፃ እንዲሆኑ መጣር ፣ እስያ ፣ ደቡብ ምሥራቅ እስያና የሜዲትራንያን አካባቢ የሰላምና የመተባበር ቀጣና እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ ፣

—አዲስ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲገነቡ ጥሪ የተደረገበት 10ኛ ዓመት በ1984 ሲታሰብ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች ከጦር መሣሪያ ክምችት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማስመልከት በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች ቅስቀሳ ማድረግ ፣

—ዘረኝነትንና የጭቆና አገዛዝን መቃወምና የሰብአዊ መብት እንዲከበር መጣር፣

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ፣ የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄና ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም በኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ፀረ ሰላም አቋም ምክንያት ባሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ከፍተኛ የጦርነት ሥጋት አለ ።

በአውሮፓ አዲስ የተጠመዱት ሚሳይሎች ያለውን የጦር መሣሪያ ሚዛን ያቃወሱ ሲሆን ይህ እርምጃ በጀኔቫ መካከለኛ ርቀት ሚሳይሎች ላይ የሚደረገውን ድርድር አወዛጋቢና የደፈረሰ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ በስትራተጂ ጦር መሣሪያ ዎች ላይ የሚካሔደውንም ንግግር አደገኛ ሁኔታ ላይ በመጣል የጦር መሣሪያ እሽቅድድሙ በአዲስ መልክ እንዲቀጥል አድርጉታል ። ከዚህም ሌላ ባሁኑ ወቅት የፀረ ሕይወት ፣ የኬሚካልና ሌሎች አሠቃቂ እልቂትን የሚያስከትሉ መሣሪያዎች በብዛት እየተመረቱ ናቸው ።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች የኑክሊየር ጦር መሣሪያን በሚመለከት አደገኛ አስተሳሰቦችንም እያራመዱ ናቸው ። «ቀድሞ የማጥቃት እርምጃ» «የኑክሊየር ጦርነትን በተወሰነ ክልል ማካሄድ» እና ሌሎች ተመሳሳይ ሐሳቦች የኒክሊየር ጦርነትን ማካሔድና ማሸነፍም ይቻላል የሚል የተሳሳተ እምነት በመፍጠር የኑክሊየር ጦርነትን የመለኮስ አደጋን የበለጠ አባብሶታል። ፀረ ሰላም ኃይሎች ወታደራዊ የበላይነትን ለማግኘት በሚያደርጉት ከፍተኛ ጥረትም ቀደም ብለው በምዕራብ አውሮፓና በሩቅ ምሥራቅ ከተዘረጉት ወታደራዊ መዋቅሮች ሌላ አዳዲስ ወታደራዊ ይዞታዎችንና ቡድኖችን በደቡብ ምዕራብ እስያና በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ በመመሥረት ላይ ይገኛሉ ። እነዚህ እርምጃዎችና በየጊዜውም በመካከለኛው አሜሪካ ፣ በካሪቢያን አካባቢና በመካከለኛው ምሥራቅ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የሚያካሔደውጣልቃ ገብነት በአፍሪካ ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ ለብሔራዊ ነፃነትና ለኤኮኖሚ ዕድገት የሚደረገውን ትግል መራራና ከፍተኛ መስዋዕትነት የሚጠይቅ አድርገውታል ።

ባሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያሉት የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች የዓለምን ኅብረተሰብ ለማጥፋት ከእጥፍ ድርብ በላይ ኃይል አላቸው ። ሆኖም የአሜሪካ የጦርነት ፖሊሲ ቀያሾች የጦር መሣሪያ እሽቅድድም ማባባስን ተያይዘውታል ። በነርሱ አስተያየት እሽቅድድሙ ፣ ሀ/ የአሜሪካ መንግሥት በኑክሊየር ጦር መሣሪያ ሶቭየት ኅብረትን ለመብለጥና ይህችኑ ሀገር በኑክሊየር ጦርነት ለማሸነፍ ያስችላል ፣ ለ/ ሶሻሊስት ሀገሮች ለጦር መሣሪያ የሚያወጡት ወጭ ካለማቋረጥ እያሻቀበ እንዲሔድ በማድረግ ኤኮኖሚያቸውን ብሎም ሶሻሊዝምን ለማዳከም ይረዳል ። ሆኖም የጦር መሣሪያ እሽቅድድሙ በካፒታሊስት ሀገሮች በኤኮኖሚው ፣ በፖለቲካውና በማኅበራዊ

Digitized by Google

መስኮች ያስከተለው ችግር የኢምፔሪያሊስቶች ሴራቸው በራሳቸው ላይ ችግር እየፈጠረባቸው ለመሆኑ አያሌ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የመሣሪያ እሽቅድድሙ በተጧጧፈበትና የኑክሊየር ጦርነት በዓለም ላይ በአንዣበበበት ባሁኑ ወቅት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ፣ የዓለም ሰላም ምክር ቤትና ሌሎች የሰላም ኃይሎችና ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ በሚደረጉ ጥረቶች ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ያለባቸው ኃላፊነት ከፍተኛ ነው። መንግሥታት የዓለም ህብረተሰብን ህልውና አደጋ ላይ የጣለውን የጦር መሣሪያ እሽቅድድም እንዲያቆሙ፣ ዓለምአቀፋዊ ችግሮችን ለመፍታት ኃይል ሳይሆን ውይይት እንዲጠቀሙ፣ ይህንንም በተግባር በማዋል የሰውን ልጅና ሥልጣኔን ከጠቅላላ ጥፋት እንዲያድኑ የሰላም ትግል በሁሉም አቅጣጫ መቀጠል ይኖርበታል።

የግርጌ ማስታወሻ

1.. ትግል ለሰላም ቅጽ 4 ቁ. 9 ነሐሴ 1975 ገጽ 9-10
2. *UNITED NATIONS AND DISARMAMENT* 1945-1970, Department of Political and Security Affairs, page 1.
3. *Ibid p.* 2.
4. *Ibid, p.* 3.
5. Joseph Gold Blatt, *Agreement for Arms Control SIPRI* (London: Taylor and Francis Ltd., 1982), p. 345.
6. *Ibid, p.* 344.
7. *United Nations Versus The Armed Race.* (New York: United Nations Departmen of Public Information, 1980), p. 3.
8. *Ibid,* p. 6.
9. *Ibid.*
10. *Ibid.*
11.. *International Affairss A monthly* journal of Political Analysis, No. 9, 1982, p. 23.
12. *Fact Sheet No.* 23, (New York: United Nations Centre for Disarmament) p. 5 and 6.
13. *The Arms Race and Arms Control SIPRI* (London: Taylor and Francis Ltd., 1983), p.237.
14. *Ibid,* p. 238.
15. *Ibid.*
16. *Disarmament*: Periodic Review by the United Nations, Vol. 6 No. 2 (New York: Department of Disarmament Affairs, 1983), p. 3.
17. *International Affairs,* No. 9 p. 24.
18. *New Times*: A Soviet Weekly Affairs, No. 38, 1983, p. 5.
19. *The Arms Race and Arms Control*: SPIRI, 1983, p. 240.
20. *United Nations and Disarmament,* 1945-1970, p. 4.
21. *Ibid,* p. 5.
22. *Ibid,* p. 122.
23. *United Nations Versus the Arms Race,*
24. *Ibid,* p. 353.
25. *Ibid,* p. 351.
26. *United Nations Versus the Arms Race,* p. 5.
27. *Ibid.*
28. *The Arms Race and Arms Control,* 1983, p. 227.
29. *United Nations Versus The Arms Race,* p. 7.
30. *U.N., Fact Sheet No.* 23, p. 1.
31. *United Nations Today* 24 *October* 1977, p. 30.

Digitized by Google

32. *Joseph Gold Blatt,* Np. 348.

33. *U.N., Fact Sheet No.* 23, p. 6.

34. *International Affairs,* No. 8, 1978, p. 13.

35. *Ibid.*

36. *Ibid.*

37. *Ibid,* p. 2.

38. *Ibid.*

39. *Ibid,* p. 3.

40. *Ibid.*

41. *International Affairs*: A Monthly Journal of Political Analysis; No. 6, June, 1983. p. 21.

42. *International Affairs,* No. 6 p. 22.

43. *Disarmament,* p. 6.

44. *Ibid,* p. 7 & 8.

45. *International Affairs,* No. p. 21.

46. *Ibid,* p. 19.

47. *Disarmament,* 1983, p. 7.

48. *Ibid.*

49. *Ibid.*

50. *The World Peace Council: What it is and What it does*/Helsinki, Information Centre of the W.P.C., 1978, p. 6.

51. *World Peace Council Programme of Action,* 1983; Helsinki Information Centre of the World Peace Council, p. 4.

52. *Op. Cit.* p. 9.

53. *Ibid.*

54. *WORLD PEACE COUNCIL ACTION PROGRAMME OBJECTIVES* 1984. Helsinki, Information Centre of the World Peace Council, 1984, p. 17.

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

BSPP

መስከረም

HOOVER
OCT 31 1985
INSTITUTION

- የሕብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር
- የካድሬ ስያሜና ተግባር በኢትዮጵያ አብዮት
  - ካለፍንበት ልምድ
- የምግባር ግንዛቤ - በማሌ አመለካከት
- የኢምፔሪያሊዝም ሥነ-ልቦናዊ ጦርነት
  - ስልትና መድረኮች

ርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 5 ቁጥር 22
ሰኔ 1977

Digitized by Google

Digitized by Google

Meskerem ET489281-1

መስከረም

ቅጽ 5 ቁጥር 22
ሰኔ 1977

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

የዝግጅት ገጽ 3

የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር 7
—አበበ ወርቁ

የካድሬ ስያሜና ተግባር በኢትዮጵያ አብዮት—ካለፍንበት ልምድ 36
—ሰሎሞን ገብሬ

የምግባር ግንዛቤ—በማሌ አመለካከት 50
—ኢሳይያስ ደምሴ

የኢምፔሪያሊዝም ሥነልቦናዊ ጦርነት—ስልትና መድረኮች 62
—ደርበው ተመስገን

ማውጫ 76
—ደግፌ ገብረ ጻድቅ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google



ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

በምግብ እራሳችንን እንድንችል

ምግብ ለሕልውና ያለው ወሳኝነት ለማንም ግልፅ ነው ። ስለዚህም በማናቸውም የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ኅብረተሰብ ተቀዳሚ ትኩረት የምግብ ፍላጐትን ማርካት ነው ፤ ይህንኑ መሠረታዊ የሕልውና ዋስትና ለማስገኘት በግብርና ረገድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ወሳኝ ናቸው ። ግብርና በአጠቃላይ የምግብና የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ መገኛ ከመሆኑም ባሻገር በተለይ በኋላቀር አገሮች የብሔራዊ ኢኮኖሚ ዋልታና የዕድገት መቀናጠሚ አርካብ ነው ። ኢሠፓ ከዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ በመነሳትና አገራችን የምትገኝበትን የዕድገት ደረጃ በማጤን «የምግብ እህል እጥረትን ለማስወገድ በምግብ አቅርቦት ራስን ለመቻል፣ ለኢንዱስትሪ ዕድገት የሚያስፈልጉትን ጥሬ ዕቃዎች በአስተማማኝ ለማቅረብና፣ . . . ለኢኮኖሚው ግንባታ መራመድ የሚያስፈልገውን ክምችት ለማመንጨት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት መፋጠን ወሳኝነት አለው » በማለት በፕሮግራሙ በግልጽ አመልክቷል ።

ይህንን ትክክለኛ መመሪያ በተግባር መተርጐም ወይም ለለመተርጐም በዕድገታችን ላይ ምን ያህል ተፅዕና እንዳለው በአጠቃላይ የሚታወቅ ጉዳይ ቢሆንም ፣ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከመቼውም በከፋ ሁኔታ ከደረሰብን የተፈጥሮ መዛባት ያስከተለብንን ችግር ለመቋቋም የግብርና ተግባራችን መሳካት ወይም አለመሳካት ፍጹም የሕልውና ጥያቄ መሆኑ በገሐድ ታይቷል ። በግብርና የተሳካ ውጤት አለመገኘት ለረሃብ የሚያጋልጠን ከመሆኑም ሌላ ጠቅላላ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያችን እንዲገታ ያደርጋል ። በአገር ውስጥ የምርት ፣ የልውውጥና የክፍፍል ሥርዓት እንዲተጓጉል ከማድረጉም ሌላ ከውጭ የሚያስፈልጉንን መሠረታዊ ሸቀጦችና የልማት መሣሪያዎች ወደአገር ውስጥ ለማስገባትም እንዳይቻል ያደርጋል ። የልማት ሂደት መደናቀፍ የሚያስከትለው ጉዳት ደግሞ በዚያ ችግሩ በደረሰበት ወቅት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በመስዋዕትነት ካልተጋፈጡት ለረጅም ጊዜ ሊጉዳ የሚችል ነው ።

ዛሬ አገራችን ከምትገኝበት የዕድገት ደረጃ አንፃር ጊዜያዊ ፍላጐተቻችንን ለማርካትም ሆነ ለዘላቂው ዕድገታችን መሠረት ለመጣል የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ አጥፍ ድርብ ጥረት ከማድረግ ሌላ አማራጭ የለንም ። ከግብርና የመነሻ ጥሪት ሳንይዝ የአጭርም ሆነ የረጅም ጊዜ ፍላጐታችንን ከኢንዱስትሪ ፣ ከማዕድንና ከንግድ በሚገኝ ፣ ውጤት ለማካካስ ቀላል አይሆንም ።

በተለይ ዛሬ በምንገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ተስፋችንን በአብዛኛው በግብርና ላይ ለመጣል መገደዳችን ዕውቅ ነው ። ለመሆኑ ይህን ተስፋችንን ዕውን ለማድረግ የአገራችን የግብርና አቅም እራሱ ምን ያህል ነው ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ። በጥቅሉ ሲነገር ከናረው ባሻገር ተጨባጭ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የኢትዮጵያችን የግብርና ዕድል ዛሬም በጣም ሰፊ ነው ። መጥኖ ከሚያልፍ የዝናብ ወቅት ከሚጠቀመው

የግብርና ክፍል ሌላ ወንዞቻችንን ገርተ ጥቅም ላይ በማዋል ለማስገኘት የሚቻለው የልማት ውጤት እጅግ ከፍተኛ ነው። በትላልቅ ወንዞች ሊለማ የሚችለው መሬት ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር በላይ እንደሚሆን የሚገመት ሲሆን፣ ትናንሽ ወንዞችን በመጥለፍና አነስተኛ ግድቦችን በመሥራት ደግሞ እስከ 300,000 ሄክታር መሬት ለማልማት እንደሚቻል ታውቋል።

ከአዝርዕት ሌላ በከብት በኩል ልናካሂድ ከምንችለው የላቀ ልማት በመለስ ዛሬ ባለን ከፍተኛ ሀብት እንኳን ተጠቃሚነታችን እጅግ የተወሰነ ነው። አገራችን በከብት ሀብት መጠን በአፍሪካ የመጀመሪያውን፣ በዓለም ደግሞ የአሥረኛነትን ደረጃ እንደያዘች ይነገራል። ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ ከሚታየው እጅግ አነስተኛ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አንፃር የዚህ ድልብ ሀብት ተጠቃሚ መሆን ጀምረናል ለማለት አያስደፍርም።

የዕድገት መነሻችን ያለጥርጥር ግብርና መሆኑን ፓርቲያችን ባስገነዘበው መሠረት ለዚህ ዐቢይ የብሔራዊ ኢኮኖሚያችን ክፍል እጥፍ ድርብ ትኩረት ልንሰጥና ፍጹም ያልተቆጠበ ጥረት ልናደርግበት ይገባል። ከተግባር መረዳት እንደቻልነው በተፈጥሮ መተማመን ብቻ የትም ሊያደርሰን አይችልም። ይልቁንም ለማናቸውም ለሥልጣኔ ወይም ለአብዮታዊ የዕድገት እመርታ የተነሳ ሕዝብ ብቁነት መሠረታዊ መለኪያ ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ያለው ችሎታ ነው። ከዚህ አንፃር ሥር ነቀል አብዮት በማካሄድ ላይ የምንገኝ ከመሆናችንም ሌላ ከአብዮታችን ፍንዳታ ጀምሮ በተግባር የተፈተንን እንደመሆናችን ጊዜያዊ ችግርን መቋቋም ብቻ ሳይሆን ላለምነው የልማት ግብም እንደምንበቃ እርግጠኞች ነን።

ሕዝባችን የተደራጀና ኃይሉን ያስተባበረ እንደመሆኑ ፍላጎቱን በተግባር የመተርጎም ችሎታውን በተደጋጋሚ አስመስክሯል። በቅርቡ በድርቅ ምክንያት በተባባሰ መልክ የተከሰተውን የተፈጥሮ ችግር ለመቋቋም የፓርቲያችን ማዕከላዊ ኮሚቴ የፖለቲካ ቢሮ ባወጣው የድርጊት ፕሮግራምና አብዮታዊ መሪያችን ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባደረጉት ብሔራዊ ጥሪ መሠረት በመስኖ ልማት ረገድ ብቻ እንኳን በአካባቢ ጥረት በድምሩ 50 ሺህ ሄክታር ያህል ማልማቱ አንድ ጉልህ ማስረጃ ነው። በተለይ ደግሞ በፓርቲያችን ግንባር ቀደምነትነት መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ በልዩ ልዩ ባለሙያዎችና ሐቀኛ ዜጎች ያልተቆጠበ ጥረት ግማሽ ሚሊዮን ያህል በድርቅ የተጠቁ ወገኖቻችንን አጓጉዞ ለም በሆኑ አካባቢዎች ለማስፈር መቻሉ ታላቅ ሕዝባዊ ክንውን ነው። ይልቁንም ሠፋሪዎቹ እየተረጋጉ፣ ከታረሰላቸውና በእነሱ ትብብር ጭምር ከለማው ድንግል መሬት እሸት መቁረጥ መጀመራቸው በሕዝባዊ አብዮታችን የበለጠ እንድንተማመን ያደርገናል። ይህ አኩሪ ውጤት በበለጠ የመንፈስ ጥንካሬ በመታገል ችግራችንን ማቃለልና በዓላማችን ለመግፋት ያደፋፍረናል።

ዛሬ ልማትና ዕድገት ስንል በተቀዳሚ የምግብ ችግርን ለማቃለል በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ልዩ አብዮት ማካሄድ ማለት መሆኑን ዜጎች ሁሉ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ከዕቅድ ጀምሮ የሚፈለገውን የምርት ውጤት እስከ ማስገኘት ባለው መዋቅርና አሠራር ብቻ ሳይሆን ተጨባጩን ሁኔታ በመንተራስ በየአካባቢው በእራስ አነሳሽነት ጭምር የላቀ ጥረት ማድረግ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል። በአመጋገብ ልምዳችንም በኩል በተደጋጋሚ እንደሚተችበት ሊጤን ይገባል። በወግ አጥባቂነትና በጣዕም

Digitized by Google

ውሱንነት ምክንያት በተለዋጭ የምግብ ዓይነቶች ለመጠቀም ሳንችል እንዳንቀር በዚህም ለኋያ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አንዱ ቁም ነገር ነው ። ምግብን ከረሃብ ሊያድን ከመቻሉ ብቻ ሳይሆን ለጤንነት ከመበጀቱና ከአልሚነቱም አንፃር ተመጣጥና መገኘቱን ማረጋገጥም ሌላው ትኩረት የሚጠይቅ ጉዳይ በመሆኑ ከወዲሁ ልናስብበት ያሻል ።

ከምግብ ችግር ጨርሶ ለመላቀቅ ሠርቶአደሩ ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ የሚያሳየው እንቅስቃሴ ከላይ እንደተገለጸው በእርግጥም ተስፋ የሚያሰጥ ነው ። ይህ ዓይነቱ በጐ ተግባር ጐልብቶ አንዱ የባህላችን ፈርጅ ወደመሆን ከተሸጋገረ በዕውን የምግብ ችግርን ማቃለል ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ተፈጥሮን ተቆጣጥረን የዕድገት ዓላማችንን ዳር እንደምናደርስ ለመተማመን እንችላለን ።

Digitized by Google

ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ
ኢትዮጵያን እንመሠርታለን !

Digitized by Google

የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር

አበበ ወርቁ

ኅብረተሰብ ከተፈጥሮ ጋር በተለያዩ ግንኙነቶች የተሣሠረ፣ ካለነዚህም ግንኙቶች ሊኖር የማይችል ማኅበራዊ ኑባሬ (Socal Being) ነው ። ለምሳሌ፣ ለኅብረተሰብ መፈጠር፣ ህልውና መጠበቅና ማደግ መሠረት የሆነው ሥራ ኅብረተሰብ ከተፈጥሮ ጋር ባለው መስተጋብር የሚከናወን ሂደት ነው። በመሆኑ ለኅብረተሰብ የሥራ መከናወኛ አስፈላጊ ሁኔታ የሆነው ተፈጥሮ ሊንከባከቡትና በጥንቃቄ ሊጠቀሙበት የሚገባ ሀብት ነው ።

ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በኅብረተሰብና በተፈጥሮ መካከል ያለው ግንኙነት የተዛባ ባሕርይ ይታይበታል ። ይህም መዛባት ከቀጠለ የሰውን ልጅ ህልውና አደጋ ላይ የሚጥለው መሆኑ ይታመናል ። በመሆኑም ባለንበት ዘመን አያሌ ሰዎችን ከሚያሳስቡት ዓለምአቀፋዊ ችግሮች አንዱ የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ጉዳይ ነው። የችግሩን አሳሳቢነት በሚመለከት አያሌ የምርምር ጽሑፎች ቀርበዋል ፤ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ብሔራዊ ስብሰባዎችና ውይይቶች ተካሒደዋል ። የችግሩ በሰፊው መስተጋባት የብዙ ሰዎችን ስሜት ስቧል። የችግሩ ዋና መወያያ ነጥብም ብዙውን ጊዜ «የአካባቢ ችግር» (Ecological Problem) የሚል ነው ።

የዚህ ችግር አሳሳቢነት ምን ያህል ነው ? እንዴት ነው የሰውን ልጅ ህልውና አደጋ ላይ ጥሎታል ለማለት የሚቻለው ? የችግሩ መንስኤ ምንድን ነው ? ሊወገድ ይችላል ? እንዴት ?

መልሶችን ለማግኘት በኅብረተሰብና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ግንኙነት፣አንድነትና መስተጋብር፣ የግንኙነቱ እድገት የያዘውን አዝማሚያ ወይም አዝማሚያዎች፣ በዚህም ግንኙነት የተከሰቱ ችግርችንና መንስኤዎችን መመርመር ያስፈልጋል ። በቅድሚያ ግን በጽሑፉ ው ስ ጥ

Digitized by Google

ሰው ፣ ኅብረተሰብና ተፈጥሮ የሚይዙትን ትርጉም ግልጽ እናድርግ ።

ሰውና ኅብረተሰብ

ሰው በማኅበራዊ ገጽታው በዓለም ውስጥ የቁሳዊና የሕሊናዊ ባህል ገንቢ ፣ በሥነ ሕይወታዊ ገጽታው ብምድር ላይ የተፈጥሮ እድገት ከፍተኛው ውጤት ነው።ሰው ከእንስሶች የሚለየው በማሰብ ችሎታውና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ፣ በንግግር ችሎታውና የምርት መገልገያ መሣሪያዎችን በማምረት ባሕሪው ነው ። የእንስሳት ባሕሪያት የሚወሰነው ለአካባቢያቸው በሚኖራቸው ደመነፍሳዊ ድርጊት ሲሆን ፣ የሰው ባሕሪ ግን በቀጥታ የሚወሰነው በማሰብ ፣ በስሜት ፣ በፍላጎት ፣ እንዲሁም ስለተፈጥሮ ፣ ስለኅብረተሰብና ስለራሱ ነባራዊ የእድገት ሕግጋት በሚኖረው የዕውቀት ደረጃ ነው። በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነትም ሰው በተፈጥሮ ላይ የተወሰነ ድርጊት ለማካሔድና ለመለወጥ ባለው ዓላማ የተግባር መገልገያዎችን ማምረቱ ነው ።[1] እንስሶች እንደሰው የማሰብ ችሎታ የላቸውም ። አካባቢያቸውን በሚስማማቸው ሁኔታ የመለወጥ ችሎታ ስለሌላቸው እራሳቸውን ከሁኔታው በማስማማት ይኖራሉ ። ሰው ግን አስተሳሰቡንና የማምረት ችሎታውን በመጠቀም ተፈጥሮን ገርቶና ለሱ ተስማሚ በሆነ መንገድ በማመቻቸት ይኖራል ።

የሰው ዓይነተኛ ባሕርያት ከኅብረተሰብና ከሥራ ተነጥለው አይታዩም ። ኅብረተሰብ ማለትም «ሰው እራሱ በማኅበራዊ ግንኙነት» ገጽታው አንፃር ሲታይ ነው ። «ኅብረተሰብ የግለሰቦች ክምችት ሳይሆን የእነኝህ ግለሰቦች የእርስ በርስ ተዛምዶና ግንኙነት ድምር ነው ።»[2]

ተ ፈ ጥ ሮ

በሰፊ ትርጉሙ ተፈጥሮ (Nature) ፤ ማንኛውንም ነባራዊ ህልውና ያለውን ነገር የሚያመለክት ጽንሰሐሳብ ነው ። በዚህ ትርጉሙ ተፈጥሮ ቁስአካል ወይም ማንኛውም ከሰው አእምሮ ውጭ ነባራዊ ህልውና ያለውን ሁሉ ያጠቃልላል ። በጠባብ ትርጉሙ ተፈጥሮ ከኅብረተሰብ ጋር የቀጥታ መስተጋብር ያለውን መላውን የተፈጥሮ ክፍልን የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ይህ የተፈጥሮ ክፍል መልክዓ ምድራዊ አካባቢ (Geographical Environmental) በመባል የሚጠራ ሲሆን፣ የመሬት ገጽታን ፣ አየርን ፣ ማዕድንን ፣ አፈርን ፣ ወንዞችን ፣ ባሕሮችን ፣ ዕፀዋትንና እንስሳትን ያጠቃልላል ። መልክዓ ምድር «የሰው ዘር መኖሪያ ፣ የማኅበራዊ እድገት ቋሚ ቅድመ ሁኔታ በመሆን በአጠቃላይ ሕይወት ያለበትና የሚያድግበት አውድ (መስክ) ነው ።»[3] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ተፈጥሮ ሲባል እንደአገባቡ የተጠቀሱትን ሁለቱንም ትርጉሞች የሚይዝ ቢሆንም በአመዛኙ መልክዓ ምድርን የሚመለከት ይሆናል።

የተፈጥሮ ሀብቶች ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ የመልክዓ ምድር አካል ናቸው ። እነኝህ ሀብቶች ሊታደሱ የማይችሉ (Non renewable) እና ሊታደሱ የሚችሉ (Renewable) ሀብቶች በመባል በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ ። ሊታደሱ የማይችሉ የተፈጥሮ ሀብቶች በዓለም ላይ መጠናቸው ውሱን የሆኑትን የተፈጥሮ ሀብቶች በተለይም የማዕድን ሀብቶችን (Mineral Wealth) ይመለከታሉ ። ሊታደሱ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶች በመሬት ላይ በሚከናወነው ተፈጥሮአዊ ሂደት የሚፈጠሩ ፣ መጠናቸውም በዚሁ ሂደት በየጊዜው በሚፈጠረውና ፍጆታ ላይ በሚውለው መካከል በሚኖረው ሚዛን የሚጠበቁ ናቸው ። እነኝህ የተፈጥሮ ሀብቶች ዕፀዋትን ፣ እንስሳትን ፣ የወንዝ ውሃን ፣ በአየር ውስጥ ያለውን አክስጅንን ፣ ወዘተ --- ያጠቃልላሉ ።[4] ይሁን እንጂ የተፈጥሮን ሀብቶች ሊታደሱና ሊታደሱ የማይችሉ ብሎ መከፋፈል አንፃራዊ መልክ ያለው መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል ። ምክንያቱም «ሊታደሱ

Digitized by Google

የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ከልክ በላይ መጠቀም እነኚህን ሀብቶች ወደማይታ ደሱ የተፈጥሮ ሀብቶች ሊለውጣቸው ይች ላል ።»[5] ለምሳሌ የደን ጭፍጨፋ በአ ንዳንድ አካባቢ ደኖችን ሙሉ በሙሉ አጥ ፍቷል ።

በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀሱትን የዋና ዋና ጽንሰ ሐሳቦች ምንነት ከጠቆምን የኅ ብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነትን ፣ ተፈጥ ሮ በኅብረተሰብ ፣ ኅብረተሰብም በተፈጥሮ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ለመመልከት እንሞክር ።

የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት መጀመር

ሰውና ሌሎች ሕይወት ያላቸው ነገሮች በአካባቢያቸው ካለው ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ያደርጋሉ።የተ ለያዩ እንስሳት ህልውናቸውን ለመጠበቅ በተፈጥሮ ሀብት ይጠቀማሉ ፤ በተፈጥሮ ላይም ተፅዕኖ ያሳድራሉ ። ነገር ግን ይህ ተፅዕኗቸው በጣም ውሱን ነው ። በመሠ ረቱ ህልውናቸው ሊጠበቅ የሚችለው እራ ሳቸውን ከተፈጥሮ ሁኔታ ጋር ደመነፍ ሳዊ (Instinctly) በሆነ ዘዴ አስማምተው በመኖር ነው ።

ሰው በተፈጥሮ ላይ የሚያሳድረው ተፅ ዕኖ ግን የተለየ ነው ። እላይ እንደተጠቀ ሰው ሰው ከተፈጥሮ የሚለየው በማሰብ ችሎታው ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ፣ በንግ ግር ችሎታውና የምርት መገልገያ መሣ ሪያዎችን በማምረት ባሕሪው ነው ። ኅብ ረተሰብን ወይም ሰውን ከተፈጥሮ የለየው ዋንኛው ባሕሪ ሥራ ነው ። ይህ ባሕሪው እሱ በተፈጥሮ ላይ የሚያሳድረውን ተፅ ዕኖ ከሌሎች እንስሳት በዓይነቱና በደረ ጃው የተለየ አድርጎታል ። እንዴት ?

ኅብረተሰብ ያደገው « በምግብ ፣ በዘር መራባት (Sex) ፣ በመከላከልና በደመነፍ ስ ላይ ተመሥርቶ ከተደራጀ ሥነ ሕይወ ታዊ የእንስሳ መንጋ» ነው ።[6] የእንስሶቹ መንጋ የሚያስፈልገውን ምግብ ለማግኘ ትና ሊያጠቃው ከሚችል ጠላት ለመከላ ከል አንዳንድ ተፈጥሮአዊ ቁሶችን ፣ ለም ሳሌ የእንጨት ቁራጭን ፣ ድንጋይን፣ ወዘተ በመሣሪያነት መጠቀም ጀመረ ። በእነዚህ መሣሪያዎች ለረጅም ጊዜ መጠቀሙ እያ ደር ፍላጎቱን ለማርካት በሚፈጽማቸው ድርጊቶች ሁሉ በተፈጥሮ መሣሪያ የመ ጠቀም ውስጣዊ ስሜት (Reflex) እና ልማድን አሳደረበት ።

ይህ ከአንድ ግብ ለመድረስ ማለትም ምግብን ለማግኘት ፣ ወይም ከጠላት ለመከ ላከል አስቀድሞ በማሰብ በተፈጥሮ መሣ ሪያዎች መጠቀም እየተደጋገመና እየዳ በረ ሲሔድ ሰው ቀስ በቀስ የራሱን መሣ ሪያ ለመቅረጽና ለማበጀት የሚያስችለ ውን ችሎታ አገኘ ። በደመነፍሳዊና በው ስጣዊ ስሜቱ በመነሣሣት የሚያከናውና ቸውን ድርጊቶች (አደን ፣ የፍሬ ለቀማ ፣ ከጠላት መከላከል ፣ ወዘተ) እያደር በን ቃት ላይ ተመሥርቶ ያካሒዳቸው ጀመር። እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው ሰው ከሌ ሎች እንስሳት የተለየው ። ምክንያቱም ማን ኛውም እንስሳ የተግባር መገልገያ መሣ ሪያ (Instruments of Labour) ለመሥራ ትና በንቃት ላይ የተመሠረተ ድርጊት ለ መፈጸም ወይም ለማካሔድ አይችልም ።

ሰው ከተፈጥሮ የሚፈልገውን ለማግኘት ማለትም ተፈጥሮን በፈለገው ወይም በሚ ስማማው ሁኔታ ለመቅረጽ የተግባር መሣ ሪያዎችን መሥራት ከጀመረ ወዲህ አን ደኛ ፣ በተፈጥሮ ላይ ያለው ጥገኝነት እየ ቀነሰ መጣ ፤ ሁለተኛ ፣ ለመኖር የሚያካሂ ደው ትግል መሠረታዊ ሥነ ሕይወታዊ አቋሙንና ተግባሩን በመለወጥ ሳይሆን ተፈጥሮን የሚገራበትና በሚፈልገው መን ገድ የሚቀርጽበትን የተግባር መሣሪያ በማሻሻል ሆነ ።[7] የዚህ ዓይነቱ መሻሻል እየተጠናከረ ሰውም በሠራቸው መሣሪያ ዎች በመጠቀም የበለጠ እያመረተ ሲሄድ፣ በዚያው አንፃር በአምራች ግለሰቦች መካ ከል ያለው የምርት ግንኙነት እያደገና እየ

Digitized by Google

ሰፋ በግለሰቦች መካከል የበላይነት የነበረውን የሥነ ሕይወታዊ ግንኙነት (Biological ties)ቦታን ወሰደ። ማለትም ቀደም ሲል ለኅብረተሰብ እድገት ሕይወታዊ ምንጭ የነበረው ከእንስሳ መንጋ መካከል ጎልቶ ይታይ የነበረው ሥነ ሕይወታዊ ግንኙነት በምርት ግንኙነት ተተካ።ከዚህ መተካት ጋርም የእንስሳቱ መንጋ የዓይነት ለውጥ አድርጎ ወደኅብረተሰብ ተሸጋገረ ። [8]

በአጠቃላይ ሰውም ሆነ ኅብረተሰብ የተፈጥሮ አዝጋሚ እድገት የደረሰበት ከፍተኛ ደረጃ ነው ። የዚህም ከፍተኛ ደረጃ ዓይነተኛ መለያ ሥራ ነው ። ስለሆነም ሥራ በአንድ መልኩ ሰው ከተፈጥሮ (ከእንስሳት ጭምር) የለየ በሌላ መልኩ ፣ ሰውና ተፈጥሮን ያገናኘ ፣ ማለትም ሰው ተፈጥሮን ለጥቅሙ የሚያውልበት ፣ የሚቆጣጠርበትና የሚጠቀምበት ሂደት ነው ። [9] ስለሆነም በሰውና በተፈጥሮ መካከል መስተጋብር ወይም ግንኙነት የጀመረው ሰው እራሱን ከተፈጥሮ ከለየበት ጊዜ ጀምር ነው ። ሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት የሚያካሒደውም በግሉ ወይም በየፊናው ሳይሆን ኅብረተሰብ ተብሎ በሚጠራው ማኅበራዊ ቡድኑ አማካይነት ነው። [10] የግንኙነቱም መሠረት ሥራ ነው ። ለዚህ ነው ካርል ማርክስ «ሥራ ከሁሉም በላይ ሰውና ተፈጥሮ የሚሳተፉበት ፣ በሰው በራሱና በተፈጥሮ መካከል ያለው ቁሳዊ ግንኙነት የሚጀምርበትና የሚቆጣጠርበት ሂደት ነው » [11] ያለው ።

በሰፊ ትርጉሙ ሲታይ የሰውና የተፈጥሮ መስተጋብር ማለት የተፈጥሮ ሀብትን ለቁሳዊ ምርት (ለምሳሌ ፣ ለኃይል ማመንጫ ፣ ለጥሬ ሀብት ፣ ለግብርና ምርትና ለራሱ ለሰው ህልውና ዋስትና ለማግኘት መጠቀምን ---» [12] ያመለክታል ። በዚህ መስተጋብር ውስጥ ተፈጥሮ በሰው ላይ ፣ ሰውም በተፈጥሮ ላይ የየራሳቸውን ተፅዕኖ ያደርጋሉ ። ይህን ተፅዕኖ አ ጠ ር ባለ መልክ እንቃኘው ።

ተፈጥሮ በሰው ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ

ሰው ተፈጥሮ የሚያሳድርበትን ተፅዕኖ በተለያዩ መንገዶች ያንፀባርቃል ። ለምሳሌ፣የፀሐይ ሙቀት ከፍ በሚልባቸው ወራት ውስጥ የሰው አእምሮ የመረበሽ ባሕርይ እንደሚታይበት ፣ የደም ግፊት ከፍተኛነት (የደም ብዛት) በሽታ ያለባቸው ሰዎች የባሰ የጤና መታወክ እንደሚገጥማቸው፣ የመኪና ግጭት አደጋ መጠን እንደሚጨምርና የሰውም ቁመት ርዝማኔ ከአንዳንድ የተፈጥሮ ክስተቶች (ለምሳሌ ፣ ከመሬት ስበት) ጋር የተያያዘ መሆኑ ይታወቃል [13] ተፈጥሮ፣ እንበል የአየር ሁኔታ ፣ የሰው አኗኗር ፣ የአለባበስ ፣ የአመጋገብ ሁኔታና በሌሎችም የሰው ድርጊቶች ላይ ተፅዕኖ አለው ። በተጨማሪም ፣ተፈጥሮ የሰው ልጅ የተለያዩ ቀለማዊ መልኮች ፣ የቆዳ ዓይነት የአፍንጫና የዓይን አቀማመጥ በአጭሩ ዛሬ የሰው ዘር መለዮ ለሆኑት አካላዊ ገጽታዎች መንስዔ ሆኗል ፤ የተለያዩ የኅብረተሰብ ቡድኖችም የተለያዩ ብሔራዊ ባሕርያት እንዲኖራቸው አስተዋጽኦ አድርጓል ። [14]

እላይ እንደተጠቀሰው ሥራ የኅብረተሰብንና የተፈጥሮን መስተጋብር የሚጠይቅ ሂደት ነው ። ተፈጥሮ የተለያዩ የሰው ምግቦችና የተግባር መገልገያ ምንጭ ሲሆን አመንጭው ግን ሥራ ነው ። ሰው የእርሻ ምርት የሚያመርትበት ፣ እንስሳትን የሚመግብበት ፣ አትክልቶችን የሚያለማበት የአየር ሁኔታ ፣ ለም አፈር ፣ ውሃ ፣ ወዘተ የምርት መገልገያ መሣሪያዎችን የሚሠራበት እንጨት ፣ ብረታ ብረት ፣ የድንጋይ ከሰል ፣ የተፈጥሮ አካል ናቸው ። በ ዚህ የሥራ ሂደት ተፈጥሮ በሰው ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ። ለምሳሌ ፣በአንድ አገር የበለጸገ የተፈጥሮ ሀብት (ለም አፈር፣ማዕድን ፣ ነዳጅ ፣ ወዘተ) መኖር የአገሩን ሕዝብ እድገት ሊያፋጥን የሚችል ሲሆን ፣ አለመ

Digitized by Google

ኖሩ ግን ሊያጓትት ይችላል። ኅብረተሰብ ከተፈጥሮ ጋር በተለያዩ መንገዶች ግንኙነት የሚያደርግ መሆኑ ተፈጥሮ በሰው፣ በኅብረተሰብና በማኅበራዊ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕኖ የሚያሳይ ነው። [15]

በአጠቃላይ ተፈጥሮ በሰው ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ቢሆንም በመላው የዓለም ሕዝብ ላይ ተመሳሳይ ወይም እኩል ተፅዕኖ አያሳድርም። ለምሳሌ፣ በተለያየ የመሬት ገጽታ ላይ (በምድር ወገብ፣ በሰሜን ዋልታ) የሚኖሩ ሕዝቦች ተመሳሳይ የአካባቢ ሙቀት አያገኙም። በተጨማሪም፣ አንድ ሕዝብ የደረሰበት የእድገት ደረጃ ተፈጥሮ የሚያሳድርበትን መጥፎ ተፅዕኖ ሊወስነው ይችላል። በእድገቱ ወደኋላ ከቀረ ሕዝብ ይልቅ በእድገቱ የገፋ ሕዝብ አያሌ የማይፈለጉ የተፈጥሮ ተፅዕኖችን በሚያመርታቸው የመከላከያ መሣሪያዎች በመጠቀም (ለምሳሌ፣ የጐርፍ አደጋን በግድብ፣ የመብረቅ አደጋን በመብረቅ መከላከያ፣ የተፈጥሮ ድርቅን ሰው ሠራሽ ዝናብ በማዝነብ፣ ወይም የውሃ ገድቦችን በማስፋፋትና በመስኖ በመጠቀም፣ የበረዶ ክምር ችግር ሲፈጠር በሰው ሠራሽ የሙቀት ኃይል በማቅለጥ፣ ወዘተ) የመቋቋም ችሎታ ይኖረዋል።

ሰው በተፈጥሮ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ

ሰው ተፈጥሮ ተፅዕኖ የሚያደርስበት ቢሆንም እሱም በተፈጥሮ ላይ በተለያዩ መንገዶች ተፅዕኖ ያደርጋል። ሰው ተፈጥሮን ለመግራትና ለራሱ በሚመቸው መንገድ ለመቅረጽ፣ ለማምረትና ለሌላም ተግባራት በሚያከናውነው ሥራ ተፈጥሮን ለውጧል፤ ተፅዕኖም አሳድሮበታል። አንዳንድ ምሳሌዎችን እንጥቀስ፤ አንደኛ፣ ሰው የአንዳንድ የተፈጥሮ እንስሳትንና ዕፀዋትን መልክ ለውጧል፤ አዳዲስ የዕፀዋት ዘሮችን ፈጥሯል። በመሆኑም ዛሬ የሚታዩት የጌጥ ዕፀዋት፣ የእህል ዘሮች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች የጥንት ዘራቸውን አይመስሉም። ሰው እጅግ በጣም ጥቂት ከነበሩት የጥንት እንስሳት ከሞላ ጐደል 400 የቀንድ ከብት ዓይነቶችን፣ 150 ፈረሶችን፣ 400 የሚደርሱ ውሾችን ለማፍራት ችሏል። *

ሁለተኛ፣ አያሌ እንስሳትንና ዕፀዋትን ከአንዱ የዓለም አካባቢ ወይም አህጉር ወደሌላ በማዛወር የተፈጥሮን የሀብት ሥርጭት ለውጦታል። ለምሳሌ፣ ቡና፣ ገብስና የሌሎችም አንዳንድ የአዝርዕት ዓይነቶች ከኢትዮጵያ ወደአያሌ የዓለም ክፍል ተሠራጭተው በሌላ የዓለም አካባቢዎች የተፈጥሮ ሀብትና ምርቶች ሆነዋል። ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ተስፋፍቶ የሚታየው የባሕር ዛፍም ወደዚች አገር ከገባ የመቶ ዓመት አካባቢ ዕድሜ አለው። ድንች፣ ትምባሆ፣ ቲማቲምና በቆሎ ከአሜሪካ ክፍለ አህጉር ወደ አውሮፓ በሰው አማካይነት የመጡ ናቸው። [16]

ሦስተኛ፣ ሰው ገድቦችን፣ የውሃ ቦዮችን፣ ሰው ሠራሽ ሐይቆችን፣ ወንዞችን ወዘተ በመሥራት፣ ደን በማልማት፣ ወዘተ በአካባቢው ሁኔታ ለምሳሌ፣ በአየር ላይ ለውጥ አድርጓል። በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች ሰው የተፈጥሮ ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮንም ፈጣሪ መሆኑን በተግባር አሳይቷል። ማለትም ሰው ከጥንት ጀምሮ ባካሔደው ሥራ ከአካባቢው ባገኘው ተፈጥሮ ላይ ተጨማሪ ተፈጥሮ አክሎበታል። ይህ ሰው ሠራሽ ተፈጥሮ «ሁለተኛ ተፈጥሮ» በመባል ይታወቃል። የሁለተኛ ተፈጥሮ ሥራ ዛሬም እንደቀጠለ ነው። በተጨማሪም ሰው የበለጠ እየተራቀቀ ሲሔድ ከዕለት ወደዕለት ስለተፈጥሮ ያለው ዕውቀት እየሰፋ፣ አዳዲስ የተፈጥሮ አካሎችን (ለምሳሌ፣ ጨረቃን፣ ማርስን፣ ወዘተ) እየዳሰሰና ሌሎች የተፈጥሮ አካላትን ለማወቅና ለመዳሰስ እየጣረ ነው።

ነገር ግን ይህ ሲባል ሰው በተፈጥሮ ላይ የፈጸመው ድርጊት ሁሉ ለሰው ልጅ ሀል

*V. Kelle and M. Kovalson, *Historical Materialism* (Moscow: Progress Publishers, 1973), p. 78.

Digitized by Google

ውና ተፈላጊና መልካም ውጤት አስገኝቷል ለማለት አይቻልም ። ሰው በራሱ ሥራ መልካም ነገሮችን የፈጠረ ቢሆንም ችግሮችንም ፈጥሯል ፤ እየፈጠረም ነው ። እነዚህ ችግሮች የሚከሰቱባቸውን አንዳንድ መልኮችና የአሳሳቢነት ደረጃቸውን እንመልከት ።

ሰው በተፈጥሮ ላይ የፈጠረው ችግር

ሰው ለአያሌ ዘመናት ከተፈጥሮ ጋር በነበረው መስተጋብር የራሱን ህልውናና የአካባቢን ተፈጥሮ የሚበክሉ ድርጊቶችን ፈጽሟል ። ለእርሻ የሚያገለግለው ለም መሬት እየመነመነ ፥ ደን እየወደመ ነው ። ለሰው ጥቅም የሚውለው የውሃ መጠ እየቀነሰ ፥ እየተመረዘና ከጥቅም ውጭ እ ሆነ ነው ። የአካባቢ አየር ፥ ወንዞችና ባሕሮች ከኢንዱስትሪና ከሌሎችም የሥራ ውጤቶች በሚወጡ ዝቃጮች እየተበከሉ ነው። አያሌ ሊታደሱ የማይችሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ለምሳሌ ነዳጅ ፥ ማዕድንና የመሳሰሉ እየተመጠጡ ነው ። በዚህም ምክንያት በብዙ አገሮች እንዲሁም በዓለምአቀፍ ደረጃ የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ከባድ ችግር ገጥሞታል ፤ ለበለጠም ችግር እየተጋለጠ ነው ።

ችግሩ በተለያዩ ነገር ግን የርስ በርስ ግንኙነት ባላቸው መልኮች ለምሳሌ ፥

1- በመሬት መሸርሸርና በአፈር መከላት፤

2- በተፈላጊ ውሃ እጥረት ፥

3- በደን መውደም ፥

4- በውቅያኖስ ውሃ መበከል ወዘተ ይከሰታል ። በዚህ አጭር ጽሑፍ የችግሩን ገጽታዎች ሁሉ ለመዘርዘርና ለማብራራት ስለማይቻል ጥቂት ምሳሌዎችን እንመለከታለን ።

የመሬት መሸርሸርና አፈር መከላት

ለም አፈር ለሰው ልጅ ከፍተኛ የምግብ ምንጭ ነው ። ስለዚህም በአጠቃላይ ለሰው ልጅ ህልውናና እድገት እጅግ በጣም አስፈላጊ የተፈጥሮ ሀብት ነው ። በተለይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከለም አፈር መኖር ጋር የተያያዘው ግብርና በ እ ያሌ ኋላቀር አገሮች ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው ። ለምሳሌ ፥ በኢትዮጵያ ግብርና ለአገሪቷ ኢኮኖሚ መሠረትና «ከአገሪቱ ጠቅላላ ምርት 46 በመቶ ፥ ከጠላላው የውጭ ንግድ 90 በመቶ ድርሻ ያለውና ከአገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ 86 በመቶ ለሚሆነው መተዳደሪያ ነው ።» [17]

ነገር ግን ይህ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው ሀብት በሰፊው በጥቅም ላይ እየዋለ ከመሔዱ ጋር እየባከነና መጠኑም እየመነመነ ነው ። ይህን ችግር በሚመለከት ስለተፈጥሮ ሀብትና ስለአካባቢ እንክብካቤ ተመራማሪ የሆነው የሶቭዬት ኅብረት ምሁር አይ ላፕቲቭ በ1979 ባሳተመው መጽሐፉ እንደሚከተለው አትቷል ።

በአሁኑ ጊዜ 1500 ሚሊዮን ሔክታር ወይም ከመላው የመሬት ገጽታ 10—11 በመቶ የሚሆነው ለእርሻ ሥራ እየዋለ ነው ። በዚህ ላይ ድርቀሽ የሚታጨድበትንና ለገጦሽ የሚውለውን መስክ ብናክልበት ከ23—30 ከመቶ እንዲሁም ምርት የሚሰጠውን ጫካ ብናክል ከ50 55 ከመቶ በሆነው የመሬት ገጽታ ሰው እየተጠቀመ ነው ። እዚህ ላይ 70 ከመቶ የሚሆነው የመሬት ገጽታ አጥጋቢ ምርት የማያስገኝ ፤ በጣም ቀዝቃዛ ወይም በጣም ደረቅ የአየር ሁኔታ ባለበት አካባቢ መሆኑን ስናስታውስ ሰው የመሬት ሽፋን የሆነውን አፈር በሰፊው እየተጠቀመበት መሆኑን እንገነዘባለን።

የአፈር አጠቃቀሙ ሁኔታ ከፍተኛ የመሬት መሸርሸርና የአፈር መከላት ችግርን እያስከተለ ነው ። ላፕቲቭ በ1977 ባሳተመው መጽሐፉ በዚህ ምክንያት የደረሰውን ጥፋት ሲገልጽ ፥ «ባለፈው መቶ ዓመት ውስጥ ብቻ መሬት 20 ሚሊዮን ስኩዌር ኪሎ ሜትር የሚሆን የልማት መሬት አጥታለች ፤ ይህም ጥፋት ዛሬ በጠቅላላው ለግብርና ጥቅም ከሚውለው መሬት ስፋት 28 ከመቶ ፥ ከጠቅላላው ከመሬት ገጽታ ስፋት 15 ከመቶ የሚሆን ነው» [19] ብሏል ። በአሁኑ ጊዜ በመሬት መሸርሸርና

• በዚህ ጽሑፍ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የዘመን አቆጣጠር እንደ አውሮፓውያን ነው

Digitized by Google

በአፈር መከላት ምክንያት መሬት በዓመት ከ6 እስከ 7 ሚሊዮን ሄክታር ስፋት ላይ ያለ የመሬት አፈር (Hectares of soil) እያጣች ነው ። ዛሬ የሚታየው የአፈር አጠቃቀም ሁኔታ ከቀጠለም ከዛሬ 50 እና 70 ዓመት በኋላ ለም አፈር ወደመራቆቱ እንደሚቃረብ መረጃዎች ይጠቁማሉ ። [21]

ይህ በመላው ዓለም ላይ የሚታይ የለም አፈር መመናመን በኢትዮጵያም (በተለይም በሰሜንና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ) ተባብሰውና ጎልተው ከሚታዩ ችግሮች አንዱ ነው ። በኢትዮጵያ በጠቅላላው በየዓመቱ 500 ሚሊዮን ቶን የሚሆን አፈር* እየተከላ ፣ ከለማው መሬትም 60 ከመቶው በከፍተኛ ደረጃ በአፈር መከላት እየተጠቃ ነው ። [22]

የመሬት መሸርሸርና የአፈር መከላት ሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት አስከፊ በሆነ መልኩ የሚገለጽበትና ግንኙነታቸው አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያሳይ ነው።ከፍተኛ የመሬት መሸርሸርና የአፈር መከላት የሚደርስባቸው የዓለም ክፍሎች አፍሪካና የሩቅ ምሥራቅ አካባቢዎች ናቸው። [23] በኢትዮጵያ በተለይም በሰሜንና በመካከለኛው ኢትዮጵያ በአፈር መሸርሸር ምክንያት ለእርሻና ለከብት ግጦሽ ሊሆን የሚችለውን መሬት ከዕለት ወደ ዕለት እየተነሰ ነው ፤ አንዳንድ አካባቢዎችም ፍጹም ከጥቅም ውጭ ሆነዋል ።

የመሬት መራቆት ዛሬ በያዘው ሁኔታ ከቀጠለ የምግብ እጥረት በተለይም በታዳጊ አገሮች መባባስና የረሃብ መስፋፋት ምን ያህል ለሰው ልጅ ህልውና አሳሳቢ እንደሚሆን መገመት ይቻላል ። በኢትዮጵያ በተለይም ከፍተኛ የአፈር መከላት በታየባቸው ክፍለ ሀገሮች ቁጥሩ 7.5 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ለረሃብ ተጋልጧል ።

ተፈላጊ (የጠቃሚ) ውሃ እጥረት

ውሀ በባሕር ፣ በበረዶ መልክ ፣ በአፈር ውስጥ (በእርጥበት መልክ) በአየር ውስጥ (በትነት መልክ) ይገኛል ። [25] ውሀ ለሰው ልጅ ምግብና የንጽሕና መገልገያ በመሆን፣ ለእርሻ ምርት ፣ ለእንስሳት ምግብነት ፣ ለአያሌ ኢንዱስትሪዎች ሥራ ፣ ወዘተ ያገለግላል ። ለእነዚህና ለሌሎችም ለሰው ልጅ ጠቃሚ ለሆኑ መሰል አገልግሎቶች የሚውለው ማንኛውም የውሀ ዓይነት ሳይሆን ከጭላ ጉደል ንጹሕ የሚባለውና ሀ/ በአንፃራዊ አነጋገር በብዛቱ መጠነኛ የሆነው፣ ለ/ ሰው በፈለገው ቦታ የተፈለገውን ያህል የማያገኘው የውሀ ዓይነት ነው ።

እስከአሁን በተገኘው መረጃ መሠረት በመሬት ላይ ያለው የውሀ መጠን 1,400 ሚሊዮን ኪዩቢክ ኪሎ ሜትር ሲሆን ፣ ከዚህ ውስጥ 94 ከመቶ የሚሆነው በውቅያኖስ ውስጥ የሚገኝ ነው ። [26] «በወንዞች በሐይቆች ፣ በጉድጓዶችና በአፈር ውስጥ ያለው» እና ለሰው ጥቅም ሊውል የሚችለው ውሀ « ከጠቅላላው ከመሬት ውሀ ከመቶ 3 እንኳን አይሆንም ። » [27]

ለምሳሌ ፣ ኢትዮጵያ አያሌ ወንዞች የፋፋቴዎችና ምንጮች ያሉባት አገር ናት ። ይህቺ አገር «በ14 ከፍተኛና መለስተኛ ተፋሳሾች የተከፈለች ስትሆን በእነዚህ ተፋሳሾች የሚያልፈው የውሀ መጠን በዓመት 101.5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ያህል ይሆናል ። » [28] ከመላው የመሬቷ ስፋትም 0.5 በመቶ በሐይቆች የተሸፈነ ነው ። [29]

ነገር ግን የውሀ ሥርጭት እንደሚፈለገው ባለመሆኑ ከኢትዮጵያ መሬት ግማሹ ከፊል ደረቅና ደረቅ (Semi arid and arid)

---

* 500 ሚሊዮን ቶን ከሚሆነው አፈር ውስጥ አንድ አምስተኛው አካባቢ በወንዞች ውሃ የሚከላና ከአገሪቷ ውጭ የሚጠራቀም ነው ። [24]

Digitized by Google



የቀድሞ የደን መጠን

« ተደጋጋሚ ድርቅ የሚያመጣውን ችግር ለመቋቋም » ከሚል የሁግግኮ እንግሊዝኛ መጽሔት የተወሰደ

መግለጫ
ዓለምአቀፍ ወሰን
የክፍለ ሀገር አስተዳደር ክልል
ዋና ከተሞች
በደን የተሸፈነ
ሚዛን
1:5,000,000
አሥመራ
መቀሌ
ጎንደር
ደሴ
ደብረ ማርቆስ
ነቀምቴ
አዲስ አበባ
ሐረር
ጎሬ
ጅማ
አሰላ
ጎባ
አዋሳ
አርባ ምንጭ

የአሁኑ ሁኔታ

ነው ። ይህ የተጠቀሰው የመሬት መጠን በአሁኑ ጊዜ የምርት ተግባር ማካሔጃ እንዳይሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ድርቅ ነው ።[30] በተጨማሪም በ1970ዎቹ አጋማሽ አካባቢ የተካሔደው ጥናት እንደሚያመለክተው በገጠር ከሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ 45 በመቶው ውሀ ሊያገኝ የሚችለው ከመኖሪያው አካባቢ ከአንድ እስከ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት በመጓዝ ነው ።[31] በተለይም በአገሪቷ ውስጥ ድርቅ ተባብሶ በታየበት ጊዜ ችግሩ ምን ያህል እንደተካረረ መገመት አያዳግትም ። በድርቁ መባባስ ምክንያት በአንዳንድ የገጠር ቦታዎች ውሀ ከርቀት በመኪና አጓጉዞ ለሕዝብ ማደል ግድ ሆኖ ነበር ።

በአዲስ አበባም ቋሚ የውሀ እጥረት አለ ለምሳሌ እ. ኢ. አ. በ1976 መጨረሻ የአዲስ አበባ የውሀ ሥርጭት በከተማው ከሚፈለገው « 57.7 ከመቶ ብቻ » ሊያረካ የሚችል እንደነበረ መረጃዎች ይጠቁማሉ ።[32]

የተፈላጊ ውሀ እጥረት በዓለምአቀፍ ደረጃም ከኢንዱስትሪ በሚወጡ ዝቃጮችና በሌሎችም መርዛማ ነገሮች ውሃቸውን በመረዙት በለሙት ካፒታሊስት አገሮች ጭምር ጉልቶ የሚታይ ችግር ነው ። በሀብታምነቷ የታወቀችው የኒውዮርክ ከተማ በአንድ ወቅት ከፍተኛ የውሀ አቅርቦት እጥረት ስለአጋጠማት የከተማዋ የውሀ ማቅረቢያ ቧንቧዎች ያስተላልፉት የነበረው ውሀ ከሚፈለገው የውሀ መጠን አንድ ሶስተኛውን ብቻ ነበር ። በዚያን ወቅት የምግብ ቤቶች ምግብ ባቀረቡ ቁጥር የምግብ ማቅረቢያዎቻቸውን ላለማጠብ ተገደው ነበር ፤ በከተማው አካባቢዎች መኪና ማጠብ ተከልክሎ ነበር ፤ በቴክሳስና በኒውሜክሲኮ የውሀ ሀብት መጠን እየተሟጠጠ መሆኑን ምሁራን ይጠቁማሉ ።[33]

በእንግሊዝ ታዋቂ ከተማም በማንቼስተር በበጋ ወራት በየቀኑ ለተወሰኑ ሰዓቶች የቧንቧ ውሀ አቅርቦት መጠን እንደሚቀንስ፣ በተወሰኑ የግሪክ አገር ቀበሌዎች አንዳንድ ጊዜ ውሀ ከወይን ጠጅ የበለጠ ውድ የሚሆንበት ጊዜ እንዳለ ይነገራል ።[34]

በጃፓን የውሀ እጥረትን ለመቋቋም በመውሰድ ላይ ያለው ርምጃ አገሪቷን ለባሰ ችግር እያጋለጣት ነው ። በአገሪቷ ዋና ከተማ በቶኪዮ ውስጥ በአንዳንድ ቀበሌዎች ከመሬት የውሀ ማውጣት ሥራ የደረቁ መሬት ወለል በዓመት ያለማቋረጥ በአያሌ ሳንቲሜትር ርዝመት እንዲሰምጥ እያደረገው ነው ።[35] በሌላ አነጋገር በዚህች አገር የውሀ እጥረትን ለማቋቋም የሚካሔደው የውሀ ሥራ አገሪቷን በባሕር ለመዋጥ እያጋለጣት ነው ማለት ነው ።

የደን መመንጠር

ደን የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ፣ ለውሀና ለአየር መጣራት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ፣ ለዱር አራዊት መጠለያና ለኢንዱስትሪ ጥሬ ሀብት የሚሆን ለኃይል ምንጭነትና ለኮንስትራክሽን ሥራዎች አገልግሎት የሚሰጥ የተፈጥሮ ሀብት ነው።

ለምሳሌ በአንድ ሄክታር ክልል ውስጥ ያለ በርች የሚባለው የዛፍ ደን (Birch forest) በቀን 47,000 ሊትር ውሀ ወደ ውጭ ያተናል ፤ ይህም ማለት ውሀን ማጣራት፣ ለአካባቢው አየር እርጥበት መስጠትና ዝናብ እንዲኖር ማድረግ ነው ።[36] የዛፍ ሥሮችን የሚሸፍን አንድ ኪሎ ግራም የሚከብድ የእንጨት ሽበት መሰል ነገር (moss) ከዝናብ 4 ሊትር ውሀ በመውሰድ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በቅጠሎቹ ውስጥ ወደአየር ያስተላልፋል ።

በተጨማሪም ደን በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ሀገሮች ከፍተኛ የኃይል ምንጭና የኮንስትራክሽን ሥራ ማከናወኛ ሀብት ነው ። በኢትዮጵያ ደንና ቁጥቋጦ የሀገሪቱ ከፍተኛ የኃይልና የኮንስትራክሽን መግሪያዎች ናቸው። ለምሳሌ፣ እ.ኢ.አ. በ1966 አካባቢ የተካሔደ ጥናት እንደሚጠቁ

Digitized by Google

ሙው ከአዲስ አበባ ቤቶች 90 ከመቶው የተሠሩት ከባሕር ዛፍ ነበር ። [38]

የደን አለመኖር አያሌ ችግሮችን ያስከትላል ። የደን መጥፋት ለም አፈርንና ሌሎችንም የመሬት የተፈጥሮ ሀብቶች ያራቁታል ። የደን ሀብት መመንመን ለሰው ሀልውናና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ተፈጥሯዊ ሁኔታ መበላሸትን ያስከትላል። ለምሳሌ በኢትዮጵያ የደን ጭፍጨፋ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ካስከተላቸው ችግሮች መካከል ፦ [39] 1ኛ /ከፍተኛ ስፋት ያለው መሬት ሙሉ በሙሉ ለም አፈሩ መራቆቱና «ለማንኛውም ዓይነት የኢኮኖሚ ጥቅም» ከመዋል ውጭ መሆኑ አያሌ ሕዝብ ለረሃብ መጋለጡ ፣ 2ኛ/ ደን በወደመባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብ ለከፍተኛ የእንጨት ችግር (ለቤት ሥራ ፣ ለማገዶ ፣ ወዘተ . . . የሚጠቀምበት) የገጠመው መሆኑ ፣ 3ኛ/ ለሰውና ለእንስሳት ምግብ ሊውል የሚችል የውሀ ችግርና የአካባቢ የአየር መዛባት (ለምሳሌ የፀሐይ ሙቀት ከፍ ማለት) ይገኙበታል።

የደን መመንጠር ለኤሌክትሪክ ማመንጭያ በተሠሩ የውሀ ግድቦች ላይ ከፍተኛ ችግር ያደርሳል ። በወንዞች ራስጌ ደን በመመንጠሩና በዚህም ሳቢያ የጐርፍ መብዛት የአያሌ የውሀ ግድቦችን (በኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦች ጭምር) በደለል የመሙላት ሂደት አፋጥኗል ። አይ ላፐቲቸ እንደሚለው ፣

ለምሳሌ - በዩኤስኤ የግድቦች በደለል መሞላት በጣም በመፋጠኑ ምክንያት አንዳንድ ጣቢያዎች በ30 ዓመት ውስጥ ከስፋታቸው 80 ከመቶ የሚሆነውን አጥተዋል።39ከ መቶ የሚሆኑት ከመቶ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከአገልግሎት ውጪ ይሆናሉ። ግድቦቹ ከ10 እስከ 15 ዓመታት ብቻ አገልግለው ከጥቅም ውጭ የሆኑበት ሁኔታም አጋጥሟል ። [40]

ደን እጅግ ጠቃሚ መሆኑ የማያጠራጥር ቢሆንም ፣ ከዕለት ወደ ዕለት ከምድረ ገጽ የመጥፋት አቅጣጫ ይዟል ። «በአሁኑ ጊዜ በመሬት ላይ የሚገኘው የደን መጠን የሰው ልጅ ታሪክ ከመመዝገቡ በፊት በምድር ከነበረው ደን መጠን ከ60—65 በመቶ የሚያንስ ነው ።

የደን መውደም የደረሰበት ደረጃና የሚካሔድበት የጥፋት መጠን ከሀገር ወደ ሀገር ወይም ከአካባቢ ወደአካባቢ ይለያያል ። የኢትዮጵያን የደን ታሪክ እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል ። ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት ከሀገሪቱ ጠቅላላ የመሬት ስፋት 40 ከመቶውን ይሸፍን የነበረው ደን ዛሬ ወደ 3.5 በመቶ አሽቆልቁሏል ። ከቅርብ ዓመታት በፊት የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የእርሻ ድርጅት (FAO) ያወጣው ጥናት እንደሚጠቁመው በኢትዮጵያ 200,000 ሄክታር ያህል የደን ስፋት በየዓመቱ እየተመነጠረ ነው ። [42] በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ በተጠቀሰው መጠንና ኋላቀር በሆነ ዘዴ በደን ሀብት መጠቀሙን ከቀጠለ በዚህ ምዕት ዓመት መጨረሻ አካባቢ ሀገሪቱ ይህ ነው የሚባል የደን ሀብት እንደማይኖራት ጥናቶች ይጠቁማሉ ። [43] በዓለም አቀፍ ደረጃም የዛሬው የደን አጠቃቀም ከቀጠለ ከዛሬ 50 እና 70 ዓመታት በኋላ የዓለም የደን ሀብት ወደመሟጠጡ እንደሚቃረብ ይገመታል ። [44]

የውቅያኖስ ውሀ መበከል

የተፈጥሮ መበከል ከሚንፀባረቅባቸው ገጽታዎች አንዱ ትልቁ የውሀ ማከማቻ የሆነው ውቅያኖስ ነው ። በመሬት አካባቢ ካለው ውሀ 94 በመቶ የሚሆነው በውቅያኖስ መልክ ያለው ውሀ መሆኑ እላይ ተመልክቷል ። ይህን ከፍተኛ የውሀ መጠን ያከማቸ የተፈጥሮ ሀብት ከዕለት ወደዕለት ተፈጥሯዊ ተግባሩን እንዳያከናውንና ጠቃሚ አገልግሎት እንዳይሰጥ እየተደረገ ነው ።

Digitized by Google

በተፈጥሯዊ ተግባሩ ውቅያኖስ የመሬትን ሙቀት በመቆጣጠር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ። በመሆኑም አንዳንድ ምሁራን የመሬት ሳንባ በሚል ስያሜ ሊጠሩ ይገባል ይላሉ ። ውቅያኖስ ከአካባቢ አየር መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ካርቦን ዳይኦክሳይድ በመውሰድ ከዚህ ከባቢ አየር ካለው ኦክሲጂን ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ይሰጣል ።[45]

በተጨማሪም ውቅያኖስ ከፍተኛ የምግብ ምንጭና የመጓጓዣ መገልገያ በመሆን ይጠቅማል ። ከዚህም በላይ ውቅያኖስ ለሰው ሕይወት አስፈላጊ ሁኔታና ጠቃሚ የተፈጥሮ ሀብት ነው ።

ነገር ግን ውቅያኖስ ይህ ተግባሩ ታውቆ እንክብካቤ አልተደረገለትም ። አንደኛ ፣ አያሌ ወንዞች ከፋብሪካና ከሌላም ቦታዎች ያከማቿቸውን ቆሻሻዎችና ሌሎችንም መርዛም ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ወደውቅያኖስ ያጓጉዛሉ ። እነኝህ መርዛም ነገሮች ቢያንስ ለአያሌ በውቅያኖስ ውስጥ ላሉ እንስሳት ሕይወት መጥፋት ምክንያት ይሆናሉ ። ወደፊትም ሌላ የባሰ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ ። ሁለተኛ ፣ ዘይት ጭነው በባሕር ወለል ከሚጓዙ መርከቦች እየሰረገ ወይም በዘይት ጋኖች ላይ በሚደርስ አደጋና በባሕር አካባቢ ካሉ የዘይት ጉድጓዶች መፈንዳት[46] ወይም በሌላ ምክንያት በየዓመቱ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ዘይት ወደውቅያኖስ ይገባል ።

ይህ የውቅያኖስ መበከል ከሚያስከትላቸው ችግሮች አንዱ ውቅያኖሱ የመሬት ሳንባ በመሆን በሚሰጠው አገልግሎት ላይ እክል መፍጠር ይገኝበታል ። ምክንያቱም በውቅያኖሱ ውሀ ገጽታ ላይ የሚስፋፋው ዘይት ካርቦን ዳይኦክሳይድ በውቅያኖሱ ውሀ እንዳይመጠጥ ያግዳል ። የዚህ ውሀ መበላሸት በውስጡ ላሉ አያሌ የእንስሳት ዘሮች መጥፋትና ቁጥር መቀነስ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው ።

የአየር መበከል

የመሬት አካባቢ አየር መበከል የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር ውስጥ መሆኑ የሚከሰትበት ሌላው ገጽታ ነው ። ከባቢ አየር በአቧራ ፣ በካርቦን ዳይኦክሳይድ ፣ በሰልፈር ፣ በሊድ ፣ በናይትሮጂንና ፀረ ተባይ (pesticides) እና በሌሎችም ነገሮች[47] ከዕለት ወደዕለት እየተመረዘ ነው ። ይህንን መመረዝ በሚመለከት አይ ላፕቴቭ እንደሚከተለው ጽፏል ።

> በእያንዳንዱ ዓመት ወደከባቢ አየር 200 ሚሊዮን ቶን ካርቦን ሞኖኦክሳይድ ፤ ከ50 ሚሊዮን ቶን የሚበልጡ የተለያዩ የካርቦን ዓይነቶች ፣ 146 ሚሊዮን ቶን የሚሆን ሰልፈርዳይኦክሳይድ ፣ 53 ሚሊዮን ቶን ናትሪክ ኦክሳይድ ወዘተ . . . እንጨምራለን ። ባለፉት 50 ዓመታት በከባቢ አየር ውስጥ ያለው የካርቦንዳይኦክሳይድ መጠን ከ10—12 ከመቶ ፤ እንዲሁም ከ1965 እስከ 1975 በ10 ዓመት ውስጥ ብቻ የብናኝ ነገሮች መጠን በ12 ከመቶ ከፍ ብሏል ።[48]

የብናኝ ወደአየር ውስጥ መግባትና በአጠቃላይም የከባቢ አየር መበከል ለሰዎችና ለሰዎች ኑሮ አስፈላጊ ሁኔታዎች ላይ ችግር የሚፈጥሩ መሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን ምን ለውጥ በማምጣት ነው በሰው ላይ ጉዳት የሚያደርሱት ለሚለው ጥያቄ ሳይንቲስቶች የሚሰጡት መልስ ይለያያል። አንዳንድ መልሶች በአየሩ ውስጥ የአቧራና የብናኝ መበራከት የጠቅላላው የመሬት መቀዝቀዝን እንዲያውም በበረዶ መሸፈንን ሊያስከትል ይችላል ይላሉ ። ሌሎች ግምቶች በአካባቢያችን የካርቦን ዳይኦክሳይድ መብዛት የመሬትን የአየር ሙቀት የሚያንረው መሆኑን ያመለክታሉ ። ያም ሆነ ይህ የአካባቢ አየር መበከል ለሰው ሀልውና ጎጂ ስለመሆኑ ግን ሳይንቲስቶች

Digitized by Google

ምንም አይጠራጠሩም ። መበከሉ እየተባባሰ ስለሆነ ችግሩ የበለጠ አሳሳቢ ነው ። ለምሳሌ ፣ ሰው በየዓመቱ 20 ሚሊዮን ብናኝ ነገሮችን ወደአየር እየጨመረና በከባቢ አየር ውስጥ ካለው ኦክስጂንም ከ10 ሺህ ሚሊዮን ቶን በላይ እየተጠቀመ ነው[50]

በአጠቃላይም ሰው ሠራሽ ነገሮች የአካባቢ አየር መበከል ከ2025 ዓመት የተለያዩ የዓለም አካባቢ የአየር ሁኔታዎች ላይ ችግር እንደሚፈጥር ነገር ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖረው ተፅዕኖ ለጊዜው የተወሰነ እንደሚሆን ይገመታል ።[51] በዚህ ግምት መሠረት ችግሩ ከሚከሰትባቸው መልኮች አንዱ የከባቢ አየር የበለጠ መሞቅ ሲሆን ፣ ይህም በበኩሉ በአያሌ የዓለም አካባቢዎች የዝናብ ሥርጭትን የሚያዛባና ከዚህም ተያይዞ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል ነው ። በተለይም በመካከለኛው አውሮፓ በእስያና በሰሜን አሜሪካ የግብርና ሥራ በዚሁ ችግር ስለሚቃወስ በዓለም ላይ ከፍተኛ የምግብ እጥረትን ይፈጥራል ።[52] የዓለም ሙቀት መጨመሩን ሲጀምርም የድርቅ ተደጋግሞ መምጣት የበለጠ ይጨምራል ።[53] አዝማሚያው ለሰው ልጅ ህልውና አሳሳቢ የሚሆን ነው ።

ተፈጥሮ በሰው ላይ ሊያደርስ የሚችለው ችግር ሲካተት

በአጠቃላይ የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት የያዘው አዝማሚያ አደገኛና ለሰው ልጅ ተስማሚ የተፈጥሮ ሀብቶችንና ሁኔታዎችን የሚያጠፋ ፣ የሰውን ህልውና ሊያሳጣ የሚችል ነው ። እላይ ዘርዘር ብሎ እንደተጠቀሰው የዓለም ሕዝብ ዛሬ በያዘው ሁኔታ ውሃን ፣ ጫካንና አፈርን መጠቀሙን ከቀጠለ ከ50 እና ከ70 ዓመት በኋላ እነኝህን የተፈጥሮ ሀብቶች እንደሚያገባድዳቸው የአካባቢውም የአየር ሁኔታ በመበላሸት በ2025 ዓመት አካባቢ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚደርስ ይገመታል ።

የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ሲጠኑ ችግሮቹ ተባብሰው በሰው ልጅ ላይ ጥፋት ሊያደርሱ የሚችሉበትን የእድገት ደረጃ በጊዜ አንፃር አስቀድሞ መገመቱ ምናልባት ሙሉ ለሙሉ ትክክል ላይሆን ይችላል ። ለምሳሌ በአንዳንድ የተፈጥሮ ሂደቶች ምክንያት ሰው ሠራሽ የተፈጥሮ መበላሸት በሰው ላይ ሊያደርስ የሚችለው አደጋ ሊዘገይ ወይም ሊፋጠን ይችል ይሆናል ። በተጨማሪም ፣ በዓለም ላይ የተከማቸው የኑክሊየር የጦር መሣሪያ በአጋጣሚም ሆነ ሆን ተብሎ በማንኛውም ጊዜ ለጥፋት ቢውል የተፈጥሮና አካባቢ ጥፋት ከተጠበቀው በፊት ሊደርስ ይችላል ። ያም ሆነ ይህ ግን ሰው አካባቢውን በማበላሸት እራሱን ለጥፋት እያዘጋጀ መሆኑ ምንም አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም ።

አሌክሳንደር ስፔርኪን የሚባለው የሶቭየት ኅብረት ፈላስፋ ሰው ተፈጥሮን በማበላሸቱ ምክንያት ሊደርሱበት የሚችሉት አደጋዎች የተለያዩ ሊሆኑ ቢችሉም ሲካተቱ በሦስት ገጽታዎች ሊታዩ እንደሚችሉ ይጠቁማል ።[54] የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ሚዛን መዛባትና ሰው ወደ ተፈጥሮ የሚጨምረው ተፈላጊ ያልሆነ ነገር ተፈጥሮ ሊቀበለው ከሚችለው በላይ መሆን ከእነኝህ ገጽታዎች አንዱ ነው ። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ተፈጥሮ ከተግባርና ከሌሎችም ማኅበራዊ ሂደቶች የተፈጠረውን ቆሻሻ (ለምሳሌ ከኢንዱስትሪ የሚወጣውን ካርቦን ዳይኦክሳይድ) በመቀበልና በማጣራት (ለምሳሌ ፣ ዕፀዋት ካርቦን ዳይኦክሳይድን በመውሰድና ኦክስጂን በመተንፈስ) አገልግሏል ። አሁን ከማኅበራዊ እንቅስቃሴ በተፈጥሮ ላይ የሚደፋው ቆሻሻ ተፈጥሮ ተቀብሎ ከሚያጣራው በላይ ሆነ ። በዚህም ምክንያት ተፈጥሮ (አከባቢ አየር) ጭምር ተበከለ ፤ እየተበከለም ነው ። ከእንግዲህ ወዲህ ሰው ከምድረ ገጽ እራሱን ከማጥፋት ለመቆጠብ ከፈለገ «አካባቢውን በአመዛኙ እሱ እራሱ ማጽዳት ፣ እንደበፊቱ ጎጂ ቆሻሻን በተፈጥሮ ላይ ከመድፋት መቆጠብና ለራሱ ህልውና አስፈላጊ ተፈጥሮ

Digitized by Google

አዊ ሁኔታን እራሱ መፍጠርና መጠበቅ አለበት ፡፡ » [55]

የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት መዛባት ያስከተለው ችግር የሚታይበት ሁለተኛው ገጽታ የሰው መወገድ ወይም የመጥፋት አደጋ ነው ። እያሌ ትናንሽ ትላትሎች ባክቴሪያዎችና ሌሎችም ጥቃቅን ነፍሳት ፣ (ለሰው በጣም ጎጂ የሆኑ ጭምር) «ከፍተኛ የሆነ የኬሚካልና የአካላዊ ገፊት ካለው ሁኔታ ጋር እራሳቸውን በማስተካከል ሊኖሩ የሚችሉ ሲሆን ፣ የሰው ሥነ ሕይወታዊ ተፈጥሮ ግን የዚህ ዓይነት እራስን በጣም ከፍተኛ ለሆነ የአካባቢ ለውጥ የማስማማት ችሎታው ዝቅተኛ ነው ። ሰው ለረጅም ጊዜ እራሱን ባስተካከለበት በአንፃራዊ አነጋገር ጠበብ ባለ የተፈጥሮ ሁኔታ (ለምሳሌ ፣ በተወሰነ የአየር ሙቀት ክልል ውስጥ) ብቻ ሊኖር የሚችል ነው ። በመሆኑም ሰው «በአካባቢው መጠነኛ የሆነ የኬሚካልና የአካላዊ ሁኔታዎች ለውጥ ሲያጋጥመው በራሱ ሊኖርና ሊያድግ የማይችል ስንኩል ወይም ደካማ ፍጡር ያፈራል ወይም ቍራሹን ይጠፋል። » [56]

የተፈጥሮ (በተለይም የዓውደ ሕይወት) ምርታማነት የመቀነስ ጉዳይ እየተባባሰ መሔድ ሰው በተፈጥሮ ላይ የፈጠረው ችግር የሚታይበት ሦስተኛው ገጽታ ነው። እላይ እንደተመለከተው ሰው አፈርን፣ውሃንና አየርን እየበከለ ፣ እነኝህ ተፈጥሯዊ ነገሮች የሚያካሒዱት ተፈጥሯዊ ተግባርን (ለምሳሌ የባሕር ተግባርን) እያደናቀፈ ነው። መጠኑ ዕፀዋትና ሌሎችም የካርቦን ዳይኦክሳይድ ተጠቃሚዎች ሊወስዱ ከሚችሉት በላይ የሆነ ካርቦን ዳይኦክዳይድ ወደአየር እየጨመረ ነው ። ይህም የአየርን ሁኔታ የሚያበላሽ መሆኑ ይታወቃል ።

አፈር በአመዛኙ ሕይወት ባላቸው ጥቃቅን ነገሮች የተሞላና ህልውናም ከውሃና ከአየር መኖር ሊነጠል የማይችል የተፈጥሮ ሀብት ነው ። «ያለ ውሃና ያለ አየር አፈር ወደ አቧራነት ይለወጣል ። » [57] ስለሆነም የእነኝህ እጅግ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና የሰው የሕይወት ምንጭ ፣ የህልውናው ቅድመ ሁኔታ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች መበላሸት ምርታማነታቸውን ይቀንሳል ። መበላሸታቸውም ካልተገታ እላይ እንደተጠቀሰው ሙሉ በሙሉ ሊጠፉ እንደሚችሉ ይታወቃል ። ይህ ጥፋት በተራው የሰውን ልጅ ለረሃብ የሚዳርግና የሚያጠፋ ይሆናል ። ዛሬም ቢሆን የነኝህ የተፈጥሮ ሀብቶች ትክክለኛ ያልሆነ አጠቃቀምና ብክላ የምርት መቀነስን (በተወሰነ አካባቢም ቢሆን) ፈጥሯል ።

የእነኝህና የሌሎችም ተዛማጅነት ያላቸው የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግሮች ናቸው የአካባቢ ችግር በመባል የሚታወቁት ። እላይ እንደተጠቀሰው ችግሮች እየተባባሱ መጥተዋል ። ይህ ሁኔታም ከቀጠለ የአካባቢ ችግር በሰው ላይ ከፍተኛ ጥፋት ወደ ሚያደርስ ችግር (ወደ ቀውስ ደረጃ) ሊሸጋገር እንደሚችልም አሌ የማይባል ሐቅ ነው ። የቀውሱም መፈጠር የሰው አለመኖርና የመኖር ጥያቄ ሆና የሚቀርብ ነው ።

የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት የገጠመው ችግር ዓለምአቀፋዊ ነው ። ይህ ችግር ለመላው የሰው ልጅ ዘር አደገኛ የሆነና መፍትሔውም በአጠቃላይ የዓለም ሕዝቦችን ትብብርና በጋራ መሥራትን የሚጠይቅ ነው ። የመሬት የተፈጥሮ ሀብት መባከን ፣ የአየርና የውቅያኖስ ውሀ መበከል ፣ የአፈር መከላት ወዘተ መንስኤያቸው ቢለያይም የሰው ልጅ የጋራ ችግሮች ፣ ሕልውናውን የሚፈታተኑ ጉዳዮች ናቸው ።

የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር አሳሳቢ ደረጃ መድረሱና የችግሩም ዓለም አቀፋዊነት የእያሌ ሰዎችን አዕምሮ አስጨንቋል ። ምሁራንን ብዕር አስነስቷል ። ዓለም አቀፋዊና ብሔራዊ ምርምርና ውይይትን ጋብዟል ። ለፖለቲካ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ የአየርን መበከል በመቃወም ለሚካሔዱ ሰላማዊ ሰልፎች) መንስኤ ሆኗል።

Digitized by Google

ዛሬ በዓለም ውስጥ ስለአካባቢ ችግር ፖሊሲ የሚቀይስ መንግሥት አለ ለማለት አያስደፍርም ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 35ኛው ጉባዔ አባል አገሮች የመሬትን የተፈጥሮ ሀብት ለዛሬውና ለመጭው ትውልድ ጥቅም እንዲውል የመንከባከብ ታሪካዊ ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ ሰሬ ውይይት አድርጓል ። [58] የዚህ ድርጅት የተለያዩ አካላትም ስለሰውና ተፈጥሮ ግንኙነት አያሌ ማሳሰቢያዎችን አስተላልፈዋል ፤ ተግባራዊ መሆን አለባቸው የሚሏቸውን ዕቅዶች ነድፈዋል ።

የችግሩ መንስዔና መፍትሔ

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ስለሰውና ተፈጥሮ ግንኙነት ችግር ሲወሳ የችግሩ መንስኤ የሆኑ አንዳንድ ምክንያቶችና መፍትሔም ሊያገኝ የሚችል ችግር መሆኑ እልፍ እልፍ ተጠቁሟል ። ነገር ግን መንስዔዎቹንና መፍትሔዎቹን የሚመለከቱትን ሐሳቦች ጠቅለል አድርጎ ለማየት እንዲቻል ለጉዳዩ ተዛማጅነት ያላቸውን መሠረታዊ ነጥቦች የበለጠ ማየቱ አስፈላጊ ነው።

የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግሮችን መመርመርና ትክክለኛ መፍትሔ መጠቆም ፣ ሳይንሳዊ የምርምር ዘዴን ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ትንተናን ፣ በተለያዩ የሳይንስ መስኮች የሚሠሩ ምሁራንን የጋራ ጥናት ፣ ወዘተ የሚጠይቅ ውስብስብና ከባድ ሥራ መሆኑን በችግሩ ላይ ጥልቅ ጥናት ያካሔዱ ተመራማሪዎች ያስገነዝባሉ ። የምርምሩ ሥራ ከባድ ቢሆንም በተለይ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ተስፋ የሚጣልባቸው የምርምር ዘዴዎች እየተቀየሱ ፣ የችግሩ መንስዔም እየታወቀና ተጨባጭነት ሊኖራቸው የሚችሉ ትንበያዎችም እየተደረገ ነው ። በዚህ በኩል የቡርዧ ምሁራንም መልካም አስተዋጽኦ አድርገዋል ። [59] ነገር ግን በአጠቃላይ አነጋገር የቡርዧ ምሁራን አቀራረብ በሰውና በተፈጥሮ ግንኙነት መዛባት ውስጥ ማኅበራዊ ክስተቶች የሚጫወቱትን ሚና ዝቅ አድርጐ የሚያዩና ችግሩንም ለመፍታት የማኅበራዊ መሠረታዊ ለውጥን አስፈላጊነት የማያመለክት ነው ።

በአያሌ የቡርዧ ምሁራን አስተያየት በሰውና በተፈጥሮ መካከል ላለው ችግር መንስኤው ፣ «የተፈጥሮ ሀብት መሟጠጥ፣ የአካባቢ መበከል ነው ፤» እነኝህም ችግሮች «የሕዝብ ቁጥር ማደግ፣ የምርትና የፍጆታ መጨመር የግድ የሚያስከትሏቸው ናቸው ።» [60] ምሁራን የተለያዩ የመፍትሔ ሐሳቦች ይሰነዝራሉ ። ነገር ግን የሁሉም የጋራ መፍትሔ ሐሳቦች ሲካተቱ «የሰውን ልጅ ፍላጐት ሰው ሠራሽ በሆነ ዘዴ (ለምሳሌ) ፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመርን በመገታት መቀነስን ፣ የቴክኖሎጂ ዕድገትን በዝግታ ማካሔድንና በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ዓለምአቀፋዊ ቁጥጥር መመሥረትን የሚያሳስቡ ናቸው ።» [61]

ማርክሲስቶች የቡርዧ ምሁራኑ ስለሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት የሚሰጡትን መንስኤና መፍትሔ አይቀበሉትም ። ለምሳሌ፣ ስለ ሕዝብ ቁጥር ፣ ስለቴክኖሎጂ ዕድገትና ስለተፈጥሮ ሀብት ማለቅ ጉዳይ ማርክሲስቶች የተለየና በሳይንሳዊ መረጃ የተደገፈ አስተያየት ያቀርባሉ ። ከዚህም በማያያዝ የችግሩን መንስዔና መፍትሔ ይጠቁማሉ

1- የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በሚመለከት

በእርግጥ በምድር ላይ ገደብ የሌለው የሕዝብ ዕድገት ለሰው ልጅ መልካም ሕልውና ጠቃሚ ነው ለማለት አይቻልም ። ያለንበት ዘመን አንዱ ባሕርይ የሕዝብ ቁጥር መናር (Population explosion) ነው ። የዓለም የሕዝብ ቁጥር በ1930 ፣ 2 ቢሊዮን የደረሰው ከብዙ ሺህ ዓመታት ዕድገት በኋላ ነበር ። ነገር ግን በ1976 ማለትም በ36 ዓመት አካባቢ ውስጥ በእጥፍ አድጐ 4 ቢሊዮን ደርሷል ። ዛሬ በያመቱ በሚያድግ ገበት መጠን (1.8 በመቶ) ከቀጠለም በ2010 ዓመት የዛሬውን ቁጥር

Digitized by Google

እጥፍ በመሆን 8 ቢሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል ። [62]

ኢ.ፌደርቭ ዛሬ በተደረሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃ መሬት ከ30 እስከ 40 ቢሊዮን ሕዝብ ለማኖር የምትችል መሆኗን ገልጾ የዛሬው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጠን ከቀጠለ የተጠቀሰው ቁጥር በ100 ዓመት አካባቢ እንደሚደርስበት ገልጿል ። [63] የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ይጨምራል ፤ ሰጊዜው የሰው ብቸኛ መኖሪያ የሆነችው የመሬት መጠን ግን ውስን ነው ። ስለሆነም ሰው በምድር ላይ ኗሪ እስከሆነ ድረስ በቁጥር ከልክ በላይ መጨመር ችግር ሊፈጥርበት እንደሚችል ይታመናል ። [64]

የሕዝብ ቁጥር መናር የከተሞችን ፣ የመንገዶችን ፣ የመሥሪያና የመዝናኛ ቦታዎችን መስፋፋትና በሌላ አነጋገር ለግብርና ሥራ የሚውለውን መሬት መቀነስን ጭምርና የብዙ የተፈጥሮ ሀብት ማለቅን ሊያስከትል ይችላል ። [65]

የሕዝብ ቁጥር መናር ሊያስከትል የሚችለውን ችግር የዓለም ሕዝብ እንዴት ሊያስወግድ ይችላል ? በመጀመሪያ ደረጃ ፣ በተግባር እንደታየውና በሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብም እንደተረጋገጠው የአንድ ሕዝብ ማኅበራዊ ዕድገት ከፍ ሲል ፣ የቁጥሩ ዓመታዊ ጭማሪ እየቀነሰ ይመጣል ። [66]

ለምሳሌ ፣ ዛሬ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የሚታየው በዕድገታቸው ወደኋላ በቀሩ አገሮች ነው ። ይህም የኋላ ቀርነታቸው አንዱ መግለጫ ነው ። በእነዚህ አገሮችም ሆነ በዓለም ደረጃ የማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት ከፍ ማለት የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የመቀነስ ውጤት አለው ። በተጨማሪም፣ የማኅበራዊ ዕድገት ከፍተኛ ደረጃ ቢደርስ እንኳን የሕዝብንም ቁጥር ሆነ የሌላውን የተፈጥሮ ሀብት በዕቅድ ለማሳደግ የሚችል ማኅበራዊ ሥርዓት ማለትም ኮሚኒዝም ወይም የዚህ ሥርዓት የመጀመሪያው ደረጃ የሆነው ሶሻሊዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ እውን ሊሆን የሚችል መሆኑን የኅብረተሰብ የዕድገት ሕጋጋት ያስገነዝባሉ ። እስካሁንም ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የመሠረቱ አገሮች የሕዝባቸውን ዕድገት በዕቅድ ለመምራት የሚያስችሉ ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔታዎች (ለምሳሌ ፣ የሕዝብ ንቃት ፣ ድርጅታዊ ጥንካሬ ፣ ዕድገትን በማዕከላዊ ዕቅድ ለመምትት የሚያስችል ሐኅበራዊ የምርት ግንኙነትና ድርጅታዊ መዋቅር) ለሟልተው ይታያሉ ።

ስለሆነም በዓለም ውስጥ የሕዝብ ቁጥር መናርንና ሊያስከትል የሚችለውን ዓለም አቀፋዊ ችግር የማስወገድ ጥያቄ በመሠረቱ የኅብረተሰብ ዕድገት ማፋጠንን ፣ የሕዝብንም ቁጥር ሆነ ሌሎች ማኅበራዊ ዕድገቶችን በዕቅድ ለመምራት የሚያስችለውን የሶሻሊስት ብሎም የኮሚኒስት ኅብረተሰብ መመሥረትን የግዴታ አስፈላጊ የሚያደርግ ነው ማለት ነው ። ፍሬድሪክ ኤንግልስ ከዛሬ 80 ዓመት በፊት እንዳለው ፡-

> የሕዝብ ቁጥር እጅግ መናርንና የበለጠ መጨመርን መቆጣጠር አስፈላጊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል በዚያን ወቅት ቁሳዊ ምርትን ለመቆጣጠር የሚችለው የኮሚኒስት ኅብረተሰብ የሰውንም መራባት መቆጣጠር ይኖርበታል ። ይህንንም ያለችግር ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችለው እሱ ነው ። [67]

በማኅበራዊ ዕድገትና ከዚህም ተያይዞ ኅብረተሰብን በዕቅድ የማሳደግ መርሕ ተግባራዊ ካልሆነ ግን የዓለም ሕዝብ ቁጥር መናር በብዙ አገሮች የሕዝብ ዕልቂትንና ሌላም አሳዛኝ ማኅበራዊ ችግሮችን በዓለምአቀፍ ደረጃም ቀውስን ሊያስከትል እንደሚችል የሚያጠራጥር አይደለም ።

ነገር ግን ዛሬ ባለው የዓለም አቀፍ ደረጃ በአገሮች በሙሉ በአንድ ጊዜ የሶሻሊስት ሥርዓት ለመመሥረት የሚያስችል ነባራ

Digitized by Google

ዊና ሕሊናዊ ሁኔታ ተጓልቶ አይገኝም። ስለሆነም የሕዝብ ቁጥር መብዛት የሚያስከትለውን ችግር ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ የሚችለው ኅብረተሰብ እስኪመሠረት ድረስ የሚወሰዱት አንዳንድ የሕዝብ ቁጥር መቀነሻ እርምጃዎች (የኑሮ ማሻሻያ ፣ ለወሊድ መቆጣጠሪያ የሚሰጡ ትምህርቶች ፣ አንድ ቤተሰብ ሊኖረው የሚገባው የልጆች መጠንን በሕግ መወሰን) የችግሩን መባባስ ለመቀነስ ወይም ችግሩ ሊያደርስ የሚችለውን ቀውስ ለማዘግየት ፣ የኅብረተሰቡም ትግል ለትክክለኛው መፍትሔ እስኪሰባሰብ ድረስ የሰውን ሕልውና ለመጠበቅ ሊረዱ ይችላሉ ። ስለሆነም የሕዝብ ቁጥር መናር ጉልቶ እንደሚታይባቸው አገሮች ሁኔታ ዲሞክራሲያዊ በሆነ ተግባራዊ መሆናቸው ተደጋፊ መንገድ ይሆናል።

እዚህ ላይ አንድ መታወስ ያለበት ነገር አንዳንድ የቡርዧ ምሁራን ዛሬ በዓለም ተስፋፍቶ ለሚታየው ረሃብ መንስዔ የዓለም ሕዝብ ቁጥር መጨመር ከዚህም ተያይዞ የተፈጥሮ ሀብት (ቢያንስ በሚረባው ሕዝብ አካባቢ) መጧጠጥ የግድ ያስከተለው ችግር ነው የሚሉት አስተያየት ሳይንሳዊነት የሌለው መሆኑ ነው ። የተለያዩ ግምቶች የሚሰጡ ቢሆንም ይህን አባባል የሚያፈርሱ አያሌ በሳይንሳዊ ጥናት የተደገፉ መረጃዎች አሉ ። ለምሳሌ ፣ በአሁኑ ጊዜ የሚታወቀው የተፈጥሮ ሀብት ብቻ ዛሬ በዓለም ውስጥ ያለውን ሕዝብ አሥር ጊዜ እጥፍ ለማኖር የሚችል መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ ። [68] ባለንበት ዘመን በምድር ላይ ያለውን ምርት የማሳደግ ችሎታ በየወቅቱ የሚያሳየው የዕድገት መጠን ከሕዝብ ቁጥር የፈጠነ ነው ።[69] በዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት (World Food and Agricultural Organization) ያጠናቀረው መረጃ እንዳሳየው ዛሬ የሰው ልጅ በግብርና መስክ የደረሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ወይም ዕድገት ያለአንዳች እንቅፋት ለመላው የዓለም ሕዝብ ምርት ማምረቻ ለማዋል ቢቻል ኖሮ አሁን ያለውን የዓለም ሕዝብ የምግብ ፍላጐት ከማርካት አልፎ ዛሬ በምድር ያለውን ሕዝብ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ እጥፍ የሚሆን መመገብ ይቻላል ።

በተጨማሪም ሮገር ሪቬል የሚባል አሜሪካዊ ስለዚሁ ጉዳይ አስተያየቱን ሲሰጥ ተገቢውን ቴክኖሎጂና የመስኖ ሥራ ቴክኒክ በመጠቀም መላው የሰብል መሬት (Gross cropped area) ቢለማ ከ 50 እስከ 60 ቢሊዮን የሚሆን ሕዝብ ለመመገብ የሚችል ምርት ለማምረት ይቻላል ብሏል ።[70]

እንዲሁም ሊመረት የሚችለውን ወደ ጐን በመተው በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያለውን የምግብ ምርት ብንመለከት ምርቱ ለሰው ልጅ በሙሉ እኩል ከተሰራጨ (ከተከፋፈለ) እያንዳንዱ የዓለም ሰው የተሟላ የምግብ መጠን ሊያገኝ ይችላል ። [71] ለዚህ ነው የቡርዧ ምሁራን በዓለም ውስጥ ለሚታየው ረሃብ መንስዔ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ነው የማለት አስተያየት ስህተት ነው የሚባለው ። የችግሩ መንስዔ ማኅበራዊ ነው ። ማለትም ዛሬ በዓለም የሚታየውን ረሃብ ለማጥፋት እንቅፋቶች ፣ ሀ/ ያለውን የዓለም ምግብ ክምችት በተገቢው ዋጋ ወይም ለሰው ልጅ ችግር አስቦ አለማሰራጨት፣ ለ/ የተደረሰበትን የቴክኖሎጂ ጥበብ በየአገሮች ለምርት ሥራ ለማዋል እንከናች መኖራቸው ፣ (ለምሳሌ ፣ ጥበቡን ማስወደዱ፣ መደበቁ ፣ ወይም ጥበቡም ሥራ ላይ ውሎ ምርቱ ቢገኝ ዋጋውን በማስወደድ ወይም በሌላ ምክንያት በመጋዘን ታሽጐ እንዲቀመጥ ማድረግና የመሳሰሉት ችግሮች) ናቸው ። የችግሮቹ መፍትሔም በመሠረቱ በለሙትም አገሮች ሆነ በታዳጊ አገሮች ያለውን ሀብት በሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ሥር ማድረግና ለሰው ጥቅም በዕቅድ ማዋልን የሚጠይቁ ናቸው ። ዛሬ በአገሩ ከሚፈለገው የምግብ ምርት በላይ በምታመርተው

Digitized by Google

የተፈጥሮ ፀጋውን የተገፈፈ ምድር
(ከሰሜን ኢትዮጵያ)

Digitized by Google

በዩናይትድ ስቴትስ እንኳን ብዙ ሰዎች በበቂ ምግብ እጦት የሚሰቃዩት ምርቱ በሠርቶ አደሮች እጅ ባለመሆኑ ነው ።[72]

2. የአካባቢ አየር ውሃና ውቅያኖስ መበከል

የቡርዧ ምሁራን የአካባቢ አየር ፣ ውሀና ውቅያኖስ መበከል በለሙት አገሮች ያለው «የምርት ዕድገት የግዴታ ያስከተለው (አይቀሬ) ውጤት ነው የሚሉት» ትክክል አይደለም ።[73] በርግጥ በኢንዱስትሪ በገፉት አገሮች የቴክኖሎጂ ዕድገት (የኢንዱስትሪ መስፋፋት ጭምር) የአካባቢ አየር መበከልን አባብሰውታል ። ነገር ግን ይኸው የቴክኖሎጂ ዕድገት ፣ ሀ/ ከፋብሪካ የሚወጡ ቆሻሻዎችን ለማጣራት የሚያስችል መሣሪያ ለመሥራት ፣ ለ/ የኢንዱስትሪ ምርት ከንውን ያለቆሻሻ ማውጣት እንዲካሔድ ማለትም ከኢንዱስትሪ የሚወጡ ቆሻሻዎችን መልሶ በጥቅም ላይ ለማዋል ወይም ለማጣራት አስችሏል ። በአሁኑ ጊዜ ከኢንዱስትሪ ምርት «ምንም ዓይነት ቆሻሻ በምንም ዓይነት ቅርጹ » እንዳይኖር ለማድረግ ይቻላል ።[74]

ይህን ዓይነቱን የአመራረት ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ ተቀዳሚ ችግሮች ሆኖ የሚቀርበው የገንዘብ ጉዳይ ነው ። ምክንያቱም ዛሬ የምርት ሂደት የአካባቢን አየር እንዳይበከል አድርጐ እንደገና ለማደራጀት ከፍተኛ ወጭ ይጠይቃል ። ለምሳሌ ፣ በአካባቢ ጥናት ታዋቂ የሆነው አሜሪካዊው የሥነ ሕይወት ምሑር ፕሮፌሰር ባሪ ኮምነር ግምት ዩናይትድ ስቴትስ ይህን ለማድረግ 600 ቢሊዮን ዶላር ያህል ያስፈልጋታል ።[75] ገንዘቡን ለዚህ ዓላማ ማዋል ወይም አለማዋሉን ፣ ለሕዝባዊ ችግር ቅድሚያ መስጠት አለመስጠቱ የሚወሰነው ደግሞ በኅብረተሰቡ ዓይነት ነው ።

በካፒታሊስቱ ዓለም (የካፒታሊስት ሥርዓት በሚከተሉ ታዳጊ አገሮች ጭምር) የኢንዱስትሪ አሠራር ዋናው ዓላማ ትርፍ ማግኘት ስለሆነ ለተፈጥሮ አካባቢ እንክብካቤ የሚደረገው ጥረት የሚፈለገውን ውጤት አላስገኘም ። ነገር ግን ይህ የኅብረተሰብ ዓይነት ለመላው የሰው ልጅ ሕልውና ተቀዳሚ ትኩረት የሚሰጥ ቢሆን ባለው ቴክኖሎጂ በመጠቀም የአካባቢን አየር ንጽሕና ለመጠበቅ በቻለ ነበር ። (የአካባቢን አየር ብክላ ለመከላከል ሞኖፖሊስቶች እንቅፋት ስለመሆናቸው በዚህ ጽሑፍ ወደፊት መረጃዎች ይጠቀሳሉ።)

ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአካባቢን መበከል መከላከል የሚቻል መሆኑን ሶሻሊስት ሥርዓት የሚከተሉ አገሮች በተግባር እያሳዩና ወደፊትም በዚህ ለመግፋት ጥረት እያደረጉ ነው ። የሶሻሊስት ኅብረተሰብ አደረጃጀት በመሠረቱ ለመላው ሕዝብ ጥቅም መከበር ቅድሚያ የሚሰጥ በመሆኑ ዛሬ በተደረሰበትና ወደፊትም በሚፈጠረው የቴክኖሎጂ ጥበብ በመጠቀም ችግሩን ሊፈታው ይችላል ። ስለሆነም የአካባቢ አየር መበከል ችግር እልባት ማግኘት በሰው ልጅ ወደከፍተኛ የኅብረተሰብ ዕድገት መሸጋገር የሚወሰን ነው ። እስከዚያም ችግሩን ለማቃለል የሚወሰዱ ጠቃሚ እርምጃዎች ግን መናቅ የለባቸውም ።

3. ስለተፈጥሮ ሀብት «ማለቅ» ጉዳይ

የሰው ልጅ ዓለም አቀፋዊ የአካባቢ ችግር የሚደርስበት የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጨረሱ ወይም ለመጨረስ በመቃረቡ ነው የሚባለው አስተያየት ትክክለኛ አይደለም ። ይህ ማለት ግን አንዳንድ የተፈጥሮ ሀብቶች (በተለይ የታወቁ የማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብቶች) ከዕለት ወደ ዕለት እያለቁ አይሔዱም ወይም ከዚህ በፊትም በጥቅም ላይ በመዋላቸው ከምድረ ገጽ የጠፉ የተፈጥሮ ሀብቶች የሉም ለማለት አይደለም ። ዋናው ነጥብ ሳይንሳዊ መረጃዎች እንደሚገልጹትና በታሪክም እስከ ዛሬ እንደተረጋገጠው ሰው በማኅበራዊ ዕድገቱ ውስጥ በአካባቢው ካሉ ነገሮች ፍላጎቱን ለማርካት የሚያስችሉትን ስልቶችና ዘዴዎች የመቀየስ ችሎታ ያለው መሆኑን መገንዘቡ ነው ። የመሬት ሀብት

Digitized by Google

የሰውን ፍላጐት ለማርካት ያለው ችሎታ ኅብረተሰቡ ካለበት ስልተምርትና ከምርት ኃይሎች ፣ (ከቴክኖሎጂና ከዕውቀት የዕድገት ደረጃው ጭምር) ጋር የተጣመረ ነው ። ሰው እንደማኅበራዊ የዕድገት ደረጃው የሚያውቀውን የተፈጥሮ ሀብት በትክክል የመጠቀምና ፍላጐቱንም ለማርካት የሚያስችሉት አዳዲስ የተፈጥሮ ሀብቶች የማግኘት ችሎታ አለው ።[76] «ይህ ባይሆን ኖሮ የሰው ልጅ ከረጅም ዓመታት በፊት ሕልውናውን ባጣ ነበር ።»[77]

ዛሬ በምድር ላይ ያለውን ሕዝብ ለመመገብ በጥንቱ የጋርዮሽ ሥርዓት ጊዜ በነበሩት የምርት መሣሪያዎች (ቀስት ፣ ድንጋይ ፣ ዱላ ፣ ወዘተ) ለማምረት አይቻልም። በጋርዮሽ ኅብረተሰብ ውስጥ ሰው ለማምረት የተጠቀመባቸው የተፈጥሮ ሀብቶችና የዛሬው የዓለም ሕዝብ የሚጠቀምባቸው የተፈጥሮ ሀብቶች የተለያዩ መሆናቸውም ግልጽ ነው ። በአጠቃላይ እስከ ዛሬ ሰው ፍላጐቱን ሊያረካባቸው የሚችሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች ከዕለት ወደዕለት እያስፋፋ የአጠቃቀም ዘዴውንም በቁጠባ የማካሔድ ችሎታው እያደገ ነው ።

በመሆኑም ሰው በምርት ሂደትና ለሌላም ማኅበረሰብ አገልግሎት የሚጠቀምባቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ለዘለዓለሙ እነኝህ ብቻ ናቸው ተብለው ሊለኩ አይችሉም ። ስለዚህ የተፈጥሮ ሀብት የሚለው ቃል ትርጉም እንደ የኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ የሚለያይ ነው ።[78] ለምሳሌ በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ይኖር የነበረ ሰው የተፈጥሮ ሀብት ሲል በአካባቢው ያሉ የሚታደኑ የእንስሳትንና ለምግብ የሚውሉ የፍራፍሬ ዓይነቶችን እንጂ ከእነዚህ ብዙም አያልፍም ። በዚህ ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ የኖሩ ሰዎች (ታላላቅ ሳይንቲስቶች ጭምር) ፍላጐታቸውን በአቶሚክ ኃይል ለማርካት (ለምሳሌ ፣ ማዕድን ለማውጣት) ፍጹም አያስቡም ነበር ።[79] ዛሬ ግን ይህ ኃይል ለብዙ አገሮች አገልግሎት እየሰጠ ነው ።

የተፈጥሮ ሀብትን የበለጠ ለማወቅና ባለውም በትክክል ለመጠቀም የኅብረተሰብን ዕድገት የበለጠ ከፍ ማለት ፣ የምርት ኃይሎችን መዳበር ይጠይቃል ። ኅብረተሰቡ ካላደገ በተፈጥሮ ሀብት እጥረት፣ ወይም በትክክል ባለመጠቀም ቀውስ ውስጥ ሊገባ ይችላል ። ስለዚህ የተፈጥሮ ሀብትን ማለቅ የመቋቋሙ ጥያቄ ዋናው ነጥብ ኅብረተሰቡን የመለወጥ ፣ የማሳደግ ጥያቄ ይሆናል ማለት ነው ። ችግሩንም ለማስወገድ የኅብረተሰብ የዕድገት እንቅፋቶችን (በዝባዥና ጨቋኝ መደቦችን ጭምር) ማስወገድና አዲስ ስልተ ምርት (ለዕድገት እንቅፋት የማይሆነውን) ሶሻሊስት ስልተ ምርት መመሥረት ያስፈልጋል ። ችግሩ ዓለም አቀፋዊ ስለሆነ ምሥረታውም ዓለም አቀፋዊ መሆን አለበት ። በሌላ አነጋገር የሰው ልጅ የደረሰበትን ችግር ለመፍታት የግዴታ ወደላቀ የዕድገት ደረጃ መሸጋገር አለበት ። ዛሬ የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት የሶሻሊስት ብሎም የኮሚኒስት ኅብረተሰብ መመሥረትን ምንያህል አስፈላጊና አንገብጋቢ እንዳደረገው የተፈጥሮ ሀብትን በትክክል የመጠቀም አስፈላጊነት ጥያቄን ብቻ በመመርመር ለማየት እንሞክር ።

በተፈጥሮ ሀብት በትክክል ስለመጠቀም

በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በያንዳንዱ አገር የሚታየው የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር አንዱ ምንጭ በተፈጥሮ ሀብት በትክክል አለመጠቀም መሆኑ ተጠቅሷል ። ይህን ነጥብ ለማብራራት በእርሻ ሥራ ከነውን የተዛባ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም የሚያስከትለውን ችግር እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል ።

የእርሻ ልማት መስፋፋት እያሌ የተፈጥሮ ሀብቶችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ

Digitized by Google

መጠቀምን ያጠቃልላል ። ነገር ግን መሬቱ ሲታረስ ፣ አፈሩ ሲገለበጥ ፣ የእርሻ መሬት ለማግኘት ሜካው ሲመነጠር ፣ ወዘተ በዕቅድ ፣ በጥንቃቄና ጥናት እንዲያዐበትል እየታሰበ ካልተካሄደ በስተቀር እያደር የተፈጥሮ ሀብት ተጓጠለው መሬት ወደ ምድረ በዳነት ይለወጣል ።

ይህ ጥፋት የሰው ልጅ የተገኘ ሥልጣኔ አብቦባቸው በነበሩት በፋርስ ፣ በሜሶፖታሚያና በግሪክ ደርሷል ።[80] በኢትዮጵያም ቢሆን የደን መመንጠርና የእርሻ ልማት በግብታዊነት መንገድ መካሄድ የአገሪቷ ለም አፈር እንዲከላና በአንዳንድ አካባቢ (በተለይም በሰሜን ኢትዮጵያ) የተፈጥሮ ፀጋው እንዲራቆት አድርጎታል ። በዚህም ምክንያት ከምርት መከናወኛነት ውጭ የሆነ መሬት ተፈጥሯል ። በዓለም አቀፍ ደረጃም ዛሬ የሚካሄደው የውሀ ፣ የደን ፣ የአፈርና የዓሣ አጠቃቀም በአሁኑ ሁኔታ ከቀጠለ እነኝህ የተፈጥሮ ሀብቶች ከ50ና ከ70 ዓመታት በኋላ መጠናቸው በጣም የመነመነ እንደሚሆን ከላይ ተጠቅሷል።

በተፈጥሮ ሀብት በትክክል አለመጠቀም የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነትን ከችግር አዘቅት ውስጥ ይከታል ። የሰው ሕልውና ቅድመ ሁኔታ የሆኑትን የተፈጥሮ ሀብቶች ያጠፋል ከተባለ መፍትሔው ምንድን ነው? መጠቀሙን ማቆም ወይስ በትክክል መጠቀም? በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ ላይ እንደ ተጠቀሰው የሰው የሕልውናውና የዕድገቱ መሠረት ሥራ ነው ። ሥራ ደግሞ ያለተፈጥሮ ሀብት መጠቀም ፍጹም የማይታሰብ ነገር ነው ። ስለሆነም የሰው ልጅ ሕልውናውን ለመጠበቅም ሆነ የበለጠ ለማደግ የግድ በተፈጥሮ መጠቀም አለበት ።

በተፈጥሮ ሀብት መጠቀም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ከሆነና በትክክል አለመጠቀም ደግሞ ችግር ከፈጠረ ፣ መፍትሔው የግድ በትክክል መጠቀም ይሆናል ። በትክክል መጠቀም ማለት ምን ማለት ነው ? ምን ዓይነት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው ሰው ወይም ኅብረተሰብ በተፈጥሮ ሀብት በትክክል መጠቀም የሚችለው ?

በተፈጥሮ ሀብት በትክክል መጠቀም (Rational utilization of resources) ማለት ይህን ሀብት «አሁን ላለውና ለወደፊቱ የኅብረተሰብ ትውልድ ዘላቂ ጥቅም ሊውል በሚችልበት ሁኔታ መጠቀም ነው»[81] በተፈጥሮ ሀብት በትክክል መጠቀም ማለት ያለውን የተፈጥሮ ሀብትና ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ለመላው የሰው ልጅ ሕልውና፣ ለመላው ኅብረተሰብ በሚበጅ ሁኔታ ፣ ዘላቂና ጊዜያዊ ጥቅምን በተመጣጠነና በሚያረካበት መንገድ መጠቀም ነው ። ይህን ትርጉም ማርክሲስቶች ብቻ ሳይሆኑ አያሌ የቡርዧ ምሁራን ጭምር ይቀበሉታል ። ችግሩ ተግባራዊ ማድረጉ ነው ። አጠቃቀሙን ተግባራዊ ማድረግ ማለትም ትክክል ያልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን ለማስወገድ ኅብረተሰብ ሊኖሩት ወይም ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆዎች አሉ ።[82] ከእነዚህ መርሆዎች ዋና ዋናዎቹ* ኅብረተሰቡ አንደኛ ፣ በአባላቱ ዘላቂ የጋራ ጥቅም ላይ የተዋቀረ መሆን አለበት ፤ ሁለተኛ ፣ አሠራሩ በዕቅድ መመራት አለበት ፤ ሦስተኛ ፣ የሚካሄደው እንቅስቃሴ በነባራዊ የዕድገት ሕግጋት ወይም በንቃት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ። እነኝህን መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ ማንኛውም የኅብረተሰብ ዓይነት ይችላል ወይ? እንዴት? ለምን? መልሱን ለማግኘት የመርሆዎቹን ትርጉም ዘርዘር አድርገን እንመልከት ።

አንደኛ ፣ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም አንዱ አንድን

* ኢ. ፌዶርቭ በትክክል መጠቀምን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መርሆዎች (Imperative) በማለት የጠቀሳቸው በአንደኛና በሁተኛ ቁጥር የተጠቀሱትን ነው ። ነገር ግን አልፎ አልፎ እርሱ እራሱ እንደሚገልጸው ለምሳሌ ፣ በገጽ 153—54 እና «በትክክል ለመጠቀም» ለሚለው ጽንሰ ሐሳብ የተጠቀሰው ፍቺ እንደሚያመለክተው በዕቅድ መጠቀም የሚለው መርህ በሦስተኛነት ሊቀርብ የሚችል ነው ።

Digitized by Google

ድርጊት «ትክክል» ወይም «ትክክል ያል
ሆነ» የሚል ትርጉም ለመስጠት ኅብረተ
ሰቡ ራሱ በዘላቂ የጋራ ጥቅም መከበር ላይ
የተዋቀረ ማኅበረሰብ መሆን አለበት ።
ምክንያቱም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ
የተፈጥሮ ሀብትንም ሆነ የሌላን ሀብት አጠ
ቃቀም በሚመለከት የሚሰጠው አስተያ
የት በመሠረቱ በመደብ ጥቅም ላይ የተመ
ረኮዘና ከመደብ አቋም የሚመነጭ ነው ።
በመሆኑም በተፃራሪ መደቦች የተከፋፈለ
ኅብረተሰብ ስለተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም
ሁኔታ የጋራ አቋም አይኖረውም ። የአንዱ
መደብ ጥቅም የመላውን የኅብረተሰብ
ጥቅም የሚያጓድል ሊሆን ይችላል ። በዚ
ህም ምክንያት ለአንዱ መደብ ትክክል
ያልሆነው ድርጊት ለሌላው ትክክል ሊሆን
ይችላል ። መደቦች የየራሳቸው ምግባራዊ፣
ኢኮኖሚያዊ ፣ ወዘተ አመለካከት አላቸ
ውና ።

የካፒታሊስት አገሮች መንግሥታት
የተፈጥሮ ሀብትን በተገቢው መንገድ ለመ
ጠቀምና ለመንከባከብ አንዳንድ እርምጃ
ዎች ለመውሰድ ተገደዋል ። በዚህም ምክ
ንያት የአየር መበከልን የሚከላከሉ ሕጎች
አውጥተዋል ፤ የደን ሀብት አጠቃቀም ሥር
ዓት እንዲይዝ ፣ የዛፎች መመንጠር እንዳ
ይፋጠን የሚያደርጉና ሌሎችም መሰል
እርምጃዎችን ወስደዋል ። [83] ነገር ግን
የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግሮች ከዕ
ለት ወደዕለት እየተባባሱ እንዳይሔዱ
ለማድረግ አልቻሉም ። ለምን ?

አንዱ ምክንያት በቁጥር አንድ የተጠቀ
ሰው መርሕ ተግባራዊ አለመሆኑን ፣ በሌላ
አነጋገር በማምረቻ መሣሪያች በግል በተያ
ዙበት የካፒታሊስትና የቅድመ ካፒታሊስት
ኅብረተሰቦች ለመላው ኅብረተሰብ አባ
ላት የጋራ ጥቅም መከበር ላይ የተዋቀሩ
አለመሆናቸው ነው ። ፋብሪካዎች ፣መሬት
ደንና የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሀብቶች በግል
የያዙት ባለንብረቶች ዋና ዓላማቸው የግል
ጥቅማቸውን ማስከበር በመሆኑ የአካባቢ
መበከል ችግር ትኩረት የሚሰጡት ጉዳይ
አይደለም ። ለምሳሌ አየሩን ወይም የወን
ዙን ውሀ የሚበክሉት ባለፋብሪካዎች ከፋ
ብሪካው የሚወጣውን ቆሻሻ ለማጣራት
ፍላጐት የላቸውም ። ምክንያቱም ይህ
ማጣራት ከትርፋቸው ትንሽ ተንሰው ተጨ
ማሪ መሣሪያ በመግዛት ማጣሪያውን እን
ዲሠሩ ያስገድዳቸዋል ። [84]

ይህ የትርፍ መቀነስ ደግሞ እያንዳንዱ
ካፒታሊስት ከሌሎች ካፒታሊስቶች ጋር
ለመወዳደር ያለውን ችሎታ ይቀንስበ
ታል ። በመሆኑም ፡—

> የፋብሪካው ባለቤቶች ከፋብሪካቸው
> የሚወጡ ቆሻሻዎችን ባገኙበት ቦታ
> መድፋትና ሌሎች ድርጅቶች ወይም
> የሕዝብ ደህንነት የሚመለከታቸው መን
> ግሥታዊ አካሎች ሕዝቡ በሚከፍለው
> ታክስ ከሚገኘው ገንዘብ እንዲያጣሩት
> ማድረግ ለግል ጥቅማቸው የበለጠ ጠቃ
> ሚ መሆኑን ይረዳሉ ። [85]

ፕሮፌሰር ባሪ ኮምነር በዩናይትድ ስቴ
ትስ ውስጥ የኢንዱስትሪና የግብርና ልማ
ት ባገሪቷ ሕዝብ ላይ የፈጠረውን ችግ
ርና የግል ባለንብረቶችም ለችግሩ መባባስ
መንስኤ መሆናቸውን በመዘርዘር ሲጽፍ
«. . . በአካባቢ መበከልን በመቆጣጠር»
እና በካፒታሊስቶች መሠረታዊ ጥቅም
ላይ ማለትም «በተቻለ መጠን ትርፍን ከፍ
የማድረግ ፍላጎት መካከል ቅራኔ » አለ
ብሏል ። [86] በታዳጊ ሀገሮች ዛሬ ተስፋፍቶ
ለሚታየው የአንድ ዓይነት ሰብል ማምረት
የመሬትን ለምነት በመጠበቅ አጠቃቀም
ላይ ሳይሆን ፣ በካፒታሊስቶች የትርፍ ማጋ
በስ ፖሊሲ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ምሁ
ራን ያስረዳሉ ። [87]

ሁለተኛ ፣ «በተፈጥሯዊ አካባቢ በትክ
ክል መጠቀምን ተግባራዊ ለማድረግ አንድ
ኅብረተሰብ የረጅም ጊዜ ዕቅድና መርሐ
ግብር ሊኖረው ይገባል ። ዕቅዱን በተግባር
ለመተርጐም ባለው ሀብት ሁሉ ለመገል
ገል መቻል አለበት ። [88] ይህን ለማድረግ
ደግሞ የኅብረተሰቡን ሀብት የጋራ (የወል)
ማድረግና በማዕከላዊነት መጠቀም አስፈ
ላጊ ሁኔታ ነው ።

የካፒታሊስት ሥርዓት በሰፈነባቸው
ሀገሮችና ይህ ሥርዓት ከቅድመ ካፒታሊ
ስት ሥርዓት (ሥርዓቶች) ጋር በተዳቀለ

Digitized by Google

ባቸው ታዳጊ ሀገሮች የመላው ኅብረተሰብ አባላትን ጥቅም ለማስከበር ዕቅድ ወይም ፕሮግራም ለመንደፍና ለዕቅዱም ተግባራዊነት የኅብረተሰቡን ሀብት በትክክል ለመጠቀም አይቻልም ። ምክንያቱም በመሠረቱ ሥርዓቱ በምርት ኃይሎች የግል ባለቤትነት ላይ የተዋቀረና ባለንብረቶቹ በፈለጋቸው መንገድ የየራሳቸውን ዕቅድና አጠቃቀም ስለሚወስኑ ነው ።

የካፒታሊስቱ ሥርዓት ዕድገቱን በዕቅድ ለመምራት ፣ የአካባቢንና ሌሎች የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታት ለምን እንደተሳነው የሚሰጡት ምክንያት ቢለያይም የተሳነው መሆኑን ግን አያሌ የቡርዧ ምሁራንና ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች ይናገራሉ ። ለምሳሌ ስለአካባቢ ሁኔታ ከፍተኛ ጥናት የሚያካሒደውንና ዘ ክለብ ኦቭ ሮም (የሮም ክበብ) በመባል የሚታወቀው ድርጅት መሥራች ፣ በብዙ የኢጣሊያን ፋብሪካዎች አመራር ውስጥ ከፍተኛ ሚና የአለው ኢጣሊያዊው ባለኢንዱስትሪ ዶ/ር አውሬሊዮ ፔሴይ በአንድ ወቅት ስለተፈጥሮ አካባቢ ባቀረበው ዘገባ ላይ «ዛሬ ያለው የካፒታሊስት አወቃቀርና ፍልስፍና የጊዜያችንን አንገብጋቢ ችግሮች ሊፈታ የሚችል አይመስለኝም[89] ብሏል ። *—

የዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲከኛ ሄነሪ ኪሲንጀር የካፒታሊስቱ ዓለም ግብ መንደፍና ተግባራዊ ለማድረግ ችግር ያለበት መሆኑን ሲገልጽ ፤— «የምዕራቡ ዓለም በከፍተኛ ችግር ውስጥ መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም ። ለጊዜያችን ተስማሚ የሆነ ፍልስፍና ወይም ፕሮግራም ለማውጣት አልቻለም »[90] በማለት ጽፏል ።

አሜሪካዊው ኮሚኒስት ጋስ ሆል የካፒታሊስት ሥርዓት አሠራር ዕቅድ የሌለው መሆኑና ይህም በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ችግር መፈጠሩን አስመልክቶ ፣ አካባቢ (Ecology) በካፒታሊዝም ሥርዓት ሥር ለመኖር እንችላለን ? በሚል ርእስ በጻፈው መጽሐፉ እንደሚከተለው ገልጿል ። «የሥርዓታችን ዋና ቀስቃሽ ኃይል ለትርፍ መጓጓት ነው ። የዚህም ውጤት የአካባቢ መበከል እና የተፈጥሮ ሀብታችንን በጭፍን መዝረፍን የሚያስከትለው ዕቅድ የለሽ ፣ ሥርዓተቢስ የምርት ክንውን ነው ። »[91]

ሦስተኛ ፣ አንድ ኅብረተሰብ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ግንኙነት ጤናማ ለማድረግና በአካባቢው ሀብት በትክክል ለመጠቀም እንዲችል የአባላቱ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ በተፈጥሮና በማኅበራዊ የዕድገት ሕግጋት ላይ የተመሠረተና የሚመራ ፣ አባላቱ ንቃታቸው ከፍ ያለ ፣ የሰውና የተፈጥሮ ውስብስብ ግንኙነትን ፣ ለሰው ሕልውና የተፈጥሮን እጅግ አስፈላጊነት የሚረዱ መሆን አለባቸው ። የዚህ ዓይነቱ ኅብረተሰብ የተፈጥሮን ችግሮች ለመፍታት የሚያወጣው ፖሊሲ ትክክልና በሕዝቡም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ይሆናል ። ሌኒን «ኅብረተሰብ ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው መስተጋብር በማኅበራዊና በተፈጥሮ የዕድገት ሕግጋት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት » ይላል ፤ ምክንያቱም «የነባራዊ ዓለም ሕግጋት - - - የሰው ንቁ ታሪክ ሠሪነት መሠረት ናቸው ። »[92]

ሰዎች ተፈጥሮን ለመንከባከብ በጐ ፍላጐት ቢኖራቸው እንኳን ስለተፈጥሮ ትክክለኛ ግንዛቤ ከሌላቸው በቀኝ እጃቸው ሲያለሙ በግራ እጃቸው ያጠፋሉ ።[93] የዚህም ውጤት ዞር ዞሮ ከችግር ማቅ ውስጥ አለመውጣት ይሆናል ። ሌኒን ሰው የተፈጥሮን ሕግ እስካለልተገነዘበ ድረስ ተፈጥሮ ለሚያስከትለው መጥፎ ነገሮች የሚ

* ፔሲ በዘገባው ላይ የሶሻሊስት ሥርዓትም ቢሆን ችግሩን የመፍታት ችሎታ አለው ብሎ አላምንም ብሏል ። እዚህ ላይ ዋናው ነገር ግን የካፒታሊዝም ሥርዓት ችግሩን ለመፍታት የተሳነው መሆኑን በተግባር ከሚታየው በተጨማሪ ካፒታሊስቶች እራሳቸው ማመናቸውን መገንዘብ ነው ።

Digitized by Google

ጋለጥና የተፈጥሮ ተገዥ መሆኑን ፣ ነገር
ግን እነኝህን ሕግጋት ካወቀ ደግሞ ከተፈ
ጥሮ መጥፎ ገጽታ ተፅዕኖ በመላቀቅ ነፃ
የሚሆን መሆኑን ሲገልጽ እንደሚከተለው
ጽፏል ፤ «የተፈጥሮን ሕግ ምንነት ፣ ይህ
ሕግ ከአዕምሯችን ነፃና ውጭ በመሆን
የሚሠሩ መሆኑን እስካልተገነዘብነው
ድረስ የሱ ባሪያ ያደርገናል ። ነገር ግን
አንዴ ይህን ሕግ ከተረዳነው… ተፈጥሮን
በቁጥጥራችን ሥር እናደርጋለን ።» [94]

በአጠቃላይ ኪሲንጀርና ሌሎችም የቡ
ርዧ ምሁራን እንደሚያምኑት ፣ ሳይን
ሳዊ ምርምር ያካሔዱ ኮሚኒስቶችና ተግ
ባር እንደሚረጋገጠው የካፒታሊስት ሥር
ዓት በዕቅድ ለመመራት ፣ የሚገጥሙትን
ማኅበራዊ ችግሮች (የአካባቢ ችግሮች
ጭምር) ሕዝቡን በንቃት በማሰለፍ ለመ
ላው ኅብረተሰብ አባላት በሚጠቅም ሁኔታ
ለመፍታት ፣ በሌላ አነጋገር በተፈጥሮ
ሀብት በትክክል ለመጠቀም የሚያስችሉ
መሠረታዊ መርሆችን ተግባራዊ ለማድረግ
ይሳነዋል ። የዚህ ዓይነቱ ችሎታ ያለው
ሶሻሊዝም ነው ። ለምን ?

አንደኛ ፣ የሶሻሊስት ሥርዓት መመሥ
ረት ኢንዱስትሪዎችን በመሬት ላይ ወይም
በከርሰ መሬት ውስጥ ያሉ የተለያዩ የተፈ
ጥሮ ሀብቶችን ፣ የእርሻ መሬትን ፣ ደንን ፣
የዱር አራዊትን ፣ የሕዝብ ወይም የመላው
ኅብረተሰብ ንብረት ያደርጋል ። በዚህም
ምክንያት «ለተፈጥሮ ሀብት ትክክል ያል
ሆነ አጠቃቀምና መበከል መሠረት የሆነ
ውን » የእነኝህ ሀብቶች የግል ባለቤትነት
ይወገዳል ። የሀብቶቹ የሕዝብ መሆን ለተ
ፈጥሮ ሀብት ትክክለኛ አጠቃቀምና እን
ክብካቤ የሚያስፈልገውን ፖሊሲ ተግባ
ራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታ
ዎችን ይፈጥራል ።

ሁለተኛ ፣ የሶሻሊስት ሥርዓት ኅብረተ
ሰብ በአባላቱ በጋራ ጥቅም መተሳሰርና
መረዳዳት ላይ የተዋቀረ በመሆኑ ከብዝበ
ዛና ከበዝባዥ መደቦች ግንኙነትና ሽኩቻ
ነፃ ነው ። በዚህም ምክንያት ነባራዊ የሆ
ነውን የወል ጥቅም ለማስከበር (በተፈጥሮ
ሀብት በትክክል መጠቀም ጭምር) ሁሉም
የኅብረተሰብ አባል የጋራ አመለካከት ይና
ረዋል ። [95]

ሦስተኛ ፣ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የም
ርት መሣሪያዎች የጋራ በመሆናቸውና በኢ
ኮኖሚው ዕድገት ፣ ሳይንሳዊ ዕቅድ ለግ
ውጣት ፣ ግብ ለመንደፍና ይህንንም ተግ
ባራዊ ለማድረግ ይችላል ። በዕቅድ መሥ
ራቱ ከሚያካትታቸው ክንዋኔዎች መካ
ከል የሚከተሉት ይገኙበታል ፣

1. የኢንዱስትሪንና የእርሻን ዕድገት
   በተመጣጠነ ሁኔታ መምራትና
   እንደተፈጥሮው ሀብት የብልጽግና
   ሁኔታ የሕዝቡን አሠፋፈር መወሰን፤
2. የተፈጥሮ ሀብት አፈላለግን ፣መጠ
   ኑንና የፍጆታን ምጣኔ (rate)
   መወሰን ፣
3. የተፈጥሮ ሀብት አወጣጥን ወይም
   አጠቃቀምን ውጤታማ በሆነ
   መንገድ ማካሔድ ፣
4. የኅብረተሰብ አባላት በተፈጥሮ
   ሀብት መጠቀም ብቻ ሳይሆን ለተ
   ፈጥሮ ሀብት መዳበር ማድረግ
   የሚገባቸውን አስተዋጽኦ መወ
   ሰን ፣
5. የገበያን ሁኔታ በማየት ብቻ ከአ
   ንዱ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም
   ወደሌላው አጠቃቀም መዛወሩን
   ማስቀረት ፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠ
   ቃቀም በጥንቃቄ እንዲካሔድ ማ
   ድረግ ፣ [96]

በተጨማሪም የሶሻሊስት ኅብረተሰብ
አባላት ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታትና
ኑሮአቸውን ለማሻሻል በየፈርጁ ስለተደ
ራጁ እርስ በርሳቸው ስለሚወያዩና ዲሞ
ክራሲያዊ አሠራርን ስለሚከተሉ የላቀ
ንቃት አላቸው ። ይህ ንቃታቸው በእነር
ሱና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ግንኙነት
በትክክል እንዲረዱ ፣ ጉዳዩ እርምጃዎችን

Digitized by Google

እንዲያስወግዱ፣ ስሕተትም ቢፈጸሙ ከፍተኛ ጉዳት ከመድረሱ በፊት በቶሎ ለማረም እንዲችሉ ንቁና ብቁ ያደርጋቸዋል። በዚህም ምክንያት የሶሻሊስት ኅብረተሰብ አባላት ንቃት ኅብረተሰቡ ለሚያወጣው ዕቅድ ተፈጻሚነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

የሶሻሊስት ሥርዓት የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ከካፒታሊስቱ ሥርዓት አጠቃቀም በዓይነቱ የተለየና የላቀ መሆኑን በተግባር ከሚታየው ባሻገር የቡርዧ ምሁራን ጭምር ይመሰክራሉ። ለምሳሌ ይህ ሥርዓት በተጠናከረበት በሶቪየት ኅብረት ውስጥ የሚካሔደውን የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣ የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነትን ችግሮች በማስወገድ አንፃር የሕዝቡን ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ፣ መንግሥቱ አካባቢን በሚበክሉ የሀገሪቷ ኢንዱስትሪዎች ላይ የሚወስደውን ርምጃ በማድነቅ ፕሮፌሰር ባሪ ኮምነር ሲጽፉ፣ በአካባቢ ችግር አፈታት፣

> የሶቪዬት ኅብረት የሶሻሊስት ሥርዓት ከገል ሀብት ሥርዓት በጣም የተሻለ ነው። ለኢንዱስትሪና ለእርሻ ልማት — እንዲያውም ከሞላ ጉደል ለእያንዳንዱ ኢኮኖሚያዊ ሕይወት—ዝርዝር ብሔራዊ ዕቅድ ማውጣት የሶቪየት ሥርዓት ዓይነተኛ ባሕሪ ነው። አካባቢያዊ ችግርችን ለማቃለል በሚደረግ ማንኛውም ጥረት የዚህ ዓይነት ዕቅድ ጠቃሚነት በዩናይትድ ስቴትስ ያለውን የተዘበራረቀ አካባቢያዊ የተባባሰ ችግር በቀርብ ለሚያውቅ ለማንኛውም ሰው የሚሰወር አይደለም።[97]

ፕሮፌሰሩ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ባለሥልጣናት የመኪና አምራች እንዱስትሪዎች አካባቢን እንዳይበክሉ ለመከላከል የሚያካሒዱትን ተስፋ አስቆራጭ ሙከራ እንዲሁም ግዳበሪያና ሌሎች ሰው ሠራሽ ፀረ ተባይ አምራች ድርጅቶች ለግላዊ ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸው ቅድሚያ በመስጠት የእርሻን ሥራ በተፈጥሮ ሀብት ትክክለኛ አጠቃቀም ላይ እንዳይመሠረት ያደረጉ መሆኑን ከገለጸ በኋላ፣ «በመጨረሻ በኤኮኖሚው እንቅስቃሴና በአካባቢ እንክብካቤ መካከል ባሉት መሠረታዊ ግንኙነቶች አንፃር የሶሻሊስቱ ሥርዓት ከግል ሀብት ሥርዓት የተሻለ ነው»[98] በማለት አስገንዝቧል።

ሶሻሊስት ሥርዓት በተፈጥሮ ሀብት በትክክል ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓት ነው ሲባል በአሁኑ ጊዜ ይህ ሥርዓት በሰፈነባቸው ሀገሮች ሁሉ የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር ፈጽሞ የለም ወይም አያሳስብም ለማለት አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ፣ የአካባቢ መበከል ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ ስላለው በካፒታሊስት ሀገሮች በሰፊው የሚካሔደው የተፈጥሮ ብከላ ለሶሻሊስት ሀገሮችም የሚደርስ ነው። ሁለተኛ፣ ዛሬ የሶሻሊስት ሥርዓት የተመሠረተባቸው ሀገሮች ቀደም ሲል በየሀገራቸው ከነበረው አሮጌ ሥርዓት የወረሱት የተፈጥሮ ሀብት ትክክለኛ ያልሆነ አጠቃቀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያስከተለው ችግር ሙሉ ለሙሉ ተወግዷል ለማለት አይቻልም። ሶስተኛ፣ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ በመሠረቱ ስለተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም አመች ሁኔታዎችን የፈጠረና ለመፍጠር የሚችል ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ አባላቱ በሙሉ አንዳንድ ትክክለኛ ካልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ከሚያስከትሉ ድርጊቶች አውቀውም ሆነ ባለማወቅ የፀዱ አይደሉም።[99]

ስለሆነም በዛሬው የሶሻሊስት ሥርዓትም ውስጥ የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት

Digitized by Google

ችግር አለ ። ነገር ግን ዋናው ነጥብ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ የተፈጥሮ ሀብት ትክክለኛ አጠቃቀም ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት የሚሆኑትን መሠረታዊ ችግሮች (የተፈጥሮ ሀብት የግል ባለቤትነት ፣ የኅብረተሰቡ አባላት በተፃራሪ ጥቅም መከፋፈልን ፣ ዕቅድ የለሽ አሠራርን ፣ ወዘተ) ያስወገድና ወደፊት የሚፈጠሩ ችግሮችንም በነባራዊ የዕድገት ሕግጋት ላይ መሥርቶ በሚያወጣው ፖሊሲ ለመፍታት የሚችል መሆኑ ነው ። ይህንንም በተግባር እያስመሰከረ መሆኑንም እላይ የተጠቀሱት መረጃዎችና በተጨባጭ የሚታየው ይመሰክራሉ ።

ማጠቃለያ

ባለንበት ዘመን የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት የያዘው አዝማሚያ ለሰው ልጅ ሕልውና እጅግ አሥጊ ነው ። አደገኛነቱ በተለያዩ መልኮች ለምሳሌ በመሬት መሸርሸርና በአፈር መከላት በተፈላጊ ውሀ እጥረት ፣ በደን መመንጠር ፣ በውቅያኖስና በአየር መበከል ይከሠታል ።

ለችግሩ መፈጠር የቀጥተኛ ምክንያቶች በተፈጥሮ ሀብት በትክክል አለመጠቀምና በዕቅድ አለመመራት በዓለም ላይ ያለውን (የሰው ልጅ የደረሰበትን) የቴክኖሎጂ ጥበብና የመሬትን የተፈጥሮ ሀብት በተገቢውና ተስማሚ በሆነው ሁኔታ ለመላው የሰው ልጆች ደኅንነት አስቦ አለማሰራጨትና ለሰው ጥቅም አለማዋል ፣ ሌሎችም ተዛማጅነት ያላቸው ዕክሎች ናቸው። በዚህ ጽሑፍ ከቀረቡትና ከሌሎችም መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ሰው በመሠረቱ ችግሩን የመፍታት ችሎታ አለው ።

የችግሩ መፍትሔ የዓለም ሕዝቦች በአንድ ላይ በመደራጀት የአካባቢ ሀብት አጠቃቀምን ፣ የኅብረተሰብ ዕድገትን (የሰውን ቁጥር ማደግ ጭምር) ሳይንሳዊ በሆነ ዕቅድ መምራትንና የሰውን ችሎታ ሁሉ ለሰው ልጅ ደኅንነት ተግባራዊ ማድረግን የሚጠይቅ ነው ። ሰው ይህን ችግር ከፈታ ዕድገቱ የበለጠ ሊገፋ ይችላል ፤ ካልፈታ ግን ራሱን በራሱ ለጥፋት ይዳርጋል ።

በዚህም ምክንያት እጅግ አሳሳቢ የሆነው የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር እልባት ማግኘት ወይም አለማግኘቱ የሚወሰነው በችግሩ ስፋት ወይም ክብደት ፣ ወይም ውስብስብነት ሳይሆን የዓለም ሕዝብ በሚወስደው ርምጃ ይሆናል ። ችግሩ ሰው ከፈታው የሚፈታ ፣ ካልፈታው ግን የሚያጠፋው ነው ። ነገር ግን የዓለም ሕዝብ ለችግሩ መፍትሔ መስጠት ወይም አለመስጠት የሚወሰነው ደግሞ በዓለም ውስጥ በሚኖረው የማኅበራዊ ሥርዓት ዓይነት ነው ።

ዛሬ የሰው ልጅ ዕድገት የደረሰበት ደረጃ በአንድ በኩል የካፒታሊዝምና የቅድመ ካፒታሊዝም ማኅበራዊ ሥርዓቶች ለተፈጥሮ ሀብት ዕቅዳዊ አጠቃቀምና ዕድገት ፣ ለሳይንሳዊ የኅብረተሰብ አመራር እንቅፋቶች ሆነው ይታያሉ ። የሥርዓቶቹ ዓላማ የሰውን ልጅ ወደከፋ ጥፋት መገፋፋት ይሆናል ። በሌላ በኩል በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉትን መርሆች ተግባራዊ ሊያደርግና የዓለም ኅብረተሰብ ዕድገትን ሊያፋጥን የሚችለው ሥርዓት (ሶሻሊዝም) በታሪክ መድረክ መሠረቱን እያጠናከረ ነው ። ወደፊትም የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር ዘላቂ እልባት ማግኘት ሠርቶአደሮችን በዓለምአቀፍ ደረጃ ሥርዓት በሚያካሂዱት ትግል ይወሰናል ። ሠርቶአደሮች በየአገራቸውም ሆነ በአካባቢያቸው የሶሻሊስት ሥርዓት መመሥረት ለሰውና ለተፈጥሮ ግንኙነት ችግር መቃለል እያደርም ሙሉ ለሙሉ መፍትሔ ማግኘት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ።

በሥርዓቱ ምሥረታ «ዓለም የሠርቶ አደሮች ትሆናለች» ። ሠርቶ አደሮች ማንኛው

Digitized by Google

ንም ዓለም አቀፋዊ ችግር ለመፍታት ኃይ ላቸውን ለማስተባበር እንቅፋት ከሚሆን መሠረታዊ ማኅበራዊ ችግር (ለምሳሌ በተ ዛራፊ ጥቅም ከመከፋፈል) ነፃ ይሆናሉ ።

ምንም እንኳን የሰውና የተፈጥሮ ግንኙ ነት አሳሳቢ ችግር መፍትሔ የሚያገኘው በሶሻሊስት ሥርዓት ምሥረታ ነው ቢባ ልም ዛሬ ባለው የዓለም ሁኔታ ችግሩን ለማ ቃለል ሀገሮች በግል ፣ በአካባቢ ፣ በአህጉ ራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወስዷቸው እርምጃዎች (ለምሳሌ የምግብ እጥረትን ለማስወገድ ፣ የቴክኖሎጂ ጥበብን ለማስ ፋፋት ወይም ለመለዋወጥ ፣ የአካባቢ አየ ርን ፣ የውሀና የውቅያኖስ መበከልን ለመ ከላከል ፣ የውሀ ልማትን በጋራ ለማካሄድ ወዘተ) ተደጋፊ ሊሆኑ ይገባል ። ይሁን እንጂ እነኚህ እርምጃዎች የሚያስገኙ ቸው መፍትሔዎች የመሸጋገሪያ መሆና ቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ምክንያ ቱም የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር ከቁጥጥር ውጭ ሆና በዓለምአቀፍ ወይም በአካባቢ ደረጃ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት ለመቋቋም አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ እንጂ ለችግሩ ዘላቂ ወይም ሥር ነቀል እልባት አያስገኙም ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. M. Rosenthal and P. Yudin, *A Dictionary of Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1967), p. 265.

2. Yu. K. Pletnikov, "Social Relations" an article in *Philosophy In USSR: Problems of Historical .Materialism* (Moscow: Progress Publishers, 1981), p. 52.

3. *Man, Society and the Environment* (Moscow: Progress Publishers, 1975), p. 21.

4. See E. Fedorov, *Man and Nature* (Moscow: Progress Publishers, 1980), p. 9 and L.P. Astanin and K.N. Blagosklonov, Conservation of Nature (Moscow: Progress Publishers, 1983), pp. 8-9.

5. L.P. Astanin and K.N. Blagosklonov, p. 8.

6. A.P. Sheptulin *Marxist-Leninist Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1978), p. 295.

7. *Ibid.*, 296.

8. *Ibid.*.

9. See F. Engels, *Dialectics of Nature*, p. 179 quoted in A.P. Sheptulin, p. 297.

10. E. Fedorov, pp. 7-8.

11. K. Marx, *Capital*. Vol. 1. Moscow, 1974, p. 173. as quoted in Society and the Environment: A Soviet View (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 25,

12. *Society and the Environment: A Soviet View*, p. 25.

13. Alexander Spirkin, *Dialectical Materialism* (Moscow: Progress Publishers, 1983), p. 258.

14. V. Kelle and M. Kovalson, *Historical Materialism: An outline of Marxist Theory of Society* (Moscow: Progress Publishers, 1973, p. 77 and V.S.

Digitized by Google

myonov, *Nations and Internationalism* (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 19.

15. *Society and the Environment: a Soviet View*, p. 25.
16. A.P. Sheptulin, p. 303.
17. የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ፣ በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የማ.ፕ.ብ. ኮሚቴ ጽ/ቤት ፣ አዲስ አበባ፤ ጥቅምት 1977 ገጽ 8 (ያልታተመ)
18. I Laptev, *The World of Man In The World of Nature (Moscow*: Progress Publishers, 1979), pp. 16-17.
19. I Laptev, The Planet of Reason (A Sociological Study of Man-Nature Relationship (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 77.
20. I. Laptev, *The World of Man In The World of Nature*, p. 17.
21. E. Fedorov, p. 144.
22. Georgi Galperin, Ethiopia: Population, Resources, Economy (Moscow: Progress Publishers, 1981), p. 169.
23. I. Laptev, *The Planet of Reason (A Sociological Study of Man-Nature Relationship)*, p. 77.
24. Georgi Galperin, p. 169.
25. I. Laptev, The World of Man in the World of Nature, pp. 18-19.
26. *Ibid.*
27. I. Laptev, *The Planet of Reason (A Sociological Study of Man-Nature* Relationship p. 78.
28. የኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት መሪ ዕቅድ፤ (1977—1986) መስከረም 1977፤ አዲስ አበባ፤ ገጽ 73
29. የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ፤ ገጽ 2።
30. ሌላው ምክንያት ያለውን ውሃ በትክክል ለመጠቀም አለመቻል ነው።
See Georgi Galperin, p. 166.
31. Galperin, p. 166.
32. ዜና የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ዘመቻ ቅጽ 4 ቁ. 19፤ 1977፤ ገጽ 32
33. I. Laptev, p. 79.
34. *Ibid.*
35. *Ibid.*
36. *Ibid.*, p. 80.
37. *Ibid.*
38. Georgi Galperin, p. 234.
39. *Ibid.*, p. 231.
40. I. Laptev, p. 81.
41. I. Laptev, *The World of Man in the World of Nature*, p. 22.
42. Georgi Galperin, p. 233.
43. *Ibid.*, p. 232.
44. E. Fedorov, p. 144.
45. *Pravda*, September 20, 1972 as footnoted in I. Laptev, The Planet of Reason (A Sociological Study of Man-Nature Relationship), p. 82.
46. See I. Laptev, The World of Man in the World of Nature, p. 20.
47. Man, Society and the Environment, p. 151.
48. I. Latev, p. 17.
49. *Ibid.*, p. 18.
50. I. Laptev, The Planet of Reason (A Sociological Study of Man-Nature Relationship), p. 82.
51. Social Problems of Man's Environment: Where We live and Work (Moscow: Progress Publishers, 1981), pp. 166-168.
52. *Ibid.*, p. 169.
53. *Ibid.*, p. 170.
54. Alexander Spirkin, p. 260.
55. G. Khozin, *The Biosphere and Politics* (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 27.
56. Alexander Spirkin, p. 261.
57. I. Laptev, p. 83.

Digitized by Google

58. See *Social Sciences*, No. 2, 1981, p. 48.
69. *Dictionary of Scientific Communism* (Moscow: Progress Publishers, 1984,) p. 101.
60. *Society and The Environment: A Soviet View*, p. 39.
61. Ibid., p. 27.
62. *Social Science*, Vol. XVI, No. 1, 1985, p. 66.
63. E. Fedorov, p. 34.
64. *Ibid.*, pp. 34-35.
65. *Ibid.*
66. *Ibid.*, pp. 24, and 34.
67. K. Marx and F. Engels, Selected Correspondece (Moscow: Progress Publishers, 1975), p. 315 as Quoted in E. Fedorov, p.25.
68. See E. Fedorov, p. 25.
69. *Ibid.*, p. 63.
70. Roger Revelle, "Can The Earth Feed The Growing Multitude?" *The UNESCO Courier*, July - August, 1974, p. 9 Quoted in E. Fedorov, pp. 38-39.
71. E. Fedorov, p. 37.
72. *Ibid.*, p. 40.
73. Society and The Environment: A Soviet View, p. 41.
74. E. Fedorov, 56.
75. *Ibid.*, p. 57.
76. *Ibid.*, p. 63.
77. *Society and The Environment: A Soviet View*, p. 40.
78. E. Fedorov, p. 9.
79. *Ibid.*, pp. 20 and 31.
80. See K. Marx and F. Engels, Collected Correspondence, p. 190, Quoted in E. Fedorov, p. 145.
81. E. Fedorov, p. 89.
82. *Ibid.*,
83. *Ibid.*, pp. 71-72.
84. *Ibid.*, p. 72.
85. *Ibid.*, p. 72.
86. Barry Commoner, The Closing Circle, New York, Alfred Knopt, 1971, pp. 268, 270, as Quoted in E. Fedorov, pp. 68-69.
87. See E. Fedorov, pp. 70-71.
88. *Ibid.*, p. 89.
89. As Quoted in E. Fedorov, p. 139.
90. Henry Kissinger, The Necessity For Choice, Prospects of American Foreign Policy, New York, 1968, p. 98 as Quoted in E. Fedorov, p. 151-152.
91. Gus Hall, Ecology: Can We Survive Under Capitalism? New York, 1972. p. 7, As Quoted in I. Laptev, The Planet of Reason (A Sociological Study of Man-Nature Relationship), p. 9.
92. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 38, p. 187, Quoted in Man, Society and The Environment, p. 19.
93. I. Laptev, pp. 77-78.
94. Lenin, *Collected Works*, Vol. 14, p. 190 Quoted in Man, Society and The Environment, pp. 19-20.
95. Society and The Environment: A Soviet View, pp. 35-36, See also I. Laptev, The World of Man in the World of Nature, p. 216.
96. I. Laptev, p. 94.
97. Barry Commoner, The Closing Circle, New York, Alfred Kropt, 1971, p. 280, As Quoted in E. Fedorov, p. 100.
98. *Ibid.*
99. I. Laptev, The Planet of Reason (A Sociological Study of Man-Nature Relationship), pp. 31-32.

Digitized by Google

የካድሬ ስያሜና ተግባር በኢትዮጵያ አብዮት

—ካለፍንበት ልምድ

ሰሎሞን ገብሬ

የኢትዮጵያ አብዮት ለብዙ አከራካሪ ጥያቄዎች ውስብስብ ባሕርያት መጠናት ግፊትና ፍላጐት የፈጠረውን ያህል ለጥያቄዎቹም ምላሽ የመስጠት ብርቱ ኃላፊነት የወደቀው በእራሱ በአብዮቱ ላይ ነው ።

ተደጋግሞ እንደተነገረው ቀደም ሲል የሕሊናዊ ሁኔታዎች አለመሟላት ለነባራዊ የአብዮቱ ግፊቶች ትንብር ማጣት ምክንያት ቢሆንም የአብዮታዊ ትግልና አመለካከት አለመዳበር ወይም በማርክሳዊ ሌኒናዊ የትግል መስክ የተካበተ ባሕል አለመኖር ለአብዮታችን ከጅምሩ አለመቀነባበር ሌላው ምክንያት ሆኗል ። ከዚህም ባሻገር ለአብዮቱ ወደፊት መግፋት ልዩ አስተዋጽኦ የሚኖረው ኃይልም ፈታኝ በሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ በመከፋፈሉ የተጠናከረና የተዋሐደ የትግል ጐራ ሆኖ ለመውጣት ጊዜ ፈጅቶበታል ።

ይህም ሲባል አብዮታችን እንዲከፍል ከተጠየቀው መስዋዕትነትና ከተገኘውም ውጤት አኳያ የአብዮታዊ ባህል አለመዳበር ያሳደረው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ለማመልከት እንጂ በአብዮቱ ሒደት ውስጥ የተነሱ ውስብስብ ጥያቄዎች ተደሞውንም ሊያጋጥሙ ባልተገባ ነበር ፤ ወይም ሌሎች አብዮቶች ተመሳሳይ ጥያቄዎች የመፍታት ኃላፊነት አልወደቀባቸውም ነበር ለማለት አይደለም ። ይልቁንም አገራችን ከፊውዳል ስልተ ምርትም በመለስ እጅግ ኋላቀር የሆኑ ማኅበረሰቦች የሚኖሩባት እንደመሆኗ መጠን በሌሎች አገሮች የአብዮት ጥያቄዎች የሚከሰቱ ችግሮች በኢትዮጵያ ሁኔታ እጅግ የተወሳሰበ መልክ ሊይዙ እንደሚችሉ ለማስገንዘብ ነው ።

አሮጌውን ሥርዓት በማፈራረስ አዲስ ሥርዓት ለመገንባት በተፋፋመ ሕዝባዊ የትግል ማዕበል አማካይነት የተቀጣጠለው የየካቲት 66 አብዮት ብዙ ጥያቄዎች ከፊቱ ተደቅነውበታል ። የፖለቲካ ሥል

Digitized by Google

ጣን ጥያቄ ከአብዮቶች ሁሉ ተቀዳሚ ምላሽ የሚጠይቅ በመሆኑ በአገራችንም ለብዙ ዓይነት ፍላጊያዎች ምክንያት ሆኖ አወዛግቧል ። የብሔረሰብ ጥያቄ የበርካታ መላምቶች መፈ... ነጥብ ሆኖ ቆይቷል። የፓርቲ ግንባታ ትግል የአብዮቱን አጋግሽ ዕድሜ የፈጀ፣ ከቅብጥብጥ ሥርዓተ አልበኞች እስከ ብልጣ ብልጥ የሥልጣን ሕልመኞች ፍጭት ተካሒዶበታል ። እንዲር የሆኑትንና አንዳንዶቹንም ጉዳዮች እንደተገቢነታቸው ወደፊት በዝርዝር የምናነግቸውን ለመጠቆም ያህል እንጂ በእነዚሁ ሥር ሊጠቃለሉ የሚችሉ የኢኮኖሚ ግንባታ ስትራቴጂን ፣ የመከላከያ ኃይል አደረጃጀትን ፣ የውጭ ፖሊሲን ፣ ወዘተ... የሚመለከቱ ባለብዙ ፈርጅ ፍላጊያዎች በአጭሩ የአሥር ዓመታት የአብዮት ዕድሜ ውስጥ ለማየት ተችሏል ።

ይብዛም ይነስ የተነሱ ጥያቄዎች ሁሉ በሐሳብ ትንብር ደረጃም ሆነ በተግባር የታዩ አጸዎችና የተከሰቱ የተግባር መገለጫዎች በየደረጃቸው ትክክለኛና ሳይንሳዊ ፈር በመያዝ እንደየአመጣጣቸው ምላሽ እያገኙ ሔደዋል ።

ሆኖም በተሻለ ጥልቀትና ስፋት ተመሳሳይ ውይይትና የሐሳብ ግልጽነት ከሚሹት ጥያቄዎችና ባለፉት ዓመታት የአገሪ መንገድ አስተያየት ካገኙት መካከል የካድሬ ጥያቄ አንዱና ሊብራራ የሚገባው ሆኖ ይታያል ። ይህ ጥያቄ በስያሜ አዲስነቱ፣ በተግባርና በሥራ እንቅስቃሴ ይዘቱና በሚያስገኘው ውጤቱ የስያሜው ባለቤት ከነበሩትም ጭምር ሁሉ ተመሳሳይና ጥልቅ ግንዛቤን ካላገኙት ጥያቄዎች አንዱ ነው ። የማሌ ርዕዮተ ዓለም ሕዝባዊ ወገናዊነቱን በ ተግባር ለማረጋገጥ ግንባር ቀደም ሠራዊቱ የሆኑትን የካድሬዎቹን አጸምና ይዘት ፣ ባሕርይና የአሠራር ስልት በጥልቀት አብራርቶ ማየት ስለሚኖርበት ይህ ጽሑፍ ለዚሁ ዓላማ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የቀረበ ነው ።

የካድሬ ስያሜ

ስያሜ ሁሉ የተግባር መገለጫ ባይሆንም ተግባር የስያሜን ትርጉም የሚያረጋግጥ ወይም የሚሽር አለበለዚያም የተሳሳተ ግንዛቤን የሚፈጥር ሊሆን ይችላል ። በተለይም በመጠሪያነቱ ለኅብረተሰቡ አዲስ ቃል ሲሆንና መገልገያነቱም እርግጥ ውን ኅብረተሰብ ሽር አዲስ ለመገንባት የሕይወትን መስዋዕትነት የሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን ሕሊናን ጭምር የሚቆጠቁጥ የመደብ ትግል ለማራመድ ሲውል በመደብ ትግሉ ተፋላሚ በሚሆኑ ክፍሎች ሁሉ እንደየመደብ አጸግቸው የሚኮንን ወይም የሚሞገስ ፍቺ በመያዝ ለተለያዩ አመለካከቶች መጋለጡ አይቀርም ።

በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥም ከላይ በጠቀስናቸው የተለያዩ አዝማሚያዎች መነሻ የካድሬ ስያሜና ትርጉም የተለያየ አመለካከትን በመፍጠር በአንድ ወቅት እንዲያውም ግንና ምንስ የሚያደርግ ገለሰብ ካድሬ መሰኘት እንዳለበት በአብዛኛው ግልጽ ሳይሆን ለመቆየት ችሏል። ለጊዜው ይህን ጉዳይ ወደኋላ የምንመለስበት ይሁንና ካድሬ የሚለውን ቃል ፍቺ ለመነሻ እንመልከት ።

በመሠረቱ ካድሬ የሚለው ቃል በስያሜውም ሆነ በይዘቱ አጠቃቀሙ ሰፊ ግልጋሎት ለመስጠትና በተለይ በሠራተኛ ፓርቲዎች ሕይወት ውስጥ ታዋቂ ትርጉሙን ለመያዝ የበቃው በሶቭየት ኅብረት የመንግሥትና ፓርቲ አካላት የአመራርና የአሠራር ሥርዓት ወሳኝ መለኪያ ሆኖ ከቀረበ በኋላ ነው ።

«ትልቁ የሶቭየት ኢንሳይክሎፔዲያ » የተሰኘው መጽሐፍ የካድሬን ተቀዳሚ ትርጉም ሲሰጥ ፣ ካድሬዎች

በድርጅቶች (ኢንተርፕራይዝ) ፣ በተቋሞች ፣ በፓርቲ ፣ በሙያ ማኅበራትና በመንግሥት ድርጅቶች በተወሰነ የሥራ መስክ ተሰማርተው የሚገኙ ዋንኛ (ቋሚ) የሠለጠኑና ሙያ ያላቸው ሠራተኞች ናቸው ። በስፋት ለመናገር ቋሚ የመሥሪያ ቤት ባልደረቦችን ሁሉ ይመለከታል [1]

ይላል ።

ካድሬ የሚለው ጽንሰሐሳብ በአሁኑ ጊዜ ማርክሲስት ሌኒኒስት የሠራተኛ ፓርቲዎች ብቸኛ መጠቀሚያነት ባሕርይ በመያዝ በኮሚኒስቶች ዘንድ የአመራርና የአሠራር ፖሊሲ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል ። ከጥቅምቱ አብዮት በፊትም ሆነ በኋላ ስለሠራተኛው ፓርቲ ድርጅታዊ መዋቅር፥ስለሠራተኛው ፓርቲ ተዋጊነትና መሪነት ሚና ፥ ስለቋሚ አብዮተኞች (Professional Revolutionaries) ወሳኝነት ፥ ወዘተ ሌኒን ባነገበት ወቅት ሁሉ ካድሬ የሚለውን ቀጥተኛ ቃል ባይጠቀምም በይዘቱ የፓርቲውን አባላት በሚወክል ጽንሰ የካድሬን ፍቺ በተለያዩ ወቅቶች ያብራራውና አጠንክር ያሠመረበት እንደነበረ ጽሑፎቹ ያመለክታሉ ።

ከዚያም ወዲህ ቢሆን በአንጋፋው የሶቭየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ የፓርቲ ሰነዶችና ምርምሮች ፥ (Party Literature) ይኸው ጽንሰሐሳብ በሰፊት ዳብር ግልጽ ፍቺ በመያዝ ዛሬ የሁሉም አገሮች የሠራተኛ ፓርቲዎች በተቀራረበ ፍቺ የሚገለገሉበት ሆኗል ።

በመሆኑም ዛሬ በፓርቲ አመራር የካድሬ ጥያቄ ሲነሳ ፥ ትርጉሙንና ይዘቱን በሚመለከት ሲተነተን ከሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ድርጅት ውጭ አይደለም ። እንዲያውም የሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ድርጅት—ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ —ባሕርያቱ ፥ የአሠራርና የአደረጃጀት መርሆ ከግንባር ቀደምነቱ የሚመነጨውን ያህል ካድሬ የሚለው ፍቺና የፓርቲው የግንባር ቀደምትነት ባሕርይም ተወራራሽነት ወይም አንድነት ያላቸው ጉዳዮች ሆነዋል።

እንደ የሠራተኛ ፓርቲ የመደቡ ግንባር ቀደምና የተደራጀው ክፍል ፥ በዓይነቱም የላቀው የመደቡ ድርጅት ነው ሲባል ግንባር ቀደም ቅጠሪ [illegible] የሚያገኙት እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይደለም ። እንዲያውም ከአባላቱ ውጭ የተጠቀሱትን ባሕርያት ሊይዝ አይችልም ። ስለዚያም የአባላቱ ይዘትና ሚና ይሆናል የተጠቀሱትን ባሕርያት ሊያላብሱት የሚችሉ ። ስለሆነም ስለፓርቲው አሠራር ፥ አደረጃጀት የአመራር ሚና ፥ ጥራት ፥ ጥንካሬ [illegible] ስለአባላቱ ማንሳታችን ነው ። አባላቱም ስንል ካድሬዎቹ ማለታችን ነው ።

ካድሬ ስንል ከላይ እንደተጠቀሰው በተለይ ከማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲዎች ትግል ዕድገት ጋር እየሰፋ በመጣው ትርጉም የፓርቲውን ተልዕኮ የሚያስፈጽሙ በማንኛውም ደረጃ በፓርቲው ፥ በመንግሥትና በኅብረተሰቡ ውስጥ በሚገኙ ማኅበራዊ ቅንብሮች ውስጥ ያሉትን አባላቱን ማለታችን ነው ። *

ስለካድሬ ትርጉም ወይም ምንነት ቢናገር ሌኒን እንዲህ ይላል ፤ «ስለፓርቲ ካድሬዎች ስንናገር ሁሉንም የፓርቲ አባላት የሚመለከት ነው ። ምክንያቱም ማንኛውም የፓርቲ አባል በተሰማራበት የሥራ መስክ የፓርቲውን አመራር በተግባር የመግለጽ ግዴታ ስላለበት ነው ። በዚህም አገባቡ የፓርቲ አባል ማለት በትርጉም ካድሬ ማለት ነው ።» [3]

ከዚህ ፍቺ አኳያ ይሆናል የሰያሚውን ታሪካዊ ግልጋሎትና የሰያሚው ባለቤት የሆኑት ክፍሎች ተግባር በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ ያላደረውን ስሜትና ያስገኘውን ውጤት የምንመረምረው ።

---

* እርግጥ ፓርቲው በሚሰጠው አመራር አባልም ባይሆን ሙያተኞች ፥ ተመራማሪዎች ፥ በልዩ ልዩ መስክ የተሰማሩ አዋቂዎች የፓርቲውን ፖሊሲ የሚያስፈጽሙ በመሆናቸውና የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላትም አወቃቀር ይህንኑ የሚያገናዝብ በመሆናቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ (ይህም በዳበሩ ሶሻሊስት አገሮች ውስጥ በተጨባጭ የሚታይ ዕውነታ ነው ።) የተጠቀሱት ክፍሎች ሁሉ ካድሬ ተብለው ይጠራሉ ። የዚህ ጽሑፍ ትኩረት ግን በተወሰነው ክፍል ላይ ብቻ በማተኮር በፓርቲው አውታሮች ውስጥ ያሉትን የሚመለከት ይሆናል ።

Digitized by Google

ኪድሬና ቅድመ ግዕከል ትግል—የርዕዮተ ዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነት አስፈላጊነት ግደግ

የኢትዮጵያ አብዮት በገብታዊነት የተቀጣጠለ አብዮት ነው ሲባል ያለአሰባሳቢ ማርክሳዊ—ሌኒናዊ የፖለቲካ ድርጅት አመራር የተከሰተ መሆኑን ለማመልከት እንጂ፣ የሕዝቡ ብሶት እንዳይበርድና በተነሣበት ስሜት እንዲቀጥል ለማድረግ ገና ከአነሳሱ ጀምሮ የሕሊና ዝግጅት የጠየቀና በዚህም አቅጣጫ መረባረብ የተደረገበት መሆኑን ለመካድ አይደለም። ምንም እንኳን ፍጹማዊ የሆነ የፊውዳል አገዛዝ ማንኛውንም ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ባህል ለማዳበር የሚያስችል መድረክ እንዳይፈጠር፣ የተደራጀ የሕዝብ ትግል እንዳይታይ በተጠናከረ መንገድ ቢከላከልም የሥርዓቱ አስከፊነት ከ'66' በፊትም በተበታተነ የከልል ዓመጾችም ቢሆን የአደባባይ ምሥጢር ሆኖ ቆይቷል።

ለብዙ ጊዜያት ግልጽና ቁልጭ ያለ እንኳን ባይሆን ዲሞክራሲያዊና ፀረ ፊውዳል የሆነ አመለካከት እያደገ በመምጣቱ የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች — ከተቀጣጠለም በኋላ ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ የታገሉትም ሁሉ —የሕሊና ዝግጅት እንደነበራቸው የሚካድ አይደለም።

የሕሊና ዝግጅታቸው በአንድ አመለካከት ሥር ሊያሰልፋቸውና ሊያደራጃቸው አልቻለም እንጂ የአብዮቱን ፍንዳታ ይበልጥ ለማገዝና ለማቀጣጠል አላገዳቸውም። እዚህ ላይ መታወስ የሚኖርበት ጉዳይ ከዚህም ይበልጥ የበሰሉ ሕሊናዊ ሁኔታዎች ቢኖሩም እንኳን፣ (ማለትም የፖለቲካ ድርጅት ቀደም ብሎ ቢመሠረትም) የአብዮቱ መቀጣጠል ወይም የዓመፅ ሂደት ገብታዊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ የለም ሊባል አለመቻሉ ነው። እ.ኤ.አ. በ1905 በፒተርስበርግ ዛሬ በሌኒንግራድ ከተማ በሠራተኞች የተደረገውን ገብታዊ የሥራ ማቆም አድማ አስመልክቶ ሌኒን ሲናገር፣

> ... በመቶና በሺህ በሚቆጠሩ ወዝአደሮች አንድነትና ብርታት ኢኮኖሚያዊ ይዘት ብቻ የነበረው እንቅስቃሴ በሚያስደንቅ ቅጽበት የፖለቲካ ይዘት ወዳለው እንቅስቃሴ መሸጋገሩ ማንንም ያስገርማል። ይህ ሁሉ የሆነው ደግሞ የነቃ የሶሻል ዲሞክራቲክ ገፊት ባልኖረበት ወይም ለነስተኛ ጭላንጭል ብቻ በሚታይበት ሁኔታ ነው[3]

ያለውን ብቻ ማስታወስ ይበቃል። የኢትዮጵያ አብዮት መቀጣጠል የጊዜና የቦታ ትንበያ በድንገት ደራሽ መልኩ የተገለጸና የዲሞክራሲያዊ አመለካከት አራማጅ ክፍሎች ሁሉ ያልተዘጋጁበት ቢሆንም፣ ከጅምሩ እንሥቶ የተሳተፉበት አብዮት ነው። ያልተዘጋጁበት መሆኑና በሒደት እያሉ ውጣ ውረዶች በመከሰታቸው በአብዮቱ ግኝቶች ጥራትና ተከታታይ ዕድገት ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል። የአብዮቱን አጠቃላይ ፖሊሲዎች ያራምዳሉ ተብለው በተገመቱ ክፍሎች ውስጥም ከትርዕ እስከ ይዘት እንዲለያዩ ምክንያት ሆኗቸዋል።

ይህም ሆኖ የኢትዮጵያ አብዮት አንዱ በሌላው ላይ ተፅዕኖ በሚኖራቸው የሕዝቡ የትግል ግፊት ግደግና የዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቢያንስ በፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት አቋም ዙሪያ መሰባሰብ የተነሣ ከጊዜ ወደጊዜ ዕድገት እያሳየ መጥቷል። ትግሉ ተከታታይ ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎችን የመውሰድና የማስወሰድ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ አካል የመፍጠር ሂደት ውስጥ በመግባት ከአብዮቱ አራማጆች ሁሉ ፊት ዓቢይ የድርጅት ጥያቄን አቅርቧል።

የሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን የመያዝ ጉዳይ ካለዚህ መደብ የፖለቲካ ድርጅት የማይቻል በመሆኑ አብዮቱ በእርግጥም በተቀዳሚ የድርጅት ጥያቄን መፍ

ታት ነበረበት ። ይህ ተቀዳሚ ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ስለመሆኑ ከግራ ኃይሎች ግንዛቤ ያልራቀ ቢሆንም በመካከላቸው የተካሔደው የፖለቲካ ሥልጣን ሽሚያ የርስ በርስ ሽኩቻን ስላስከተለ በቀላሉ ለጥያቄው መልስ ለመስጠት አልተቻለም ነበር ።

ሠራተኛው መደብ የመደራጀትና ሥልጣን የመያዝ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበት ሒደትና ይዘት ነው ለረዥም ጊዜ የአብዮተኞችን (በኋላም በካድሬ ስያሜ የሚታወቁትን) ባሕርይ ምንነትና ትርጉም ሲወስን የቆየው ። ወደዚህ ለመምጣት በመጠኑም ቢሆን የጥያቄዎቹን ይዘት ፣ ስፋትና ጥልቀት በአጭሩ መመልከቱ ያገባል ።

ዓቢዩ ጉዳይ በጊዜው ሥልጣን ይዞ የነበረው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የመደብ ባሕርይ አንዱና ዋናው እንዲያውም እስከ ኢሠፓአኮ ምሥረታ ዋዜማ ድረስ አከራካሪና የልዩነት መነሻ ሆኖ መቆየት ነው ። አንዳንዶቹ የደርግን መደባዊ ባሕሪና በሚከተለው ፖሊሲ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በትንተና ከማዳበርና በትክክል ለመረዳት ከመጣር ይልቅ ደርግን በታሪክ ውስጥ ከታዩና አሁንም ከሚታዩ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት (ወታደራዊ አምባገነን ወይም ጁንታ) ጋር ቀኖናዊ (ጭፍናዊ) በሆነ አቀራረብ ለማያያዝ ሞክረዋል ፤ ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋም ያላቸው ኃይሎች (አብዮተኞች) ከመሰባሰብና የግራውን ኃይል ከማጠናከር ይልቅ ይኸንኑ ቀኖናዊ ትንተና በግድ ተቀባይነት እንዲያገኝ እያሌ ግፊቶች አድርገዋል ።

በአንድ በኩል አብዮቱ ተከታታይ ርምጃዎች እየወሰደ በመምጣቱ ፣ በሌላ በኩል በጥቅሉ ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋሞችን ለጊዜው ይበልጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው በሚል ምክንያት «ለአንድ ዓላማ የሚታገሉ» ክፍሎች የተለያዩ ድርጅቶችን ማቋቋም መርጠዋል።

በኢሠፓአኮ አንደኛ ጉባኤ ላይ በጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በቀረበው ማዕከላዊ ሪፖርት «በአጠቃላይ በሰፊው ሕዝብ መካከል (ደርግ) ከፈጸማቸው እያሌ አብዮታዊ ተግባራት ሌላ ፣ በራሱ ውስጥ አድፍጠው በነበሩት ከሐዲዎች ላይ በየጊዜው የወሰዳቸው የማያወላውሉ አቋሞች ለአብዮቱ ወደፊት መገፋት ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው »[4] በማለት እንደተጠቀሰው በመካከል ያለ የአቋም ልዩነትን አገናዝቦ ግልጽ አቋም ለመውሰድ በደርግ ውስጥ ካሉ አብዮተኞች በስተቀር በሌሎች ብዙ አብዮተኞች ዘንድ ረዥም ጊዜ ፈጅቷል ። ለዚህም መጓተት አንዱ ምንጭ በኢትዮጵያ አብዮት ሒደት ውስጥ የሠራተኛውን የበላይ ገዥነት እውን ለማድረግ በሚካሔደው ትግል የደርግን የሽግግር ሚና ጠንቅቆ አለመገንዘብ ነው ።

ዋናው ችግር የደርግን አብዮታዊ ፖሊሲዎች ሁሉ(ለአብዮተኞች ምቹና ይፋ መድረክ የፈጠሩት የየካቲት '66' ፖለቲካ ት/ቤትና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት መቋቋምን ጨምሮ) ከደርጉ አጠቃላይ የመደብ ባሕርይ ጋር ለማገናዘብ ካለመቻል ወይም ካለመሻት የተፈጠረ ነበር ለማለት ይቻላል ። በመሆኑም የመንግሥት ጥያቄ ለረዥም ጊዜ የሐሳብ አንድነት ያልታየበት ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል ።

ይህንን እዚህ ላይ አቁመን የድርጅት ጥያቄንም በሌላ በኩል ብንመለከት በአብዮቱ ካምፕ የተከሰተው ልዩነት ከላይ ከተጠቀሰው እምብዛም የተለየ አይደለም ። ሁለቱ ጥያቄዎችም ካላቸው ተደጋጋፊ ግንኙነት ሁኔታው ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም ነበር ።

የድርጅት ጥያቄ ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ ተቀዳሚ አጀንዳ እንደነበረ የሚታወቅ ሲሆን ፣ በተለይም ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት ለመጣል የሚያስችለው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም (ብ. ዲ. አ. ፕ)

Digitized by Google

ሚያዝያ 12 ፥ 1968 ከወጣም በኋላ በዚህ
ረገድ ለተያቄው ምላሽ ለመስጠት የበለጠ
ሕጋዊ መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ ተመቻ
ችቷል ። ፕሮግራሙ በሁሉም ዘርፍ የመሸ
ጋገሪያና ለኮሚኒስቶችም መለስተኛ የመሆ
ኑን ያህል ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊ
ስት የሆኑ ኃይሎችን ሁሉ የማስተባበር
ይዘት እንደነበረው ይታወቃል ። ሆኖም
በፖለቲካ ይዘቱ ፕሮግራሙ የሠራተኛውን
መደብ የመሪነት ሚና ተቀዳሚ አድርጐ
ስለሚነግ ለዚህ መደብ የፖለቲካ ድርጅት
መከሰት የአብዮተኞች ትኩረት ሊሆን
ፀተገባ ነበር ። ቁልፉና ወሳኙ የአብዮተ
ኞች ጥያቄ ይህ ነውና ።

ፕሮግራሙ ስለሕዝባዊ አብዮታዊ ግን
ባር ድል ዋስትና ሲገልጽ ለወዝአደሩ
ፓርቲ የመሪነት ሚና የሚሰጠውን ተቀ
ዳሚ ትኩረት በሚመለከት የሚከተለውን
አስፍሯል ፦

> . . . የዚህ አብዮታዊ ግንባር ድል ዋስትና
> የሚኖረው የወዝአደሩ ፓርቲ ተደራጅቶ ፣
> ተጠናክሮና ታግሎ የግንባሩን አመራር
> ሲጨብጥ በመሆኑ በመንግሥት በኩል
> ለዚህ ተግባር የተለየ ድጋፍ መስጠት ።
> በሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም ታንጾ ትግሉን
> የሚመራ የወዝአደር ፓርቲ እንዲቋቋም
> ለሚጣጣሩ አብዮታዊ ቡድኖችና ግለሰ
> ቦች በመንግሥት በኩል የማያቋርጥ
> ድጋፍ መስጠት [5] (ሥርዝ የተጨመረ) ።

ሆኖም በአብዮተኞቹ መካከል የኮሚኒ
ስቶች መለስተኛ ፕሮግራም የሆነው የፀረ
ፊውዳልና የፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎችና
ዲሞክራቲክ ድርጅቶች ኅብረት መረግ
መጃ መሆኑን በሐሳብ ብቻ ሳይሆን በተግ
ባርም ተቀብሉ የወዝ አደሩን ፓርቲ ለመ
ፍጠር ከመታገል ይልቅ ለተበታተነ ድር
ጅታዊ ስብስብ የተሰጠው ትኩረት አመ
ዘነ ። እንዲያውም በዲሞክራሲያዊ አብ
ዮት ውስጥ ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያ
ሊስት ኃይሎችን አስተባብር የሚመራው
የሠራተኛው መደብ ፓርቲ ሳይፈጠርና ለዚ
ህም መፈጠር ከሁሉ በፊት ሊደረግ የሚገ
ባው የርዕዮተ ዓለምና የመሥመር ትግል
በትድሚያ ሳይጸዋ በአብዮተኞች መካ
ከል (አስተባባሪ በሌለበት ሁሉም የራሱን
ድርጅት እያጠናከረ) መተባበር የሚለው
ድፍን የትግል ስልት ተመረጠ ። የሁኔታ
ዎች አስገዳጅነት ያመጣው ሆኖም ምክን
ያት ይቀርብለት ነበር ።

ከዚያም በማለፍ በየካቲት ወር 1969
የሠራተኛውን ፓርቲ ለመመሥረት በወቅቱ
የነበሩት ኅቡዕ ድርጅቶች የፈጠሩት ኅብ
ረት (ኢማሌድህ) ከላይ የጠቀስናቸውን
ዋና ዋና የልዩነት ነጥቦች እንደያዙ ወደኅ
ብረቱ በመቀላቀላቸው የብ. ዲ. አ. ፕሮግ
ራም ከወጣ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ እንኳ
የሠራተኛውን መደብ የፖለቲካ ድርጅት
ሊፈጥሩ አልቻሉም ። እንዲያውም በተቃ
ራኒው ወደአንድ የመገናኛ ነጥብ ከማም
ራት ይልቅ እየተራራቁ መጡ ። በዚህም
ምክንያት የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ከመ
ፍረከረካቸውም ባሻገር በአባልነት ጸን
ተው የቆዩትም አንድ የፖለቲካ መሥመር
ለማራመድ ከተስማሙ በኋላም እርስ በርስ
የመቻኮት አፍራሽ አዝማሚያዎችን በገ
ሐድ አሳይተዋል ። ሽኩቻው የአብዮቱን
ካምፕ ለማዳከም አስተዋጽኦ በማድረግ
አስፍስፈው አብዮቱን ለመቀልበስ ይጠባ
በቁ ለነበሩ አድኃሪያን ምቹ ሁኔታ ፈጥ
ሯል ።

በመጨረሻ የተረፉት የኅብረቱ አባል
ድርጅቶች ግለሰብ አብዮታውያንን በችሎ
ታቸውና አስተዋጽኦያቸው በማዋሐድ
አንድ ማዕከል ለመፍጠር በተስማሙበት
ወቅት የሁኔታውን አሳሳቢነት በመግለጽ
በጋራ ልሳናቸው ያስቀመጡትን ብንመለ
ከት ይህንኑ በውል ይጠቁማል ። የጋራ
ልሳኑ

Digitized by Google

> . . . የአመለካከት አንድነት ከተገኘና ይህ ነው የሚባል የፖለቲካ መሥመር ልዩነት በሌለበት ወቅት በቅርጽ ላይ በማተኮር ብቻ ሲሻኮቱ ቆይተዋል ። . . . በዚህም ሳቢያ በአብዮታውያን መካከል የማያስፈልግ ቅራኔ እየተነሳ አጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ተፈጥሮአል ። በጠባብ ቡድናዊ አመለካከት የተዋጡ አባላት ከአንድነት ይልቅ ልዩነት እንዲጉላ ገፋፍተዋል [6]

በማለት በአብዮቱ ወገኖች ላይ ይደርስ የነበረው ን አደጋ አመልክቷል ።

ቀደም ብሎ ለመጥቀስ እንደተሞከረውና በወቅቱ የነበሩት የኢማሌድህ አባል ድርጅቶች በሚያወጡት «የኅብረት ድምፅ » እንዳሰፈረው «ኮሚኒስቶች ሁኔታዎች ስለሚያስገድዱቸው እንጂ ምንጊዜም ለየብቻ የመደራጀት ፍላጐት የላቸውም» ቢባልም [7] «- - - እውነተኛ አብዮታውያን ዓላማቸው አንድ ስለሆነ በአንድ ፕሮግራም በአንድ ድርጅት መሰባሰብ አለባቸው » [8] የሚለውን በፓርቲ ምሥረታ የትግል ታሪክ ውስጥ የተመዘገበውን መርሕ ተግባራዊ ሊያደርጉ አልቻሉም ። ለዚህም ምክንያቱ በመካከላቸው ይካሔድ የነበረው የፖለቲካ ሽኩቻና መርሑን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ለማድረግ ቀላል ሆኖ አለመገኘቱ ነው ።

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው አወዛጋቢ የፖለቲካ ጥያቄዎች ምንም እንኳ በአጭሩ ሊፈቱ የሚችሉበት ሁኔታ ሩቅ ነበር ባይባልም ፣ በአብዮቱ ገስጋሴ ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ ፣ በአብዮተኞቹ የጋራ አመለካከትና እንቅስቃሴ ላይ ያስከተሉት ጉዳት ከፍተኛ ነው ። በድርጅታዊ አንድነት የሚገለጽ የፖለቲካ መሥመር አንድነት ከሌለ በስተቀር የአብዮተኞች የትግል ኅብረት ጥራትና ጥንካሬ የጐደለው ስለሚሆን በይዘታቸውና በእንቅስቃሴያቸው ላይ የተለያየ አመለካከት የመፈጠሩ ሁኔታ የግድ የሚከተል ጉዳይ መሆኑ አይቀርም ።

ድርጅታዊና አመለካከታዊ (ርዕዮተ ዓለማዊ) አንድነት በሌለበት ሁኔታ ደግሞ የሰያሚ ተመሳሳይነት ሊኖር አይችልም ። የድርጅት አባላት እንደሚታቀፉበት ድርጅት የውስጥ ሕይወት መላላትና መጥበቅ ከዓላማ ጽናት ማለትም ርዕዮተዓለማዊ ገልጽነት እስከ ሥምሪት ውጤታማነት ድረስ በተለያየ መለኪያ ስለሚታዩ ስለሚወከሉት መጠሪያ አንድ ግንዛቤ ሊያስተላልፉ አይችሉም ። ይህ ሁኔታ እንኳንስ በተበታተነ መልክ ተደራጅተው በሚገኙ የድርጅት አባላት ቀርቶ በአንድ ድርጅት ውስጥም በሚኖር የአባልነት ሥርዓተ ደንብ የተዛባ ይዘት መነሻ የሚታይ ችግር መሆኑ የማይቀር ነው ።

ይህንኑ ድርጅታዊና ርዕዮተ ዓለማዊ አንድነት በውል ለማረጋገጥ ነው ሌኒን በሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ 2ኛ ጉባኤ ወቅት ለውይይት በቀረበው የፓርቲው ረቂቅ ደንብ አንቀጽ አንድ ላይ አምርሮ የተከራከረው ። ሌኒን በተለይም ፓርቲው ፈታኝ ወቅት ውስጥ በነበረበት ጊዜ የፓርቲ አባላትን መቀበያ ደንብ እጅግ የላላ ከሆነ ሊከተል የሚችለውን ችግር ሲገልጽ ፣ «- - - በፓርቲ ሕይወት - - - - ውስጥ በቀጥታ ይህ የላላ ሁኔታ ነው ያለጥርጥር ለማንኛውም ዓይነት ውዥንብረኞች ፣ ወላዋዮችና አድርባዮች በሩን የሚከፍተው » [9] ብሏል ።

እንግዲህ ይህ በተቃራኒው በነበረበት ተጨባጭ ሁኔታ ማለትም ለአንድ ዓላማ እንታገላለን የሚሉ ግን ለየብቻ የተዋቀሩ ድርጅቶች በሚገኙበት ሁኔታ የየድርጅቶቹ አባላት ሕይወትና ይዘት ምን ያህል የተዘበራረቀና ለተለያዩ የዲስፕሊን ሥርዓቶች ተገዥ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም ። እነዚህ አባላት በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸው የስያሜ ፣ የተግባር ጥራትና ገልጽነት የሚለካውም እንዲሁ ከዚሁ የተለያየ ሁኔታ በመነሣት ይሆናል። ድርጅቶቹ የሚያራምዱት የፖለቲካ መሥ

Digitized by Google

መርና የሚከተሉት አሠራር በአባሎቻቸው (ካድሬዎቻቸው) ይዘትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም ። ምክንያቱም ካድሬን ከድርጅት ፣ ድርጅትን ከመሥመሩ ፤ እንዲሁም መሥመሩን ተፈጻሚ ከሚሆንበት የአሠራር ስልት ለይቶ ማየት አይቻልም ።

ይህ በተለይ የማርክስ ርዕዮተዓለምን በሚያራምዱ የሠራተኛ ፓርቲዎችና ኅብረተሰቦች ውስጥ ሁሉ ተፈጻሚ የሚሆን ጉዳይ ነው ። ሌ ድዋን ስለዚህ ሲናገር ፣ «ካድሬ የድርጅቱ አንድ ክፍል ስለሆነ ከድርጅቱ ውጭ ልናስበው አንችልም » [10] በማለት የድርጅቱ ቅርፅና ይዘት የአባላቱን (የካድሬዎቹን) ሕልውና እንደሚወስን በግልጽ አስፍሮታል ።

በዚህ ምክንያት የተለያዩ ድርጅቶች ከላይ እንደተጠቀሰው ምንም እንኳ ለአንድ ዓላማ ነው የምንታገለው ቢሉም ለተለያዩ የአብዮቱ ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ የተለያየ ከመሆኑም ባሻገር ይኸው ልዩነት ድርጅታዊ ልዩነትንም ለማስፋት መንስዔ በመሆኑ የአብዮቱ ካድሬዎች የሚለው አጠቃላይ አነጋገር በወቅቱም ሆነ ረዘም ላለ ጊዜ ትክክለኛና የካድሬን አንድወጥ ትርጉም ለማስተላለፍ አልበቃም ።

የካድሬ አቋም እንደየድርጅቶቹ አቋም የሚወሰነውን ያህል ትርጉሙም እንዲሁ እንደየድርጅቶቹ ይዘትና ቅርጽ ተወሰነ ። በወቅቱ አነጋጋሪ የነበረውና በርካታ አብዮተኞች ምላሽ ከመስጠት የሚሸሹትና የሚሸኮኩበት ጉዳይ ከላይ እንደተጠቀሰው የጊ. ወ. አ. ደርግ ባልደረባ እንዱ ነበርና ፣ የነበሩት ድርጅቶች በዚህ ረገድ ያላቸው የሐሳብ ቅርበትና ርቀት የካድሬን ገጽታ ለመወሰን ምክንያት ሆነዋል ።

በተለይም ሌኒን አበክሮ እንደሚያስተምረው ለአባልነት የሚያበቁ መለኪያዎች በስፋትና በላሉ ቁጥር ይኸው የላላ ሁኔታ ለውኸንብረኞች ፣ ለወላዋዮችና ለአድርባዮች ሰፊ በር ይከፍታል ። ድርጅቶች በመርካከር ለመደራጀት በመምረጣቸው የተለያዩ ዝንባሌ ያላቸው አስመሳዮች መርገው ለመግባት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ፈጠረላቸው ። ስለሆነም ድርጅቶች የፊውዳል ቅሪቶችንና ለጊዜው የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ የሚፍጨረጨሩትን ጭምር በአባልነት (በካድሬነት) በማቀፋቸው የድርጅት አባልነት (ካድሬነት) ትርጉም ተራማጅነትን ብቻ ሳይሆን አድርባዮችንም የሚጨምር ሊሆን ቻለ ። ምንም እንኳ ድርጅቶቹ የኅብረተሰቡ ችግሮች በውስጣቸው የሚንፀባረቁባቸው በመሆናቸው በመጠኑም ከዚህ ሊፀዱ አይችሉም ነበር ቢባሉም ችግሮቹ ለመስፋፋት የሚችሉበት ሰፊ ሁኔታ ለማግኘታቸው ግን ራሳቸው ድርጅቶቹ ምክንያት ሆነዋል ።

እርግጥ በድርጅቶቹ ውስጥ ያሉት ሐቀኛ አብዮተኞች ይህን አዝማሚያ በተደጋጋሚ አልታገሉትም ማለት አይቻልም ። እንዲያውም በድርጅቶች ውሕደት የወዝአደሩን ፓርቲ ለማምጣት መረማመጃ ሆኖ ተመርጦ የነበረውን ስልት ተግባራዊ ለማድረግ ባወጡት የጋራ ተግባር መመሪያቸው ውስጥ የሚከተለውን አስፍረው ነበር።

> ሊማሊድነን አጠናክሮ የወዝአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር አንደኛው መንገድ ከውስጪ አድኃሪ አዝማሚያዎችን መታገል ፣ ብሎም ማስወገድ ነው ። ይህ ዓይነቱ ትግል ከፊውዳላዊ አሉባልታ የተለየ ነው ። ይህ ዓይነቱ ትግል <u>የሚበትን ሳይሆን ወደጠራ አንድነት የሚያመራ ፣ ፊውዳላዊ አሉባልታ - ሀሜታና የመሳሰሉትን ኋላቀርና ፀረ ማርክሲስት የሆኑ የሊቦርጌው ሥርዓት የአስተሳሰብ ቅሪቶችን የሚዋጋ የአሠራር ዘዴ ነው</u> ።[11] (ሥርዝ የተጨመረ) ።

ትግሉ በዚህ አመለካከት ለምሮ ባለመውጣቱ ውሉ አድሮ በድርጅቶቹ ላይ ያንዣብብ የነበረው በታኝ ሁኔታና የውጭ

Digitized by Google

ተፅዕና ወይም አድኃሪ አዝማሚያ ከው ስጥ በድርጅቶቹ ኃይል ተጠናክር ኅብ ረተሰቡ ውስጥ ለመስፋፋት ምክንያት ሊሆን ችሏል ።

ስለዚህ ይኸው የተፈጠረው ውዥንብር የካድሬን ትርጉም ውዥንብር ውስጥ ከተ ተው ። በሕዝቡ ዘንድ ሐቀኛ ካድሬዎችና የካድሬን ሳይንሳዊ ትርጉም የሚያሟሉ ቢኖሩም የድርጅቶቹ የአድኃሪነት ገጽታ ካድሬ ማለት እርስ በርሱ የሚጠላለፍና የሚጠባበቅ በዚሁ የመበላለጥ እሽቅድ ድም ውስጥ ወርተራው ሲደርስ የሚበርቅ ጊዜ ሲጨልምበት አንገቱን የሚደፋ «ታጋይ» የሚል ትርጉም አስከተለ ።

ዋናው የአብዮቱ ጥያቄ ተረስቶ እሽቅ ድድሙ በመስፋቱ ወደአንድ ማዕከላዊ አመራር ሊሰባሰቡ የሚገባቸው የኅብረተ ሰቡ ክፍሎች (ሠራተኞች ፣ ምሁራን አብዮ ተኞች ፣ ገበሬዎችም ሳይቀሩ ወዘተ. . .) እየተነጣጠሉ በየድርጅቶቹ ውስጥ እንዲ ገቡ ከመዳረጋቸውም ባሻገር በአባላቱ (ካድሬዎቹ) የታየው ውጣ ውረድ ታሪካዊ ተልዕኳቸውን በአንድነት እንዳይወጡ እን ቅፋት ፈጠረባቸው ።

ልዩነቱ በመሠረቱ መነሻው ከላይ በተጠ ቀሱት ዓበይት ጥያቄዎች ላይ ግልጽ አቋም ባለመያዝ የመጣ ቢሆንም ለኅብረተሰቡ አብዮታዊ ኃይላት በሙሉ የችግሩ ምንጭ ግልጽ ሆኖ ስለማይታይ ካድሬ መሆን ማለት የማይጨበጥ ፣ ዛሬ ውሎ ነገ ም ን እንደሚኮን የማይታወቅበት ቅርጽና ይዘት የሌለው ሥራ ሆኖ ለመገመት ችሎአል ። እንዲያውም በውጣ ውረዱ ሂደት ውስጥ እንዳንድ «ካድሬዎች» አድኃሪነታቸው እየተጋለጠ ከመድረክ በወጡ ቁጥር ከላይ የጠቀስናቸውን ዓበይት ጥያቄዎች አጣ መው በመተርጉም ለውድቀታቸው ምክ ንያት አድርገው መኮነናቸውን ስለሚቀ ጥሉ ትዝብት እያተረፉ የካድሬንም ስያ ሜና ተግባር በገምት ውስጥ ሊከቱት ችለ

ዋል ። በተጨማሪም የድርጅቶቹ ሽኩቻ ባስከተለው መዘዝ አንዳንድ ሀቀኛ አብዮ ተኞች ከተሰለፉበት ከግንባር ቀደም ትግል ለጊዜውም ቢሆን መገለላቸው ውዥንብሩን የበለጠ አባባሰው ።

ቀድሞም ካድሬ የሚለውን አባባል ድር ጅታዊና ርዕዮተ ዓለማዊ አንድነት ካለው የፖለቲካ ድርጅት ውጭ ለመረዳት መጥ ከር የተሳሳተ መሆኑ ግልጽ ነው ። እንኳ ንስ የሠራተኛው 'መደብ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ ቀርቶ ይህም ተሟልቶ ይገኝ በነበ ረበት እንደሺየትናም ባለችው ሀገር ውስጥ የካድሬ ውስብስብ ችግሮች ከድርጅት ጋር ካለው ተዛምዶ አኳያ መታየት እንዳለበት ሌ ድዋን ሲያመለክት ፣ —

. . . የፓርቲ ካድሬዎች ያለባቸውን ጠን ካራና ደካማ ጐን ለማየት በምናደርገው ጥረት ከድርጅት ጥያቄ ነጥለን ርዕዮተ ዓለማዊ ብቃታቸውን በመመርመርና ደረ ጃቸውን በመመዘን ብቻ ከታቀብን ፣ ድር ጅት በካድሬዎች ላይ ያለውን ተፅዕኖና ገፊት ለመመልከት ከተሳነን ፣ የካድሬ ዎችን ችግር በትክክል ለመመርመርና ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለማረፍ የሚያስች ለንን ዋነኛ መሠረት ስተናል ማለት ነው [12]

በማለት ገልጾታል ።

ከላይ በዚሁ የአመለካከት ፈር ጥያቄ ውን ለመተንተን እንደተሞከረው በድርጅ ታዊ ትግል ሂደት ውስጥ የታዩ እንከኖች ለካድሬዎች ስያሜና ተግባር የተዛባ ትር ጉም መፍጠር ምክንያት ሆነዋል ።

የርዕዮተዓለማዊ ብቃትና ብስለት አስተዋጽኦ

ከላይ በተጠቀሰው የድርጅት ችግር ጋር በቅርብ የተያያዘ ቢሆንም ርዕዮተ ዓለማዊ ብቃትና ብስለት በካድሬዎች ይዘትና ትር ጉም ላይ የራሱ የሆነ ልዩ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ስለሆነም በመጠኑ ከዚህ አኳያ የተንፀባረ ቀውን ሁኔታ ማሳየቱ ተገቢ ነው ።

Digitized by Google

የማንኛውም ማኅበራዊ አብዮት ዓላማ አዲስ ኅብረተሰብ መገንባት ቢሆንም አሮጌውን የማፈራረሱ ተግባር እራሱን የቻለና ቀዳሚ ምዕራፍ የሚይዝ ነው ። የኢትዮጵያም አብዮት ተቀዳሚ ትኩረት የአድኃሪውን ሥርዓት መሠረትና ላዕላይ መዋቅሮች ማፈራረሱ ላይ ስለሆነና በተለይ የማፈራረሱ ተግባር ቀደም ብለው በተወሱትና ሌሎችም ውስብስብ የፖለቲካ ችግሮች የተዋጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ መረጋጋት እስኪገኝ ድረስ አያሌ ጊዜያት አልፈዋል ። በነዚህ ጊዜያት ውስጥም የአብዮታውያን ትግል ይበልጥ ያተኮረው በማፈራረሱ ተግባር ላይ ስለሆነ የሚለኩትም በዚሁ ውስጥ በሚጫወቱት ሚና ነው ። ማለትም ይዘትና ቅርፃቸው ከዚሁ አሮጌውን ሥርዓት ከማፈራረሱ ተግባር ጋር በመነፃፀር የሚታይ ነው ።

ይህ ክንዋኔ በአብዮታውያን (በካድሬዎች) ባሕርይና ይዘት ላይ በሁለት አቅጣጫ ተፅዕኖ ይኖረዋል ። በአንድ በኩል የማፈራረሱ ተግባር ከመገንባቱ ሂደት በአንፃሩ ስለሚቀል ማንኛውንም የኅብረተሰብ ክፍል የማሳተፍ ጠባዩ የጎላ ይሆናል ። ለምሳሌ በአፍላው የአብዮት ወቅት ተግባሩ የተማሪዎችን ፣ የመምህራንን ፣ የቢሮ ሠራተኞችን የገበሬዎችን ፣ የነጋዴዎችን ወዘተ . . . ተሳትፎ የሚጋብዝ በመሆን የአሮጌውን ሥርዓት ቁንጮ ለመገርሠስ ተችሎአል ። ይህ የሕዝባዊነቱ መረጋገጫ ቢሆንም እያደር አብዮቱ እድገት እያሳየ ሲሔድ ተሳትፎውን ከአጠቃላይ ዓመፅነት ወደተቀነባበረ ትግል ስለሚለውጠው ብሎም በአብዮቱ ውስጥ ምላሽ ሊያገኙ የሚገባቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች የመደብ ባሕርይ ቁልጭ እያለ ስለሚመጣ የተወሰኑ ክፍሎችን ቀጥተኛ አመራር ይጠይቃል ።

በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ ከተወሰነ ደረጃ በኋላ በተለይ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ በተደረገው ትግል ከላይ በተጠቀሰው መዋቅራዊ ችግርና ርዕዮተ ዓለማዊ ልዩነት ቢኖርም የካድሬዎች ሚና ሰፋ ብሎ የሚታይበት ሁኔታ ተፈጥሮአል። የፊውዳሉንና በአጠቃላይ የአሮጌውን ሥርዓት የኢኮኖሚ መሠረት በመጣልና አዲስ የንብረት ግንኙነት ለማዋቀር በተካሔደው ትግል ካድሬዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። አዲሱን ለማዋለድ አሮጌውን ከታሪክ ትቢያ ለመቀላቀል ባደረጉት ትግል (ትግሉ የመደብ ትግል በመሆኑ ጉራ መለየቱ አይቀርምና) የካድሬዎች ሚናና ተግባር የተወሰኑ መደቦችንና የተቀጥላዎቻቸውን ጥላቻ አትርፏል ። ስለሆነም እነዚህ መደቦች ምንም እንኳ ህልውናቸው እየመነመነ ቢሔድም በኅብረተሰቡ ውስጥ ለዘመናት በቀረጹት ሥነ ልቡና አማካይነት በአንፃራዊ ሁኔታም በአዲሱ ኅብረተሰብ ውስጥም ተሸጋግሮ ሊንፀባረቅ በሚችለው አድኃሪ ማኅበራዊ ሥነ ልቡና ጭምር በተጠቀሱት ክፍሎች (ካድሬዎች) ላይ ድምርና ድፍን ውግዘት እንዲከተል አድርገዋል ። በመሆኑም ካድሬ የሚለው ቃል (በሥርዓቱ አብዮታዊ ለውጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ በሚችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሕሊና ጭምር) አልፎ አልፎ ጥርጣሬ ሲፈጥር በመቻሉ ለትርጉም መዛባት አንዱ አስተዋጽኦ ያደረገ ጉዳይ ነው ። ይህ በመደቦች ሹምሽር ወቅት የሚጠበቅና ከመደብ ጠላቶች የሚሠነዘር ነው ።

በሌላ በኩል አሮጌውን ሥርዓት የማፈራረሱ ተግባር ከያንዳንዱ የሚጠይቀው ችሎታና ብቃት በግንባታው ወቅት ከሚፈለገው ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ በመሆኑ በኅብረተሰቡ ውስጥ ብቻ ሳይሆን የካድሬ ስያሜ ባለቤት በሆኑት ክፍሎች ሕሊና ውስጥ ጭምር የተወሰነ የአመለካከት ስሕተት ፈጥሯል ። አብዮት ሊፈታቸው የሚገቡ ጥያቄዎች በየእድገቱ ደረጃ እየተወሳሰቡ ይመጣሉ ። ለውስብስብ የእድገት ሁኔታዎች ምላሽ መስጠት ደግሞ የማፈ

Digitized by Google

ራረሱን ተግባር ያህል ቀላል ሳይሆን ከፍ
ተኛ ጥረትና ግስተዋል ይጠይቃል ። በተ
ወሰነ ደረጃና ጊዜ አጠቃላይ ወገናዊነትን፣
እምነትን ፣ ፍላጎትንና ስሜትን ብቻ የሚሹ
ጉዳዮች ሲኖሩ በሌላ ደረጃና ወቅት ደግሞ
አርቆ አስተዋይነትን ፣ ብስለትን ፣ ሳይን
ሳዊ አመለካከትን የሚሹ ያጋጥማሉ ።
«. . . የመደብ አቋም የስሜትና የምኞት
ብቻ ሳይሆን የተወሰነ ዕውቀት መላበስን
ጭምር የሚጠይቅ ነው» [13] በማለት ሌ
ድዋን እንዳስቀመጠው በማፈራረስ ሂደት
ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ አመለካከት እያ
ደገ የሚመጣውን የአብዮት ጥያቄ ለመፍ
ታት የሚያስችል መሣሪያ አይሆንም ።

ሌኒን ስለፖለቲካ ትምህርት ከፍሎች
ዓላማና የአመራር እድገት ሲናገር ፦

> በአንድ ወቅተ መግለጫዎች ፣ ሀተታዎች፣
> ሰነዶችና ድንጋጌዎች አስፈልገው ነበ
> ር ። በዚህ ረገድ ብዙዎቹን አይተናል ።
> በአንድ ወቀትም እንደትና ምን ለመገ
> ንባተ እንደፈለግን - እስካሁን ያልታዩ
> ምን አዲስ ጉዳዮችን ለማግኘት እንደ
> ምንጥር ለሕዝቡ ለማሳየት ጠቀመው
> ናል ። ነገር ግን ለመገንባት የምንፈልገ
> ውን ነገር ለሕዝቡ በማሳየት ለመቀ
> ጠል እንችላለን ? አንችልም ? ... ታላላ
> ቅ የፖለቲካ ጉዳዮችን እያጉላን የምናቀ
> ርብበት አስገዳጅ ሁኔታ ጊዜው አልፎ
> አል ። ዛሬ ጉዳዮቹ በተግባር መገለጽ
> አለባቸው [14]

እንዳለው ሁሉ ችግሮች ከአጠቃላይ የማሳ
ወቅ ይዘት ወደተግባር የመገለጽ ሂደት
ተሸጋግረዋል ። ለዚህም ተመጣጣኝ ባህል
ማዳበር ያስፈልጋል ።

እርግጥ ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ በውጭ
በኋላም በየካቲት '66' ፖለቲካ ት/ቤት የሚ
ሰጠው የርዕዮተ ዓለም ትምህርት ይህንኑ
የእድገት ችግር ለመቋቋም ከፍተኛ አስተ
ዋጽኦ ቢያደርግም የአብዮቱ እድገት ችግ
ሮች ውስብስብነት ተከታታይ ብቃትን
የሚጠይቁ ናቸው ። ተመጣጣኝ ምላሽ ካል
ተገኘ ደግሞ በአሠራር ላይ ችግር እንዲ
ታይ ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር የባሕ
ርይም ችግር መፈጠሩ አይቀርም ።

ንቃት ዝቅተኛ ከሆነ በማሳመን ከመሥ
ራት ይልቅ ማስገደድ የአሠራር ምርጫ
ይሆናል ። ለመማር ከመዘጋጀት ይልቅ ሁሉን
አዋቂ ሆኖ መቅረብ አመዛኙ ባሕርይ ይሆ
ናል ። ይህ እንደአዝማሚያነቱ አደገኛ የመ
ሆኑ ጉዳይ በተወሰነ የሥራ መስክ የተሠ
ማሩትን ከፍሎች (ካድሬዎች) ምንነት በማ
ንፀባረቅ ከፍተኛ ጉታችና አሳሳች ተፅዕኖ
ያደርጋል ። እራስን የማረም ሳይሆን እራ
ስን የመከላከል ባሕርይ ይፈጠራል ። ከዚህ
በመነጨ ሁኔታም ከማስተማር ይልቅ የማ
ዘዝ ዝንባሌ ብቻ ያድግና የስያሜው ባለ
ቤት በሆኑት ካድሬዎች ላይ ጥቅልና የተ
ዛባ አመለካከት ይፈጥራል ።

ከዚህ ጋር ተያይዞም ይህንኑ አንቂና አደ
ራጅ ክፍል በታኞች ፣ ጥቅም ፈላጊዎችና
ከፋፋዮች ሠርገው ሲቀላቀሉበት ጥቅል
ተግባሩን የሚያጉድፍ ትርጉም እንዲይዝ
ያደርገዋል ። ይህም በተወሰነ እድገት ተን
ፀባርቆ ስያሜና ተግባርን ጎጂ ሁኔታ ላይ
ከመጣሉም ባሻገር የተሳሳተ ትርጉም እን
ዲይዝም በ3ኛ ደረጃ አስተዋጽኦ ያደረገ
ጉዳይ ነበር ። ይህን ሀቅ ለመግለጽ ነው
የኢሠፓአኮን መቋቋም ለግብሰር ጓድ መን
ግሥቱ ኃይለ ማርያም ታኅሣሥ 7 ቀን 1972
ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ባሰሙት ንግ
ግር ፦

> እስከአሁን ባለፍንበት የአብዮታችን
> ሂደት ውስጥ ሰፊው ሕዝብ ካድሬነትን
> በአመዛኙ በበጉነተ የሚያወሳው ይሁን
> እንጂ በአብዮትና በካድሬስም የአስነዋሪ
> ግብርቸ ትዝታም አለው ። ሐቀኛ አብዮ
> ተኞችና ካድሬዎች ምንጊዜም ለሰፊው
> ሕዝብ ደኅንነተ በግንባር ቀደምተነትና
> በመስዋዕትነት ሲጋፈጡ ፣ ... የስም
> አብዮተኞችና ካድሬዎች የዚህን ተቃራኒ
> ሲፈጽሙ ቆይተዋል ። ... በትምክህ
> ትና በትዕቢት የአብዮተኝነትን ሥነ ምግ
> ባር በመጣስ ... በአዛዥነት በመቀም
> ጥላቻን ከሰፊው ሕዝብ አትርፈዋል [15]

Digitized by Google

ያሉት ።

ይህ በአብዮት ሂደት ውስጥ የመጀመሪያውና በታሪክ ውስጥ ያልታየ ጉዳይ አልነበረም ። አንድ ወጥ የሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ድርጅት ሥልጣን በያዘበትም ሁኔታ በሶቭዬት ኅብረትም የታየ ክስተት ነው ። ሌኒን «የሶቭዬት ሥልጣን አጣዳፊ ተግባሮች» በተሰኘው ጽሑፉ ይህንኑ ሁኔታ ሲገልጽ «... ጀብደኞችና ቀጣፊዎች ... ጉረኞችና ለፍላፊዎች ፣ ... ያልታዩበት ጥልቀት ያለውና ኃያል የሕዝብ ንቅናቄ በታሪክ ውስጥ ጭራሽ ታይቶ አይታወቅም» [16] በማለት ጽፏል ።

በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥም ይኸው ሁኔታ የካድሬ ባሕርይ ተደርጎ በመወሰድ አልፎ አልፎ የተሳሳተ አመለካከት ፈጥሮ ቆይቶአል ። ሲጠቃለል በየጊዜው የሚከሰቱ የእድገት ጥያቄዎች በተመጣጣኝ የሥርዓቱን ግንባር ቀደም አራማጆች ርዕዮተ ዓለማዊ ብስለትና የሥራ ጥራት ይጠይቃል ማለት ነው ። ይህ ካልሆነ ወይም በአፋጣኝ የሚሆንበት ሁኔታ ካልተመቻቸ ኅብረተሰቡ ለሥርዓቱ አራማጆች (ካድሬዎች) የሚሰጠው ትርጉም የተዛባ ይሆናል ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

ዛሬ ያለንበት ሁኔታ ከላይ ያነሳናቸው አከራካሪ የአብዮቱ ጥያቄዎች የተፈቱበት ወቅት ነው ። በመሆኑም ከነሱ ይመነጭ የነበረው የተዛባ አመለካከት ተወግዷል። ቅድመ ሁኔታው በኢሠፓአኮ ከዚያም በኢሠፓ ምሥረታ ለካድሬዎች ርዕዮተ ዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነት መሠረት ተጥሏል ። ምንም እንኳ የተለያዩ ጉታችና አፍራሽ አዝማሚያዎች ሁሉ በኢሠፓ ምሥረታ ከመቅጽበት ጨርሶ ሊወገዱ ይችላሉ ባይባልም ምክንያቶቻቸው ግን አከራካሪ የፖለቲካ ጥያቄዎች ሊሆኑ አይችሉም ።

ማንኛውንም አብዮታዊ ፓርቲ ከጅምሩ እስከ ጉልምስናው የሚያጋጥመው የብቃት ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ሲሆን በኢሠፓም ውስጥ ይህ ጥያቄ የማይታለፍ ጉዳይ ነው ። የብቃት ጥያቄን ለመመለስ ኢሠፓ የካድሬዎችን የርዕዮተ ዓለም ጥንካሬ ከፍ ማድረግና ለሥራቸውም አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር አቅዷል ። በኢሠፓ ፕሮግራም እንደተጠቀሰው ለፓርቲው አባላት ጥንካሬ መሠረቱ የመደብ ምንጫቸው ቢሆንም ለአዲስ ድርጅታዊ ሕይወትና ኃላፊነት እንዲበቁ የርዕዮተ ዓለምና የሙያ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ይኸው በየደረጃው የሚካሔድ ይሆናል ። ከዚህም ጋር ፓርቲው በተገቢው የምልመላ ፣ የግምገማ ፣ የምደባ ፣ የእድገትና የዝውውር ፖሊሲ አማካይነት ካድሬዎች የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል ። [17]

የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የፓርቲው የካድሬ ፖሊሲ እንዲነደፍ ውሳኔ አስተላልፏል ። በዚሁ ስብሰባ ላይ የቀረበው የድርጅት ዘርፍ ሪፖርት «የኢሠፓ የካድሬ ፖሊሲ የካድሬዎችን አያያዝና አጠቃቀም ገልጽ» የሚያደርግ ሲሆን ፣ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎች የሚወጡ መሆኑን ይዘረዝራል ። በሪፖርቱ እንደተጠቀሰው ፦—

> መመሪያዎቹ የካድሬን ጉዳይ በሚመለከት ሚከናወኑ ሥራዎች በቂ ገንዛቢ በማስገኘት አባላትን በችሎታቸውና በዝንባሌያቸው ለማሰማራትና የሰው ኃይልን በሚገባ በመጠቀም ፓርቲው ባሉት ጥቂት ካድሬዎች ከፍተኛ ውጤት እንዲያገኝ ከማስቻሉም ሌላ የዕውቀትና የልምድ ሽግግርን ለማረጋገጥ ፣ ካድሬዎችን ኮትኩቶ ለከፍተኛ ኃላፊነት በማብቃት የአመራር ተከታታይነትን ለማግኘት እርግጠኛ የምንሆንበት የአሠራር ዘዴ ያስገኛሉ ።ይህም በአንድ በኩል የፓርቲውን የመሪነት ሚና የሚረዳ ሲሆን በሌላ በኩል የካድሬዎችን ሕይወት የሚመለከቱ ጉዳዮችን በጥንቃቄ ለመያዝና ካድሬዎችም ሙሉ እምነታቸውን በፓርቲው ላይ ጥለው ከተሰጣቸው ኃላፊነት ጋር በተያያዙ ሥራዎች ላይ እንዲያተኩሩና የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ የሚያግዛቸውን የአሠራር ስልት ለመዘርጋት ያስችሉናል ። [18]

Digitized by Google

ስለዚህ ለካድሬ ትርጉም መስጠት እንዱ ምክንያት ሆኖ የቀረበው የርዕዮተዓለማዊ ብስለትና ብቃት ጉዳይ በተከታታይነት በፓርቲው ሕይወት ውስጥም ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ ነው። በሽግግር ስም በድምሩ አብሮ መጓዝ አይኖርም። የዓላማና የተግባር አንድነትን አምኖ መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ በተጨባጭ ተግባር ለመግለጽ የራስን ብቃትና ግንዛቤ ማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው። ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ባቀረቡት ሪፖርት እንደገለጹት፦—

> በፓርቲያችን መዋቅር ውስጥ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ እያንዳንዱ አባል በአመለካከቱ፣ በሥራና በማኅበራዊ ኑሮው ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ልዕልናና በኢትዮጵያችን ለሶሻሊዝም መገንባት በመቆም የድርጅቱን አቋም በተግባር መግለጽ ይኖርበታል። ለዚህም ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ማጥናትና፣ ማስጠናት፣ የተገለጸ የዕለት ተዕለት ሕይወት መመሪያ ማድረግ ግዴታው ነው። [19]

ከሁሉ በላይ የኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም የራስን ሕሊና ጭምር ነፃ የሚያደርግ እንደ መሆኑ መጠን፣ ካድሬዎች የካድሬነትን ትክክለኛ ትርጉም በኅብረተሰቡ ው ስጥ ለማስረጽ ብቃታቸውን እያሳደጉና በተግባር እያስመሰከሩ መሔድ ይጠበቅባቸዋል። በማንኛውም የፓርቲ ሥራ ላይ ስለሚሠማሩ ኮሚኒስት ካድሬዎች ሌኒን ሲናገር፣ «በተግባር ፊንታ ወሬን የሚያስቀድሙትን ሊናቸው ጋር የማይጣጣም አንዳችም ቃል የማይተነፍሱ» [20] መሆን አለባቸው ብለዋል። ይህ በፓርቲው ሕይወት ውስጥ ወሳኝ ሲሆን ስለሚሆንም ሆነ ተግባሩ ለውግብር በተጋለጠበት የአብዮት ታሪክ ውስጥ ላለፉ አብዮተኞችና ወደፊትም ይህንኑ ጉዞ ለሚያጠናክሩ ዕልፍ አዕላፍ የአብዮት ካድሬዎች የእንቅስቃሴያቸው መሠረታዊ ጉዳይ መሆን ይኖርበታል።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. Great Soviet Encyclopedia Vol. 11, (Moscow: 1973), p. 428.
2. ሌ ድዋን፣ ምርጥ ጽሑፎች (ሃኖይ 1977) ገጽ 428
3. ሌኒን፣ ስብስብ ሥራዎች ቅጽ 8 (ሞስኮ፣ 1974)፣ ገጽ 92
4. ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ፣ የጊ. ወ. አ. ደርግ ሊቀ መንበርና የአብዮታዊው ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ በኢሠፓአኮ አንደኛ ጉባኤ ላይ ያቀረቡት ሪፖርት (አዲስ አበባ ሰኔ 9 ቀን 1972) ገጽ 23
5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም፣ ክፍል 3፣ ገጽ 26
6. «የኅብረት ድምፅ» ቅጽ 2 ቁጥር 5 የካቲት 1971) ገጽ 15
7. ከላይ የተጠቀሰው «የኅብረት ድምፅ» ገጽ 15
8. ከላይ የተጠቀሰው የኢሠፓአኮ አንደኛ ጉባኤ ሪፖርት፣ ገጽ 45

Digitized by Google

9. ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች (ሞስኮ 1974) ቅጽ 6 ፣ ገጽ 500
10. ሌ ድዋን ፣ ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 431
11. የኢትዮጵያ አብዮትና ኢማሌድኅ ለኢማሌድኅ ካድሬዎች የሥራ መመሪያ (አዲስ አበባ ፣ ሰኔ 1970) ያልታተመ ፣ ገጽ 6
12 ሌ ድዋን ፣ ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 432
13. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 452
14. ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች (ሞስኮ ፣19 ቅጽ 33 ፣ ገጽ 73
15. ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ ፣ የጊ.ወ.አ. ደርግ ሊቀ መንበርና የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ታኅሣሥ 7 ቀን 72 ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉት ንግግር (በማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር የተዘጋጀ አ. አ. 1972) ገጽ 34
16. ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች (ሞስኮ 1974) ቅጽ 27 ፣ ገጽ 262
17. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ፕሮግራም 1976 አዲስ አበባ፣ገጽ 157 - 158።
18. ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓ ማ.ኮ. ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ያቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ፣መጋቢት 1977 አዲስ አበባ፣ገጽ 38(ያልታተመ)
19. ከላይ የተጠቀሰው ።
20. ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች ቅጽ 33 ገጽ 439 ፣ በቪ· ሻይኮቫ ፣ «የሰፊው ሕዝብ ርዕዮተ ዓለማዊ ትምህርት» በተሰኘው ጽሑፍ ላይ እንደተጠቀሰው ፣ ገጽ 24

Digitized by Google

የምግባር ግንዛቤ በግሌ አመለካከት

ኢሳይያስ ደምሴ

ሰው እንደ የኅብረተሰቡ የእድገት ደረ
ጃና የምርት ግንኙነት ባሕርይ ቢለያይም
በኑሮው የርስ በርስ ግንኙነት ያለው ፣
በተዘዋዋሪም ይሁን በቀጥታ አንዱ በአ
ንዱ ላይ ተደጋግፎ የሚኖር ነው ። አንድ
ሰው በሚያገኛቸው ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራ
ዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ላይ በተዘዋዋሪም
ይሁን በቀጥታ የሌላው ሰው ተሳትፎ አለ
በት። ሰው በሕይወት ለመኖር ምግብ ፣ ልብ
ስና መጠለያ ያስፈልጉታል ። ይሁን እንጂ
እነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን የሚያሟሉ
ቁሳዊ ነገሮች የሚገኙት በሌሎችም የሥራ
ኃይል ቅንጅት እንጂ በራሱ ብቻ አይደ
ለም ። ለምሳሌ ፣ አንድ አርሶ አደር ለምግቡ
ከሚያስፈልጉት ቁሳቁሶች ጤፍን፣ አተርንና
በርበሬን ፣ ጨውን ዘይቱን ፣ ቅመማ ቅመ
ሙን ፣ ልብሱን ፣ ወዘተ . . . የሚያገኘው
በራሱ ኃይል ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የሥራ
ኃይል አማካይነት ነው ። በተጨማሪም ያመ
ረተውን የሚፈጨው ፣ አተርን የሚከካውና
በርበሬውን ወቅጦና ቀምሞ የሚያቀርበ
ውም አብዛኛውን ጊዜ ሌላ መሆኑ በተግ
ባር የሚታይ ነው ። ይህ የሚያሳየን በኅ
ብረተሰቡ ውስጥ በማንኛውም መልክ የሰ
ዎችን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ግንኙነት ፣
የኑሮአቸውን ተደጋጋፊነት ነው ። ይህ መደ
ጋገፍ ከሥራ ክፍፍል ሂደትና መዳበር ጋር
የበለጠ ውስብስብና የሰፋ ይሆናል ።

በአጠቃላይ ሰው ብቸኛ አይደለም። ህል
ውናው የማኅበራዊ ግንኙነቶች ው ጤ ት
ነው ። የሚኖረውም በእነዚሁ ግንኙነቶች
ውስጥ ነው። በመሆኑም አንድ ግለሰብ ከማ
ኅበራዊ ግንኙነት ውጭ የሆነ ግለሰባዊ
ህልውና ወይም እንቅስቃሴ የለውም ማለት
ይቻላል ። ሰው ያለ ሰው የርስ በርስ ግንኙ
ነት መኖር አይችልም ። የአንዱ ህልውና
ከሌሎች ጋር ባለው የርስ በርስ ግንኙነት
ይኖራል እንጂ ብቻውን ከኅብረተሰቡ
ውጭ ህልውና ኖሮት የሚንቀሳቀስ አይ
ደለም ።

Digitized by Google

ሰው በማኅበራዊ ግንኙነቱ ውስጥ የሚፈጽመው ድርጊትና የሚያካሒደው እንቅስቃሴ ካለበት የኅብረተሰብ ጥቅም (ፍላጎት) ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የኅብረተሰቡ ግዴታዎች አሉ ። ከእነዚህም ግዴታዎች መካከል የድርጊቶቹን የሚፈልገውን አቅጣጫ መያዝ ፣ መልካም ወይም ተቀባይነት ያለው ፣ የማይፈለግ አቅጣጫ መያዝን መጥፎ ወይም ተቀባይነት የሌለው በሚሉና በመሳሰሉት መለኪያዎች አማካይነት ኅብረተሰቡ የግለሰቡን ባሕሪ መቆጣጠሩን የሚያንፀባርቁ የአስተሳሰብ ዓይነቶች ምግባራዊ አስተሳሰቦች (Moral views) ይባላሉ ። በሌላ አነጋገር «ከአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ጥሩ ወይም መጥፎ ፣ ተገቢ ወይም ተገቢ ያልሆነ ፣ ቅን ወይም ቅን ያልሆነ በማለት የሰዎችን ድርጊቶች የሚመዝነው አስተሳሰብ ምግባራዊ አስተሳሰብ በመባል ይታወቃል ።» [1] የምግባራዊ አስተሳሰብ አጠቃላይ ቅንብርም ምግባራዊ ግዕዝ (ልማድ Moral Norm) ይባላል ።

በአንድ ኅብረተሰብ ተቀባይነትና ጠቃሚነት ወይም ፋይዳ ባለው ምግባራዊ አስተሳሰብ ላይ ተመሥርቶ የግለሰብን ባሕሪ ፣ ድርጊት ወይም አንድን ማኅበራዊ እውነታ መቀበል ወይም አለመቀበልን በሚመለከት በሰዎች የሚሰጠው አስተያየት ምግባራዊ አስተያየት (Moral Judgement) ይባላል ። [2] በግለሰብ ባሕሪ ወይም ድርጊት ላይ ምግባራዊ አስተያየት መስጠት ድርጊቱ የሚያስከትለውን ማኅበራዊ ፣ እንዲሁም ምግባራዊ ውጤቶችን በማመዛዘን ላይ የተመሠረተ ይሆናል ። [3] ምግባራዊ አስተያየት ከምግባራዊ ግዕዝ ይለያል ። ምግባራዊ ግዕዝ «ሰዎች በአንድ ዓይነት ምግባራዊ አስፈላጊ በሚባል ጉዳይ መሠረት አድራጎታቸውን እንዲፈጽሙ የሚያስገድድ» ሲሆን ፣ ምግባራዊ አስተያየት ግን «ምግባራዊ አስፈላጊ ጉዳይ መከበር ወይም አለመከበሩን የሚያሳውቅ» ነው ። [4] ምግባራዊ አስተሳሰቦች ፣ ግዕዝንና አስተያየቶች በአጠቃላይ ምግባር (Morality) ይባላሉ ። በሰፊ ትርጉሙ ምግባር «የግለሰብን ባሕሪ መቆጣጠርን ፣ የግለሰቦችን ድርጊት ከሌሎች ሰዎች ወይም ከአንድ ማኅበረሰብ ማስተባበርን ፣ ሰዎችን ማስተማርን ፣ የሚፈለጉ ምግባራዊ ባሕርያትንና ግንኙነቶች መፍጠርንና ማጠናከርን የሚመለከቱ የአስተሳሰብና የሐሳብ ፣ የግዕዝና የአስተያየቶች ቅንብር ነው ።» [5]

ምግባር ከማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ቅርጾች አንዱ የሆነ ከሰዎች ቁሳዊ ማኅበራዊ ግንኙነት የሚመነጭ ፣ መልሶም ግለሰቦች በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ የሚኖራቸውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ነው ። የግለሰብ ወይም የኅብረተሰብ ቡድን እንቅስቃሴ ከጠቅላላው ማኅበረሰብ ጥቅም ጋር ግጭት እንዳይኖረው ማኅበራዊ መግቻና መመዘኛ በመሆን ያገለግላል ።

ምግባር በቅድመ መደብ ፣

ምግባር በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት የተከሰተ ፣ በእድገት ሂደቱም ቀስ በቀስ የመደብ ባሕርይ የያዘ [6] የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ቅርጽ ነው ። ስለሆነም ምግባር ከመደብ ኅብረተሰብ ጋር የተከሰተ ሳይሆን በቅድመ መደብ ኅብረተሰብ የነበረ ፣ አሁንም ያለና የሚኖር ነው ።

በቅድመ መደብ ኅብረተሰብ ምግባር የሰዎች ሁሉ የጋራ መንፈሳዊ ፣ ቁሳዊ ጥቅም ማንፀባረቂያና እንደ ማስከበሪያም ሆና በማገልገል እርስ በርስ መተሳሰብን ፣ በማኅበራዊ ህላዌ ውስጥም የበኩሉን የሥራ ድርሻ መወጣትን ፣ መከባበርን ፣ ሰብአዊ ፍቅር መኖርንና በወንዶችና በሴቶች መካከል የነበረውን የሥራ ክፍፍል አውቆ ኃላፊነትን መወጣትን የሚመለከት የውዴታ ግዴታ ግዕዝ ነበር ። በዚህ ወቅት በሰዎች መካከል መደባዊ ቅራኔ ባለመኖሩ ተፃራሪ

Digitized by Google

ምግባሮችም አይኖበሩም ። በዝባዥና ተበዝባዥ በሌለበት ሥርዓት የኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ ቡድኖች የሚያካሒዱት እንቅስቃሴ የጋራ ጥቅምን (ማኅበራዊ ጠቀሜታን) የሚያራምዱ እንጂ የሚፃረሩ አይደሉም ። ይሁን እንጂ የጋራ ጥቅምን ወይም ማኅበራዊ ጠቀሜታን በትክክል ባለመረዳት ወይም በተግባር አፈጻጸም ላይ ግለሰቦች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ላይወጡ ይችላሉ ። ይህም ሁኔታ ኅብረተሰቡ ከሚመራበት ምግባር አኳያ ሲታይ የማኅበራዊ ጥቅምን ፈር ስለሚያስለቅቀው ፣ የግለሰቡን ማኅበራዊ ቦታም ስለሚያሳንሰውና ጥቅሙንም ስለሚጎዳ ፣ ግለሰቡ ተመልሶ በምግባራዊ ግዕዛት ሥር እንዲውል ማኅበራዊ አስተያየት ወይም ተግሣጽ ይሠነዘርበታል ። ግለሰቡም ከግንዛቤ ጉድለት እንጂ ከመደብ ቅራኔ የመነጨ መሠረታዊ ስሕተት ወይም ድርጊት ባለመፈጸሙ ምግባራዊ አቋሙን በኅብረተሰቡ ፍላጎት አኳያ በቀላሉ ያስተካክላል ። ቅድመ መደብ ኅብረተሰብ በዘመኑ የኖሩትን ምግባራዊ ግዕዛን ማኅበራዊ ጥቅሙንና ፍላጎቱን በእያንዳንዱ ግለሰብ ዘንድ አስከብረውባቸዋል ፤ ግለሰቦችም በኅብረተሰቡ አባልነታቸው ማኅበራዊ ድርሻቸውን በትክክል እንዲወጡ የውዴታ አስገዳጅም ሆነው አእምሮአዊና አካላዊ እንቅስቃሴያቸውን መቆጣጠሪያ አድርገዋቸዋል ።

የምግባር መደባዊ ይዘት

የምግባር ግዕዛትና ፋይዳዎች (moral norms and values) ሊለወጡ ወይም ሊዳብሩ ይችላሉ ። ይህም የሚሆነው ከምርት ኃይሎች እድገት ፣ ከመደብ ሽረት ፣ አሊያም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት አኳያ ነው ። በመደብ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ምግባር መደባዊ ጠባይ ይይዛል ። የመደብ ሹም ሽር በሚካሔድበት ጊዜም ታዳጊው መደብ የራሱ የሆነ ምግባር ይኖረዋል፡የሰዎችንም እንቅስቃሴና አዝማሚያ (ትክክለኛነቱን ወይም ተፃራሪነቱን) የሚመለከተው በመደቡ ማኅበራዊ ጥቅም አንፃርና በራሱ ምግባራዊ ግዕዛት መለኪያነት ይሆናል ። በአንድ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ኅብረተሰቡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት እየዳበረ በሔደ ቁጥር የማኅበራዊ ግንዛቤ አድማሱ እየሰፋ የመሔዱን ያህል የምግባር እድገቱም የዚያኑ ያህል ሊጨምር ይችላል።

ሰዎች የአንድ ኅብረተሰብ አባል ሆነው ሲኖሩ የማኅበራዊው ግንኙነቶች ከሚኖራቸው ቅርጽና ይዘት የሚያንፀባርቁ የባሕርይ መመሪያዎችንና የማኅበራዊ ፋይዳዎችን (social values) ይፈጥራሉ። እነዚህ መመሪያዎች የተዋቀሩበት ማኅበራዊ ግንኙነት ሲፈርስ አብረው ይለወጣሉ፤ወይም በአዳዲስ ፋይዳዎች ይተካሉ ። በዚህም ረገድ ምግባራዊ ግዕዛትም ከማኅበራዊ ግንኙነት ለውጥ ወይም መፍረስ ጋር በተጓዳኝነት ከእድገቱ አኳያ ይለወጣሉ ። ለምሳሌ ፣ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ምግባር አንድ ዓይነት ግዕዛት ነበሩት ፤ ሆኖም ኅብረተሰብ በመደብ ሲከፋፈል ምግባራዊ ግዕዛትም የመደብ ባሕርይን ይዘው ተለውጠዋል ፤ አድገዋልም ።[7]

ይህ ለውጥ የምግባር ግዕዛት መሠረታቸው ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት መሆኑን ያሳያል ። የምግባራዊ ግዕዛት መሠረታዊ ዓላማም በአንድ ሥርዓት የምርት ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ ከመደቦቹ ፍላጎት አኳያ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቱን ማጠናከር ወይም መፃረር ነው ። እነዚህ ግዕዛት በአንድ ሥርዓት ውስጥ ካሉት መደቦች መካከል አንዱ በግንኙነቱ ውስጥ ያሉትን ተፃራሪ ጥቅሞች ሲዋጋባቸው ፣ ሌላው ደግሞ ያሉትን ጥቅሞች በማስከበርና ይበልጥም አጥቂ እየሆኑ እንዲሔዱ በማድረግ ይጠቀምባቸዋል

የመደብ ቅራኔዎች አድገው የመደብ ሹም ሽር ሲደረግ የምግባር ፋይዳዎችም እንደዚሁ ከቆሙለት መደብ ጋር አብረው ይሻራሉ ። በተለይም በአንድ ሥርዓት የኤኮኖሚ የበላይነትን የያዘው መደብ በማስ

Digitized by Google

ከበሪያና በአስገዳጅነት ይጠቀምበት የነበረው ላዕላይ መዋቅሩ ጨርሶ ስለሚፈራርስ የዚሁ ዘርፍ የነበረውና ለመደብ ጥቅም ማስከበሪያ የሚያገለግለ ምግባርም አብወር ይወገዳል ።

ምግባር በሰዎች ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ የተፈጠረ ነው። በአንድ ወቅት የሚኖሩ መደቦችም እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ምግባር አላቸው ። የገዥው መደብ ምግባር በተገዥው መደብ ምግባር ላይ ተፅዕኖ አድርጓል ፣ያደርጋልም ። የገዥው መደብ ምግባር የመደቡን ጥቅምና የበላይነት ሲያጓላ በተቃራኒው በገዥው መደብ የበላይነት አንፃር የሰፊውን ሕዝብ ጭቆና ትክክለኛ አድርጎ ይቀበላል ። [8] ተጨቋኙ መደብ ጥቅሙን ለማስከበር ሲል ለሚወስደው የተቃውሞ እርምጃ በመደቡ ምግባር አኳያ ፣ ትክክለኛ ግምት ቢሰጠውም በገዥው መደብ ምግባር አንፃር ደግሞ ትክክል ሆና ባለመታየቱ ተፅዕኖ ያደርግበታል ። ለምሳሌ ፣ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ በሚያካሒዱበት ወቅት ለካፒታሊስት የተገዙ አንዳንድ ሠራተኞች ገብተው እንዳይሠሩ መከላከል በወዝአደሩ ምግባር ረገድ አግባብ ሆና ሲገኝ በገዥው መደብ ምግባር አኳያ ግን ተቀባይነት የሌለውና ውጉዝ ነው ።

በኢኮኖሚ ግንኙነት የበላይነት የሚይዘው መደብ ምግባር ምንጊዜም ቢሆን የተጨቋኙን መደብ ወይም መደቦች ምግባር ይጫናል ። ለተግባራዊነታቸውም ዕንቅፋት ይሆናል ። የእያንዳንዱ መደብ የምግባር ግዕዛት በኢኮኖሚ ግንኙነቱ ውስጥ የቆመለትን መደብ ጥቅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለማስከበር የሚጫወቱት ሚና አላቸው ። ምክንያቱም « ሰዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሥነ ምግባር ሐሳቦችን የሚያመነጩት የመደብ ይዞታቸው ከተመሠረተባቸው ተግባራዊ ግንኙነቶች ማለትም ምርትና ልውውጥን ከሚያካሒዱባቸው የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ነው » [9] በግንኙነቶች ውስጥ መደቦች የሚኖራቸውን ጥቅም የማስከበር አስገዳጅነት ለመደቡ ተስማሚ ምግባራዊ ግዕዛትን ያመነጫል ። በእነዚህ ምግባራዊ ግዕዛትም ፣ መጥፎና ጥሩ ፣ ትክክልና ትክክል ያልሆኑ በማለት ከመደባዊ ጥቅማቸው አንፃር የግለሰቦችንም ሆነ የቡድኖችን እንቅስቃሴ ይገመግማሉ ። ለምሳሌ በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበር ባሪያው ጥር ግር ያመረተውን የምርት ውጤት እንዳለ ለጌታው ማስረከቡ ፣ የባሪያው እንደዕቃ መሸጥና መለወጥ የምርት ግንኙነት ባሕርይ ነው ። ይሁንና ይህ በባሪያው ምግባር አኳያ ሲታይ ኢሰብአዊና ትክክል ያልሆነ ድርጊት ሲሆን ፣ የባሪያ አሳዳሪው ምግባር ግን ተገቢና ትክክል አድርጎ ከመቀበሉም በላይ የራሱ መደብ የመብት ጥያቄ አድርጎ ይመለከተዋል ። ምክንያቱም ባሪያ ለባሪያ ጌታው እንደገል ንብረቱ ሆና በመቆጠር እንዲሸጠውና እንዲለውጠው የኢኮኖሚ ግንኙነቱ ይፈቅድለታል ።

ተበዝባዡ መደብ ጭቆና እየበዛበትና ኑሮው ይበልጥ እየቆረቆዘ በሔደ ቁጥር ብዝበዛንና ጭቆናን በመቃወም የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ትክክለኛነት የሚያሳዩ የተለያዩ የምግባር ግዕዛት ከዚህ እንቅስቃሴ ባሕርይ ይመነጫሉ ። ለምሳሌ በአንድ የገበሬዎች አካባቢ የእህል እጥረት ተፈጥር ረሃብ ቢስፋፋና ደሀ ገበሬዎች የሚበሉት አጥተው እየተቸገሩ ሳለ ሀብታም ገበሬዎች እህላቸውን ደብቀው አንሸጥም ቢሉ ድሀ ገበሬዎቹ በኃይል አስገድደው እንዲሸጡ ቢያደርጓቸው ድርጊቱ በድሀ ገበሬዎች ምግባር አንፃር ትክክለኛ ሆና ሲታይ ለሀብታም ገበሬዎች ምግባር ግን ትክክል አይደለም ። በሌላም አነጋገር ሕዝብ በረሃብ እያለቀ የገል ሀብቴ ነው በማለት ሀብታም ገበሬዎችና የመሬት ከበርቴዎች እህ

Digitized by Google

ላቸውን እንሸጥም ብለው ቢደብቁ ወይም ዋጋውን እጅግ አንረው ከገበሬው የመግዛት ዓቅም በላይ ቢያደርጉ አስገድዶ በተገቢ ዋጋ እንዲሸጡ ማድረግ በድሀው ገበሬ ምግባራዊ አስተያየት ተገቢና አስፈላጊ ድርጊት ነው ።

እነዚህ ከኢኮኖሚ ግንኙነት የሚፈልቁ የምግባር ግዕዛት የየመደቡን ፍላጎት የሚያንፀባርቁ ስለሆኑ ምንጊዜም ቢሆን እርስ በርሳቸው አይጣጣሙም ። ተፃራሪ መደቦች በመካከለኛው በሚኖረው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቅራኔ የተነሣ የበላይነትን ይዞ ጥቅምን ለማስከበር ወይም የአንድን መደብ ብቸኛ አሸናፊነትና ገናናነት ለመቀዳጀት ሳያቋርጡ ትግል ያካሒዳሉ ። በዚህ ረገድ የምግባር ግዕዛት አስተዋጽኦ አላቸው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት የገዥ መደብ አባላት ይህን ሥርዓት የሚደግፉ ምግባረ ግዕዛት ሁለንተናዊ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ይጥራሉ ። በሌላ አነጋገር ካፒታሊስቱ የራሱ ምግባራዊ መለኪያዎች በመላው ኅብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ወይም የመላው ኅብረተሰብ ምግባራዊ ግዕዛት ሆነው እንዲቆጠሩ ጥረት ያደርጋል ። የራሱን ግዕዛት የሌላ መደቦች አባላት ሲጥሱም ይኮንናቸዋል ። ካፒታሊስቱ ወዝአደሩ የራሱ የሆኑ የምግባር ግዕዛት ያሉት መሆኑንም አይቀበልም ።

የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ራስ ወዳድነት ፣ ግለኝነት ፣ ለትርፍ መጓጓት ፣ ጥላቻና የርስ በርስ ውድድር የገነነው መደብ ምግባር የሚቀበላቸው ባሕሪያት ናቸው ።[10] በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር «ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል ፤» «ከራስ በላይ ነፋስ» ወዘተ . . . የሚሉት አባባሎች በካፒታሊስቱ ሥርዓት ዘንድም ምግባራዊ ተቀባይነት ያላቸው አባባሎች ናቸው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት የመጀመሪያ የእድገት ደረጃ ወቅት ቡርዧው ከስግብግብነቱ የተነሣ ወዝአደሩን ረጂም የሥራ ሰዓት (ለምሳሌ በቀን ለ16 ሰዓት ያህል) ማሠራቱ በምግባር አንፃር ሲታይ ትክክል አይደለም የሚል አመለካከት የለውም ። ከዚህም በቀር ለሥራ ያልደረሱ ሕፃናትን ከዕድሜአቸውና ከዓቅማቸው በላይ በማሠራት መበዝበዙን ምንም ዓይነት የምግባር ጉድለት አድርጐ አይቆጥረውም ። ዛሬም ቢሆን ጊዜና ቦታ ሲያጋጥመው ተመሳሳይ ድርጊት ቢፈጽም ከምግባር ወቀሳ ነፃ እንደሆነ አድርጎ መመልከቱ የቡርዧው መደብ ባሕርይ ነው ። በተቃራኒው ግን የወዝአደሩ ምግባር ይህን ዓይነቱን ድርጊት ፍጹም የሆነ ኢሰብአዊ ድርጊት ነው በማለት ይኮንነዋል ።

ማንኛውም መደብ የራሱ የሆነ ምግባር አለው ቢባልም በየትኛውም ሥርዓተ ማኅበር የገዥ መደቦችን ብንመለከት አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ የጋራ ባሕርያት አላቸው ። ለምሳሌ ፣ «ሀብታምና ደሀ» ዓለም «ከተፈጠረ» ጀምሮ እስከ «ኅልፈተ» ዓለም ድረስ ጸንተው ይኖራሉ የሚለው እምነት በገዥ መደቦች (በዝባዥ መደቦች) ዘንድ ምግባራዊ ተቀባይነት አለው ። በሀብታምና በድሀ መካከል ያለው ልዩነት ከማንኛውም የመደብ ሥርዓት የኢኮኖሚው ግንኙነት የሚመነጩና ከመደብ ሥርዓት ማክተም ጋር አብረው የሚያከትሙ መሆናቸውን የበዝባዥ መደብ አባላት ከለመቀበላቸውም ሌላ ዘላለማዊ ናቸው ይላሉ ። ይሁን እንጂ ይህ ልዩነት የሰዎች ኑሮ በኢኮኖሚያዊ እኩልነት ላይ በሚመሠረትበትና ሁሉም እንደፍላጐቱ በሚያገኝበት ኅብረት ሥርዓተ ማኅበር አይኖርም ።

ተበዝባዥ መደቦች የሀብታምና ደሀ መኖር የተፈጥሮ ሥርዓት አድርገው በመቀበል ለሀብታሞች ተገዢነታቸውን እንዲያሳዩ በዘብዙ መንፈሳዊ አስተሳሰባቸውን እንዲያስገዙ የገዥዎች ግዕዛ ምግባር ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል ። በፕሮፓጋንዳቸው የአንድ ከበርቴ ሀብት የሠራተኛ ጉልበት ብዝ

Digitized by Google

በዛ ውጤት መሆኑ ቀርቶ «እግዚአብሔር ሰጠ ፣ እግዚአብሔር ነሳ ፤ (እግዚአብሔር ወሀበ እግዚአብሔር ነስአ) » የሚለውን ኢሳይንሳዊ አባባል በማስተጋባት እግዚአብሔር ጥንቱን ሲፈጥር «የመረቀው»ና ያስባለት የዕድሉ ፀጋ ሆኖ በተገኘው መደብ ምግባር ግንዛቤ ውስጥ እንዲሰርጽ ያደርጋሉ ። ድሃ መሆን በኤኮኖሚው ግንኙነት ባለው በብዝበዛው አስከፊ ሁኔታ ምክንያት በመሆኑ ሳይሆን «ፈጣሪው» ድሃ ሁን ስላለውና የዕድሉ ጽዋ (ፈንታ) ስለሆነ የራሱን ሥራ ኃይል በመበዝበዝ ሀብታም የሆነውን ሰው መቃወም ከምግባር አንፃር ተገቢነት የሌለው መሆኑን እንዲቀበል ፣ በአስተሳሰቡና በእንቅስቃሴው ላይ ተፅዕኖ ይደረግበታል ።

ሁለንተናዊ የምግባር ዘርፎች (ድንጋጌዎች)

ምግባር ከመደባዊ ይዘቱ በተጨማሪ ለተለያዩ መደቦች ባሕርያት መቆጣጠሪያ የሚሆኑና ለተለያዩ ዘመናት ጸንተው የሚኖሩ ባሕርይ መቆጣጠሪያ ደንቦችንም ያቅፋል ። ማለትም የተለያዩ መደቦች በወል ሊከተሏቸው የሚገቡ የምግባር ድንጋጌዎች አሉ ። እነኝህ ደንቦች ለመላው ኅብረተሰብ አባላት ሁለንተናዊ ተፈጻሚነት አላቸው ። ያለ እነሱ ተግባራዊነት የኅብረተሰቡ ሕልውና ሊጠበቅ አይችልም ።

የእነኝህ ምግባራዊ ዘርፎች ተግባር የኅብረተሰቡ አባላት የመላውን ኅብረተሰብ ሕልውና አደጋ ላይ ሊጥል ከሚችል ድርጊት (ለምሳሌ ፣ በግለሰቦች የቀን ተቀን ግንኙነት በኃይል መጠቀም) እንዲቆጠቡ መከልከል ፣ በሰዎችም የዕለት ተዕለት ኑሮና ግንኙነት መጠነኛም ቢሆን መተማመን እንዲኖር ፣ ለኅብረተሰቡ መሠረታዊ ሕልውና የሚጠቅሙ ድርጊቶችን አባላቱ እንዲፈጽሙና የመሳሰሉትን ማድረግ ነው ። ለምሳሌ ወላጆች ለልጆቻቸው ፣ ልጆች ለወላጆቻቸው የሚኖራቸው ፍቅር ፣ በዕድሜ የገፉ ሰዎችን የማክበርና የመርዳት ዝንባሌ ፣ ለበሽተኞች ርዳታ ለመስጠት የሚኖር ፈቃደኝነትና የመሳሰሉት በሁሉም መደቦች ዘንድ ከምን ዓላማ አንፃር ተግባራዊ ይሆናሉ ለሚለው ጥያቄ የተለያየ መልስ ሊኖር ቢችልም ተመሳሳይነት ያላቸው ምግባራዊ ገዕዛት ናቸው ።

ሁለንተናዊ ምግባራዊ ገዕዛት (universal elements of moral norms) ምንም እንኳን በተለያዩ ዘመናትና ለመላው የኅብረተሰብ አባላት የጋራ ተፈጻሚነት ያላቸው ቢሆንም በኅብረተሰብ የታሪክ ሂደት ውስጥ የተፈጠሩና ከዚሁ ኅብረተሰብ ዕድገት ጋር እየዳበሩ ፣ አዳዲስ ገዕዛትን እየጨመሩ የሚሄዱ ናቸው ። በመሆኑም ፣ እነዚህን ሁለንተናዊ ምግባራዊ ገዕዛት ከኅብረተሰብ ታሪክ ነጥሎ ማየት ትክክል አይደለም ። ልክ የአንድን መደብ ጥቅሞችን እንደሚያንፀባርቁት ገዕዛት ሁለንተናዊ ምግባረ ገዕዛትም የኅብረተሰቡ ዕድገት ውጤት ናቸው ። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከተፈጠሩ አያሌ ዘመናት ያለፉ ቢሆንም ፣ ከጊዜ ወደጊዜ እየዳበሩ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ ይተላለፋሉ ። የተለያዩ የታሪክ ዘመናትም ለእነኝህ ሁለንተናዊ የምግባር ድንጋጌዎች ዕድገት የተለያዩ አመች ሁኔታ ይፈጥሩላቸዋል ።[11]

ሁለንተናዊ ምግባረ ገዕዛት መሠረታዊ ምንጩ መደባዊ ጥቅም ባይሆንም ያሉበት ማኅበራዊ የምርት ግንኙነት በኅብረተሰቡ አባላት ዘንድ በመከበራቸው ተግባራዊ በመሆናቸውና በመዳበራቸው ላይ ተፅዕኖ አለው ። የሰው በሰው መበዝበዝ እስካልተወገደ ፣ አንዱ መንግሥት የሌላውን መንግሥት ብሔራዊ ኀልውና ከመድፈር እስካልተቆጠበ ድረስ ፣ በተለይም በአለንበት ዘመን የኢምፔሪያሊዝም የጦረኝነትና የጭፍጨፋ ፖሊሲ እስካለ ድረስ ሁለንተናዊ ምግባረ ገዕዛት መጣሳቸው የማይቀር ነው ። ኢምፔሪያሊስቶችና ተከታዮቻቸው ለሰው ልጅ ሕልውና ፣ ለምግባሩ መከበር

Digitized by Google

ቆመናል ቢሉም በተግባር ግን እጅግ የሚዘገንንና ውጉዝ ድርጊት ሲፈጽሙ ይታያሉ ።

ሁለንተናዊ ምግባረ ግዕዛት በመላው ኅብረተሰብ የሚከበሩትና ለመከበራቸው አመች ሁኔታ የሚፈጥርላቸው በመደብ አልባ ኅብረተሰብ ውስጥ ብቻ ነው ። ምክንያቱም «በአባላት መካከል በሙሉ ጓዳዊ ግንኙነት በሰፈነበት በመደብ አልባ ኅብረተሰብ ውስጥ ብቻ ነው ለእነኝህ የባሕርይ ሕግጋት መከበር አመች ሁኔታ የሚኖረው ።» [12] መደብ አልባ የሆነው ኮሚኒስት ሥርዓት ሲመሠረት እነኝህ ሁለንተናዊ ምግባረ ግዕዛት አጠቃላይ የሰው ልጅ ምግባራዊ ግንኙነት ብቸኛ መገለጫ ይሆናሉ ።

ምግባር የአንድ መደብ ማኅበራዊ መለኪያ ሆና ያገለግላል ሲባል የመደቡን አባላትም ግለሰባዊ እንቅስቃሴ ከመደቡ ማኅበራዊ ጠቀሜታ አንፃር ይቆጣጠራል ማለት ነው ። የምግባር ግዕዛት በግለሰቦች ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት ፥ ልምድና ስሜት ላይ ይንፀባረቃሉ ። ከዚህም በቀር የግለሰቦችን አስተያየትና እምነት የተወሰነ አቅጣጫ እንዲይዝ ያደርጋሉ ። ግለሰቦች ካሉበት ማኅበራዊ ኑሮ አፈንግጠው ማኅበራዊ ጠቀሜታውን የሚፃረር ፍላጐትና ድርጊት እንዳይኖራቸው ምግባረ ግዕዛት ይከላከላሉ ። [13] ለምሳሌ በዘር ልዩነት (አፓርታይድ) ፖሊሲ አንዱ ገጽታ የሆነው የደቡብ አፍሪካ የገዥ መደብ ምግባር የአንድን ነጭ ከጥቁር ጋር መቀመጥ ፥ ነጭ ከጥቁር ጋር የወዳጅነትም ሆነ የጋብቻ ግንኙነት መመሥረትን ፥ ከጥቁር ጋር አብሮ በአንድ አካባቢ መኖርንና አብሮ ባንድ የመመገቢያ ሥፍራ መቀመጥን ወዘተ . . . አጥብቆ ስለሚከላከል በማንኛውም ግለሰብ ነጭ ላይ ማኅበራዊ አስገዳጅነት ይጥልበታል ። ከዚህ መሥመር ውጭ የወጣ የነጭ ዜጋም ማኅበራዊ ተቀባይነት እንዲያጣና ቁሳዊና መንፈሳዊ ጥቅሙ እንዲነካ ይደረጋል ። ከዚህም የተነሣ ግለሰቡ ሳይወድ በግድ በማኅበራዊ አስገዳጅነት ሥር እንዲውል ይደረጋል ። ይህ እንግዲህ የአንድ መደብ ምግባራዊ ግዕዛት የኅብረተሰቡን አባል ፥ ግለሰባዊም ሆነ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ እንደት በማኅበራዊ ጥቅሙ ሥር ለማዋል እንደሚያገለግሉ ያመለክታል ።

በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር በሠራተኛው መደብ ምግባር አኳያ አንድ የሠራተኛ ማኅበር መሪ ከካፒታሊስቶች ጋር በመመሳጠር የሠራተኛውን መደብ ማኅበራዊ ጥቅም አሳልፎ ቢሸጥ የሚደርስበት ውርደትና ማኅበራዊ ተቀባይነት ማጣት መገንዘብ ይቻላል ። የፈጸመው ስሕተት ምግባራዊ ውግዘት ስለሚያስከትልበት በሠራተኛው ዘንድ ተቀባይነት ያጣል ፤ ማኅበራዊ ጥቅሙም ይነካል ። እንዲህ ያለ ስሕተትም እንዳይፈጸም የሠራተኛው መደብ ግዕዘ ምግባር በግለሰብ አባላት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ በማድረግ ተመሳሳይ ስሕተት ላለመፈጸም ማኅበራዊ መመሪያ ይሆናል ።

በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር የአንድ የመሬት ከበርቴ ጢሰኞች በያመቱ ከሚያመርቱት እህል የተወሰነባቸውን ድርሻ በርቀት ለሚገኘው የመሬት ከበርቴው እየጫኑ ወስደው ማስረከቡን ለግቆም ከተስማሙ በኋላ ከመካከላቸው አንዱ ወይም ሁለቱ ከስምምነታቸው ውጭ ጭነው ወስደው ለመስጠት ቢያስቡ የአካባቢውን ግዕዘ ምግባር እንደመጣስ ይቆጥሩታል ። ወይም ተግባራዊ ቢያደርጉትም በገቡት ውዴታ ግዴታ አኳያ ምግባራዊ ግዴታን መጣስ ይሆንና በአካባቢው ጭሰኞች ዘንድ ማኅበራዊ ተቀባይነት ያጣሉ ። የውርደት መንፈስም ይሰማቸዋል ። እንዲሁም በአንድ ማኅበረ ሰብ ክልል በአንድ ግለሰብ ቤት ላይ የእሳት ቃጠሎ ቢደርስ ማንኛውም የማኅበረሰቡ አባል ወጥቶ ርዳታ የማድረግ ማኅበራዊ ግዴታ ከሚገለጽባቸው አንዱ

Digitized by Google

ምግባራዊ ግዴታ ነው ። ይሁንና ይህ ዓይነት ቃጠሎ ሲታይ አንድ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች ለርዳታ ሳይወጡ ቢቀሩ ምግባራዊ ግዴታቸውን ሳይወጡ እንደቀሩ ተቆጥር ማኅበራዊ ወቀሳና ተግሳጽ ይሰነዝርባቸዋል ። የደህና ዋልህና የደህና እደርህን ሰላምታ እንኳን ማኅበረሰቡ ሊነሳቸው ይችላል ። ከዚህ አኳያም በግለሰቦች እንቅስቃሴ ላይ የምግባር ማኅበራዊ አስገዳጅነት ምን ያህል እንደሆነ መገመት ይቻላል።

በአንድ ሥርዓት ሰዎች (ከኢኮኖሚ ቦታቸው አንፃር) ላሉበት መደብ ወይም ማኅበረሰብ የሚጠበቅባቸውን ታማኝነትና ማኅበራዊ ግዴታ መወጣታቸውን ፣ ባለው ሥርዓት ውስጥ ለሚኖራቸው የኃላፊነት ቦታ ብቃታቸውንም ለመገምገም ከሚያስፈልጉት መለኪያዎች አንዱ ምግባር ነው። በየትኛውም ደረጃ የምግባር ግዴታውን መወጣት የማይችል ወይም በምግባሩ ያልተመሰከረለት ግለሰብ ማኅበራዊ ተቀባይነት አያገኝም ። ኃላፊነቱን ቢያገኝ እንኳ ምግባራዊ እርአያነቱ አጠራጣሪ ስለሚሆን ተደማጭነትን ያጣል ።

ምግባር የግል ሳይሆን ማኅበራዊ ግብ መምቻ ነው ። አንድ ግለሰብ ምግባራዊ ግዴታውን እንዲወጣ የሚጠበቅበትም ከግላዊ ግቡ ለመድረስ ሳይሆን ከማኅበራዊ ግቡ ለመድረስ ከሚያስፈልገው አኳያ ነው። እርግጥ ግቡ ማኅበራዊ በመሆኑ የግለሰቡንም ፍላጐት የሚያሟላ ነው ። ምግባር በሰዎች ዘንድ የሚገለጸው በዕለት ተዕለት ሥራቸው ፣ በእርስ በርስ ግንኙነታቸው ፣ በአስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው ፣ በአካላዊ እንቅስቃሴያቸው ፣ በማኅበራዊ ተሳትፎአቸውና አስተዋጽአዋቸውና በመሳሰሉት ሁኔታዎች አማካይነት ነው ።

የምግባርና የሕግ ልዩነትና ግንኙነት

በማንኛውም ኅብረተሰብ የምግባር ተፈጻሚነት በሰዎች ማኅበራዊ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው ። ለተግባራዊነቱም የቆመ መንግሥታዊም ሆኑ ሕዝባዊ ተቋሞች የሉም ። መመሪያዎቹም እንደ ሕግ፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተጽፈው ሳይሆን በኅብረተሰቡ አስተያየት ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ ትምህርትና እምነት የሚንፀባረቁ ናቸው ።[14]

የምግባር ደንቦች ከሕግ ደንቦች ይለያሉ። የሕግ ደንቦች የሚደነገጉትና ተግባራዊነታቸውም የሚረጋገጠው በሕግ አውጭና አስፈጻሚ ተቋሞች አማካይነት ነው ። ይሁንና «የምግባር ደንቦች ከሰብአዊ ግንኙነቶች የሚገኙ ልምዶችን በመቅሰም ፣ እንዲሁም በቁሳዊ ሕይወት ላይ ተመርኩዘው የሚፈጠሩትን የምግባር እርአያነትንና ሰዎች ስለ መልካምና መጥፎ ፣ ስለትክክለኛነትና ትክክል አለመሆን ያላቸውን አስተሳሰቦች በማጠቃለል በኅብረተሰብ ወይም በመደብ ይመሠረታሉ ።[15] የሕግ ደንቦች ከአውጭዎች ማለትም ከገዢው መደብ ፍላጐት አንፃር ግባቸው ተወስና በጽሑፍ ሰፍረው የሚገኙና ተግባራዊነታቸውንም በባለቤትነት የሚከታተልና የሚቆጣጠር የተወሰነ አካል ሲኖራቸው የምግባር ደንቦች ግን በቆሙለት የኅብረተሰብ ዓይነት ወይም መደብ ታሪካዊ የተግባር ልምድ ጸንተው የሚኖሩና በማኅበራዊ አስተያየት ፣ ተከታታይነትና ተቆጣጣሪነት ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው ።

የምግባር ግዕዝ ማንኛውም ግለሰብ ሊወጣው የሚገባ አስገዳጅነትና ግዴታው ሆና ይገለጻል ሲባል በአስፈጻሚ ሕጋዊ ተቋሞች አስገዳጅነት ሳይሆን በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ አስተያየትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተውን የረጅም የመግባባት ልምዱን በማክበር ነው ። የምግባር ግዕዛትን የጣሰ ግለሰብ ወይም ቡድን በሕግ ፊት ቀርቦ ከሕግ ውጭ የሆነ አድራጎት በመፈጸሙ ይህን ዓይነት የገንዘብ ወይም የእሥራት ቅጣት ተቀጥተሃል ሊባል አይቻልም። እርሱም ቢሆን ማኅበራዊውን የምግባር ግዕዛት ከመጣሱ በፊት ፣ ከሕግ አስተሳ

Digitized by Google

ሰብ የሚመነጭ ቅጣት ይደርስብኛል ብሎ አያስብም ። የምግባር ግዕዛት የሚገኙት ከራሱ ከኅብረተሰቡ የእንቅስቃሴ ባሕርይ ፣ ከሰዎች ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስተጋብር በመመንጨት ሲሆን ለግለሰቦችም ሆነ ለቡድኖች ኢምግባራዊ እንቅስቃሴ የሚሰጠው ፍርድም የኅብረተሰቡ አስተያየት ነው ። ይህ አስተያየትም በማኅበራዊ ጠቀሜታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የአፈጻጸም ፣ የተፈጻሚነቱ ስልትና ዘዴ ይለያይ እንደሆነ እንጂ እንደሕግ የአስገዳጅነት ኃይል አለው ። የምግባር ግዕዛት ተፈጻሚነትና ክብደትም የሚለከው ከዚህ አኳያ ነው ።

በአንድ መደባዊ ሥርዓተ ማኅበር ታሪካዊ ወቅት ሊኖር የሚችለው የገዥውን መደብ ጥቅም የሚያንፀባርቅ ሕግ ብቻ ሲሆን ፣ በአንፃሩ ግን የተለያዩ መደቦችን ጥቅም የሚያስከብሩ የተለያዩ ምግባራት በተመሳሳይ ወቅት ይኖራሉ ። ሕግም የበላይነት ያለውን የገዥ መደብ ምግባር ተግባራዊነትና ተቀባይነት ሊያገዝና ሊደግፍ ይችላል ። ከዚህ አንፃር የገዥው መደብ አንድን ድርጊት ከምግባራዊው አመለካከቱ አኳያ ትክክል ነው ወይም ትክክል አይደለም [16] ብሎ ምግባራዊ ርምጃ በሚወስድበት ወቅት የሕግ አጋዥነት ይኖራል ። ለምሳሌ የፊውዳል ሥርዓት ሰፍኖባት በነበረችው ኢትዮጵያ አንድ ግለሰብ በፍርድ ቤት ከዳኛ ፊት በሚቀርብበት ጊዜ ሸማውን አደገድጎ መግባት የፊውዳሉ መደብ የምግባር ጥያቄ ሲሆን ፣ አንድ ግለሰብ ሳያደገድግ ከዳኛ ፊት ቢቀርብ «ፍርድ ቤቱን በመድፈር» ተብሎ በሕግ ሊቀጣ ይችላል።

የኤኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ያለው መደብ ምግባርና ሕግ ዝምድና አላቸው ። በብዝበዛ ሥርዓታት ሁለቱም ብዝበዛንና ጭቆናን ያጠናክራሉ ፤ የሠርቶ አደሩንም ንቃተ ሕሊና ለማጨለም እንደ መሣሪያ ያገለግላሉ ። [17] የሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣኑን ቢጨበጠበት ሶሻሊስት ሥርዓትም የሠራተኛው መደብ ምግባርና ሕግ የዓላማ አንድነት አላቸው ። ሁለቱም የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስከበር የቆሙ ናቸው ። ጆሴፍ ስታሊን እንዳለው ከምግባር ግዕዛት መካከል የሕግ ደንቦች ሆነው የሚሠራባቸው ሊኖሩ ይችላሉ ፤ ይህም በብዙኃኑ ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ ያላቸውና ተፈላጊነታቸውም በጐላ ተግባር የተረጋገጠላቸው ናቸው ። [18] ለምሳሌ በሶሻሊስት ሥርዓት ሳይሠሩ መብላትን የሠራተኛው ምግባር የማይቀበለው ከመሆኑም በላይ የሶሻሊስት አገሮች የማይሠራ እንደማይበላ በሕግነት ደንግገውታል ። በካፒታሊስት ኅብረተሰብም ውስጥ የሥርዓቱ ሕግና ምግባር አንድ ዓይነት ማኅበራዊ መሠረት (የቡርዧው የመደብ ጥቅምና የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት) ያላቸውን ያህል ማኅበራዊ ግንኙነቱን ከማስከበር አኳያም የዓላማ ተመሳሳይነት አላቸው ። የገዥው መደብም ጥቅሙንና ፍላጐቱን ለማስከበር እንደአስፈላጊነቱ በተለዋዋጭነት ሲጠቀምባቸው ይታያል ።

አንዳንድ የቡርዧ ምሁራን ምግባር ሕሊናዊ (መንፈሳዊ) ሕይወትን ብቻ የሚገዛ እንጂ በምንም ዓይነት ከሰዎች ቁሳዊ ሕይወት ጋር ያልተያያዙ አድርገው ሲያቀርቡ ፣ የሕግ ግዕዛት ደግሞ በሰዎች መካከል የሚኖረውን ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት የሚመለከቱ ናቸው ይላሉ። በመሠረቱ የሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ወይም ንቃተ ሕሊና (ምግባር ጭምር) የቁሳዊ ሕይወታቸው ነፀብራቅ ወይም የሰዎች ማኅበራዊ ግንኙነት ውጤት ሲሆን ማኅበራዊ ግንኙነቱን የሚቆጣጠር ወይም ሰዎች በማኅበራዊ ግንኙነቱ ካላቸው ቦታ ፍላጐት አኳያ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ተገቢነቱን ወይም ተገቢአለመሆኑን የሚገመግሙ ዘርፎች አሉት ። ከነዚህም ዘርፎች አንዱ ግባር ነው ። በመሆኑም

Digitized by Google

ምግባር እንደሕግ በሰዎች ቁሳዊ ሕይወት ውስጥ የሚጫወተው ሚና አለ ።

ምግባር በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ሚና

ፖለቲካ የአንድ መደብ መሠረታዊ ጥቅም አንፀባራቂና የመደቦች የርስ በርስ ግንኙነት የሆነውን ያህል ምግባርም የአንድ መደብ ጥቅም ወይንም አንድ መደብ ከሌሎች መደቦች ጋር ያለውን ግንኙነት ያመለክታል ።[19] ለምሳሌ የቡርዧው ምግባር ዓይነተኛ ዓላማ የበዝባዥና ተበዝባዥ ግንኙነት እንዲቀጥል ማድረግ ነው ። በመሆኑም የሠርቶ አደሮችን መሠረታዊ ሕልውና ይነካል ፤ መብታቸውን ይገፋል ፤ በሰዎች መካከል መከፋፈልን ፣ በበላይነት መተያየትንና ለሀብት ማጋበስ የሚደረግ ፉክክርን እንደትክክለኛና ቋሚ ባሕርይ አድርጎ ይቀበለዋል ። ከዚህ አኳያ «ወደር የሌለው ራስ ወዳድነት የቡርዧ ምግባር መሠረታዊ መርሕ ነው »[20] ማለት ይቻላል ። የካፒታሊስት የፖለቲካ ሥርዓት የዚህኑ ሥርዓት የገዥ መደብ ጥቅም ማስከበርና ማስፋፋት ነው ። የዚህ ገዥ መደብ ጥቅም መስፋፋት የአያሌ ሕዝቦች መጨቆን ፣ መበዝበዝና ለረሃብና ለእርዛት መጋለጥን ያስከትላል ።

የኢምፔሪያሊስት ምግባርም ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት የሚያራምዱትን የብዝበዛ ፣ የጭቆናና የጦረኝነት ፖሊሲ ፣ የሚፈጽሙትን ኢሰብአዊ ድርጊት የሚቀበልና የሞኖፖል ካፒታሊስት ጥቅሞችን የሚያስከብር በዚያው አንጻር የምዝብር ሕዝቦችን መብትና ነፃነት የሚያንኳስስ ነው ።

ይሁንና የኢምፔሪያሊዝም ፖለቲካና ምግባር ተጓዳኝነት እየጎላ በሔደ ቁጥር በዓለም ላይ ከሰብአዊውና ከምግባራዊ ጭቆና ለመላቀቅ የሚታገሉት ሠራተኛችና ሌሎች ተራማጅ የኅብረተሰብ ክፍሎች ይበረክታሉ ። በዚህም ትግል የሰውልጅ ከብዝበዛና ጭቆና ነፃ የሚወጣበት ጊዜ እጅግ እየተቃረበ ይሔዳል ። ከፍተኛና ትክክለኛ የሆነው የሠራተኛው መደብ ምግባር ታሪካዊ ተልዕኮ ምዝብር ሕዝብ ከብዝበዛና ጭቆና ተላቆ ፍትሕ የሰፈነበት አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት እንዲችል አስተዋጽኦ ማድረግ ይሆናል ።

ተራማጅና ሰብአዊው ምግባር ከብዝበዛና ጭቆና ለመላቀቅ ለሚደረገው ታሪካዊ ተጋድሎ ግብ መምቻ መግሪያ ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ እያደገ የመጣው የሠራተኛው መደብ ምግባር የዚህ ዓይነቱ መግሪያ ነው ። የዚህ መደብ ምግባር ከካፒታሊዝም ኢሰብአዊና ርህራሄ የለሽ ባሕርይ ምክንያት በሠራተኛው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ውስጥ ከሠራተኛው የመነጨና የዳበረ ነው ።

የካፒታሊዝም ሥርዓት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት እየገፋ ሲሔድ የብዝበዛ ስልቱና ባሕርዩ ይቀያየራል። በአንፃሩም የሠራተኛውን የትግል ስልትና ዘዴ ይለዋወጣል ፤ ያድጋል ፤ ወደከፍተኛ የትግል ደረጃ ይሸጋገራል። የሠራተኛውም ምግባር መመዘኛዎች ተገቢነት የሚታየው ከእያንዳንዱ ወቅትና የመደብ ትግል ባሕርይ አኳያ ነው። ከዚህም የተነሣ የምግባር አስተያየቶችና መስፈሪያዎች ከየታሪካዊ ወቅቱና አስገዳጅነት አኳያ ይለዋወጣሉ ።[21] በአንድ ወቅት ፣ ሠራተኛው ያመርትባቸው የነበሩትን የምርት መገልገያዎች መሰባበር ዓይነተኛ የትግል ስልቱ እንደነበር ሲታወስ ይህም በወቅቱ የምግባራዊ አስተያየቶች ተገቢነት ያለው ነበር ። ይሁንና ባለንበት ዘመን የሠራተኛው መደብ የትግል ባሕርይ የመጠንም ሆነ የዓይነት ለውጥ በማሳየቱ ግብታዊ የምርት መግሪያ መሰባበር በሠራተኛው ዘንድ የምግባር ተገቢነት አይኖረውም ።

«እያንዳንዱ ለሁሉም ፣ ሁሉም ለያንዳንዱ ጥቅምና ፍላጐት መሟላት ይሠራ » የሚለው ዘይቤ የዳበረ የሠራተኛው ም–

Digitized by Google

ባር መንደርደሪያ ሐሳብ ነው ። ከዚህ በመነሣት ኮሚኒስቶች ማኅበራዊነትንና ጓዳዊነትን ፥ ለኮሚኒዝም ዓላማዎች ታማኝነትን፥ ሶሻሊስታዊ ሀገር ወዳድነትን ፥ ምርታማነትን ማሳደግ ፥ ሶሻሊስት ሀብት ማካበትንና መንከባከቡን ፥ ማኅበራዊ ግዴታን መገንዘብንና ማኅበራዊ ጥቅሞችን ማስከበርን፥ በጋራ ጥቅሞች ላይ የተመሠረተ የሕዝቦች የርስ በርስ ግንኙነት መመሥረትንና ማስፋፋትን ፥ ሰብአዊ መብት ማክበርን ፥ ታማኝነትንና እውነተኛነትን ፥ በግል ሕይወት ውስጥ ቀናነትንና ደግነትን ፥ የቤተሰብ ፍቅርንና መተሳሰብን ፥ ለሕፃናት ልዩ እንክብካቤን ፥ የብሔር ትምክህተኝነትንና ጠባብነትን እንዲሁም የዘር መድልዎን መቃወምን ፥ ከኮሚኒዝምና ከሰላም ጠላቶች ጋር ምንም ዓይነት እርቅ አለማድረግን ፥ ከሁሉም አገር ሠርቶ አደሮች ጋር የትግል አንድነት መመሥረትን [22] ወዘተ አንድም ጊዜ ወደኋላ ሳይሉ ለማራመድ ጥረት ያደርጋሉ ።የሠራተኛው መደብ ምግባር በዚህ የመደብ ትግል ውስጥ አድርባይነትን ፥ ሥርዓተ አልበኝነትን ወዘተ ይዋጋል ።

የሠራተኛው ምግባር በሰብአዊ ርኅራኄ ላይ የተመሠረተ የሰው በሰው መበዝበዝንና ጭቆናን እጥብቆ የሚዋጋ ፥ በሰዎች መካከል ፍትሕ ፥ ርትዕ ፥ ነፃነት ፥ ወንድማማችነት ፥ እኩልነት ፥ ወዘተ የሰፈነበት ማኅበራዊ ኑሮ እንዲኖር የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ነው ። ሰብአዊ ርኅራኄ ሲባል ሰውን በማንኛውም ቁሳዊ ጥቅሙና መንፈሳዊ ሕይወቱ በእኩልነት ማየቱና ሰብአዊ መብቱን ማክበሩ ነው ። የሰዎች ቁሳዊና መንፈሳዊ ጥቅሞች በእኩልነት ደረጃ መከበር የሚችሉት ደግሞ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት ሲጠፉ ብቻ ነው ። የጭቆና ሥርዓት ሳይጠፉ ጥቅሞቹ ሊከበሩ አይችሉም ። በመሆኑም የሠራተኛው ምግባር ብዝበዛንና ጭቆናን ለማጥፋት የሚካሔደውን ትግል ትክክለኛነት በሚገባ ይቀበላል ።

የሠራተኛው ምግባር የማኅበራዊ ጠንቆች ምንጫቸው የመደቦች ቅራኔ መሆኑን በመገንዘብ የቅራኔው መንስኤ የሆነውን ማኅበራዊ ግንኙነት ለማፍረስ የሚካሔደውን ትግል ያጠናክራል ። ሌኒን ለታላቁ ሩስያ አብዮት የሠራተኛው ምግባር ጥንካሬ ለትግሉ መሳካት ያደረገውን አስተዋጽኦ ሲገልጽ «የእኛ ወዝአደር ምንም እንኳን በቁጥር አነስተኛ ቢሆንም ፥ በድኅነትና በግል ይዞታ ምክንያት ከፍተኛ ሥቃይ ቢደርስበትም ትግሉን በአሸናፊነት ተወጥቶታል ፤ ምክንያቱም የምግባር ጥንካሬ ስለነበረው ነው» [23] ብሏል ። የምግባር ጥንካሬም የሚመነጨው ዓላማን በውል ከመገንዘብ የተነሣ በመሆኑ በፖለቲካው ትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። የዓላማው ምንነት የኅብረተሰቡን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ከሆነም የምግባር ልልነትንና ከፖለቲካ ትግሉ ፈር መውጣትን ያስከትላል ። በሌላ በኩል ለፖለቲካ ታማኝነት የምግባር ጥንካሬ አስተዋጽኦ የሚያደርገውን ያህል የአድኃሪ መደቦች ለፖለቲካም ሽንገላ አንዱ መንስኤ የምግባር ድክመት መሆን መረሳት የለበትም ። [24]

የወዝአደሩ ትግል ነፃ አውጭነት የራሱን መደብ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ተጨቋኝ መደቦች ወይም መላ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጭምር የሆነውን ያህል የወዝአደሩም ምግባር መግሪያነቱ ለሠራተኛው መደብ ብቻ ሳይሆን ለመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ነው ። የሠራተኛው ፍላጎት ብዝበዛንና ጭቆናን ለማስወገድና መደብ አልባ ሥርዓትን ለማስፈን እስከሆነ ድረስ የሠርቶ አደሩም ሕዝብ ፍላጎት ይኸው ነው። ብዝበዛንና ጭቆናን ለማስወገድ የሚያገለግል ምግባር ደግሞ የሰፊው ሕዝብ ምግባር ይሆናል ። ከዚህ በኋላ ኢንግልስ የአሁኑን ሥርዓት ባሕርይ ተከቶ ዘላቂነት የሚኖረው ዓይነተኛው ቁም ነገር መጭውን

Digitized by Google

ሥርዓት የሚወከለው ነው ። ይህም የሠራተኛው ምግባር ነው » [25] ብሏል ።

ብዝበዛና ጭቆና በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ የሠራተኛው መደብ ምግባር ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ከትክክለኛ ፍላጐቱ አንፃር በአንድነት አሰልፎና አስተባብሮ ሥርዓቱን እንዲገረስስ ማድረግ ሲሆን ሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣኑን በጨበጠበት ሥርዓት ደግሞ የምግባሩ ትኩረት ሰፊው ሕዝብ የጨበጠውን የበላይነት እያረጋገጠ የሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታውን እንዲያካሒድ ማስቻል ነው ።

ሶሻሊስት ሥርዓትን በመገንባት ሂደት ውስጥ የሠራተኛ ምግባር ቀስ በቀስ እየተለወጠ ኮሚኒስታዊ ባሕርይን ይቀዳጃል ። ይህም የመላውን ሠራተኛ ሕዝብ ፍላጐት የሚያሟላ ይሆናል ። [26]

የግርጌ ፡ ክሊታዎች

1. A.P. Sheptulin, *Marxist-Leninist philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1978), p. 428.
2. I. Frolov, ed., *Dictionary of Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1984), p. 275.
3. *Fundamentals of Marxist - Leninist* philosophy (Moscow: Progress Publishers, 1978 p. 482.
4. *Dictionary of Philosophy*, p. 276.
5. *The Fundamentals of Marxist-Leninist Philosophy* (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 346.
6. *Great Soviet Encyclopedia*, Vol. 16, (New York: Macmillan Inc., 1973), p. 549.
7. V.G. Afanasyev, *Marxist Philosophy* (4th edition) (Moscow: Progress Publishers, 1980), pp. 374-375.
8. F. Engel's, *Anti-Duhring* (1st edition) (Moscow: Progress Publishers, 1947), p. 117.
9. Ibid., p. 117.
10. V.G. Afanasyev, p. 375.
11. A.P. Sheptulin p. 436.
12. Ibid.
13. *Great Soviet Encyclopedia*, Vol. 16, p. 549.
14. V.G. Afanasyev, p. 374.
15. A.P. Sheptulin, p. 450.
16. *Political terms* (Moscow: Novosti Press Agency Publishing House, 1982), p. 47.
17. ሕግና ፍርድ ፤ ቅጽ 1 ፤ ቁ. 1 ፤ ሀዳር 1976 ፤ ገጽ 18 ።
18. J.V. Stalin, *Questions of Leninism*, pp. 131-32.
19. STP, (supplement), 1984, p. 11.
20. V.G. Afanasyev, p. 375.
21. F. Engels, p. 113.
22. A.P. Sheptulin, pp. 456-57.
23. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 32, p. 276.
24. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 17, p. 166.
25. F. Engels, pp. 113-14.
26. A.P. Sheptulin, p. 456.

Digitized by Google

የኢምፔሪያሊዝም ሥነልቦና ጦርነት

—ስልትና መድረኮች

ደርበው ተመስገን

የዓለም አብዮታዊ ኃይሎች እየተጠና ከሩ በመምጣታቸው በወታደራዊ ኃይል የሶሻሊስቱ ዓለም የማይበገር መሆኑን የተረዳው የኢምፔሪያሊዝም በጦር መግ ሪያ የበላይነቱን ለመቀዳጀት ከሚያደርገው ዝግጅት ጐን እንደአይነተኛ መግሪያ የሚ ጠቀምበት የርዕዮተዓለም ጦርነት ነው። በአንድ የአሜሪካ ወታደራዊ መዝገበ ቃላት እንደተተረጎመው «የሥነ ልቦና ጦርነት የጠላትን ፣ የወዳጅን ወይንም የገለልተኛ ኃይሎችን አስተሳሰብ ለመ ለወጥ ፣ እንቅስቃሴያቸውንም በተፈለ ገው አቅጣጫ ለመምራት አስቀድሞ በተ ጠናና በታቀደ ስልት የሚነዛ ፕሮፓጋንዳ ነው ።»[1] ከዚህ ፍቺ እንደምንረዳው የኢ ምፔሪያሊዝም ሥነልቦና ጦርነት ዓላማ በጦር መግሪያ ኃይል ሊንበረከክ ያልቻለ ውን ፀረ ብዝበዛ ኃይል ጠላት ፣ ወዳጅ፣ ገለ ልተኛ ብሎ በመከፋፈል ኃይሉን ማዳከ ምና የታጋይነት ወኔውን መስለብ ነው።

በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል በሚካሔደው ትግል ውስጥ የኢምፔሪያ ሊዝምን የጭቆናና የብዝበዛ ሥርዓትና የበላይነት ለመጣል የሚታገሉት የሶሻ ሊዝም ኃይሎች ሶሻሊስት አገሮች ፣ በካፒታሊስት አገሮች የሚገኙት ሠራ ተኛ ሕዝቦች ፣ ለነፃነታቸው የሚታገሉ የአርነት እንቅስቃሴዎች እንደመሆናቸው የሥነልቦና ጦርነትም እነዚህን ኃይሎች ኢላማ ያደረገ ነው ። የሥነልቦና ጦርነት ስሙ እንደሚያመለክተው፣ ኢምፔሪያሊ ስቶች እንደሚጠቀሙበት የሕዝቦችን ማኅበራዊና ሥነልቦናዊ ሁኔታ በማጥናት ባህርያቸውን በተፈለገው መልክ መቅ ረጽ ፣ ተግባራቸውን መቆጣጠርና ለአንድ ለተፈለገ ዓላማ ማዋል በመሆኑ በሕዝ ቦች አስተሳሰብ ላይ የተከፈተ ጦርነት ነው ። ይሁንና በቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ሕዝቦችን የማጥናቱ ሥራ አስተሳሰባቸ ውን ከኅብረተሰብ ጭብጥ ሁኔታዎች ጋር

Digitized by Google

በማቆራኘት በዓለም ላይ ስላሉ ክስተቶች ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ አይደለም ። ስለነገሮች በምክንያት ላይ የተመሠረተ አመለካከት እንዲኖርም አይደለም ። ዓላማው የሕዝቦችን ስሜት በተጣመመና ለኢምፔሪያሊስቶች ጠቃሚ በሆነ መንገድ መቅረጽ ነው ።

ሥነ ልቡናዊ ጦርነት በነገሮች ትክክለኛ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ አይደለም ስንል በጥናት ላይ ያልተመረኰዘና በግብታዊነት የሚካሔድ ነው ማለታችን አይደለም ። ይልቁንም የካፒታሊዝም ዕድገት ያፈራቸውን የሥነልቦናና የማኅበራዊ ኑሮ « ጠበብት » ይጠቀማል ፤ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብም ያወጣል ። በዩናይትድ ስቴትስ ብቻ « 40,000 ምሁራን ስለማኅበራዊ ግንኙነት እንደሚያጠኑና ከመቶ በላይ ታዋቂ ኩባንያዎች ለዚሁ ተግባር ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ በዓመት እንደሚያወጡ »[2] ጥናቶች ያመለክታሉ ።

ለዚህ ተግባር የተቀጠሩ የቡርዧ ምሁራን በሚያቀርቧአቸው ጥናቶች አማካይነት የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ፣ » የሕዝቦች የፖለቲካ አስተሳሰብ በአብዛኛው የሚመሠረተው በየዕለቱ ከሚያጋጥሟቸው ልምዶች ብቻ ሳይሆን በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች እንዲሁም ከሰው ከሚያገኙት ተላላፊ ወሬ ነው ፣ ብዙሃኑ ሕዝብ ምንም የማያመዛዝንና የነገሩትን የሚቀበልነው» ከሚል የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ደርሷል ። ከዚህ ሕዝቦችን የመናቅ አመለካከት በመነሳት ለኢምፔሪያሊዝም ጉጂ መስሎ የሚታያቸውን ሁሉ ያፍናሉ ። ዓላማቸውን የሚያራምድ መስሎ ከታያቸውም ፈጥረው ወይም አነስተኛ የዕውነት ፍንጭ ይዘው አጋኖ ማስተጋባትን እንደ ዓይነተኛና ቋሚ ስልት ይጠቀማሉ ።[3] ቀደም ሲል በተጠቀሰው ኢሳይንሳዊ መደምደሚያ ላይ የተመሠረተው የኢምፔሪያሊዝም ሥነ ልቦናዊ ጦርነት የካፒታሊስት አገሮች የውጭ ግንኙነት ፖሊስ አንድ አካል በመሆን ለኢምፔሪያሊዝም ዲፕሎማሲያዊና ኤኮኖሚያዊ ፖሊሲ ዓይነተኛ ማስፈፀሚያ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል ። ሶሻሊዝምን ለማዳከም ፣ የሕዝብን አእምሮ የተሳሳተ መረጃ ለመመገብና ሐቅን ለማጣመም ባለው ዓላማ ኢምፔሪያሊዝም የዘመኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያፈራቸውን ግኝቶች ሁሉ ይጠቀማል ። በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር የሠራተኛው ሕዝብ ገንዘብ እየወጣባቸው በኢምፔሪያሊዝም መዲናዎች የሚታተሙ መጻሕፍት ፣ የሚሠሩ ፊልሞች የግል ሀብትን ዘለዓለማዊነት ፣ የካፒታሊዝምን በጐነት በመስበክ የግልሀብት የማካበት ፍላጎት ፣ ግለኝነትና «ነፃ» ውድድር የሰዎች የተፈጥሮ ባህርይ ናቸው ብለው ለማሳመን ይሞክራሉ ፤ ሠራተኛውን ሕዝብም የተሳሳቱ አስተሳሰባቸው እስረኛ ያደርጋሉ ።

በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ የሚገኙ ተጨቋኝና ተበዝባዥ ሕዝቦች የጉስቁልናቸውን መሠረታዊ ምክንያት እንዳይገነዘቡ የኢምፔሪያሊዝም የፕሮፓጋንዳ መድረኮች ጉልህ ሚና ይጫወታሉ ። «በምዕራቡ ዓለም ጋዜጣ ፣ ሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ፣ ሲኒማ ሰዎች ትኩረታቸውን በወሲብ ፣ . . . በግላዊ ኑሮ ፣ በወንጀል ፣ ሆን ተብሎ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በሚፈጠር «ዝነኛ » ግለሰብ (ለምሳሌ የኪነት ሰው) በዘመናዊ ሙዚቃ ፣ በዳንስ ፣ በፋሽን ልብሶችና በመኪና ላይ እንዲጥሉ ፣ »[4] የካፒታሊዝምን ቀውስና ቅራኔ እንዳያጤኑ ፣ የችግራቸው መንስዔ የግል ሀብትና ሞኖፖሊስቶች መሆናቸውን እንዳይገነዘቡ በማድረግ ላይ ናቸው።

Digitized by Google

በአሁኑ ጊዜ በምዕራቡ ዓለም የማዝናኛ ፕሮግራሞች ለይስሙላ የጊዜ ማሳለፊያና መዝናኛ ተብለው ይዘጋጃሉ ። ይሁን እንጂ በይዘታቸው ከኅብረተሰቡ ተጨባጭ ሁኔታ ርቀው የሕዝቦችን አስተሳሰብ ወደ ሕልምና ወደ ማይጨበጥ ዓለም የሚገፋፉ «የሕዝብ አእምሮ አንደንዛዥ ዕፅ ናቸው »

የፕሮፓጋንዳ አውታሮችን ለሥነ ልቡና ጦርነት የመጠቀም ስልት ለሞኖፖሊስቶች በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ የመግደል ያህል ጥቅም አለው ። በአንድ በኩል በዓለም ላይ ታላላቅ የሚባሉት የዜና ማሠራጫና የፊልም ኢንዱስትሪዎች ፣ የመጻሕፍት አሳታሚ ድርጅቶች የሞኖፖሊስቶች ንብረት እንደመሆናቸው እጅግ በርካታ ትርፍ የሚያስገኙ ናቸው። የእንግሊዙ የማኅበራዊ ኑሮ ምሁር ፕሮፌሰር ተርንስቶል ማስሚዲያ -አሜሪካ በተሰኘው መጽሐፋቸው እንደገለጹት በ1979 (እ. ኤ. አ.) ብቻ አሜሪካ ፊልሞች ፣ የሙዚቃ ሸክላዎች ፣ ቴፕና ካሴቶች ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች በመሸጥ፣ «አሶስዬትድ ፕሬስ » እና « ዩናይትድ ፕሬስ ኢንተርናሺናል » በተባሉት የዜና ድርጅቶቿ አማካይነት ዜና በማሰራጨት ከ1.5—2 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ትርፍ አግኝታለች ። አይ. ቲቪ (ITV) የተሰኘውን የእንግሊዝ የግል ቴሌቪዥን ድርጅት ጅት በማስታወቂያ ሽያጭ ብቻ በ1955 (እ.ኤ.አ.) 4.8 ሚሊዮን ዶላር አትርፎ ነበር ። ይህ ዓመታዊ ገቢ በ1960 ወደ 160 ሚዮን ዶላር ከፍ ሲል በ1970 ዎቹ ዓመታት ከዚሁ ቴሌቪዥን ማስታወቂያ ሽያጭ የተገኘው ገቢ የእንግሊዝ ጋዜጦች በጠቅላላ ከሚያገኙት ገቢ የበለጠ ሊሆን ችሏል ። [5] ከታላላቆቹ የዜና ሞኖፖሊስቶች አንዱ የሆነው ሮይ ቶምሰን «በዘመናችን የቴሌቪዥን ጣቢያ ባለቤት መሆን የወረቀት ገንዘብ አትሞ የማውጣት ፈቃድ ከማግኘት ጋር ይመጣጠናል » [6] ያለው ለዚህ ነበር ። እያንዳንዱ የካፒታሊዝም የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ግዙፍ የሞኖፖሊስቶች የንግድ ድርጅት በመሆኑ ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኝ ኢንዱስትሪ ለመሆን በቅቷል ። በዩናይትድ ስቴትስ በ1970ዎቹ ዓመታት ዕለታዊ ጋዜጦች በዓመት 10 ቢሊዮን ዶላር ፣ መጽሔት 2.5 ቢሊዮን ዶላር ፣ ሬዲዮ 1.6 ቢሊዮን ዶላር ፣ ቴሌቪዥን 5 ቢሊዮን ዶላር ትርፍ [7] ለሞኖፖሊስቶች አስገኝተዋል ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ለሞኖፖሊስቶች የሚሰጡት አገልግሎት ትርፍ በማስገኘት ብቻ የሚወሰን አይደለም ። ይልቁንም ዓይነተኛ ተልእኳቸው የሥርዓቱንና የግል ሀብትን ዘለዓለማዊነት መስበክ ነው ። እነዚህ የፕሮፓጋንዳ አውታሮች የካፒታሊስቱን ዓለም የዕድገት ደረጃ ከፍተኛነት በተለይም የአሜሪካን የአኗኗር ዘይቤ ምቹነት በመስበክ ፣ ሶሻሊዝምንና ኮሚኒዝምን በማጥላላት የፀረ ኢምፔሪያሊስቱን ትግል ለመከፋፈል በመሞከር ከፍተኛውንና ዋንኛውን ሚና ይጫወታሉ ።

የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ አውታሮች የካፒታሊዝምን ዕድሜ የማራዘም ተልዕኳቸውን ለመወጣት የተለያዩና እጅግ የረቀቁ ስልቶችን ይጠቀማሉ ። በእነዚህ ስልቶች አማካይነትም በሶሻሊስት አገሮችና ለነፃነታቸው በሚታገሉ ሕዝቦች መካከል የትግል አንድነትና መተማመን እንዳይኖር የኮሚኒዝም ፍራቻና ጥርጣሬ በሕዝቦች ዘንድ እንዲፈጠር ይጥራሉ ። በይበልጥም የአሉባልታ መነሻዎች የሚሆኑ የፈጠራ ወሬዎችን በመንዛት የወሬ ሽብርን ያደፋፍራሉ ። ለዚህም ዓላማ የሚውሉና «ብላክ » ፕሮፓጋንዳ

Digitized by Google

በመባል የሚታወቁ ጽሑፎችን ከስለላ ድርጅቶች ያገኛሉ ። «ከታመኑ የወሬ ምንጮች» ፣ «ከዲፕሎማቲክ ምንጮች» የሚል ቅጥያ እየተሰጣቸው በምዕራብ የዜና ድርጅቶች የሚሠራጩ ዜናዎች ያልሆነውን ሆነ ብለው ፣ ትክክለኛውን አጣመው የሕዝብን አስተያየት ለማሳሳት የሚነዙ ናቸው ። ዜናዎቹ የሚሠራጩበትን ዓላማ ይፈጽማሉ ተብለው እስከተገመተ ድረስ ስለሐቀኝነታቸው ኢምፔሪያሊስቶች የሞራል ግዴታ ጣጣ ውስጥ አይገቡም ። የካፒታሊስት አገሮች የዜና ድርጅቶች በሞኖፖሊስቶች እጅ መሆናቸው የአገሩ መንግሥት ለዜናዎች ኃላፊነትን እንዳይወስድ እንደመሸፈኛ ያገለግላል ።

በዚህ መልክ የዜና ድርጅቶች የሚያሰራጩትን ወሬ የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ፣ የእንግሊዝ የዜና ማሰራጫ ድርጅት (ቢ ቢሲ) ፣ የጀርመን ድምፅ ሬዲዮና ሌሎችም የካፒታሊስት አገሮች የውጭ ሬዲዮ አገልግሎቶችና ጋዜጦች ተቀብለው በመላው ዓለም ያስተጋባሉ ። በአሜሪካ የኢንፎርሜሽን ድርጅት (USIS) ሥር ሆና በአሜሪካ የፀጥታ ምክር ቤት በኩል ከፕሬዚዳንቱ የቅርብ አመራር የሚያገኘው የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ 41 ፣ በዓለም ዙሪያ 61 የማሰራጫ አንቴናዎችን በመትከል በ38 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች በሳምንት 845 ሰዓት ዜናና ፕሮግራሞችን ያሠራጫል ። የአሜሪካ ጦር ሠራዊት ከአሜሪካ ውጪ 250 የሬዲዮ ፣ 34 የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ከአሜሪካው የስለላ ድርጅት ጋር በቅንጅት በማካሄድ የአገሮችን የሰላምና የሕዝቦችን ደህንነት የሚያናጉ ፣ አንዱን ሕዝብ በሌላው ላይ ለጦርነት የሚያነሳሱ ዜናዎችን ያሠራጫል ። ፡

የኢምፔሪያሊዝም የፕሮፓጋንዳ አውታሮች የአጠቃላዩ ፀረ ኮሚኒስት ስትራቴጂ አንድ አካል እንደመሆናቸው የሞኖፖሊስቶችን ዓላማ እንደሚያራምዱ በዕለት ተዕለት ሥርጭታቸው በገሀድ በመታየት ላይ ነው ። ሕዝቦች ለነፃነት ፣ ለእኩልነት ፣ ለሶሻሊዝምና ለሰላም የሚያደርጉትን ትግል አጣመውና አዛብተው ያቀርባሉ ። ለኮሚኒዝምና ለአብዮታዊ ኃይሎች ባላቸው ጭፍን ጥላቻ በፈጠራ ወሬ የሕዝቦችን አመለካከት ለማዛባት ይጥራሉ ። በሰፊው ለተያያዙት የጦር መሣሪያ ምርትትና ፀረሰላም እንቅስቃሴ መንስኤው «የኮሚኒዝም አደጋ» ነው ብለው ያቀርባሉ ። የቅኝ አገዛዝና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ምዝበራና ጭቆና ያንገሸገሸው አንድ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሰን ሲነሳሳ «የኮሚኒዝም ሴራ» ብለው ይኮንኑታል ። ለመብት የሚደረገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ «ሽብር ፈጠራ» ብለው ያወግዛሉ ። በአንፃሩ ግን ለፖለቲካ ፣ ለኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፍትሕ የሚታገሉ ሕዝቦችን በቅጥረኝነት የሚወጉ ፣ ሕፃናትን ፣ አረጋውያንን ሰላም የሚነሱ ፣ ታጋዮችን የሚያሳድዱ ፣ ሽብር ፈጣሪዎችን «አርበኞች» ፣ «የነፃነት ታጋዮች» እያሉ ያስተጋባሉ ።

በማዕከላዊ አውሮፓ ተቋቁመው ከአሜሪካው የስለላ ድርጅት በሚያገኙት ድጋፍ በሶሻሊስት አገሮች ላይ የፀረ ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ከሚያካሂዱት የሬዲዮ ጣቢያዎች መካከል «ሬዲዮ ፍሪ ዩሮፕ» እና «ሬዲዮ ሊበርቲ» ይገኙበታል ። እነዚህ የሬዲዮ ጣቢያዎች ሶሻሊስት አገሮች

Digitized by Google

የኢምፔሪያሊስት የመገናኛ ዘዴዎች የአፍራሽ ተልዕኮ ገጽታ
STP (ሶሻሊዚም ንድፈሐሳብና ተግባር ቁ.4 ፣ 1985) ከተባለው መጽሔት የተወሰደ ።

Digitized by Google

የጨበጡትን የዕድገት እርከን በማንቋሸሸ
አፍራሽ ሚና ይጫወታሉ ። የእነዚህ የሬዲዮ
ጣቢያዎች ፕሮፓጋንዳ በአብዛኛው በሶሻ
ሊዝም የኢኮኖሚ ፖሊሲ ላይ ያተኮረ ነው ።
ይህም ያለምክንያት አይደለም ። ሁሉቱን
ማኅበራዊ ሥርዓቶች የሚለያቸው መሠረ
ታዊ ነጥብ የሀብት ይዞታና የኢኮኖሚ
አስተዳደር ነው ። በካፒታሊዝም የግል
ሀብትና በዚህም ሳቢያ የሚከሰተው የሰ
ዎች በሰዎች መበዝበዝ የሥርዓቱ መሠረ
ታዊ ባህርይ ነው ። በሶሻሊዝም ሀብት
የመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ነው ፤ በመ
ሆኑም አንዱ ሌላውን አይበዘብዘውም ።
በዚህ ምክንያት ለካፒታሊዝም የሚታ
ገሉ ኃይሎች የካፒታሊዝምን ጥንካሬ
ቢሰብኩ ፣ የሶሻሊዝምን በእቅድ መሥራት
ቢያጥላሉ ፣ በኢኮኖሚ አስተዳደር ድክ
መት አለ ብለው ቢያናፍሱ የሚያስደ
ንቅ አይሆንም ። ካፒታሊዝም በአራት
መቶ ዓመታት የደረሰበትን የዕድገት
ደረጃ ሶሻሊዝም ሰባ ዓመት በማይሞላ
ጊዜ የመጨበጡን ሐቅ ግን በየትኛውም
አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ የሚንዱት አልሆ
ነም ፤ አይሆንምም ።

የሥነ ልቦና ጦርነት ባታዳጊ አገሮች

የኢምፔሪያሊዝም ፕሮፓጋንዳ አው
ታሮች ሶሻሊስት አገሮችንና ሶሻሊዝምን
በማጥላላት ፣ በካፒታሊስት አገሮች ያሉ
ሠራተኛ ሕዝቦችን በልዩ ልዩ ዘዴዎች በማ
ዘናጋት በርዕዮተ ዓለም መስክ በኮሚኒ
ዝም ላይ ዘመቻ እንደያዙ ሁሉ ታዳጊ አገ
ሮች ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ ፍትሕ የሚያ
ደርጉትን ትግል ለመበታተንና ለማኮላሸት
ከፍተኛ ሙከራ በማድረግ ላይ ናቸው ።
ኢምፔሪያሊዝም በአፍሪካ ፣ በእስያና በላ
ቲን አሜሪካ በቅኝ ግዛት መንኮታኮት ያጣ
ውን ጥቅም በተዘዋዋሪ መንገድ መልሶ
ለማግኘት የሚያደርገው መሯሯጥ በገሃድ
የሚታይ ነው ።

አብዛኛዎቹ ታዳጊ የአፍሪካ ፣ የእስያና
የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች የፖለቲካ ነፃነታ
ቸውን የተቀዳጁ ቢሆንም ፣ ከካፒታሊስቱ
ዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት የተላቀቁ አይደ
ሉም ። ከእነዚሁ ታዳጊ አገሮች አብዛኛ
ዎቹ በኢምፔሪያሊዝም የፖለቲካና የኢ
ኮኖሚ እንዲሁም የባህል ጥገኝነት ሥር
ያሉ ናቸው ። በመሆኑም የእነዚህ አገሮች
ሠራተኛ ሕዝቦች የፖለቲካ ነፃነትን ብቻ
ሳይሆን ከኢምፔሪያሊዝም ተፅዕኖ በመ
ውጣት የኢኮኖሚና የባህል ነፃነትን ለመ
ቀዳጀት አዲስ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥር
ዓት እንዲኖር እየታገሉ ነው ። ከዚህ በላቀ
ሁኔታም የካፒታሊዝም የዕድገት ጐዳና
ለሠራተኛ ሕዝቦች አንዳችም የፖለቲካና
የኢኮኖሚ ፍትሕ እንደማያስገኝ እየተገነ
ዘቡ በመምጣታቸው የሶሻሊዝምን የዕ
ድገት ፈለግ እየተከተሉ ነው ።

በተለይ በአፍሪካ እ. አ. አ. ከ1970ዎቹ
የመጀመሪያ ዓመታት ወዲህ የአንጐላ ፣
የሞዛምቢክ ፣ የዚምባብዌ ሕዝብ ከቅኝ
ግዛት ቀንበር መላቀቅና ኢትዮጵያን ጨምሮ
የሶሻሊዝምን የዕድገት ጐዳና መከተል
ኢምፔሪያሊዝምን ክፉኛ አስፈርቶታል ።
ከዚሁ ጋር በደቡባዊ አፍሪካ የሚካሔደው
ፀረ አፓርታይድ ትግል መፋፋምና በታ
ዳጊ አገሮች የፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች
እየተጠናከሩ መምጣት የኢምፔሪያሊዝ
ምን መንኮታኮት የማይቀር መሆን እያመ
ለከቱ መጥተዋል ። ስለዚህ የኢምፔሪያሊ
ዝምና የአድኅሮት የወቅቱ ፀረ ሰላምና ፀረ
ዕድገት ድርጊት ከጭንቀት የመነጨ መሆኑ
አያጠያይቅም ።

በዚህ ከታሪክ ሒደት ጋር በሚጋጭ
ሙከራ ኢምፔሪያሊዝም በተፅዕናው ክል
ል ውስጥ የሚገኙ የታዳጊ አገሮች ሕዝቦ
ችን በሥሩ ለማቆየት እንዲሁም ሶሻሊ
ስት የዕድገት ጐዳና በመረጡ አገሮች
ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር ከፍ
ተኛ ደባ በመፈጸም ላይ ይገኛል ። ለዚህ
ዓላማውም በታዳጊ አገሮች በተዘረጉ የባ
ህል ተቋሞች ፣ የንግድ ፣ የቱሪዝምና የባ

Digitized by Google

ይህ ፀረ—ኩባ ሬዲዮ ጣቢያ ነው? ልምድ ያለው የሽብር ዜና አቅራቢ ያስፈልጋችኋል?
ከሞስኮ ኒውስ ፣ ቁ. 25 ፣ እ.ኤ.አ. 1985 ጋዜጣ የተወሰደ ።

Digitized by Google

ሀል ልውውጥ አውታሮችና መስኮች ይጠ
ቀማል ። ለጨቋኝና ለፀረ ዲሞክራሲ መን
ግሥታት ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ድጋፍ
በመስጠት የሕዝቦችን ትግል በኃይል ለማ
ንበርከክ ይሞክራል ። ቅጥረኞችን በማ
ስታጠቅ ሕዝቦችን እርስ በርስ ያጨፋ
ጭፋል።ይህ ሁኔታ ዛሬ በደቡባዊ አፍሪካና
በመካከለኛው ምሥራቅ በየዕለቱ ጉልቶ
የሚታይ ክስተት ሆኗል ።

ኢምፔሪያሊዝም የታዳጊ አገሮች ሕዝቦ
ችን ትግል ለመበታተን ከሚጠቀምባቸው
ልዩ ልዩ ሥልቶች በወቅቱ ግንባር ቀደም
ሚና በመጫወት ላይ ያሉት ግዙፍ የፕሮ
ፓጋንዳ አውታሮች ናቸው ። በተለይም
የዓለም ሰላም ጠባቂ ነኝ የሚለው የአ
ሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በሥነ ልቦና
ጦርነት በኩል የያዘው ዘመቻ ሁኔታውን
ግልጽ ያደርገዋል ። የአሜሪካ ኢምፔሪ
ያሊዝም ባለፉት ሐያ አምስት ዓመታት
ጦርነት በመክፈት ፣ የንግድ ማዕቀብ በማ
ድረግ ፣ የማጥላላት ዘመቻ በማካሔድ የኩ
ባን ታጋይ ሕዝብ አብዮታዊ ወኔ ለመፈታ
ተን ያደረገው ሙከራ አልበቃ ብሎት በቅ
ርቡ «ራዲዮ ማርቲ» የተሰኘ ጣቢያ ከፍቶ
በኩባና በጠቅላላው የላቲን አሜሪካ ሕዝብ
ላይ ከመቼውም ጊዜ የተጠናከረ የፕሮፓ
ጋንዳ ጦርነት እያካሔደ ነው ። ለዚህ ተግ
ባሩም በአሜሪካ ኮንግረስ ውሳኔ 14 ሚሊ
ዮን ዶላር ተመድቧል ። የተወሰደው ርምጃ
የመጀመሪያውና አዲስ ባለመሆኑ ባያስደን
ቅም ፣ ለሬዲዮ ጣቢያው የተሰጠው ስያሜ፣
ሬዲዮ ጣቢያው ኩባ ከስፓኝ ቅኝ አገዛዝ
ነፃ በወጣችበት መታሰቢያ ዕለት ሥራ
ውን መጀመሩ ግን ለላቲን አሜሪካ ሕዝብ
የራሱ የሆነ መልእክት አለው ። ይህ ፀረ
ሶሻሊስት የሬዲዮ ጣቢያ የተሰየመው በታ
ዋቂው ኩባዊ የነፃነት ታጋይና ዲሞክራት
በነበረው በሆሴ ማርቲ ስም ነው ። ሆሴ
ማርቲ የኩባና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች
ከስፓኝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ እንዲወጡ የብዕ
ርና የጦር ሜዳ ፍልሚያ ያካሄደ ታዋቂ
አርበኛ ነው ። በመሆኑም በመላው የላቲን
አሜሪካ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ አክብሮት
አለው ። የዚህን የላቲን አሜሪካ የነፃነት
አባት ስም የአሜሪካ መንግሥት ለመስሪ
ፕሮፓጋንዳ ጣቢያው መጠሪያ ማድረጉ
ጣቢያው ለሕዝቦች ደኅንነትና ነፃነት
የቆመ የሚያስመስለውን ካባ ለማላበስ
ነው ። ይሁን እንጂ የኢምፔሪያሊስቶች
ፍላጐት የላቲን አሜሪካን ሕዝብ የማይ
ነጥፍ የሞኖፖሊስቶች ጥገት ማድረግ
መሆኑን ከማንም የተሰወረ አይደም ።

ይህን መሰሉ የኢምፔሪያሊስቶች ተን
ኮል በሌሎች አብዮታዊ ሀገሮች ላይ በልዩ
ልዩ መልክ የሚፈጸም ነው ። አብዮታዊት
ኢትዮጵያ ከዚህ ውጭ አይደለችም ። የአሜ
ሪካ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ አብዮት
ፍንዳታ ማግሥት በአገሪቱ የነበረውን የፖ
ለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅም አጥቶ ሲባረር
እንደማንኛውም ታዳጊ አገር የኢትዮጵያን
ሰፊ ሕዝብ አስተሳሰብ ወደራሱ ለመሳብ
በአገር ውስጥ ሲጠቀምበት የነበረውን
መድረክም አጥቷል ። አብዮቱ በወሰደው
ቆራጥ ርምጃ የአሜሪካ የኢንፎርሜሽን
ድርጅት (USIS) በኢትዮጵያ ከፍተኛ
የፕሮፓጋንዳ ሚና የነበረው ሲሆን፣
በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች በቤተ መጻሕ
ፍት ስም መረቡን ዘርግቶ ነበር ። በተለ
ይም አዲስ አበባ ውስጥ የነበረው ጽ/ቤቱ
ለአገር ውስጥ ጋዜጦች፣ ራዲዮና ቴሌቪ
ዥን ዜናና ፊልሞችን በማቀበል፣ የእንግ
ሊዝኛ ቋንቋ በማስተማር ስም ካፒታሊዝ
ምን በተለይም የአሜሪካንን «ታላቅነት»
በመስበክ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ።
ታዲያ በአገር ውስጥ ያጣውን መድረክ
በአሁኑ ወቅት በዋሽንግተን የአሜሪካ
ድምፅ ራዲዮ አማካይነት በአማርኛ ቋንቋ
ጭምር ፕሮግራም በመክፈት ለመተካት
ቢሞክር የሚያስደንቅ አይሆንም ።

ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ አብዮት
ላይ የሚነዛው እድኀሪ ፕሮፓጋንዳ ከአ
ዓድ አቅጣጫ ብቻ የሚመጣና በአንድ
ይነት መድረክ አማካይነት የሚሰራጭ
አይደለም ። ከኢምፔሪያሊስቱ ሰፈር በጋ

Digitized by Google

ዜጦች፣ በመጽሔቶች ፣ በፊልም ፣ በቴፕና በቪዲዮ ካሴት ከሚነዛው ፀረ ሶሻሊስትትና ፀረ ኢትዮጵያ አብዮት ፕሮፓጋንዳ ሌላ«ጠላቶቻችን በአሁኑ ጊዜ የውጭ ቋንቋዎች ሳይቀጠሩ በአማርኛ ፣ በትግርኛ ፣ በኦሮምኛ ፣ በሶማልኛ ከ10 ያላነሱ የተለያዩ ሬዲዮ ጣቢያዎች በቀን ለ፬/.ዓት ከ10 ደቂቃ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያካሂዱብናል ። [10]

ኢምፔሪያሊዝም በታዳጊ አገሮች ላይ የሚያደርሰው የርዕዮተ ዓለም ተፅዕና ሲወሳ በተለይም በቴሌቪዥን አማካይነት የሚካሔደው የባህል ወረራ ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም ። ቴሌቪዥን ማኅበራዊ ንቃተ ሕሊናን በማሳደግ በኩል ከሁሉም ሚዲያ ዘርፎች የበለጠ ተቀባይነት እያገኘ በመጣበትና በየግለሰቡ ቤት ያለው ሲደመር ከ500 ሚሊዮን በላይ [11] የቴሌቢዥን ሥርጭት መቀበያዎች ባሉባት ዓለም ለልማትም ይሁን ለጥፋት ውጤታማ መሣሪያነቱ አያጠያይቅም ። በመሆኑም ኢምፔሪያሊስቶች ከፍተኛ ትኩረት የሰጡት የሕዝብ መገናኛ ሊሆን ችሏል ።

ታዳጊ አገሮች በፈለጉት መጠንና አመለካከት ፊልሞችን ለመሥራት የሠለጠነ ሰው ኃይሉም ፣ ቴክኖሎጂውም የላቸውም።የገንዘብ አቅማቸውም ውሱን ነው። ስለዚህም ፊልም በአገራቸው ከማምረት ይልቅ ከውጭ ማስመጣትን እንዲመርጡ ሁኔታዎች ያስገድዱቸዋል ። በመሆኑም ዛሬ በታዳጊ አገሮች ከውጭ ተገዝተው በብሔራዊ ቴሌቪዥኖች የሚቀርቡ ዶኩመንታሪ ፕሮግራሞች ድርሻ እስከ 90% ከፍ ሊል ችሏል ። [12] የካፒታሊስቱ ዓለም ፊልም ኢንዱስትሪዎች ከትርፍም ባሻገር የካፒታሊዝምን ዕድሜ በማራዘም በኩል የሚያገኙትን ጠቀሜታ በመመዘን ፊልሞችን ለታዳጊ አገሮች በርካሽ ይሸጣሉ ። «በ1976 (እ. አ. አ.) በዩናይትድ ስቴትስ በ200,000 ዶላር የተሠራ የ30 ደቂቃ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ለኮስታሪካ ከ60 እስከ 70 ዶላር ፣ ለኬንያ ከ25 እስከ 30 ዶላር በሆነ ዋጋ ቀርቧል ።» [13] በካፒታሊስቱ ዓለም ላለው ኅብረተሰብ የሚታዩ ፊልሞች ሕዝቡ የካፒታሊዝምን ቀውስ ምክንያትና ውጤት እንዳያውቅ የሚጋርዱ እንዲሁም ስለኮሚኒዝም የተዛባ አመለካከት እንዲኖረው የሚያደርጉ ናቸው ። በርካሽ ዋጋ ለታዳጊ አገሮች የሚሰራጩ ፊልሞች ፀረ ኮሚኒስት ሐሳቦችን ከመንዛት በተጨማሪ የቡርዧውን ባህል «በጉንት» ፣ በምዕራቡ ዓለም ያለው ኑሮ ምቾት ደስታ የሰፈነበት አስመስሉ በመስበክ በተለይም የታዳጊ አገሮች ምሁርና ከተሜ የራሱን አገር ታሪክ ፣ ባህልና ወግ እንዲንቅ፣ ከሕዝቡ አኗኗር ጋር የማይመጣጠን የሸቀጣሸቀጥ ጣዕምና ፍላጐት እንዲያዳብር፣ ከራሱ ሕዝብም እንዲርቅ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ይኸው የኅብረተሰብ ክፍል ራሱን በምዕራብ የኑሮ ዘይቤ ውስጥ እንዲያስቀምጥና ከአውሮፓዊው የበለጠ አውሮፓዊ ፣ ከአሜሪካዊው በለጠ አሜሪካዊ እንዲሆን አድርገው እስየሳሰቡን ይቀርጻሉ ።

የምዕራብ የዜና ማሠራጫና የፕሮፓጋንዳ አውታሮች በታዳጊ አገሮች ላይ የሚያካሒዱት ፀረ ኮሚኒስትና ፀረ አብዮት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ትኩረት ያረፈው ሶሻሊዝምን የዕድገት ጐዳና አድርገው በመረጡ አገሮች ላይ ነው ። ይህ ያለምክንያት አይደለም ። የእነዚህ አገሮች ምሳሌነት ገና ከተፅዕኖአቸው ሥር ወዳልወጡ አገሮች እንዳይዛመት አጥብቀው ስለሚፈሩ ነው። በመሆኑም ሶሻሊዝምን የመረጡ አገሮች ምንጊዜም ከችግር እንዳይላቀቁ ማናቸውንም ደባ እየፈጸሙባቸው በመጨረሻ ሕዝ

Digitized by Google

ባቸው «ሶሻሊዝም ማለት ድኅነትና ጦርነት ማለት ነው» ወደሚል መደምደሚያ እንዲደርስ ይመኛሉ ። ይህንኑ ምኞታቸውን ተፈፃሚ ለማድረግም የለየላቸው የውስጥ አድኃርያንና ግራ መሰል ቡድኖችን በማደራጀትና በማስታጠቅ የአገሮችን ሰላም ይነሳሉ ። አጐራባች አገሮችን ለጦርነት ይገፋፋሉ ፤ የሕዝቡን አንድነት የሚከፋፍሉ ልዩ ልዩ ቅስቀሳዎችን ያካሒዳሉ ።

ኢምፔሪያሊዝም የታዳጊ አገሮች ሕዝቦችን ከሚከፋፍልበት ዘዴ አንዱ ብሔረተኝነት ነው ። እሱም ልዩ ልዩ መልኮችን ይይዛል ። በአንድ በኩል ለወዝ አደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ተፃራሪ የሆነ በትምክህተኝነት የተሞላ እጉል ብሔራዊ ኩራትና ስሜት በመፍጠር የእያንዳንዱን አገር ሕዝብ ከሶሻሊስት አገሮች የመነጠል ሥልት ነው ። ይህ በተለይ በፀረ ሶቭየት መልኩ ይከሰታል ። ሌላው ሥልት በውስጥ የሚነዛው ጠባብ ብሔረተኝነት ነው። እንደሚታወቀው ታዳጊ አገሮች ከዕድገታቸው ኋላቀርነት የተነሣ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ጐሳዎች ፣ ነገዶችና ብሔረሰቦች የሚኖሩባቸው ናቸው ። ይህን ተጨባጭ እውነታ መነሻ በማድረግ አንዱ ሌላውን እንዲጠላና እንዲነሳበት ፣ አንዱ ሌላውን እንዲወጋ ሤራ ይሸርባሉ ፤ ይቀስቅሳሉ ፤ ይገፋፋሉም ።

በተለይ የሶሻሊስቱን የዕድገት ጐዳና በመረጡ አገሮች ውስጥ የሚታዩ የሽግግር ወቅት ችግሮችን (የተፈጥሮን ችግርን እንኳን ሳይቀር) ሶሻሊዝም የፈጠራቸው ችግሮች አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። በዚህም መሠረት ኢምፔሪያሊስቶች የአድኃሪ ፕሮፓጋንዳቸው ኢላማ ባደረጉት መንግሥትና ሕዝብ ላይ የሚነዙት አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ለተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች የሚቀያስ ሆኖ ፣ ሕዝቡ በራሱ መንግሥት ላይ እምነት እንዲያጣና እንዲጠራጠር ፣ ለሶሻሊዝምና ለሰላም ከሚያደርገው ትግል እንዲዘናጋ በረቀቀ ስልትና ዘዴ የሚታቀድ ነው ።

በታዳጊ አገሮች ላይ ከሚካሔደው የኢምፔሪያሊዝም ፕሮፓጋንዳ አኳያ በተለይ የአሜሪካ የስለላ ድርጅት ሲ. አይ. ኤ ከፍተኛ ድርሻ አለው ። ሲ. አይ. ኤ. ስለታዳጊ አገሮች «ጥናትና ምርምር» ለሚያካሂዱ ምሁራን በገፍ ገንዘብ በመክፈልና መረጃዎችን ለዓላማቸው በሚያመች መልክ በጋዜጦች ፣ በመጽሔቶች ፣ በመጻሕፍት ወዘተ እንዲሰራጩ በማድረግ ለአሉባልታ መነሻ የሚሆኑ የፈጠራ ወሬዎችን በመንዛትና ሕዝብን በማዘናጋት ሰፊ ሚና አለው ።

ሲ. አይ. ኤ. የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን ለሚፈልገው ዓላማ ለመጠቀም እንደሚሞክር በአንጐላ የተፈጸመውን ሁኔታ መገንዘቡ በቂ ነው ። በ1975 (እ. አ. አ.) በአንድ በኩል አንጐላ ከፖርቱጋል ቅኝ አገዛዝ ለመውጣት ትግሏን ያፋፋመችበት ፣ በሌላ በኩል የአንጐላ ነፃ መውጣት የማይቀር መሆኑን የተገነዘቡ ኢምፔሪያሊስቶች አሻንጉሊት መንግሥት በአገሪቱ ለመትከል የሚሯሯጡበት ወቅት ነበር ። ለዚህም ዓላማ አሁን በኢምፔሪያሊዝምና በዘረኛው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ጉን የተሰለፈውን የዮናስ ሳቪምቢን ቡድን በማዘጋጀት ላይ ነበሩ ። ይህን የቅጥረኞች ቡድን በትጥቅ አደራጅተው በአንጐላ የበላይነቱን እንዲይዝ በነበራቸው ፍላጐት ለዓላማቸው መሳካት መንገድ መፈለግ ጀመሩ ። ዛሬ የኒካራጉዋን ፀረ-አብዮተኞች ለማስታጠቅ «በአካባቢው የኮሚኒዝምን መስፋፋት ለመቋቋም» እያሉ እንደሚያናፍሱት ሁሉ ፣ ያንጊዜ በአንጐላም «ሶቭየት ኅብረት ኤም. ፒ. ኤል. ኤን በገፍ እያስታጠቀች ነው» የሚል ዜና ማራገብ ያዙ ። ይህንኑ መረጃ በወቅቱ ኪንሻሳ ውስጥ የነበሩ የሲ. አይ. ኤ. የፕሮፓጋንዳ «ጠበብት» መክረውበት ለመነሻ «ኤሊዎ»

Digitized by Google

እና «ሳሉንጉ» በተባሉ የኪንሻሳ (ዛዬር) ጋዜጦች እንዲታተም ተደረገ። ከዚያም በአውሮፓ በእስያና በላቲን አሜሪካ ለሚገኙ የሲ. አይ. ኤ. ጣቢያዎች ተላልፎ በየአካባቢው በሚገኙ የታላላቅ ዜና ድርጅት ወኪሎች በሆኑ የሲ. አይ. ኤ. ምልምል ጋዜጦች እጅ እንዲገባ ተደርጉ መረጃው በመላው ዓለም የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ተነዛ።[14]

ይህ በኢምፔሪያሊዝምና በሳቪምቢ ፀረ አብዮት ቡድን መካከል የተፈጠረው ቃል ኪዳን ዛሬ በደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት ተጠናክር የአንጉላን የሶሻሊዝም ግንባታ ጥረት በመፈታተን ላይ ነው ። ለዚህ የፀረ አብዮት ግንባር መፈጠር ያን ጊዜ ከኪንሻሳ እንዲመነጭ ተደርጉ በመላው ዓለም በመገናኛ አውታሮች የተነዛው «የሶቭየት አደጋ» ዜና አስተዋጽኦ አድርጓል ። ሲ. አይ. ኤ. በአንጉላ ላይ የፈጸመው አሁንም የሚፈጽመው ድርጊት ፣ አሜሪካ የአፍሪካን አህጉር በሚመለከት የምታራምደው ፖሊሲ አጠቃላይ አካል ነው ። በመሠረቱ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የሚያራምደው የአፍሪካን ሕዝቦች የራስ በራስ የመወሰን መብት የመጣስ ፖሊሲ ነው »[15] የአፍሪካ ሕዝቦች አህጉራቱ የሰላም ቀጠና እንድትሆን ፣ ለኢኮኖሚ ነፃነትና ለዕድገት የሚያደርጉትን ትግል የመበታተን ፖሊሲ ነው ።

ሲ. አይ. ኤ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን የሚጠቀመው በተዘዋዋሪ መንገድና በረቀቀ ስልት ብቻ አይደለም ። በዩናይትድ ስቴትስ የሪፑብሊካን ፓርቲ አባል በሆነው ኤድዋርድ ቦላንድ ሰብሳቢነት የተቋቋመው የአሜሪካ ምክር ቤት መርማሪ ኮሚቴ እንዳረጋገጠው ለፈጠራ የፕሮፓጋንዳ ዜናዎች መነሻ የሚሆኑና በሲ. አይ. ኤ. ገንዘብ የሚካሔዱ ከ 200 በላይ መጽሔቶች ፣ የዜና አገልግሎቶች ፣ የሬዲዮ ጣቢያዎች ፣ ሌሎችም የፕሮፓጋንዳ አውታሮች አሉ ። [16]

በልዩ ልዩ መድረኮችና ስልቶች ኢምፔሪያሊዝም ወደታዳጊ አገሮች የሚያስተጋባውን ፕሮፓጋንዳና የሚያካሔደውን ፀረ ሶሻሊስት እንቅስቃሴ ስትራቴጂያዊ ግብ በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል ። እነዚህም፥

አንደኛ ፣ የአርነት እንቅስቃሴዎችን ከሶሻሊስቱ ዓለምና ከዓለም አቀፉ የሠራተኛ መደብ እንቅስቃሴ በመነጠል የዓለምን አብዮታዊ ኃይሎች አንድነት መበታተን ፣

ሁለተኛ ፣ ታዳጊ አገሮች ለማኅበራዊ ዕድገት የሚያደርጉትን ጥረት ማደናቀፍ ፣ በተለይም የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ የተከተሉ አገሮች በዕድገታቸው ምንም ዓይነት እርምጃ እንዳያሳዩ እንቅፋት መፍጠር ፣መልሶም ማጥላላት ፣

ሦስተኛ ፣ ታዳጊ አገሮች ከካፒታሊስቱ ዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት ምንጊዜም እንዳይላቀቁ ማድረግ ፣ የካፒታሊዝምን መሠረት በእነዚህ አገሮች በማጠናከር የኢኮኖሚ ነፃነታቸውን መገደብ ፣ ከገዥ መደቦቻቸው ጋር የጠበቀ ግንባር በመፍጠር ለአጠቃላዩ ፀረ—ኮሚኒስት እንቅስቃሴ እንደ አጋር መጠቀም ናቸው ። [17]

በአጠቃላይ ኢምፔሪያሊዝም ሕዝቦች ለተሟላ ነፃነት የሚያደርጉትን ትግል ለማኮላሸትና ታዳጊ አገሮችን በተዕፅናው ክልል ሥር ለማቆየት የሚፈጽመው ደባ ስትራቴጂያዊ ዓላማና ግብ ይህ ሆኖ ሳለ ፣ እውነተኛ ገጽታውን ለመሸፋፈን የተለያየ ሥልቶችን ይጠቀማል ።

የኢፔሪያሊዝም የፕሬስ «ነፃነት» ጥያቄና አዲስ ዓለም አቀፍ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት

የቡርዧው መንግሥትና ሞኖፖሊስቶች ለጋራ ጥቅማቸው የፈጠሩት ግንባር ይፋ እንዳይወጣ በምዕራቡ ዓለም የሕዝብ መገ

Digitized by Google

ናኛ ዘዴዎች «ነፃ»እና የሰፊው ሕዝብ የዲሞክራሲ መድረኮች እንደሆኑ አድርገው ለማቅረብ በመሞከር ላይ ናቸው ። በዚህም መሠረት የቡርዧው የጋዜጠኝነት ሥራ «የማንም ተፅዕኖ የሌለበት ነው» ይላሉ ። ይህም ተቀባይነት ያገኘ ዘንድ ቡርዣው ገና ታዳጊ በነበረበትና ከፊውዳሊዝም ጋር የጥቅም ግጭት ያደርግ በነበረበት ወቅት የሰፊው ሕዝብ ወገን መስሎ የቀረበበት የነፃነትና የዲሞክራሲ ጥያቄ ዛሬም የቡርዧው መርሕ ተደርጐ ይቀርባል ። አልፎ አልፎም ስለድኅነትና ጉስቁልና ፣ ስለመራብ ፣ ስለኋላቀርነት የሚያወሱና የሚቆረቆሩ መስለው ለመታየት ቢሞክሩም የእነዚህን ክስተቶች መንስዔና መወገጃ ዘዴ ለማንሳት አይደፍሩም ፤ ምክንያቱም የሕዝቦች ጉስቁልናና ኋላቀርነት መንስኤ ይፋ መውጣት ካፒታሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ተጠያቂ የሚያደርግ ነው ።

በመሠረቱ ዲሞክራሲና ነፃነት የፖለቲካ ፈርጆች እንደመሆናቸው ከማኅበራዊ ቡድኖችና መደቦች ግንኙነት ውጭ የሚታዩ አይሆኑም ፤ በፖለቲካ ነባራዊ ሕግ ፣ ማለትም በመደቦች ፣ በአገሮችና በመንግሥታት ግንኙነት ሕግ የሚገዙ ናቸው ። ይህም ዞሮ ዞሮ መሠረቱ በመደቦች መካከል ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት ነው ። ይልቁንም በሁለቱ ማኅበራዊ ሥርዓቶችና በመደቦች መካከል የሚካሔደው ትግል በልዩ ልዩ መልኩ በተፋፋመበትና የርዕዮተ ዓለም ትግሉ ጐልቶ በታየበት በአሁኑ ወቅት የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን ከመደቦች ጥቅምና ፍላጐት ውጭ አድርጐ ማቅረብ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም ።

በመሆኑም ዛሬ የቡርዧው የፕሮፓጋንዳ አውታሮች የፖለቲካ አቋም የማይስወስዱና ወገን ሳይለዩ ሐቅን የሚያቀርቡ መስለው ለመታየት ያጠለቁት «የነፃነትና የዲሞክራሲ» ካባ እየተገፈፈ ነው ። የቡርዧው መንግሥትና ሞኖፖሊስቶች እንዲሁም የጋዜጣ ድርጅቶች የካፒታሊዝምን ሕልውና ለማራዘም ፣ የሕዝቦችን የነፃነት ጥያቄ ለማድበስበስ እጅና ጓንት ሆነው በመሥራት ላይ መሆናቸው የአደባባይ ምሥጢር እየሆነ ነው ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አጠቃቀም መደባዊ መሆኑና ቡርዧው ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ለማስከበርና ሥልጣኑን ለመጠበቅ የሚጠቀምበት መሆኑ እየታወቀ በይበልጥም ዛሬ በምዕራቡ ዓለም የኅትመት ሥራና የኢንፎርሜሽን ሥርጭት በግዙፍ የሞኖፖል ድርጅቶች ሥር ተሰባስቦ ከፍተኛ ትርፍ በሚያስገኝበት ሁኔታ «የፕሬስ ነፃነት ማለት በመገናኛ ዘዴዎች የመነገድ ፣ እነርሱም በሕዝብ ላይ በሚያሳድሩት ተፅዕኖ መደባዊ ጥቅምን የማስጠበቅ ነፃነት ማለት ነው ።» [1] ዛሬ ይህ ሐቅ ገሐድ እየወጣ በመሆኑ የቡርዧው ዜና ማሠራጫ አውታሮች ተአማኒነታቸው እየቀነሰ መጥቶ ካፒታሊዝም በሚገኝበት አጠቃላይ ቀውስ ውስጥ ገብተዋል ። የቡርዧው የሕዝብ መገናኛ አውታሮች በካፒታል አካልነታቸውና መሣሪያነታቸው ፣ በሕዝቦች የነፃነት እንቅስቃሴ ላይ የሚሠሩትን ደባ ፣ በሕዝቦች ባህል ፣ አስተሳሰብና አኗኗር ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ለመቋቋም በተለያዩ መድረኮች ለአዲሱ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ትግል በመደረግ ላይ ነው ።

የዓለም አቀፉ የኢንፎርሜሽን ሥርዓትና ሥርጭት መዛባት ሲታይ በከፍተኛ ተፅዕኖ ሥር የሚገኙት አሁንም ታዳጊ አገሮች ናቸው ። እነዚህ አገሮች የዘመኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያፈራው የመገናኛ ቴክኒክ ባለቤቶች አይደሉም ። በመሆኑም በአመዛኙ ከታላላቅ የሞኖፖል ድርጅቶች የሚደርሳቸውን ዜና ተቀብለው የሚያስተጋቡ ናቸው ። እነርሱ ለዓለም ኅብረተሰብ የሚ

Digitized by Google

ሰጡት ዜና በጣም አነስተኛ ነው ። ስለታዳጊ አገሮች የሚነገር ዜና ይበልጡኑ ከተጨባጭ ሁኔታ ውጭ በካፒታሊስቶች ጥቅም አንፃር እየተዘጋጀ የሚሰራጭ ነው ። በተለይም ዛሬ በመገናኛ ዘዴዎች ፈጣን ዕድገት የተነሳ የሕዋው መገናኛ ማለትም የሳተላይት ግንኙነት ሥራ ላይ መዋሉ ድንቅ ነው ቢባልም በአንድ በኩል ሕዝቦች ለኢምፔሪያሊዝም የባህል ወረራና የሐሳብ ተፅዕና በከፍተኛ ደረጃ እንዲጋለጡ አድርጓል።

ለእውነተኛ ዲሞክራሲና ነፃነት ፣ ለሶሻሊዝም የሚታገሉ ሕዝቦች በኢኮኖሚና በፖለቲካ መስከ የራሳቸው ዕድል ወሳኞች ለመሆን እንደሚታገሉ ሁሉ የኢምፔሪያሊዝምን የባህል ወረራ እየታገሉ ናቸው ። በተለይም ታዳጊ አገሮች ዛሬ ከምን ጊዜውም በበለጠ የቡርዧውን «የአስተሳሰብ ቅኝ አገዛዝ» ለመቋቋምና በባህልና ሥነ ጥበባት መስክም በራሳቸው ባህልና ወግላይ የተመሠረተ ዕድገት እንዲኖራቸው ይሻሉ ። የኢምፔሪያሊዝም የፕሮፓጋንዳ አውታሮች በሕዝቦች አስተሳሰብ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕና እንዲገደብ ፣ በየአገሮቹ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ፣ በዕድገት ችግሮቻቸው ላይ ያተኮረ ፣ የአገርን ጥቅምና ዕድገት የሚያራምድ ብሔራዊ የሕዝብ መገናኛ አውታር እንዲኖር በመታገል ላይ ናቸው ። ዛሬ በተዛባ ሁኔታ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚፈሰው የኢንፎርሜሽን ሥርጭት ሚዛናዊ እንዲሆን ፣ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ለሕዝቦች ልዩነት ሳይሆን ፣ ለአንድነት ፣ ለጦርነት ሳይሆን ለሰላም ፣ ለጭቆናና ብዝበዛ ሳይሆን ለነፃነትና እኩልነት ፣ ለሰዎች የተሻለ ኑሮ እንዲቆሙ ፣ በአጠቃላይ «አዲስ ዓለም አቀፍ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት » እንዲኖር በተባበሩት መንግሥታት ፣ በዩኔስኮ ፣ በገለልተኛ አገሮች ትግል እየተደረገ ሲሆን አንዳንድ በጎ ፍንጮች በመታየት ላይ ናቸው ። የገለልተኛ አገሮች የጋራ የዜና ልውውጥ መድረክ (News Agency Pool) እንዲሁም የአፍሪካ የዜና አገልግሎት ድርጅት መቋቋም የዚሁ ትግል ውጤት ነው ።

የ«አዲስ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት» ጥያቄ ለአብዮታውያን የርዕዮተ ዓለም ትግሉን የማድበስበስ ጥያቄ አይደለም ። በ«አዲስ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት» መሰፈን የርካዮተ ዓለም ትግሉ ያከትምለታል የሚል ሐሳብም የላቸውም ። በሌላ በኩል ግን በሁለቱ ማኅበራዊ ሥርዓቶች መካከል የሚካሔደውን ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል ወደሥልቦናዊ ጦርነት በማሸጋገር የዓለምአቀፍ ግንኙነቶችን ለማሻከር ፣ የአገሮችን ብሔራዊ ክብርና ሉዓላዊነት (Sovereignity) ለመዳፈር የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን መጠቀም ለጦርነት ከሚደረገው ዝግጅት ያላነሰ አደገኛነት አለው ና የዲሞክራሲና የሰላም ኃይሎች ሁሉ አጥብቀው ይቃወሙታል ።

ይህ ትግል ገና የሚፈለገውን ፍሬ ባያስገኝም አዝማሚያው ኢምፔሪያሊዝምንና አድኅሮትን የሚያስከፋ ሆኗል። ለፍትሐዊ የኢንፎርሜሽን ሥርጭት የሚደረገው ትግል በአንድ በኩል በሐሳቦች ንግድ በገፍ የሚታፈሰውን ትርፍ የሚቀንስ ፣ ከዚህም በላይ ሕዝቦችን የሐሳብ እሥረኛ ለማድረግ ያለውን ጉጉት የሚገድብ እንደሚሆን ይታመናል ። ይሁን እንጂ ኢምፔሪያሊስቶች «ነፃ የኢንፎርሜሽን ሥርጭት» በሚል በተጽዕኖአቸው ለመቀጠል ይፈልጋሉ ።

«ነፃ የኢንፎርሜሽን ሥርጭት» የሚለው የኢምፔሪያሊስቶች አቋም የካፒታሊስቶች ፍላጐትና ጥቅም ማስጠበቂያ ፕሮፓጋንዳ የመንዛት ፣ በታዳጊ አገሮች ላይ ዛሬ ያለውን ተፅዕና የመቀጠል ፣ የኢምፔሪያሊዝምን የወረራ ፖሊሲ የማራመድ ጥያቄ ነው ። ዩናይትድ ስቴትስ ከተባበሩት መንግሥታት የትምህርት ፣ የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) የወጣችው ፣ እንዲሁም እንግሊዝና ሌሎች ካፒታሊስት አገሮች ከድርጅቱ ለመውጣት የቃጣቸው

Digitized by Google

ይኸው ፍላጐት የሚሟላበት ሁኔታ እየ ጠበበ በመምጣቱ ነው ። ይሁንና «የነፃ ኢንፎርሜሽን ስርጭት» አቋም በሕዝቦች ጥቅምና ሕልውና የመነገድ አቋም በመ ሆኑ ለዕውነተኛ ነፃነትና ለፍትሕ በቆሙ ኃይሎች ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ።

ዘመናችን ተጨቋኝና ተበዝባዥ ሕዝ ቦች ለተሟላ ነፃነትና እኩልነት የተፋፋመ ትግል የሚያደርጉበት ዘመን ነው ። ኢም ፔሪያሊዝም የሕዝቦችን ትግል ለማኮላ ሸት የፈለገውን ሥልትና መድረክ ቢጠቀ ምም እጅግ ቢበዛ የሕዝቦችን የተሟላ የ ድል ወቅት ማዘግየት ካልሆነ በቀር ትግሉን እስከ መጨረሻው መበተን የሚችልበት ሁኔታ ፈጽሞ የለም ፤ ምክንያቱም የሕዝ ቦች ትግል የታሪክ ድጋፍ አለውና ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Georgi ARBATOV: *The War of Ideas in Contemporary International Relations* (Progress Publishers, Moscow, 1973) 186

2 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 160

3 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 167

4 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 170

5. N.S. BIRYUKOV, *Television In The West And Its Doctrines* (Moscow: Progress Publishers, 1981), p. 66.

6 ዮሪ ካሽሉብ ፣ ኢምፔሪያሊዝም በዜና ማሠራጫ መስክ ፣ ሞስኮ ፣ የኖቮስቲ አገል ግሎት ማተሚያ ቤት ፣ 1984) ገጽ 10

7. Vitaly Petrusenko, *The Monopoly Press*. The International Organization of Journalists,, 1976. p. 48.

8. Georgi ARBATOV,

9. PYOTR MANCHKHA, *Problems of Africa Today* (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 141.

10 «ሠርቶ አደር» ቅጽ 6 ፣ ቁጥር 258

11. A. Grachev, N. Yermoshkin. A New Information Order or psychological warfare, Progress Publishers, Moscow, 1984, p. 7.

12 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 25

13 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 41

14. Dirty Works: The CIA In Africa (London: Z Press, London, 1980), p. 128.

15. UN Cloaking the CIA, (London: the Free Press, 1980), p. 128.

16 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 121 እና 122

17. Contemporary Anti - communism:- Policy .and Ideology, edited by O. REINHOLD and F. RYZAENKO, (Progress Publishers Moscow, 1976) p. 175.

18. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 28, p. 461.

Digitized by Google

የመስከረም መጽሔት ማውጫ

ቅጽ 5 ቁጥር 19—22

ደግፌ ገብረ ጻዲቅ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወሩ የሚወጣው መስከረም መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 19 መስከረም 1977 አንስቶ በተከታታይ የወጡትን ርእሶች በዚህ እትም (ቅጽ 5 ቁጥር 22 ሰኔ 1977) አቅርቧል ። ይህ ማውጫ በቅጽ 4 ቁጥር 18 ሰኔ 1977 ከቀረበው የስምና የአርእስት ማውጫ የቀጠለ ሲሆን ዓላማውም ተገልጋዮች እያንዳንዱን ቁጥር ከማገላበጥና ጊዜ ከማጥፋት እንዲድኑ ማድረግ ነው ።

Digitized by Google

ስም ማውጫ

መዝገቡ ምትኬ	ቁጥር	19	ገጽ	35 — 60
ስለሞን ገብሬ	ቁጥር	22	ገጽ	36 — 48
ኃይሉ አርአያ	ቁጥር	20	ገጽ	70 — 80
አሰፋ ሀብቱ	ቁጥር	20	ገጽ	6 — 33
አበበ ወርቁ	ቁጥር	19	ገጽ	61 — 75
	ቁጥር	22	ገጽ	7 — 35
አብዱልአዚዝ ጁኔይዲ	ቁጥር	21	ገጽ	9 — 32
አያልነህ የሻው	ቁጥር	19	ገጽ	14 — 34
ኢሳይያስ ደምሴ	ቁጥር	22	ገጽ	50 — 61
ዮሐንስ ገብረ ሥላሴ	ቁጥር	21	ገጽ	47 — 64
ደርበው ተመስገን	ቁጥር	22	ገጽ	62 — 75
ግርማ ተፈራ ዘማርያም	ቁጥር	20	ገጽ	34 — 53
ፈለቀ ዋጉ	ቁጥር	21	ገጽ	33 — 40

Digitized by Google

የአርዕስት ማውጫ

ሕዝባዊ ቁጥጥርና አንዳንድ ችግሮቹ	ቁጥር	20	ገጽ	34 — 53
ሕ ግ	»	21	ገጽ	33 — 46
ሕግ በሽግግር ወቅት	»	21	ገጽ	33 — 46
መ ደ ብ	»	21	ገጽ	9 — 32
መደብ ፣ የሠራተኛ	»	21	ገጽ	9 — 32
መሪ ዕቅድ	»	19	ገጽ	76 — 80
መሪ ፓርቲ	»	19	ገጽ	3 — 4
መሪ ፓርቲና መሪ ዕቅድ	»	19	ገጽ	76 — 80
የመሪ ፓርቲ ፕሮግራምና ደንብ ሚና	»	19	ገጽ	3 — 4
መብት	»	19	ገጽ	35 — 60
መብትና ግዴታ	»	19	ገጽ	35 — 60
ግሌና ምግባር	»	22	ገጽ	50 — 61
ምግባራዊ ግንዛቤ	»	22	ገጽ	50 — 61
የምግባር ግንዛቤ—በግሌ አመለካከት	»	22	ገጽ	50 — 61
ምግብ	»	22	ገጽ	3 — 5
በምግብ ራሳችን እንድንችል	»	22	ገጽ	3 — 5
የሠራተኛ መደብ ዕድገት በአፍሪካ	»	21	ገጽ	9 — 32
ሥነ—ልቦና	»	22	ገጽ	62 — 75
ሥነ—ልቦናዊ ጦርነት	»	22	ገጽ	62 — 75
ራስን መቻል	»	22	ገጽ	3 — 5
ሰላም	»	21	ገጽ	47 — 64
ለሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚደረገው ትግል	»	21	ገጽ	47 — 64
ሰብአዊ መብት	»	19	ገጽ	35 — 60
የሶሻሊዝም መሠረት ግንባታ	»	20	ገጽ	6 — 33
ሶሻሊዝምን መገንባት	»	20	ገጽ	6 — 33
ሽግግር	»	19	ገጽ	5 — 13
ሽግግርና ሕግ	»	21	ገጽ	33 — 46
በሽግግር ወቅት የሕግ ሚና	»	21	ገጽ	33 — 46
በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳደርና አመራር	»	19	ገጽ	5 — 13
ቁጥጥር	»	20	ገጽ	34 — 53
ቁጥጥርና ችግሮቹ	»	20	ገጽ	34 — 53

Digitized by Google

ትራንስፖርት	»	20	ገጽ	54 — 69
ትራንስፖርትን ሶሻሊስታዊ ፈር ማስያዝ	»	20	ገጽ	54 — 69
ተፈጥሮ	»	22	ገጽ	8 — 10
ተፈጥሮና ኅብረተሰብ	»	22	ገጽ	7 — 30
ኅብረተሰብ	»	22	ገጽ	8 — 30
የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር	»	22	ገጽ	7 — 33
ነፃነት	»	19	ገጽ	35 — 60
አብዮታዊት ኢትዮጵያና ካድሬ	»	22	ገጽ	36 — 48
አብዮትና ካድሬ	»	22	ገጽ	36 — 48
ኢሠፓ	»	21	ገጽ	3 — 7
ኢምፔሪያሊዝም	»	22	ገጽ	62 — 75
የኢምፔሪያሊዝም ሥነ ልቦና ጦርነት፣ ስልትና መድረኮች	»	22	ገጽ	
ኢንዱስትሪ	»	19	ገጽ	14 — 34
የኢንዱስትሪ አጀማመር በኢትዮጵያ	»	19	ገጽ	14 — 34
ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ	»	19	ገጽ	14 — 34
የኢንዱስትሪ ዕድገት አቅጣጫ	»	19	ገጽ	14 — 34
የኢኮኖሚ አስተዳደርና አመራር	»	19	ገጽ	5 — 13
ኢኮኖሚ በግብርና አንጻር	»	20	ገጽ	6 — 33
አንድ የዓለም ቋንቋ እንዴት ይፈጠራል ?	»	20	ገጽ	70 — 80
ካ ድ ሬ	»	22	ገጽ	36 — 48
የካድሬ ስያሜና ተግባር በኢትዮጵያ አብዮት ካለፍንበት ልምድ	ቀጥር	22	ገጽ	36 — 48
የዓለም ቋንቋ	»	20	ገጽ	70 — 80
ዕቅድ	»	19	ገጽ	76 — [illegible]
የወቅቱ ጥሪ	»	20	ገጽ	3 — 5
የዜጐች መሠረታዊ መብቶች፡ነፃነቶችና ግዴታዎች	»	19	ገጽ	35 — 60
የየብስ ትራንስፖርት	»	20	ገጽ	54 — 69
የየብስ ትራንስፖርትን ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ የተደረገ ጥረት	»	20	ገጽ	54 — 69
ድ ር ቅ	»	20	ገጽ	3 — 35

Digitized by Google

	»		ገጽ	6 — 33
ግብርና	»	20	ገጽ	6 — 33
በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የሶሻሊዝም መሠረት ግንባታ	»	20	ገጽ	6 — 33
ግ ዴ ታ	»	19	ገጽ	35 — 60
ጥሪ የወቅቱ	»	20	ገጽ	3 — 5
ጦር መሣሪያ ትነሳ	»	21	ገጽ	47 — 64
ጦርነት ፣ ሥነ ልቦናዊ	»	22	ገጽ	62 — 75
ፓ ር ቲ	»	19	ገጽ	76 — 80
	»	21	ገጽ	3 — 7
ፓርቲና የመሪነት ሚናው	»	21	ገጽ	3 — 7
የፓርቲውን የመሪነት ሚና ማሳደግ	»	21	ገጽ	3 — 7
ፕሮግራምና ደንብ ፣ የመሪ ፓርቲ	»	19	ገጽ	3 — 4
የፖለቲካ ሥርዓትና ተግባሩ	»	19	ገጽ	61 — 75
ፖለቲካና ሥርዓቱ	»	19	ገጽ	61 — 75
ቋ ን ቋ	»	20	ገጽ	70 — 80

Digitized by Google

Hoover Institution Library
3 6105 071 108 968

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

B.S.P.P.